ይህ መሠረታዊ የእምነት ትምሕርት በሥነ-መለኮት ትምህርት ሊቃውንትና በቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው በቂና ግልጥ የሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ስላለው ነው። ይህ የሠራዊነት ባሕርይ ለአእምሮ የሚመችና ለመረዳት የቀለለ ባይሆንም፥ በሥላሴ አካላት ውስጥ ያለውን ግንኙነት ለመገንዘብ የሚረዳ ትርጉም ይሰጣል። ለትምህርቱም እንደ ዮሐንስ 15፡26 እና መዝሙር 104፡30 ያሉት ጥቅሶች ግልጥ የሆኑ መረጃዎች ናቸው። በዮሐንስ 15፡26 ክርስቶስ ሊልክልን ቃል የገባው አጽናኝ ‘‘ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ’’ ተብሏል። ‘‘መውጣት (መሥረፅ)’’ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት የመጀመሪያ ቋንቋ፥ ጊዜው ትንቢታዊና ኃላፊ ሳይሆን፥ የአሁን ጊዜ መሆኑ ያለምንም ተቃውሞ ተቀባይነት ስላለው፥ መንፈስ ቅዱስ ከመጀመሪያው

* በቅርብ የተደረጉ ዋና ዋና የእምነት መግለጫዎችን ዝርዝር በመጽሐፉ መጨረሻ ይመልከቱ።

የሥላሴ አካል ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግንዘብ የሚረዳ ሆኗል። በመዝሙር 104፡30 የተጻፈው ‹‹መንፈስህን ትልካለህ›› የሚለው ቃልም ተመሳሳይ መረጃ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት እርግጠኛ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ›› እና ‹‹የክርስቶስ መንፈስ›› ተብሎ ከተጠቀሰው ማረጋገጥ ይቻላል›› (1ኛ ቆሮ. 2፡11-12፤ ገላ. 4፡6፤ ሮሜ 8፡9)። ከእነዚህ ሁለት የማረጋገጫ መንገዶች የመንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ የእምነት ትምህርት ነው ብሎ ከውሳኔ ላይ መድረስ ይቻላል።

የመንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት ዘላለማዊ ስለመሆኑ። የመሥረፅን መሠረታዊ ትምህርት ከምናረጋግጥባቸው ነገሮች አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት ዘላለማዊ መሆኑ ነው። ይህን ጉዳይ በሚመለከት የክርስቲያኑ ኅብረተሰብ አስተሳሰብ አንድ ዓይነት አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥም ይህ ጥያቄ ዋና ዋና የሥነ-መለኮት ትምህርቶች በሚለው ርእሰ ጉዳይ ውስጥ ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ተነሥቶ ያወዛግብ የነበረ ነው። እስከዛሬም የግሪክ ኦርቶዶክስ [Greek Orthodox] እና የሮም ካቶሊካዊት አብያተ ክርስቲያን [Roman Catholic Church] በዚህ ጉዳይ ስምምነት ላይ ለመድረስ አልቻሉም። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፥ መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ክርስቶስ ሥጋን በለበሰ ጊዜ ነው በማለት ከክርስቶስ ሥጋ መልበስ ጋር ስታያይዘው፥ የሮም ቤተ ክርስቲያን ግን ሠራዒነቱ ከዘላለም በፊት የሆነ ነገር ነው ብላ ታምናለች። የፕሮቴስታንት [Protestant] አብያተ ክርስቲያናትም ይህን ጉዳይ በሚመለከት ከሮም ቤተ ክርስቲያን አሳብ ጋር ይስማማሉ።

የመንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት ዘላለማዊ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ የተደገፈና በእግዚአብሔር ቃል የተረጋገጠ ነው። ከዮሐንስ 15፡26 በእርግጠኝነት የምንረዳው ይህ ግንኙነት ዘላለማዊ መሆኑን ነው። የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ባላት አቋም ላይ ያለው ግልጥ የሆነ ችግር፥ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ጊዜ በመሥራት ላይ ስለነበር ያኔ መሥረፁ ሐቅነት አለው የሚል መሆኑ ነው (መዝ. 104፡30)። መንፈስ ቅዱስ በፍጥረትም ሆነ ከዚያ በኋላ የነበረ ሥራው ሁሉ ሠራዒነቱን ያረጋግጣል።

የሠራዒነቱ መሠረታዊ ባሕርይ ዘላለማዊነቱን ያሳያል። የመንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት ፅንሰ-አሳብ ከመፈጠር፥ በሰው የአስተሳሰብ ክልል ውስጥ ከመሆን፥ በመጀመሪያ ከመኖር (ሕላዌነት) አሳብም ሆነ ከሰው ሰብአዊ ግንኙነት ውጭ የሆነና ለየት ያለ ጭብጥ ነው። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ መሥረፁ (መውጣቱ) ለሕልውናው አስፈላጊ ነበር። ያለ መንፈስ

ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱ አሁን ባለው መለኮታዊ ባሕርይ አይገኝም ነበር። የክርስቶስ ሥጋ መልበስ በጸጋ የሚዋሐዱትን የፍቅርንና የጽድቅን ባሕርያት ለመግለጥ የሚያገለግል ቢሆንም፥ የመንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት ከክርስቶስ ሥጋ መልበስ ጋር ሊወዳደር አይችልም። የክርስቶስ ሥጋ መልበስ ለመለኮት የማያስፈልግ ነበርና።

የመሥረፅና የመወለድ ግንኙነት። የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ሁለተኛውና ሦስተኛው የሥላሴ አካላት ከመጀመሪያው የሥላሴ አካል ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለመግለጥ የሚጠቀሙበት መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ የተወሰደ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ልጁ ሲናገር፥ መወለዱ ለዘላለም እንደሆነ የሚያረጋግጥ ሲሆን (መዝ. 2፡7) ከላይ እንደተመለከትነው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር ደግሞ መውጣት (መሥረፅ) ይለዋል። ቃላቱ ሊያቀርቡት የሚችሉትን እውነት ለመግለጥ፥ ለመረዳትም በቂ አይደሉም፥ ቢባልም እንኳ የትኛውም የሰው አስተሳሰብ ይህን ልዩነት ሊያሻሽለው አይችልም። ነገር ግን መውለድ የሚለው ቃል በምንም ዓይነት አሁን በምድር ከምናውቀው የመወለድ አስተሳሰብ ነጻና የማይወዳደር መሆኑንና ሠራዒነትም ዘላለማዊ መሆኑን ማስታወስ ይገባል። በተጨማሪ መውለድን ለመሥረፅ ልንጠቀምበት አንችልም፥ ምናልባት ክርስቶስ ከአብ ዘንድ ወጣ ማለት ብንችል እንኳን፥ መንፈስ ቅዱስ ተወለደ ማለት ግን አንችልም።

የመንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት ከአብና ከወልድ ስለመሆኑ። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት ብዙ ጊዜ በታሪክ የሚነሣው አወዛጋቢ ነገር፥ መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ከአብ ብቻ ነው ወይስ ከአብና ከወልድ? የሚለው ጥያቄ ነው። በ325 ከክርስቶስ ልደት በኋላ በኒቅያና፥ በ381 ከክርስቶስ ልደት በኋላ በቁስጥንጥንያ [Constantinople] የተደረጉት የመጀመሪያዎቹ ጉባኤዎች ያወጡአቸው የእምነት መግለጫዎች፥ መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ከወልድም ጭምር መሆኑን ባይገልጡም እንኳ በውስጠ ታዋቂነት የታመነ ነበር። በ589 ከክርስቶስ ልደት በኋላ፥ በቶሌዶ [Toledo] የተካሄደውና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናትን ብቻ የሚወክለው ጉባኤ ግን፥ ሥርፀት ከወልድም ጭምር ['ፈሊዮክዌ'/'filioque'] እንደሆነ የሚናገር ቃል በግልጥ በእምነት መግለጫው ላይ ጨመረ። ይህ ቃል በታከለ ጊዜ ምክር ያልተጠየቀችው የግሪክ ቤተ ክርስቲያን፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ትምህርቱን የማትቀበል መሆኗን ገለጠች። ይህች ቤተ ክርስቲያን ለሥርፀት አሳብ በዋናነት የምንጠቀምበትን የዮሐንስ 15፡26 ቃል ሥርፀት ከአብ ብቻ እንደሆነ ነው የሚናገረው ብላ ተከራከረች። የምዕራብ፥ ወይም የሮም ቤተ ክርስቲያን ግን፥ መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ከአብና ከወልድ መሆኑ ግልጥ ነው በማለት አሳቧን አጸናች። ለዚህም ገላትያ 4፡6 ''የልጁ መንፈስ'' ሮሜ 8፡9 ''የክርስቶስ መንፈስ''

የሚሉ ቃላት በማስረጃነት የሚጠቀሱ ሆኑ። በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ የተላከው በአብና በወልድ ነው በማለት (ዮሐ. 16፡7) በማስረጃነት ቀርቧል። *መሥረፅ* ከአብና ከወልድም ጭምር ነው የሚለው አሳብ የሮምና በተሐድሶ የተገኙት የሌሎች (ፕሮቴስታንት) አብያተ ክርስቲያናት የጸናና ቀጥተኛ አመለካከት ሆኗል።

የመንፈስ ቅዱስ ሠራዊነት ከሥራዎቹ ጋር ያለው ግንኙነት። የመሥረፅ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ለሥነ-መለኮት ትምህርት አዋቂዎች ብቻ የሚጠቅም ቴክኒካዊ አባባል ቢመስልም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚናገር ዋና አሳብ በውስጡ ይገኛል። ስለ ክርስቶስ ስንመለከት፥ ለዘላለም መወለዱ፥ ጊዜውን ጠብቆ የሰውን ልጅ ለመዋጀት ከሚፈጽመው ሥራ ጋር የተያያዘ ነበር። ክርስቶስ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ታዛዥ እንደሆነ፥ መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ በመሥረፅ ለአብና ለወልድ ታዛዥ ሆነ። ክብርን በፈቃደኝነት በመተው ራስን ማስገዛት፥ ሦስቱ የሥላሴ አካላት ለዘላለም የነበራቸውን ክብር ሳይቀነስና የመለኮትነት ባሕርያቸውን ሳያጡ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ዮሐ. 14፡16፥ 26፤ 15፡26፤ 16፡7)። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ስለ አብና ስለ ወልድ የሚደረግ ቢሆንም፥ በራሱ ኃይል ሥራውን ማከናወኑ ዘላለም ላለው መለኮትነትና ክብር ምስክር ይሆነዋል። ስለዚህ፥ መንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለም የተላከው በክርስቶስ ቦታ ሆኖ እውነትን ሊገልጥና፥ በተለይ ደግሞ የክርስቶስ ተልእኮ ታውቆ አብና ወልድ እንዲከብሩ ነው (ዮሐ. 16፡13-15)። ክርስቶስ እራሱን ትሑት ባደረገ ጊዜ ክብር እንዳልፈለገ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም የራሱን ክብር አይፈልግም።

የመወለድና የመሥረፅ መሠረታዊ የእምነት ትምሕርት መግለጫዎችን በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ውስጥም ማየት እንችላለን። አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን እንደላከ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስን እንጂ አብን ጨርሶ አይልክም። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ሁልጊዜ የራሱ ፈቃድ ለሆነው ለአብና ለወልድ ፈቃድ በመገዛት፥ በምድር ላይ ያለ ሥራውን ከግብ ያደርሳል እንጂ፥ አብንም ሆነ ወልድን አይልክም። የሥርፀት ፅንሰ-አሳብ በቀላሉ የሚገባ ባይሆንም፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ በሥላሴ መካከል ያለውን ግንኙነት በሰዎች ቋንቋ የሚያስረዳ ነው።

4. የመንፈስ ቅዱስ ባሕርያት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጡት የመንፈስ ቅዱስ ባሕርያት፥ እርሱ ፍጹም አምላክ እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ የሚገልጡ ናቸው። ቢያንስ ሰባት ነገሮችን በመጥቀስ ይህን ለመግለጥ ይቻላል።

1. መንፈስ ቅዱስ የሕይወት ባለቤት እንደሆነ ተገልጧል (ሮሜ 8፡2)። በዚህ ጥቅስ ረገድ የዘላለማዊ ሕይወት አስቀድሞም በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ ነበር። አሁን ግን ይህ ሕይወት እግዚአብሔር ፍጥረታቱ በዳግም ልደት መንፈሳዊነት ወይም ዘላለማዊ ሕይወት እንዲኖራቸው ማድረጉን ያሳያል።

2. ከዚህ በፊት እንደተገለጠው የአካላዊ ሕልውና ባሕርያቱ በርካታ ምስክሮች ናቸው፤

3. እግዚአብሔር ብቻ ሊኖረው የሚችለውን በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የመገኘት ባሕርይ መንፈስ ቅዱስም አለው (መዝ. 139፡7)፤

4. መንፈስ ቅዱስ ሁሉን አዋቂ ነው (1ኛ ቆሮ. 2፡10-11)፤

5. መንፈስ ቅዱስ ሁሉን አድራጊ ነው። ይህ በመፍጠር ሥራው ውስጥም ተገልጧል (ዘፍጥ. 1፡2)፤

6. ቅድስና በመንፈስ ቅዱስ ስም ውስጥ መገኘቱ፥ ቅድስና ባሕርይው መሆኑን ያመለክታል (ሉቃስ 11፡13)፤

7. የመንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊነትም በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጧል (ዕብ. 9፡14)። ማንኛውም የባሕርይ መግለጫ ማንኛውንም ነገር ሙሉ ለሙሉ የሚገልጥ አይደለም። ቢሆንም በግልጥ ከቀረቡት ባሕርያቱ የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገባ የታወቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ይቻላል።

5. የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች

የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት በሥራዎቹ ውስጥም ይታያል። የዚህ መጽሐፍ አብዛኛው ክፍል በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ መጠን፥ እዚህ ነጥብ ላይ መለኮትነቱ እንዴት በሥራው እንደተገለጠ መረዳቱ ብቻ ይበቃል። የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በሙሉ መለኮትነቱን የሚያመለክቱ ናቸው። የመፍጠር ሥራውን በሥዕላዊ አገላለጥ ለመጥቀስ ይቻላል (ዘፍጥ. 1፡2)። የመፍጠር ሥራ የመለኮት ሥራ መሆኑ ግልጥ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ዳግም የመፍጠር ሥራ ሌላው ሥዕላዊ መግለጫ ነው (ዮሐ. 3፡6)። በመንፈስ ለሞቱ መንፈሳዊ ሕይወትን መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። አማኞችን የመቀደስ ሥራውንም መጥቀስ ይቻላል (2ኛ ተሰ. 2፡13)። ያልተቀደሰውን መቀደስ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ምስክርነት እንዳለ የሚቀበሉ ሁሉ በሚሠራቸው ሥራዎች እንደተገለጠው፥ መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑን ፈጥነው በቀላሉ ለመረዳት አይቸገሩም። ስለ መንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ቻርልስ ሆጅ

በተናገረው ቃል ማጠቃለል ይቻላል፦ ‘‘ስለዚህ እርሱ አምልኮ የሚገባው ሆኖ ቀርቧል። በመጽሐፍ ቅዱሳችን የሥላሴን የእምነት ትምህርት እንደ መሠረታዊ የሃይማኖታችን እውነት ዘወትር እንድናስታውስ ያስገነዝበናል። ይህም በጥምቀት መሠረታዊ መመሪያና በሐዋርያት ቡራኬ ብቻ ሳይሆን፥ ያለማቋረጥ ወደ እርሱ እንድንመለከትና በመንፈሳዊ ጥቅማችን ሁሉ በእርሱ እንድንታመን፥ እንደ መለኮታዊ መምህራችንና ቀዳሻችን እንድናከብረውና እንድንታዘዘውም ነው።’’

ከአሳታሚው መግለጫ

ብሉይ ኪዳን የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን፥ ለእግዚአብሔር መጠሪያ ሦስት ታላላቅ ስሞች መሰጠታቸውን እንግራለን።

በመጽሐፉ ውስጥ እግዚአብሔር በዕብራይስጥ ቋንቋ በተደጋጋሚ ‘ኤል’ (‘El’) ወይም ‘ኤሎሂም’ (‘Elohim’) በሚል ስም ይጠራል። ኤሎሂም የሚለው ስም የእውነተኛው እግዚአብሔር ወይም የአሕዛብ አማልክት መጠሪያ ሊሆን ይችላል። በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ኤሎሂም የሚለው ስም ‘‘God’’ በሚለው ቃል ይተረጎማል። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የአሕዛብ አማልክት ‘‘አማልክት’’ በሚል ስያሜ ተጠቅሰው እናገኛለን። እውነተኛው አምላክ ግን ‘‘እግዚአብሔር’’ ወይም ‘‘አምላክ’’ ተብሎ ተጠቅሷል። ይህ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዘፍጥረት 1፡1 ነው። የቃሉ አተረጓጎም አከራካሪ ቢሆንም ‘‘ኃያል’’ መፈራትና መከበር የሚገባው አምላክ የሚለውን አሳብ የሚያጠቃልል ይመስላል። ኤሎሂም የሚለው ቃል ብዛትን የሚያመለክት በመሆኑ የሥላሴን አሳብ ያዘለ ነው። ስለሆነም በዚህ ስም ውስጥ ሦስቱ ሥላሴ ይገኛሉ።

ሁለተኛውና ዋነኛው የእግዚአብሔር ስም በዕብራይስጥ ‘ያህዌህ’ (‘Yahweh’) የሚለው ሲሆን፥ ይህ ስም እውነተኛ ለሆነው ጌታ፥ እግዚአብሔር ብቻ የተሰጠ ነው። በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ‘LORD’፥ ‘GOD’ ወይም ‘Jehovah’ ተብሎ ተተርጉሟል። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ‘‘እግዚአብሔር’’ ተብሎ ይጠራል። ‘‘ያህዌህ’’ የሚለው ስም በተለይ ለእስራኤል ኪዳን የገባውን እና እውነተኛውን የቃል ኪዳን አምላክ የሚያመለክት ነው። ይህ ስም ከፍጥረት ጋር በተያያዘ ሁኔታ በዘፍጥረት 2፡4 ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰ ቢሆንም፥ ትርጉሙ ግን በዘጸአት 3፡13-14 ላይ እግዚአብሔር ራሱ ለሙሴ ‘‘ያለና የሚኖር እኔ ነኝ’’

በማለት ራሱን የገለጠበት ነው። ይህ ስም እግዚአብሔር ብቸኛና ዘላለማዊ፥ በራሱ ሕልውና ያለው አምላክ ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ልዩ ልዩ ጠባዮች ለማሳየት ከሌሎች ስሞች ጋርም ተቀናጅቶ ይገኛል፤ ይኸውም 'ይርኤ' (ዘፍጥ. 22፡13-14)፥ 'ንሲ' (ዘጸ. 17፡15)፥ ''ሰላም'' (መሳ. 6፡24)፥ ''ጽድቅ'' (ኤር. 23፡6)፥ ወዘተ...።

ሦስተኛው በብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ ቋንቋ የምናገኘው የእግዚአብሔር አምላክ ስም 'አዶናይ' ('Adonai') ሲሆን፥ ትርጉሙም ''ጌታ'' ወይም ''አለቃ'' ማለት ነው። ይህ ስም በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ''Lord'' ወይም ''Master'' ተብሎ ተተርጉሟል። ቃሉ ጌትነትን የሚያሳይ ነው። ብዙ ጊዜ ኤሎሂም ከሚለው ስያሜ ጋር ተቀናጅቶ የሚገኝ ሲሆን (ዘፍጥ. 15፡2)፥ በዚህ አገባቡ የእግዚአብሔርን አለቅነት ወይም ጌትነት አጠንክሮ ያስገነዝባል። እነዚህ የእግዚአብሔር ስሞች በብሉይ ኪዳን ውስጥ በመቀናጀት ተጠቅሰዋል። በቅንጅት ከሚታወቁት ከነዚህ ስሞች ውስጥ ''ያህዌህ ኤሎሂም'' ወይም ''አዶናይ ኤሎሂም'' የሚሉት በብዛት ይገኛሉ።

3

መንፈስ ቅዱስ የተገለጠባቸው አምሳያዎች

መንፈስ ቅዱስ የተገለጠባቸው አምሳያዎች በብዙ የሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ የሚገባቸውን ያህል በቂ ስፍራ የማይሰጣቸው ናቸው። አምሳያዎች በራሳቸው ውሱን ቢሆኑም፥ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትን ለማነልበትና ለመግለጥ መሰጠታቸው ግን ግልጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ እንደተሰጡ መመሪያዎችና ትእዛዛት፥ የራሳችንን እምነትና የሰዎችን አስተሳሰብ በከፍተኛ ሁኔታ በማከል አምሳያዎችን ለመመልከት መሞከር፥ ተገቢ ባልሆነ መንገድ እንድንጠቀምባቸው የሚያጋልጠን ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉ እንደ ሌሎች ሥዕላዊ መግለጫዎች (ምሳሌዎች፥ ምልክቶች፥ ንጽጽሮችና ነገሮች ወዘተ.) አምሳያዎች እውነትን ለመረዳት የሚረዱን በከፍተኛ ጥንቃቄ ስንጠቀምባቸው ነው። አንዳንዶች ይህን ምክንያት በማድረግ አምሳያዎችን በተወሰነ መንገድ ብቻ ይጠቀሙባቸዋል። ከዚህ አንጻር ስንመለከት፥ ለብዙ ጊዜያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጡት አምሳያዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የተጠቀምን ባቸው በጣም የተወሰኑት ብቻ መሆናቸውን እንረዳለን። በዚህ ክፍል በቀረበው የአምሳያዎች ጥናት ግን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታ ባይገለጡ እንኳን፥ ለግንዛቤ ቀለል ያሉና ምቹ አምሳያዎችም ታክለዋል።

አምሳያዎች መንፈሳዊ እውነትን ለመግለጥ ካላቸው ጥቅም አኳያ በሚገባ አልተገነዘብናቸውም። ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር [Lewis Sperry Chafer] ስለዚህ ጉዳይ ያለን ግንዛቤ መጎልበት እንዳለበት የሚከተለውን ተናግሯል፦

"ማንኛውም ዓይነት የንግግር መግባቢያ የራሱ የሆነና የተረጋገጠ እውነት አለው። ስለዚህ ንግግሩ በቀረበበት ዘይቤ ምክንያት የያዘው እውነት ሊሰጠው ከሚገባው ግምት በታች መሆን የለበትም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የአነጋገር ዘይቤዎች ሁሉ በቀጥታ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርጠው አገልግሎት ላይ የዋሉ ስለሆኑ፥ በምንም ዓይነት የሰዎችን አስተሳሰብ የሚወክሉ አይደሉም ብለን የምናስብበት ምክንያት መኖር የለበትም።"

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ በሚያስተምረው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ ከተጠቀመባቸው በርከት ያሉ አምሳያዎች ጋር ሲወዳደር፥ ለመንፈስ ቅዱስ የተጠቀመባቸው አምሳያዎች አነስተኞች ናቸው። ቢሆኑም የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ትኩረት በመስጠት ለመግለጥ የተሰጡ እነዚህ አምሳያዎች ባይኖሩ ኖሮ፥ ይህን ትምህርት ሙሉ ለሙሉ መረዳት እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ነበር። ከዚህ በመቀጠል አምሳያዎቹን በዝርዝር እንመለከታለን።

1. ኃይልን መልበስ

በሉቃስ 24፡49 ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ "እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ። እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" የሚል ትእዛዝ ሰጥቷቸው ነበር። በዚህ ክፍል ክርስቶስ ያመለከተው በጰንጠቆስጤ ዕለት ስለተፈጸመው የመንፈስ ቅዱስ መውረድና የሰዎች በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ልምምድ መሆኑ ግልጥ ነው። በዚህ አገላለጥ የልብስ አምሳያ ሰብአዊ ድካምን የመሸፈን ውጫዊ ባሕርይ የሚያመለክት ሲሆን፥ ተግባሩም ከላይ እንደሚለበስ ልብስ የሚታየው አካል መለኮትን ወክሎ መቅረቡን መጠቆም ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ እውነትን ለመግለጥ የመልበስ አምሳያ በተደጋጋሚ ቀርቧል (2ኛ ቆሮ. 5፡3፤ ኤፌ. 4፡24፤ 6፡11-17፤ ቈላ. 3፡10፥ 12፤ 1ኛ ተሰ. 5፡8፤ ራእይ 19፡8፥ 13-14)። ኤፍ. ኢ. ማርሽ [Marsh] የተባለ የሥነ-መለኮት ሊቅ ይህን አምሳያ ለመግለጥ ባቀረበው ጥልቅ ውይይት ውስጥ እኛ ራሳችን በምንለብሳቸውና (ሮሜ 13፡12፤ ኤፌ. 4፡24፤ 6፡11፥ 14፤ ቈላ. 3፡10፥ 12፤ 1ኛ ተሰ. 5፡8) እግዚአብሔር በሚያለብሰን መንፈሳዊ አልባሳት መካከል ልዩነት እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር አሳይቷል። ኃይልን መልበስ እግዚአብሔር ከሚያለብሰን አልባሳት መካከል አንዱ ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር ተያይዞ እርሱ በውስጣችን ለሚሠራው ሥራ ውጫዊ መረጃ (ማረጋገጫ) በመሆን የተሰጠንን ተልእኮ በብቃት እንድንወጣ የሚያስችለን ይህን ኃይል መልበስ ነው። በሐዋርያት አገልግሎት ውስጥ በሰዎችም ሆነ በሁኔታዎች ላይ የተገለጠው ኃይል ይህ ነበር።

2. ርግብ

ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ የተገለጠው የመንፈስ ቅዱስ አምሳያ ርግብ ነበር። በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳያ በክርስቶስ ላይ መውረዱን አራቱም ወንጌላት ገልጠውታል (ማቴ. 3፡16፤ ማር. 1፡10፤

ሉቃስ 3፡22፤ ዮሐ. 1፡32)። ከእነዚህ ክፍሎች በስተቀር ይህን አምሳያ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ተብራርቶ አናገኝም። በአዲስ ኪዳን የርግብ ስም የተጠቀሰባቸው ሌሎች ሁለት ስፍራዎች አሉ። ክርስቶስ ''እንደ ርግብ የዋሆች'' (ማቴ. 10፡16) ስለመሆን የተናገረበት ክፍል፥ በቤተ መቅደስ ውስጥ ለመሥዋዕት ይቀርቡ ዘንድ ስለመሸጣቸው (ማቴ. 21፡12፤ ማር. 11፡15፤ ሉቃስ 2፡24፤ ዮሐ. 2፡14፥ 16) የሚናገሩት ክፍሎች ናቸው።

በብሉይ ኪዳን ርግብ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት እንደሆነ ተጠቅሷል። አምሳያነቱም ከመንፈስ ቅዱስም ይልቅ የክርስቶስ ነው። ከጥፋት ውኃ በኋላ በኖኅ የተለቀቀችው ርግብ፥ አንዳንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት የሚያሳይ ዓይነተኛ ምሳሌ ተብሎ ይጠቀሳል። ማኪንታሽ [Mackintosh] የተባለ የሥነ-መለኮት ሊቅ ይህች ርግብ ''በክርስቶስ ያለውን እረፍትና ድርሻውን የሚያገኝ የታደሰ አእምሮን የምታሳይ ናት'' ብሏል። ርግብ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆና በግልጥ የቀረበችው በወንጌላት ውስጥ ብቻ ነው።

ርግብ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆና ስትቀርብ፥ መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዩ ቢያንስ አራት ነጥቦችን ከተፈጥሮዋ መጥቀስ እንችላለን። እነዚህም፡-

1. ውበት፥ 2. ጨዋነት፥ 3. ሰላም፥ 4. ሰማያዊ ባሕርይና አመጣጥ ናቸው። የርግብን ጠቅላላ ባሕርያት ስንመለከት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆና የመቅረቧን ተስማሚነት እንገነዘባለን።

3. የመንፈሱ መያዣ

በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ የተጠቀሰው 'አራቦን' የሚለው የግሪክ ቃል ''መያዣ'' የሚል ትርጉም አለው (2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ 5፡5፤ ኤፌ. 1፡14)። ይኸውም አንድ ነገር ለማድረግ ቃል መግባት ወይም ቃልን መስጠት ማለት ነው። ታየር የተባለው ጸሐፊ በግሪክ-እንግሊዝኛ መዝገበ-ቃላቱ ''ቀብድ'' ብሎ ተርጉሞታል። መያዣው መንፈስ ቅዱስ የሚሰጣቸው ስጦታዎች ሳይሆኑ፥ እራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱ አብ ሊሰጠን ቃል ለገባልን፥ ገና ላልተቀበልናቸው፥ ግን የራሳችን ለሆኑት ወደፊት ደስታችንን ሙሉ ለሚያደርጉልን ስጦታዎች ሁሉ እንደ ቀብድ ነው። ማርሽ ምሳሌ በመጠቀም እንደሚከተለው ገልጦታል። አንድ ሕፃን አባቱ ያወረሰው ንብረት በሙሉ የእርሱ ለመሆኑ ምንም ጥርጣሬ እንደሌለው ሁሉ፥ አሁን ባይጠቀምበትና ባይደሰትበም እንኳን፥ ሁሉም

ነገር በንብረትነት የእርሱ ለመሆኑ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። እንዲሁም የጌታ ልጆች በመሆናችን እኛም የጌታ የሆነውን እንደ ልጁ የመውረስ መብትና ተስፋ አለን።

መንፈስ ቅዱስ የምን መያዣ ነው ብለን ብንጠይቅ፥ መልሱን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይሰጠናል። ይኸውም ወደፊት ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ማንኛውም በረከት የሚል ነው። ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ሕልውና ተረጋግጦልናል። የእርሱ ሕልውና ዋስትናችን ነው። ርስታችን፥ ደኅንነታችን፥ ክብራችን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ክርስቶስን ወደ መምሰል መጓዛችንና ከኃጢአት ክፉ ኃይል ነጻ መሆናችን ሁሉ *መንፈስ ቅዱስን* በመቀበላችን ተረጋግጧል።

4. እሳት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኙ ብዙ ምሳሌዎች፥ እሳትም ለተለያየ ትርጉም ጥቅም ላይ ውሏል። ለምሳሌ ርግብ የክርስቶስም የመንፈስ ቅዱስም ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል። ማርሽ የተባለው ጸሐፊ መንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰሉን ከመጥቀስ ሌላ፥ ስድስት ምልክቶችን እንደሚከተለው አቅርቧል፦

1. የእግዚአብሔር ሕልውና ምልክት (ዘጸ. 3፡2)፥ 2. እግዚአብሔር ሰዎች ያቀረቡትን መሥዋዕት የመቀበሉ ምልክት፥ (ዘሌዋ. 9፡24፤ 1ኛ ነገሥት 18፡38፤ 2ኛ ዜና. 7፡1)፥ 3. የእግዚአብሔር ጥበቃ ምልክት (ዘጸ. 13፡21፤ ዘካ. 2፡5)፥ 4. የእግዚአብሔር ቅጣትና ፈተና ምልክት (ሚል. 3፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡7፤ ዕብ. 12፡29፤ ራእይ 1፡14)፥ 5. የእግዚአብሔር ቃል ምልክት (ኤር. 5፡14፤ 20፡9)፥ 6. የእግዚአብሔር ፍርድ ምልክት (ዘሌዋ. 10፡2)።

እሳት አምሳያ ሆኖ የቀረበለት ሰባተኛ ጉዳይ *መንፈስ ቅዱስ* ነው። በጳንጠቆስጤ እለት *መንፈስ ቅዱስ* ሥራውን ባከናወነበት ወቅት "እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው። በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው" (ሐዋ. 2፡3)። ወዲያውም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ (ሐዋ. 2፡4)። በዚህ ቦታ እሳት ለምን እንደታያቸውና ትርጉሙ ምን እንደሆነ አልተገለጠም። ከዚህ በፊት የእሳት አምሳያ የተጠቀሱባቸውን ክፍሎች መሠረት በማድረግ፥ ሐዋርያት ከፊታቸው ባለው አገልግሎታቸው እግዚአብሔር አብሯቸው እንደሚኖር፥ እንደሚጠብቃቸው፥ እንደሚያጽናናቸው፥ እንደሚቀድሳቸውና አገልግሎታቸውን እንደሚያጸና ማሳየቱ ነበር ለማለት እንችላለን። በምድረ በዳ አዲስ በተሠራው የመገናኛ ድንኳንም ሆነ፥ ሰሎሞን ባሠራው አዲስ

ቤተ መቅደስ (ዘጸ. 40፡34፤ 1ኛ ነገሥት 8፡10-11) ላይ በማታ እንደ እሳት፥ ቀን ደግሞ በደመና የተገለጠው ዓይነት ሁኔታ በጳንጠቆስጤ ዕለትም መታየቱን እንገነዘባለን። ይህ በፈታቸው ለነበረው ኣገልግሎትና ምስክርነት እነርሱን ለመለየት የተደረገ ነበር።

በማቴዎስ 3፡11-12 "በእሳት ያጠምቃችኋል" የሚለው ቃል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚያያዝ ኣይመስልም። ምክንያቱም ቀጥሎ ያለው ቃል ስለ ክርስቶስ ሁለተኛ መምጣትና "ገለባን በማይጠፋ እሳት ስለማቃጠል ስለሚናገር" (ማቴ. 3፡12) ባለንበት የጸጋ ዘመን የጀመረው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፥ በሺሁ ዓመት መጀመሪያ ከሚኖረው የእሳት ጥምቀት ጋር በተነጻጻሪነት መቅረቡን ከዚህ እንረዳለን።

5. ዘይት

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በኣዲስ ኪዳን በእግዚኣብሔር ሰዎች ሕይወት ውስጥ ዘይት ትልቅ ስፍራ ነበረው። በማንኛውም ጊዜ ስለ ዘይት ዋነኛ ኣምሳያነት ስናስብ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ኣገልግሎት እንደሚናገር እናያለን። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ፥ ቅድስት በተባለው ስፍራ የነበረው መቅረዝ ያለማቋረጥ ብርሃን እንዲሰጥ ያደረገው የወይራ ዘይት፥ የመንፈስ ቅዱስን የመግለጥና የኣብርሆት ኣገልግሎት ያሳያል። ከዘይቱና ከሚሰጠው ብርሃን በስተቀር የክርስቶስን ክብር የሚገልጠው የተለያየ ቅብ የመቅረዝ ማስቀመጫ የጎብስቱ ጠረጴዛ እና ሌሎች እቃዎች ሙሉ በሙሉ ጨለማ በሆነ ስፍራ ነበሩ። ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የመድረሻው መንገድ ገና ቀናና ቀጥተኛ ኣልነበረም (ዘጸ. 27፡20-21)።

በብሉይ ኪዳን ለመሥዋዕት ይቀርቡ በነበሩ ነገሮች ውስጥ ዘይት ተፈላጊነት ያለው ነገር ነበር። ትልቅ ክፍልም ነበረው። በእህል ቁርባን ውስጥ (ዘሌዋ. 2፡1-16) ዘይቱ ከዱቄት ጋር ከመደባለቁ ሌላ በዱቄቱም ላይ እንዲፈስ ይደረግ ነበር። ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ፡- "ይህ ሁሉ የክርስቶስ ሕይወትና ኣገልግሎት በልዩ መንገድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን፥ ግንኙነቱ ክርስቶስ በምድር ላይ ሰው ስለሆነ፥ ለተግባሩ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብርታትን እንደሚያገኝ ወይም እንደሚጠነክር የሚያሳይ ነው" ብሏል። ዘይት ለምጻም ከነጻ በኋላ በቤተ መቅደስ በሚፈጸመው ሥርዓት ውስጥም ኣገልግሎት ላይ ይውል ነበር (ዘሌዋ. 14፡10-29)።

ዘይት ካህናት ለኣገልግሎት በሚሾሙበትም ሆነ፥ ለመገናኛው ድንኳን ኣገልግሎት ለእግዚኣብሔር በሚሰጡበት (የምረቃ) ሥነ-ሥርዓት ወቅት ተግባር ላይ ይውል ነበር (ዘጸ. 40፡9-16፤ ዘሌዋ. 8)። ዘይት

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው ግንኙነት ሊቀ ካህናችን የሆነውን ክርስቶስን ለሚወክለው ለአሮን ብቻ ሳይሆን ለልጆቹም ያገለግል ነበር። ይህ ሁኔታ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በክርስቶስ ብቻ ሳይወሰን ለክርስቲያኖችም እንደሚሆን የሚያሳይ ነው። የመገናኛው ድንኳን፥ መሠዊያውን ጨምሮ በውስጡ ያሉት ነገሮች በሙሉ በዘይት ይቀቡ ነበር። ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሰውን በመዋጀት ረገድ የሚያከናውናቸውን ሥራዎች ያመለክታል። ዘይት ንጉሥን በማንገሥ ሥርዓት ውስጥ ያገለግል ነበር (1ኛ ሳሙ. 10፡1፥ 16፡13፤ 1ኛ ነገሥት 1፡39፤ መዝ. 23፡5 ወዘተ...)። ይህም በንጉሥነት አገልግሎት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያለውን ተግባር ይገልጣል።

ዘይት ለምግብነት ማገልገሉ የተለመደ ሲሆን (ራእይ 6፡6) አንዳንዴም ለመድኃኒትነት (ማር. 6፡13፤ ያዕ. 5፡14)፥ አልፎ አልፎም እንደ ገንዘብ ለዕቃዎች ልውውጥ አገልግሏል (1ኛ ነገሥት 5፡11)። በእነዚህ የዘይት አገልግሎቶች ውስጥ የተለየ ትርጉም ለማግኘት አንችልም። በአሥሩ ቆነጃጅት ምሳሌ ውስጥ (ማቴ. 25፡3-8) በባሕላዊ ልማድ ኩራዙ ብርሃን እንዲሰጥ የሚያደርገው ዘይት፥ የመገለጡ መንፈሳዊ ትርጉም፥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ማመልከት መሆኑ ግልጥ ነው። እንዲሁም በመዝሙር 45፡7 እና በዕብራውያን 1፡9 የተጠቀሰውን "የደስታ ዘይት" እዚህ ላይ ማንሣት ይቻላል።

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ሥዕላዊ በሆነ መንገድ እንደተጠቀሰው፥ ዘይት የሚከተሉትን ተግባሮች የሚያሳይ አሳብ ያዘለ ነው፡- የመቀደስ፥ የመግለጥ፥ የአብርሆት፥ የመለየት፥ የመፈወስ እና የመደገፍ። አምሳያዎች ሁልጊዜ ለዋናውና ለእውነተኛው ነገር ጥላ ስለሆኑ እጅግ አጥጋቢ በሆነ መንገድ የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት ይገልጣሉ።

6. ማኅተም

በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ ያህል መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች የመዋጀት ተግባር ማረጋገጫ ማኅተም ሆኖ ቀርቧል (2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ ኤፌ. 1፡13፤ 4፡30)። በእነዚህ ክፍሎች መንፈስ ቅዱስ ማኅተም አድራጊውን ሳይሆን ማኅተሙን ሆኖ መቅረቡ ግልጥ ነው። እግዚአብሔር በአማኙ ውስጥ ማደሩና መኖሩ በአማኝ ውስጥ የመጀመሪያው የመዋጀት ሥራ ሙሉ ለሙሉ ወደ ፍጻሜ ለመምጣቱ ምልክትና ማኅተም ነው። ማኅተም የሚለው ቃል የሚከተሉትን ነገሮች ያመለክታል፡-

1. ዋስትናን፥ 2. ደኅንነትን ወይም ጥበቃን፥ 3. ባለቤትነትን፥ 4. ሥልጣንን። ማርሽ በተጨማሪ፡- 5. "ማኅተም በሰዎች መካከል

ያለቀለት የንግድ ውልን''፥ 6. የእውቅና ምልክትነትን፥ 7. ምስጢራዊነትን፥ 8. ማስገደድን (ማዘዝን) እንደሚያሳይ አሳብ ካቀረበ በኋላ፥ ''ማኅተም በሚያትመው ነገር ላይ ቅርፁን ወይም አሻራውን ይተዋል'' ብሏል። እነዚህ ነገሮች በሙሉ በአማኝ ሕይወት ውስጥ ግሩም ፍጻሜ አግኝተዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር የመዋጀት ቃል ኪዳኑን እንደሚፈጽም የሚያረጋግጥ መተማመኛና ዋስትና ይሰጣል።

7. አገልጋይ

መንፈስ ቅዱስ በሥራው ብዙ ጊዜ የአገልጋይን ስፍራ ይይዛል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያገለግል ዘንድ ወደ ዓለም እንደተላከ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም ያገለግላል። ከብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት ለመግለጥ ልንጠቀምበት የምንችለው፥ የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሚስት እንደፈለገለት የሚናገረውን ታሪክ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በግልጥ ባያሳይም ተመሳሳይነቱን ለማወዳደር ያገለግላል። የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሙሽራ ፈልጎ እንዳገኘለት፥ መንፈስ ቅዱስም የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ለሆነው ለክርስቶስ ሙሽራ ይፈልግለታል። ልክ እንደ አብርሃም አገልጋይ ሙሽራዋን በማግኘትና በማዘጋጀት በመጨረሻም ለክርስቶስ በማቅረብ ተልእኮውን በተሳካ ሁኔታ ይወጣል። የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሚስት ለማግኘት ያለፈበት ዝርዝር ታሪክ ወደ ሩቅ አገር መጓዙ፥ ለሙሽራዋ ስጦታ መስጠቱ፥ ሙሽራዋ ሙሽራውን ለመቀበል ውሳኔ ያደረገችው እራስዋ መሆንዋ፥ በመጨረሻም ሙሽራዋ ሁሉን ነገር ትታ ወደ ሙሽራው መምጣትዋ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ በአሁኑ ጊዜ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ እያመጣ የክርስቶስ ሙሽራ ለማድረግ የሚሠራውን ሥራ አምሳያነት በሚገባ ይገልጣል።

8. ውኃ

ውኃ እጅግ በተትረፈረፈ መጠን የመፈጠሩ ሁኔታ ወሰን የማይገኝላቸውን ነገሮች ለመግለጥ ጥሩ ምሳሌ ሆኗል። በዚህ መልኩ ያየነው እንደሆነ፥ በጥፋት ውኃና በቀይ ባሕር የተገለጠውን የእግዚአብሔር ብርቱ ፍርድ ያሳያል። ውኃ በምሳሌነት ያገለገለበት ሁለተኛ አስፈላጊ ነገር፥ በእውነተኛነቱ ተወዳዳሪ የሌለውና መጠነ ሰፊ የሆነ መገለጥ የሚሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ. 3፡5፤ ኤፌ. 5፡26)። ውኃ ቅኔያዊ በሆነ የአነጋገር ዘይቤ ታላቅ ሥቃይን፥ ችግርን፥ መከራን፥ ለመግለጥም አገልግሏል (መዝ. 69፡2፥ 14)። በዚህ ስፍራ ልናተኩርበት የተፈለገው ሦስተኛ የውኃ አምሳያ ግን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ሦስተኛ የሥላሴ አካል ሆኖ የቀረበው መንፈስ ቅዱስ ነው።

ከዚህ በታች መንፈስ ቅዱስና አገልግሎቱ በውኃ አምሳያነት የቀረቡባቸውን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ሁለት ጥቅሶች እንመለከታለን። በዮሐንስ 4፡14 ጌታ ኢየሱስ የሰማርያይቱን ሴት ባነጋገረበት በዚህ ክፍል፡- ‘‘እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ’’ ብሎ ሲናገር እንመለከተዋለን። ይህን ክፍል ከዮሐንስ 7፡37-39 ጋር በማገናዘብ፥ ጌታ የሚሰጠው ውኃ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት እንችላለን። ምክንያቱም በሁለተኛው ክፍል ውኃ የመንፈስ ቅዱስ አምሳያ መሆኑ በግልጥ ቀርቧል፥ ‘‘ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል፤ ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ። ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና’’ (ዮሐ. 7፡37-39ን ከሚከተሉት ጥቅሶች ጋር ያወዳድሩ፤ መኃልየ ዘሰሎሞን 4፡12፥ 15፤ ምሳሌ 5፡15-16፤ ኢሳ. 41፡17-18፤ 43፡2፥ 19-20፤ 58፡11፤ ኤር. 31፡12)። በዮሐንስ 4 የታየው የውኃ ጉድጓድ፥ በዮሐንስ 7 የሚፈልቅ ምንጭ ሆኖ እንመለከታለን። ይህ በጳንጠቆስጤ ዕለት የጀመረ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በአሁኑ ዘመንም እንደሚቀጥል የሚያሳይ ነው። ይህ አምሳያ ከመንፈስ ቅዱስ የሚፈልቀው የዘላለም ሕይወት፥ እንዲሁም እጅግ ሰፊ የሆነውን ኃይሉንና የማንጻት አገልግሎቱን ሁሉ ይገልጣል። ስለዚህ ይህ አምሳያ እነዚህን ነገሮች መግለጥ ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ሆነን መንፈሳዊ በረከት ሁሉ ከውስጣችን እንዲፈልቅ እራሳችንን እንድንሰጥ ሊቀሰቅሰን ይገባል።

9. ነፋስ

የነፋስና የመንፈስ ቅዱስ ጠባይ በብዙ ረገድ ተመሳሳይ ስለሆነ፥ ነፋስ አምሳያ ሆኖ በመቅረቡ መንፈስ ቅዱስን በጥሩ ሁኔታ ይገልጠዋል። የነፋስ ኃይል፥ የማይታይ መሆኑ፥ ቁሳዊ ያልሆነ ተፈጥሮውና የተፈጠረበት ታላቅ ዓላማ በመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውናና ሥራ ውስጥ ያሉ ታላላቅ ነገሮችን ይገልጣል። ነፋስ በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ከተጠቀሰበት ከዘፍጥረት 8፡1 ጀምሮ በመጨረሻ እስከተጠቀሰበት እስከ ራእይ 7፡1 ድረስ በሁሉም ቦታ የተጠቀሰው በተለመደ መልኩ ሲሆን፥ ሦስት ክፍሎች ብቻ ነፋስን የመንፈስ ቅዱስ አምሳያ አድርገው አቅር በውታል።

በዮሐንስ 3፡8 መንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን በሚመለከት ለሚያከናውነው ሥራ በነፋስ ምሳሌነት ተገልጧል። ‘‘ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል። ድምጹን ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም። ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።’’ በዚህ ክፍል መንፈስ ቅዱስ ቁሳዊ ተፈጥሮ ስለሌለው ባይታይም መለኮታዊ ተግባሩን በብቃት እንደሚፈጽም የሚያሳይ ገለጣ ቀርቧል።

በሐዋርያት ሥራ 2፡1-2 ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ምልክት ሆኖ እናየዋለን። ‘‘በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ። ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው’’ በዚህ ስፍራ ነፋስ በግልጥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባይያያዝም፥ ለተፈጸመው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጫዊ ምልክት ሆኖ መታየቱ የማያሻማ ነው። ነፋስ ‘‘ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ልክ እንደዚሁ ሞላው...በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው’’ (ሐዋ. 2፡4)። ይህ የሚያሳየው የመንፈስ ቅዱስን ብርቱ ኃይል ሲሆን፥ እግዚአብሔር ሥልጣኑን የገለጠው በዚህ መንፈስ መምጣት ነው።

ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ አምሳያ ሆኖ የቀረበበት ሦስተኛ ሁኔታ ደግሞ የብሉይ ኪዳን ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው እንደጻፉት በተገለጠበት በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡21 ነው። ‘‘በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።’’ በዚህ ክፍል ነፋስ የሚል ቃል ባይገኝም፥ በነፋስ ተገፍቶ የሚንቀሳቀስ የመርከብ ሥዕል በግንዛቤ ውስጥ እንዳለ በቀላሉ ማየት እንችላለን። ከዚህም ነቢያት መልእክታቸውን ይሰጡ ዘንድ አቅጣጫ የሚያሳያቸውና ጉልበትና ብርታትን የሚሰጣቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ መልእክታቸው ከእግዚአብሔር እንደነበር ማረጋገጥ እንችላለን።

አምሳያዎችንና ምልክቶችን በሙሉ በአንድነት ያጠቃለልናቸው እንደሆነ፥ አብዛኛው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በግልጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፍሮ እናገኛለን። በመንፈስ ቅዱስ ተረትቶ እራሱን ያስገዛ አማኝ፥ ከላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነውን ኃይል በመልበስ በመንፈስ ቅዱስ ሕልውና ዋስትና አማኝቶ፥ ተቀድሶና ተቀብቶ ለአገልግሎት ይለያል። የክርስቶስ ኢየሱስን ፍጹምነት መረዳት እንችል ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን በሙላት ይገልጥልናል። የተትረፈረፈ ኃይልና ከፍተኛ ዓላማ ያለው መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ይሠራል። እያንዳንዱ አስፈላጊ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስቀድሞ በተለያዩ አምሳያዎች በመገለጡ፥ ለዚህ ለተከበረና ወሰን ለሌለው አካል ልባችንንና ሕይወታችንን በመስጠት ልናመልከው፥ ልንወደውና፥ ልንታዘዘው ይገባል።

— ክፍል ሁለት —

መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን

4

መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ውስጥ

የ19ኛው ክፍለ-ዘመን የሥነ-መለኮት ሊቅ የነበረው ታላቁ የሆላንድ ተወላጅ አብርሃም ካይፐር [Abraham Kuyper]፥ በዓይነተኛ ወይም በዋና ሥራው መጀመሪያ ‹‹የመንፈስ ቅዱስ ሥራ›› በሚል ርእስ ሥር ሲገልጥ፥ ማንኛውም ጠንቃቃ የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ እምነት ትምህርት አጥኚ ልብ ሊለውና ሊያስተጋባው ስለሚገባ አንድ ነገር እንዲህ በማለት ጽፏል፦ ‹‹ማንኛውም ሰው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ለማስተማር በሚዘጋጅበት ጊዜ፥ ከመቼውም ይልቅ የመለኮታዊ ምሪት አስፈላጊነት በጥልቀት ይሰማዋል። በቃላት ለመግለጥ ከምንችለው በላይ የእግዚአብሔርንና የነፍስን ጥልቅ ምሥጢር የሚነካ ጉዳይ ስለሆነ፥ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የቤተሰቡን ጥብቅ ጉዳይ በምሥጢር እንደሚጠብቅ ሁሉ፥ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥም ነፍሳችን ከሕያው እግዚአብሔር ጋር ያላትን ቅርበት የሚያሳየውን የተቀደሰ ምሥጢር ስናጠና አቀራረባችን በከፍተኛ ጥንቃቄና በተሰበረ ልብ መሆን አለበት።››

ለእግዚአብሔር ላደረች ነፍስ አስደናቂ ደስታን ማጎናጸፍ ዓላማው የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሠረተ አሳብ የተመሠረተው ብዙ ጊዜ ግልጥ በሆነ መገለጥ ላይ ነው። ጉዳዩን በሚያጠኑ ሁሉ ዘንድ በከፍተኛ ጥንቃቄ መተርጎምን የሚጠይቅ ስለሆነ፥ ስሕተቶችን ለማስወገድ ሲባል በዚህ ክፍል አንዳንድ ሁኔታዎች በመጠነኛ ጥልቀት ብቻ ተገልጠዋል። ብዙውን ጊዜ እጅግ ሰፊ የሆኑ እውነቶች የተገለጡት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተሠራጭተው በሚገኙ ጥቂት ክፍሎች ነው። ወሰን የሌለውን እውነት አብጠርጥሮና ተንትኖ ለማቅረብ መጣጣር፥ ከርእሱ እጅግ ሰፊነትና በየዘመናቱ ከተከሠቱ እውነትን የማዛባት ወይም ችላ የማለት አደገኝነት ጋር ሲነጻጸር፥ ከንቱ ወይም ፍሬ ቢስ ድካም መሆኑ ሁሉም በመጠኑ ሊሰማው ይገባል።

እስካሁን ስለ ጉዳዩ ከተጻፉ ጽሑፎች አንጻር ስናጤነው በአተረጓጎም ረገድ ሁለት ከፍተኛ አደጋዎች መታየታቸው የተለመደ ነው። የመጀመሪያው፥ ልምምዳችንን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ልንተረጉመው ሲገባ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በልምምዳችን የመተርጎም ዝንባሌ ነው። ምንም እንኳን የሰው ልምምድ ከአንዳንድ የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርቶች ጋር እጅግ የተቀራረበ ቢሆን፥ በተለመደው መንገድ ላይሄድ

ይችላል። ቢሄድም በሚገባ አይተረጎም ይሆናል። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተመሠረተ መገለጥ ይልቅ፥ በሰዎች ልምምድ ላይ እንደነገሩ የተመሠረተ ትምህርት ታላቅ ጉዳት አለው። ሁለተኛው አደጋ ደግሞ ከመጀመሪያው አደጋ በተቃራኒ ርቆ የሚሄድና የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ ትምህርት፥ ሰዎች በተቀበሉት እውነት የሚወስን ነው። ብዙዎቹ መንፈሳዊ ነገሮች ሰዎችን ሁሉ የሚያረኩ አይደሉም። ብዙውን ጊዜ በዝርዝር የጥናት ዘዴ መጠቀምና በታወቁት መገለጦች ሁሉ መስማማት በመሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ ያለውን ውበት ሁሉ ለማሳየት አስፈላጊ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ለቀዝቃዛና ሕይወት ለሌለባቸው ተመራማሪዎች የተዘጋ ቢሆንባቸውም፥ መንፈስ ቅዱስ እራሱ ለሚያስተምራቸው ሰዎች ግን ግልጥ ነው። ይህን አስቀድሞ የተገነዘበ ሰው፥ የጠለቁ እውነቶችን ሊያስተምር በሚያስችለው መንፈስ ቅዱስ ላይ ተደግፎ ስሜቱን በማደስና በመነቃቃት ይቀርባል።

ከብሉይ ኪዳን ይልቅ በአሁኑ ጊዜ ለሚመለከተን ለአዲስ ኪዳን የበለጠ ቅድሚያ ትኩረት መስጠታችን ተገቢ ቢሆንም፥ ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን መገለጥ እጅግ ጠቃሚ የሆነ መንደርደሪያ እንደሚሆነን መዘንጋት የለብንም። በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል የሚደረግ ንጽጽር የአዲስ ኪዳንን እውነትና ውበት ይበልጥ እንድንረዳ ያደርገናል። መንፈስ ቅዱስን የሚመለከተውን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በአጠቃላይ ከዘላለም እስከ ዘላለም ካላየነው በቀር የተሟላ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ሥራው የእግዚአብሔር ታላቅ ዓላማ አካል እንደሆነና ፈቃድና ባሕርይውን የሚያመለክት መሆኑን እንረዳለን።

ማንኛውም የክርስትና እምነት ትምህርት ከእግዚአብሔር ታላቅ ዓላማ ጋር የመያያዙ ነገር መሠረታዊ ነው። ለመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትም የተለየ ሕግ የለም። መንፈስ ቅዱስ በጊዜ ውስጥ የተገለጠ ሥራ እንዳለው ሁሉ፥ በዘላለማዊነት ውስጥም የሚሠራው ሥራ አለ። መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ሥራው በግልጥ ቢታወቅም ዋና መገለጡ ግን በአዲስ ኪዳን ነው። ያለፈ ሥራው ግን በብሉይ ኪዳን ዘመን ለተገለጠ ተግባሩ ተገቢ መግቢያ እንደነበረ ለማየት እንችላለን። ስለዚህ በዚህ መሠረታዊ የውይይት አሳብ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ ለመወሰን ምንም ዓይነት ሙከራ አይደረግም።

በማንኛውም መንገድ ከፋፍለን የምናየውና በየትኛውም ጊዜ የተፈጸመው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥ ዘላለማዊና ቋሚ በሆነ የአምላክ ድንጋጌ ውስጥ የሚጠቃለል ነው። ሆኖም ለምርምርና ጥናት አመቺ ይሆን ዘንድ፥ አንዳንድ የአከፋፈል መንገድን መጠቀም አስፈላጊ ስለሚሆን "የመንፈስ ቅዱስ ሥራ" የሚል አንድ ርእስ እንዲኖር ማድረግ የሚጠቅም

ይሆናል። የሚያስገርመው ነገር ግን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ከአምላክ ዘላለማዊ ድንጋጌ ውስጥ አስፈላጊ ክፍል ለሆነው ለዚህ ጉዳይ የሰጡት ትኩረት እጅግ አነስተኛ መሆኑ ነው። የአምላክን ሁሉን ቻይነት የሚቀበሉ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለአጠቃላዩ ድንጋጌ በጣም አስፈላጊና መቅረት የሌለበት ክፍል በመሆኑ፥ በጥንቃቄም ሊጠና የሚገባ ስለመሆኑ ይስማማሉ። ይህን የእውነት ክፍል የመረመርን እንደሆነ፥ በደኅንነት እቅድ ውስጥ በቀጥታ የነበሩ ቢያንስ አራት ዋና ዋና ተግባራትን የሚገልጥ ሆኖ እናገኘዋለን።

1. የመንፈስ ቅዱስ ታዛዥነት

ሠራዒነትን የሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ወልድ ከአብ እንደወጣ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ የወጣ ነው ይላል። በሥላሴ አካላት ውስጥ ባለው በዚህ ዘላለማዊ ግንኙነት ላይ በመመሥረት፥ በዘላለማዊው የደኅንነት እቅድ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያውና ሁለተኛው የሥላሴ አካላት ለሆኑት ለአብና ለወልድ የመታዘዝን ስፍራ እንደወሰደ እንመለከታለን። በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ታዛዥነት እንደተገለጠው (ዮሐ. 14፡16-17፥ 26፤ 15፡26፤ 16፡7፥ 13)፥ የመንፈስ ቅዱስ ታዛዥነት በአንድ የተለየ ዘመን የተወሰነ ሳይሆን በየትኛውም ዘመን ነበር። በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ክፍሎች የመንፈስ ቅዱስ ታዛዥነት ቅደም ተከተል ተዛብቶ አያውቅም። ወልድ ለአብ ሁልጊዜ ታዛዥ እንደነበረ መንፈስ ቅዱስም ለአብና ለወልድ ሁልጊዜ ታዛዥ ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ምንም ዓይነት የበታችነትን የሚያመለክት ሳይሆን፥ የአምላክን ዓላማ በመፈጸም አንድነት ውስጥ ሕልውናውን ጠብቆ የተሰጠውን ስፍራ በፈቃደኝነት መውሰዱን የሚያሳይ ነው። ይህ በፈቃደኝነት የተወሰደ የበታችነት ስፍራ የተገለጠውን ሁሉና አገልግሎቱን ለመረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው። ክርስቶስ እስከ ሞት ድረስ እንኳ መታዘዙ ተገቢ እንደነበረ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስ የማይታየው የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ በመናገር አብን ማክበሩ ስለ አምላክና ስለ ሥላሴ የምናውቀውን ተገቢ ያደርገዋል። ክርስቶስ ትሑት ሆኖና እራሱን ዝቅ አድርጎ አዳኝ የሚለውን ክብር እንዳገኘ፥ መንፈስ ቅዱስም ለአብና ለወልድ በፈቃዱ እራሱን በታዛዥነት ማስገዛቱ በመጨረሻ ክብርን የሚያቀዳጀው ይሆናል። ይህም ዘላለማዊውን አምላክ በማክበር መሠረታዊውን የእግዚአብሔር ዓላማ ከግብ የሚያደርስና ከዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ ልቆ የሚታይ ነው።

2. በመፍጠርና ፍጥረትን በመጠበቅ ተግባር ውስጥ ያለው ድርሻ

የፍጥረትን አፈጣጠር የሚገልጠው ታሪክ 'ኤሎሂም' የሚለውን የእግዚአብሔር ስም መጠቀሙ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ ድርሻ እንዳለው እንደሚያሳይ ይገመታል። ይህ አመለካከት ስለ ጉዳዩ በግልጥ በሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመደገፍ ወደፊት በሌላ ርእስ ሥር ይቀርባል። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ ከተገለጠው ነገር ሁሉ ጋር በሚስማማ አኳኋን ይሆናል። በመፍጠር ሥራ ውስጥ ብቻ ሳይሆን፥ ፍጥረትን በመጠበቅ ተግባርም መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳለው አንዳችም ጥርጥር የለም። ፍጥረትን በመጠበቅ ተግባር ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ በዝርዝር ተለይቶ ባይቀርብ እንኳን በዓለም ላይ በአንድ ጊዜ፥ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ መንፈስ ፍጥረትን ጠብቆ ከማቆየት ተግባር ጋር የተያያዘ ግንኙነት እንዳለው መገንዘቡ አይከብድም። ይህ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ሥራዎች መካከል የሚቆጠር ነው።

3. የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለሁለተኛው የሥላሴ አካል

የሥላሴ አካላት በባሕርይ አንድ በመሆናቸው በማንኛውም ሁኔታ ይደጋገፉሉ። ይሁን እንጂ በ'ኪኖሲስ' ['kenosis'] ዘመን መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ጋር ያለውን ግንኙነት በሚመለከት የተለየ ችግር ተከሥቶ ነበር። የሥላሴ አካላት ካላቸው ዘላለማዊ እቅድ እንደ አንዱ ክፍል ሁለተኛው የሥላሴ አካል ወልድ የነበረውን ክብርና ኃይል በፈቃደኝነት ለጊዜውም ቢሆን በተወበት ጊዜ፥ የሚያስፈልገውን አገልግሎት ሲሰጥ የቆየው መንፈስ ቅዱስ ነው። በዚህ እቅድ መሠረት ሦስተኛው የሥላሴ አካል መንፈስ ቅዱስ፥ ሁለተኛውን የሥላሴ አካል ወልድን ከድንግል እንዲወለድ አድርጓል። በውስጡ በማደርም እራሱን ዝቅ አድርጎ አገልግሎቱን እንዲፈጽም የሚያስፈልገውን ችሎታ ሁሉና በሰዎች መካከል ለሚኖረው ኑሮ ኃይልን በመስጠት አገለገለው። ይህን በጣም አስፈላጊ የሆነ ርእስ ወደፊት በተለያዩ አቅጣጫዎች በጥልቀት እንመለከተዋለን።

እነዚህን አገልግሎቶች መንፈስ ቅዱስ ስለመፈጸሙ በተብራራ ሁኔታ ባይገለጥም፥ በተለያዩ ጥቅሶች በተገለጠው ዘላለማዊ እቅድ ላይ በመመሥረት ወደዚህ ውሳኔ ለመድረስ እንችላለን (ሐዋ. 2፡23፤ ሮሜ 8፡29፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡7፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡9፤ ቲቶ. 1፡2)። የመዋጀትና የተመረጡትን የማዳን ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ስለሆነ፥ ሥራውን እንደ እግዚአብሔር እቅድ ይሠራል። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ውስጥ ዋነኛና ተቀዳሚ ናቸው።

4. የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለቅዱሳን

ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ውስጥ ዋና ትኩረት የሚሰጠው፥ አብና ወልድ ለሚኖራቸው ድርሻ ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ መኖሩ ቢታሰብም በሚገባ ሲገለጥ ግን አይታይም። ኤ. ኤ. ሆጅ [A. A. Hodge] እና ቻርልስ ሆጅ የተባሉ ሁለት ጸሐፊዎች፥ ‹‹የመዋጀት ቃል ኪዳን›› በሚል ርእስ ባቀረቡት ሥራቸው፥ በመዋጀት ሥራ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ምን እንደሆነ ሳያብራሩ ቀርተዋል። ደኅንነትን ለሰዎች በመስጠት መለኮታዊ እቅድ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥተኛ ትኩረት በተለይ ለአብና ለወልድ ቢሆንም፥ በክርስቶስ ሞት ዋስትና የተገኘውን የጸጋ ጥቅም ከሕይወት ጋር የሚያዛምደው የመንፈስ ቅዱስ ሥራም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሙሉ እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ካለው ታላቅ ዓላማ ጋር የተያያዘ ቢሆንም፥ የሥራው አንዳንድ ክፍሎች ከሌሎቹ ይልቅ አስፈላጊ ስለሆኑ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል።

የዘላለም ሕይወት። የዘላለምን ሕይወት የመስጠት ሥራ የመዋጀትን እቅድ ሙሉ በሙሉ ለማሳካት በጣም አስፈላጊ ነው። ሦስቱም የሥላሴ አካላት የዘላለምን ሕይወት ከመስጠት ተግባር ጋር ግንኙነት እንዳላቸው መጽሐፍ ቅዱሳችን ያሳየናል። የመጀመሪያው የሥላሴ አካል የአማኞች ሁሉ አባት ሆነ (1ኛ ቆሮ. 8፡6፤ ኤፌ. 4፡6)። የሁለተኛው የሥላሴ አካል ሕይወት የአማኞች ንብረት ሆነ (ዮሐ. 11፡25፤ 14፡6፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡12)። ሦስተኛው የሥላሴ አካል ደግሞ፥ ዳግም ልደትን ይሰጣል (ዮሐ. 3፡5፤ ቲቶ. 3፡5)። ዳግም የመውለድ ዋነኛ ሚና የሦስተኛው የሥላሴ አካል መሆኑን እናያለን። የዘላለምን ሕይወት በመስጠት ተግባር ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነው።

መገለጥ። መለኮታዊ ጥበብን ለሰዎች የመስጠት ተግባር የመንፈስ ቅዱስ ልዩ የሆነ አገልግሎቱ ነው። እራሱን ለሰዎች መግለጥ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ ሲሆን፥ ይህን ዓላማ የማስፈጸም ተግባር ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ነው። እንደ ሌሎቹ አስፈላጊ አገልግሎቶች ሁሉ፥ መገለጥን በመስጠት ሥራ ውስጥ ሌሎቹ የሥላሴ አካላት ሁሉ የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። ለምሳሌ ክርስቶስ በሕይወቱና በአገልግሎቱ አምላክን ገለጠው። ነገር ግን በዘመናት ሁሉ፥ ክርስቶስ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ እንኳን አምላክን በመግለጥ (በማስተዋወቅ) ሥራ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በሕያውነት ይሠራል።

በመገለጥ ሥራ ውስጥ ሦስት ደረጃዎች እንዳሉ የእግዚአብሔር ቃል ያሳየናል። አንደኛው፥ የእግዚአብሔር ፈቃድና

ጥበብን መግለጥ ተቀዳሚ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ወደፊት በሚቀርበው ጥልቅ ውይይት እንደምናየው፥ የመንፈስ ቅዱስ የመግለጥ ሥራ በቃል በተላለፉ ትንቢቶችና እግዚአብሔር ፈቃዱን ለሰዎች በገለጠባቸው የተለያዩ መንገዶች ውስጥ ተገልጧል። ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፍጥረት ያለ መለኮታዊ መገለጥ መረዳት የማይቻል ነገር ነው። እነዚህን የመሰሉ መገለጦች በመጽሐፍ ቅዱሳችን በተለያዩ ስፍራዎች ቢገኙም፥ ከሙሴ በፊት በነበረው ዘመን በሰፊው ይታዩ ነበር። ሁለተኛው ዓይነት መገለጥ፥ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉትን ቃል የሚያሳይ ነው። በዚህ ክፍል የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥ አንዳንድ ጊዜ በመጀመሪያ መገለጥ፥ ግለትም እንደ ትንቢት ባለው፥ ወይም ከሰው ልጆች ታሪክ በፊት በተፈጸመው ነገር ላይ ያተኮረ ቢሆንም፥ የሰውን ልጅ ታሪክ ያለ አንዳች ስሕተት እንዲመዘገብ ባደረገው ምሪት ውስጥ ያለ ነው። ይህ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በእጃችን ባለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚታይ ሲሆን፥ የእውቀቱን ምንጭ፥ የትክክለኛነቱን ዋስትና፥ የመገለጡን ፍጻሜ ሳይንተራስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የመጻፉን እርግጠኛነት ያሳያል። ሦስተኛው መገለጥ የእግዚአብሔርን ቃል እንድንረዳና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ከሕይወታችን ጋር እንድናዛምደው የሚያደርግ ክፍል ነው። የሦስቱ የመገለጥ ደረጃዎች ተግባር፥ የሰው ልጅ አምላካዊውን ጥበብ ከዓላማው ጋር ፍጹም በሚስማማ መጠንና ጥልቀት እንዲያገኝ ማድረግ ነው። የዚህ ክፍል መሠረታዊ ትምህርት ረዘም ያለ ውይይትን የሚጠይቅ ስለሆነ ወደፊት በጥልቀት እንመለከተዋለን። በዚህ ስፍራ መለኮታዊ ጥበብን የመስጠት ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ኃላፊነትና ድርሻ መሆኑን መጥቀስ በቂ ነው።

የመንፈሰ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር። በየትኛውም ስፍረ-ዘመን* [Dispensation/ዲስፐንሴሽን] መንፈስ ቅዱስ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ መሆኑ ግልጥ ቢሆንም፥ በቤተ ክርስቲያን ዘመንም ሆነ በሺሁ ዓመት መንግሥት፥ በቅዱሳን ውስጥ ማደሩ ከአገልግሎት ድርሻዎቹ አንዱ ነው። የመንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ ማደር ግልጥ የሆነ መለኮታዊ ጸጋንና የብዙ መንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ክንውን ማረጋገጫ ነው። በዚህ ዘመን አብና ወልድ በአማኙ ውስጥ እንደሚያድሩ ቢነገርም፥ አመዛኙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ ያለውን ሰፊ አገልግሎት በአስረጂነት በማቅረብ ጠቅላላ ሳይሆን፥ አብዛኛው ግንኙነት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መሆኑን ያሳያል። እርሱ ወኪላቸው ነው።

* በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ተጨማሪ መግለጫ ይመልከቱ።

ስለዚህ እርሱ በአገልግሎቱ የአብና የወልድን ዓላማ ይፈጽማል። ይህ እውነት ከመንፈስ ቅዱስ ባሕርይና እርሱ ከሌሎቹ የሥላሴ አካላት ጋር ካለው ግንኙነት ጋር ፍጹም የሚስማማ ነው።

ማንኛውንም መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ ነው። በተለያዩ ስፍረ-ዘመናት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ችሎታን መስጠት እንደሆነ እንመለከታለን። የሰው ልጅ በውድቀት ምክንያት አምላክን ሊያገለግለውም ሆነ ደስ ሊያሰኘው አይችልም። በዘመናት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለተለያዩ የአገልግሎት ተግባራት ኃይልንና ጥበብን መስጠት ነው። በብሉይ ኪዳን ይህ ተግባር በተለይ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር የተያያዘው በእግዚአብሔር ምርጫ ለተወሰኑ አማኞች የሚደረግ ሆኖ እንጂ፥ ሁሉን በሚያቅፍ ሁኔታ አልነበረም። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ዘመንም ሆነ በሺሁ ዓመት ዘመን [Millenium/ሚሌኒየም]፥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለአማኞች ሁሉ የተሰጠ ነው። የግነልገል ብቃትና ደረጃዎች በተለያዩ ስፍረ-ዘመናት ታይተዋል። በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር በእቅዱ ውስጥ ለሰዎች ያለውን ሥራ ማስተዋል ይቻላል።

ቅድሰና። አምላክ ለሰው ልጆች ያለው እጅግ በጣም አስፈላጊ እቅድ ፍጹም ቅዱስ እንዲሆኑ መሻቱ ነው። በእግዚአብሔር ቃል እንደምናገኘው (ሮሜ 15፡16፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13) የመንፈስ ቅዱስ ዋና ሥራ አማኞችን መቀደስ ነው። ሦስቱም የሥላሴ አካላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የመቀደስ ተግባራት በሚመለከት የተያያዙና አብረው የሚሠሩ ቢሆኑም፥ በተለይ በመቀደስ ሥራ ሂደትና አፈጻጸም ተግባር ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ዋና አከናዋኝ ነው። በአማኙ ሕይወት ውስጥ ያለ የትኛውም አገልግሎት ይብዛም ይነስ ከአማኙ መቀደስ ጋር ይያያዛል።

መማለድ። የመንፈስ ቅዱስ የመማለድ ተግባር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድ ቦታ ብቻ ተጠቅሷል (ሮሜ 8፡26)። አንድ ጊዜ ብቻ መጠቀሱ አስፈላጊነቱ ዝቅተኛ መሆኑን አያሳይም፥ ምክንያቱም የዚህ አገልግሎት አስፈላጊነት ግልጥ ነውና። መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚጸለይ ለአማኙ ማስተማር ብቻ ሳይሆን፥ እርሱ ራሱ በእግዚአብሔር ፊት ስለ አማኙ ይማልዳል። ክርስቶስ በሰማይ ሆኖ ለአማኞች እንደሚማልድ፥ መንፈስ ቅዱስ በምድር ሆኖ ይማልድልናል። የሁለቱም ምልጃ ውጤታማ ስለሆነ በምድር ላይ ያለውን የአንዱን አገልግሎት ሌላው ያጸናዋል።

የቤተ ክርስቲያን መመሥረት። በጸጋ ስፍረ-ዘመን ላይ የተወሰነው ይህ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት እግዚአብሔር አምላክ አማኞችን ከራሱ ጋር የማስታረቅ ሁሉን ቻይነት ዓላማውን ከገለጠባቸው ታላላቅ መንገዶች አንዱ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቤተ ክርስቲያን በዘላለማዊ ሕይወት አንድ እንደሆነች፥ ይህም አንድነት ሊከፋፈል ከማይችለው ከሥላሴ አካላት አንድነት ጋር ያለውን ቅርበት ያሳየናል (ዮሐ. 17፡21)።

በስፍረ-ዘመናት የታየውን ልዩነትና ተነጻጻሪነት ባለመዘንጋት፥ የመንፈስ ቅዱስ ዋና ተግባር የሆኑትን እነዚህን ትምህርቶች አጥብቆ መያዝ በፊታችን ያለ ተግባራችን ነው። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት ሁሉ በሥላሴ አካላት የሥራ ድርሻ ውስጥ ያሉ ናቸው። የእነዚህ አገልግሎቶች ጊዜያቸውን ጠብቆ መፈጸም፥ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ፥ በርሱ በብርታትና በኃይል እየተፈጸመ ለመሆኑ ማስረጃ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በዝርዝር በምንመለከትባቸው በሚቀጥሉት ምዕራፎች እያንዳንዱ ሥራ ለአጠቃላዩ የእግዚአብሔር ዓላማ አስፈላጊ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ይሆናል። ማለትም የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት፥ የአብና የወልድን ሥራ ያህል በቦታው አስፈላጊ ነው። አንዱ ያለ ሌላው ሙሉ ሊሆን አይችልም። አብዛኛው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የታቀደው በኃጢአት ወደ ዓለም መግባት ሳቢያ በአምላክ የመዋጀት ተግባር ቢሆንም፥ አገልግሎቱ ለአስቸኳይ ወይም ለድንገተኛ ጊዜ ብቻ እንደሆነ አድርጎ የመቁጠር ስሜት መወገድ አለበት። ከዘላለም ጀምሮ የታየ እንደሆነ፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የክርስቶስ ሥራ መለያ የሆኑትን፥ ጽድቅን፥ ፍቅርን፥ ሁሉን ቻይነትን፥ ሁሉን አዋቂነትንና ጸጋን የሚገልጥ መሆኑን፥ በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል።

ከአሳታሚው መግለጫ

ምንም እንኳን የስፍረ-ዘመንን መሠረታዊ ፅንሰ-አሳብ በአጭሩ ማመልከት የሚቻል ቢሆንም፥ ካዘለው መሠረታዊ አሳብ የተነሣ በጉዳዩ ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ መስጠቱ እጅግ አስፈላጊ ነው።

"ስፍረ-ዘመን" የሚለው ቃል "ዲስፐንሴሽን" [Dispensation] የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚገልጥ ነው። "ዲስፐንሴሽን" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል 'አይኮኖማይን' የሚለውን የግሪክ ቃል ትርጉም ይዟል። የግሪኩ ቃል "ማስተዳደር" ወይም "መጋቢነት/አገልግሎት" የሚል ትርጉም አለው። ይህ ቃል አዲስ ኪዳን ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል። በወንጌላት ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሁለት ጊዜ ይህን ቃል (ሉቃስ 12 እና 16) በአንድ ጌታና ባሪያ መካከል ያለውን ግንኙነትና ኃላፊነት

በተመለከተ ተጠቅሞበታል። ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ በ1ኛ ቆሮንቶስ 4፡12 ውስጥ ለእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋዮች እንድንሆን እንደሚፈልግብን ለማሳሰብ ተጠቅሞበታል። በቲቶ 1፡7-8 ላይም ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ኃላፊነት ለማሳየት ተጠቅሞበታል።

ከሥነ-መለኮታዊ ትምህርት አኳያ ስንመለከተው፥ ለምሳሌ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቃሉ የሚያመለክተው፦ ‘‘በተለያዩ ዘመናት ውስጥ በእግዚአብሔርና በሰዎች ወይም ጎሳዎች መካከል ያለውን የጸና ግንኙነት፥ እንዲሁም የሚከተሉትን የሰዎች ግዴታዎች ጭምር የሚያሳይ ነው።’’ ዳንኤል ፉለር (Daniel Fuller) የተባለ አንድ የሥነ-መለኮት ሊቅ እንዲህ በማለት አቅርቦታል፦ ‘‘እግዚአብሔር በተለየ መንገድ ከሰው ጋር የሚሠራበት ዘመን።’’ ዶር. ኤች. ኤ. አይረንሳይድ (Dr. H. A. Ironside) የተባለ ሌላ የሥነ-መለኮት ሊቅ ‘‘ለየት ያሉ የሕይወት መመሪያዎች ወይም ሥርዓቶች በአንድ ዘመን የሚያስፈልጉ፥ በሌላ ዘመን ግን የማይታዩ’’ ሲል፥ ዶር. ሲ. አይ. ስኮፊልድ [Dr. C. I. Scofield] በመባል የሚታወቅ ምሁር ደግሞ ‘‘ልዩ የሆኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ መገለጦችን የሚያሳዩ የሙከራ ዘመኖች’’ በማለት ገልጦታል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሦስት ስፍረ-ዘመናት የሚያሳይ አሳብ እናገኛለን። ጳውሎስ የተሰጠው መጋቢነት ለየት ያለ መሆንን በቈላስይስ 1፡25-26 ሲያመለክት ‘‘ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ’’ በማለት ስለ ቀድሞ ዘመን ይናገራል (ይህም የሕግ ስፍረ-ዘመን ተብሎ የሚታወቀው ነው)። በኤፌሶን 3፡2 ደግሞ ለኤፌሶን ሰዎች ‘‘ለእናንተ ስለተሰጠኝ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት’’ ይላል። ይህም ያለንበትን የጸጋ ዘመን የሚያመለክት ነው። በሦስተኛ ደረጃ ያለውን አሳብ ማየት የምንችለው በኤፌሶን 1፡10 ጳውሎስ ‘‘በዘመን ፍጻሜ’’ በማለት የሚያቀርበው፥ ሊመጣ ያለውን ዘመን (የሺህ ዓመት መንግሥት) ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና የሚከተሉትን የዘመናት ክፍፍሎች ማየት እንችላለን፦ 1ኛ. የኤደን ገነት ዘመን (ቅንና ንጹሕ)፥ 2ኛ. ከአዳም ውድቀት እስከ ኖኅ ዘመን (የሕሊና ዘመን)፥ 3ኛ. ከውኃ ጥፋት በኋላ (የሰው አስተዳደር)፥ 4ኛ. ልዩና የግለሰብ ግንኙነት በአብርሃምና በቤተሰቡ የተገለጠበት ዘመን (የቃል ኪዳን ዘመን)፥ 5ኛ. የሙሴ ዘመን (የሕግ ዘመን)፥ 6ኛ. የጸጋ ዘመን (የአሁኑ የቤተ ክርስቲያን ዘመን) እና 7ኛ. የሺህ ዓመት መንግሥት ዘመን።

መጽሐፍ ቅዱስ በአብዛኛው የሚያተኩረው በሕግ፥ በጸጋ እና በሺሁ ዓመት መንግሥት ዘመን ላይ ነው። በእነዚህ ሦስት ዘመናት ላይ ያለውን ግልጥ ግንኙነት መገንዘብ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ላይ ያለውን ዓላማ በደንብ ለመረዳት እጅግ ጠቃሚ ነው።

5

መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ

ስለ መፍጠር በብሉይ ኪዳን በተሰጠው መገለጥ ውስጥ፥ መፍጠር የአምላክ ሥራ እንደሆነ በሥላሴ አካላት መካከል ልዩነት ሳይደረግ በተደጋጋሚ ተገልጧል። ቢሆንም በዋና ዋና የአምላክ ሥራዎች ውስጥ ለእንዱ የሥላሴ አካል ቅድሚያና የበለጠ ትኩረት ሲሰጥ፥ ለእያንዳንዱ የሥላሴ አካል የተወሰነ ክፍል መስጠት ግን የተለመደ ነው። ከዚህ አንጻር ስለ መፍጠር ሥራ የሚናገሩት አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች፥ በሥላሴ አካላት መካከል ልዩነት ሳያደርጉ የፍጥረታት ፈጣሪ አምላክ መሆኑን ሲናገሩ፥ ቅድሚያ ወይም ትኩረት ለእንዱ አካል የሚሰጡ ክፍሎች ደግሞ እግዚአብሔር አብን ያስቀድማሉ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ የመፍጠር ሥራ ብዙ ጊዜ የክርስቶስ መሆኑ ተገልጧል (ዮሐ. 1፡3፤ ቈላ. 1፡16-17)። በፍጥረት ሥራ መንፈስ ቅዱስ ግልጥ የሆነ ግንኙነት እንዳለው በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠ ሲሆን፥ እንዲያውም መፍጠር ከመንፈስ ቅዱስ ታላላቅ ኃላፊነቶች አንዱ እንደሆነ በአጥጋቢ ሁኔታ ተዘርዝሯል።

ወደ ሁለት ተቃራኒ አቅጣጫዎች ርቆ በመሄድ የሚሰጥ ትርጉም መወገድ አለበት። አንዳንዶች፥ አንዱ የሥላሴ አካል በአንድ የተወሰነ ሥራ ላይ ያለውን ሚና ለመግለጥ በሚያደርጉት ሙከራ፥ የቀሩት የሥላሴ አካላት በዚያ ሥራ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ በማሳነስና በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሌለ ልዩነት በመፍጠር ስሕተት ይሠራሉ። ለምሳሌ አንድ ሰው (በዮሐንስ 1፡3 እና ቈላ. 1፡16-17) የተጻፈውን ቃል ብቻ በመውሰድ በሌሎች ክፍሎች ውስጥ የተገለጡትን የሥላሴ አካላት ድርሻ ወደ ጎን ቢተው፥ የመፍጠር ሥራ ሁሉ በወልድ ተፈጽሟል ከሚል የተሳሳተ ውሳኔ ላይ ይደርሳል። ይህ ውሳኔ ሌሎቹ የሥላሴ አካላት በመፍጠር ሥራ ውስጥ ተሳታፊ መሆናቸውን በግልጥ ከሚያስረዱ ክፍሎች አሳብ ጋር ይጋጫል። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ የመፍጠር ሥራ በሚቀርብበት ጊዜ፥ የአብንና የወልድን የመፍጠር ሥራ ለማሳነስ ወይም ለማጥፋት የሆነ ተደርጎ መተርጎም የለበትም። ሌላው የስሕተት አቅጣጫ ደግሞ፥ በመፍጠር ሥራ ውስጥ የሥላሴ አካላት ያላቸውን የተለያየ ድርሻ ወደ ጎን ትቶ፥ አብ ፈጣሪ ሲሆን ወልድና መንፈስ ቅዱስ ግን ሥራውን የሚያስፈጽሙ ወኪሎች ናቸው ወደሚል አቋም መድረስ ነው። ይህም አቋም የመጽሐፍ ቅዱስን

አሳብ ይጥሳል። የሥላሴ አካላት በመፍጠር ሥራ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ጥርት ባለ መንገድ መለየት የማይቻል ቢሆንም፥ የመፍጠር ሥራ የሁሉም የሥላሴ አካላት እንደሆነ መቀበልና ስለ አፈጣጠር ተግባራቸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን ልዩነት ብቻ ማመልከት ለቅዱስ ቃሉ መገዛት ነው።

1. የመንፈስ ቅዱስ የመፍጠር ሥራ ማረጋገጫዎች

የተለዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚሰጡት ማረጋገጫ። የመንፈስ ቅዱስን የመፍጠር ሥራ መሠረታዊ ትምህርት ቢያንስ በሦስት መንገዶች ማረጋገጥ ይቻላል። የመጀመሪያውና ዋናው ማረጋገጫ፥ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ ድርሻ እንዳለው በግልጥ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መኖራቸው ነው (ዘፍጥ. 1፡2፤ መዝ. 33፡6፤ 104፡29-30፤ ኢዮብ 26፡13፤ 33፡4፤ ኢሳ. 40፡13)። መንፈስ ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል ‘ሩአክ’ የሚለው ሲሆን፥ ምናልባት እስትንፋስ ወይም ነፋስ ከሚለው ቃል የመጣ ሳይሆን አይቀርም። ይህም ሕይወትን፥ ኃይልንና ቁሳዊ ያልሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ የሚያሳይ ነው። ቃሉ ለሌሎች ጉዳዮችም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሷል። እነዚህን የተለያዩ ጥቅሶች መመርመር አስደናቂ የሆኑ መሠረታዊ እውነቶችን ይገልጣል።

ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው የመጀመሪያ ጥቅስ የሚገኘው፥ ምድር አንዳች ነገር ያልነበረባት ባዶ እንደነበረችና ጨለማም በጥልቁ ላይ እንደነበር በተገለጠበት ክፍል ነው (ዘፍጥ. 1፡2)። ስለ እግዚአብሔር መንፈስ የተነገረው ቃል ‘‘የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር’’ ይላል። ጃን አዌን [John Owen] የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ ስለ መንፈስ ቅዱስ በጻፈው ዋና ሥራው ውስጥ፥ ይህ መገለጥ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ ለነበረው ድርሻ ግልጥ መሆኑን አመልክቷል። በመቀጠልም የሚከተለውን ብሏል፦

> ‘‘‘መስፈፍ’ የሚለው ቃል፥ አንዲት ርግብ በጎጆዋ ውስጥ ለጣለችው እንቁላል ሙቀትን ለመስጠት ወይም የተፈለፈሉ ጫጩቶችዋን ለመመገብ ከምታደርገው ዝግ ያለ እንቅስቃሴ ጋር የሚመሳሰል ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ፥ ሁሉም ነገር እንደ ሙት ባሕር ነበር። ምድር አንዳችም ነገር ያልነበረባት ባዶ ነበረች። ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ በጥልቁ ላይ መስፈፍ፥ ለዚህ ሙት ለሆነና ሥርዓት ላጣ ነገር ብርታትን አመጣለት። ልንገምተው ከምንችለው በላይ የተለያየ ዓይነትና ቅርፅ ይዘው የነበሩ ነገሮች በዚህ ምክንያት ያማሩ ሆኑ።’’’

ይህን የመጀመሪያ መገለጥ የሚያረጋግጠው መዝሙር 33፡6 ነው፡- ‘‘በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ።’’ በመዝሙር 33፡6፥ ‘‘እስትንፋስ’’ የሚለው ቃል በዘፍጥረት 1፡2 ‘‘መንፈስ’’ ከሚለው ቃል ጋር አንድ ነው። ‘‘የእግዚአብሔር መንፈስ’’ የሚለው ቃል ለሦስተኛው የሥላሴ አካል ትክክለኛ መለያው ሲሆን፥ ‘‘እስትንፋስ’’ የሚለው ቃል ግን፥ ‘‘ከአፉ’’ የሚለውን በመጨመርና ከተለመደው የቃሉ ትርጉም ሰፋ በማድረግ ምንነቱን የሚገልጥ የአነጋገር ዘይቤ ሆኖ መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ነው። ይህ ክፍል የሰማይ ሠራዊት በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መፈጠራቸውን ይገልጥልናል።

መዝሙር 104፡30፥ ተመሳሳይ ምስክርነት ይሰጣል፡- ‘‘መንፈስህን ትልካለህ፥ ይፈጠራሉም፤ የምድርንም ፊት ታድሳለህ።’’ ምንባቡ በአጠቃላይ ስናየው ስለ መጀመሪያው የፍጥረት ሥራ የሚናገር ባይመስልም፥ ‘‘ይፈጠራሉም’’ የሚለው ቃል ግን ስለ መጀመሪያው የፍጥረት ሥራ የሚያስረዳ ያስመስለዋል። ሌሎች ክፍሎች ከሚያስተምሩት መሠረታዊ ትምህርት ጋር ስናነጻጽረው፥ የተላከው መንፈስ በፍጥረት ሥራ ውስጥ ተጠምዶ እንደነበር ይህ ክፍል ያስረዳናል። መፍጠር ብቻ ሳይሆን፥ ፍጥረታት ወቅትን እየተከተሉ እንዲታደሱ ማድረግም በኃላፊነት ክልሉ ያለ ተግባር ነው።

በኢሳይያስ 40፡12-14፥ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ እንደሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቁሞ እናያለን፡-

> ‘‘ውሆችን በእፍኙ የሰፈረ፥ ሰማይንም በስንዝር የለካ፥ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ፥ ተራሮችን በሚዛን ኮረብቶችንም በሚዛኖች የመዘነ ማን ነው? የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ፥ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? ወይስ ማን መከረው? የፍርድንስ መንገድ ማን አስተማረው? እውቀትንስ ማን አስተማረው? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?’’

በዚህ ክፍል መንፈስ ቅዱስ ማንም ሊያስተምረው ሆነ ሊያማክረው ያልተገባ፥ ሁሉን የሚችል ፈጣሪ ሆኖ እናየዋለን። እርሱ ያለ አንዳች አማካሪና አስተማሪ ውሆችን በእፍኙ ሰፍሯል፤ ሰማይን በስንዝር ለክቷል፤ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ ይዟል፤ ተራሮችንና ኮረብቶችንም በሚዛን መዝኗል። በዚህ ሕዋን በማቀድና በማደራጀት ተግባር ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ድርሻ እንደነበረው በግልጥ እናያለን።

ኢዮብ ብዙ ምንባቦች ውስጥ ምስክርነቱን ሰጥቷል። በኢዮብ 26፡13፦ ‘‘በመንፈሱ ሰማያት ውበትን አገኙ፤ እጁም በራሪይቱን እባብ ወጋች’’ ይላል። መጽሐፍ ቅዱስን ቃል በቃል በመተርጎም የሚያስተምሩ [Conservatives] የጥቅሱ የመጀመሪያ ክፍል መንፈስ ቅዱስ ሰማያትን ውብ አድርጎ ስለ መፍጠሩ የሚናገር መገለጥ ነው ይላሉ። ያንግ [Young] የተባለው ጸሐፊ፦ ‘‘እግዚአብሔር ሰማያትን ውብ ያደረገው በመንፈሱ ነው’’ ብሏል። በዚህ ምስክርነቱ ኢዮብ ሰማያትን ያስዋበና ያስጌጠ፥ ከዋክብት ለሰማይ ውበት እንዲሰጡና ሥርዓት እንዲይዙ ያደረገ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ያሳየናል።

በኢዮብ 33፡4 ደግሞ፥ ‘‘የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፥ ሁሉን የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ’’ በማለት ኤሊሁ ይመሰክራል። ይህን ቃል በዘፍጥረት ከተመዘገበው ታሪክ ጋር ስናወዳድረው፥ የኤሊሁን ምስክርነት ትክክለኛነት እናረጋግጣለን። ስለ መንፈስ ቅዱስ በግልጥ ከተገለጡት ቃሎች ጋር ሲወዳደርና አብሮ ሲታይ፥ ይህን መሠረታዊ ትምህርት፥ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚመረምሩትና እንደሚቀበሉት፥ ጠብቀውም እንደሚያቆዩትና ለመንፈሳዊ አእምሮ በቂ ማረጋገጫ እንደሚሰጡ መመልከት እንችላለን።

‘ኤሎሂም’ የሚለው ስም አጠቃቀም። መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ መካፈሉን የምናረጋግጥበት ሁለተኛ ማስረጃ ደግሞ፥ በመፍጠር ሥራ ውስጥ ለፈጣሪ በተሰጠውና ብዙ ቁጥር በሆነው ‘ኤሎሂም’ በሚለው ስም ነው። ‘ኤሎሂም’ የሚለው ቃል ልክ ለአሕዛብ አማልክት እንደሚሰጠው ዓይነት ብዙ ቁጥር መሆኑ የማያሻማ ነው። አንዳንዶች ግን ብዙ ቁጥር ታላቅነትን ለማስረዳት (ማለትም መጠኑንና ታላቅነቱን ለማሳየት ብዙ ውኃ ማለት ሲገባን ብዙ ‘‘ውኖች’’ እንደምንለው ዓይነት) እንጂ የሥላሴ ማረጋገጫ አድርገን ልንጠቀምበት ጨርሶ አንችልም በማለት ይህን አሳብ ይቃወማሉ። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳንም ጭምር እጅግ በርካታ ማስረጃዎች ካሉት የሥላሴ ትምህርት አንጻር ስናየው፥ ይህ ብዙ ቁጥር ለተጠቀሰበት የእግዚአብሔር ስም እንደሚሆንና፥ በእግዚአብሔር ውስጥ ከአንድ በላይ የሆነ አካል እንዳለ የሚጠቁም ስለመሆኑ ልንስማማ እንችላለን። ይህ የብዙ ቁጥር አጠቃቀም ትክክለኛ ላለመሆኑ የምናቀርበው አንዳችም ማስረጃ የለም። አሳቡን በመቃወም የሚከራከሩት፥ የሥላሴን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የማይቀበሉ [Unitarian/ዩኒተሪያን]፥ አይሁዳውያንና የሥነ-መለኮትን ትምህርት ከዓለም እውቀት ጋር የሚቀላቅሉ (‘‘ሊበራል’’) ናቸው። በፍጥረት ታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ ጎላ ብሎ የተጠቀሰው ብዙ ቁጥር፥ የመንፈስ ቅዱስን በመፍጠር ሥራ መሳተፍ በከፍተኛ ማስረጃ የሚያረጋግጥ ነው።

'ኤሎሂም' የሚለውን ቃል የሚመለከተው እያንዳንዱ አጠቃቀም፥ ስለ ሦስቱም አካላት እንጂ ስለ አንዱ አካል ሥራ ብቻ የሚናገር አይደለም። ስለዚህ እግዚአብሔር ፍጥረታትን እንደፈጠረ በሚናገረው በዘፍጥረት 1፡1 ስለ አንድ አካል ብቻ ሳይሆን፥ በሦስት አካል ስለተገለጠ ሥሉስ አምላክ ነው። በዚህ ስም የተጠቀሰ የእግዚአብሔር ሥራ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትም እንደሆነ መመልከት እንችላለን። ስለ መንፈስ ቅዱስ የመፍጠር ሥራ የተለየና ግልጥ የሆነ ሌላ ጥቅስ ባይኖር እንኳን፥ በዚህ ለእግዚአብሔር የተሰጠ የብዙ ቁጥር ስም ብቻ ትምህርቱን ለማረጋገጥ ይቻላል።

በፍጥረታት መካከል መሆኑን የሚመለከት አሳብ። መንፈስ ቅዱስ ከፍጥረታቱ ጋር አብሮ የመሆኑን አሳብ በማረጋገጫነት በግልጥ ከሚናገሩ ጥቅሶችና የእግዚአብሔርን ስም በብዙ ቁጥር ከሚጠቅሰው የሰም አጠቃቀም ሌላ፥ በመፍጠር ሥራ ውስጥ ተካፋይ እንደነበር የሚያስረዳ ሦስተኛ አሳብ የሚከተለው ነው። በመፍጠር ሥራ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ተካፋይ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። አብሮ ነበርና የክርስቶስ በምድር ላይ በሥጋ መገኘት ለሰው ልጆች ሲባል የተሠራ እንደሆነ ሁሉ፥ የመንፈስ ቅዱስም በፍጥረት ሥራ ውስጥ መገኘት ለታላቅ ተግባር መሆኑ ግልጥ ነው። መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ሥራ ውስጥ ስለነበረው ተሳትፎ በዘፍጥረት 1፡2 በግልጥ ተጠቅሷል።

እግዚአብሔር ከፍጥረታቱ የተሻለና ውሱን ከሆኑ ቁሳዊ ነገሮች እጅግ የላቀ ነው። ሥነ-ሥርዓትን ይዞ ከሚጓዘው ፍጥረተ ዓለም [Cosmological/ካዝሞላጂካል] አሳብ እጅግ የላቀ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። በፍጥረታቱ ውስጥ፥ ወይም መካከል መሆኑ ደግሞ ለመፍጠር ብቻ ሳይሆን፥ ፍጥረታትን ጠብቆ ለማቆየትና የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለማድረግ ነው። ''ዲይስቶች'' [Deists] እግዚአብሔር ከፍጥረታት እጅግ የላቀ ስለሆነ በነሱ መካከል ሊገኝ አይችልም የሚለውን አቋም ያዙ። ''ፓንቲይስቶች'' [Pantheists] ደግሞ እርሱ በፍጥረታቱ ውስጥ ያለ ብቻ ነው፥ በማለት ከፍጥረታት እጅግ የላቀ መሆኑን ከመቀበል ወደ ኋላ ይላሉ። አመለካከታቸው የተሟላ አይደለም እንጂ፥ ሁለቱም እግዚአብሔር ከፍጥረት ጋር ያለውን ግንኙነት ያምናሉ። ሆኖም ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ፥ አንዱን ከሌላው በማመዛዘን ብናያቸው በቂና የተሟሉ እንዳልሆኑ እንረዳለን።

እግዚአብሔር በፍጥረታት መካከል የመሆኑ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው። ትምህርቱ በአጠቃላይ ተቀባይነት አግኝቷል። ይህን አሳብ ከሥላሴ ጋር ወዳለው ግንኙነት ብናመጣው ለየትኛውም አካል መዛመድ እንደሚችል እንገነዘባለን። ስለዚህ

አምላክ ከፍጥረታቱ ጋር፥ ወይም በፍጥረታቱ ውስጥ የመኖሩ መሠረታዊ ትምህርት፥ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ ድርሻ እንደነበረው ያመለክተናል። በመፍጠር ታሪክ ውስጥ "የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ እንደነበር (ዘፍጥ. 1፡2) የሚናገረው ቃል ለዚህ ጉዳይ በአስረጅነት ቀርቧል። ይህ የማስረጃ አሳብ በራሱ ብቻ በቂ ባይሆንም፥ ሌሎች የማስረጃ አሳቦችን ለማጠናከር ግን በጣም ይጠቅማል። በእነዚህ ምስት የተለያዩ ማስረጃዎች፥ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ በፈጣሪነት የመካፈሉን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት እናነለብታለን። ሌሎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መመርመር ደግሞ የመፍጠር ሥራውን ባሕርያት ይገልጡልናል።

2. የመንፈስ ቅዱስ የመፍጠር ተግባር

የእግዚአብሔር የአፈጣጠር ተግባር በአዲስ ኪዳን እንደተገለጡት ሌሎች ሥራዎቹ፥ በሥላሴ አካላት መካከል ግልጥ ልዩነት ፈጥሮ የሚያቀርብ አይደለም። ነገር ግን በጉዳዩ ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት ማድረግ በመፍጠር ሥራ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያለውን ድርሻ ለማመልከት የሚረዳን ይሆናል። በዚህ መልክ የታወቁ አራት የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎችን ቀጥለን እንመለከታለን።

ፍጥረትን ሥርዓት የማስያዝ ተግባር። በዘፍጥረት 1፡2 መንፈስ ቅዱስ በጥልቁ ላይ ሰፍፎ እንደነበር የሚያመለክት ቃል እናገኛለን። ይህም ጥልቅ በጥቅሱ መጀመሪያ ክፍል ከተጠቀሰውና ሥርዓት ካጣው የምድር ባዶነት ጋር የሚደመር ነገር ነው። ስለ ፍጥረት ቀጥሎ በተሰጠው መገለጥ ሥርዓት ያጣ የምድር ባዶነት በሥርዓት ወደተገነባ ትክክለኛ ዓለም ተቀይሮ እናገኛለን። መዝሙር 33፡6 የሰማይ ሠራዊት በመንፈስ ቅዱስ መፈጠራቸውን በመናገር ይህን ነገር ያረጋግጠዋል። ከዚህ ጥቅስ በርካታ ነገሮችን ማውጣት ቢቻልም፥ አንድ እውነት ግን የማይታለፍ ነው። ይኸውም ከማንኛውም ፍጥረቱ ይልቅ ሰማያት የእግዚአብሔርን ሥርዓት ወይም ጥበብ ይገልጣሉ። የእንቅስቃሴ ሥርዓት፥ የአደረጃጀትና የቁጥር ፍጹምነት ሁሉ በሰማያት ይገኛሉ።

ፍጥረታትን የመቅረጽ ተግባር። የኢዮብ አባባል ለዚህ አሳብ መልካም ምስክርነትን ይሰጣል። "በመንፈሱ ሰማያት ውበትን አገኙ፥ እጁም በራሪይቱን እባብ ወጋች።" በራሪይቱ እባብ የምትለው ቃል ኦፌን እንዳለው የከዋክብት ክምችት የሚገኝበትን ስፍራ (Milky Way/ ሚልኪዌይ) የሚያመለክት ከሆነ፥ ሰማያት የተሠሩበት ቅርፅና ውብ አሠራር በመንፈስ ቅዱስ የተከናወነ መሆኑን መረዳት አስቸጋሪ አይደለም።

ደግሞም ከሰማያት አሠራርና ከተሠሩበት ዕቅድ አንጻር በሥላሴ አካላት መካከል መጠነኛ ልዩነት ለማየት ይቻላል። የመጀመሪያው የሥላሴ አካል የእቅዱ አውጭ፥ ሁለተኛው የሥላሴ አካል እቅዱ ወደ ፍጻሜ እንዲመጣ የቀሩት ነገሮችን አድራጊ፥ ሦስተኛው የሥላሴ አካል ደግሞ ሥራውን ፈጻሚና እግዚአብሔር ወደሚያስበው ማጠቃለያ የሚያመጣ ነው ለማለት እንችላለን። ይህን አሳብ የሥላሴ አካላት በደኅንነት ሥራ ውስጥ ባላቸው ድርሻ ለማብራራት ይቻላል። የደኅንነትን ሥራ አብ ፈቀደ፤ ወልድ በሞቱ የአብን ፍቃድ ፈጸመ፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በተመረጡት ሰዎች ሕይወት ውስጥ ደኅንነት እንዲፈጸም አደረገ። በፍጥረት ሥራ ውስጥም መንፈስ ቅዱስ ሰማያትን በእቅዱ መሠረት አስውቦ እንደሠራቸው ተገልጧል። የፍጥረታት ሁሉ ውበት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተያያዘ መሆኑንና የሥላሴ አካላት ሳይሳተፉበት የሚፈጸም የእግዚአብሔር ሥራ እንደሌለ መዘንጋት አያሻም።

ለፍጥረታት ሕይወትን የመስጠት ተግባር። ስለዚህ ሥራ ኤሊሁ ግልጥ የሆነ ምስክርነት ይሰጣል፥ ‘‘የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፥ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ’’ (ኢዮብ 33፡4)። የፍጥረት አፈጣጠር ታሪክም ይህንኑ እውነት ይመሰክርልናል። ‘‘እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፥ በአፍንጫውም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፥ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ’’ (ዘፍጥ. 2፡7)። አዌን ስለ ሰው ልጅ አፈጣጠር ሲጽፍ፥ ‘‘ይህ ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው’’ ይላል። የእግዚአብሔር መንፈስ፥ እንዲሁም የእግዚአብሔር እስትንፋስ አንድ ናቸው። በዮሐንስ 1፡4 እንደተገለጠውም ሁለተኛው የሥላሴ አካል ሕይወትን ከመስጠት ጋር ግንኙነት እንዳለው እናያለን፦ ‘‘በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።’’ መንፈስ ቅዱስ ከሕይወት ጋር ያለው ግንኙነት ሕይወትን ሰጭ በመባል ተገልጧል። እንደገና በመፍጠር ሥራ ውስጥም ይህንኑ እንመለከታለን። በልጁ ውስጥ የነበረው ሕይወት የመስጠት ሥራ፥ በመፍጠር ወይም በማደስ ውስጥ ያለ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ምናልባትም ሕይወትን ለፍጥረታት ሁሉ፥ በተለይም ለሰው ልጆች የሰጠ መንፈስ ቅዱስ ነው።

ከሰው ልጆች ሕይወት አንጻር ሲታይ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ለሕይወት የተለየ ዋጋና ጥራትን ይሰጣል። ‘‘እግዚአብሔርም አለ፥ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር’’ (ዘፍጥ. 1፡26)። ሌሎች ነገሮች ከተፈጠሩበት በተለየ መንገድ የሰው ልጅ ሲፈጠር ሕይወትን የሰጠ መንፈስ ቅዱስ ነው። አዌን ስለዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ብሏል፦

"በዚህ በተበጀ የምድር አፈር ውስጥ እግዚአብሔር የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት። ይኸውም እጅግ አስፈላጊና ሕያው የሆነ መንፈስ ከራሱ የሆነ፥ የራሱ የሆነ፥ ከዚያ በፊት አስቀድሞ ያልተፈጠረ ነገር ነው። በዚህም ምክንያት ሰው ከመላእክት ያነሰና፥ ከሌሎች እንስሳት በላይ የሆነ መካከለኛ ፍጥረት ሆነ። አካሉ እንደሌሎች እንስሳት ከቁሳዊ ነገር የተሠራ ሲሆን ነፍሱ ግን እንደ መላእክት የእግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይል ውጤት ነው" (ዘፍጥ. 2፡7)።

በሥላሴ አካላት መካከል ልዩነት ሳያደርግ ሕይወትን የሚሰጥ እግዚአብሔር መሆኑን ቢገልጥም፥ የሰው ልጅ ሲፈጠር ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር የተለየ ግንኙነት ያለው መምሰሉ ግን ግልጥ ነው።

ፍጥረታት የተፈጠሩት ለእግዚአብሔር ክብር ነው። ስለ መፍጠር ሥራ ሊጠቀስ የሚገባው አራተኛ ነገር፥ ፍጥረታት የተፈጠሩበት ዓላማ ለእግዚአብሔር ክብር መሆኑ ነው። ይህም በመዝሙር 33፡6፥ "በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ" በሚለው ቃል ተገልጧል። ለፍጥረታት የመጨረሻ ውበትና ክብርን ያጎናጸፋቸው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ለማመልከት በኢዮብ 26፡13 "በመንፈሱ ሰማያት ውበትን አገኙ" የሚል አስደናቂ አገላለጥ ተጠቅሷል። መዝሙረኛው ዳዊት ደግሞ፥ "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ" (መዝ. 19፡1) በማለት የመንፈስ ቅዱስን ለፍጥረት ውበትና ሞገስ የመስጠት ሥራ ውጤት ይናገራል። ፍጥረታት ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር መፈጠራቸውን ባጠቃላይ ስናጠና ልንገነዘበው የሚገባ መሠረታዊ ነገር ነው። የመንፈስ ቅዱስ ዋናውና ትልቁ ሥራ፥ ለእግዚአብሔር አብና ለእግዚአብሔር ወልድ ክብር ማምጣት ነው። በአሁኑ ዘመን ስላለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ዓላማ ክርስቶስ ሲናገር፦ "የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል። እርሱ ያከብረኛል ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና" (ዮሐ. 16፡13-14) ብሏል። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንጊዜም ይህ ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ክብር ለማንጸባረቅ በሚያከናውነው ሥራ ውስጥ ጌታን ያሳያል እንጂ ከፊት አይሆንም።

በመፍጠር ሥራ ውስጥም መንፈስ ቅዱስ የተለየ ድርሻ እንዳለው ተመልክተናል። እርሱ ፍጥረታትን ሥርዓት አስያዘ፤ ለፍጥረታት ሕይወት ሰጠ፤ ደግሞም ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር ለማምጣት ለፍጥረት ውበትን አጎናጸፈ።

3. ፍጥረታትን ጠብቆ የማቆየትና የማደስ ሥራ

መንፈስ ቅዱስ ፈጽሚል ከምንለው ከመጀመሪያውና ከዋናው የመፍጠር ተግባር ሌላ፥ ፍጥረታትን ጠብቆ በማቆየትና በማደስ ሥራ ውስጥ ትልቅ ድርሻ እንዳለው እንመለከታለን። በፍጥረታት ውስጥ ወይም ከፍጥረታት ጋር አብሮ የመኖሩ መሠረታዊ ትምህርት፥ በዓለም ላይ ያለውን ቀጣይ ሥራ ለማመልከት ጠቃሚ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ግልጥ የሆነ መረጃ ይሰጣል። በመፍጠር የመጀመሪያ ሥራ መሳተፍ ብቻ ሳይሆን ፍጥረታትን ጠብቆ የማቆየት ተግባርም እንዳለው በበርካታ ጥቅሶች ለማረጋገጥ ይቻላል። ለምሳሌ በመዝሙር 104፡29-30 ‘‘ፊትህን ስትሰውር ይደነግጣሉ፤ ነፍሳቸውን ታወጣለህ ይሞታሉም፥ ወደ አፈራቸውም ይመለሳሉ። መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም፥ የምድርንም ፊት ታድሳለህ’’ ይላል። ለምሳሌ ይህ ክፍል በጥቅሉ የመንፈስ ቅዱስን የመፍጠር ሥራ ከማረጋገጡ ሌላ፥ በዓለም ላይ በቋሚነት ስለሚታየው፥ በተለይም ወቅትን እየጠበቀ ስለሚሆነው የፍጥረታት ተሐድሶ ይናገራል። እግዚአብሔር ፍጥረታትን በተወሰነ መጠን ቢፈጥራቸውም፥ ራሳቸውን ለማቆየት የሚችሉ አድርጓቸዋል። ለዚህ ነው እንስሳትና ዕፅዋት ዘራቸውን ጠብቀው ማቆየት የሚችሉት። ከዚህ ከምናየው ውጫዊ ሥርዓት ሌላ ፍጥረታትን የማቆየት፥ የመምራትና የማደስን ሥራ የሚያከናውነው መንፈስ ቅዱስ ነው። ተፈጥሮአዊውን ዓለም ከመጠበቅ፥ ከማቆየትና ከማደስ ሌላ፥ ቀላልና ቀጥተኛ ያልሆነ ተግባርም ሲያከናውን ይታያል። በመንፈሳዊ ግዛት ውስጥ እንቅስቃሴዎችና አዲስ ሕይወት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳላቸው ሁሉ፥ በተፈጥሮአዊ ግዛት ውስጥም እንዲሁ ነው። በተለያየ መልኩ የምናየው የአዲስ ሕይወት ውበት፥ ከፍጥረታቱ ጋር አብሮ ለሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ሥራ ምስክር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥራው የሚናገረውን ምስክርነት ስንመረምር፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃላፊነት ታላቅና አስፈላጊ መሆኑን እንረዳለን። ብዙ ጊዜ ትኩረት የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ላለው ሥራ ቢሆንም፥ በተፈጥሮአዊው ዓለም ውስጥ የሚያከናውነው ሥራም በሚታየው ፍጥረት መካከል አዲስና አስደናቂ ነገር ሊያመጣ የሚችል ነው። የማፍለቅ (የማስገኘት) የመፍጠርም ሆነ ፍጥረታትን የመጠበቅ ሥራው ለዳግም መፈጠር፥ ለዳግም ልደትና ሕይወትን ለመስጠት ሥራዎቹ መግቢያ ናቸው። ተፈጥሮአዊው ዓለም የመንፈስ ቅዱስን ወሰን-የለሽ ጥበብ፥ ኃይል፥ ክብርና ታማኝነት ሊገልጥ የሚችል በቂ ማስረጃ ነው። ይህም ከቅዱሳን ጋር በሚኖረው ኅብረትና ለሕይወታቸው ደስታን በማጎናጸፍ አገልግሎቱ ከሚገለጠው መንፈሳዊ ልምምድ ጋር ይነጻጸራል።

6

መገለጥ በብሉይ ኪዳን

1. የመለኮታዊ መገለጥ [Revelation] ዓይነቶች

እግዚአብሔር እራሱን በተለያየ መንገድ ለሰው ልጆች ገልጧል። መገለጡን ግልጥና ቋሚ በሆነ መንገድ በቃሉ የሰጠው፥ ለዘለላም ተጠብቆ እንዲኖር፥ በሚገባ እንዲጠናና የእውነት ሁሉ መለኪያ እንዲሆን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን በማጥናት ቃሉ የሚያስተላልፈውን መልእክት በሚገባ ለመለየትና ለመረዳት እንችል ዘንድ፥ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ችሎታን መስጠቱ ሁለተኛው የመገለጥ ዓይነት ነው። ከተጻፈው ቃል በተጨማሪ ዘላለማዊ ቃል የሆነው ክርስቶስ ራሱ በሕይወቱ፥ በአገልግሎቱና በሞቱ እግዚአብሔርን ለመግለጥ መጣ። ከሞት በመነሣቱም በቅዱሳት መጻሕፍት ለተገለጠው ወደር የለሽ የእግዚአብሔር ባሕርያት ተጨባጭ ማረጋገጫ ሆነ። እግዚአብሔር ከክርስቶስና ከቅዱሳት መጻሕፍት ሌላ በፈጠራቸው ፍጥረታት ውስጥ ራሱን ገለጠ። የቁሳዊ ፍጥረታት ውበትና ሥነ-ሥርዓት ስለፈጠራቸው አስደናቂ አምላክ ይናገራሉ።

በብሉይ ኪዳን የተገለጠው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከሌሎች መገለጦች ሁሉ የተለየ ነው። ቃሉ ከመጻፉ በፊትና በተጻፈበት ጊዜ፥ እንዲሁም ክርስቶስ በሥጋ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት፥ በተለይ ደግሞ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ዘላለማዊ ፈቃዱን፥ እውነቱንና ፕሮግራሙን ለአንዳንድ ሰዎችና ቡድኖች ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ገልጦላቸዋል። አንዳንዴ በነቢያት፥ ሌላ ጊዜ በሁኔታዎች፥ ደግሞም በታላላቅ ድንቆች ፈቃዱን ለሕዝቡ ይገልጥ ነበር። ጌታ ራሱን ለሰዎች የገለጠባቸው በርከት ያሉ ሁኔታዎች እንዳሉ ቢነገርም፥ በእውነተኛነቱ የታወቀውና ተቀባይነት ያለው፥ ለዚህ ዘመን የሚሆን ብቸኛ ምንጭ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከዚህ በታች የምንመለከተው፥ ይህን መገለጥ በመስጠት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የነበረውን ድርሻ ይሆናል።

2. የብሉይ ኪዳን መገለጥ መጠን

የብሉይ ኪዳን መገለጥ ክርስቶስ በሥጋ ከመምጣቱ በፊት የነበረውን ነገር ሁሉ ይጨምራል። በዚህ ክፍል የቀረበው፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያለ ምንም የጽሑፍ ሰነድ ከሰው ልጆች ጋር ያደረገው ቀጥተኛ ግንኙነት ብቻ ነው። የማስረጃ ምንጮቹም በወግ በተገለጡ ሁለት ምድቦች ተከፍለዋል።

ከሙሴ በፊት የነበረ መገለጥ። ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ቅዱሳት መጻሕፍትን ከማቅረባቸው በፊት የተለያዩ መገለጦች ተሰጥተው ነበር። በብሉይ ኪዳን ቢያንስ ሁለት መጻሕፍት፥ ኦሪት ዘፍጥረት እና መጽሐፈ ኢዮብ፥ ከቅዱሳት መጻሕፍት ዘመን በፊት ስለነበሩ ታሪኮች ይናገራሉ። በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ታሪኮች እንደቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፥ ጸሐፊዎቹ በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፏቸው ቢሆኑም፥ የሚያወሩት ታሪክ ግን ከዚያ ዘመን በፊት ስለነበረ ጉዳይ ነው። ስለ እግዚአብሔር እና ስለ አሠራሩ በዚያ ዘመን የተገለጡት ነገሮች ሁሉ በእርሱ ዘንድ ያለው እውነት እንዲታወቅ እግዚአብሔር ራሱ የሠራው ታላቅ ሥራ ውጤቶች ናቸው። ኢዮብ እና ጓደኞቹ የነበራቸው እውቀት በሙሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት በፊት እግዚአብሔር ራሱን ግልጥ በሆነ መንገድ ያስተዋወቀበት ሁኔታ እንደነበር ያሳያሉ። መጽሐፈ ኢዮብ ስለ ሥነ-መለኮት በቂ እውቀት የሚሰጥ ነው። ኢዮብ እና ጓደኞቹ ስለ እግዚአብሔር የነበራቸው እውቀት የተገለጠበት ነገር እግዚአብሔር ራሱን ያለ በቂ ምስክር እንዳልተወ ያሳያል።

ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ድረስ የተሰጡ መገለጦች። ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ድረስ በነበረው ዘመን፥ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ለሰው ልጆች መገለጥን ሰጥቷል። በዚያ ዘመን በብሉይ ኪዳን የተወሰነ ክፍል በጽሑፍ የተሰጠው መገለጥ ትልቅ ስፍራ ነበረው። ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር በነቢያት በኩል በቀጥታ ለሕዝቡ ይናገር ነበር። ነቢያት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ካመጡት መልእክት መካከል እጅግ የተወሰነው ክፍል ብቻ ተመዝግቦ ሊቆይ ችሏል። እግዚአብሔር ከአዳም ጀምሮ የሰጠው መልእክት በኦሪት ዘፍጥረትና በቀሩት የብሉይ ኪዳን ክፍሎች መገለጡ የተሰጠባቸው ዋና ዋና መንገዶች ሳይቀየሩ ቆይተዋል። በጽሑፍ የሰፈረው ቃል የመጀመሪያ ዓላማ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መገለጥ ያለ አንዳች ስሕተት ለሚቀጥለው ትውልድ ማቆየት ቢሆንም፥ በወቅቱ የተሰጠው ቀጥተኛ መገለጥ በዘመኑ ለነበሩ ሰዎች ወቅታዊ መመሪያና ለችግራቸው መፍትሔን ለመስጠት ነበር። ደግሞም ለቀረው ዘመን የእውነት መመሪያነትም ነው። ለዚህ ነው ቃሉ በተሟላ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈረው።

3. የብሉይ ኪዳን ነቢያት

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ወደር በሌለው ሁኔታ ቻይነቱ ቀጥተኛ መገለጥን ይሰጥ የነበረው፥ ብዙ ጊዜ በሕዝቡ መካከል በነቢይነታቸው በታወቁ ሰዎች በኩል ነበር። ነገር ግን መገለጥ የተሰጠው

ለነቢያት ብቻ ነው ብሎ ውሳኔ ላይ መድረስ ስሕተት ይሆናል። ትንቢት በመገለጥ መልክ ለሕዝቡ የሚሰጥ መልእክት ሲሆን፥ መገለጥ ደግሞ ያ የተሰጠው መልእክት ሕዝቡ ዘንድ መድረሱና ተቀባይነት ማግኘቱ ነው። ካይፐር እንዳለው፥ ‹‹እግዚአብሔር ለነቢያት ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም መልእክትን ሰጥቷል፤ ለምሳሌ፦ ለሔዋን፥ ለቃየል፥ ለአጋር፥ ወዘተ.። አንድ ሰው የተሰጠውን መልእክት ለሌሎች እንዲያደርስ ካልታዘዘ በስተቀር መገለጥን መቀበል ወይም ራእይን ማየት ብቻ ነቢይ አያደርገውም። ‘ናቢ’ የሚለው የዕብራይስጥ ቃል፥ ከእግዚአብሔር መልእክት ስለሚቀበል ሰው ሳይሆን፥ ወደ ሕዝቡ መልእክትን ስለሚያመጣ ነቢይ ነው የሚናገረው። ስለዚህ መለኮታዊ መገለጥ የሚሰጠው ለነቢያት ብቻ ነው ብሎ መቀበል ስሕተት ነው።›› መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ እንደሚያደርገው የብሉይ ኪዳን ነቢያት የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ ለማድረስ ዋናዎቹ አገልጋዮች ነበሩ።

በታሪካዊ አመጣጣቸው ላይ በመመሥረት የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ሥራ ስናጠና፥ የተለያዩ ነቢያት ያገለገሉባቸውን ወቅቶች ቢያንስ በሰባት ታሪካዊ ጊዜያት ከፍለን ልንገልጣቸው እንችላለን። እነዚህ ሰባት የተለያዩ ጊዜያት፥ በተወሰኑ ሁኔታዎች የተከፋፈሉና አንዱ በሌላው ላይ የሚደረብ ቢሆኑም፥ ልዩ የሚያደርጋቸው የራሳቸው ባሕርይ እንዳላቸው በቀላሉ መመልከት ይቻላል።

ከአብርሃም በፊት የተሰጠ መገለጥ። ከአብርሃም በፊት እግዚአብሔር በማዘውተር ለሰው ልጆች መገለጥን ሰጥቷል። እንደ ሄኖክ እና ኖኅ ያሉ ሰዎች በዚያ ጊዜ መገለጥ የተሰጣቸው ቢሆኑም፥ ብዙ መገለጥ የተሰጣቸው ግን በነቢያት አገልግሎት ምንም ድርሻ ያልነበራቸው ሰዎች ናቸው። እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜ ለአዳም፥ ለሔዋን፥ ለቃየንና ታሪካቸው ላልተመዘገበ ሌሎች ሰዎች ሁሉ መልእክት ሰጥቷል። ለእነዚህ ሰዎች የመጣው መልእክት በቅድሚያ ለሌሎች የሚተላለፍ ሳይሆን ለራሳቸው ነው። ቀጥሎ በስፋት የተሰጠው መገለጥና የኖኅ የነቢይነት አገልግሎት ልናስተውለው የሚገባ ነው። አዲስ ኪዳን ደግሞ የሄኖክን አገልግሎት ጨምሮ ይገልጣል (ይሁዳ 14)። ሄኖክ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያልተገለጠና ስለ ወደፊቱ የሚናገር ጥልቅ የሆነ መሠረታዊ ትምህርት መግለጡ፥ በአሪት ዘፍጥረት ውስጥ ከታየው የበለጠ የነቢይነት አገልግሎት በዚህ ዘመን እንደነበር ያሳየናል።

ለአብርሃም የተሰጠ መገለጥ። በትንቢት ታሪክ አብርሃም የነበረበት ዘመን ቅድሚያ የያዘ ነው። አብርሃም እግዚአብሔር ያነጋገረውና የባረከው ነቢይ ስለመሆኑ በግልጥ ተነግሯል (ዘፍጥ. 20፡7)። አብርሃም

በታሪክ ውስጥ ያለውን ቦታ በሚመለከት በርካታ መገለጦች የተሰጡት ሲሆን፥ የእግዚአብሔር ታላቅ ዓላማም በሕይወቱ እንዲገለጥ ተደርጓል። ነገር ግን መልእክቱን ለሌሎች እንዲያስተላልፍ ስለመጠየቁ የተገለጠ አንዳችም ነገር የለም። ታሪኩ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ እንዲቀር ከመደረጉ ውጪ ለሌሎች እንዲያስተላልፍ የተሰጠው አንዳችም ትእዛዝ አልነበረም። በኖረበት ዘመንና ከእርሱም በኋላ እግዚአብሔር ለይስሐቅ እና ለያዕቆብ በመናገር የሰጠውን መልእክት አጽንቷል።

ለሙሴ የተሰጠ መገለጥ። የሙሴ የሕይወት ዘመን ከፍተኛ የነቢይነት አገልግሎትና እጅግ ሰፊ የሆኑ መገለጦች የተገኙበት ነው። በዚያ ዘመን ‘‘ፔንታቱክ’’ ተብለው የሚጠሩት አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ከመጻፋቸውም ሌላ፥ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ከማውጣት ተግባር ጋር የተያያዙ በርካታ መገለጦች አስፈልገው ነበር። እግዚአብሔር በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ሙሴን የተገናኘበት መንገድ ነቢይ የጠራበትን ልዩ ጥሪ ያሳያል። የሙሴ ነቢይነት በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ የታወቀና ተቀባይነት ያገኘ ነበር። እግዚአብሔር ግልጥ ባልሆነ ራእይ ሳይሆን ‘‘አፍ ለአፍ’’ ይናገረው ነበር (ዘኍል. 12፡8)። ሙሴ ያበረከተው ዋና ነገር፥ አምስቱን መጻሕፍት መጻፉ ቢሆንም፥ ስላልተገለጡ ብቻ ሌሎች የነቢይነት አገልግሎቶች ጨርሶ አላበረከተም ማለት አንችልም። በሙሴ ሕይወት የነቢይነት ሥራና ባሕርያት በሙላት ይታዩ ነበር። ወንድሙ አሮን እና እኅቱ ማርያምም ነቢያት ስለነበሩ በሥራው ያግዙት ነበር። ቢሆንም፥ አጋዦቹ በደረጃም ሆነ በመብት ከእርሱ በታች ነበሩ (ዘጸ. 7፡1፤ 15፡20)። በነቢይነት የተጠቀሰች የመጀመሪያይቱ ሴት ማርያም ናት።

በዘመነ መሳፍንት የተሰጠ መገለጥ። ዘመነ መሳፍንት ከሙሴ ዘመን ጋር በቀጥታ ሊነጻጸር የሚችል ነው። ይህ የሽንፈትና ተስፋ የመቁረጥ ዘመን ነበር። በመሳፍንት የመጨረሻ እና ሰፊ ከሆነው የነቢያት ዘመን የመጀመሪያ ከሆነው ሳሙኤል በስተቀር በስም የተጠቀሰ አንድም ነቢይ በዘመነ መሳፍንት አልነበረም። ዲቦራ ሴት ነቢይት እንደነበረችና (መሳ. 4፡4) ለጌዴዎን መንገድን ያመቻቸና ስሙ ያልተጠቀሰ አንድ ነቢይ (መሳ. 6፡8) እንደነበር ብቻ ተጠቅሷል። ይህ ዘመን የእግዚአብሔር ቃል የራቀበትና ራእይም የማይገለጥበት ዘመን ነበር (1ኛ ሳሙ. 3፡1)። አንዳንድ ጊዜ ግን እግዚአብሔር እንደ ጌዴዎን ላሉ ሰዎች ይናገር ነበር (መሳ. 6፡12ቀ.)። ሆኖም አብዛኛውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ የነቢያቱን ስም፥ ወይም እግዚአብሔር በምን መንገድ መልእክቱን እንዳስተላለፈ አይገልጥልንም (መሳ. 2፡20፥ 22፤ 10፡11-14፤ 13፡3-20፤ 20፡18፥ 23፥ 28)።

በቀደሙት ነገሥታት ዘመን የተሰጡ መገለጫች። በሳሙኤል ጀምሮ የጽሑፍ ነቢያት በመባል በሚታወቁት ነቢያት ባበቃው የእስራኤል ነገሥታት ዘመን፥ የነቢያት አገልግሎት እርምጃ እንዳሳየ እንመለከታለን። ሥልጣንን የተሞላ መገለጥ ያመጡ፥ በሕዝቡ መካከል የተከበሩና ልዩ ስፍራ የተሰጣቸው ነቢያት ተነሥተው ነበር። ነቢያት ራእይ ወይም መገለጥ የሚሰጣቸውና ትንቢት የሚናገሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፥ በመለኮታዊ ኃይል ተመርጠው እግዚአብሔርን በመወከል ለዚህ አገልግሎት ተለይተው በሕዝቡ መካከል የተቀመጡ ሰዎች ነበሩ። የሳሙኤል አመላለድና አስተዳደግ ያልተለመደ ቢሆንም እግዚአብሔር ነቢያትን የጠራበትን አጠራር የሚገልጥ መንገድ ነው። የሳሙኤል የነቢይነት አገልግሎት ለዳዊት እና ለሰሎሞን ተቀብቶ መንገሥና ለተገለጠው ለመንግሥታቸው ክብር ምክንያት እንደነበር አንዳችም ጥርጥር የለም።

በሳሙኤል የሕይወት ዘመን የነቢያት ትምህርት ቤት ተመሠረተ (1ኛ ሳሙ. 19፡18-24)። ትምህርት ቤቱ የተመሠረተው ምናልባት ነቢያት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ለማገልገል ከፍተኛ ፍቅር ያለው አእምሮ በነበራቸው ወጣቶች ሁኔታ በመማረካቸው ሳይሆን አይቀርም። የነቢያት ትምህርት ዋና ተግባር ነቢያት በውስጡ ትምህርት ማስተማራቸው ሲሆን፥ ከእግዚአብሔር መገለጥን ማግኘትና በመካከላቸው ድንቅና ተአምራት መፈጸሙም የተለመደ ነገር ነበር። ነቢያት ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ባያውቅም፥ ንጉሥ ሰሎሞን እራሱ ከነቢዩ ናታን ተምሮ ነበር።

በነገሥታት ዘመን የነቢያት ሥልጣን በተደጋጋሚ ታይቷል። ሳኦል በራሱ ላይ ውድቀትን ያመጣው ለነቢያት ሥልጣን በቂ ትኩረት ሊሰጥ ባለመቻሉ ነው (1ኛ ሳሙ. 13፡13-14)። ንጉሥ ዳዊት በነቢዩ ናታን (2ኛ ሳሙ. 12) እንደዚሁም በነቢዩ ጋድ (2ኛ ሳሙ. 24፡13 በግልጥ ተገሥጿል። በዚህ ዘመን በሰፊው ይታወቁ የነበሩ ነቢያት አኪያ፥ ኢዩኤል፥ ኤልያስና ኤልሳዕ ናቸው። አልፎ አልፎም እንደ ሕልዳና ያሉ ነቢያት ታይተዋል (2ኛ ነገሥት 22፡14፤ 2ኛ ዜና 34፡22)። አብዛኛው የነቢያት መልእክት ከጊዜው ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነበር። ሰፋ የሚሉት የኢሳይያስ እና የኤርምያስ መልእክቶች የመጡት በኋላ ነው። የነቢያት አገልግሎት አስፈላጊነት እጅግ ታላቅ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ ነቢያት ከነገሥታቱም ላቅ ያለ ምግባራዊ ሕይወት የነበራቸውና በመልእክታቸው በሚሰጡት ድጋፍ የተነሣ የማንኛውም ገዥ አመራር መሳካት ምክንያት ነበሩ። በዘመናቸው ከተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰኑትን የጻፉት እነርሱ እንደሆኑ ሲገመት፥ አብዛኛዎቹ ግን በካህናት እና በጻፎች መሆኑ የማያሻማ ሐቅ ነው። ስለዚህ ነቢያት መልእክታቸውን በጽሑፍ በማስቀረት የተጫወቱት ሚና አነስተኛ ነው ለማለት እንችላለን።

ከምርኮ በፊትና በምርኮ ወቅት የተሰጡ መገለጦች። ይህ ወቅት በኋላ ተማርከው የተወሰዱት ሕዝቅኤልና ዳንኤል የጻፏቸውን መጻሕፍት ጨምሮ፥ ነቢያት መልእክት በመናገርም ሆነ በጽሑፍ ለማስቀረት በመጣር የታወቁበት ታላቅ ዘመን ነው። በእነዚህ ዘመናት ነቢያት ምን እንዳስተማሩና ምን እንዳደረጉ ጭምር የሚናገሩ ታላላቅ መጻሕፍት ተጻፉ። ነቢያት እንደጠቆረ ከባድ ደመና በመቅረብ ላይ የነበረውን የእግዚአብሔር ፍርድና ሊመጣ ስላለው ምርኮ የማስጠንቀቂያ መልእክቶቻቸውን ወደፊት ሊገለጥ ካለው መንግሥት ክብር ጋር አቀናጅተው በመናገር አቀረቡ። እንደ ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ሕዝቅኤል እና ዳንኤል ያሉ በዚያን ዘመን ያገለገሉ ታላላቅ ነቢያት፥ ዘመኑ ታላቅ የነቢያት ዘመን መሆኑን የሚያሳዩ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ምሳሌዎች ናቸው። መልእክታቸው አንዳንዴ ተቀባይነት ባያገኝም፥ የነቢይነት ስጦታ እንደነበራቸው ግን በርካታ መረጃዎች አሉ። በመልእክታቸው ስፋትም ሆነ በአቀራረባቸው ውበት እና ጥራት፥ በየትኛውም ጊዜ ከተገለጠው የነቢያት መልእክት እጅግ የላቁ ነበሩ። ከጠቀስናቸው ታላላቅ ነቢያት ሌላ በዘመኑ ያገለገሉ በርካታ ነቢያት ነበሩ። ከእነርሱም ዓዙር፥ ሐናንያ፥ ሆሴዕ፥ ኢዩኤል፥ አሞጽ፥ አብድዩ፥ ዮናስ፥ ሚክያስ፥ ናሆም፥ ዕንባቆምና ሶፎንያስ ይገኙበታል። ስማቸው ባይጠቀስም ከእነዚህ ነቢያት ጋር ያገለገሉ ሌሎችም በርካታ ነቢያት እንደነበሩ የማያጠራጥር ነው። ልክ እንደ ሌሎቹ ዘመናት በዚህ ዘመን የተጠቀሰ የሴት የነቢይነት አገልግሎት አነስተኛ ነው። በኢሳይያስ ሚስት እንደምናየው የነቢያት ሚስቶች የባሎቻቸውን አገልግሎት በተወሰነ መጠን ይካፈሉ ነበር (ኢሳ. 8፡3)።

ከምርኮ በኋላ የተሰጡ መገለጦች። የብሉይ ኪዳን ነቢያት አገልግሎት ማጠቃለያ የሚገኘው ከምርኮ በኋላ ነው። መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ ስለዚህ ዘመን ዋናውን ታሪካዊ መሠረት ሲሰጡን፥ የሐጌና የዘካርያስ፥ በኋላም የሚከያስ አገልግሎት ለዚህ ዘመን የተገለጠውን የነቢይነት ዋና አገልግሎት ያሳዩናል። እነዚህ ሦስት ነቢያት በጽሑፍ ያስቀሩልን የመልእክታቸውን የተወሰነ ክፍል ብቻ ነው። በዘሩባቤል መሪነት የተካሄደው የቤተ መቅደስ ግንባታ ሥራ የተሳካ የሆነው፥ በነቢዩ ሐጌና በነቢዩ ዘካርያስ አገልግሎት በተገኘው የማያቋርጥ እርዳታና ማበረታቻ ነው። ከስድሳ ዓመት በኋላ ዕዝራ ለሚፈለገው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ (ተሐድሶ) መምጣት ምክንያት ሆነ። ከዕዝራ በኋላ ጥቂት ቆይቶ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ነህምያ፥ ከተማይቱን እና ቅጥሯን የመገንባት ፍላጎት በሕዝቡ ውስጥ እንዲነሣሣ አደረገ፤ ለዚህም ኃላፊነት ከዕዝራ በቂ ድጋፍን አገኘ።

ሚልክያስ የመጣው በነህምያ አገልግሎት ዘመን ሲሆን፥ የእርሱ የነቢይነት አገልግሎት የታየው ግን በኋለኛው የነህምያ የሕይወት ዘመን ሳይሆን አይቀርም። መልእክታቸውን በጽሑፍ ካስቀሩልን የብሉይ ኪዳን ነቢያት የመጨረሻው፥ የሚልክያስ መልእክት በወደፊቱ ጉዳይ ላይ ማተኮሩ ከጊዜው ጋር የሚስማማ ነው። ሚልክያስ ሕዝቡን ስለ ኃጢአቱ በማስታወስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እና ስለ ክርስቶስ መምጣት በሥዕላዊ መግለጫ ግሩም በሆነ መንገድ ያቀርበዋል። ስለ ጌታ ቀን መምጣት በመናገር ሁለተኛው ኤልያስ የሆነውን የመጥምቁ ዮሐንስን መምጣት እንዲጠባበቁ በማበረታታት መልእክቱን ያጠቃልላል።

እውነተኞች ነቢያትን በሙሉ ከሌሎች ሰዎች የሚለያቸው የከበረ ነገር፥ አገልግሎታቸው የእግዚአብሔርን ቃል መናገር መሆኑ ነው። መልእክታቸው ትንቢት ነው የምንልበት ዋና ምክንያት፥ እነርሱ ካልገለጡት ሊታወቅ የማይችለውን የወደፊት ነገር መናገራቸው አይደለም። ነቢያት ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት ሕዝቡን እንደመራ ለመናገር፥ ያለፈውን ጊዜ በማስታወስ ይጽፋሉ። በሌላ ጊዜ ደግሞ በጊዜው ለተፈጠረው ችግር ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ የሚያብራሩ ግልጥ መመሪያዎችን ይሰጣሉ። ኢየሩሳሌም በተከበበች ጊዜ ንጉሥ ሕዝቅያስ ምን ማድረግ እንዳለበት የተናገረው ነቢዩ ኢሳይያስ ነበር። ብዙ ጊዜ መልእክታቸው በኃጢአት ላይ ስለሚመጣ ፍርድ ነው። እግዚአብሔርን ማምለክ እና መታዘዝ አስፈላጊ መሆኑን የሚናገሩ ምክሮችና ማበረታቻዎች በመልእክታቸው ይገኙ ነበር። በዚህ በተቀደሰ አገልግሎታቸው ምክንያት ነቢያት የአገር መሪዎች፥ ጀግኖች፥ ተሐድሶ አምጪዎች፥ የእግዚአብሔር ወኪሎችና በማንኛውም ዓይነት ርእስ ይሁን መገለጥን የሚያመጡ ነበሩ። ሕይወታቸው እና አገልግሎታቸው በብሉይ ኪዳን የምናየውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ መልካም አቅጣጫ ለማስያዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

4. መገለጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

መገለጥን የተቀበለ ሰው ሁሉ ነቢይ ነው ማለት ባይቻልም፥ አንድ ሰው መገለጥን ሳይቀበል እውነተኛ ነቢይ ሊሆን ጨርሶ አይችልም። ነቢይነት በግልጥ ከሚያሳየው ውጫዊ ምልክት ሌላ፥ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን አሳብ ለነቢያቱ የሚገልጥበት ምስጢር ጭምር ነው። ይህን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በሚመለከት በግልጥ የተሰጠ ማረጋገጫ መኖሩን ብሉይ ኪዳንን በምናጠናበት ጊዜ እናገኛለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚሰጡት ቀጥተኛ ምሰክርነት። መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን የነበረውን አገልግሎት በሚመለከት

የሚመሰክርልንን ቃል የምናገኘው በአዲስ ኪዳን ውስጥ መሆኑ እንግዳ ነገር ይመስላል፦ ‹‹ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ›› (2ኛ ጴጥ. 1፡21)። በብሉይ ኪዳን የተገለጠው ትንቢት በሙሉ መልእክቱን ባመጡ ሰዎች ችሎታ የተገለጠ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ራሱ የሰጠው መገለጥ እንደሆነ እንመለከታለን። አንድ ጀልባ በላዩ የተሳፈሩትን ሰዎች ወደሚፈለገው ስፍራ እንደሚያደርሳቸው ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስ በነቢያት ልብ ውስጥ የሚሠራው ሥራ እንዲሁ ነው። ነቢያት ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በመስጠት መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ለሚሠራው ሥራ ፈቃደኞች መሆናቸውን እንመለከታለን። የመገለጡ ምንጭ ግን እግዚአብሔር ራሱ ነበር።

ይህ በአዲስ ኪዳን የምናገኘው ቃል የተመሠረተው በብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ላይ ነው። መንፈስ ቅዱስ መገለጥን በመስጠት ስለሚያከናውነው ሥራ ዳዊት ምስክርነቱን ሰጥቷል። ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ ቃሉም በአንደበቴ ላይ ነበር›› (2ኛ ሳሙ. 23፡2)። ነቢዩ ሕዝቅኤል መገለጥን የሰጠው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን በተደጋጋሚ ተናግሯል (ሕዝ. 2፡2፤ 8፡3፤ 11፡1፥ 24)። ሚክያስ ለነቢይነት አገልግሎቱ ኃይልንና ብርታትን የሰጠው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ይናገራል (ሚክ. 3፡8)። ቅዱሳት መጻሕፍት የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መሆናቸውን የሚናገሩ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶችን በተጨማሪ ማመልከት ይቻላል (ማቴ. 22፡43፤ ሐዋ. 1፡16፤ 4፡25፤ 28፡25፤ ዕብ. 3፡7፤ 9፡6-8፤ 10፡15)። ቅዱሳን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በመንፈስ ቅዱስ (በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር) ተነድተው የመጻፋቸው እውነት የሚጽፉትን መገለጥ አስቀድመው መቀበላቸውን ያመለክታል። ይህ የመገለጥ ተግባር ለሦስተኛው የሥላሴ አካል መሰጠቱ ታላቅ ጉዳይ ነው።

ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተገለጡ ምስክርነቶች። አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ስለ መንፈስ ቅዱስ በቀጥታ አይናገሩም። የተለመደው አገላለጥ፥ ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል›› የሚል ነው። ይህ አባባል ራሱ መንፈስ ቅዱስ በመገለጥ ውስጥ የሚያከናውነውን ሥራ ያመለክታል። ኦዌን እንዳለው፦ ‹‹እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል ተናገረ ወይም የእግዚአብሔር ቃል ወደ እነርሱ መጣ የሚል ቃል ስናገኝ፥ ለመግለጥ የተፈለገው የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ነው።›› ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ውስጥ ያለው ተግባር የተገለጠው፥ በብሉይና በአዲስ ኪዳን መገለጦቹ ከእግዚአብሔር እንደሚሰጡ በሚያሳዩ ግልጥ ጥቅሶች ነው።

5. መገለጥ የተሰጠባቸው መንገዶች

እግዚአብሔር አሳቡን ለነቢያት ለማሳወቅ ሲል መገለጥን ለመስጠት የተጠቀመባቸው ቢያንስ አራት የተለያዩ የልዩ መገለጥ መንገዶች አሉ። እነዚህ መንገዶች ምን ያህሉ ተፈጥሮአዊ እና ምን ያህሉ ተአምራዊ ሆነው እንደተቀናጁ ማንም ለመገመት አይችልም። ምንጊዜም ቢሆን ትኩረት የተሰጠው መገለጡ ላመጣው ውጤት እንጂ፥ መገለጡ ለመጣበት መንገድ ወይም ዘዴ ባይሆንም፥ መገለጡ የመጣበትን መንገድ ማጥናቱ የመገለጡን ሰማያዊ ባሕርይ ያሳየናል።

በንግግር ወይም በቃላት። ከእግዚአብሔር ዘንድ መገለጥ የመጣበት ዋነኛው መንገድ ንግግር ወይም ቃል ነው። በብሉይ ኪዳን ‘‘እግዚአብሔር እንዲህ ይላል’’ የሚለው ቃል በብዙ ስፍራ ይገኛል። እንደ ኢሳይያስ 6፡1-10 ያሉትን ምንባቦች ከሐዋርያት ሥራ 28፡25 ጋር ማወዳደር በእነዚህ ጊዜያት የተናገረው የሥላሴ አካል መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ያረጋግጡልናል። ብሉይ ኪዳን ተናጋሪውን ‘‘እግዚአብሔር’’ እና ‘‘ጌታ’’ ብሎ ሲጠራ፥ አዲስ ኪዳን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ብሎ ይጠራዋል። እግዚአብሔር ተናገረ ስንል፥ የተናገረበት መንገድ ምን እንደሆነ አጠቃልሎ መናገር አይቻልም። በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ በተጠመቀበት ጊዜ በጴጥሮስ፥ በያዕቆብ እና በዮሐንስ ፊት መልኩ ነጭ እስኪመስል ድረስ በተለወጠበትና፥ ጳውሎስን በተገናኘው ጊዜ እንደሆነው ዓይነት ብዙ ጊዜ በድምፅ ተናግሯል።

በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሔር በተመሳሳይ መንገድ ተናግሯል። ለምሳሌ በሲና ተራራ ሕዝቡ ሙሴ ነቢይ መሆኑን እንዲያምኑበትና እንዲሰሙት፥ እነርሱ በሚረዱትና ምስክር ሊሆን በሚችልበት መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግሯል (ዘዳ. 19፡9)። ሳሙኤል በተጠራ ጊዜ ደግሞ (1ኛ ሳሙ. 3፡1-14)፥ የእግዚአብሔር ድምፅ የኤሊ ድምፅ እስኪመስለው ድረስ የእግዚአብሔርን ድምፅ መለየት አቅቶት ነበር። ስለዚህ የቅዱሳት መጻሕፍትን የቃላት አጠቃቀም ትክክለኛነት የሚቀበል ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር የሚናገረው የሰው ንግግር በሚመስል እውነተኛ ቃላትና ድምፅ መሆኑን ሊረዳ ይችላል። እርግጥ እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ብቻ እንዲጠቀም አይገደድም። የሰው ድምጽ ወይም ሌላ ንግግር የሚያስተላልፍ የመገናኛ መንገድ መጠቀም ለመግባባት አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ግን የቃላት ንግግር እንኳ በማያስፈልገው መንገድ ውጤት የሚያመጣ መልእክት ለሰዎች ልብ ማድረስ ይችላል። አማኝ ዘወትር ከመንፈስ ቅዱስ ይማራል፤ የተማረውን ለሌሎች በሚገባ ለመግለጥ ግን ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ነገር ይሆንበታል።

ስለዚህ እግዚአብሔር አንዳንዴ ከሰው ድምጽ ጋር የሚመሳሰል የመገናኛ መንገድን በመጠቀም፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ በቀጥታ ለልብ መናገር እንደሚችል እንረዳለን።

እግዚአብሔር መልእክት ለመስጠት በቃላት መጠቀሙን ልብ ልንለው የሚገባ አስፈላጊ ነገር ነው። መገለጥ ለአእምሮ ከሚመች ምክንያታዊ ምሪት እጅግ ይልቃል። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚገልጠውና የሚያስረዳው ግልጥ የሆነ መልእክት አለው። የሰው ልጅ ይህን መልእክት ግልጥ በሆኑ ቃላት ይቀበለዋል። የዚህ መንገድ ግልጥነት ስሜትን ከሚነካ፥ ወይም በሕይወት ላይ ተጽዕኖን ከሚያሳድር ነገር በላይ ነው። መልእክቱ ተጨባጭና ግልጥ ነው። እግዚአብሔር መልእክቱን ራሱ ጽፎ ወደ ሰዎች ልጆች ልኮት ቢሆን እንኳን ኖሮ መልእክቱ ይበልጥ እውነተኛና ትክክለኛ አይሆንም ነበር። እግዚአብሔር ፈቃዱ እንዲታወቅ የማድረግ ዓላማው ሁሉ በዚህ ውስጥ ይሟላል።

ሕልም። ሁለተኛው መገለጥን የመቀበያ መንገድ ሕልም ነው። ይህ ዘዴ እግዚአብሔር መገለጥን በመስጠት ለሰው ልጆች የሚናገርበት የተለመደና ተቀባይነት ያለው መንገድ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑ ብዙ መረጃዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን (ዘፍጥ. 20፡3-7፤ 31፡10-13፥ 24፤ 37፡5-20፤ 40፡5-16፤ 41፡11-13፥ 15-32፤ 42፡9፤ ወዘተ.)። እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ከተናገራቸው ሰዎች ብዙዎቹ ነቢያት አልነበሩም። (ለምሳሌ፦ አቤሜሌክ፥ ላባ፥ የፈርዖን የጠጅ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ አዛዦቹ አለቃ፥ ፈርዖን ራሱ) እግዚአብሔር በሕልም የተናገራቸው ሰዎች ነበሩ። መልእክትን በሕልም መቀበል ለነቢያት የተለመደና ተቀባይነት ያለው ነው። በሙሴ ላይ ባደረጉት ማጉረምረም እግዚአብሔር አሮንንና ማርያምን ሲገሥጻቸው እንዲህ ብሏል፥ ‘‘ቃሌን ስሙ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ’’ (ዘኍል. 12፡6)። በተቃራኒው ደግሞ የሙሴን ከፍተኛ የነቢይነት ስፍራ ሲያረጋግጥ ‘‘ሙሴን ግን ፊት ለፊት አናግረዋለሁ’’ ብሏል። አንዳንድ ጊዜ አብርሃም እንደነበረበት ሁኔታ በከባድ እንቅልፍ ከእግዚአብሔር ዘንድ መገለጥ ይሰጣል (ዘፍጥ. 15፡12)። ዳንኤልም በአንድ ወቅት በዚህ ሁኔታ ላይ ነበር (ዳን. 10፡9)። ሐሰተኛ ነቢያት ከእግዚአብሔር ዘንድ መገለጥን በሕልም ሳያገኙ አግኝተናል በማለታቸው እግዚአብሔር ሲነቅፋቸውና ሲገሥጻቸው እንመለከታለን (ኤር. 23፡25)። እንዲህ ያለው መገለጥ ወደፊት በብዛት እንደሚሰጥ በኢዩኤል 2፡28-32 ተተንብዮአል። ጴጥሮስ የዚህ ትንቢት ሙሉ ፍጻሜ ገና ሊመጣ ባለው መንግሥት ቢሆንም፥ ከፊሉ ግን በሐዋርያት ሥራ 2፡16-21፥ እንደተፈጸመ አረጋግጧል። ከእነዚህ በርካታ

ጥቅሶች የምንረዳው፥ መገለጥን የመቀበያው መንገድ ትልቅ ስፍራ እንዳለው ነው።

ራእይ። ከሕልም ጋር በቅርብና በግልጥ የተያያዘው ሌላ መንገድ ራእይ ነው። ነቢያት የሚታወቁበት የዕብራይስጥ ቃል፥ ‘‘ተመልካች’’ ማለት ሲሆን፥ ይህ መጠሪያ ራእይን ከማየት አኳያ፥ የሚሰጣቸው ነበር። አንዳንድ ጊዜ ራእይ ከሕልም ጋር አብሮ የሚሰጥ መገለጥ እንደሆነ ጥርጥር የለንም። በሌላ ጊዜ ደግሞ ነቢዩ ሙሉ ለሙሉ ንቁ በሆነና ባላንቀላፋበት ሰዓት መልእክት መቀበሉን የምናስበው ተኝቶ ለመሆኑ ምንም ማስረጃ ስለማናገኝ ነው። የኢሳይያስ (ኢሳ. 1፡1፤ 6፡1)፥ የሕዝቅኤል (ሕዝ. 1፡3) እና የሚክያስ (1ኛ ነገሥት 22፡19) መገለጦች በዚህ ክፍል የሚመደቡ ናቸው። በንግግር ከሚመጡ ቀጥተኛ መልእክቶች በተቃራኒ፥ በአንዳንድ ሕልሞች እንደሚሆነው ሁሉ፥ ራእይም መልእክቱ ሁልጊዜ ቶሎ ግልጥ የሚሆንና የምንረዳው አይደለም። ሕዝቅኤል በራእይ ያየውን መልእክት መረዳት አለመረዳቱ የሚያጠያይቅ ነው። ሁሉም የነቢያት መልእክቶች በጊዜው ለተፈጠሩ ሁኔታዎች የሚያስተላልፉት መልእክት እንደነበር ከመረዳት አንጻር፥ በጊዜው ለነበሩ ሁኔታዎች የተሰጡ ራእዮች በሙሉ በዚያው መልካቸው ለተቀባዮቹ ግልጥ እንደነበሩ ማሰብ እንችላለን።

ተፈጥሮአዊ ባልሆነ እንቅልፍ [trance] የሚሰጡ መገለጦች።* በሰማያዊ መገለጥ ውስጥ መልእክት የምንቀበልበት አራተኛው መንገድ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ እንቅልፍ ነው። ተፈጥሮአዊ ያልሆነ እንቅልፍ በራሱ የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም። ነገር ግን ሰዎች ከእግዚአብሔር መልእክት የሚቀበሉበት አንዱ መንገድ ነው። ብዙ ጊዜ በሕዝቅኤል እንደሆነው ከራእይ ጋር ይቀናጃል (ሕዝ. 8፡3፤ 11፡24)። በአንዳንድ ሁኔታዎች ተፈጥሮአዊ ባልሆነ እንቅልፍ የምንቀበለውን መገለጥና ሕልምን መለየቱ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። ምክንያቱም ተፈጥሮአዊ ያልሆነው እንቅልፍና፥ ሰማያዊ በሆነው ተጽዕኖ የሚመጣ ከባድ እንቅልፍ ተመሳሳይ ናቸው (ዘፍጥ. 15፡12፤ ዳን. 10፡9)። ተፈጥሮአዊ ያልሆነ እንቅልፍ የእግዚአብሔርን መገለጥ ለመቀበል የግድ አስፈላጊ አይደለም።

በብሉይ ኪዳን ሰዎች የእግዚአብሔርን መገለጥ የተቀበሉባቸው የተለያዩ መንገዶች እነዚህ ሲሆኑ፥ የሰዎች ልምምድ ግን እንደ ሌሎቹ መለኮታዊ ተግባራት ሁሉ የተፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ ሙሉ በሙሉ እንድንረዳ ሊያደርገን አይችልም። ነገር ግን እግዚአብሔር በራሱ መንገድና ሰዎች ሊረዱት በሚችሉት ሁኔታ መልእክቱን አስተላልፏል ማለቱ በቂ ነው። መንገዶቹ ጥቅም ላይ ለዋሉባቸው ዘመናት ፍጹም ተስማሚ ነበሩ። በዘመናችን የእነዚህ ሁሉ ቦታ፥ ሙሉ መገለጥ በሆነው መጽሐፍ ቅዱስና

* ይህ ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው ራእይ በሚያይበት ጊዜ የሚገኝበትን አካላዊ ሁኔታ ነው።

በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ተተክቷል። በየዘመናቱ እግዚአብሔር እራሱን የመግለጥና የማሳወቅ ፍላጎት እንዳለው በእነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ እናረጋግጣለን።

6. በአዲስ ኪዳን የተሰጡ መገለጦች

አጠቃላይ ሁኔታውን ስናየው፥ በአዲስ ኪዳንና በብሉይ ኪዳን በተሰጡ መገለጦች መካከል መሠረታዊ ልዩነት የለም። ዘላለማዊው አምላክ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ራሱን የመግለጥ ሥራውን ቀጥሏል። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን በተወሰኑ ሁኔታዎች እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸው አዳዲስ መንገዶች ታይተዋል።

በክርስቶስ በኩል የተሰጡ መገለጦች። በብሉይ ኪዳን ትንቢት የተነገረለት መሢሕ፥ በአዲስ ኪዳን በሥጋ እንደተገለጠና በአገልግሎቱ ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር መገለጥ እንደታየ እንመለከታለን። መንፈስ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስን በአገልግሎቱ ይረዳው ነበር፤ ቢሆንም ዋናውን የመግለጥ ሥራ ክርስቶስ ራሱ ነበር የሚያከናውነው። ይህ በአዲስ ኪዳን ለተሰጠ ሰፊ መገለጥ መሠረት ጥሏል። የሰው ሥጋ በመልበስ የተገለጠው አምላክ፥ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ሊሰጡ ይቻላቸው ከነበረ ማንኛውም ነገር የላቀ ልዩ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው።

በአማኞች ውስጥ የተሰጠ መገለጥ። ከብሉይ ጋር ሲወዳደር በአዲስ ኪዳንም ሰፊ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ይሰጣል። ከጴንጤቆስጤ ዕለት ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ በማደር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት የመገለጥ ምንጭ ሆኖለታል። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውቁ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። አሁን ግን ቀድሞ ባልነበረ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ አማኙን ይመራል፥ ያስተምራል፥ ይረዳልም። መገለጥ መሠረታዊ መንገዱን ያልተወ ሲሆን፥ ውጤታማነቱም በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት እየሰፋ ሄዷል።

በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል የተሰጡ መገለጦች። የተሟላ መገለጥ በጽሑፍ መልክ የተገኘው በአዲስ ኪዳን ነው። በሐዋርያት ዘመን ለፍጻሜ ቀርቦ የነበረው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል፥ አሁን በተሟላ መልኩ በእጃችን ይገኛል። ስለዚህ በዚህ ዘመን የተሰጠው የመገለጥ ባሕርይ በአብዛኛው የተመሠረተው በጽሑፍ ሰፍሮ በደረሰን መገለጥ ነው። በሕልም፥ በራእይ እና ተፈጥሮአዊ ባልሆነ እንቅልፍ ውስጥ በመሆን በሚሰጥ መገለጥ ፋንታ፥ በሕይወት የሚሆን መመሪያ በተለይ የሚገኘው በጽሑፍ ሰፍሮ በተላለፈልን መገለጥ ሆነ። ይህ ሲባል ግን በጽሑፍ ሰፍሮ ከተላለፈልን መገለጥ ሌላ

በብሉይ ኪዳን የነበሩት ዓይነት መገለጦች በአዲስ ኪዳን አልታዩም ማለት አይደለም። አዲስ ኪዳን ወደ እውነት መምጣት ሲጀምር የቀድሞዎቹ የመገለጥ መንገዶች ስፍራቸውን እየለቀቁ ሄዱ። ምንም እንኳን ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ቀደም ባሉት ጊዜያት ሕልምና ራእይ እንደገና በአገልግሎት ላይ ቢውሉ (ኢዩ. 2፡28ቀ.፤ ሐዋ. 2፡16-21)፥ በአሁኑ ጊዜ ወግ አጥባቂ ክርስቲያኖች ሕልምና ራእይን በመሳሰሉ ሁኔታዎች መጠቀምን ከፍተኛ የጥያቄ ምልክት ያኖሩበታል። መገለጥ በአዲስ ኪዳን የተሟላና በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኝ ተደርጎ ይታያል።

ወደፊት የሚሰጡ መገለጦች። ሁለቱም ኪዳናት በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ላይ በማትኮር ወደፊት ስለሚፈጸሙ መገለጦች ይናገራሉ። በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ወቅት ከሚከናወነው ሁኔታ የእግዚአብሔርን ልጅ ክብር በሙላት የሚያሳይ ልዩ መገለጥ ይሆናል። ያለንበት ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ሲሆን፥ እግዚአብሔርም በዚሁ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይታወቃል። ወደፊት የሚመጣው ዘመን ግን በማያቋርጠው የእግዚአብሔር መንፈስ አገልግሎት የሚታጀብ ሆኖ፥ ዘመኑም በክብሩ የሚገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ዘመን ይሆናል። ይህ የመለኮታዊ መገለጦች ሁሉ ቁንጮ ነው።

7

መንፈስ ቅዱስ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ ውስጥ

1. የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር* አስፈላጊነት

መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ከነበሩት በርካታ አገልግሎቶችና፥ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡት ከሚገባ ትምህርት፥ እስትንፋሰ-እግዚአብሔርን ያህል የሚቀርቡ ሥራዎች እጅግ ጥቂት ናቸው። አብዛኛዎቹ የክርስትና መሠረታዊ እምነቶች በከፍተኛ ሁኔታ የተመሠረቱት፥ በአዲስ ኪዳን በተሰጠው መገለጥ ላይ ነው። ለቸልተኛ (ግድ የለሽ) ተመልካች እንኳን አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ላይ መመሥረቱና፥ አንዱ ኪዳን ከሌላው ተለይቶ ሙሉ የሆነና አጥጋቢ መገለጥ ሊሰጥ አለመቻሉ የታወቀ ነው። ለቅዱሳት መጻሕፍት መገኘት ምክንያት የሆነው የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሠረታዊ ትምህርት፥ በሁለቱም ኪዳናት ውስጥ የጎላ ልዩነት የለውም።

የእምነት ድንጋጌያቸው እንደሚያሳየው፥ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሠረታዊ ትምህርት፥ የአብዛኛዎቹ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት አቋም ነው። በምእመናኑም ሆነ በአገልጋዮቹ እንዲሁም በተለያዩ የእምነት ክፍሎች ዘንድ ባሉ በአብዛኛዎቹ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች መካከል በመጠን የተለያየ ልዩነት ቢኖርም፥ ሁሉም የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት፥ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ትምህርት ላይ ያላቸው ይፋ አቋም አንድና ተመሳሳይ ነው። ሆኖም በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ትምህርት ላይ የተለያዩ አመለካከቶች ባላቸው ቡድኖች መካከል ሰፊ ውይይትና ጥልቅ ክርክር መደረጉ አይካድም። እነዚህን በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ላይ የተደረጉት ጥልቅ ውይይቶች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንመለከታቸውም።

የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በአንዳንድ የዘመኑ አስተማሪዎች ቸል ቢባልም፥ አስፈላጊነቱን ማስረዳቱና

---

* ይህ ጥምረ ቃል፥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በእንግሊዝኛ ‘‘ኢንስፓሬሽን’’ [Inspiration] ለሚለው ቃል ትርጉም ውሏል። ‘‘እስትንፋሰ-እግዚአብሔር’’ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉበት ተግባር ነው።

መግለጥ ግን አስቸጋሪ ነገር አይደለም። ቅዱሳት መጻሕፍት በተአምራዊ መንገድ የተጻፉ የእግዚአብሔር ቃል፥ ያለዚያም ስሕተት ሊኖራቸው የሚችል የሰዎች ሥራ ጥርቅሞች መሆናቸውን መለየቱ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በትነር [Boettner] የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ የሚከተለውን አሳብ በጽሑፉ አስፍሯል፦

> ‘‘የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ትምህርት ጥያቄ ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ መሆኑ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ ነው። ቤተ ክርስቲያን ግልጥ የሆነና ሥልጣን ያለው መረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለምታገኝ መሠረተ እምነቱን ለማቀነባበር ቀላል ሆኖላታል። ማድረግ ያለባት፥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት መመርመርና በመሠረተ እምነት ድንጋጌዋ ላይ ማስፈር ብቻ ነው። ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ባይኖራቸውና መታረም፥ መስተካከል፥ አንዳንድ ክፍሎችም በግልጥ መወገድ ቢኖርባቸው ኖሮ፥ ቤተ ክርስቲያን ልትወጣው በማይቻላት ከፍተኛ ችግር ውስጥ በገባች ነበር። በቤተ ክርስቲያን ዓላማም ሆነ፥ ልትገነባው የሚያስፈልጋትን መሠረተ እምነት ትምህርት አስመልክቶ ወደማያልቅ የአመለካከት ልዩነትና ግጭት ውስጥ ትገባ ነበር።’’

የእስትንፋሰ-እግዚአብሔርን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ለመደገፍ የመከራከሪያ አሳቦችን ማቅረብ የዚህ ትምህርት ዓላማ አይደለም። ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያሉ መረጃዎችን የማቅረብ ሙከራ አይደረግም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ መረጃዎችም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በሚገልጥ መልካቸው ብቻ ይቀርባሉ። በእምነት ዓይኖቻቸው ነገሮችን ለሚያዩ ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው መረጃ ግልጥና በቂ ነው። ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ ስለዚሁ ጉዳይ የሚከተለውን ጽፏል፦

> ‘‘ቤተ ክርስቲያን በዘመናት ሁሉ በተቀበለችው የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ጸንታ የምትቆመው፥ የዚህ ትምህርት ደጋፊዎች ከተቃዋሚዎች ይልቅ ማስተጋባት ወይም ሰብአዊ የሆነ መከላከያ ማቅረብ ስላለባቸው ሳይሆን፥ እውነቱ በመለኮታዊው አዋጅ ውስጥ የተገለጠ በመሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት ቅዱሳንም ሆኑ ሐዋርያት እግዚአብሔር የሚነግራቸውን ቃል ከማመን በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም።’’

2. የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ትርጉም

በመጽሐፍ ቅዱስ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር አሳብ የተጠቀሰው በጥቂት ስፍራዎች ነው። በኢዮብ 32፡8፥ ኤሊሁ ‘‘ነገር ግን በሰው ውስጥ መንፈስ አለ፤ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ይሰጣል’’

ብሏል። በዚያን ጊዜ አሁን በምናየው መልኩ የተዘጋጀ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ባለመኖሩ ይህ ቃል ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አጻጻፍ የሚናገር ነው ብሎ መቀበል በጣም ያስቸግራል።

በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16፥ ከተጻፈው ‘‘እስትንፋሰ-እግዚአብሔር’’ (‘‘የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ’’) ከሚለው ቃል የምንረዳው፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያስገኘው የእግዚአብሔር ሥራ ማለት ቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጡት በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሆኑን ነው። በዚህ መልክ የተገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት ለትምህርት፥ ለተግሣጽ፥ ልብን ለማቅናትና በጽድቅም ላለው ምክር ጠቃሚ የሆኑት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ወይም እስትንፋስ ስላለባቸው እንደሆነ በዚህ ጥቅስ ተገልጧል። ይህ እውነት ቅዱሳት መጻሕፍት አንዳች ስሕተት የሌለባቸውና በመለኮታዊ ሥልጣን የተሞሉ መሆናቸውን ያሳያል። ይህን እውነት ለማረጋገጥ ሲባል በቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኙትን በርካታ ምስክርነቶች እንደገና ለማቅረብ መሞከር እምብዛም አስፈላጊ አይደለም። ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ክርስቶስ ራሱ በተደጋጋሚ ተጠቅሞበታል። ጸሐፊዎቹ እራሳቸውም ጽሑፎቻቸው በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተገኙ መሆ ናቸውን ተናግረዋል። የቅዱሳት መጻሕፍት ይዘትና መልእክታቸው የመለኮታዊ መገለጥ ውጤት፥ የመልእክት አመዘጋገባቸው ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ መሆኑን መመልከት እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መኖር አውቆ ስለ ሕልውናው ማረጋገጥ ሳያስፈልገው ለእርሱ መናገሩን እንደሚቀጥል ሁሉ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትም የእግዚአብሔር መንፈስ ውጤቶች መሆናቸውን አውቆና ተቀብሎ ይገልጣል።

ልንዘነጋው የማይገባ ሌላ ነገር፥ ቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊ ብቻ ሳይሆኑ ሰብአዊም መሆናቸውን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት የቋንቋ ይዘት የጸሐፊውን የቃላት ችሎታ ያሳያል። የጸሐፊዎቹ ስሜት፥ ሰብአዊ እውቀትና ልምምድ፥ ተስፋ...ወዘተ. ሁሉ የእግዚአብሔርን መንፈስ ሕልውና በማያስተባብል መልኩ በጽሑፎቻቸው ውስጥ ተንፀባርቋል። ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳቸው እንደሚመሰክሩት፥ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ቃል በቃል እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያስጻፋቸው ቢሆኑም፥ ብዙዎቹ ግን እንዲህ አይደሉም። በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ ያለው መለኮታዊም ሆነ ሰብአዊ ተጽዕኖ መጠን የተለያየ ቢሆንም፥ ሁሉም ግን በእኩልነት ለእግዚአብሔር ዓላማ ተገቢ የሆኑና መንፈሱ በእኩልነት ያለባቸው ናቸው። በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መመርመር፥ ቅዱሳት መጻሕፍት የመለኮትና የሰው ሥራ ውጤቶች መሆናቸውን የሚያሳየውን መረጃ ያጸናዋል።

ስለዚህ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ትርጉም እግዚአብሔር ተአምራዊ በሆነ መንገድ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችን ሰብአዊ ችሎታ፥ የግል ባሕርይ፥ የአጻጻፍ ስልት፥ ስሜት ወይም ሌላ የሰብእና አቋማቸውን ሳይቀይር፥ ቋሚና ሙሉ የሆነ መልእክቱ ያለ አንዳች ስሕተት እንዲጻፍ ያደረገበትን ሁኔታ ያመለክታል። ጸሐፊዎቹ በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ሳይቀሩ በተአምራዊ ሁኔታና በሥልጣን እየመራ ያጻፈበት መንገድ ነው። ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር መንፈስ (እስትንፋሰ-እግዚአብሔር) ያለባቸው መሆ ናቸውን፥ ቃሉም በትክክል የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እንድንተማመንና ለእምነታችንና ለሕይወታችን እንዲጠቅመን ተሰጥቶናል።

3. እስትንፋሰ-እግዚአብሔር፤ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

ከዚህ ቀደም መንፈስ ቅዱስ መገለጥን በመስጠት ረገድ ሰለሚያከናውነው ተግባር የተመለከትናቸውን ብዙ ነገሮች በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ ውስጥም እንደገና ልንጠቅሳቸው እንችላለን። ነገር ግን የመገለጥ የመጀመሪያና ዋና ተግባር፥ እግዚአብሔር ካልገለጣቸው በቀር ሊታወቁ የማይችሉ ነገሮችን መግለጥ ሲሆን፥ እስትንፋሰ- እግዚአብሔር ግን፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በጽሑፍ ማስፈር ነው። መገለጥን ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ እውነቶችም ተመርጠው እንዲጠቃለሉ ያደርጋል። የጸሐፊዎች የአእምሮና የአስተሳሰብ ውጤትም ተደምሮበታል። በዚህ ልዩ አገልግሎቱ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው ሌሎች እውነቶች ሁሉ ተገልጠውበታል። ቅዱሳት መጻሕፍት በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት የመሰጠታቸው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በስድስት የተለያዩ ክፍሎች ቀጥሎ ቀርቧል።

የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች ምስክርነት። የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች፥ የጻፉት ነገር ሁሉ ገብቷቸውና ተረድተውት ነው የጻፉት ለማለት ባንችልም፥ የሚጽፉት ነገር ሁሉ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤት መሆኑን አውቀው እንደጻፉት ግን አንዳች ጥርጣሬ የለንም። ዋርፊልድ [Warfield] የተባለው ጸሐፊ እንዳለው፥ ‘‘የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች፥ የሚጽፉት ነገር በመለኮታዊ መንፈስ የተጻፈ የሰው ሥራ ውጤት እንደሆነ ቆጥረው ሊያሻሽሉት ወይም ሊያድሱት አልሞከሩም። ቅዱሳት መጻሕፍት፥ እግዚአብሔር በሰዎች ተጠቅሞ የጻፋቸው የመለኮት ውጤቶች ናቸው።’’’ የጻፏቸው መጻሕፍት እስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሆ ናቸውን ለማረጋገጥ ሳይሞክሩ አውቀው የተቀበሏቸው መሆኑን እንረዳለን። በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በግልጥ

ያውቁት እንደነበር የሚያመለክቱ ክፍሎችም ይገኛሉ። ዳዊት የጻፋቸው ጽሑፎች የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤቶች መሆናቸውን ተናግሯል። ‘‘የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ፥ ቃሉም በአንደበቴ ላይ ነበረ። የእስራኤል አምላክ ተናገረኝ፥ የእስራኤል ጠባቂ እንዲህ አለ’’ (2ኛ ሳሙ. 23፡2-3)። ኢሳይያስም የጌታ ቃል በተመሳሳይ መንገድ እንደተጻፈ ጠቅሷል፥ ‘‘ከእነርሱ ጋር ያለው ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ይላል እግዚአብሔር፤ በአንተ ላይ ያለ መንፈሴ በአፍህም ውስጥ ያደረግሁት ቃሌ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ ከአፍህ ከዘርህም አፍ ከዘር ዘርህም አፍ አያልፍም፥ ይላል እግዚአብሔር’’ (ኢሳ. 59፡21)። ኤርምያስም እግዚአብሔር ቃሉን በአፉ ውስጥ እንዳኖረለት መስክሯል። ‘‘እግዚአብሔርም እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ፥ እግዚአብሔርም፦ እነሆ፥ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ...አለኝ’’ (ኤር. 1፡9)። የነቢያቱ ጽሑፎች፥ እግዚአብሔርን በእውነት በሚያመልኩ ሁሉ ዘንድ እንደ እግዚአብሔር ቃል ወዲያውኑ ተቀባይነት አግኝተዋል። ጽሑፎቻቸው የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤቶች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ምንም ማስረጃ ለማቅረብ አለመሞከራቸው፥ ማረጋገጫ ማቅረቡ አስፈላጊ እንዳልነበረ የሚያመለክት ነው። የጽሑፎቹ ባሕርይ ራሱ ለጸሐፊዎቹም ሆነ ለአንባቢዎች በቂ ማስረጃ ነበር።

የነቢያት የቋንቋ አጠቃቀም። በብዙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፥ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ብቻ ሊብራሩ የሚችሉ ተደጋጋሚ ዓረፍተ ነገሮችን እናገኛለን። ‘‘እግዚአብሔር እንዲህ ይላል’’ ወይም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመቶ በሚቆጠር ስፍራ ይገኛሉ። ጸሐፊዎቹም ብዙ ጊዜ ቃሉን እግዚአብሔር እንደተነገራቸው ይጠቅሳሉ፥ ወይም ደግሞ ሥልጣን ያላቸው የእግዚአብሔር ተወካዮች ሆነው ይናገራሉ። በሁለቱም ሁኔታዎች ጽሑፎቹ ተአምራዊ መገለጦችና እስትንፋሰ-እግዚአብሔር እንደሆኑ ተብራርቶ ቀርቧል።

የቃይሳት መጻሕፍት ርእሶች። በብዙ ጥቅሶች የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች ‘‘የእግዚአብሔር ቃል፥ ቃሉም፥ ቃሌም፥ የአፉም ቃል፥ የቅዱሱ ቃል፥ የእርሱ ቃል’’ በሚሉ አገላለጦች ተሰይመዋል። እነዚህን የመሳሰሉ አገላለጦች ከአንድ መቶ ጊዜ በላይ በብሉይ ኪዳን ተጠቅሰዋል። አገላለጦቹ ብሉይ ኪዳን በአጠቃላይ እና በከፊል የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የሚያመለክቱ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ጥቅሶቹ እግዚአብሔር ራሱ የተናገራቸው ሲሆኑ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ነቢያት ስለ እግዚአብሔር ሆነው የተናገሯቸው ሆነው እናገኛቸዋለን (መዝ. 107፡11፤ 119፡11፤ ምሳሌ 30፡5)። በሁሉም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለቅዱሳት መጻሕፍት

የተሰጡት እነዚህ አርእስት፥ በእያንዳንዱ መጽሐፍ ላይ መለኮታዊውን የእስትንፋሰ- እግዚአብሔር ማኅተም የሚያኖሩ ናቸው።

የክርስቶስ ምስክርነት። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የመንፈስ ቅዱስ ሥራና እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤቶች እንደሆኑ ግልጥ የሆነው ምስክርነት የወጣው ከራሱ ከክርስቶስ አፍ ነው። በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውስጥ ስላለው የእግዚአብሔር ሥራ ከሚናገሩት ብዙ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች መካከል ሥራው የመንፈስ ቅዱስ መሆኑን የሚናገሩት ከዚህ ቀደም የጠቀስናቸው ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው (2ኛ ሳሙ. 23፡2-3፤ ኢሳ. 59፡21)። ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን ሲጠቅስ ግን፥ የእትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን በግልጥ ተናግሯል። ይህ ገለጣ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ የየትኛው የሥላሴ አካል ተግባር መሆኑን ከመለየቱም ሌላ፥ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤቶች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ በመሆኑ እጅግ ጠቃሚ ነው። ብሉይ ኪዳንን ለመንቀፍና ለማጥላላት መሞከር፥ የክርስቶስን ቃል እንደ መንቀፍና ማጥላላት ይቆጠራል።

ክርስቶስ ከፈሪሳውያን ጋር በተነጋገረ ጊዜ፡- ‘‘ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?’’ ብሎ ጠየቃቸው። ‘‘የዳዊት ልጅ ነው’’ አሉ። እርሱም ‘‘እንኪያስ ዳዊት፥ እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል?’’ ብሎ መለሰላቸው (ማቴ. 22፡42-43)። ክርስቶስ በዳዊት የተጻፈውን መዝሙር 110፡1 ሲጠቅስ፥ ዳዊት ጽሑፉን በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ እንደጻፈውና በዚህም ጽሑፍ የገዛ ልጁን ‘‘ጌታ’’ ብሎ እንደጠራው እንመለከታለን። ይኸው ታሪክ በማርቆስ ወንጌል ተጽፎ እንደምንመለከተው፥ ክርስቶስ ስለ ዳዊት ልጅ ባቀረበው ጥያቄ እንዲህ ብሏል፡- ‘‘ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስከማደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ’’ አለው (ማር. 12፡36)። በዚህ ክፍልም መንፈስ ቅዱስ ይህን መዝሙር በመጻፍ የነበረውን የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ተግባር ክርስቶስ ሲመሰክር፥ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደተናገረው ገልጧል።

የሐዋርያት ምስክርነት። የሐዋርያት ምስክርነት እጅግ በርካታና የክርስቶስን ምስክርነት ያህል ግልጥ ነው። ጴጥሮስ በመዝሙር 41፡9 የተጻፈው ቃል ስለመፈጸሙ ሲናገር፥ ‘‘ወንድሞች ሆይ ኢየሱስን ሊይዙት መሪ ስለሆናቸው ስለ ይሁዳ፥ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተናገረው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ይገባ ነበር’’ ብሏል (ሐዋ. 1፡16)። ሁለተኛውን መዝሙር ሲጠቅስ ደግሞ፥ ‘‘በመንፈስ ቅዱስ በብላቴናህ በአባታችን በዳዊት አፍ እንደተናገረ’’ በማለት ጠቅሷል (ሐዋ. 4፡24-25)። ጳውሎስ በኢሳይያስ 6፡9-10 ያለውን ቃል ሲጠቅስ ደግሞ፥

"መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ ለአባቶቻችን..." በማለት አስፍሮታል (ሐዋ. 28:25)። ተመሳሳይ ጥቅሶችን በዕብራውያን 3:7፤ 10:15-16 እና በሌሎችም የአዲስ ኪዳን ክፍሎች እናገኛለን። ሁሉም ምስክርነቶች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤቶች መሆናቸውንና የተጻፉት ግን በሰዎች መሆኑን ያረጋግጣሉ።

በንግግር ከተሰጡ መገለጦች ጋር ያለው ተመሳሳይነት። በንግግር ስለተሰጡ መገለጦች በ2ኛ ጴጥሮስ 1:20-21 የተጻፈው ቃል የትንቢት ሁሉ ምንጭ ስለሆነው ተአምራዊ የእግዚአብሔር ሥራ ሲናገር፥ "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" በማለት ሁሉም ትንቢቶች የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጤቶች መሆናቸውን በግልጥ ተናግሮታል። ይህ ቃል በንግግር የተሰጡ ትንቢቶችን ብቻ የሚመለከት ነው ልንል አንችልም። ምክንያቱም አንዳንድ ትንቢቶች (ለምሳሌ ትንቢተ ዳንኤል) አስቀድሞ የተሰጡት በቃል ሳይሆን በጽሑፍ ነው። በዚህ ክፍል ከተጻፉት ቃሎች ጋር ሊወዳደር የሚችለው "የተነገሩት" የሚለው ቃል ሲሆን፥ ጸሐፊዎቹ በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው እንደጻፉት በ2ኛ ጴጥሮስ ከተጻፈው ቃል ለመመልከት ይቻላል። በቃል የተሰጡት ትንቢቶች ከመንፈስ ቅዱስ የወጡ ከሆነና፥ በተመሳሳይ መንገድ በጽሑፍ የቀረቡ ትንቢቶችም የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ከሆኑ፥ የብሉይ ኪዳን መልእክቶች በሙሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንችላለን። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መገለጥን በመስጠት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፥ በተጻፈው ቃል እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት ሥራ ውስጥም መኖሩን እንመለከታለን።

ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ-እግዚአብሔር የመሆናቸውን እውነትና፥ ይህንንም ሥራ በወኪልነት የሚያከናውነው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን የሚያስረዱ ግልጥ ማረጋገጫዎች በርካታ ናቸው። ጄምስ. ቢ. ግሪን [James B. Green] የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ እንዲህ ብሏል፦

> "ሕግጋት፥ ነቢያት፥ የኢየሱስ ትምህርቶችና የጳውሎስ መልእክቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆኑ በግልጥ ተነግሯል። መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ስለመሆኑ 3000 ጊዜ ያህል በተለያየ መንገድ ራሱ ለራሱ ምስክርነት ሰጥቷል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ አንድን ነገር ምን ያህል ጊዜ ቢገልጠው ሰዎች ሊያምኑት ይችላሉ?"

4. የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መጠን

የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ስንመረምር፥ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶችን በሙሉ የያዘ እንደሆነ እንገነዘባለን። ታሪኮችን፥ ግጥሞችን፥ ትያትሮችን፥ ስብከቶችን፥ የፍቅር ታሪኮችና የጻሐፊዎቹን ውስጣዊ የአምልኮ አሳቦችን የሚያሳዩ ጽሑፎችን ሁሉ እናገኛለን። እስትንፋሰ-እግዚአብሔር በቅርጻቸውም ሆነ በአጻጻፋቸው፥ እንዲሁም በእውቀቶቹ ምንጮች ወይም በዚያ በሚካተተው እውቀት ላይ ሳያተኩር፥ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶችን ሁሉ የሚነካ ዋና ጉዳይ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ያሏቸው የተለያዩ የአጻጻፍ ዘይቤዎች፥ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር እንዴት በእነዚህ ልዩነቶች ውስጥ እንደሠራ ጥያቄ ሊያስነሡ ይችላሉ።

ተአምራዊ፥ ወይም ሰማያዊ የሆነውን ነገር ለመመዘን የሚደረግ ሙከራ ሁሉ እንደ ውድቀት ተቆጥሮ የሚወገዝ ነው። የሰው ልጅ ይህ ከሰው ልምምድ በላይ ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመመዘን ምንም መለኪያ የለውም። እስትንፋሰ-እግዚአብሔርን ለማብራራት ስንሞክር ከሕይወታችን ጋር ያለውን ዝምድና ማየት እንችላለን። የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ትምህርት ቢያንስ በሰባት ነገሮች ከሕይወታችን ጋር ይዛመዳል።

ያልታወቀው ያለፈ ጊዜ። አንዳንድ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት ለሰዎች ያልታወቀና ሊታወቅም ያልታቀደ ኃላፊ ጊዜ እንደነበር በሥልጣን ይናገራሉ። ለምሳሌ፦ በኦሪት ዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፎች፥ ሙሴ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ በየትኛውም ወግ ሊጠቃለሉ ስለማይችሉና የሰው ልጅ ከመፈጠሩ በፊት ስለተፈጸሙ ነገሮች ይናገራል። በኢሳይያስና በሕዝቅኤል ውስጥ ከሰው የተፈጥሮ ክልልና እውቀት ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች ተጠቅሰው ይገኛሉ። በቅዱሳት መጻሕፍት የተጠቀሱትን መልእክቶች ለማስፈር በቅድሚያ፥ መገለጥ ማለትም መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠው መልእክት ላይ ያለው ድርሻ እና እስትንፋሰ-እግዚአብሔር መልእክቱ ያለ ስሕተት እንዲጻፍ ለማድረግ አስፈላጊ ናቸው። አንዳንዶች ይህ የአፈጣጠር ታሪክ በብዙ ዝርዝር ሁኔታው ከአረማውያን ትምህርቶች ጋር የሚመሳሰል ነው ይላሉ። ስለ ፍጥረታት አፈጣጠር የሚያስረዳ መገለጥ ቅዱሳት መጻሕፍት ከመጻፋቸው በፊት ተሰጥቶ፥ ሰው ይህን መገለጥ ሌላ ነገር እየጨመረበትና እየለወጠ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ካለው መገለጥ ውጭ አድርጐት ሊሆን ይችላል። ስለ ፍጥረታት ታሪክ ሌሎች ጽሑፎች መኖራቸውና እነዚህ ጽሑፎችም ከኦሪት ዘፍጥረት ታሪክ ጋር መመሳሰላቸው፥ የኦሪት ዘፍጥረትን እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት የሚያዛባ ሊሆን አይችልም። ሙሴ ኦሪት ዘፍጥረትን ለመጻፍ ሌሎች መጻሕፍትን

ተጠቅሞ እንደሆነና እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጠው ነገር የለም። ሌሎች መጻሕፍትን ተጠቅሞ ቢሆን፥ የአረማውያን የፍጥረታት ታሪክ አሳብ በጽሑፉ ቢኖርበት፥ ወይም ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ ወጎች በእውነታው ላይ ያከሉት ነገር ቢኖር፥ በማንኛውም ጊዜ እውነቱን ከሐሰት ለመለየት እውነት የሆነው ነገር ሁሉ እንዲመዘገብና ሐሰት የሆነው እንዲቀር የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ አስፈላጊ ነበር። ሙሴ በጽሑፍ የሰፈሩ አሳቦችን ተጠቅሞ ወይም ሲወርድ ሲዋረድ ለመጣ ወግ የሚስማማ አንዳንድ ነገር የወሰደ ሊሆን ቢችልም፥ የጽሑፉ ዋና ምንጭ ግን ያለ ምንም ጥርጥር ሰማያዊ መገለጥ ነው።

ታሪክ። አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች በምድር ከተፈጸሙ ታሪኮች ጋር የሚስማሙ ናቸው። እንደነዚህ ባሉት ክፍሎች ጸሐፊው በብዙዎች ዘንድ ስለታወቁ ታሪካዊ ድርጊቶችና፥ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ምሪት ያልተጻፉ ሊሆኑ ስለሚችሉ ሌሎች ጽሑፎችም ይናገራል። በብዙ ረገድ ጸሐፊው የጻፈው የተለየ መገለጥ የሌለበትና እንደ ማንኛውም ዓይነት ግልጥ ታሪክ ነው። በእንደዚህ ዓይነቱ ታሪክ ምን ያህሉ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ነው? በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት እንደምናየው እስትንፋሰ-እግዚአብሔር በትክክለኛ አገላለጦች እንጂ፥ በመሠረታዊ እውነቶች ምንጭ ላይ አያተኩርም። መንፈስ ቅዱስ የተፈጸሙትን ትክክለኛ ሁኔታዎች ብቻ ከታሪኩ ውስጥ እንዲመርጡና ማከል የሌለባቸውን ነገር እንዲተዉ በማድረግ ጸሐፊዎቹን እንደመራቸው ለመገንዘብ እንችላለን። የዚህ ውጤት አንዳችም ስሕተት የሌለበት፥ የማይዛነፍ፥ እውነተኛ የሆነና በእግዚአብሔር ትኩረት የተሰጣቸውን ታሪኮች ማግኘት ይሆናል።

ሕግ። የብሉይ ኪዳን የተወሰነ ክፍል የግለሰብንም ሆነ የጠቅላላ ሕዝቦችን ሕይወት የሚገዙ ሕጎች የተጻፉበት ነው። እንዲህ ያሉት ሕጎች በተለይ ‘‘ፔንታቱክ’’ ተብለው በሚጠሩት አምስት የሙሴ መጻሕፍት ውስጥ በሦስት ታላላቅ ክፍሎች ቀርበዋል። እነዚህም ትእዛዛት፥ የሕዝቡን ግብረገባዊ ሕይወት የሚመሩ፥ ለሕዝቡ ሃይማኖታዊ ሥርዓት መመሪያን የሚሰጡና በማኅበራዊ ሕይወት ላይ የሚያተኩሩ የፍርድ ሕጎች ናቸው። አንዳንድ ሕጎች እግዚአብሔር ቃል በቃል በሰጣቸው ትእዛዛት ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ፥ ይዘታቸው በእግዚአብሔር መነገራቸውን የሚያረጋግጥ ነው። በሌላ ረገድ ደግሞ ሙሴ እንደ ነቢይ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ፊት በመወከል በጽሑፍ ሊቀበላቸው ፈጽሞ አስቸጋሪ የሆኑትን ትእዛዛት ራሱ ቃል በቃል ለሕዝቡ ሲሰጥ እንመለከታለን። ነገር ግን ሁለቱም ዓይነት ትእዛዛት ልክ እንደ ሌሎቹ የቅዱሳት መጻሕፍት ትእዛዛት ኃይል ያላቸው ናቸው። ሕጉ በፍጹምነት የእርሱን አሳብ በሚገልጥ መንገድ እንዲሆን

በማሰብ በሚጻፍበት ጊዜ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር እስከ መጨረሻው ሠርቷል። ማለትም ሕጉ ከስሕተት ተጠብቆ የእግዚአብሔርን ፍላጐት በሙሉ ያካተተ እንዲሆን ሥልጣን ያለውና ለያዘውም ነገር ሁሉ ትክክለኛ መሠረት ያለው ሆኗል።

ቃል በቃል መመዝገብ። አስቀድሞ እንደተገለጠው፥ የእግዚአብሔር ቃል ከሆነው መጽሐፍ ቅዱስ፥ አንዳንዶቹ ክፍሎች በቀጥታ በእግዚአብሔር የተነገሩ ትእዛዛትና መገለጦች ናቸው። በዚህ ውስጥ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ ምንድር ነው? ብለን ብንጠይቅ፥ መልሱ ትእዛዛቱና መገለጦቹ እግዚአብሔር በሚፈቅደው መንገድ ያለ አንዳች ስሕተት እንዲጻፉ ማድረግ ነው የሚል ይሆናል። እግዚአብሔር በበኩሉ መልእክቱን ተፈጥሮአዊ ወይም ተአምራዊ በሆነ መንገድ ጸሐፊው ተቀብሎ ሊጽፈው በሚችለው ሁኔታ ተናግሯል። በዚህ ዓይነት የጸሐፊው ሥራ ቃል በቃል መመዝገብ በመሆኑ፥ የሚጠቀምበት የአጻጻፍ ዘይቤ የሚጫወተው ሚና አነስተኛ ይመስላል። ይህ ሲሆን ቃል በቃል መጻፍ ከሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች የተሻለ ሥልጣን እንዳለው ተደርጐ መቆጠር የለበትም። በታማኝነት የተመዘገበ የሰዎች ኃጢአትም ሆነ ምናልባት እውነት ላይሆን የሚችል የተደጋገመ ንግግር ቢኖርም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጻፉ፥ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር በሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በነጻነትና በእኩልነት መሠራጨቱ እሙን ነው። እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ጽሑፉ በትክክል እንዲመዘገብና ሊሳሳት የማይችል እንዲሆን እንደ ማኅተም የሚያረጋግጥና፥ አንባቢው ቅዱሳት መጻሕፍትን በሙሉ እምነትና እርግጠኝነት እንዲቀበላቸው የሚረዳ ነው።

የአምልኮ ጽሑፎች። ስለ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ስናስብ ከፈታችን ድቅን የሚልብን ጥያቄ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ መዝሙረ ዳዊት ካሉ የአምልኮ ጽሑፎች ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው? የሚለው ነው። እንደዚህ ስላሉ ጽሑፎች ስናስብ፥ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ፥ ጸሐፊው የሚያስበውንና የሚሰማውን በትክክል እንዲመዘግብ ማድረግ ብቻ ነው ወይስ ከዚህ ላቅ ያለ ሥራ አለው? የሚል ጥያቄ ማንሣት ተገቢ ይሆናል። የሰዎች ንግግር በተመዘገበባቸው ቦታዎች እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተባለውን ነገር እውነትነት ያረጋግጣል ማለት አይደለም። ለምሳሌ፦ በውድቀት ታሪክ ውስጥ ሰይጣን አዳምና ሔዋንን ሲፈትናቸው፥ ‘‘ሞትን አትሞቱም’’ (ዘፍጥ. 3፡4) እንዳላቸው የሚናገረው ቃል ሲጻፍ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ድርሻ ሰይጣን ያለው ነገር በትክክል ከመመዝገቡ ላይ እንጂ ይህ የሰይጣን ቃል እውነት መሆኑን ማረጋገጥ አይደለም። መዝሙሮቹን በተመለከተም የጻፉት ሰዎች እንደ ማንኛውም ሰው ሊሳሳቱ የሚችሉ ኃጢአተኞች ስለሆኑ ልምምዳቸውም ሆነ በጽሑፍ ያሰፈሩት አሳባቸው የግድ ትክክል ነው ለማለት አንችልም።

ታዲያ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ነገሮችን በትክክል እንዲመዘገቡ ከማድረግ ሌላ የሚሠራው የለም?

የዚህን ጥያቄ መልስ ከመዝሙራት ከራሳቸው እናገኛለን። መጻሕፍቱን በምንመረምርበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲጻፉ ሲያደርግ፥ አሳባቸው በትክክል እንዲመዘገብ ብቻ ሳይሆን፥ እርሱን እንዲገልጡ፥ እውነተኛ አምልኮን እንዲያሳዩ፥ ጸሎት ለሚያደምጠው እግዚአብሔር መጸለይ ያለበት መሆኑን እንዲያመለክቱ፥ የመንፈስን ደስታና የኃጢአትን ክብደት እንዲያሳዩና ስለ ወደፊቱ እንዲተነብዩ ጭምር ተደርገው ነው። ዳዊት በልምምዱ ስለተረዳው የእግዚአብሔር ጥበቃና ቸርነት ይናገራል። በምስጋናውም ከግንዛቤው በላይ ስለሆነው፥ ስለ ትልቁ ዳዊት- ስለ ክርስቶስ ያመለክታል። ከፍተኛ ደስታውንም እንዲህ በማለት ይገልጣል፦ ‘‘ስለዚህ ልቤን ደስ አለው፥ ምላሴም ሐሴት አደረገች፤ ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፤ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም’’ (መዝ. 16፡9-10)። ዳዊት ካለው ነገር ውስጥ ብዙው ከራሱ ሕይወት በላይ ነው። ሥጋው በተስፋ ስለምታድር ልቡን ደስ እንዲለው ነፍሱ ለዘላለም በሲኦል እንደማትቀር መናገር ይችላል። ‘‘ነገር ግን ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም’’ ሲል፥ ከራሱ ልምምድ በላይ ስለ ክርስቶስ መናገሩ እንደሆነ ግልጥ ነው። ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ ቀን መልእክቱ፥ ይህን በማረጋገጥ (ሐዋ. 2፡25-31) በክርስቶስና በዳዊት መካከል ያለውን ልዩነት ጠቁሟል።

ስለዚህ በአምልኮ ጽሑፎች ውስጥ፥ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ፥ አሳቦቹ በትክክል እንዲመዘገቡ ከማድረግ በላይ ነው። የዚህን ትክክለኛ አፈጻጸም ለማስረዳት የማይቻል ቢሆንም፥ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር የጸሐፊዎቹ አሳብ በትክክል እንዲመዘገብ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፥ አሳባቸውም በእግዚአብሔር መልካም ቸርነት የተዘጋጀ እንዲሆን አድርጓል። እስትንፋሰ-እግዚአብሔር አስፈላጊ የሆነውን ብቻ የሚመርጥ ስለሆነ የጸሐፊዎቹ ልምምድ በሙሉ አልተመዘገበም። ዋርፊልድ የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ ጉዳዩን እንደሚከተለው ያብራራዋል፦

> ‘‘እስኪ አንድ መዝሙረኛ ጤነኛ ለሆነ ሃይማኖታዊ ልምምድ የሚሆኑትን ጥቅሶች ለመጻፍ እግዚአብሔር እንዴት እንዳዘጋጀው አስቡ፦ ለሃይማኖታዊ ስሜት ትክክለኛ መመዘኛ ባለው አካባቢ ስለመወለዱ፥ ትክክለኛ የሆነ ቤተሰባዊ አቅጣጫ እንዲይዝ ያደረጉ ወላጆች እንደነበሩት፥ ሃይማኖታዊ አመለካከቱ ትክክለኛ አቅጣጫ ይይዝ ዘንድ የማይዛነፍ ምሳሌነትና አስተዳደግ ሊለግሡት የቻሉ ዓይነተኛ ወላጆችን ማግኘቱ፥ እውነተኛና ግልጥ የሆነ ስሜቱን ያለ ችግር መግለጥ ይችል ዘንድ የሚያበቃውን ትክክለኛ ልምምድ

በሕይወት ባለፈባቸው ሁኔታዎች ውስጥ መማሩ፥ ለእነዚህ ነገሮች ሁሉ ትክክለኛ አገላለጥ እንድንፈልግ የሚያስገድዱን ይሆናሉ።››

እግዚአብሔር ልጆቹን ለአንድ ጉዳይ ለማዘጋጀት በሚያደርገው ጥንቃቄ የሚሰጠውን ነገር፥ ከእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ጋር ልናየው እንጂ ልናምታታው አይገባም። የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ጽሑፎችን በሚመለከት በእግዚአብሔር ድምፅ የተገለጠው፥ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር አሠራር ውስጥ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በሰዎች ልብ ውስጥ በሚሠራው ሥራ በሚጻፉ መገለጦች የሚካተት ነው።

ነቢያት ለነበሩበት ዘመን የተናገሩት መልእክት። አብዛኛው የነቢያት መልእክት የሚያተኩረው፥ የዚያ ዘመን ሕዝብ በሚያስፈልገው ጉዳይ ላይ ነበር። የወቅቱ ነቢይ በዘመኑ ለነበሩ ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ፥ የማጽናኛና የማበረታቻ መልእክት ያስተላልፍ ነበር። ሠራዊቱን ይመራል፥ መሪዎችን ይመርጣል። ሕዝቡ የሚያስፈልገውን ጥበብ በተለያየ መገለጥ የሚያመጡ የእግዚአብሔር መሣሪያዎች ነቢያት ነበሩ። እርግጥ ለዚያ ትውልድ ብቻ እንዲጠቅሙ በነቢያት ከተሰጡ መልእክቶች መጽሐፍ ቅዱስ የዘገበው ጥቂቱን ብቻ ነው። አብዛኛዎቹ የነቢያት መልእክቶች በጽሑፍ የተላለፉልን ግን ለታሪክ ጠቃሚነትና በዘመናት ለሚነሡ ትውልዶች ሕያው ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ነው። ለመሆኑ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ይህን ከመሰሉ ጽሑፎች ጋር ያለው ዝምድና ምንድር ነው?

በሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደምናየው፥ በዚህ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነትም የተወሰኑትንና አስፈላጊ የሆኑትን መልእክቶች ብቻ መርጦ ማካተት የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ጸሐፊዎች መልእክቶችን የሚጽፉት ወይም የሚያስተላልፉት እንደ እግዚአብሔር አሳብ ብቻ ነበር። እስትንፋሰ-እግዚአብሔር፥ የተጻፈው ነገር ትክክል መሆኑንና የነቢያት መልእክትም የማይወድቅ መሆኑን ያረጋግጥልናል። ይህ ነገር የእግዚአብሔር ሰዎች ባይሆኑም፥ የነቢይነትን ድምፅ ላሰሙና ይህን ለማድረግ በእግዚአብሔር ለተመሩ ጥቂት ሰዎችም እውነት ነው። በዚህ የአጻጻፍ ስልት የሚታየው የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ፥ ታሪክ ብለን በጠራነው የአጻጻፍ ስልት ላይ ካየነው ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው። ነቢያት የሚያቀርቡትን መልእክት፥ ታሪኩንና የሚቀርብበትን ቋንቋ በመምረጥ፥ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ ሕያውነትና በሁለቱም መልእክቶች ውስጥ ያለውን ተመሳሳይነት እናያለን።

ስለ ወደፊቱ የሚናገሩ ትንቢቶች። የነቢያት መልእክቶች ብዙ ጊዜ ስለ ወደፊቱ ማለት ስለሚመጣው ነገር የመጠቆም ዓላማ አላቸው።

ስለሚመጣው ፍርድም ያስጠነቅቃሉ። ከቅጣት በሚመጣ የመልካም ፍሬ ልምምድ ውስጥ ከመሢሑ ጋር ስለሚመጣው ክብርና ነጻነትም ይናገራሉ። ከጠቅላላው የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል በግምት አንድ አራተኛው ስለ ወደፊቱ ጉዳዮች የሚናገሩ ናቸው። እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ከእንደዚህ ዓይነቱ የነቢያት መልእክት (ትንቢት) ጋር ልዩ የሆነ ግንኙነት አለውን?

አብዛኛዎቹን የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት፥ ጸሐፊዎቹ ይረዷቸው ነበር። በታሪክ ሂደት የተፈጸሙ ድርጊቶችን በሰፊው ይገነዘቡ፥ በመዝሙራቱ ይደሰቱም ነበር። የጻፉት ነገር በአሳባቸው ውስጥ ያለፈ እንደመሆኑ፥ የግንዛቤያቸው ተጽእኖ አለበት። ስለ ወደፊቱ ጉዳይ የሚናገሩ የነቢያት መልእክቶች ግን ከጸሐፊዎቹ መረዳት በላይ የሆኑ ጉዳዮችን ያካትታሉ። ነቢያት ራሳቸው የጻፉት ነገር አንዳንዴ ለእነርሱ ግልጥ እንዳልነበረ ተናግረዋል። ጴጥሮስ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ብሏል፦ ‘‘ለእናንተም ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፤ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር’’ (1ኛ ጴጥ. 1፡10-11)።

የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ ከየትኛውም የአጻጻፍ ዓይነት ይልቅ ስለ ወደፊት በሚናገሩ የነቢያት መልእክቶች ተረጋግጧል። እዚህ ውስጥ የሰዎች ጥበብ ዋጋ የለውም። ጥቃቅን የምንላቸው ነገሮች ሁሉ ትክክል መሆን አለባቸው። እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ከየትኛውም ቦታ ይልቅ በዚህ ስፍራ የሚፈተን ሊሆን፥ የተፈጸሙ ትንቢቶች የሚሰጡት ምስክርነት እንዲጻፍ ምክንያት የሆነውን የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ያረጋግጣሉ። ስለ ወደፊቱ የሚናገሩት የነቢያት መልእክቶች የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ እቅድና ፍቃዱን የሚያሳዩ መገለጦች ናቸው። ራእዮችና በከባድ እንቅልፍ ላይ የሚሰጡ መልእክቶች፥ በወደፊቱ ጉዳይ በሚሰጡ መገለጦች ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። በተለይ በመንፈስ ቅዱስ የሚገለጥ የእግዚአብሔር ኃይል አስፈላጊነት የማያጠያይቅ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶችን በሚመለከት እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ያለውን የተለያየ ሥራ ለይቶ ማየት ቢቻልም፥ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር በሁሉም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንድ ዓይነት ባሕርይ ነበረው። መንፈስ ቅዱስ፥ ሐሰት ቀርቶ የእግዚአብሔር አሳብ ብቻ እንዲጻፍ፥ መገለጦች በትክክለኛና በጥሩ ቋንቋ እንዲሰፍሩ በማድረግ፥ በታሪክ ትክክለኛ ምርጫንና የእውነተኛ ዓላማ ጭብጥን በማመልከት፥ እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ ጋር ያለውን የልብ

ቅርበትና እንዲሁም መገለጥን፥ በትንቢትም ለወቅቱ የሚያስፈልጉ ወይም ስለ ወደፊቱ የሚጠቁሙ ሁኔታዎችን በማሳየት፥ ስለ እምነት ደግሞ ትክክለኛ መመዘኛ የሚሆኑና የማይወድቁ እውነቶችን በማመልከት ይመራል። የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ ለታሰበበት ዓላማና እቅድ የዋለው ከሰው ውጭ በሆነ ኃይል፥ በተፈጥሮ ሕግ ወይም በእግዚአብሔር ጥንቃቄ በሚሰጥ እውቀት ብቻ አይደለም። ነገር ግን በሁሉም ስፍራ የሚገኘው መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ልብና ጉዳይ ውስጥ በመሆን፥ የእግዚአብሔርን እውነት በመግለጥ ብቻ አስደናቂውንና በጽሑፍ ታሪክ የመጀመሪያው የሆነውን ብሉይ ኪዳን እንዲጻፍ አደረገ። እነዚህ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በገጾቻቸው የያዟቸው ነገሮች፥ በማይናወጠውና ዘላለማዊ ጠቢብ በሆነው መንፈስ ቅዱስ መመራታቸውን የሚያመለክት መረጃ ያካተቱ ናቸው።

5. እስትንፋሰ-እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን

እስትንፋሰ-እግዚአብሔር በአዲሰም ሆነ በብሉይ ኪዳን አንድ ነው። ስለ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ያየነውን ጭብጥ፥ ለአዲስ ኪዳን ልንጠቀምበት ፍጹም ተስማሚ የሆነና ተገቢም ነው። እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን፥ በአዲስ ኪዳንም የሰውን ሚና ሳያጓድል ተአምራዊ በሆነ መንገድ ለእያንዳንዱ ቃል የሚሠራና ስሕተት የሌለበት ነው። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንደ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እኩል መለኮታዊ ጅማሬና ፍጹምነት ያላቸው ሲሆኑ፥ በሥልጣንም እኩል ናቸው። እዚህ ላይ በዝርዝር ልናመለክተው ባንችልም፥ እያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤት መሆኑን የሚያመለክቱ የራሱ ማረጋገጫዎች አሉት።

በአዲስ ኪዳን የምናየው የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር አፈጻጸም፥ በብሉይ ኪዳን ካለው ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው። ልክ በብሉይ ኪዳን እንዳየነው፥ በአዲስ ኪዳንም ስላልታወቀው የቀድሞ ኃላፊ ጊዜ በማየት፥ በመዘገባቸው ታሪኮች ትክክለኛነት፥ በግብረገባዊ መመዘኛዎቹ፥ የክርስቶስን ቃል በመጥቀሱ፥ በአንዳንድ ክፍሎች የአምልኮ ወይም የሰዎች ሕይወት በማቅረብ ባሕርዩ፥ በተጻፈበት ጊዜ በነበሩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት ባቀረበው ትምህርትና፥ ስለ ወደፊቱ ጊዜያት በቀረቡት ትንቢቶች ትክክለኛነት ሁሉ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔርን ሥራ ለማየት እንችላለን። ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን፥ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሰዎችን እንደ ድልድይ (መሸጋገሪያ) ተጠቅሞ፥ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ብቻ በሚገልጥ መንገድ የአዲስ ኪዳን መልእክት እንዲቀርብ አድርጓል። በሥልጣንም ሆነ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የአዲስ ኪዳንና የብሉይ ኪዳን

ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ናቸው። ከዚህ በታች ስለ አዲስ ኪዳን እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት በብሉይ ኪዳን ያልታዩ አንዳንድ ልዩ የሆኑ ነጥቦችን እንመለከታለን።

የአዲስ ኪዳን እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት በኢየሱስ ክርስቶስ ተረጋግጧል። የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ትክክለኛ ሥልጣን ያላቸውና ተአማኒ መሆናቸውን ቀደም ሲል ክርስቶስ ከተናገራቸው አሳቦች ተመልክተናል። ለየት ባለ አኳኋን ቢሆንም፥ ይህ ሁኔታ በአዲስ ኪዳን ተአማኒነት ላይም እንደሚሠራ እናያለን። ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ትቶ ከመሄዱ በፊት፥ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራቸውንና አዳዲስ እውነቶች የሚገልጥላቸውን መንፈስ ቅዱስ እንደሚልክላቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር (ዮሐ. 16፡12-15)። ስኮፊልድ የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ ይህን እውነት እንዲህ ሲል በአጭሩ ገልጦታል፦ "አዲስ ኪዳን በቅድሚያ በክርስቶስ ተአማኒነት እንዲያገኝ በመደረጉ 1ኛ. ክርስቶስ በግልጥ የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም በማለት ያልገለጠላቸው ነገር መኖሩን በማመልከቱ (ቁ. 12)፥ 2ኛ. የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል (ቁ. 13) በማለት መገለጥ፥ መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ የተሟላ እንደሚሆንና ይህ እንዲሆን ግን ተጨማሪ መልእክቶችን ገና መስጠት እንዳለበት በማሳየቱ፥ 3ኛ. ይህን መገለጥ እንዲቀበሉና ምስክሮች እንዲሆኑ አንዳንድ ሰዎችን በመምረጡ (ማቴ. 28፡19፤ ዮሐ. 15፡27፤ 16፡13፤ ሐዋ. 1፡8፤ 9፡15-17)፥ 4ኛ. እነዚህ ሰዎች ቃሉን በሚናገሩበት ጊዜ መልእክታቸው የሱን ቃል ያህል ሥልጣን ይኖረው ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን በመስጠቱ (ማቴ. 10፡14-15፤ ሉቃስ 10፡16፤ ዮሐ. 13፡20፤ 17፡20) ተረጋግጧል። (ለምሳሌ ያህል 1ኛ ቆሮ. 14፡37፥ ስለ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ደግሞ ዘጸ. 4፡15፤ ራእይ 22፡19ን ይመልከቱ)።"" ስለዚህ ሐዋርያት የተናገሩትም ሆነ የጻፉት፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ሥልጣንና እውነት ሲሆን፥ የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ-እግዚአብሔርና በጰንጠቆስጤ ቀን ወደ ዓለም የተላከው መንፈስ ቅዱስ ውጤት መሆናቸውን የሚያሳይ ብቃት እናይባቸዋለን። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በዓለም ላይ ለዘላለም ነዋሪ በሆነው መንፈስ ቅዱስ ሥራ ምክንያት የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤት እንደሆኑ ሁሉ፥ የመንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን መገኘትም የአዲስ ኪዳን ጽሑፎችን የእስትንፋሰ- እግዚአብሔር ውጤት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ሥራ መሆናቸውን ሐዋርያት ተናግረዋል። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን አጻጻፍ ስናጠና ጸሐፊዎቹ ራሳቸው ሥራቸው እስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሆኑን

የሚያውቁና የእግዚአብሔርም ሥልጣን በእነርሱ መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን፥ በሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ መኖሩን በግልጥ መናገራቸውን እንመለከታለን። ትምህርታቸው የእግዚአብሔር ሥልጣን እንዳለው ስለመናገራቸው በርከት ያሉ ጥቅሶችን ማመልከት እንችላለን። ለምሳሌ ዋርፊልድ የተባለ ጸሐፊ የሚከተሉትን ጥቅሶች ለዚህ እውነት በማስረጃነት አቅርቧል፦ 1ኛ ቆሮ. 2፡13፤ 14፡37፤ ገላ. 1፡7-8፤ 1ኛ ተሰ. 4፡2፥ 15፤ 2ኛ ተሰ. 3፡6፥ 12፥ 14። የምስክርነታቸው አስደሳች ማጠቃለያ፥ አንዱ የሌላውን ጽሑፍ እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት ማወጁ ነው። ዋርፊልድ 1ኛ ጢሞ. 5፡18 ከዘዳግም፦ "መጽሐፍ እንደሚል የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር"፥ ከሉቃስ፦ "ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል" የሚሉትን ቃላት በመጥቀስ ሁለቱም ክፍሎች የቅዱስ መጽሐፍ አካል መሆናቸውን እንደሚያረጋግጥ ተነግሯል" ብሏል። ጴጥሮስ፥ ጳውሎስ የጻፈውን ሁሉ ለመረዳት ባይችልም እንኳ፥ የጳውሎስ መልእክቶች በሙሉ የቅዱሳት መጻሕፍት አካል መሆናቸውን መስክሯል (2ኛ ጴጥ. 3፡16)። በተጨማሪም የጳውሎስን መልእክት የሚያጣምሙ ሁሉ፥ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችንም ማጣመማቸው እንደሆነ ተናግሯል።

ዋርፊልድ ይህን አሳብ ሲያጠቃልል፦ "የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የቅዱሳት መጻሕፍትን እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት መናገራቸው፥ ያለምንም ግፊት በአጠቃላይ ለቅዱሳት መጻሕፍት የሚሠራ ነው፤ ይህም ማለት እነርሱ ራሳቸው ከጠቅላላው ጋር እንዲቀላቀሉ ላደረጓቸው አዳዲስ መጻሕፍትና ከእምነት አባቶች መጻሕፍት መካከል እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ቆጥረው ለተቀበሉአቸው ሁሉ ነው" ብሏል።

የብሉይ ኪዳን ክፍሎች የአጠቃቀሰ ሁኔታ ለእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ማረጋገጫ ነው። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት መቀበላቸው የብሉይ ኪዳንን ጥቅሶች በመጥቀሳቸውና ሲጠቅሱም በሚጠቀሙበት ዘዴ የተረጋገጠ ነው። ይህን እውነት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት በምናረጋግጥበት ጊዜ ተመልክተነዋል። በሌላ መልኩ ስናየው ደግሞ፥ ይህ መንገድ ወይም ዘዴ፥ የአዲስ ኪዳንን እስትንፋሰ- እግዚአብሔርነት ያረጋግጣል። በአዲስ ኪዳን የተመለከቱ ብዙ ጥቅሶች የተወሰዱት "ሰፕቱዋጀንት"* [Septuagint] ተብሎ ከሚታወቀውና የግሪክ ቋንቋ ትርጉም ከሆነ ብሉይ ኪዳን ነበር። ሰፕቱዋጀንት የትርጉም ሥራ በመሆኑና

* "ሰፕቱዋጀንት" ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2ኛው ምዕተ ዓመት ገደማ የተተረጎመ የግሪክ ብሉይ ኪዳን ነው። ይህ መጽሐፍ በአማርኛ "የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም" በመባል ይታወቃል።

እንደ መገኛው ቋንቋ ማለትም እንደ ዕብራይስጥ ፍጹም ባለመሆኑ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር በዕብራይስጥ የተጻፈውን ያህል በግሪክኛው ትክክል አይደለም ብለው አንዳንድ ሰዎች ያስባሉ። ይህን ለማለት የሚደፍሩት፥ ጸሐፊዎቹ ከብሉይ ኪዳን የተጠቀሱ አንዳንድ ጥቅሶች በአዲስ ኪዳን ለየት ያለ ትርጉም ሊሰጥ በሚችል አኳኋን በራሳቸው አገላለጥ በመጻፋቸው ነው። ይህም ቢሆን ዋናው ጉዳይ፥ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ከብሉይ ኪዳን ሲጠቅሱ የመራቸው መንፈስ ቅዱስ መሆኑ ነው።

ጋውሰን [Gaussen] የተባለው ጸሐፊ፥ ሆርን [Horne] የተባለው ሰው በጥናቱ የደረሰበትን ነገር ሲጠቅስ እንዲህ ብሏል፦

> ‹‹የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ከብሉይ ኪዳን ከጠቀሷቸው ጥቅሶች መካከል ሰማንያ ስምንቱ በእስክንድርያ [Alexandria] ከተተረጐመው ሰፕቱዋጀንት ከተባለውና በግሪክ ቋንቋ ከተጻፈው መጽሐፍ ጋር ፍጹም የሚስማሙ ናቸው። ስድሳ አራቱ ከዚህ ትርጉም የተወሰዱ ሆነው የቃላትን አጠቃቀም በሚመለከት ጥቂት የአገላለጥ ልዩነት አላቸው። ሠላሳ ሰባቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው፥ ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ቃል ያልተጠቀሙ ናቸው። አሥራ ስድስቱ ከዚህ ትርጉም ይልቅ፥ በቀጥታ ከዕብራይስጡ ጋር ይስማማሉ። በመጨረሻም ሀያዎቹ ከዕብራይስጡም ሆነ ከሰፕቱዋጀንት ትርጉም የተለዩ፥ ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን በራሳቸው አገላለጥ የጠቀሱበትን ምክንያት ለመረዳት እንዲመች አድርገው ያቀረቧቸው ናቸው።››

ይህ ነገር ለእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ትምህርት እንቅፋት ከመሆን ይልቅ፥ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን በመመርመር ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ትክክለኛነትና ሥልጣን ከምናገኛቸው አስደናቂ ምሳሌዎች አንዱ በመሆን፥ መንፈስ ቅዱስ የሁለቱም ኪዳኖች ጀማሪ መሆኑን ያረጋግጣል።

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ያገኙት ተቀባይነት። በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት ውስጥ ያለውን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሚመለከት አንድ በጣም አስፈላጊ ነገር ሳይጠቀስ መታለፍ የለበትም። የቀድሞይቱን ቤተ ክርስቲያን ስንመለከት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተቀባይነት ያገኙት ወዲያውኑ ነው። የአዲስ ኪዳን ካኖን* [canon] ስለተዘጋጀበት ጊዜ ብዙ የተለያዩ አሳቦች የተሰነዘሩ

* ‹‹ካኖን›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው፥ የጥንት ቤተ ክርስቲያናት የእምነታቸው መመሪያና መተዳደሪያ እንዲሆኗቸው የተቀበሏቸውን የመጻሕፍት ስብስብ ነው። ቃሉ ከግሪክኛ የተገኘ ሲሆን፥ ትርጉሙም ‹‹የሚለካ›› ወይም ‹‹መለኪያ›› ማለት ሲሆን ይችላል። በሃይማኖት አካባቢዎች ‹‹ካኖን›› በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ተጽፈዋል የሚባሉትንና በዚህም ምክንያት በመንፈሳዊነት ረገድ በጣም ዋጋ ያላቸውን መጻሕፍት ያመለክታል።
(የግርጌ ማስታወሻው በተከታዩ ገጽ ይቀጥላል።)

ቢሆንም፥ የቅዱሳት መጻሕፍት ዘገባ ራሱ እንደሚመሰክረው ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተቀባይነት ያገኙት ወዲያውኑ ነው።

ዋርፊልድ የተባለው ጸሐፊ አሳቡን ሲያጠቃልል፡ ‹‹የአዲስ ኪዳን ካኖን ፍጻሜ ያገኘው፥ ሐዋርያት በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ተጽፏል ተብሎ የሚታመንበትን የመጨረሻ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ለቤተ ክርስቲያናት በሰጡ፥ ማለት የዮሐንስ ራእይ በ98 ዓ.ም. ገደማ በተጠናቀቀ ጊዜ ነበር።›› ቀደምት ቤተ ክርስቲያናት በሐዋርያት የተጻፉትን ቅዱሳት መጻሕፍት ለሕይወታቸው መመሪያ እንዲሆኑ አድርገው፥ ልክ ዛሬም በኛ ዘመን አብያተ ክርስቲያናት እንደሚጠቀሙባቸው ተቀብለዋቸው ነበር። በክርስትና ዓለም፥ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተቀባይነትን እስኪያገኙ ብዙ ዓመታትን ቢወስድም፥ ይህ የሆነው ግን መጻሕፍቱን ለመቀበል ካለመፈለግና በጥርጥር በመሞላት የተነሣ አልነበረም። ያ የሆነው የመገናኛ ርቀትና የቋንቋ ልዩነቶች ከፈጠሩት ችግር የተነሣ ነበር።

ስለዚህ የአዲስ ኪዳን የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ከብሉይ ኪዳን ጋር አንድ ነው። የሰዎች የማሳመኛ ክርክር የእስትንፋሰ-እግዚአብሔርን አሠራር ሊለውጠው አይችልም። የብሉይ ኪዳን የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሠረታዊ ትምህርት በሙሉ የአዲስ ኪዳንም የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ነው።

ለዚህም ነው ከሌሎች በርካታ ክርስቲያናዊ ጽሑፎች የተለዩት። የካኖን ሂደት የተጀመረው በ95 ዓ.ም. ገደማ ከመጨረሻው ደቀ መዝሙር (ከዮሐንስ) ሞት በኋላ ሲሆን፥ ለብዙ ዓመታት ቀጥሏል።

የአዲስ ኪዳን ካኖን ውሳኔ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የተደረገ ሳይሆን፥ የክርስቲያኖች የጋራ ስምምነት ውጤት ነው። በጣም የቆየው የካኖን ዝርዝር የእስክንድርያ ጳጳስ የሆነው አትናቴዎስ በ387 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ ላይ ይገኛል። በደብዳቤው፥ በአሁኑ አዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን 27 መጻሕፍት ዘርዝሯል። የካርታጎው [Carthage] ጉባኤ በ397 ዓ.ም. በጉዳዩ ላይ ሳይነጋገር የአትናቴዎስን ዝርዝር አጽድቋል።

በአሁኑ ጊዜ ‹‹ቅዱሳት መጻሕፍት›› ብለን የምንጠራው ካኖን የተጀመረው በአይሁዳውያን ሲሆን፥ ይህም አሁን ‹‹ብሉይ ኪዳን›› ብለን የምንጠራውን 39 መጻሕፍት ያቀፈ ነው። ዛሬ የካቶሊክ ካኖን 80 መጻሕፍትን (በ1545 በትሬንት ጉባኤ የተጨመሩትን 14 መጻሕፍት ጨምሮ)፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካኖን 81 መጻሕፍትን፥ የፕሮቴስታንትና የግሪክ ኦርቶዶክስ ካኖን 66 መጻሕፍትን ያጠቃልላሉ።

8

በብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለሰው ልጅ

1. ለፍጥረታት ሁሉ የነበረው አገልግሎት

801 መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ያከናውን የነበረውን ተግባር ለመረዳት፥ አገልግሎቱ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ለፍጥረታት ሁሉ የሚዳረስ እንደነበረ ማሰብ እጅግ መሠረታዊ ነገር ነው። እርግጥ ለአንዳንዶች የመፍጠርና አስፈላጊውን ነገር በማድረግ የመንከባከብ አጠቃላይ አገልግሎቱ ብቻ የደረሳቸው ቢሆንም፥ መንፈስ ቅዱስ በኃጢአት ለወደቀው የሰው ልጅ ያከናወነው ታላቅ ሥራ ጐልቶ የሚታይ ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ የጻፉ ሰዎች ስለ ጉዳዩ የሚጠቅሱት አልፎ አልፎ ቢሆንም፥ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ የሠራው ሥራ በባሕርይ የተለየ ሆኖ የአዲስ ኪዳኑን ያህል አስፈላጊ ነበር።

ካይፐር የተባለው ጸሐፊ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አጠቃላይ ባሕርያት በሁለት አሳቦች ገልጦታል፦

> ‘‘የመጀመሪያው፥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በተመረጡት ላይ ብቻ የተወሰነና በእነርሱ ሕይወት በሚፈጸም ዳግም ልደት የሚጀምር አይደለም። ነገር ግን አገልግሎቱ ሕይወት ያላቸውንም ሆነ የሌላቸውን ፍጥረታት የሚነካ ሲሆን፥ በተመረጡትም ላይ አፈጻጸሙን የጀመረው ከፍጥረታቸው መጀመሪያ ነው። ሁለተኛው ደግሞ፤ መንፈስ ቅዱስ በፍጥረታት ውስጥ ያለው ዋና ሥራ በማንነቱ፥ በችሎታውና በከፍተኛ ተሰጥኦው ፍጥረታትን በሕይወት ማቆየትና ማልማት ሲሆን፥ ይህም እርሱ የሚሰጠውን የዘላለም ሕይወት፥ ማለትም ደኅንነትን መሠረት በማድረግ ነው።’’

ካይፐር እንደገለጠው የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አጠቃላይ ባሕርያት የሚገልጡ አሳቦች በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን በብዛት ይገኛሉ። እስካሁን ድረስ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር፥ መገለጥን በመስጠትና በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውስጥ ስላለው ሥራ ተመልክተናል። እነዚህ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በአገልግሎቱ ‘‘ፍጥረታትን ሁሉ ያዳርሳል’’ የሚለውን አጠቃላይ

አሳብ የሚያረጋግጡ ናቸው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ጨምረን የምንመለከታቸው ነገሮች፥ ከብሉይ ኪዳን ታሪኮች ተለይቶ የማይታየው መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን የሰው ልጅ ሕይወት በአገልግሎቱ እንደሚነካ የሚያስገነዝቡ ብዙ ግልጥ ምሳሌዎችን እናገኝባቸዋለን።

2. የኃያሉ መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር

ብሉይ ኪዳን ካለንበት ዘመን ጋር ሲነጻጸር። ባለንበት የጸጋ ስፍረ-ዘመን መንፈስ ቅዱስ አማኞች ዳግም ከተወለዱበት ቅጽበት ጀምሮ በሕይወታቸው ያድራል። መንፈስ ቅዱስ የዳነውን ሰው ሕይወት የራሱ ማደሪያ ቤተ መቅደስ ማድረጉ ለእግዚአብሔር ጸጋ አንዱ ምስክር ነው። እስከ ጳንጠቆስጤ ዕለት ድረስ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንዲህ አማኞችን ሁሉ የሚያጠቃልል የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት አልነበረም። በብሉይ ኪዳን ዘመን፥ አማኞች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች ይሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔር እቅድ ባይሆንም፥ በሉዓላዊ ፈቃዱና በራሱ ዓላማ የተወሰኑ ሰዎችን በመምረጥ ማደሪያው ያደርጋቸው ነበር።

ስለ ማደሪያነት የሚናገሩ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች። ስለዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚናገረው የመጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚገኘው በዘፍጥረት 41፡38 ፈርዖን ስለ ዮሴፍ በጠየቀው ጥያቄ ላይ ነው። ‘‘በውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን እንደዚህ ያለ ሰው እናገኛለን?’’ ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ባከናወነው ተግባርና በኋላም በብሉይ ኪዳን በግልጥ በቀረበው አሳብ መሠረት ስንመለከተው፥ ፈርዖን ፈቅዶና አስቦ ሳይሆን በአጋጣሚ ለዚህ ታላቅ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የመጀመሪያ ምስክርነቱን የሰጠ ለመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትም መስክረዋል።

ስለዚህ ጉዳይ አፈጻጸም የሚናገሩ በርካታ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ይገኛሉ። ለካህናት የሚሆነውን ልብስ ይሠሩ የነበሩት ሰዎች ‘‘የጥበብ መንፈስ የሞላባቸው’’ (ዘጸ. 28፡3) እንደሆኑ ተነግሯል። የማደሪያው ድንኳን በሚሠራበት ጊዜ ቀያሾች የነበሩት ኤልያብና ባስልኤል የተባሉት ሙያተኞች ‘‘በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብ በማስተዋልም በእውቀትም የእግዚአብሔር መንፈስ ሞላውበት’’ ተብሎ ተጽፎላቸዋል (ዘጸ. 31፡3ን ከ35፡30-35 ጋር ያወዳድሩ)። ሙሴን እንዲረዱ የተመረጡት ሰባ ሽማግሌዎች መንፈስ ቅዱስ እንዳደረባቸው ተነግሯል (ዘኍል. 11፡17፥ 25)። የነዌ ልጅ ኢያሱም ‘‘መንፈስ ያለበት ሰው’’ (ዘኍል. 27፡18) ተብሎለታል። በዘመነ መሳፍንትም እስራኤልን ነጻ ለማውጣት የተነሡት መሳፍንት በመንፈስ የተሞሉ እንደነበሩ ተነግሮላቸዋል፦ ጎቶንያል (መሳ. 3፡10)፥ ጌዴዎን (መሳ. 6፡34)፥ ዮፍታሔ (መሳ.

11:29)፤ እና ሳምሶን (መሳ. 13:25፤ 14:6፥ 19፤ 15:14)። ኤ. ቢ. ሲምፕሶን [A. B. Simpson] የተባለ ጸሐፊ በዚህ ዝርዝር ላይ ዲቦራን በመጨመር ይህች ሴት መሪ መንፈስ ቅዱስ እንዳደረባት ገልጿል (መሳ. 4:4ቀ.)። መንፈስ ቅዱስ በሳኦል እና በዳዊት ሕይወትም አድሮ ነበር (1ኛ ሳሙ. 10:9-10፤ 16:13)። ነቢዩ ዳንኤልም መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ነበር (ዳን. 4:8፤ 5:11-14፤ 6:3)። ምንም እንኳን ሁልጊዜ ባይሆን፥ ነቢያት በሙሉ መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸው እንደነበር ምንም ጥርጥር የለንም። ከእነዚህ ካየናቸው የተለያዩ ክፍሎች በመነሣት፥ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን በተለያዩ ቅዱሳን ላይ ያድር እንደነበር ለመናገር እንችላለን።

በብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የማደር ልዩ ባሕርያት። መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን፥ በሰዎች ውስጥ የሚደሩ አገልግሎት በጸጋ ዘመን ከሆነው ተመሳሳይ አገልግሎት ጋር ሲነጻጸር በባሕርይ ጨርሶ የተለያዩ ናቸው። በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ለማደር ሲመጣ፥ ከሚያድርበት ሰው መንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ ጋር ጨርሶ ግንኙነት አልነበረውም። በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት እንዲያድር ዳግም መወለድ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ የተጠቀሰበት አንዳችም ቦታ የለም። እርግጥ ለሳኦል እግዚአብሔር አዲስ ልብን ለውጦለታል (1ኛ ሳሙ. 10:9)። ነገር ግን ይህ ልምምድ በሌሎች ቦታዎች የታየና የተለመደ አይደለም።

በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ከታወቀው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት የብሉይ ኪዳኑ የሚለይበት ሁለተኛ መንገድ፥ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት በሉዓላዊነቱ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ሲሆን፥ በተለይ የተያያዘው ከአንድ የተለየ የአገልግሎት ጥሪ ጋር መሆኑ ነው። ስለዚህም ለዚህ ልዩ ተግባር ኃይልንና ጉልበትን ይሰጣል። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት ሁሉም በይገባኛልነት ጠይቆ የሚያገኘው መብት አይደለም። ጥቂቶች ብቻ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች የነበሩ ሲሆን፥ እነዚህም ሰዎች በአንድ በተለየ ስጦታቸው የታወቁ ነበሩ። ሰዎቹ ብዙ ጊዜ መሪዎች፥ ነቢያት፥ ወይም በሌላ ጉዳይ የታወቁ ነበሩ።

ሦስተኛውና ትልቁ ልዩነት ደግሞ፥ በብሉይ ኪዳን የነበረው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት ብዙ ጊዜ ለተወሰነ ወቅት መሆኑ ነበር። የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነታችንን እናጣ ይሆናል በማለት ሠግተው አያውቁም። በእርግጥ አገልግሎቱ በኃጢአት ምክንያት ሊገታ ይችላል። በብሉይ ኪዳን ግን ቅዱሳን የመንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ማደር ልዩ መብት እንደሆነና ልክ እንደተሰጣቸው ሁሉ በማንኛውም ጊዜ ሊወሰድ እንደሚችል ያውቁ ነበር። በዚህ ዓይነት ነው መንፈስ ቅዱስ

ከሳኦል እንደተወሰደ የተነገረው (1ኛ ሳሙ. 16፡14)። ዳዊትም ኃጢአት ካደረገ በኋላ እግዚአብሔርን "ከፊትህ አትጣለኝ፥ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ" ሲል በትሕትና የለመነው ስለዚህ ነው (መዝ. 51፡11)። ማንኛውም ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ ስለማይወሰድ፥ የዳዊትን ዓይነት ጸሎት ይጸልይ ዘንድ ጨርሶ አይገባም። በብሉይ ኪዳን ግን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነትን የማጣት ከፍተኛ አደጋ ነበር።

በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለውን የአፈጻጸም ልዩነት ክርስቶስ በወንጌላት ውስጥ ባስተማረው ትምህርት ግልጥ አድርጎታል። ክርስቶስ፥ "በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል" (ዮሐ. 7፡38) ሲል፥ ከጰንጠቆስጤ ዕለት ጀምሮ በሙላት ስለተገለጠው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት መናገሩ ነበር። ዮሐንስ ይህን ጉዳይ ሲያብራራ፥ "ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደምና ነበርና" (ዮሐ. 7፡39) በማለት ግልጥ አድርጐታል። በዮሐንስ 14፡17 በብሉይ ኪዳን እስከ ጴንጤቆስጤ ቀን ድረስ የነበረውን አሠራርና በአሁኑ ጊዜ ያለውን አሠራር በማነጻጸር ቀርቧል። ክርስቶስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር "እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፥ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ" (ዮሐ. 14፡17) በማለት መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የመኖሩ ነገር ገና ወደፊት የሚፈጸም ጉዳይ እንደነበር በጊዜው አሳውቋል። በዮሐንስ 16፡13 ክርስቶስ ገና ሊመጣ ያለ መሆኑን ለማሳየት "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ" በማለት ስለ መንፈስ ቅዱስ ተናግሯል። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የማደሩ ነገር በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚሆን፥ አልፎ አልፎ እንጂ ሁልጊዜ የማይፈጸም፥ ደግሞም ከአንድ የተለየ ተልእኮ ጋር የተያያዘና ያንን ተልእኮ ለመፈጸም የሚያስችል እንደሆነ እናያለን።

3. የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ሥራ

ከመንፈስ ቅዱስ ማንነት በመነሣት እርሱ በቅዱሳን ሕይወት ውስጥ ብቻ ሳይሆን፥ ባልዳነ ሰው ሕይወት ውስጥ ጭምር ኃጢአትን በመከልከል አገልግሎት እንደተጠመደ መገመት አስቸጋሪ አይደለም። ኃጢአትን በመከልከል አገልግሎቱ በቀጥታ የተጠቀሱ ጥቅሶችን የምናገኘው በጥቂቱ ቢሆንም፥ ስለተለያየ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት

በምናጠናበት ጊዜ አብዛኛዎቹ አገልግሎቶቹ የሚያዘነብሉት ኃጢአትን ወደ መከልከል እንደሆነ እንመለከታለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማሰረጃነት። እግዚአብሔር ከጥፋት ውኃ በፊት የነበረውን ሥልጣኔ ሲቃወም "መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም" ብሏል (ዘፍጥ. 6፡3)። እግዚአብሔር መንፈሴ በሰው ላይ መኖሩ ይቋረጣል ብሎ ሲናገር፥ ከጥፋት ውኃ በፊት መንፈሱ በሰው ላይ የመኖሩ አገልግሎት እንደነበር በቂ መረጃ ነው። በዚህ አገልግሎቱ መንፈስ ቅዱስ የሰይጣን ኃይልና የሰው ልብ ክፋት (ኃጢአት) እንዳይገለጥ ከልክሎ ወይም አቅቦ ነበር።

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትም መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ከኃጢአት የመከልከሉ (የመጠበቁ) ተግባር በጸጋ ስፍረ-ዘመን ሁሉ እንደቀጠለ ያሳዩናል። እንደ 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡7 አሳብ መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን ይከለክላል። "የዓመፅ ምስጢር አሁን ይሠራልና ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ።"

ኃጢአትን ከመከልከል (ከማቀብ) ጋር የተያያዙ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች። ኃጢአትን በመከልከል የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በሚመለከት በግልጥ የሚናገሩ ጥቅሶች ጥቂቶች ቢሆኑም፥ ሌሎች አገልግሎቶቹን በምናጠናበት ጊዜ፥ ኃጢአትን ከመከልከል ጋር በቅጥታ የተያያዙ በርካታ ተግባራት እንዳሉት እንመለከታለን። እግዚአብሔር ፈቃዱን ለማሳወቅና ስለ ፍርዱም ለማስጠንቀቅ በቃል እንዲተላለፍ የሰጠውን መገለጥ ስንመለከት፥ ኃጢአት ወደ መከልከል አገልግሎት ያዘነበለ ነው። በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተጻፈውን ቃል ስንመለከት ተመሳሳይ ነገር እናገኛለን። በዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ሦስተኛው የሥላሴ አካል መንፈስ ቅዱስ፥ (መዝ. 51፡ 11፤ ኢሳ. 63፡10-11) እንዲሁም መልካም መንፈስ (ነህ. 9፡20፤ መዝ. 143፡10) ተብሎ መጠራቱ ተጨማሪ መረጃ ነው። እነዚህ መጠሪያዎች ስለ ማንነቱ ብቻ ሳይሆን፥ ስለ ሥራውም ጭምር ስለሚናገሩ ከኢሳይያስ በጠቀስነው ጥቅስ የምናገኘው በተለይ በመንፈስ ቅዱስ ላይ በማመፃቸው ስለመጣባቸው ፍርድ ነው። ይህ ዓመፅ ማንነቱን ያለመቀበል ብቻ ሳይሆን፥ ኃጢአትን ለመከልከል አብሯቸው የመኖሩን አሳብ አለመቀበላቸው ጭምር ነው። መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ከሰዎች ግብረገባዊ አኗኗርና ጠባይ ጋር በጣም አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት እንደነበረው ከእነዚህ በርካታ ነገሮች መናገር ይቻላል። በአጠቃላይ በዘመናት ያለውን ሁኔታ የተመለከትን እንደሆን ኃጢአትን የመከልከል (የማቀብ) አገልግሎቱን እንገነዘባለን። ይህም መንፈስ ቅዱስ ወደፊት በሺህ ዓመቱ መንግሥት ወቅት፥ በከፍተኛ ሁኔታ ኃጢአትን የመከልከልና የተቀደሱ

ባሕርያትን የማጠናከር ታላቅ ሥራውን የሚያመለክት ነው (ኢሳ. 32፡15ቀ.፤ 44፡3-5፤ ሕዝ. 36፡26ቀ.፤ ዘካ. 12፡10)።

4. አብርሆት* [Illumination] እና የአገልግሎት ብቃት

በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ የታወቀው፥ በተለያዩ አገልግሎቶች ውስጥ ብቃትን "በአብርሆት" እና ጥበብን በመስጠት ነው።

መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ የተጠቀሰው አብርሆትና ጥበብ መስጠትን ጨምሮ ለተለያዩ አገልግሎቶች ብቃት በመስጠት ተግባሩ ነው። እጅግ ሰፊና የተለያዩ አገልግሎቶቹን ከዚህ አንጻር ልንመለከት እንችላለን። ይህ ለአገልግሎት የማብቃት ተግባር በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ካለው የተትረፈረፈ ጸጋ ጋር በተነጻጻሪነት የሚቀርብ ቢሆንም፥ ለብሉይ ኪዳን ዘመን ምዕና እግዚአብሔር ሕዝቡ ከሆነው እስራኤል ጋር ለነበረው የቃል ኪዳን ጎብረት ፍጹም ተስማሚ ነው።

የጥበብ ሰጦታ። በመጽሐፍ ቅዱስ የምንመለከተውና የመጀመሪያው የመንፈስ ቅዱስ ተግባር፥ ለአመራርና ለአስተዳደር የሚሆን ጥበብን መስጠት ነው። ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑ በርካታ መግለጫዎች በመላው ብሉይ ኪዳን የምናገኝ ሲሆን፥ ይህም ከሰው ልጅ ጥበብና ማስተዋል በላይ የሆነ መገለጥ የነበረውንና ፈርዖን እንኳ የመሰከረለትን ዮሴፍን በመመልከት መጀመር እንችላለን (ዘፍጥ. 41፡38-40)። ኢያሱ የተሰጠውን አገልግሎት በብቃት ይወጣ ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ በላዩ ላይ ነበር (ዘኍል. 27፡18)። በዘመነ መሳፍንት ደግሞ ጎቶንያል (መሳ. 3፡10)፥ ጌዴዎን (መሳ. 6፡34)፥ ዮፍታሔ (መሳ. 11፡29) የተሰጣቸውን ተግባር ለመፈጸም ያስቻላቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦል (1ኛ ሳሙ. 10፡10) እና በዳዊት (1ኛ ሳሙ. 16፡13)፥ ላይ በኃይል መውረዱ፥ በእስራኤል ላይ በንጉሥነት የሚያገለግሉበትን ጊዜ አሻግሮ በማየት፥ ለዚያ ሥራቸው ብቃትን ለመስጠት ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእነርሱ ላይ የመውረድ ዓላማ ብቃትን መስጠት ነበር። ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ ለሚያስገዙ ሁሉ የሚሰጥ ብቃት ከመሆን ይልቅ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ እንደፈቀደ የሚያደርገውና፥ በአዲስ ኪዳን ዘመን መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንደሚያከፋፍለው ዓይነት የሚፈጸም ነበር።

---

* "አብርሆት" [Illumination] የሚለው ቃል ትርጉም የመንፈስ ቅዱስ በጽሑፍ የቀረበው ቃል ያዘለውን እውነት ለአንባቢው በመግለጥ ረገድ የሚያከናውነው ተግባር ነው።

የልዩ ችሎታ ስጦታ። ብቃትን በመስጠት ውስጥ የምንመለከተው ሁለተኛ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥ ለተለያዩ ሙያዎች የሚሰጥ ልዩ ችሎታ ነው። የካህናትን ልብስ ስላዘጋጁ ሰዎችና (ዘጸ. 28፡3) በማደሪያው ድንኳን ሥራ ውስጥ ስለተሳተፉ ሰዎች (ዘጸ. 31፡3ን ከ35፡30-35 ጋር ያወዳድሩ) ከዚህ ቀደም ከሌላ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ተጠቅሷል። በጥቂት ስፍራዎች የተጠቀሱት አንዳንድ ሁኔታዎች፥ ምናልባት እጅግ ሰፊ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለመግለጥ ብቻ ይሆናል። መሊንስ [Mullins] የተባለ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ የጢሮሱን ኪራምን በመጥቀስ፥ ‘‘የናስንም ሥራ ሁሉ ይሠራ ዘንድ በጥበብ እና በማስተዋል በብልሃትም ተሞልቶ ነበር’’ (1ኛ ነገሥት 7፡14) የሚለው ቃል፥ ምናልባት የመንፈስ ቅዱስን ለሥራው የማብቃት ተግባር ሳይገልጥ አይቀርም ብሏል። እንዲህ ያለው የመንፈሳዊ ብቃት አሳብ ተፈጥሮአዊ ችሎታን የሚያገል አይደለም። ተደብቆ በኖረ ተፈጥሮአዊ ችሎታ ላይ የሚጨመር ኃይልና ተልእኮን ከግብ ለማድረስ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ልዩ መነቃቂያ ነው። የተፈጥሮ ችሎታ ባይገለልም ያለ መንፈስ ቅዱስ ምሪት ብቃት ማግኘት አይቻልም።

ያልተሰመደ የሰውነት ጥንካሬ (ጉልበት) ስጦታ። በዚህ አንጻር ልንመለከተው የሚገባ ሦስተኛ ነገር ደግሞ፥ አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ሰው ከሚኖረው ጥንካሬ በላይ የሚገለጠው ብርታትና ጉልበት ነው። ለዚህ ግልጥና ዋና ማስረጃ የሚሆነን የሳምሶን ሕይወት ይሆናል። ሳምሶን መንፈስ ቅዱስ በላዩ በወረደ ጊዜ፥ ከሰዎች ብርታት በላቀ ኃይል እጅግ ከፍ ያለ ተግባር ይፈጽም እንደነበር እንመለከታለን (መሳ. 13፡25፤ 14፡6፥ 19፤ 15፡14)። በተደጋጋሚ በሠራው ኃጢአት ምክንያት ይህን ብርታቱን ለጊዜው ያጣው ቢሆንም፥ በሕይወት ዘመኑ መጨረሻ ሰዓት ላይ ለአንድ ጊዜ እንደገና አግኝቶት እንደነበርም ተረድተናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ ባንመለከትም የብሉይ ኪዳን ጀግኖች የፈጸሟቸው ብዙ ተግባራት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታገዙ እንደነበር አንዳች ጥርጣሬ የለንም። ቀደም ሲል በቃል ስለሚሆን መገለጥና ትንቢት፥ እንዲሁም እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት የሠራውን በተመለከትን ጊዜ ስለ ሰዎች ያከናወነው እጅግ አስፈላጊ ተግባር በሰፊው ተብራርቷል። በእነዚህ ሁሉ ዋና ዋና የአገልግሎት መስኮች የሰው ልጆች የአእምሮ ኃይል፥ ከመንፈስ ቅዱስ በሚገኘው ብቃት እጅግ ልቆ እንደነበር ለማየት እንችላለን። ተአምራዊ መገለጥ፥ የነቢይነት ስጦታ፥ ሕልም በመተርጐም የታየው መንፈሳዊ ጥበብና ቅዱሳት መጻሕፍት በሚጻፉበት ጊዜ የታየው አስተማማኝ ምሪት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ዋና አገልግሎት ነበር። ልክ እንደ ሌላው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ሁሉ፥

እነዚህ አገልግሎቶችም በስጦታው ሉዓላዊነት ብቻ የሚገለጡ እንጂ፥ ለፈለጋቸው ሁሉ የሚገኙ እንዳልሆኑ እንመለከታለን።

መንፈስ ቅዱስ በጥቅል ለሰው ሁሉ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያመለክቱ የሚመስሉ አንዳንድ ክፍሎች እንደ ነህምያ 9፡20 እና ምሳሌ 1፡23 ቢገኙም፥ የመንፈስ አገልግሎት በብሉይ ኪዳን እንደዛ እንዳልነበረ ጥልቅ የሆነ የብሉይ ኪዳን ጥናት ያመለክታል። በብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በነቢያትና እግዚአብሔር በመረጣቸው ሰዎች በኩል ብቻ ይታወቅ ነበር። የመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሁሉ የማደሩ ልዩ ጸጋ፥ እንዲሁም የሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ፍሬን የማፍራት ሰፊ ዕድል፥ ለአዲስ ኪዳን የተጠበቀ ነገር ነበር።

5. የብሉይ ኪዳን ተአምራት

የብሉይ ኪዳን ተአምራት መጠን። የብሉይ ኪዳን ጥናት በእግዚአብሔር ኃይል ስለተከናወኑ አያሌ ተአምራት ይገልጣል። በአዲስ ኪዳን እንደተደረገው ተአምራቱን ለማብራራት የተሞከረበት ስፍራ ባይኖርም፥ ተአምራቶቹን ያከናውናቸው የነበረው የእግዚአብሔር ኃይል እንደነበረ በግልጥ ይታያል። ታላላቅ ተአምራት ከታዩባቸው ሦስት ዘመናት ሁለቱ (የሙሴና የኤልያስ-ኤልሳዕ ዘመን) በብሉይ ኪዳን ሲገኙ፥ በክርስቶስና በሐዋርያት ዘመን የሆነውና ሦስተኛው ግን በአዲስ ኪዳን ይገኛል። በብሉይ ኪዳን የተፈጸሙትን ተአምራት፥ ልዩነት ሳይኖር መለኮት ይፈጽማቸው ወይም ከሥላሴ አካላት የአንዱ ተግባር ይሁኑ በቀጥታ የምናየው ማስረጃ የለም።

መንፈሰ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ከተፈጸሙ ተአምራት ጋር ያለው ግንኙነት። በብሉይ ኪዳን፥ ተአምራት የተፈጸሙት በመንፈስ ቅዱስ ስለመሆኑ አንዳችም ማስረጃ አልተጠቀሰም። ተአምራትን የሚያደርገው ኃይል፥ በሥላሴ አካላት መካከል ልዩነት ሳያደርግ በእግዚአብሔር የተደረገ ነው ይለዋል። ተአምራትን ማድረግ እያንዳንዱ የሥላሴ አካል ተግባር፥ በአጠቃላይም የአንድ አምላክ ሥራ ነው። ነገር ግን ሦስተኛው የሥላሴ አካል፥ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ተአምራቶቹን ያከናወነ መሆኑን የሚናገሩ አንዳንድ ጥቅሶች እናገኛለን። መንፈስ ቅዱስ በመፍጠርና ፍጥረታትን በመጠበቅ ተግባር መሰማራቱ በጣም አስፈላጊ እንደነበር ግልጥ ነው። የመንፈስ ቅዱስ በሁሉም ስፍራ መገኘት ከሌሎች የሥላሴ አካላት ይበልጥ ተጠቅሶ ይታያል። ይህ ባሕርይ በሦስቱ የሥላሴ አካላት ውስጥ እኩልና አንድ ቢሆንም፥ በነቢይነትም ሆነ በሌላ በማንኛውም አገልግሎት በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚሰጠው ብቃት ከአገልግሎቶቹ ጋር ያለውን የጠበቀ

ግንኙነት ያሳያል። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን የተደረጉ ተአምራት "በእግዚአብሔር" የተከናወኑ ሲሆኑ፥ አንዳንዶቹን መንፈስ ቅዱስ እንዳከናወናቸው ግልጥ ነው።

የሚቀርቡት አሳቦች በሙሉ የምንፈልገውን ያህል ግልጥ ባይሆኑም፥ አዌን የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ ወደሚቀጥለው ማጠቃለያ ደርሷል፦ "መንፈስ ቅዱስ ከሚፈጽማቸው የተለመዱ ተግባራት ልዩ የሆነው ሦስተኛ ነገር ተአምራትን ማድረጉ ነው። በብሉይ ኪዳን ተደጋጋሚ ተአምራት ካደረጉት መካከል ሙሴ፥ ኢያሱ፥ ኤልያስና ኤልሳዕ ሌሎችም ሲገኙ፥ አይሁዳውያን ባይሳሳቱ ኖሮ፥ ሙሴ ያደረጋቸው ተአምራት ከሁሉም ይልቁ ነበር። እነዚህ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ኃይል ውጤቶች ናቸው። ተአምራት በእርግጥ በተፈጥሮ ምክንያት ሊኖሩ ከሚችሉ ነገሮች ጋር የሚዛመዱ ቢሆኑም፥ እጅግ ከፍ ያሉና የላቁ መሆናቸው ግን አያጠራጥርም"።

በብሉይ ኪዳን ጊዜ በነበረው መንገድ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች ብዙ ተአምራት እንደሠሩ እንረዳለን። ለምሳሌ፥ ሳምሶን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት ለሰው ጨርሶ የማይቻል ነገር ሲፈጽም እናያለን። አብድዩ የእግዚአብሔር መንፈስ ኤልያስን ወደማያውቀው ስፍራ እንዳይወስድበት መፍራቱን ገለጠ (1ኛ ነገሥት 18፡12)። ሕዝቅኤልም በመንፈስ ቅዱስ መነሣቱን ተረድተናል (ሕዝ. 3፡12ቀ.)። ይህ ዓይነቱ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር፥ እግዚአብሔር ተአምራትን በሚያደርግበት ጊዜ ከሚፈጸመው ጋር ተመሳሳይ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ከተፈጸሙ ተአምራት ጋር ያለው ግንኙነት። ወንጌላት ክርስቶስ በተአምራት መልክ የፈጸማቸውን ሰፊ አገልግሎቶች መዝግበዋል። እነዚህ መጪሑ በሚመጣበት ጊዜ ለሚታየው ነገር ትንቢታዊ ምልክቶች ናቸው። ክርስቶስ ሁለት ጊዜ ተአምራትን የሠራው፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሆነ ተገልጧል። በማቴዎስ 12፡28 ክርስቶስ በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን እንደሚያወጣ ተናገረ። ደግሞም በሉቃስ 4፡14-18 በሽተኞችን የመፈወሱ ሥራ በመንፈስ ቅዱስ የመቀባት ውጤት እንደሆነ ተጽፏል። የክርስቶስ ሥጋዊ ባሕርይ ከመለኮታዊ ባሕርይ ጋር የተዋሐደ ቢሆንም፥ ተአምራትን ለማድረግ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ካስፈለገው፥ ኃጢአተኛ የሆነ ሰው ተአምራትን ለማድረግ ምን ያህል በመንፈስ ቅዱስ ሊደገፍ ይገባዋል? ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተአምራትን የማድረጉ ጉዳይ፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ነቢያት አድርጎ በሾማቸው ሰዎች በኩል ያደረጋቸው ተአምራትም የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ለመሆናቸው የሚቀርብ ጠንካራ ማስረጃ ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ተአምራትን የማድረግ ውክልና ለማን እንደተሰጠ የሚናገር ግልጥ ማረጋገጫ ባይኖርም፥ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ለተፈጸሙ ብዙ ተአምራት መለኮታዊ ወኪል ነው ብለን ማሰብና፥ ሌሎቹም የሥላሴ አካላት ተመሳሳይ አገልግሎት ሊኖራቸው እንደሚችል አለመዘንጋት ተገቢ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን የነበረውን ተግባር በአጠቃላይ መመልከት ለመሠረታዊ የእምነት ትምህርት አስፈላጊ ነው። አስፈላጊነቱ በአሁኑ ጊዜ ላለው አገልግሎት አቅጣጫ የሚሰጥ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን፥ በየዘመናቱ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ስለሚገልጥና መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የስፍረ-ዘመናት ልዩነቶች ለማየት የሚያስችሉ አንዳንድ መመሪያዎችን ስለምናገኝበት ነው። መንፈስ ቅዱስ በጸጋ ዘመን ለቅዱሳን ሁሉ የሚሰጠው አገልግሎት ከሌሎች ዘመናት ጋር ሲነጻጸር፥ የተለየና የተትረፈረፈ ሁኔታ የሚታይበት ነው። በጣም ውሱን የሆነ መብት የነበራቸውን፥ ነገር ግን እጅግ የከበረ ሕይወት የኖሩትን በርካታ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ስንመለከት፥ መንፈሳዊ መብት በሙላት የተገለጠልን እኛ ክርስቲያኖች ሕይወታችንን ሙሉ በሙሉ ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር በመስጠት የመንፈስ ፍሬዎችን ሁሉ ልናፈራ ይገባል።

— ክፍል ሦስት —

መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር ያለው ግንኙነት

9

መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ መወለድ ጋር ያለው ግንኙነት

1. የወንጌላት ባሕርይ

ቅዱሳት መጻሕፍትን በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚተረጉም ማንኛውም ሰው፥ የወንጌላትን ታሪክ የመተርጐምን ያህል ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ተግባር እንደሌለ ያውቃል። የተፈጸሙት ድርጊቶች እጅግ ቀጥተኛና ግልጥ፥ አጻጻፋቸው ልጆች እንኳ አንብበው ሊረዱትና ሊጠቀሙበት በሚችሉት አኳኋን ቀለል ያለ ቢሆንም፤ የሕግ፥ የጸጋ እና የእግዚአብሔር መንግሥት ሰፍረ-ዘመናት ጉዳዮች በአንድ ላይ በጥምር መቅረባቸው የአተረጓጐሙን ችግር ይበልጥ ሰፊ አድርገውታል።

ክርስቶስ በምድር የኖረው የሙሴ ሕግ እንደ ፀሐይ ሊጠልቅ በተቃረበበት ጊዜ ነው። ሕግ ከመታዘዝ ይልቅ፥ ብዙ ጊዜ በጣሱትና ቃል በቃል በተረጎሙት ፈሪሳውያንና በለዘብተኞቹ ሰዱቃውያን ዘንድ የተሳሳተ ትርጉም የተሰጠው ቢሆንም፥ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለእስራኤል የሰጠውና ለአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ሕዝቡ የተገዛበት ዋና ደንብ ነበር። ሕግ እስራኤልን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት እንደ ሞግዚት እንዲያገለግል ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፥ ሕዝቡ ግን በታቀደለት ዓላማ ሊገለገልበት አልቻለም (ገላ. 3፡24)።

ክርስቶስ በመስቀል ሞቱ ብቻ ሳይሆን፥ በምድር ላይ ሕይወቱ ባሳየው ፍጹም ታዛዥነት ሕግን ለመፈጸም ወደ ምድር መጣ። እርሱ ‘‘ከሕግ በታች ተወለደ’’ (ገላ. 4፡4)። ሕግን እየጠቀሰና እየተረጐመ አስተምሯል። ሰዎች አዳዲስ ነገር በመጨመር አዛብተውት የነበረውን የእግዚአብሔር እውነት አስተካክሏል። በትምህርቱ ሕግን እየተመለከተ እንዳስተማረ ሁሉ፥ ወደፊት ሊገለጥ ስላለው አስደናቂ መንግሥትም ተናግሯል። የእግዚአብሔርን መንግሥት መመሪያ ለሕዝቡ አስተማረ፤ የተወሰኑ ሰዎችን ብቻ ለይቶ የማየትን አደገኝነት አስጠነቀቀ፤ ከውጫዊ የኃይማኖት ልምምድ ይልቅ በእውነተኛና ልባዊ በሆነ ሃይማኖት ላይ በማትኮር አስተማረ። መሢሐዊ መልእክቱን በፍጹም ግልጥነትና በልዩ

መገለጥ አቀረበ። የሕዝቡ አለማመን እየጨመረ መምጣቱ በመስቀል የመሞቱን ወቅት መቅረብ የሚያሳይ ስለነበር፥ ትምህርቱ ስለዚህ ዘመን በሚናገሩ እውነቶች ላይ እንዲያተኩር አደረገ። የእግዚአብሔርንም መንግሥት በምስጢራዊ መልኩ ማቅረብ ጀመረ። እግዚአብሔር ለዳዊት ገብቶለት የነበረው ቃል ኪዳን ፍጻሜ አይሁዶች ክርስቶስን ባለመቀበላቸው ቃል ኪዳኑ ሳይሻር ለሌላ ወቅት ተላልፎ ሌላ ያልተገለጠ ተስፋ ተከሠተ። ስለዚህም ከሕዝብ ሁሉ (ከአሕዛብም ሆነ ከአይሁድ) አንድ አዲስ ጎብረተሰብ ለመመሥረት የነበረው ዓላማ ግልጥ ሆነ። ይህ ጎብረተሰብ እግዚአብሔር ለአሰራኤል ከገባው ቃል ኪዳን የተለየ ጥሪና መድረሻ (ርስት) ያለው ነው። ክርስቶስ በነቢይነት አገልግሎቱ በምድር የኖረው በሦስቱም ግለት በሕግ፥ በጸጋና በእግዚአብሔር መንግሥት ስፍረ-ዘመናት ውስጥ መሆኑን በማሰብ፥ የወንጌላትን ታሪክ በትክክልና ለሕይወት በሚጠቅም መንገድ ለመተርጎም የሚቻለው እርሱ ስለ ሦስቱ ስፍረ-ዘመናት እያስመለከተ መናገሩንም በመገንዘብ ነው።

የክርስቶስ በሥጋ መምጣት (ተሠገም)። ክርስቶስ በነቢይነቱ ከገለጠው ረቂቅ እውነት ሌላ፥ ሥጋ ለብሶና የሰው መልክ ይዞ ለጊዜው በሰብዓዊነት መወሰኑ የሚያስደንቅ ነው። ወንጌላት አስደናቂና ሰፊ መገለጦችን፥ ጠቃሚ እውነትን፥ እና የክርስቶስን የምድር ኑሮ ፍጻሜ ግለት ሞትና ትንሣኤውን በመጨመር የሚናገሩ ናቸው። የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በነዚህ መጻሕፍት ላይ ጥናት ቢያደርግ እንኳን የያዙትን መጠነኛ እውነት ብቻ ነው መገንዘብ የሚችለው። ብሉይ ኪዳን የመሢሑን መምጣት ወደፊት እያየ በመጠበቅ ስሜት የሚናገር ሲሆን፥ አዲስ ኪዳን ደግሞ ከሐዋርያት ሥራ ጀምሮ የክርስቶስን ሥራ ወደ ኋላ እየተመለከተ ክርስቶስ ምን እንዳደረገና ምንስ እንደሚያደርግ ተርጉሞ በመተንተን ያሳያል።

የሙሴ ሕግ አሰከ መሰቀሉ ድረስ ቃጥሏል። ቢያንስ እስከ ክርስቶስ ሞት ድረስ ያለው አብዛኛው የወንጌላት ታሪክ በሕግ ስፍረ-ዘመን የተፈጸመ ነው። ከክርስቶስ ሞት በኋላ ሕግ ፍጻሜ ስላገኘ የሽግግሩ ዘመን በሚገባ መጀመሩን እናያለን። በወንጌላት ውስጥ ያለው ተቀዳሚ ታሪክ፥ መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር በምድር የነበረውን ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን፥ ከሰዎች ጋር ስለነበረው ግንኙነት የምናገኘው፥ ብዙ አዳዲስ ነገሮችን ሳይሆን ጥቂት ነገሮችን ነው።

2. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በወንጌላት ውስጥ

የመንፈሰ ቅዱስ ሥራ መሢሐዊነት። ለመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርት የወንጌል ዘመን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ምክንያቱም

ግንኙነት ያለው ስለሆነ ነው። በብሉይ ኪዳን፥ መንፈስ ቅዱስ ከመሢሕ ጋር ስላለው ግንኙነት የሚናገሩ ትንቢቶች ነበሩ። አንዳንዱ ይበልጥ አጠቃላይ ቢሆንም፥ አብዛኛው ስለ ሺሁ ዓመት መንግሥት የሚናገር ነው። ለዚህ ጉዳይ ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ጥቅሶች አንዱ ኢሳይያስ 11፡2-3፥ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ላይ እንዳረፈ ይናገራል። በኢሳይያስ 42፡1-4 የተነገረው ትንቢት ደግሞ በክርስቶስ አካላዊ ሕልውናና በሥራው እንደተፈጸመ ተጠቅሷል (ሉቃስ 4፡17-21)። መንፈስ ቅዱስ በአካላዊነቱ ብቻ ሳይሆን በመሢሕነት ዘመኑም ለሰው ልጅ ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ነው የተገለጠው። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከሁሉም የመሢሐዊነት ዓላማ ተነጥሎ የሚታይ አለመሆኑ ግልጥ ነው (ኢሳ. 32፡15ቀ.፤ 44፡3-5፤ ሕዝ. 36፡26ቀ.፤ ዘካ. 12፡10)።

መንፈስ ቅዱስ በወንጌላት የነበረው ሥራ የብሉይ ኪዳንን አሠራር የተከተለ ነው። ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ሕይወት በተመለከተ በወንጌላት የሚያከናውነው ሥራ ለእያንዳንዱ ሰው በግል የተፈጸመና ሉዓላዊ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደሆነው በወንጌላትም አንዳንድ ቅዱሳን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር። ይህ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለጥቂቶች ብቻ እንደነበር የምንረዳው፥ በዚህ ሁኔታ በመንፈስ መሞላታቸው የተጠቀሰ አራት ሰዎች ብቻ በመሆናቸው ነው። እነርሱም መጥምቁ ዮሐንስ (ሉቃስ 1፡15)፥ ኤልሳቤጥ (ሉቃስ 1፡41)፥ ዘካርያስ (ሉቃስ 1፡67)፥ እና ስምዖን (ሉቃስ 2፡25) ናቸው።

ደቀ መዛሙርቱም በስደት በገዥዎች ፊት በቆሙ ጊዜ፥ ምን እንደሚመልሱ የሚነግራቸው መንፈስ ቅዱስ እንደነበር ተጠቁሟል (ማቴ. 10፡20፤ ማር. 13፡11፤ ሉቃስ 12፡12)። በዮሐንስ 20፡22፥ ለመንፈሳዊ ጉዳያቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለመስጠት እስከ ጰንጠቆስጤ ዕለት ድረስ ያገለገለ ጊዜያዊ ሙላት እንዳገኙ ተጽፏል። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መግለጫዎች፥ ለአሁኑ ዘመን በመመሪያነት እንዲያገለግሉ የተሰጡ ሳይሆኑ፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደነበር የቀጠለ ሥራውን የሚያሳዩ ናቸው።

በወንጌላት ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተጻፈውን ስናጠና ልንመለከተው የሚገባ እጅግ ታላቅና አስፈላጊ ነገር፥ ለክርስቶስ ያለውን አገልግሎት ነው። በአሁኑ ዘመን ስላለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ግን ቆይተን የምንመለከተው ይሆናል።

3. የክርስቶስ ከድንግል መወለድ

በቀላሉ ልንረዳቸው የማይቻለን ሁኔታ ከተገለጡ ምስጢራትና ጥቂት የእግዚአብሔር ተአምራዊ ሥራዎች መካከል ዋናው የክርስቶስ መወለድ ነው። የክርስቶስ መወለድ የሰውን ምክንያታዊ አቀራረብና የተለመዱ የተፈጥሮ ክስተቶችን ያልተከተለና ተአምራት ሁሉ የታዩበት ነው። ሌሎች ተአምራዊ ነገሮች ከተፈጥሮ ሕግ ጋር የሚስማሙ ቢመስሉም፥ ክርስቶስ የተወለደበት መንገድ ግን የእግዚአብሔርን የባሕርይ ለውጥ የሚጠይቅ ይመስላል። ነገሩን በእምነት መቀበሉ የሚያስቸግር ባይሆንም፥ የክርስቶስን መወለድ ለመግለጥ የምንጠቀምበት አነጋገር ትርጉም፥ ለሥነ-መለኮት ሊቃውንት ከፍተኛ ችግርን የፈጠረ ነው። ክርስቶስ ከድንግል መወለዱን የሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ጠንካራ ተቃውሞ ቢገጥመውም፥ ማዕከላዊ እውነትና አስፈላጊ በመሆኑ፥ በብዙ አዋቂዎች ዘንድ በርካታ የመከላከያ አሳቦች ቀርበውለት እስከዛሬ ጸንቶ ቆሟል። ማንም ቅዱሳት መጻሕፍት የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤቶችና የማይሻሩ መሆናቸውን ተቀብሎ ቀላልና ንጹሕ በሆነ እምነት ቢቀርብ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን በጥንቃቄ በመመርመር ክርስቶስ ከድንግል መወለዱን አስመልክቶ ለሚገጥመው ችግር መፍትሔ ያገኘለታል። ስለዚህ ጉዳይ ለሚነሡት ጥያቄዎች ሁሉ መልስ መስጠቱ የማይቻል ቢሆንም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጥ የሆኑ በርካታ እውነቶች መኖራቸው ግን አያጠራጥርም።

ኢየሱስ የተፀነሰው ከመንፈሰ ቅዱስ ነው። ለኢየሱስ መፀነስ ምክንያት የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መኖሩን ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጥ ይመሰክራሉ። ማቴዎስ ይህን ነገር ግልጥ አድርጎ ማርያም ‘‘ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች’’ በማለት፥ መልአኩ ለዮሴፍ *ያመጣውን* መልእክት ጭምር ጽፏል። ‘‘እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። ... የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና... ’’ (ማቴ. 1፡18፥ 20-21)። ሉቃስ ደግሞ ይህን ጉዳይ ይበልጥ ግልጥ አድርጐታል። መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት ‘‘መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል’’ (ሉቃስ 1፡35)። እነዚህ ሁለት ክፍሎች ኢየሱስ ያለ ሰብአዊ አባት መወለዱን በማያጠራጥር ሁኔታ ይገልጣሉ። ይህም የመንፈስ ቅዱስን ታላቅ ሥራ ያሳያል።

በሌሎች የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች እንደሚሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ተግባር ውስጥ ሁለት የሥላሴ አካላት፡- አብና መንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ ነበራቸው። ከመዝሙር 40፡6 በመጥቀስ በዕብራውያን 10፡5 እንደተጻፈው ክርስቶስ፡- ‘‘መሥዋዕትንና ቁርባንን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ’’ ይላል። በዚህ ስፍራ ክርስቶስን ሥጋ የማልበስ ሥራ የአብ ሆኖ ቀርቧል። በሌላ በኩል ደግሞ በዕብራውያን 2፡14 ክርስቶስ ሥጋና ደም መልበሱ በፈቃዱ የፈጸመው ተግባር መሆኑን እናያለን። ሰብአዊ ከሆነው የክርስቶስ ሕይወት ጋር የተዋሐደው መለኮት ሁለተኛው የሥላሴ አካል ነው። ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነውን ይህን ምስጢር ክርስቶስ የተፀነሰው በመንፈስ ቅዱስ ነው በሚለው ቃል መግለጥ ይቻላል። ከሰብአዊነት ጋር የተዋሐደው ሁለተኛው የሥላሴ አካል ሲሆን፥ የመጀመሪያው የሥላሴ አካል፥ ሰብአዊ የሆነው ክርስቶስ አባት ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን እንደ አባት የጠቀሰበት ቦታ ጨርሶ የለም።

የክርስቶስ እናት ማርያም። ክርስቶስ ሰው የሆነው የዮሴፍ እጮኛ ከነበረችው ከማርያም በተለመደው መንገድ በመወለድ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ቀደም ሲል ከተመለከትነው እውነት ጋር እኩል በሆነ አመለካከት ያሳያል። ክርስቶስ የተፀነሰው ተአምራዊ በሆነ መንገድ ቢሆንም፥ የመወለዱ ሁኔታ ግን ተፈጥሮአዊ በሆነና በተለመደው ሁኔታ ነበር። የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መሢሑ ድንግል ከሆነች ሴት እንደሚወለድ የተናገሩት ቃል በማርያም በኩል ፍጻሜ ማግኘቱ ግልጥና የማያሻማ ነው (ዘፍጥ. 3፡15፤ ኢሳ. 7፡14፤ ማቴ. 1፡18፥ 20-23፤ 2፡11፥ 13፥ 20-21፤ 12፡48፤ 13፡55፤ ማር. 3፡31፤ 6፡3፤ ሉቃስ 1፡35፥ 43፤ 2፡5-7፥ 16፥ 34፥ 48፥ 51፤ 8፡19-20፤ ዮሐ. 19፡25-27፤ ሐዋ. 1፡14፤ ገላ. 4፡4)። ስለ ማርያም የክርስቶስ እናትነት በርካታ ማስረጃዎችን ለማቅረብ ይቻላል። ይህን እውነት ለዘብተኛ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንኳን ጠንከር ብለው ሊክዱት አልሞከሩም። በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ይህን ነገር የተጠራጠሩ መናፍቃን ብቻ ነበሩ። ‘‘ሴሪንቲያን’’ [Cerinthian] የተባሉት መናፍቃን፥ ክርስቶስ የተፀነሰው በተአምር መሆኑን ክደው፥ ሰው የሆነው ኢየሱስ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ሰማያዊ መንፈስ ነበረው የሚል አቋም አንጸባርቀዋል። ይህ አቋም ግን የተለመደውን የአወላለድ ሁኔታ የሚክድ አይደለም። ዶሴቲሲያውያን [Docetists] ግን ‘‘አካሉ እውነተኛ አይደለም’’ በማለት፥ ኢየሱስ በሥጋ አልተወለደም ወደሚል አሳብ ያዘነብላሉ።

4. የኢየሱስ አፀናነስ ሁኔታ

የክርስቶስን የአፀናነስ ሁኔታ በምናጠናበት ጊዜ፥ መፍትሔ ልናገኝለት የሚያስቸግረን ዋና ጉዳይ የሰብአዊነቱን መነሻ ማወቁ ነው። ክርስቶስ ከማርያም መወለዱ ግልጥ ቢሆንም፥ የአካላዊ ሕልውናው አንዳንድ ሁኔታ ከሰው ዘር ጨርሶ የተለየ ነበር። የአምላክ ሰው መሆን ታላቅ ተአምር ቢሆንም፥ ያለ ኃጢአት የሆነ ሰው ጅማሬ ደግሞ ከፍተኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት ችግር ይሆናል። ይህን ጉዳይ በሚመለከት ብዙ ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ። የክርስቶስ ሰብአዊነት ከማርያም ብቻ የተወሰደ ነውን? ሰብአዊነቱ የመፈጠር ወይስ የመወለድ ውጤት ነው? የኃጢአት ወደ ሰው ዘር መተላለፍ [Imputation/ኢምፒዩቴሽን] በክርስቶስ ሰብአዊነት ላይ እንዴት አልሠራም? የክርስቶስ ሰብአዊ ተፈጥሮ ያለ ኃጢአት የነበረ ነውን ወይስ የተቀደሰ? እነዚህና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ስለ ክርስቶስ መፀነስ ጥናት በምናካሄድበት ጊዜ የሚነሡ ናቸው። ግልጥ የሆነ መገለጥ ሳናገኝ በምክንያት ብቻ ተመሥርተን ለማስረዳት ከመሞከር ዝም ማለት፥ የክርስቶስን መፀነስ ትምህርት ለመከላከል ከሚሠሩ ከፍተኛ ስሕተቶች ራስን ለመጠበቅ ያስችላል። ይህን የእውነት ክፍል በጥንቃቄ መመርመሩ፥ ክርስቶስ ከኃጢአት ነጻ በመሆን ተፀንሳ ከነበረች ማርያም በሰብአዊነቱ ተወለደ የሚለውን አሳብና ስለ አምላክና ሰው መዋሐድ የሚሰጡትን የመናፍቃን መግለጫዎች ሐሰተኛነት ለማረጋገጥ ይረዳናል።

የክርስቶስ ሰብአዊነት የመውለድ ወይስ የመፈጠር ውጤት? *

የቅዱሳት መጻሕፍት ቋንቋ የክርስቶስ ሥጋ መልበስ የመወለድ ስርፀት መሆኑን ያብራራል። ለዚህ ነው ክርስቶስ ተወለደ (ማቴ. 2፡1)፥ ተፀነሰ

---

* የነፍስ የመጀመሪያ ምንጭ ጥያቄ ለዘመናት ሲያከራክር የቆየ ነገር ነው። ለዚህ ጉዳይ ሦስት መልሶች ቀርበዋል፦ 1. የሰው ነፍስ ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ሁሌ የሚኖር ነው። ከአንድ የሕይወት ዓይነት ወደ ሌላው የሚተላለፍም ሲሆን፥ ቀደም ሲል በነበረው አኗኗር መሠረት ወደ ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ዓይነት ሕይወት ሊሄድ ይችላል። ይህ አሳብ ቅድመ-ሕልውና [Pre-existence/ፕሪ-ኤግዚስተንስ] ይባላል። 2. ሁለተኛው፥ በሰው መፀነስ ጊዜ እግዚአብሔር አዲስ ነፍስ በመፍጠር ከዚያ አካል ጋር እንዲዋሐድ ያደርጋል የሚለው የ‘‘ክሪኤሽኒዝም’’ [Creationism] አሳብ ነው። 3. ሌላው፥ ነፍስም ሆነ አካል የመፀነስ ውጤቶች ናቸው የሚል ሲሆን፥ ይህም የ‘‘ትራዱሲያኒዝም’’ [Traducianism] አስተሳሰብ ነው።

የመጀመሪያው አሳብ ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው በመሆኑ ልንቀበለው አይገባም። ‘‘ትራዱሲያኒዝም’’ ሆነ ‘‘ክሪኤሽኒዝም’’ ብዙ ችግሮች ያሉባቸው ከመሆኑም በላይ፥ የትኛውንም ቢሆን ማረጋገጡ ፍጹም አይቻልም። በታሪክ፥ የምዕራባውያን ቤተ ክርስቲያን ትራዱሲያኒዝምን የተቀበለች ሲሆን፥ የምሥራቃውያን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ክሪኤሽኒዝምን ተቀብላለች። ምናልባት ትክክለኛው መልስ ከሁለቱ መካከል የሚገኝ ሲሆን፥ ይህንንም ሚች በሆነው አእምሯችን በአሁኑ ጊዜ መረዳቱ አይቻለንም።

(ማቴ. 1፡20)፥ የበኩር ልጅዋን ወለደች (ሉቃስ 2፡7)፥ ከሴት የተወለደውን (ገላ. 4፡4) የሚሉ ቃላት የምናየው። የክርስቶስ መወለድ ከሌላው ሁሉ የተለየ መሆኑ ግልጥ ነው። እርሱ ከድንግል ተወለደ። ስለ ክርስቶስ መወለድ ለመግለጥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀምበት ቋንቋ ጥያቄውን ሙሉ በሙሉ የሚመልስ አይደለም። ችግሩ የአወላለዱ ሳይሆን የአፀናነሱ ሁኔታ ነው።

የክርስቶስ ሰብአዊነት ያለ ኃጢአት ነው? ወይስ እንዲሁ የተቀደሰ? ከኃጢአት ነጻ የሆነውን የክርስቶስ ሰብአዊነትና የመፍጠር አሳብ ለማስወገድ በምንሞክርበት ጊዜ፥ የሚገጥመን ዋና ችግር፥ ኃጢአተኛ ከሆነ የሰው ልጅ የተቀደሰ ሕፃን ለማግኘት የመቻሉ ጉዳይ ነው። ከማርያም የተወለደው ልጅ ያለ ኃጢአት የመሆኑ ነገር ከክርክር በኋላ ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስን በሚቀበሉ መካከል ሁሉ ተቀባይነትን ያገኘ አሳብ ነው። ማርያም፥ እንዴት ቅዱስና ያለ ነቀፋ ወይም ኃጢአት የሆነ ልጅ እናት ሆነች? የሚለው ጥያቄ ግን የሚያከራክር ነው።

ዘመናውያን የሆኑ የሮማ ካቶሊክ እምነት ተከታዮች ያለ ኃጢአት የሆነው ክርስቶስ ጉዳይ ንፁሕ በሆነችው እናቱ በማርያም የሚገለጥ ነው በማለት ችግሩን ሊፈቱ ይሞክራሉ። ሞራን [Moran] የተባለ ሰው ሲጽፍ፡- ‘‘... የአዳኛችን እናት በመሆኗ በእግዚአብሔር ቸርነት ኢየሱስን ከፀነሰችበት ሰዓት ጀምሮ ከዘር ወደ ዘር ከሚተላለፍ የውርስ ኃጢአት ነጻ ሆና ነበር። ይህ የማርያም ልዩ መብት የሆነ ክብር በእግዚአብሔር ተገለጠ። በኋላም ትርጉሙ ለቤተ ክርስቲያን በሚገባ መልኩ በከፍተኛ ትኩረት ተቀረጸ’’ ብሏል። የፕሮቴስታንት አማኞች ስለዚህ ጉዳይ የሚያቀርቡት ተቃውሞ፥ ይህ ትምህርት በቅዱሳት መጻሕፍት ያልተጠቀሰ ከመሆኑም በላይ፥ ችግሩን ጨርሶ የሚፈታ አይደለም የሚል ነው። ነገሩን ከክርስቶስ ወደ ማርያም የሚያስተላልፍ በመሆኑና ሁለቱም ወላጆችዋ ሰዎች መሆ ናቸው ችግሩን ይበልጥ ያባብሰዋል። ማርያም የሰው ዘር ኃጢአት ተካፋይ ሆና ሳለ የወለደችው ልጅ ቅዱስ መሆኑ ነው ሌላው ችግር። ለዚህ ነው ችግሩ ከክርስቶስ ሰብአዊነት ጋር የተያያዘ የሚሆነው።

የክርስቶስ ሰብአዊነት የመፈጠር ውጤት ከሆነ ችግሩ ቀላል ሊሆን ይችላል። ሰብአዊነት በፅንስ የተላለፈ ከሆነ ግን ነገሩ የግድ መግለጫ የሚፈልግ ይሆናል። ሼድ [Shedd] የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ ይህን ጉዳይ በሚመለከት የሰጠው መልስ፥ የክርስቶስ ሰብአዊነት ከመለኮት ጋር ከመዋሐዱ በፊት ተቀድሷል የሚል ነው። ‘‘ሰብአዊ ተፈጥሮ ከቃል (‘ሎጎስ’ [Logos]፥ ዮሐ. 1፡ 1) ጋር ከመዋሐዱ በፊት ተአምራዊ በሆነ መንገድ ፍጹም እንዲሆን ተቀድሷል’’ ብሏል። ይህን አሳቡን ለማጠንከር ክርስቶስ ቅዱስና ያለ ኃጢአት ነው የሚሉ አሳቦችን ጨምሮ የተለያዩ

ጥቅሶችን አቅርቧል። ሼድ ሲያጠቃልል፦ ‹‹በዚህ ዓረፍተ ነገር አገላለጥ ሁሉም የሥነ-መለኮት አዋቂዎች ይስማማሉ። የሰው ዘር በሙሉ ኃጢአተኛ በመሆኑ ድንግል ማርያምም ኃጢአተኛ ነች። ስለዚህ ይህን ኃጢአተኛነት በክርስቶስ አካል ላይ እንዳታስተላልፍ ይህ አካል ከቃል ጋር አንድ ከመሆኑ ወይም ከመዋሐዱ በፊት ሊዋጅና ሊቀደስ ይገባው ነበር›› ብሏል። ሼድ ሳይገነዘበው የቀረ ነገር ግን፥ ቅዱስ በመሆንና በመቀደስ መካከል ያለውን ልዩነት ነው። በሰማይ ያሉ ቅዱሳን ሁሉ የተቀደሱና ከኃጢአት የነጹ ተደርገዋል። ይህ ከዘላለም ጀምሮ የተነገረለት የእግዚአብሔር ጸጋ መገለጫ ነው። ነገር ግን ኃጢአትን ጨርሶ የማያውቅ ቅዱስ ቢኖር ኖሮ የእርሱ ጉዳይ የተለየ ይሆን ነበር። ስለ ክርስቶስ የተነገረው ይህ ነው፦ ‹‹ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን›› ተብሎ ተጽፏልና (2ኛ ቆሮ. 5፡21)።

ስለዚህ የክርስቶስ ሰብአዊነት የመጣው በመፍጠር ተግባር ነው፥ ወይም ኃጢአተኛ የሆነው ሰብአዊ ተፈጥሮ ከመለኮት ጋር ከመዋሐዱ በፊት ተቀድሶ የተላለፈ፥ ከሚሉት ሁለት አሳቦች አንዱን መምረጥ የግድ ይሆናል። የትራዱሲያኒዝምን አሳብ በመደገፍና በማስፋፋት የታወቀው አውግስጢኖስ [Augustine] በአጠቃላይ ስለ ሰው ዘር የነበረውን የተምታታ አሳብ እንዲህ በማለት አጠቃሎታል።

> ‹‹የክርስቶስ ነፍስ ከአዳም ዘር ነፍስ የመጣ ከሆነ፥ እርሱ ወደዚህ ምድር በሚመጣበት ጊዜ ከድንግል በፍጹምነት እንዲወለድ ከእውነተኛም ሆነ በውርስ ከሚተላለፍ ኃጢአት ነጻ እንዲሆን አስቀድሞ በእርሱ የሚሆነውን በማሰብ አንጽቶ አዘጋጅቶታል። የሰዎች ሁሉ ነፍስ የመጣው ከአንዱ ከአዳም ነፍስ ካልሆነ ግን፥ የአዳም የመጀመሪያ ኃጢአት የሚተላለፈው በሥጋ ብቻ ስለሚሆን የሰው ልጆችን ነፍስ ሁሉ የፈጠረው የእግዚአብሔር ልጅ ለራሱ ነፍስን በመፍጠር እንዲዋሐድ ያደረገው ከኃጢአተኛ ሥጋ ጋር ሳይሆን ‘በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ ነው’›› (ሮሜ 8፡3)።

በሁለቱም አስተሳሰቦች መቀደስ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያመለክት ስሜት መኖሩ ግን ግልጥ ነው። የመፍጠርን አሳብ የሚያንፀባርቀው አዌንም የመቀደስን አሳብ በማረጋገጥ እንዲህ ብሏል፦ ‹‹በተአምራዊ መንገድ የተሠራው የክርስቶስ ሰብአዊ ተፈጥሮ ከመፀነሱ ጀምሮ የተቀደሰና ሊይዘው በሚችለው መጠን በጸጋ የተሞላ ነበር። ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ የተወለደ ስላልነበረ የአዳምን የውርስ ኃጢአት የሚቀበልበት ምንም ምክንያት አልነበረም። የማናገኝበትን የኃጢአት ወንጀል ከእርሱ መፈለግ የማይገባ ነው። አዳም በተፈጠረበት ዕለት እንደነበረው ሁሉ አንዳችም ጉድፍ የማናገኝበት ፍጹም ንጹሕ ነበር።››

ይሁን እንጂ አዌን የተጠቀመበት የቅድስና አሳብ ሼድ ከተጠቀመበት ለየት ያለ ስሜት አለው። ለአዌን መቀደስ መልካምና ውብ የሆነውን ጸጋ በማሳየት ክቡርና ልዩ ለሆነ አገልግሎት መለየት ሲሆን፥ ሼድ ግን ከዚህ ሌላ መቀደስ ከጉድለት የመንጻትን አሳብ የሚጨምር መሆኑን ያምናል።

የክርስቶስ ሰብአዊነት ኃጢአትን የማያውቅ ነበር ወይንስ ተቀድሶ ነው? የሚለው ጥያቄ ክርስቶስ ለዘላለም ያለ ኃጢአት ነበር በሚለው መልካም አመለካከት ሊመለስ ይገባል።

የአዳም ኃጢአት ወደ ክርስቶስ ተላልፏልን? የኃጢአት ውርስ (መተላለፍ) መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በክርስቲያኖች አካባቢ እንደዋና ርእስ ተቆጥሮ ብዙ ጊዜ የሚጠና ሳይሆን፥ በአጠቃላይ በደኅንነት ፕሮግራም ውስጥ ማዕከላዊነት ያለው መሆኑ ግልጥ ነው። ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከው መልእክት ማዕከላዊ ትምህርት የጽድቅና የኃጢአትን መተላለፍ ያዘለ መሠረታዊ ትምህርት ነው። የእግዚአብሔር ጽድቅ በሙላት በእርሱ በሚያምኑ ሁሉ ላይ ይሆን ዘንድ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ የሰው ዘር ኃጢአት በሙሉ በእርሱ ላይ ሆነ። የአዳም ኃጢአት ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ በእርሱ ላይ መኖሩ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም፥ ክርስቶስ በተፀነሰ ጊዜ በእርሱ ላይ ኖሯልን? የሚለው ጥያቄ የሚያነጋግር ነው። በሮሜ 5፡12-21 ላይ የሚደረግ ጥናት በአዳም በደል ምክንያት ፍርድ ለኩነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደመጣ፥ በውርስ በመተላለፍም የአዳም ዘር የሆነ ሁሉ ባለ ዕዳ እንደሆነ ያሳያል። የኃጢአት ባሕርይ ከወላጆች የሚወረስ ሲሆን፥ ኃጢአት ግን ሰው በቀጥታ ከአዳም የሚወርሰው ነገር ነው። የኃጢአት ተፈጥሮ ወደ ክርስቶስ የተላለፈበትን መካከለኛ መንገድ አዌን ባቀረበው በመቀበል ካጠቃለልነው የኃጢአት በሰው ላይ መሆን ችግር ተቃለለ ማለት አይደለም። ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጥ እንደሚያስረዱት፥ የአዳም ኃጢአት እስከ መስቀሉ ድረስ በክርስቶስ ላይ አልሆነም። ታዲያ ይህ እንዴት ሊብራራ ይችላል?

በሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዘንድ ለዚህ ጉዳይ የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑ ያለ ምክንያት አይደለም። ቅዱሳት መጻሕፍት እስከ መስቀሉ ድረስ የአዳም ኃጢአት በክርስቶስ ላይ ያለ መሆኑን ቢናገሩም፥ ምክንያቱን ግን አያብራሩም። ለዚህ ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ መልስ ማግኘት ባይቻልም አንዳንድ ነገሮችን መመልከት ግን ይቻላል።

በመጀመሪያ የምንመለከተው ነገር፥ ፍርድ የተመሠረተው ከአዳም በወረሰነው ኃጢአት የተነሣ መሆኑን እንጂ፥ በምንሠራው ኃጢአት ላይ አለመሆኑን ነው። ኃጢአት በሰው ልጅ ላይ የመኖሩ ጉዳይ የሰው ልጅ በፈራጁ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም መሆኑን ያሳያል። ሰው ኃጢአትን ከአዳም መውረሱ፥ ኃጢአትን በመሥራቱ እና በፈቃዱ ወይም በምግባሩ

ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግበት አይደለም፤ ምንም እንኳን በመለኮታዊ በረከት ላይ የሚያመጣው ልዩነት ቢኖር። በዚህ አንጻር የክርስቶስን ጉዳይ ስንመለከት የኃጢአት መተላለፍ ጉዳይ እርሱ በመስቀል ላይ የእኛን ስፍራ እስኪወስድ ድረስ የሚነሣ ነገር አልሆነም። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ከአዳም የወረስነው ኃጢአት በእርሱ ላይ ሆነ (1ኛ ጴጥ. 2፡24)።

ልንመለከተው የሚገባ ሁለተኛ ነገር፥ ክርስቶስ እንደ ሁለተኛ አዳምነቱ፥ የአዲሱ ሰው ራስ መሆኑ ነው። ክርስቶስ እውነተኛ ሰው ለመሆን ሥጋ መልበሱ የግድ አስፈላጊ ቢሆንም፥ ሲፀነስ ግን የአዳምን ኃጢአት መካፈሉ አስፈላጊ አልነበረም። ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የአዳምን ኃጢአት ወርሶ ነበር፥ ማለት የእግዚአብሔርን ዓላማ የሚቃረንና በክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ፕሮግራም ውስጥ ከመሰቀሉ በፊት ሊከናወን የማይችል ጉዳይ ነው። የሰው ልጅ ሁሉ "በአዳም ውስጥ" የሚታይ መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ የምንመለከት ሲሆን፥ ክርስቶስ "በአዳም ስለመሆኑ" የተነገረ አንዳችም ነገር የለም። "በክርስቶስ ውስጥ" መሆናችን "ከአዳም ጋር" ያለንን ግንኙነት ማቋረጥ ነው። እነዚህ ሁለት አሳቦችና ስፍራዎች በተቃራኒ አቅጣጫዎች ያሉ ናቸው።

ሦስተኛው ነገር የመዋጀት ዓላማ ከግብ ይደርስ ዘንድ አዳኙ ለማዳን የሚችልና የሚፈቅድ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። "በአዳም ያሉ" ሁሉ ለማዳን የሚፈቅዱም ሆነ የሚችሉ አይደሉም። ክርስቶስ ሲፀነስ ኃጢአት በእርሱ ላይ ቢኖር ኖሮ፥ አምላክና ሰው ሊዋሐዱ ካለመቻላቸውም ሌላ፥ በኃጢአተኞች ምትክ መሥዋዕት ሊሆንም አይችልም ነበር። ደግሞም የኃጢአትን ፍርድ በፈቃደኝነት በመውሰድ፥ ያለ ኃጢአት ሆኖ ለኃጢአተኞች ከመሞት ይልቅ፥ ኃጢአት ለራሱ ኃጢአት ይሞት ነበር። ስለዚህ ስለ ክርስቶስ ከምናውቃቸው ነገሮች ሁሉ ተነሥተን እርሱ በተፀነሰ ጊዜ የአዳምን ኃጢአት አልወረሰም በማለት ለማጠቃለል እንችላለን።

5. የክርስቶስ ሰብአዊነት

ተግባራዊ ከሆነው ነገር አንጻር ስናየው የክርስቶስን የመፀነስ ሁኔታ ከመመርመር ይልቅ፥ በጣም አስፈላጊው ነገር ሰብአዊ ባሕርዩን አጥንተን የምንደርስበት ማጠቃለያ ነው። እዚህ ላይ የምናተኩረው በግምታዊ ነገር ሳይሆን በመገለጥ ላይ ነው። የምንደርስበት ማጠቃለያም የአካላዊ ሕልውናውን መሠረታዊ ትምህርት ለመወሰን በጣም አስፈላጊ ይሆናል። የመለኮትንና የሰብአዊነትን ውሕደት የምንመለከትበትን መሠረታዊ ትምህርት በዝርዝር ለማየት እንችልም። ይህ የሚቻለው፥ የመንፈስ ቅዱስ

ሥራ ውጤት በሆነው በክርስቶስ ሰብአዊነት ላይ ስናተኩር፥ ሰብአዊነቱ ሊለያይ በማይችል ሁኔታ ከመለኮት ጋር መዋሐዱ፥ ሁለተኛው የሥላሴ አካል እውነተኛ ሰብአዊነት እንደለበሰ ያለምንም መወሳሰብ ሊያረጋግጥልን ይሆናል።

የክርስቶስ ሰብአዊነት የተሠራባቸው ነገሮች። ለክርስቶስ ሰብአዊነት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ መሟላታቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጥ ይናገራሉ። ክርስቶስ ሥጋና ደም የሆነ፥ እንዲሁም ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር የሚያደርገውን ነገር የሚፈጽም እውነተኛ አካል ነበረው (ዕብ. 2፡14)። ቁሳዊ ያልሆኑት ክፍሎች ማለትም ነፍስ (ማቴ. 26፡38፤ ማር. 14፡34፤ ዮሐ. 12፡ 27፤ ሐዋ. 2፡27) እና መንፈስ (ማር. 2፡8፤ 8፡12፤ ሉቃስ 23፡46፤ ዮሐ. 11፡33፤ 13፡21) በሰብአዊነቱ ውስጥ ተካተዋል። አንዳንድ የአካሉ ባሕርያት ጊዜያዊ የሆኑና በታላቅ ክብር ከሞት ከተነሣ በኋላ የቀሩ ቢሆኑም፥ ሰብአዊነቱንና ፍጹም መሆኑን የሚያስቀሩ አይደሉም። አካሉ በትንሣኤ መቀየሩ የሥጋ ለባሽ ሁሉ ባሕርይ ነው። ክርስቶስ ከሞተ በኋላ በትንሣኤ መንፈሳዊ አካል የማግኘቱ ነገር በእርሱ የሞቱ ሁሉ በትንሣኤ የሚለማመዱት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጥ የሚያስተምሩት፥ ክርስቶስ ሥጋ በለበሰ ጊዜ የወሰደው መለኮት ያደረበትን የሰው አካል ብቻ ሳይሆን፥ ሰብአዊ ተፈጥሮንም መሆኑን ነው። ስለ ክርስቶስ ሥጋ መልበስ ስንናገር አንድ ሰው ውስጥ ማደሩን አይደለም፤ እንደዚያ ሆኖ ቢሆን ሁለት ሰውነት አለው ማለት ይሆን ነበር። ቻርልስ ሆጅ እንዳለው፡- "የእግዚአብሔር ልጅ ራሱን ከሰብአዊ ባሕርይ ጋር እንጂ ከሰብአዊ አካል ጋር አላዋሐደም። የዚህ ማስረጃችን የክርስቶስ አንድ አካልነት ነው።" የክርስቶስ ሰብአዊነት ሙሉ መሆኑንና፥ ከዚህ የተለየ አመለካከት ግን፥ ከተገለጠው እውነት እጅግ የሚያርቅ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል።

ኃጢአት የሌለበት ሰብአዊ ተፈጥሮ። ከሌላው የሰው ዘር ባሕርይ ሁሉ ጋር ሲነጻጸር፥ ክርስቶስ በቁሳዊም ሆነ ቁሳዊ ባልሆነ አካሉ ኃጢአት አልነበረበትም። ያለ ኃጢአት መሆኑ ለመለኮትና ለሰው መዋሐድ በጣም አስፈላጊ ነበር። ይህም ኃጢአት ቢኖርበት ኖሮ መለኮት ኃጢአት ካለበት ሰብእና ጋር በኋላ ይዋሐድ ዘንድ የማይቻለው እንደነበር ከዚህ እንረዳለን። የመለኮት ባሕርይ ወደ ሰው የሚተላለፍ ስላልሆነ፥ ሁለቱም ባሕርያት ለክርስቶስ ባሕርይነት የሚጠቀሱ ይሆናሉ። ስለዚህ ክርስቶስ ሰብአዊ ተፈጥሮው ኃጢአተኛ ቢሆን ኖሮ ይህ ባሕርይ በኖረው ነበር። ለማንኛውም የክርስትና መሠረታዊ ትምህርት የክርስቶስ ተፈጥሮ ያለ ኃጢአት መሆኑን መረዳት የግድ ነው። ለዚህም መጻሕፍት በርካታ ምስክርነት ይሰጣሉ (ኢሳ. 53፡9፤ ዮሐ. 8፡46፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21፤ ዕብ. 4፡15፤ 7፡26፤ 1ኛ

ጴጥ. 1፡19፤ 2፡22፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡5)። የክርስቶስ ከኃጢአት የተጠበቀ ተፈጥሮ፥ በመፀነሱ ወቅት የነበረ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጤት ነበር።

ሰብአዊ ተፈጥሮው የሰው ልጅ አካላዊ ውሱንነት ነበረው። የክርስቶስ ሰብአዊ ተፈጥሮ ከማንኛውም ኃጢአት የተጠበቀ ቢሆንም፥ ሰብአዊ ውሱንነትንም ይጋራል። ኃጢአትን ለማድረግ የማይችል ቢሆንም፥ ሰብአዊ ተፈጥሮው ፈተና ያለበትና ኃጢአትን ማድረግ የማያቅተው ነበር ለማለት ነው። ሁሉን አዋቂነቱ [Omniscience]፥ ሁሉን ቻይነቱ [Omnipotence]፥ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ መገኘቱና ወሰን የለሽነቱ [Omnipresence] በአጠቃላይ የክርስቶስ መለኮታዊ ባሕርያት ቢሆኑም ሰብአዊነቱ እነዚህ ባሕርያት ያሉት አልነበረም። ከኃጢአት ተፈጥሮ ሌላ የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ ከውድቀት በፊት ከነበረው የአዳም ባሕርይ ጋር ተመሳሳይ ነበር። ከመለኮታዊ ባሕርያቱ ሌላ ከሰው ተፈጥሮአዊ ባሕርይ የተለየ ወይም የተጨመረ ነገር በሰብአዊነቱ አልተገለጠም። ዋናው ልዩነት ግን የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ ከመለኮታዊ ባሕርይ ጋር የተዋሐደ መሆኑ ነው።

ክርስቶስ የዳዊት ዘር ነው። የክርስቶስ አፀናነስና አወላለድ ብዙ ያልተለመዱ ነገሮች ታይተውበታል። እነዚህ ነገሮች የተፈጠሩት እንዴት እንደሆነ ባናውቅም፥ ክርስቶስ የተወለደው የዳዊት ዘር ከሆነችው ማርያም መሆኑ ግልጥ ነው። በዚህም እንደ ሰው ከዳዊት ጋር እንዴት እንደተያያዘ እናያለን። ከኃጢአት በቀር የእስራኤል የዘር ባሕርይ በክርስቶስ ውስጥ እንደሚታይ ማረጋገጥ ይቻላል። ዘርን በተመለከተ ክርስቶስን እውነተኛ እስራኤላዊ አይደለህም ብሎ የከሰሰው የለም። እግዚአብሔር ዓላማውን በሙሉና ለዳዊት የገባውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም የክርስቶስ ከዳዊት ዘር መሆን አስፈላጊ ነበር። ስለ ሺህ ዓመት መንግሥት የተነገረው ትንቢትና እግዚአብሔር በምድር ያለው ዓላማ መፈጸም መሠረቱ የክርስቶስ ከዚህ ዘር መውጣት ነው። የክርስቶስ ሰብአዊነት እውን የሆነው በመፈጠር ነው የሚለው አሳብ ይህን አስተሳሰብ የሚያስቀር ባይሆንም፥ ከመፀነሱና ከመወለዱ ጋር የተያያዙ ተፈጥሮአዊ ክሥተቶችን ያጠቃለለ ነው።

ሰዎች፥ ስለ ክርስቶስ አፀናነስና አወላለድ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ተመሥርተው የሚሰጧቸው አመለካከቶች በጉጉት ለሚመለከቷቸው ሁሉ የሚያረካ መልስ የሚሰጡ አይደሉም። ነገር ግን እምነትንም ሆነ ምክንያትን የሚያረኩ በቂ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጠዋል። አፈጻጸሙ ባይገባንም፥ ክርስቶስ የተወለደው በመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ መሆኑ የተገለጠ እውነት ነው። ዘላለማዊ የሆነው ሁለተኛ የሥላሴ አካል ፍጹምና ያለ ኃጢአት ከሆነው ሰብአዊነት ጋር ለዘለላም ተዋሐደ። ይህ የሆነው እግዚአብሔር ራሱን ሊገልጥልንና የመዳንን መንገድ በክርስቶስ በኩል ይሰጠን ዘንድ ነው።

10

መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሕይወት

1. መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ የልጅነት ሕይወት

ክርስቶስ ሊወለድ አካባቢና አገልግሎቱን በሕዝብ መካከል በግልጥ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ ስላለው የልጅነትና ወጣትነት ሕይወቱ የሚታወቀው እጅግ በጣም ጥቂት ነው። የተወለደበት ወቅት ሁኔታዎችና የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በነበረ ጊዜ ቤተ መቅደስ ውስጥ መገኘቱን የሚጠቅሱ ታሪኮች ብቻ ይገኛሉ። ስለሆነም በዚህ የሕይወት ዘመኑ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስለነበረው ግንኙነት በሰፊው እንመለከተው ዘንድ የተገለጠልን ነገር ብዙ አይደለም። ጉዳዩ እንዲህ ቢሆንም፥ ከተገለጠልን ጥቂት ነገር በመነሣት ጠቃሚ ወደሆኑ በርካታ ነጥቦች ለመድረስ እንችላለን።

ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ከተፀነሰበት ዕለት ጀምሮ ነው። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እንደነበረበት በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ትንቢቶች በግልጥ ያስረዳሉ። እንደ ኢሳይያስ 11፡2-3፤ 42፡1-4 እና 61፡1-2 ያሉት ጥቅሶች ይህን በሚመለከት እጅግ ግልጥ የሆነ ማስረጃ የሚሰጡ ናቸው። ወንጌላትም የእነዚህን ትንቢቶች መፈጸም በተደጋጋሚ የተናገሩ ሲሆን፥ በተለይ ከተጠመቀ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ ግልጥ ሆኗል (ሉቃስ 4፡1)። ለጥያቄዎች ሁሉ የሚሆን ማስረጃ ለማቅረብ ባይቻልም፥ ከተፀነሰ ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱን ግን በበቂ ሁኔታ ልናመለክት የምንችለው ነገር ነው። ይህን አስተሳሰብ የሚደግፉ በርካታ ማስረጃዎችን ለማቅረብ ይቻላል።

በሥላሴ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ የሥላሴ አካላት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ማየቱ አያዳግትም። በዚህ ምክንያት የክርስቶስ አካል በድንግል ማርያም ማኅፀን ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና አብሮት እንደነበረና በመንፈስ ቅዱስም እንደተሞላ እናያለን።

መጥምቁ ዮሐንስ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ ተገልጧል (ሉቃስ 1፡15)። የክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ለሆነው ዮሐንስ ይህ በረከት ከሆነ፥ ለክርስቶስ እንደማይሆን መገመት አስቸጋሪ ነው።

በዮሐንስ 3፡34 መሠረት ለክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ ተሰፍሮ አልተሰጠውም። በእያንዳንዱ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር እንደሆነና አገልግሎቱም የተትረፈረፈ እንደነበር እንረዳለን። በዚህ ጥቅስ ውስጥ በግሪክ "መስጠት" የሚል ትርጉም የሚሰጠው ግሥ፥ በሰዋሰዋዊ አገባቡ የአሁን ጊዜን ለመግለጥ የተነገረ በመሆኑ፥ የሚገልጠው ነገር የሚቀጥልና እንደ ባሕርይ የሚታይ እንደሆነ ያመለክታል።

ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ከመፀነሱ ጀምሮ አይደለም የምንልበት አንዳችም ምክንያት የለም። አካላዊ ሕልውናው ከዘላለም ጀምሮ ቅዱስና ያለ ኃጢአት ስለነበር፥ የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት የሚያግድ አንዳችም ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ የነበረው ዓላማ ታላቅ ስለሆነና የመንፈስ ቅዱስ ሙላትም ከአካላዊ ሕልውናው ጋር መኖሩ የተረጋገጠ ስለሆነ፥ ክርስቶስ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስ በሙላት ነበረው ብለን ለማጠቃለል እንችላለን።

የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሙሉ ያሉት ነበር። የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ስለነበረ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሙሉ ነበሩት ለማለት ይቻላል። ማንኛውም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቷል ማለት፥ መንፈሳዊ ስጦታዎች ሁሉ አሉት ማለት አይደለም። ነገር ግን የአማኙ ሰብአዊ ባሕርያት በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ሆኗል ማለት ነው። በክርስቶስ አካላዊ ሕልውና ግን ሰብአዊ ባሕርይው ፍጹምና መንፈሳዊ ስጦታዎችን ሁሉ የያዘ ነው። ፍጹም በሆነው ሰብአዊነቱና በመለኮታዊ ባሕርዩ መካከል ያለውን ልዩነት በጥንቃቄ ለመመልከት መቻል አለብን። የክርስቶስን አካላዊ ሕልውና በሚመለከት ሁለቱም ነገሮች እውነት ቢሆኑም፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለሰብአዊ ተፈጥሮ ከተሰጡት ስጦታዎች ጋር የሚያያዝ ነው። የማስተማር፥ የአገልግሎት፥ የማስተዳደር፥ የመግዛት፥ ወንጌልን የመስበክ፥ የመጋቢነት፥ የማጽናናትና የመስጠት ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን እንደሚሠሩ ሁሉ፥ በክርስቶስም በከፍተኛ ደረጃ ተፈጽመዋል። ከዚህም ሌላ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ለጊዜው ብቻ የታዩት እንደ ትንቢት፥ ተአምራትን የማድረግ፥ የፈውስና መናፍስትን የመለየት ስጦታዎች በሙሉ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ በሙላት ሠርተዋል። በማንም ከተደረገው በላይ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሕይወት በሙላት ተገልጧል (ዮሐ. 3፡34)። እነዚህ ስጦታዎች ከመለኮታዊ ባሕርይ የመጡ ወይም ከጊዜ በኋላ ያገኛቸው ሳይሆኑ፥ ገና ከመፀነሱ ጀምሮ አብረውት የነበሩ ናቸው። ስለዚህ የክርስቶስ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ብቻ ሳይሆን፥ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በሙሉ የያዘ ከፍተኛ መገለጥም ነው።

የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ የሚያድግ ነበር። አካላዊ ሕልውናው ለዘላለም የማይለወጥ መሆኑ በዕብራውያን 13፡8፡- ‘‘ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው’’ በሚል ቃል ተገልጧል። ከዘላለም እስከ ዘላለም የማይለወጠው መለኮታዊ ባሕርዩ እንደሆነ ተደርጐ ነው ይህ ቃል መተርጐም ያለበት። ባሕርዩ የማይለወጥ ሆኖ፥ አካላዊ ሕልውናው ግን በሰብአዊ ባሕርይ ብቃት ሊጨምር መቻሉን እናያለን። መለኮታዊው ባሕርይ ለዘላለም የማይለወጥ ቢሆንም፥ ሰብአዊው ባሕርይ ለእድገት ለውጥ የተጋለጠ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክርልናል።

በክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ከምናያቸው ነገሮች አንዱ፥ በሥጋው እያደገ መሄዱን ነው። ሥጋዊ እድገቱ የተለመደውን ሰብአዊ የእድገት ፈለግ የተከተለ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ለክርክር ክፍተት ሳይተው ግልጥ አድርጐ አሳይቶናል። ክርስቶስ የተወለደው እንደ ማንኛውም ሕፃን ሲሆን፥ ቀጥለው ባሉት ዓመታት እንደ ማንኛውም ሰው ሙሉ ወደ መሆን እንዳደገ እናያለን። ይህ በሉቃስ 2፡40፥ 52 በግልጥ ቀርቧል፡- ‘‘ሕፃኑም አደገ...በጥበብና በቁመት በሞገስም።’’ የክርስቶስ ሥጋ ከተለመደው ተፈጥሮአዊ (አካላዊ) ባሕርይ፥ ገጽታና እድገት የተለየ ሁኔታ ባይታይበትም፥ ሙሉ በሙሉ ከኃጢአት የተለየና ፈጥኖ ማደግ የሚችል ነበር። በኃጢአተኛ ሰው ላይ የማይታይ ፍጹምነትም እናገኝበታለን። ስለ ክርስቶስ በምናስብበት ጊዜ፥ በተቃራኒ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው ነገር፥ ምናልባት ሥጋው ባልተለመደ ሁኔታ ጠንካራና ጸጋን የተሞላ፥ በዘር እየተላለፈ ለሰው ልጅ ሁሉ ከተረፈው ኃጢአታዊ ባሕርይ ነጻ ሆኖ የኖረ ነው የሚል ይሆናል። በተለይ በአሥራ ሁለት ዓመቱ በቤተ መቅደስ የተፈጸመው ታሪክ የሚናገረው ስለ አእምሮው ኃይል ቢሆንም፥ በሌሎች ሁኔታዎችም ከዕድሜው በላይ አድጐ እንደነበር ያመለክታል። በዚህ ስፍራ እንደ ወትሮው ሁሉን የማወቅ መለኮታዊነቱ ቢኖርም፥ አምላካዊ ባሕርዩ ግን በይፋ አይታይም።

ክርስቶስ በአካልና በጥበብ እንዳደገ በወንጌላት ተጽፏል። አካሉ ውስጥ ሰብአዊና መለኮታዊ የሆኑ፥ እንዲሁም እርስ በእርስ ሊነጻጸሩ የሚችሉ ባሕርያት ነበሩት። እነርሱም አላዋቂነትና ሁሉን አዋቂነት፥ ደካማነትና ሁሉን ቻይነት (አድራጊነት) ናቸው። እነዚህ ተቃራኒ የሚመስሉ ባሕርያት በአንድ አካል ውስጥ ለመኖር መቻላቸውን የምንረዳው፥ የባሕርያቱን እውነተኛ ተፈጥሮ፥ ማለት መለኮታዊነትንና ሰብአዊነትን ስናጤን ነው። ስለዚህ ከየትኛውም መለኮታዊነቱ ሳንለየው፥ የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ በእውቀትና በአእምሮ ብስለት ማደግ የሚችል እንደነበር ለመናገር እንችላለን። ይህም በሉቃስ 2፡40፥ 52 ክርስቶስ ‘‘ጥበብም ሞልቶበት’’ በተባለበትና ‘‘በጥበብ ያድግ ነበር’’ ተብሎ

በተጠቀሰበት ስፍራ በግልጥ ቀርቧል። ክርስቶስ ራሱ በሰብአዊው ባሕርይ በእውቀት ውሱን እንደነበር ተናግሯል (ማቴ. 24፡36፤ ማር. 13፡32፤ ዮሐ. 14፡10)። ይህ በጥበብ እያደገ መሄድ አብሮት በተነጻጻሪነት ከሚቀርበው ያለማወቅ ጋር እንዴት ሊገለጥ ይችላል?

በቅድሚያ ሰብአዊ ተፈጥሮ ሁሉን አዋቂ ሊሆን አለመቻሉ ግልጥ ነው። ሰው የቱንም ያህል በጥበብ ቢሞላ፥ ሰብዓዊ አእምሮው በመለኮት ካልተረዳ በስተቀር፥ የእግዚአብሔር ተፈጥሮ ብቻ የሆነው ሁሉን አዋቂነት ሊኖረው አይችልም። ሰብአዊ ተፈጥሮው እንደ ማንኛውም ሰው፥ አንዳንድ ነገሮችን ለመረዳት መገለጥን የሚሻ ቢሆንም፥ የክርስቶስ አእምሮ እስከዛሬ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ጥበበኛ አእምሮ መገለጫ ነበር። በሰብአዊነቱ ውስጥ ውሱንነት መኖሩ የሚታመን ቢሆንም፥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ግን አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ሥጋ ለለበሰው ክርስቶስ የተሰጠው፥ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፥ ኃጢአት ለማስወገድና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የሚያስችለውን እውቀት ለማደል ነበር። በአንዳንድ ሁኔታዎች፥ የእውቀት ጉድለት በፅንሰ- አሳብና በተግባራዊ ልምምድ ውስጥ ይታያል። ማለትም ክርስቶስ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ (ዕብ. 5፡8)። እርሱ ፈተናን ያወቀው በዚያው ውስጥ በማለፍ ነው (ዕብ. 2፡18)። በሁሉም ነገር ወደ ፍጹምነት ያደገው ባሳለፋቸው ነገሮች ነው (ዕብ. 2፡10)። እነዚህ ሁሉ ነገሮች በሰብአዊ ተፈጥሮ በኩል የክርስቶስ አካላዊ ባሕርያት ሆኑ።

2. መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጥምቀት አንጻር

የክርስቶስ በዮሐንስ እጅ መጠመቅ ብዙ ውይይት የሚያስነሣ ጉዳይ ነው። የጥምቀቱ አተረጓጎም የተለያየ ቢሆንም፥ የመሢሕነት አገልግሎቱ መጀመሩን የሚያመለክት ስለመሆኑ ሁሉም አስተሳሰቦች ይስማማሉ። ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ እንደተጠመቀና በዚህም ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ እንዳረፈበት በወንጌላት ተጽፏል። የዚህ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ትርጉም ምንድን ነው?

ጥምቀት መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ አገልግሎት መስጠት የጀመረበት ጊዜ መግለጫ አይደለም። ክርስቶስ ገና ከመፀነሱ ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ ተገልጧል። ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መውረድ አገልግሎቱን ለክርስቶስ እንደጀመረበት ጊዜ ተደርጐ ሊቆጠር አይገባም።

የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አዲስ ምዕራፍ። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ብዙ ጊዜ ከውጫዊ መግለጫ ጋር የተያያዘ ቢሆንም፥ ሁልጊዜ ግን

እንደዚያ መሆን የለበትም። ክርስቶስ ራሱን ለአገልግሎት ባዘጋጀባቸው ዓመታት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ቢሆንም፥ ከሌላው ጊዜ ጋር ሲወዳደር እነዚህን የዝግጅት ጊዜያት እንዴት እንዳሳለፈ ግልጥ አይደለም። በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በላዩ መውረዱ አዲስ የአገልግሎት ምዕራፍ መጀመሩን እንጂ፥ ግንኙነቱ የተለየ ለውጥ ማምጣቱን አያመለክትም። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክርስቶስ መሢሕ መሆኑን የሚያሳዩ ውጫዊ ምልክቶች መታየት መጀመራቸው፥ እንዲሁም የሠራቸው ተአምራትና የነቢይነት አገልግሎቱ ዋናዎቹ መረጃዎች ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መውረድ ውጫዊና የሚታይ እንደሆነ ሁሉ አገልግሎቱም ውጫዊና የሚታይ ነው።

የሥላሴ ሕንድነት ሕንደገና መገለጡ። ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ የተፈጸመው ነገር ስለ ሥላሴ በግልጥ ከሚያሳዩ ትምህርታዊ መረጃዎች አንዱ ነው። ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ እግዚአብሔር አብ ከሰማይ፥ ‘‘በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው’’ (ማቴ. 3፡17) በማለት ተናገረ። ከውኃው ውስጥ በመውጣት ላይ እንዳለ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወረደበት። ከዚህ የተሻለ ስለ ሥላሴ የሚገልጥ ነገር መሻት አያስፈልግም። በዚህ ክፍል የሥላሴ አካላት አንድነትም ተገልጧል። የክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነት በግልጥ ተነገረ። መንፈስ ቅዱስም በክርስቶስ ውስጥ በቋሚነት እንደሚኖር ተገለጠ። ሦስት አካላዊ ሕልውና ቢገለጥም አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንዳለ ግልጥ ነው።

3. መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ የነቢይነት አገልግሎት ውስጥ

ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ እንደ ነቢይ ኖሯል፤ እንደ ነቢይም አስተምሯል። ይህ አገልግሎቱ በፈጸማቸው ተአምራት የተረጋገጠ ሲሆን፥ ያልተለመዱ ትምህርቶቹ ደግሞ ብዙዎች ነቢይነቱን እንዲገነዘቡ አድርጓቸዋል። ክርስቶስ በፈቃዱ ሥጋ በለበሰ ጊዜ በተቀበለው ሰብአዊ ውሱንነት የተነሣ፥ ለነቢይነት አገልግሎቱ ሙሉ ለሙሉ የተደገፈው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ነበር። ይህን ግጠቃለያ ለመስጠት ክርስቶስ ራሱ ያስተማረውን መሠረት ለማድረግ ይቻላል።

የነቢይነት ሰጦታ ዋና ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን መገለጦችን በመስጠት ስለነበረው ከፍተኛ ሚና ቀደም ብለን በሰፊው ተመልክተናል። አዲስ ኪዳንም መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ መገለጥን የመስጠት አገልግሎት እንዳለው በግልጥ ይናገራል። ክርስቶስ በተለይ ስለዚህ ጉዳይ ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥቷል። ወንጌልን

በመስበካቸው ምክንያት በገዥዎች ፊት ለፍርድ ሲቀርቡ ምን መመለስ እንዳለባቸው እንዳያስቡና የሚናገሩትን የሚሰጣቸው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ለደቀ መዛሙርቱ ገልጦላቸዋል (ማቴ. 10፡19፤ ማር. 13፡11፤ ሉቃስ 12፡12)። ሐዋርያት ስለሚያስፈልጋቸው መንፈሳዊ መገለጥ ሲናገር ደግሞ፥ የነቢይነት አገልግሎታቸውን መፈጸም ይችሉ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ትምህርት እንደሚቀበሉ ተናግሯል (ዮሐ. 16፡13-14)። ሐዋርያት ለአብያተ ክርስቲያናት የጻፏቸው የተለያዩ መልእክቶችም ይህን ያረጋግጣሉ። ስለዚህ የነቢይነትን አገልግሎት ማከናወን የመንፈስ ቅዱስ የተለመደ ተግባር ነው።

ክርስቶስ ለመሰበክ በመንፈስ ቅዱስ ታቀባ። የነቢይነት አገልግሎቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስላለው ግንኙነት የሚናገሩ ቢያንስ ሁለት ጥቅሶች አሉ። በማቴዎስ 12፡18-21 ያለው አሳብ ከኢሳይያስ 42፡1-4 የተወሰደ ሲሆን፥ ይህ ትንቢት በእርሱ ሕይወት ውስጥ እንደተፈጸመ ተናግሯል። ከትንቢቱ የምንረዳው፥ መንፈስ ቅዱስ መሢሑን በነቢይነት ሥራው እንደሚያግዘው ነው። ከዚህ ጥቅስ ይበልጥ ማስረጃ የምናገኘው ክርስቶስ በናዝሬት ምኩራብ ባስተማረበት ወቅት ኢሳይያስ 61፡1-2ን በመጥቀስ፥ ‘‘ዛሬ ይህ የመጽሐፍ ቃል በጆሮአችሁ ተፈጸመ’’ (ሉቃስ 4፡21) ብሎ በተናገረበት ቦታ ነው። ለስብከት አገልግሎት ዝግጅት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚቀባ በኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት በክርስቶስ ሕይወት መፈጸሙን እናያለን። የመለኮት ባሕርያት በሙሉ በክርስቶስ ውስጥ የነበሩ ቢሆንም፥ በምድር በኖረበት ጊዜ በነበረው ውሱንነት ሳቢያ የነቢይነት ስጦታውን ለመለማመድ በመንፈስ ቅዱስ መደገፍን መረጠ። ክርስቶስ ይሰብክ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ‘‘ተቀባ’’። መንፈስ ቅዱስ ይሰጠው የነበረ አገልግሎት ነቢይነቱን በቋሚነት እንዲቀጥል አስቻለው።

4. መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ከፈጸማቸው ተአምራት ጋር ያለው ግንኙነት

ክርስቶስና ሐዋርያት በምድር የኖሩበት ጊዜ ምስክርነታቸው ይጸና ዘንድ በእግዚአብሔር ኃይል በእጃቸው የሚከናወኑ ታላላቅ ተአምራት በከፍተኛ ሁኔታ የታዩበት እንደሆነ እናያለን። መንፈስ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ የፈጸመውን ሥራ በምናጠናበት ጊዜ፥ እርሱ ካደረጋቸው በርካታ ተአምራት ጋር መንፈስ ቅዱስ ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ ለመጠየቅ እንገደዳለን። ይህን ግንኙነት የሚገልጡ በርካታ ጥቅሶች ባይኖሩም ከአንዳንድ ውሳኔዎች ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ በቂ ጥቅሶች ግን አሉ።

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተደረጉ የክርስቶስ ተአምራት። በወንጌላት ውስጥ ክርስቶስ ካደረጋቸው ተአምራት መካከል በተለይ ሁለቱ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት እንደሆኑ እናያለን። የመጀመሪያው የሚገኘው በማቴዎስ 12፡28 ክርስቶስ አጋንንትን የሚያወጣው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን ባመላከተበት ስፍራ ነው። ‘‘እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።’’ ክርስቶስ አጋንንትን ባወጣበት በብዙ ስፍራ፥ መንፈስ ቅዱስን ባይጠቅስ እንኳን፥ ይህ ጥቅስ ሌሎች ክፍሎችም ተመሳሳይ ሁኔታን እንደሚከተሉ የሚያሳይ ነው ለማለት እንችላለን። ሉቃስ 11፡20 ደግሞ ከላይ ማቴዎስ የመዘገበውን ታሪክ ሉቃስ በራሱ አገላለጥ የመዘገበበት ነው።

ተአምራትን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚያያይዘው ሁለተኛ ክፍል ደግሞ ሉቃስ 4፡14-15፥ 18 ነው። ከኢሳይያስ 61፡1-2 የተጠቀሰውና ከዚህ በፊት ያየነው ክርስቶስ ስለ ራሱ እንዲህ በማለት የተናገረው ነው፦ ‘‘የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፥ ለታሠሩትም መፈታትን፥ ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ፥ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል’’ (ሉቃስ 4፡18-19)። የዚህ ክፍል ዋና አሳብ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲቀጥል የተደረገውን የክርስቶስ የነቢይነት አገልግሎት ማወጅ ቢሆንም፥ ይህን አገልግሎቱን ያጠናከሩትን ማለት ‘‘ለዕውሮች ማየትን፥ ለታሠሩት መፈታትን’’ የመሰጠት ተአምራዊ ተግባርንም የሚያመለክት ነው። ይህ ከሆነ ተአምራት የተደረጉት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑ ግልጥ ነው። በሉቃስ 4፡14 ‘‘ኢየሱስ በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ’’ የሚለውን ቃል መጥቀስ ይቻላል። የመለኮት ኃይል በተለያየ መልክ መገለጡ መንፈስ ቅዱስ ስለ እርሱ ሆኖ የሚያከናውነው ሥራ ውጤት መሆኑን ያሳያል።

ክርስቶስ ተአምራትን በራሱ ኃይል ፈጽሟልን? ከዚህ በላይ ባየናቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች፥ ቢያንስ አንዳንዶቹ ክርስቶስ ያደረጋቸው ተአምራት የተፈጸሙት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን አረጋግጠናል። ብዙ ጊዜ የሚነሳው ጥያቄ ግን፥ ክርስቶስ በራሱ መለኮታዊ ባሕርይ ያደረጋቸው ተአምራት አሉ ወይ? የሚል ነው። የክርስቶስ ሥጋን መልበስና ውሱንነትን መውሰዱ ያለውን ማንኛውንም መለኮታዊ ባሕርይ አላስቀረበትም፤ ነገር ግን መለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርይውን ከሰዎች ጋር እንደሰው በማይጋጭ መልኩ እንዲኖር ራሱን የገለጠበት መንገድ ነው። የሰው ሥጋ መልበሱ ክርስቶስን በሰብአዊ ባሕርይ ብቻ አልወሰነውም። ሁለቱን ባሕርያትም ነጣጥለን ማየት አንችልም። ነገር ግን ሥጋ መልበሱ

ከሰዎች ጋር እንደ ሰው ለመኖር እንዲችል አድርጐታል። በመስቀል ላይ ከመሞቱ በፊት በነበረው ውሱን ሥጋ እንኳን በአምላክነቱ ሁሉን አድራጊ ነበር። ታዲያ ተአምራትን ያደረገው የሥላሴ ሁለተኛ አካል ነው ወይስ ሦስተኛው? ይህ ጥያቄ እንደ ነቢይነት ባሉ በሌሎች የክርስቶስ ሥራዎች ውስጥ ሊነሣ ይችላል።

ይህን ችግር በአጠቃላይ መፍታት የማይቻል ቢሆንም፥ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በግልጥ በሚታየው ሁለተኛ የሥላሴ አካል ኃይል፥ ክርስቶስ በምድር በነበረ ጊዜ ሊጠቀምበት ይችል እንደነበረና እንዳይጠቀምበትም ጨርሶ አለመታገዱን የምናይበት ነገር አለ። ክርስቶስ በምድር በነበረ ጊዜ ምርጫ ስላልነበረው ሳይሆን በፈቃዱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተጠቀመ። የክርስቶስን ተአምራት በሚመለከት ‘‘ኃይል’’ (‘ዱናሚስ’) የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ተጠቅሷል (ማር. 5፡30፤ ሉቃስ 5፡17፤ 6፡19፤ 8፡46)። ኃይሉ ከእርሱ የወጣ መሆኑም ተመልክቷል። የክርስቶስን ልብስ ጫፍ በመንካት ስለተፈወሰችው ሴት መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፥ ‘‘ወዲያውም ኢየሱስ ከእርሱ ኃይል እንደወጣ በገዛ ራሱ አውቆ’’ ይላል (ማር. 5፡30፤ ሉቃስ 8፡46)። እንደገና በሉቃስ 5፡17 ለፈውስ የተገለጠው ኃይል የክርስቶስ እንደነበረ ተገልጧል። ‘‘እርሱም እንዲፈውስ የጌታ ኃይል ሆነለት።’’ እንደ ሉቃስ 6፡19 አባባልም ፈውስን ለማምጣት ኃይል ከኢየሱስ ወጥቷል። በመጨረሻም ልንለው የምንችለው ነገር፥ ክርስቶስ ተአምራትን ያደረገው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን፤ በራሱም ኃይል ተአምራትን ለማድረግ ቢፈልግ ኖሮ ይችል እንደነበረና ምናልባትም አንዳንድ ጊዜ አድርጐት ይሆናል የሚል ነው። ስለ ሥላሴ አካላት የፈቃድና የተግባር አንድነት ያሰብን እንደሆን፥ ሁለተኛውና ሦስተኛው የሥላሴ አካላት ታላላቅ ተአምራትን እንደሚያደርጉ ማመን ይቻላል።

11

መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሥቃይና ክብር ውስጥ

1. *መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ሥቃይ ጋር ያለው ግንኙነት*

በጥናትና ጥሞና በአጭር ጊዜ ከማንጨርሳቸው ጉዳዮች አንዱ የክርስቶስ *ሥቃይ* ነው። ከዚህ ጥናት በርካታ ልብን የሚነኩ እውነቶችና መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ይወጣሉ። መንፈስ ቅዱስ ከዚህ ጉዳይ ጋር ያለው ግንኙነት የተጠቀሰው አልፎ አልፎ ቢሆንም፥ ክርስቲያኖች በመከራ ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ ከፍተኛና ጠቃሚ አገልግሎት እንደሚሰጣቸው የሚያስገነዝብ መልእክት አለው። መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር ስላለው ግንኙነት ከተገለጠልንና ከምናውቀው ነገር ተነሥተን፥ በመከራው ውስጥ ብርታትን እና ጽናትን የሰጠው እርሱ ነበር ለማለት እንችላለን። ይህን ጉዳይ የሚገልጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጥቂት ቢሆኑም፥ አገልግሎቱ የመንፈስ ቅዱስ መሆኑ ግልጥ ነው።

ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ በደረሰበት ሥቃይ መቅኖ መንፈስ ቅዱስ የነበረው አገልግሎት። በኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት በሕይወቱ ይፈጸም ዘንድ ክርስቶስ በምድር በነበረ ጊዜ፥ ‘‘የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ’’ ነበር (ኢሳ. 53፡3)። በመከራው ይጸና ዘንድ ማበርታት የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነበር። ወንጌላዊው ማርቆስ ከክርስቶስ ፈተና ጋር በተገናኘ ሁኔታ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ እንዳወጣው ጽፏል። ‘‘ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው’’ (ማር. 1፡12)። በምድረ በዳ እያለ ያገለገሉት መላእክት ቢሆኑም፥ ከፈተናው በኋላ ግን ‘‘ኢየሱስ በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ’’ ሲል ሉቃስ ጽፏል (ሉቃስ 4፡14)። ስለዚህ በቀጥታ የተገለጠ ነገር ባይኖርም፥ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን በሥቃይ እና ፈተናው ሰዓት እንዳገለገለው መናገሩ አስቸጋሪ አይደለም።

ይህን እውነት ለማረጋገጥ ጉዳዩን በሁለት አቅጣጫዎች መመልከት ይቻላል። የመጀመሪያው የሥላሴ አካላት ባላቸው አንድነት ረገድ እርስ በርስ መደጋገፋቸው ነው። እያንዳንዳቸው የሥላሴ አካላት በሁሉን ቻይነት ባሕርያቸው ለመጠቀም ነጻ ስለሆኑ የመደጋገፋቸው ጉዳይ

አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ሁለተኛው የሥላሴ አካል ግን በፍቃዱ ክብሩን በመተው ዝቅ በማለቱ፥ ሌሎቹ የሥላሴ አካላት ያገለግሉት ዘንድ ተገቢ ነበር።

ሁለተኛው አቅጣጫ ደግሞ ክርስቲያኖች በምድር ላይ እያሉ አጽናኝ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጣቸው የተትረፈረፈ አገልግሎት አንጻር የምንመለከተው ይሆናል። ቅዱሳን በማንኛውም የሕይወት ውጥረት ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሊያበረታቸውና ሊያጽናናቸው (ዮሐ. 14፡26፤ 15፡26)፥ ደግሞም የእግዚአብሔርን እውነት ሊያስተምራቸው ዝግጁ ነው።

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ የማያቋርጥ አገልግሎት ይሰጠው እንደነበር በመናገር ማጠቃለል ይቻላል። አዌን ሲጽፍ፦ ‘‘በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በገጠመው ፈተና፥ ችግር እና ሥቃይ መንፈስ ቅዱስ ይመራው፥ ያበረታውና ያጽናናው ነበር። በመንገዱና በሥራው ሁሉ እነዚህ ነገሮች ያጋጥሙት ነበርና። ለእኛ ብሎ ራሱን ዝቅ ያደረገበትን ትልቁን ክፍል የምናየው በዚህ ነው። ይህ እግዚአብሔር ቃል የገባለትና እርሱም የሚጠብቀው ነገር ነበር’’ ብሏል (ኢሳ. 1፡7-8፤ 42፡4፥ 6፤ 49፡5፥ 8)።

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት በደረሰበት ሥቃይ መንፈስ ቅዱስ የሰጠው አገልግሎት። እንደ ዕብ. 9፡14 አባባል፥ ክርስቶስ በሞተ ጊዜ ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ የሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ነው። ‘‘ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?’’ የሚለውን ቃል አተረጓጎም በሚመለከት የተለያዩ አመለካከቶች ተንፀባርቀዋል። ለምሳሌ ዌስትካት [Westcott] የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ የግሪኩን ቋንቋ ሰዋስዋዊ አጠቃቀም በመመርኮዝ ‘‘በዘላለም መንፈስ’’ የሚለው ቃል ስለ ክርስቶስ መንፈስ የሚናገር ነው ሲል፥ ሌሎች ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ። ለምሳሌ ሙል [Moule] የተባለ ሰው ከዌስትካት ተቃራኒ የሆነ አሳብ ያለው ሲሆን ስሚተን [Smeaton] የተባለው ደግሞ በቀጥታ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ ‘‘የዘላለም መንፈስ የሚለው ቃል አንዳንዶች እንደሚያስቡት የክርስቶስ መለኮታዊ መንፈስ ሳይሆን፥ ብዙ ጊዜ እንደምንቀበለው መንፈስ ቅዱስ ነው።’’ የግሪኩ ቃል ለሁለቱም ትርጉም የሚስማማ በመሆኑ፥ ወደ አንድ ማጠቃለያ መድረስ ያለብን በሥነ-መለኮት ትምህርት መሠረት ነው። ጥያቄው ክርስቶስ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው መላ አካላዊ ሕልውናውን

ነው ወይስ ሰብአዊ ባሕርዩን ብቻ? የሚል ነው። ስሚተን ሲጽፍ፦ ‘‘በዚህ ጥቅስ ውስጥ መለኮታዊ ባሕርዩን እንደ ካህን፥ ሰብአዊነቱን ደግሞ እንደ መስዋእት አድርጎ መውሰድ ትክክል አይደለም። መላ አካላዊ ሕልውናው ካህንም፥ መሥዋዕትም ነው። ሁሉም ነገር የሆነው በአካላዊ ሕልውናው ውስጥ ላሉ ሁለት ባሕርያት ነው። ሐዋርያው ‘ራሱን መሥዋዕት አደረገ’ ይላልና’’ ብሏል።

መንፈስ የሚለው መንፈስ ቅዱስን ከሆነ፥ ክርስቶስ ራሱን በመንፈስ ቅዱስ በኩል ለእግዚአብሔር የሰጠው እንዴት ነው? ምንባቡ ለዚህ አሳብ የሚጠቅም ምንም አይሰጠንም። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን አጠቃላይ አሳብ ስንመለከት፥ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ በሰጣቸው አገልግሎቶች አንጻር፥ በሞቱም እንደረዳው ለመናገር እንችላለን። ከሥጋ መልበሱ ጀምሮ እስከ መስቀል ሞቱ ድረስ ያለው ክንውን በሙሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑንም መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል። ክርስቶስ በምድር ላይ እንዲኖር የተደረገው በመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ፥ በሞቱም ያጸናው መንፈስ ቅዱስ ነው። በጌቴሴማኒ ባሳለፈው ከባድ የመከራ ሰዓትና ወደ መስቀሉ በመሩት ሌሎች ወሳኝ ጊዜያት ሁሉ ለክርስቶስ በታማኝነት አገልግሏል።

. . . . ክርስቶስ በመስቀል ላይ እያለ በመዝሙር 22፡1 ስለ እርሱ የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ ‘‘አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውከኝ?’’ በማለት በታላቅ ድምጽ ጮኸ (ማቴ. 27፡46)። ራሱን አሳልፎ የሰጠው በእግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚለውን እውነት ሳንለውጥ፥ ለእርሱ የነበረው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በዚህ ስፍራ ተቋርጦ ነበር ለማለት እንችላለን። መንፈስ ቅዱስ፥ ክርስቶስ ውሳኔ አድርጎ ወደ መስቀሉ የሚወስደውን ዘላለማዊ የእግዚአብሔር እቅድ ሲፈጽም እርዳታ ቢያደርግለትም፥ የኃጢአትን ሸክም ሊሸከም የቻለ ክርስቶስ ብቻ ነበር። በዚህ ተግባር መንፈስ ቅዱስ ሊያግዘው አይችልም ነበር።

በክርስቶስ የመስቀል ሥቃይ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የነበረው ሥራ ሰብአዊ ባሕርዩ በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ እንዲቆይ ማድረግ፥ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲያስገዛና ትእዛዙን እንዲጠብቅ መርዳት፥ እንዲሁም ወደ መስቀል በሚያመራው ጎዳና እንዲጠነክርና እንዲበረታ ማድረግ ነበር። በዚህ ሁሉ የሚያገለግለው የክርስቶስን ሰብዓዊ ባሕርይ፥ በእርሱም በኩል የክርስቶስን አካላዊ ሕልውና ነበር። ብሩህ የሆነ አእምሮ፥ ይህ ወሰን የሌለው እውነት ሙሉ በሙሉ ልንረዳ የማይቻለን መሆኑን መመስከር አለበት።

2. መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ትንሣኤ እና መክበር ጋር ያለውን ግንኙነት በሚመለከት

መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ራሱን ባዋረደ ጊዜ ድርሻ እንደነበረው ሁሉ፥ በትንሣኤና በመክበሩም ውስጥ ድርሻ እንደሚኖረው የሚጠበቅ ነበር። ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ይህን ጉዳይ በሚመለከት ሙሉ አሳብ አልሰጡም፤ ወይም የሰጡት አሳብ እጅግም ግልጥ አይደለም።

ሥላሴ ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር ያለው ግንኙነት። መጽሐፍ ቅዱስ በሥላሴ አካላት መካከል ልዩነት ሳያደርግ፥ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው እግዚአብሔር መሆኑን በተደጋጋሚ ይናገራል። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 2፡24 ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ ሲናገር፥ ‘‘እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሳው’’ ብሏል። ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት ሙታንን በማስነሣት በሞት ላይ ያለውን ኃይል ገልጧል። ለማርታም፥ ‘‘እኔ ትንሣኤ እና ሕይወት ነኝ’’ ብሏታል (ዮሐ. 11፡25)። በዮሐንስ 10፡17-18 ላይ ደግሞ እንዲህ በማለት አስታውቋል፦ ‘‘ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።’’ የክርስቶስ ትንሣኤ የተከናወነው በራሱ ኃይል መሆኑን ከሚናገረው ከዚህ ክፍል ጋር ሲነጻጸር፥ ኤፌሶን 1፡17-20 ክርስቶስን ከሞት ያስነሣው እግዚአብሔር አብ መሆኑን ይናገራል። እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር ወልድ ሁለቱም በክርስቶስ ከሙታን መነሣት ውስጥ ድርሻ ካላቸው ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን እንላለን?

መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር ያለው ግንኙነት። መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ትንሣኤ ውስጥ ያለውን ድርሻ የሚያሳዩ ሦስት ዋና ዋና ጥቅሶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። ሮሜ 8፡11፥ ‘‘ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።’’ ‘‘እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ’’ የሚለው አገላለጥ ለዚህ ሚች ሥጋችን ሕይወት መስጠት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ክፍሉን የመተርጎም ችግር ቢኖርም የቃሉ ትክክለኛ አነባበብ እና ትርጉም እንደዚህ መሆኑ አያጠራጥርም። ‘‘ሕይወት’’ የሚለው ቃል ወደፊት በቅዱሳን ትንሣኤ የሚሰጠው ‘‘የትንሣኤ ሕይወት’’ ሳይሆን አይቀርም። ካልቪን ግን ቃሉን ሲተረጉም ይህ ሕይወት አሁን ያለንበት መንፈሳዊ

ሕይወት ነው በማለት ሆጅ ሊያስተባብለው የሞከረውን አሳብ አቅርቦ ነበር። ለዚህ ቃል የተሻለ ትርጉም ነው ብለን የምንገምተው ግን በቅዱሳን ትንሣኤ ስላለው ሥራ የሚናገር ነው የሚለውን አሳብ ነው። የዚህ ጥቅስ መጀመሪያ ክፍል ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ የሚናገር መሆኑ ግን በሚገባ ግልጥ አይደለም። ‘‘ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ’’ እንጂ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ከሞት አነሳው አይልም። ‘‘መንፈስ’’ የሚለው ቃል ምናልባት መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ቢሆን እንኳ፥ ‘‘የእርሱ’’ የሚለው ቃል ‘‘ከሙታን ያስነሣው እርሱ’’ በሚለው ቃል ውስጥ እንዳለው ‘‘እርሱ’’ እንደሚለው ቃል ይበልጥ አብን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ይህ አሳብ ሲጠቃለል መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ከሙታን ካስነሣው ከአብ ዘንድ ስለሆነ የእኛም ትንሣኤ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን በማደሩ የተረጋገጠ ሆኗል ከሚል አሳብ ላይ እንደርሳለን። ስለዚህ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ልንል የምንችለው ነገር ቢኖር፥ በክርስቶስ ትንሣኤ ውስጥ ድርሻ ነበረው ብቻ ነው።

ሁለተኛው ክፍል የሚገኘው ‘‘በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ’’ የሚለው ቃል በተጻፈበት በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡18 ነው። ከእውነተኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት አንጻር ጥቅሱ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያመለክታል ማለት ይቻላል። ክርስቶስ ምንም የመንፈሳዊ ሕይወት ተሐድሶ የሚያስፈልገው አልነበረም። የሥጋ ትንሣኤ ግን ያስፈልገው ነበር። ይህ አሳብ በመነጻጸር እንዲህ በሚል አባባል ተጠቅሷል፦ ‘‘በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ።’’ ‘‘በመንፈስ’’ የሚለው አባባል የሚያመለክተው በቀጥታ የሥጋ ትንሣኤን ነው። ይህ ማጠቃለያ ከዚህ ጥቅስ ቀጥሎ ባለው ምንባብ ላይ በሚደረግ ትንታኔ ለሚገጥም ችግር መፍትሔ ይሆናል። በቁጥር 19 ላይ ያለውና ‘‘በእርሱም’’ የሚለው ቃል ከመንፈስ ጋር እንጂ፥ ያለ አካል መንፈስ ሆነ የማለት አሳብ የለውም። የመጽሐፍ ቅዱስ አስረጂዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ያላቸው አሳብ ቢከፋፈልም እና ለዘብተኞች መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ትንሣኤ ውስጥ ድርሻ እንዳለው ለመካድ ቢሞክሩም፥ ይህ ክፍል መሠረታዊውን ትምህርት የሚደግፍ መረጃ ሆኗል።

በሮሜ 1፡4 የሚገኘው ሦስተኛ ክፍላችን ይሸውም ‘‘የቅድስና መንፈስ’’ የሚለው ቃል፥ ከሦስተኛው የሥላሴ አካል ይልቅ የክርስቶስን ቅዱስነት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ካልቪን ይህን አገላለጥ ለመንፈስ ቅዱስ የተጠቀመበት ቢሆንም፥ ያ ክፍል መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት አይደለም ያለው ሆጅ ትክክል ሳይሆን አይቀርም። መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ትንሣኤ ውስጥ ስላለው ድርሻ ቅዱሳት

መጻሕፍት የሚሰጡት ምስክርነት በሁለት አከራካሪ አሳቦች የተከፈለ ሲሆን፥ የተሻለ ክብደት ያለው ግን 1ኛ ጴጥሮስ 3፡18 ብቻ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ከሞት በማስነሣት ሥራ ውስጥ የነበረው ድርሻ በትክክል አልተገለጠም። አዌን፡- በመቃብር የነበረውን የክርስቶስን ሙት አካል ቅዱስና ከማንኛውም በተፈጥሮ ሂደት የሚመጣ መበስበስ ነጻ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነው የሚል እምነት አለው። ምንም እንኳን ይህ የአዌን አሳብ ከመዝሙር 16፡10 ከተገለጠውና አካሉ መበስበስን እንደማያይ ከሚያመለክተው አሳብ ጋር የሚስማማ ቢሆን፥ አሳቡ የአመለካከት ዓይነት ብቻ ተደርጐ ሊቆጠር የሚገባ ነው። የበለጠ እርግጠኛ የምንሆነው የክርስቶስ ትንሣኤ፡- መንፈሳዊ አካል ማብጀትን፥ ከውጫዊ አካል አንጻር የቁሳዊነትንና የመንፈሳዊነትን ባሕርይ መያዝን ያካተተ በመሆኑ ነው። መፍጠር እና በትንሣኤ ሕይወትን መስጠት በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ውስጥ መሆኑ፥ የክርስቶስ ነፍስና ሥጋ እንደገና መዋሐድ ከመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ጋር የሚስማማ ነው። የትንሣኤ ክንውን ከማንኛውም ተአምራዊ ድርጊት ይልቅ የእግዚአብሔርን ኃይልና ክብር ያሳያል።

መንፈሰ ቅዱስ ከክርስቶስ መካበር ጋር ያለው ግንኙነት። ከተመለከትነው ማስረጃ በመነሣት መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ትንሣኤ ውስጥ ድርሻ እንደነበረው ሁሉ በመካበሩ ውስጥም ድርሻ እንዳለው ለማሰብ እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለዚህ ጉዳይ የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም። ካይፐር፥ ‘‘በክርስቶስ ከፍ ከፍ ማለት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያለው ድርሻ በቀላሉ የሚገለጥ አይደለም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ከክርስቶስ ዕርገት፥ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ መቀመጥም ሆነ ከዳግም መምጣቱ ጋር መንፈስ ቅዱስ ስላለው ግንኙነት የሚናገረው ነገር የለም’’ ብሏል። ከመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ አንጻር ያየነው እንደሆነ እርሱ ከአዳኛችን የተባረከ ንጉሣዊ ግዛት ጋር ግንኙነት ሳይኖረው አይቀርም ብለን ማሰብ እንችላለን። በእኛ ውስጥ በሚሠራው ሥራ፥ በከበረው አዳኛችንና በውስጣችን ባደረው መንፈስ ቅዱስ መካከል እጅግ የጠበቀ ግንኙነት አለ ብለን ልንቀበል እንችላለን። የክርስቶስን ሥቃይና ሞት ብቻ ሳይሆን የትንሣኤውን ኃይል፥ የጸጋውንና የክብሩን ባለጠግነት ከመንፈስ ቅዱስ ተምረናልና። መንፈስ ቅዱስ ወሰን በሌለው ጊዜና ሁኔታ ክርስቶስን በሁሉም መንገድ እንዳገለገለ፥ ለክርስቲያንም በሥጋዊ ኑሮውም ሆነ፥ ኋላ በመካበሩ የሚሰጠው አገልግሎት ወሰን የሌለውና አስደናቂ ነው።

— ክፍል አራት —

መንፈስ ቅዱስ በደኅንነት ሥራ

12

ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ

1. መለኮታዊ ቸርነት እና ሉዓላዊነት

የእግዚአብሔር ቸርነትና ሉዓላዊነት ትምህርት፥ የአምላክ ኃይል በዳነው ላይ ብቻ ሳይሆን፥ ባልዳነው ዓለም ላይም እንደሚሠራ ያስተምራል። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በቅድሚያ ለክርስቲያኖች ቢሆንም፥ የእግዚአብሔር አብን እና የእግዚአብሔር ወልድን ፈቃድ በዓለም ውስጥ ለመፈጸም እንደሚሠራም የተረጋገጠ ነው። ዝብርቅርቅ ባሉና ኃጢአት በሰፈነባቸው ወቅቶች ውስጥም መንፈስ ቅዱስ የሚሠራ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጥልናል። በዘፍጥረት 1፡2 የተጠቀሰው ሁኔታ መሬት ያለ መንፈስ ቅዱስ ነበረች ማለትን አያመለክትም። በኖኅ ዘመን የነበረው ኃጢአተኛ ትውልድም ከኃጢአቱ በመንፈስ ቅዱስ ታግዶ ነበር (ዘፍጥ. 6፡3)። በብልሹው ዘመነ መሳፍንት ጊዜ፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታጠቀው ሳምሶን ኖሯል። ከምርኮ በፊት በእስራኤል ውድቀት ዘመን የነበሩ ነቢያት በኃጢአተኛና በማያምን ሕዝብ መካከል ለማገልገል፥ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ኃይል የሚያሳዩ ሕያው ምስክሮች ነበሩ። በአዲስ ኪዳንም እግዚአብሔር፥ ‘‘ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ’’ እንደሚፈልግ እንድናውቅ ተጽፏል (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በየትኛውም ዘመን ለሚኖረውና ላላመነ ትውልድ፥ በተለይ ደግሞ በዓለም ባለችው ቤተ ክርስቲያን በቋሚነት በሚኖርበት በዚህ የጸጋ ዘመን፥ የተለየ አገልግሎት እንዳለው ለመመልከት እንችላለን።

2. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ መጠን

መንፈስ ቅዱስ ላልዳኑ ሕዝቦች የሚሠራው ጠቅላላ ሥራ አንዳንድ ጊዜ ‘‘ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ’’ [Common Grace/ካመን ግሬይስ] በመባል ይታወቃል። ይህ ሥራ ኃጢአት መከልከልንና ወንጌል የመግለጥ ተግባርን ሁሉ ይጨምራል። ለምሳሌ ቻርልስ ሆጅ ለሁሉ ስለተሰጠ ጸጋ ሲናገር፦ ‘‘መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም አቅጣጫ ይሁን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፥ እርሱ የእውነት፥ የቅድስናና የሕይወት መንፈስ በመሆኑ ሰዎች እውነትን እንዲቀበሉና እንዲያውቁ በአእምሯቸው ላይ ተጽዕኖ በማድረግ፥ ኃጢአትን በመከልከል፥ ለእውነት በማነቃቃት፥ ጥበብንና ብርታትን በመስጠት መልካም በምንለው ሁኔታ ውስጥ ሁሉ አለ... ይህን ነው በሥነ-መለኮት ቋንቋ ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ የምንለው’’ ብሏል።

ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጆን ካልቪን በሚከተለው መልክ ገልጦታል፦

“ለሰው ልጆች የጋራ ጥቅም የሚውሉ እጅግ አስደናቂ የሆኑ መለኮታዊ የመንፈስ ስጦታዎች፥ እርሱ ደስ እንደሚለውና እንደሚፈቅድ የሚያከፋፍላቸው መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። ለማደሪያው ድንኳን ግንባታ ያስፈልግ የነበረን ጥበብ እና ችሎታ የእግዚአብሔር መንፈስ ለባስልኤልና ለኤልያብ መስጠት የነበረበት ስለዚህ ነው። በሰው ልጅ ሕይወት እጅግ አስደናቂ የምንላቸው እውቀቶች በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት ቢገለጡልን ልንደነቅ የማይገባንም ከዚህ የተነሣ ነው። ይህን በማድረጉም እግዚአብሔር ከኃጢአተኞች ጋር ግንኙነት መፍጠሩ ለምንድነው ብለን የምንጠይቅበት ምክንያት የለም። ታማኝ በሆኑ ሰዎች ላይ ስለሚያድረው የእግዚአብሔር መንፈስ በምንናገርበት ጊዜ፥ እኛን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አድርጎ የቀደሰንን መንፈስ ማለታችን ነው። እንዲሁም የዚህ መንፈስ ኃይል እንደ ተፈጥሮ ሕግ ፍጥረታት እንዲባዙ፥ የተፈጥሮ እንቅስቃሴያቸውም በሥርዓቱ እንዲቀጥል፥ የዝርያቸውም ባሕርይ እንዲጠበቅ ያደረገ ነው። ስለዚህ በፊዚክስ፥ በሎጂክ [Logic]፥ በሒሳብና በሌሎችም የሳይንስ ጥበቦች እንረዳ ዘንድ ጌታን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፥ እግዚአብሔርን በማይፈሩ ሰዎች ድካም እና አገልግሎት የተገኙ ቢሆኑ እንኳን ልንጠቀምባቸው ይገባል። ከእግዚአብሔር የተለገሱንን እነዚህን ነጻ ስጦታዎች ከመጠቀም ቸል ብንል ቸልተኝነታችን በሚያስከትለው ውጤት ከመሠቃየት በቀር ምርጫ የለንም።”

3. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ጠቃሚነት

መንፈስ ቅዱስ ላልዳኑ ሰዎች ወንጌልን ለመግለጥ የሚያከናውነው ሥራ፥ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለመፈለግ ከሚያከናውነው ሰፊ ሥራ አንዱና ዋናው ነው። ወንጌልን ያለ እርሱ እርዳታ መረዳት አይቻልም። ሥራው ወንጌልን ለመስበክና በክርስቶስ ኢየሱስ በሚሆን እምነት ሁለንተናዊ ጥረት ማድረግን ለመግለጥ የታቀደ ነበር። “ለሁሉም የተሰጠ ጸጋ” እግዚአብሔር ለተመረጡት ከሚያደርገው “ውጤታማ ጥሪ” የሚቀድም ነው። ወንጌልን ለዓለም በመግለጥ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊነቱ፥ ከእግዚአብሔር እቅድ አንጻር ብቻ ሳይሆን፥ ወንጌል በሚገባ እንዲሰበክ ከማድረግ ጭምር ነው። ነፍሳትን ለክርስቶስ ለመማረክ ፍላጎት ያለው ክርስቲያን ሁሉ ይህን ጉዳይ በጥንቃቄ ማጥናት አለበት። ምክንያቱም እግዚአብሔር ባልዳኑ ነፍሳት ላይ ስላለው አሳብ መመሪያ የሚሰጥ ስለሆነ ነው።

ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ሊነጣጠሉ በማይችሉ ሁለት ጠቃሚ ክፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

አንደኛው፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከመለኮታዊ የቸርነት ሥራ ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ ኃጢአትን በመከልከልና የዓለምን የኃጢአት ሂደት በማገድ የሰውን ልጅ ታሪክ በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ እንዲዋጥ ማድረግ ሲሆን፥ ሁለተኛው፥ የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያመለክቱ መገለጦች የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ሲሆኑ፥ የመዳንን መንገድ በተፈጥሯዊ አእምሮው መረዳት ለማይችለው ሰው የደኅንነትን መንገድ ተረድቶት እንዲቀበለው ማድረግ ነው። በዘመነ ክርስትና ሁሉ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ትኩረት፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የደኅንነትን መንገድ ለጠፉ ነፍሳት ማመልከትና የሚያድን እምነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ይህን አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ለመደገፍ የምናቀርባቸው ጥቅሶች ጥቂት ቢሆኑም፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር ግን እጅግ አስፈላጊ ነው።

ከዓለም ጋር ግንኙነት ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከበርካታ ምክንያቶች የተነሣ በጣም አስፈላጊ ነው። ሰይጣን ኃይል አለው፤ ክርስቲያኖችንና እውነትን ይጠላል። ስለዚህ ለወንጌል ስርጭት አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ ለማመቻቸትና በኃጢአተኛው ዓለም ውስጥ ሥርዓትን ለማስከበር ይህን ኃይል መታገል ያሻል። በመሆኑም ኃጢአትን ከመከልከልና ክርስቲያን በዓለም ሳለ የሚኖረውን አንጻራዊ ነጻነት ከማብራራት አኳያ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን ለጠፉ ነፍሳት የመግለጥ ሥራ፥ በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የመጥራት ሥራውን ለመፈጸም እጅግ አስፈላጊ ነው። የሰውን ድካም በማገዝ ነፍሳት እንዲድኑ ያደርጋል። ስለዚህ ይህ መሠረታዊ ትምህርት የወንጌል ሥራ ሙሉና አርኪ ውጤት እንዲያገኝ በማድረግ ጠቀሜታ አለው።

4. የጸጋ ለሰው ልጅ አስፈላጊነት

የአዳም ውድቀት ብዙ ችግሮችን አስከትሏል። ከእነዚህም መካከል ኃጢአት ወደ ሰው ዘር ሁሉ መተላለፉ፥ የሰዎች ከክርስቶስ ተለይተው መንፈሳዊ ሞት መሞታቸው፥ በግልጥ የሚታይ የውድቀት ባሕርይ መያዛቸውና ለዚህ ጥናታችን በጣም አስፈላጊ የሆነውን ጉዳይ፥ ማለት የእግዚአብሔርን እውነት ለመረዳት አለመቻላቸው ይገኙበታል። የሰው ልጅ ደካማ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ መስክሯል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 2፡14፥ ‘‘ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም’’ ተብሎ በቀጥታ ተጽፏል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡18 ደግሞ ወንጌል ለሚጠፉት ሞኝነት እንደሆነ ተገልጧል፦ ‘‘የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።’’

ያልዳኑ አሕዛብ በጨለማ እንደሚመላለሱም ተገልጧል፦ ‹‹እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸው ደንዳናነት ጠንቅ ልቡናቸው ጨለመ፤ ከእግዚአብሔርም ሕይወት ራቁ›› (ኤፌ. 4፡18)። በሮሜ 8፡7 መሠረት ፍጥረታዊ አእምሮ ለእግዚአብሔር ሕግ መገዛት አይችልም፦ ‹‹ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና መገዛትም ተስኖታል።›› ክርስቶስ በዮሐንስ 6፡44፥ ‹‹የላከኝ አብ ካሰበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም›› ማለቱ ተፈጥሮዊው ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት እንደማይችል መናገሩ ነው ። ከፍጥረታዊ የብቃት ጉድለት ሌላም ሰይጣን የጠፉትን ሰዎች ልብ አሳውሯል (2ኛ ቆሮ. 4፡4)። እግዚአብሔር ካልረዳውና ሁኔታዎችን ካልለወጠለት በቀር የሰው ልጅ ተስፋ በሌለው ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ፍጡር ነው።

በሰው በኩል ጉድለት (ያለመብቃት) የሚመጣው ጠቅላላ አቋሙ የተበላሸ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔርንና ጸጋውን ባለማወቅ ስሜቱን፥ ፍላጎቱንና አዝማሚያውን ብቻ ሲያጣምምና ማስተዋሉ ሲጨልምበት ነው። የሰው ልጅ በኃጢአት በመውደቁ ክፉ እና ደግን የመለየት አቅሙን አላጣም። ከውድቀት በኋላ እንኳን ኃላፊነት ያለበትና አንጻራዊ ነጻነት ያለው ነው። የማስተዋል ችሎታው እስካሁን ስላለ ምናልባት በዚህ አንጻር ያልተለመደ ብርታት ልናይበት እንችላለን። ለመልካም ነገር ያለው የተቃና አሳብ መጣመምና የክፋት አዝማሚያ ከወደቀው ተፈጥሮው የመነጨ ሲሆን፥ መነሻው ደግሞ በተፈጥሮው ጽድቅ ወዳድ የሆነውን እግዚአብሔር ለመቀበልና በዚያም ደስ ለመሰኘት ፈጽሞ አለመቻሉ ነው። የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እንዲጠላ የሚያደርገው ዋነኛ ምክንያት እርሱን አለማወቁ ነው። የሰው ፈቃድ፥ የተፈጥሮ ብቃትን የማለፍ ኃይሉ፥ ከሰው ልጅ ውድቀት በፊትም ሆነ አሁን ምንም ልዩነት የለውም። በራሱ የእግዚአብሔርን እውነት ለመረዳት ጨርሶ አይችልም። ስለዚህ የዚህ ችግር መፍትሔ የሚገኘው፥ ፍጥረታዊ ሰው በሚደርስበት የእድገት፥ ወይም የተዳፈነ ችሎታን በማነልበት ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ኃይል በሚገለጥበት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ከዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጭ እግዚአብሔር ለጠፋው የሰው ዘር ሳይገለጥ የሚቆይ፥ የክርስቶስ ሞትም ለሰው ልጅ የማይጠቅም፥ እግዚአብሔር የተመረጡትን ለማዳን የነበረው ዓላማም ሊሟላ ጨርሶ የማይችል ይሆን ነበር። ስለዚህ የዚህ መሠረታዊ ትምህርት ጠቃሚነት ጠንቃቃ ጥናትን የሚጠይቅ ይሆናል።

5. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ባሕርያት

አስቀድመን እንደገለጥነው ‹‹ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ›› የሚለው ቃል መንፈስ ቅዱስ በዓለም ላይ ስለሚያከናውነው ሥራ የሚናገሩ ብዙ አሳቦችን የሚያጠቃልል ነው። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ፥ የሰው ዘር የእግዚአብሔርን ነገር

ለመቀበል ያለበትን ችግር ለመረዳት ልዩ አስተዋጽኦ አለው። በዚህ ስሜት ስናየው ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ በማንኛውም ጊዜ በምንም ዓይነት መንገድ የተሰጠውን የእግዚአብሔር እውነት የሚገልጥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው። አርምኒያን [Arminian]* የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ይህን ጸጋ "በቂ ጸጋ" [Sufficient Grace/ሰፈሽንት ግሬይስ] ብለው ይጠሩታል። ይህን የመሰለና ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ እምነትን ሊያመጣ የሚችል የተሟላ መገለጥ ይሰጣል ይላሉ። "ውጤት አስገኝ ጸጋ" [Efficacious Grace/ኤፊኪሸስ ግሬይስ]፥ ወይም "የማይገታ ጸጋ" [Irresistible Grace/እሪዚስተብል ግሬይስ] በመባል የሚታወቀውም ቢሆን በዚሁ እውነት ክልል ውስጥ ያለ ሲሆን፥ በባሕርይና በአሠራሩ ግን የተለየ ነው። ውጤት (ወይም 'ሥርየት') አስገኝ ጸጋ የምንለው፥ ወንጌልን ውጤታማ በሆነ መንገድ በመግለጥ ሰዎችን ወደሚያድን እምነት የሚመራ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው። ይህን የጸጋ ጉዳይ፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጤትን በሚያስገኝ ጸጋ ውስጥ፥ በሚለውና በሚቀጥለው ምዕራፍ በሰፊው እንመለከተዋለን።

ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያለው ግንኙነት። የእግዚአብሔር ቃል ለጠፉ ነፍሳት መሰበክ እንዳለበት ቅዱሳት መጻሕፍት አበክረው ይናገራሉ። ወንጌላችን "የማዳን ኃይል ነውና" (ሮሜ 1፡16)። ሰዎች ደግሞ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ ታዘዋል። ለዚህ ነው ጳውሎስ ይህን ጥያቄ በማንሣት "ካልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?" (ሮሜ 10፡14) ብሎ "እምነት ከመስማት ነው መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው" ወደሚል ማጠቃለያ (ሮሜ 10፡17) የደረሰው። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ የተጠቀሰው፥ እግዚአብሔርንና ጸጋውን ለዓለም ለመግለጥ የሚያገለግል መለኮታዊ መንገድ ነው። ይህ ቃል ነው የመንፈስ ሰይፍ ተብሎ የተጠራው። እግዚአብሔር ራሱን ለመግለጥ ሲፈልግ ሌሎች የተለያዩ መንገዶች ቢኖሩትም የደኅንነትን መንገድ ለሰው ልጅ የገለጠው ሊሰበክና ሊነበብ በሚገባው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በአንድ ወይም በሌላ መልክ ቅዱሳት መጻሕፍት ባይሰጡን ኖሮ ደኅንነት ሊገኝ አይችልም ነበር። ስለዚህ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመምራት የሚፈልጉ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ አለባቸው።

እንደ ጥምቀትና ቅዱስ ቁርባን ያሉት ቅዱሳት ምሥጢራት ለወንጌል ምስክርነት የሚያበረክቱት ድርሻ አላቸው። የእነዚህ ምስጢራት ጥቅም በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከሚገባ በላይ ስፍራ የተሰጣቸው ቢሆንም፥ የወንጌልን መልእክት በአምሳያነት ለመግለጥ የየራሳቸው ስፍራ

* የአርምኒያን [Arminian] የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ስማቸውን የወሰዱት የዚህ ትምህርት ጀማሪ ከነበረው ከጀኮበስ አርምኒየስ [Jacobus Arminius] ነው። አርምኒየስ ከ1559-1609 ዓ.ም. የኖረ የሆላንድ ተወላጅ ነው።

አላቸው። በተለይም ቅዱስ ቁርባን ‘‘ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን የምንናገርበት’’ በመሆኑ በሚገባ መካሄድ አለበት (1ኛ ቆሮ. 11፡26)።

የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ መሠረታዊ ትምህርት ጋር ያለውን ግንኙነት ስንመለከት፥ ከመሠረታዊ ትምህርቱ አንጻር ሁለት ተቃራኒ አቅጣጫዎችን ለማየት ይቻላል። ሉተራውያን* [Lutherans] የሥነ-መለኮት ሊቃውንት የእግዚአብሔር ቃል የተለየ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የማያስፈልገው፥ ለውጤታማነት በራሱ ኃይል ያለው ነው ብለው እስኪናገሩ ድረስ በእግዚአብሔር ቃል ሕያው ባሕርይ ላይ ያተኩራሉ (ዕብ. 4፡12)። የሉተራን ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ በዓለም ውስጥ መኖሩንና ኃይሉን ሙሉ ለሙሉ ብትቀበልም፥ ሥራው ግን በቃሉ ላይ ብቻ እንደተወሰነ ታመለክታለች። የሉተራውያንን አቋም ቻርልስ ሆጅ ባጭሩ ሲገልጠው፥ ‘‘ይህ መለኮታዊ ውጤታማነት በቃሉ

---

* የሉተራን ቤተ ክርስቲያን የተሰየመው፥ ማርቲን ሉተር (1483-1546) በተባለው ሰው ስም ነው። ማርቲን ሉተር በጀርመን አገር በአይስሌበን ከተማ ተወለደ። በ1506 ዓ.ም. የአውገስቲኒያን መነኩሴ፥ በ1507 ደግሞ ቄስ ሆነ። ትምህርቱን የተከታተለው በኤርፈርት ዩኒቨርስቲ ሲሆን፥ በ1512 ዓ.ም. ከዊተንበርግ ዩኒቨርስቲ ዶክትሬቱን ተቀብሏል። እዚያው እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አስተምሯል።

በ1510 ዓ.ም. ሮምን በጎበኘበት ጊዜ የካህናቱ ብልሹ ድርጊት በጣም ያሳዘነው ሲሆን፥ አንዳንዶቹ የሮም ቤተ ክርስቲያን ትምህርቶችም አጠያያቂ ሆኑበት። በ1517 ዓ.ም. ጳጳሱ በሮም ከተማ የቅዱስ ጴጥሮስን ቤተ ክርስቲያን ለማሠሪያ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ያስችል ዘንድ በዊተንበርግ አጠገብ ‘‘ኢንደልጀንስ’’** እንዲሸጥ ጃን ተጸል የሚባል ሰው ላከ። ሉተርም ይህን ድርጊት አጥብቆ ተቃወመ። ለውይይት ሊቀርቡ ይገባል ያላቸውን 95 ነጥቦች ዘርዝሮ በመጻፍ በቤተ ክርስቲያኑ በር ላይ ለጠፈ። ሉተር የሮም ቤተ ክርስቲያንን ሥልጣንና ድርጊት የተቃወመ ሲሆን፥ አሳቡም በብዙ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር። በመጨረሻም በ1520 ዓ.ም. የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ሉተር እምነቱን እንዲቀይር ወይም እንዲወገዝ አዘዘ። ሉተር በወርምስ ከተማ ከቤተ ክርስቲያኑ ባለሥልጣናት ጋር ቢገናኝም፥ ትእዛዙን አልተቀበለም። የመከላከያ አሳቡን በዚህ ታዋቂ በሆነ አባባሉ ነበር የደመደመው፡- ‘‘ሕሊናዬ የእግዚአብሔር ቃል ምርኮኛ ነው...እዚህ ቆሚያለሁ፤ ምንም ነገር ለማድረግ አልችልም።’’

ሉተር ወደ ቤቱ ሲሄድ ከመንገድ በጓደኞቹ ታፍኖ ለአንድ ዓመት ያህል በምሽግ ተደብቆ ኖረ። በዚህ ቦታም ታላቅ ሥራ መሠኑ የተረጋገጠለትን፥ መጽሐፍ ቅዱስን የሕዝቡ ቋንቋ ወደሆነው ጀርመንኛ የመተርጎም ሥራ ጀመረ።

** ‘‘ኢንደልጀንስ’’ [Indulgence] በሕይወት ያሉ ሰዎች ከጊዜያዊ ቅጣት እንደሚድኑ ተስፋ የሚሰጥ፥ ለሞቱ ደግሞ ከፐርግቶሪ*** በቶሎ ነጻ እንዲሆኑ የሚያደርግ በቤተ ክርስቲያን የሚሸጥ የምስክር ወረቀት ነው።

*** ‘‘ፐርግቶሪ’’ [Purgatory] በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት፥ አማኞች ከሞቱ በኋላ ሙሉ ይቅርታ ሰላልተደረገለት ኃጢአታቸው የሚሠቃዩበትና መንግሥተ ሰማይ ለመግባት የሚጠብቁበት ቦታ ነው።

ውስጥ ያለና ከቃሉም ለይተን ልናየው የማይቻለን ነው›› ብሏል። ይህ አመለካከት ያለበት ትልቅ ችግር፥ ብዙ ያልዳኑ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ቢሰሙም ሆነ ቢያነቡ በሕይወታቸው ምንም ለውጥ ያለመከሠቱ ነው። ሉተራውያን ለዚህ ምላሽ፥ መንፈስ ቅዱስ ሥራውን የሚሠራበት ኃይል የተመሠረተው በእምነት ላይ ነው ይላሉ። አንድ ሰው የማያውቀውን ነገር እንዴት ሊያምን እንደሚችል ለመግለጥ ግን አስቸጋሪ ነው። እውነቱ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ፥ ያላመኑ ሰዎችን ይወቅሳል። የደኅንነትን መንገድ ይገልጥላቸዋል፤ ይህም ሆኖ አንዳንዶች ከወንጌል እውነት ያፈገፍጋሉ። መንፈስ ቅዱስ ላላመኑ ሰዎች ወንጌልን በመግለጥ ረገድ ያለው ሥራ ግን፥ የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ተግባር እንጂ በሰዎች መቀበልና አለመቀበል የሚወሰን አይደለም። የብዙ ክርስቲያኖች ልምምድ፥ ሰው ስለ ደኅንነት ተረድቶ ለተወሰነ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ሊያምፅና ክርስቶስን ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆን ሊቆይ፥ በመጨረሻም በክርስትና ወደማመን ውሳኔ ላይ ሊደርስ እንደሚችል ያሳያል።

ለሁሉ ስለተሰጠ ጸጋ በተቃራኒ አቅጣጫ የያዘው ሌላ መሠረታዊ ትምህርት፥ የእግዚአብሔር ቃል ጨርሶ አያስፈልግም የሚል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ኃጢአትን ከመከልከል፥ ቸርነትን ከማድረግ፥ ከእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት (አድራጊነት) አጠቃላይ ሥራ ጋር የግድ ግንኙነት አለው ማለት ባንችልም፥ የወንጌሉ የምስራች የሚመጣው ግን በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ውስጥ ድርሻ የለውም የሚለው አንዱ ከረር ያለ አቋም በሁለት ተቃራኒ የሥነ-መለኮት አመለካከቶች ይደገፋል። እነርሱም ‹‹ራሽነሊዝም››* [Rationalism] እና ‹‹ሚስቲሲዝም››** [Mysticism] ናቸው። በእርግጥ ‹‹ዲይስቶች›› የሚያስቡት፥ እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ እንደማይኖርና ማንኛውም መንፈሳዊ ልምምድ የሰው አእምሮ የተለመደ ተግባር ነው ብለው ነው። በእነርሱ አመለካከት ለሁሉ የተሰጠ አጠቃላይ ጸጋ ሙሉ ለሙሉ የሰው ልጅ በእውቀቱ ብርታት የደረሰበት ተፈጥሮአዊ ሂደት ነው። ከ‹‹ዲይስቶች›› ይልቅ ለዘብ ያለ አቋም ያላቸው ‹‹ፐሌጂያን›› [Pelagian] በመባል የታወቁት ሲሆኑ፥ በእነርሱ አስተሳሰብ ሰው በተፈጥሮው እውነትን ለመረዳትና ከዚህ መረዳቱ አንጻር የራሱን

* ራሽነሊዝም፡- ይህ ቃል የሚያመለክተው፥ በመረጃ ላይ የተመረኮዘ ነገር የሚከተል የአስተሳሰብ መርህን ነው።

** ሚስቲሲዝም፡- ይህ ቃል ከራሽነሊዝም ተቃራኒ የሆነና አንድ ሰው በስሜቱ የሚመራበት የአስተሳሰብ መርህ ነው። (ቃሉ ሰው ከመናፍስት ዓለም ጋር አንድ ዓይነት ግንኙነት ላይ እንዲደርስ የማድረግ የጠለቀ አሳብንም አዝሏል። ይህ ልምምድ እንደ ግለሰቡና የእምነት ቡድኑ ሁኔታ ይለያያል።)

ውሳኔ ለማድረግ የሚችል ነው። የራሽነሊዝም አሳብ የቅዱሳት መጻሕፍትን መገለጥ በሁሉም አቅጣጫ የሚቃወም ሲሆን የካልቪን ሥነ-መለኮት ትምህርት ተከታዮች* ይህን ትምህርት የተሳሳተ ነው በማለት በትኩረት አልተመለከቱትም።

የ"ሚስቲክ" [Mystic] አሳብ ከፍ ብለን ያየነውን አመለካከት በቀጥታ የሚቃረን ነው። የዚህ አስተሳሰብ አራማጆች እግዚአብሔር ሊቀበሉት ፈቃደኛ ለሆኑ ሁሉ ቀጥተኛ መገለጥን ይሰጣል በማለት የተገለጠው እውነት ተቀባዮቹ በሚገባ ሊረዱት የሚችሉት ነው ይላሉ። ይህ አመለካከት ከክርስትና ጋር ያላቸውን የአስተሳሰብ ግንኙነት ሁሉ በማለፍ ያልዳኑ ሰዎች እንኳ ሊረዱት የሚችሉት ዓይነት ልዩ መገለጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ማግኘት ይችላሉ የሚለውን ስሕተት ሁሉ ይጨምራል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሳይሰሙ እውነተኛ ደኅንነት ሊያገኙ አይችሉም። ወንጌል ወዳልደረሰበት አካባቢ የሚሄዱ ሚሲዮናውያን እንኳን፥ ክርስቲያናዊ ኅብረተሰብ ወይም በልዩ መገለጥ የዳነ አንድ ክርስቲያን አግኝተው አያውቁም። የእነርሱ አመለካከት የተመሠረተው በቃሉ፥ ወይም በልምምድ ሳይሆን፥ በመላ ምት ላይ ስለሆነ ውድቅ ሊሆን ይገባዋል።

መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውነው ሥራ በተለይ የማያምኑ ሰዎች ወንጌልን እንዲረዱ ማድረግ ነው። መንፈስ ቅዱስ ቃሉ በሚሰበክበት ጊዜ በተፈጥሮው ለዚህ እውነት ዕውር የሆነ ሰው እንዲገነዘብ ይረዳዋል። ለሚጠፉ ሰዎች የመጸለይ አስፈላጊነት ከግንዛቤ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ይህን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ጠቃሚነት ማወቅ ተገቢ ነው።

ለዓለም የሚሰጠው የመገለጥ መጠን። መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን በዓለም ላይ እንዲኖር ያስፈለገበት ተቀዳሚ ምክንያት፥ እውነትን ለዓለም የመግለጥ አገልግሎቱ ነው። እንደ ክርስቶስ ቃል፦ "እርሱ መጥቶ ስለ ኃጢአት፥ ስለ ጽድቅ፥ ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል" (ዮሐ. 16፡8)።

---

* ጄን ካልቪን [John Calvin](1509-1564) የተወለደው በፈረንሣይ ሲሆን፥ አብዛኛውን ጊዜውን በሥራ ያሳለፈው ግን ጄኔቫ (ስዊዘርላንድ) ውስጥ ነው። ሉተር [Luther] የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ትቶ ከሄደ ከ15 ዓመታት በኋላ፥ እርሱም በ1534 ዓ.ም. ይህችን ቤተ ክርስቲያን በመልቀቅ ከተሃድሶ ትምህርት መሪዎች መካከል አንደኛው ለመሆን በቃ። ዛሬ ትምህርቱ "ሪፎርምድ ቲያሎጂ/Reformed Theology"** በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ ይህም ለፕሬስቢቴሪያን እና ለ"ሪፎርምድ" ቤተ ክርስቲያናት መሠረት ነው።

** "ሪፎርምድ" የሚለው ቃል፥ በእንግሊዝኛ የሥነ-መለኮት ሊቃውንትን ለማመልከት፥ ወይም የቤተ ክርስቲያን ዓይነቶችን ለመግለጥ በጥቅም ላይ የሚውለው የካልቪናውያንን ትምህርት ከሉተራውያንና ከአናባፕቲስት ለመለየት ነው። የዚህ ትምህርት መሠረታዊ ጅማሬ የመጀመሪያው የአዳሽ እንቅስቃሴ መሪ ከነበረው የዙሪክ (የስዊዘርላንድ) ሰው ኧልሪክ ዝዊንግሊ፥ እና "የክርስትና ሃይማኖት ተቋም" የሚለውን ምርጥ የፕሮቴስታንት የሥነ-መለኮት ትምህርት ሥራን ከጻፈው የጄኔቫው ጄን ካልቪን የወጣ ነው።

ይህ ሦስት ዘርፍ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ቀጥሎ ባለው ክፍል ውስጥ የበለጠ ግልጥ ሆኖ ቀርቧል። ዓለምን ስለ ኃጢአት የመውቀስ ሥራው በተለይ ያለማመንን ኃጢአት በሚመለከት ባልዳነው ሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚያመለክተውን ጉዳይ የመግለጥ ሥራ እንደሆነ በቁጥር ዘጠኝ ‹‹ስለ ኃጢአት በእኔ ስለማያምኑ ነው›› በሚለው ቃል ተገልጧል። በክርስቶስ ሞት ምክንያት የኃጢአት ኩነኔ የለም። የክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔርን ጽድቅ ጥያቄ ሁሉ የሚያሟላ ሆኗል። ያልዳኑ ሰዎችን የመጨረሻ ዕጣ የሚመለከት ወሳኝ ጥያቄ በክርስቶስ የማመንና ያለማመን ጉዳይ ብቻ ነው። ባሕርይን ከማነጽ ወይም በተሻለ የቅድስና ሕይወት መኖርን ከማበረታታት በላይ፥ ለመዳን በክርስቶስ ማመን የግድ አስፈላጊ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ ግልጥ ያደርገዋል።

መንፈስ ቅዱስ ለዓለም የሚገልጠው ሁለተኛ ነገር፥ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው። እንደ ዮሐንስ 16፡10 አባባል፥ ይህ መገለጥ አስፈላጊ የሆነው፥ እርሱ በምድር ላይ ከእንግዲህ ስለማይኖር ነው፤ ‹‹ስለ ጽድቅም ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው።›› ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ሕልውናውና የማስተማር ሥራው የእግዚአብሔር ጽድቅ መግለጫ ነበር። ወደ ሰማይ በሚያርግበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ስፍራውን ተክቶ ማገልገሉ አስፈላጊ ሆነ። ለማያምኑ ሰዎች እንደሚሰጠው አገልግሎት ከሆነ፥ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጽድቅ በሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች ይገልጣል። የመጀመሪያው ነገር፥ ጉዳያችን ጻድቅ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር መሆኑ ነው። ይህ ማንኛውም ምድራዊ የመምሰል ወይም የማነጻጸር ጥያቄ አይደለም። የእኛ ሕይወት የሚታየውና የሚለካው በእግዚአብሔር አካላዊ ሕልውናና ጻድቅነት ነው። ለማያምን ሰው መንፈስ ቅዱስ የሚገልጠው ሁለተኛ ነገር፥ እግዚአብሔር ለአማኝ የሚሰጠውና በክርስቶስ በኩል የሚገኝ ጽድቅ መኖሩን ነው። እርግጥ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ የሚያኖረውን ይህን ጽድቅ በሚገባ ሳይረዱ በእምነት ወደ ክርስቶስ የሚቀርቡና የሚድኑ እንዳሉ ጥርጥር የለንም። እንዲሁም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የጎደላቸውን ጽድቅ እንደሚሰጣቸው በድንግዝግዝ ብቻ የሚረዱና አስደናቂው የማጽደቅ ሥራ ያልገባቸው ብዙዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን ያልዳነ ሰው ቢያምን እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ልክ እንደ ጻድቅ ሰው ከእርሱ ጋር ጉዳዩን ሊፈጽም እንደሚችል በትክክል ማመን ይገባዋል። ይህ መገለጥ ከወንጌል የሚለይ አይደለም።

ላልዳኑ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሰጣቸው ሦስተኛ መገለጥ ደግሞ መስቀሉ ከፍርድና ከሰይጣን ጋር ያለው ግንኙነት ነው። ክርስቶስ ሲናገር፥ መንፈስ ቅዱስ ዓለምን የሚወቅሰው፥ ‹‹ስለ ፍርድ የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው›› (ዮሐ. 16፡11) አለ። ፍርድ እውነተኛና

የማይቀር መሆኑን መንፈስ ቅዱስ ላልዳነው ሰው ልብ ይገልጥለታል። ያልዳኑ ሰዎች ኃጢአት ፍርዱን በመስቀል ላይ እንደተቀበለና በክርስቶስ ለሚታመኑ ሁሉ ከኃጢአት ፍርድና ከኩነኔ ነጻነት እንደተሰጣቸው ሊያውቁ ይገባል። ስለ እነርሱ ክርስቶስ እንደተፈረደበትና እንደሞተ፥ ስለዚህም የኃጢአት ፍርድ እንዳለፈላቸው ማየት አለባቸው። ለዚህም ምልክት እንዲሆን "የዚህ ዓለም ገዥ" የሆነው ሰይጣን እንደተፈረደበት ተጠቅሷል። ሰይጣን በመስቀል ላይ ተሸንፏል። መስቀሉ በሰይጣን ላይ የተገለጠ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ሰይጣን በፍርድ ከተወገዘና ከተፈረደበት ቆይቷል። አሁን የተፈረደበትን ፍርድ ለመፈጸም ብቻ በመጠባበቅ ላይ ነው። እግዚአብሔር ሰይጣን በዚህ ዘመን ታላቅ ኃይል እንዲሆን ቢፈቅድለትና ነጻነት ቢሰጠውም፥ መጨረሻው ግን የታወቀ ነው። ክርስቶስን ለመቀበል ፈቃደኞች የማይሆኑ ሁሉ የእርሱ የመጨረሻ ዕጣ ተካፋዮች ይሆናሉ።

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ላልዳኑት ሰዎች ያለው አገልግሎት ግልጥ የሆኑ ሦስት መሥመሮችን የተከተለ ነው። በመጀመሪያ ያልዳነ ሰው ደኅንነት በክርስቶስ በማመን ላይ የተመሠረተ መሆኑን መረዳት አለበት። ሁለተኛው ነገር ጽድቅ የእግዚአብሔር አካላዊ ሕልውና ክፍል እንደሆነና ይህም ለኃጢአተኞች በክርስቶስ በኩል የተዘጋጀላቸው መሆኑን መገንዘብ ነው። ሦስተኛው ነገር ደግሞ ባልዳነ ሰው ላይ ፍርድ መምጣቱ የማይቀር እውነት እንደሆነና ኃጢአተኞች ይድኑ ዘንድ፥ በምትካቸው በተፈረደበትና በተገደለው ክርስቶስ ውስጥ መገኘት ያለባቸው መሆኑ ነው። እነዚህ ነገሮች ሁልጊዜ በግልጥ የሚታዩ ባይሆኑም፥ ኃጢአተኛ ይድን ዘንድ በክርስቶስ ላይ መመሥረት ያለበት መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ላልዳነ ሰው ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች አንዱ፥ ውጤት ሊያመጣ የሚችል የወንጌል ስብከት እንዲኖር ማድረግ መሆኑ መናገር እንኳ የሚያስፈልገው አይደለም።

6. ኃጢአትን የመከልከል ተግባር

የመንፈሰ ቅዱሰ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር በብሉይ ኪዳን።
የመንፈስ ቅዱስ ዓለምን ከኃጢአት የመጠበቅ ሥራ በታላቁ መከራ ጊዜ፥ ማለት ከዚህ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ ኃጢአተኛነት ከሚበዛበት፥ ያልተከለከለ ኃጢአት ምን እንደሚመስል ለማሳየት እግዚአብሔር ከሚጠቀምበት ከዚያ ጊዜ በቀር በየትኛውም ዘመን ይገኛል። ነገር ግን ኃጢአትን የመከልከል ሁኔታው በየዘመናቱ የተለያየ ነበር።

በዘፍጥረት 6፡3፥ "እግዚአብሔር መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም እርሱ ሥጋ ነውና..." አለ በሚለው ቃል ውስጥ የብሉይ ኪዳን

ኃጢአትን የመከልከል ተግባር መመሪያ ይገኛል። ይህ ክፍል በኖኅ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን በመከልከል ረገድ የነበረውን ሰፊ ተግባር ያሳየናል። ከኃጢአት የሚጠብቀው የእግዚአብሔር እጅ በግሩም ሁኔታ የተገለጠው ኢዮብ በእግዚአብሔር እንደተጠበቀ በሚናገረው በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ነው። በኢዮብ ላይ የደረሰው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር የተፈቀደ ቢሆንም፥ ሰይጣን እግዚአብሔር ከፈቀደለት ውጭ በኢዮብ ላይ ምንም ለማድረግ አይችልም ነበር። በግልጥ ባይነገርም፥ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ተግባር እንደነበር መሠረታዊው ትምህርት ያረጋግጥልናል።

ኃጢአትን የመከልከል አብዛኛው የመንፈስ ቅዱስ ተግባር በተለያየ መንገድ እንደሚፈጸም ተገልጧል። መንፈስ ቅዱስ በነቢያት አማካይነት የገለጠው እውነት፥ በተለይ ሊመጣ ስላለው ፍርድ የገለጠው ነገርና የቅዱሳት መጻሕፍት ኃይል ኃጢአትን ለመከልከል የረዱ ነገሮች ናቸው። በዓመፃቸውና መንፈስ ቅዱስን በማስመረራቸው ምክንያት በሕዝቡ ላይ የመጣባቸው ፍርድ (ኢሳ. 63፡10-11) የራሱ የሆነ ውጤት ነበረው። የመንፈስ ቅዱስ ሕልውናና ኃይል ኃጢአትን ለመከልከል እጅግ ረድቷል። በብሉይ ኪዳን ዘመናት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የሰውን ልጅ የታሪክ አቅጣጫ ለመለኮታዊ ቸርነትና ጥበቃ በማዘጋጀት ላይ ነበር።

የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር በዚህ ዘመን። የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር በብሉይ ኪዳን እንደነበር ሁሉ በዚህ ዘመንም ቀጥሏል። ለዚህ አገልግሎቱ ተጨማሪ የሆነ ማረጋገጫ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡7 እናገኛለን፦ "የዓመፅ ምስጢር አሁን ይሠራልና ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ።" የዚህ ክፍል የመነጋገሪያ አሳብ የዓመፅ ሰው፥ እርሱም የጥፋት ልጅ የሆነው የሚገለጥበትን የጌታ ቀን መምጣት የሚመለከት ጉዳይ ነው (2ኛ ተሰ. 2፡3)። በዚህ ክፍል መሠረት የሚከለክለው እስከሚወገድ ድረስ የጥፋት ልጅ ሊገለጥ አይችልም። ስለዚህ ይህ ዘመን የጥፋት ልጅ እንዳይገለጥ ባደረገውና ዓመፅ ከልካይ በሆነው መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ይጠቀማል። ይህ ዓመፅን የሚከለክል አካል በብሉይ ኪዳን መሠረት ስንመለከተው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እንረዳለን።

የቅዱሳት መጻሕፍት ተርጓሚዎች ዓመፅ የሚከለክለውን አካል ማንነት በሚመለከት አልተስማሙም። በሰፊው የታወቀውና አንደኛው አመለካከት፥ ይህ ዓመፅን የሚከለክለው አካል በምድር ላይ ያለ ሰብዓዊ መንግሥት ነው የሚል ነው። ሰብዓዊ መንግሥት ግን የዓመፅ ልጅ በሚገለጥበት በታላቁ የመከራ ጊዜም ይኖራል። ሕግና ሥርዓቶች ሁሉ የሚያዘነብሉት ኃጢአትን ወደ መከልከል ቢሆንም፥ ሁኔታቸው በዚህ ክፍል እንደተገለጠው አይደለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል ይህን

ዓላማ ከፍጻሜ እንዲያደርሱ እንደተደረጉና ጥቅም ላይ እንደዋሉ የሚታዩ ናቸው። ስለዚህ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር መንገዱ ምንም ይሁን ምን፥ ከእግዚአብሔር የሚመጣ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አድርጎ መቁጠር የተሻለ ነው። ነገር ግን ቲሰን [Thiessen] የተባለ የሥነ-መለኮት ሊቅ እንደጻፈው "ኃጢአትን የሚከለክል ማነው? ዴኒ [Denney]፥ ፊንድሊ [Findley]፥ አልፎርድ [Alford]፥ ማፊት [Moffat]፥ የተባሉ ሰዎች ይህ በተሰይ በሮም ግዛት ውስጥ የነበረውን ሕግና ሥርዓት የሚያመለክት ነው ብለዋል። ነገር ግን ኃጢአትን በሚከለከለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውስጥ ሰብአዊ መንግሥታት በአስፈጻሚነት ቢያገለግሉም፥ በእነርሱ አሠራር ላይ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በጎ ተጽዕኖ እንደምታደርግ እናምናለን። ደግሞም ከእያንዳንዱ ሰብአዊ መንግሥት ጀርባ ያን መንግሥት የመሠረተውና ያቋቋመው እግዚአብሔር አለ (ዘፍጥ. 9፡5-6፤ ሮሜ 13፡1-7)። እርሱም ይቆጣጠረዋል (መዝ. 75፡5-7)። ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የዓመፅን መስፋፋት የሚገታ እግዚአብሔር ራሱ ነው" ብሏል።

አንዳንዶች የሚያቀርቡት አመለካከት ደግሞ፥ የኃጢአትን እውነተኛ ባሕርይ ሰዎች እንዳይረዱ በማድረግ ሰይጣን ራሱ ዓመፅን (ኃጢአትን) ይከለክላል የሚል ነው። ሰይጣን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በተገለጠበት ሁኔታ ስናየው፥ ይህን አሳብ ማጣጣሙ አስቸጋሪ ይሆናል። ሰይጣን በዓለም ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ታላቅና ለማምት የሚያስቸግር ቢሆንም፥ በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዓለም አቀፍ ሥልጣን እንደተሰጠው አልተነገረም። በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡3-10 እንደተገለጠው የዓመፅ ልጅ ከመምጣቱ በፊት ኃጢአትን የሚከለክለው ይወገዳል። ይህ ሰይጣን ነው ማለት ፈጽሞ አስቸጋሪ ነው። በተቃራኒው የታላቁ መከራ ጊዜ የሰይጣን ሥራ በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጥበት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዚያ ክፉ ቀን ሰይጣን ወደ ምድር እንደሚጣልና የጥፋት ኃይሉን እንደሚጠቀም ይናገራል (ራእይ 12፡9)። ስለዚህ ሰይጣን ዓመፅን የሚከለክል ነው ብሎ ማሰብ በምክንያታዊነት የሚያዝ አቋም አይደለም።

በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን ለመከላከልና ሰዎችን ለመርዳት የታገለ መሆኑን ካመን፥ በዚህም ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲሠራ፥ ተመሳሳይ አገልግሎት እንደሚኖረው አንጠራጠርም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በምድር እያለች በዓለም ላይ የመጨረሻ ፍርዱን የሚያመጣ ባይሆንም፥ በስሙ የተጠሩ ሕዝቦቹን የማውጣት ዓላማውን ለመፈጸም ግን፥ ሉዓላዊነቱ በሰዎች ድካምና ክፋት ላይም ሆነ በሰይጣን ኃይል ላይ ይሠለጥናል። በቤተ ክርስቲያን ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ሥራ ያገኘው ግንዛቤ መጠነኛ ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጥበቃ ውጭ ኃጢአት በሞላበት ዓለም ውስጥ መኖሩ ለክርስቲያኖች አስቸጋሪ ይሆን ነበር።

ኃጢአትን በመከልከል ተግባር የሚጠቅሙ ነገሮች። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ሥራ የሚናገሩት ሰፊ ነገር የለም። ነገር ግን የኃጢአትን አቅጣጫ የሚቆጣጠሩ ሌሎች በርካታ ነገሮች መኖራቸው ለዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል። መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ክርስቲያን በምድር ላይ ሲኖር ዓለም በኃጢአት እንዳትቀጥል ለሚያደርጉ ኃይሎች የሚሰጠው አስተዋጽኦ በርካታ ነው። የክርስቲያኖች አንድነት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፥ የመጽሐፍ ቅዱስን መመዘኛ ባታሟላ እንኳን፥ በዓለም ላይ ከፍተኛ በጎ ተጽዕኖ ታሳድራለች። መጽሐፍ ቅዱስ በደረሰበት ቦታ ሁሉ ባመኑት ላይ ብቻ ሳይሆን፥ ባልዳነው ዓለም ላይም በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ያሳድራል። በእግዚአብሔር ተሹመው የተቀመጡ ሰብአዊ መንግሥታትም ለመለኮታዊ ዓላማ ፍጻሜ አንድ መንገድ ናቸው። እነዚህ ክንውኖች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ባይሆኑም፥ ይህን ዓላማውን ለመፈጸም እርሱ የሚጠቀምባቸው ሁኔታዎች ናቸው። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ሥራ፥ አስፈላጊ ከሆኑ የእግዚአብሔር ሥራዎች አንዱና ለመለኮታዊ ቸርነትና ጥበቃ ለሁሉ የተሰጠ የጸጋ ክንውን አካል መሆኑን ለማየት እንችላለን።

7. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ውሱንነት

ቀደም ሲል ካደረግነው ውይይት በመነሣት፥ ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ከሥርየት አስገኝ ጸጋ በጣም ያነሰ መሆኑን መረዳቱ አያስቸግርም። ያልዳነ ሰው ወንጌልን በሚገባ እንዲረዳና በተረዳው ነገር የአስተዋይነት እርምጃ እንዲወስድ ለመምራት ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ የሚሠራው ሥራ ቀላል ባይሆንም፥ በሰው ፈቃድ ላይ ምንም ለማድረግ ስለማይችል ደኅንነትን ለመስጠት የሚበቃ አይደለም። ሁለት ያልዳኑ ሰዎች እኩል ወንጌልን ተረድተው አንዱ ወደሚያድን እምነት ጨርሶ ላይደርስ፥ ሌላው ደግሞ በክርስቶስ አምኖ ሊድን ይችላል። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ያልዳኑትን ወደ ደኅንነት ሊያመጣ ከሚችል ከየትኛውም ዓይነት ሥርየት አስገኝ የእግዚአብሔር ሥራ የተለየ መሆን አለበት።

ለሁሉም የተሰጠ ጸጋ፥ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከሚረዳበት ልምምድ ያነሰ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ራሳቸውን በሰጡ ክርስቲያኖች ውስጥ ማደር፥ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት እንዲረዱ ብርሃን ይሆንላቸዋል። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ በአጠቃላይ ደኅንነት ርእስ ላይ በቂ ገለጣን በመስጠት በእምነት መሠረት ላይ ያሳርፋል። ይህ ጸጋ በደኅንነት እውነት ክልል ውስጥ እንኳ ከተፈጥሮአዊ ሰው መረዳት በላይ አይደለም። ከግብረገባዊና አሳማኝ ከሆነ እውቀት ጋር የቀረበ ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን፥ በራሱ ወደ ውሳኔ የሚያመጣ ምንም ነገር ግን የለውም።

ለሁሉም የተሰጠ ጸጋ፥ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ባደረ ክርስቲያኖች የሚታየውን ልምምድ ያለምንም ገደብ የሚሰጥ አይደለም።

ለሁሉም የተሰጠ ጸጋን ብቻ በተለማመዱ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑት ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ሊገኙ አይችሉም። ያልዳኑ ሰዎች አንዳንዶቹን ክርስቲያናዊ አኗኗሮች ውጫዊ ሕይወት መኖር ቢችሉም፥ የውስጣዊ ለውጥ ልምምድ ጨርሶ የላቸውም። እርግጥ በአንዳንድ ሁኔታዎች የዳነውንና ያልዳነውን ሰው ለመለየት ማስቸገሩ የሚካድ አይደለም።

ምንም እንኳን ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ በባሕርዩና በውጤቱ ውሱን ቢሆን፥ ያለምንም ሁኔታ የተገለጠ ነው ለማለት አይቻልም። ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በግልጥ የተያያዘ ባይሆንም፥ ሃይማኖታዊ ስሜትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ ጋር የተያያዙ ለመሆናቸው አያጠራጥርም። ይህ ለሁሉ የተሰጠ የጸጋ ደረጃ ግን የወንጌልን ጉዳይ ለመረዳት የሚያበቃ አይደለም። በስፋት ስንመለከተው ኃጢአትን የመከልከል ኃይል ሳይኖረው እንደማይቀር እናስባለን። ሰዎች ደኅንነት ሳያገኙ በውጫዊ መንገድ ክርስቶስን እንዳመኑ የመናገራቸውና፥ ጥሩ ግብረገባዊ ሕይወት የመኖራቸው ምክንያት ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ውጤት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ቻርልስ ሆጅ እንዲህ ብሎ ጽፏል፦ ‘‘ያልተለወጡ ሰዎች ንስሐ እንደገቡ፥ እንዳመኑ፥ የመንፈስ ቅዱስ ተካፋይ እንደሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ቃል መልካምነትና ሊመጣ ያለውን ኃይል እንደቀመሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ተነግሯል።’’ ስለዚህ ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ሥራ ውስጥ ሁለንተናዊ ከሆነው ሃይማኖታዊ ስሜትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ጀምሮ ደኅንነትን እስከመግለጥ ድረስ የተለያዩ ደረጃዎች መኖራቸው የሚያጠራጥር አይደለም። በዚህ ሁሉ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ክርስቶስን ለደኅንነታቸው ወደ ማወቅ ደረጃ ይመጡ ዘንድ በሥራው ይተጋል። ያለዚህ ቀዳሚ አገልግሎት የሥርየት ጸጋ የሚቻል አይደለም።

መንፈስ ቅዱስ ላልዳነው ዓለም ያለው የጸጋ ሥራ የማያልቅና፥ እግዚአብሔር በጽድቅ የተሞላ ፍርዱ ዓላማ የሆኑት ሁሉ የክርስቶስ ኢየሱስን አዳኝነት ወደ ማወቅ እንዲደርሱ የሚታገል መሆኑን የሚያሳይ ሌላ ማረጋገጫ ነው። ያለዚህ አገልግሎት ይህች ዓለም ለክርስቲያኖች የማይቻሉ ሁኔታዎችን የምትፈጥርና የወንጌል ስብከትም ውጤት የማይታይባት ትሆን ነበር። አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም በሆነ ክብር የሚቆመው የጸጋ ምርኮ፥ በክርስቶስ የተሰጠውን ተግባር ለመወጣት መንፈስ ቅዱስ ላለው ውጤታማ ኃይል በቂ ምስክር የሚሆን ነው።

13

ውጤት አስገኝ ጸጋ

1. የትምህርቱ አስፈላጊነት

ሰዎች ውጤት ባለው የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት እምነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሥነ-መለኮት ትምህርት ቋንቋ ‘‘ውጤት አስገኝ ጸጋ’’* ይባላል። ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ ቀጥሎ በጊዜም ሆነ በታማኝነት ቅደም ተከተል ሰዎችን ወደ ደኅንነት ለማምጣት የሚያስፈልገው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሥርየት አስገኝ ጸጋ ነው። ይህ ጉዳይ በአንዳንድ የሥነ-መለኮት ትምሕርቶች በአግባቡ ግንዛቤ ያላገኘና የተሳሳተ ትርጉም የተሰጠው ነው። ይሁን እንጂ ትምሕርቱ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥሩ ውጤት የሚሰጥ አቅጣጫን በተመለከተ ሁሉ ያመለክታል። እግዚአብሔር ሰዎችን በማዳን ረገድ ያለውን እጅግ አስፈላጊ ተግባር ያመለክታል። ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትም አስፈላጊ የሆነ ክፍል ነው።

ከተግባራዊነት አኳያም የአማኝን ደኅንነት በተመለከተ የመንፈስ ቅዱስ ተግባር በጥንቃቄ ሊጠና የሚገባውና እጅግ አስፈላጊም ነው። ይህ ትምህርት በክርስቶስ ለሚያምን ሁሉ እግዚአብሔር በሕይወቱ ስለሚሠራው ሥራ የሚናገር የከበረ መገለጥ፥ ለመንፈሳዊ ልምምዱ እና ክቡር ለሆነ ተስፋው መሠረት ነው። መንፈስ ቅዱስ በደኅንነት ውስጥ ስላለው ሥራ ግልጥ የሆነ አሳብ ከተያዘ፥ ስለ ደኅንነት ዋስትና የሚነሡ በርከት ያሉ ውዥንብሮችን ለማስወገድ ይቻላል። ይህ ትምህርት ‘‘ደኅንነት የሚገኘው በሥራ ነው’’ የሚለውን ፍልስፍና ውድቅ ያደርገዋል። የደኅንነታችንን ዋስትና ከስሜታዊ ልምምድ ነጻ ያደርጋል። በተጨማሪም ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ትክክለኛ ስፍራ በመስጠት፥ ‘‘የቅድስና [Holiness] እንቅስቃሴ’’** ከተባለው ቡድን የተሳሳተ ገለጣ ነጻ ያወጣል።

---

* በዚህ መጽሐፍ ‘‘ውጤት አስገኝ ጸጋ’’ እና ‘‘ሥርየት አስገኝ ጸጋ’’ የሚሉትን ሐረጎች በማፈራረቅ ተጠቅመንባቸዋል።

** በ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ መጀመሪያ ላይ በርከት ያሉ አነስተኛ የሃይማኖት ክፍሎች፥ ፍጹምነትን በዚህ በምድራዊ ሕይወት ልንደርስበት የምንችለው ነገር ነው በማለት ያስተምሩ ነበር። አብዛኛዎቹ የዚህ ትምህርት ተከታዮች በጃን ዌስሊ [John Wesley] ከተመሠረተው የመቶዲስት [Methodist] ቤተ ክርስቲያን የወጡ ናቸው። አንዳንድ ፍጹምነትን በሕይወት ዘመናችን እንለማመዳለን የሚሉ አብያተ ክርስቲያናት፥ ከጸንጠቆስጣዊ አብያተ ክርስቲያን ጋር በሚስማማ አሳባቸው፥ በልሳን መናገርንና የፈውስ ስጦታዎች በዚህ ዘመን እንደሚሠሩ ያምናሉ።

ደግሞም በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ራሱ እንዴት አድርጎ በመሥራት ላይ እንዳለ ለመረዳት ጥሩ መሠረትን ይሰጣል።

አንድ ሰባኪ ትክክለኛ ወንጌል ይሰብክ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በደኅንነት ውስጥ ያለውን ሥራ አጥርቶ መረዳቱ እጅግ አስፈላጊና መሠረታዊ ጉዳይ ነው። የእግዚአብሔር አስፈላጊ ሥራ፥ ሰው ማድረግ ያለበት ነገርና ነፍሳትን ለክርስቶስ ለመማረክ የሚያስፈልገው የእግዚአብሔር ኃይል ተገቢ ግንኙነታቸው ይታያል። ይህ ሰባኪው በራሱ መርሐ ስብከትና ችሎታ ላይ ከመደገፍ ነጻ የሚያደርገው ሲሆን፥ ወንጌልን በሥልጣን እና በኃይል ለመስበክ ማድረግ ካለበት ጥረት ሳይዘናጋ፥ ለፍሬያማ አገልግሎቱ በእግዚአብሔር ላይ እንዲደገፍ የጸሎትን ኃይል ወደ መለማመድ ይመራዋል። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚኖረው ኅብረትም በአገልግሎቱ ከፍተኛ ለውጥ ያስገኝለታል።

ይህን ትምህርት በተለያየ መንገድ ለማብራራት የሚጥር ማንኛውም ጸሐፊ፥ አቀራረቡ ትሕትናን የተሞላ መሆን አለበት። መሠረታዊው የእምነት ትምህርት ከሕይወት ጋር የሚዛመድበት ነገር እጅግ ሰፊ ነው። በዚህ ትምህርት ውስጥ የሰው ጥበብ ጣልቃ ገብነት ቢታይም መለኮታዊው ጥበብ እጅግ አስፈላጊና ዋነኛ ነው። ከሰው ጥበብ ይልቅ መለኮታዊው ጥበብ ለውጤታማ ትምህርት ዋነኛ ስለሆነ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን ብቻ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

2. ውጤት አስገኝ ጸጋ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት

የውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚለው ርእስ የሥነ-መለኮት ትምህርት ቋንቋ ቢሆንም፥ ቀድሞም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ያለው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ደኅንነት የሚያመጣ መለኮታዊ ጥሪ እንዳለ በተደጋጋሚ ይናገራሉ (ሮሜ 1:1፥ 6፥ 7፤ 8:28፥ 30፤ 9:11፥ 24፤ 11:29፤ 1ኛ ቆሮ. 1:1፥ 2፥ 9፥ 24፥ 26፤ 7:15፥ 17፥ 18፥ 20-22፥ 24፤ ገላ. 1:6፥ 15፤ 5:8፥ 13፤ ኤፌ. 1:18፤ 4:1፥ 4፤ ቈላ. 3:15፤ 1ኛ ተሰ. 2:12፤ 4:7፤ 5:24፤ 2ኛ ተሰ. 2:14፤ 1ኛ ጢሞ. 6:12፤ 2ኛ ጢሞ. 1:9፤ ዕብ. 3:1፤ 9:15፤ 1ኛ ጴጥ. 1:15፤ 2:9፥ 21፤ 3:9፤ 5:10፤ 2ኛ ጴጥ. 1:3፥ 10)። ደኅንነትን የሚያስገኝ ይህ መለኮታዊ ጥሪ፥ ወንጌልን በመግለጥ እና ወደሚያድን እምነት በመምራት ውጤት ማምጣቱ እርግጠኛ ስለሆነ "ውጤት አስገኝ ጸጋ" በመባል ይታወቃል። ከዚህኛው የእግዚአብሔር ሥራ በተነጻጻሪነት ወንጌልን ለሚሰሙ ሁሉ የሚደረግ

አጠቃላይ የደኅንነት ጥሪ አለ። በዚህ ስሜት ነው ክርስቶስ ‹‹ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና›› ያለው (ማቴ. 9፡13)።

ለንስሐና ለእምነት የሚደረግ ጥሪ ሁልጊዜ ተቀባይነት የማያገኝ መሆኑ ግልጥ ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ራሱ፥ ‹‹የተጠሩ ብዙዎች ናቸው የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና›› ብሏል (ማቴ. 22፡14)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ጥሪ የሚናገሩ በርካታ ጥቅሶችን በምንመረምርበት ጊዜ የሚናገሩት፥ ሥርየት ስለሚያስገኘው ጥሪ መሆኑን እንረዳለን። ስለዚህ ውጤት አሰገኝ ጥሪ ከአጠቃላይ ጥሪ ጋር በተነጻጻሪነት እንደቀረበ ሁሉ፥ ውጤት አሰገኝ ጸጋም ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ ጋር በተነጻጻሪነት ይቀርባል። ተግባራዊ ዓላማን በሚመለከት፥ ጸጋው በጥሪው ውስጥ እንደሚካተት በማሰብ መለኮታዊ ጥሪና በውስጡ ያለው ጸጋ እንደ አንድ ጉዳይ እንደሚታዩ ለማሰብ እንችላለን።

ስለ ውጤት አሰገኝ ጥሪ የሚናገሩ በርካታ ክፍሎችን በማጥናት የዚህን እውነት ብዙ ገጽታዎች ለመግለጥ እንችላለን። የመጀመሪያው ነገር ይህ መሠረታዊ ትምህርት ያለጥርጥር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑ ነው። ደኅንነትና መለኮታዊ ጥሪ አንዱ ያለ ሌላው ሊሆኑ የማይችሉና የማይነጣጠሉም ናቸው። ክርስቲያኖች ‹‹ቅዱሳን ልትሆኑ የተጠራችሁ›› (ሮሜ 1፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡2)፥ ‹‹ለዘላለም ሕይወት›› የተጠራችሁ (1ኛ ጢሞ. 6፡12)፥ ‹‹ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን›› ተጠርታችሁ (1ኛ ጴጥ. 2፡9)፥ ‹‹በገዛ ክብሩና በበጎነቱ›› የተጠራችሁ (2ኛ ጴጥ. 1፡3) ተብለዋል። ጳውሎስ ‹‹ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ›› (ሮሜ 1፡1፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡1)። ‹‹አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም፥ እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው›› (ሮሜ 8፡30)። ስለ ክርስቲያኖች፥ ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ›› (ሮሜ 1፡6)፥ እና ‹‹እንደ አሳቡም ለተጠሩ›› (ሮሜ 8፡28) ተብሎላቸዋል። በጣም አስፈላጊ የሆነ ጥቅስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡23-24 ይገኛል፡- ‹‹እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ፥ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፤ ለተጠሩት ግን አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎች ቢሆኑ የእግዚአብሔር ኃይል እና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።›› ላልተጠሩ ሰዎች ወንጌል ሞኝነት ሆኖ ሲቀር፥ ለተጠሩት ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ከእነዚህ ክፍሎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለደኅንነት የመጥራቱ አገልግሎት በጣም አስፈላጊና በበርካታ ስፍራዎች የተጠቀሰ መሆኑን በመናገር ለማጠቃለል እንችላለን።

3. ውጤት አስገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ሥራ ነው

ውጤት አስገኝ ጸጋ በቀላሉ ልንረዳው የማይቻለን አሠራር ቢሆንም፥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጠው አፈጻጸሙ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። አብዛኛዎቹ የካልቪን የሥነ-መለኮት ትምህርት መምህራን፥ ስለዚህ አሳብ ያላቸው አስተያየት አንድ ሲሆን፥ ቅዱሳት መጻሕፍትም በርካታ ምስክርነት ይሰጣሉ። ቻርልስ ሆጅ በጉዳዩ ላይ የሚከተለውን ጽፏል፦

> ‹‹ማንኛውም ድርጊት ከሚከተሉት በሦስት ወይም በአንዱ መንገድ ምክንያት ሊከናወን ይችላል፦ 1ኛ. የእግዚአብሔር ኃይል በቀጥታ ሲገባበት (ተአምራት)፥ 2ኛ. በእግዚአብሔር ተቆጣጣሪነትና ምሪት የተፈጥሮ ኃይላት ነገሮች እንዲከሠቱ በማድረግ (ምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥ)፥ 3ኛ. እግዚአብሔር በቀጥታ በሰው ልብና ፈቃድ ውስጥ በመሥራት ሰው እርሱ የሚጠብቅበትን እንዲፈጽም በማድረግ ማድረግ።›› ውጤት አስገኝ ጸጋ በሦስተኛው አሳብ ውስጥ የሚጠቃለል ነው።

ውጤት አስገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት የታመነ ምስክርነት ይሰጣሉ። ስለ ውጤት አስገኝ ጥሪ የሚናገሩ ክፍሎች በሙሉ ሥራው የእግዚአብሔር መሆኑን አስቀድመው መገንዘባቸውን ያመለክታሉ። ውጤት አስገኝ ጸጋ ከሰው ነጻ ፈቃድ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ጋር የተዛመደ ነው። ለዚህ ነው ጳውሎስ፥ ‹‹ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ›› ወዘተ. (ሮሜ 1፡1) የተባለው። በቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊ ጥሪ ለሰው ነጻ ፈቃድ ስፍራ እንደሚሰጥ የሚናገር አንዳችም ነገር የለም። መለኮታዊ ጥሪ ሁሉን ቻይና ሉዓላዊ ከሆነው እግዚአብሔር የሚመጣ ነው።

በሰው ልጅ አጠቃላይ ውድቀትና ብቁ ያለመሆን ላይ ባላቸው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መሠረት፥ የካልቪን የትምህርተ-መለኮት መምህራን ውጤት አስገኝ ጸጋ ያለምንም እርዳታ እግዚአብሔር ራሱ የሚፈጽመው ተግባር መሆኑን ያረጋግጣሉ። ሰው ወንጌልን በሚሰማበት እና በሚረዳበት ደግሞም ደኅንነት እንደሚያስፈልገው በሚገነዘብበት ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ቅድመ አስፈላጊነት ሙሉ ለሙሉ ቢስማሙም፥ ውጤት አስገኝ ጸጋ ግን የሰውን ልብ በክርስቶስ ባለ እምነት ላይ እንዲያርፍ ለሰው ፈቃድ ኃይል መስጠት የእግዚአብሔር ሥራ ነው በማለት ይገልጡታል። በሁሉም ረገድ የውጤት አስገኝ ጸጋ ግብ ደኅንነት ነው፤ ምክንያቱም ደኅንነት የሚፈጸመው በእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ነውና።

"የዌስትሚንስተር የእምነት መግለጫ" [Westminster Confession] እንደሚከተለው ያሰፍረዋል፦

"ሀ. እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሕይወት የወሰናቸውንና ደስ የተሰኘባቸውን ብቻ ራሱ በወሰነና ባቀደ ጊዜ ከፍጥረታቸው ኃጢአተኞችና ሟቾች ከሆኑበት ደረጃ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ወዳለ ጸጋ እና ደኅንነት በቃሉ እና በመንፈሱ ጥሪ ያደርግላቸዋል። የእግዚአብሔርን ነገር ይረዱ ዘንድ መንፈሳዊ አእምሮአቸውን ለደኅንነት ያበራላቸዋል፤ ድንጋይ ልባቸውን ወስዶ የሥጋ ልብ ይሰጣቸዋል። አእምሮአቸውን በታላቅ ኃይል በማደስ ለበጎ ነገር ይወስናቸዋል፤ ልክ በነጻነትና በምርጫቸው እንደሚመጡ ዓይነት በሚገባ ወደ ክርስቶስ በመሳብ በጸጋ ብቁ ያደርጋቸዋል።

"ለ. ይህ ውጤት አስገኝ ጥሪ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ነጻ እና ልዩ ጸጋ ነው። ይህ የሚሆነው በሰው ውስጥ ቀድሞ በሚታይ አንዳች ነገር ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ፥ አነቃቅቶትና አድሶ ለጥሪው መልስ መስጠት እንዲችልና የተሰጠውን ጸጋ አምኖ እንዲፈጽም እስኪደረግ ድረስ ሰው ምንም ማድረግ አይችልም ነበር።"

ውጤት አስገኝ ጸጋ በአሠራሩ ምክንያት አንድ ጊዜ የሚከናወነውን የቅጽበት ተግባር እንጂ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ሂደት አይደለም። ከዚህ ቀደም ብለው ያሉ ዝግጅቶች በሙሉ በራሱ ደኅንነትን መስጠት የማይችል ለሁሉ የሚሆን ጸጋ አካል ናቸው። ብዙ ክርስቲያኖች ወደ ደኅንነት ለመራቸውና እግዚአብሔር ለሁሉ በሚሆን ጸጋ ላከናወነው ሥራ ምስክርነት መስጠት ይችላሉ። የውጤት አስገኝ ጸጋ ሥራ ግን የተለየና ወሳኝ ነው። አንዲት ነፍስ ከመንፈሳዊ ሞት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት በቅጽበት ትሸጋገራለች። የእግዚአብሔር ተግባር እንደመሆኑ መጠን ሥራው በቀላሉ ለአእምሮ የሚገባ አይደለም። እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር ከአበጀው በኋላ፥ ሕያው ነፍስ ያደረገው እንዴት እንደሆነ የሰው አእምሮ ለመመርመር እንደማይችል ሁሉ፥ የውጤት አስገኝ ጸጋ አሠራርንም መመርመር አይችልም።

4. የውጤት አስገኝ ጸጋ እርግጠኛነት

ርእሱ እንደሚያመለክተው ውጤት አስገኝ ጸጋ አንድን ነፍስ ወደ ደኅንነት በማምጣት ሥራው ሁልጊዜ ውጤታማ ነው። ይህ ጸጋ ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ ጋር ሲነጻጸር ለየት ይላል። ከዚህ የምናገኘው ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ በቀጥታ ሊገታ የሚችል መሆኑንና "አርምኒያን" እንደሚሉት ደኅንነትን ለማምጣት በቂ ቢሆንም እንኳ፥ ውጤታማ አለመሆኑን ነው።

ውጤት አስገኝ ጸጋ ግን ውጤታማ የሆነው ለሁሉ ከተሰጠ ጸጋ በመጠንና በኃይል በልጦ ሳይሆን፥ ሁሉን ቻይ ከሆነው እግዚአብሔር የሚወጣና የሚፈለገውን ውጤት ማምጣቱም እርግጠኛ ስለሆነ ነው። ከእግዚአብሔር ሥራዎች አንዳንዶቹን ላለመቀበል ይቻል ይሆናል። በክርስቲያን ሕይወት በሚገኝ ኃጢአት ምክንያት የሚያዝነው መንፈስ ቅዱስ፥ ክርስቲያን ከክፉ መንገዱ እንዲመለስ የሚያቀርበው ልመና ተቀባይነት አያገኝም ይሆናል። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ሥራ እውነትን ለመቀበል ፈቃደኝነትን የሚጠይቅ ባይሆንም ውጤት አስገኝ ጸጋ ግን ልንገታው የማንችለው ቅጽበታዊ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ቻርልስ ሆጅ ሲጽፍ፦ ‘‘በአውግስጢኖስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መሠረት፥ ውጤት የማስገኘት መለኮታዊ ጸጋ፥ በዳግም ልደት ውስጥ የሚመሠረተው፥ በመስማማት ወይም ጠንክሮ በመተባበር ወይም ተቀባዩ በጸጥታ በመቆየት ሳይሆን በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ ነው። ‘የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል’ የተናገረውን መፈጸም ነው። የአውግስጢኖስ ትምህርት ይህ እንደሆነ ታምኖበታል’’ ብሏል።

ውጤት አስገኝ ጸጋ የማይገታ ነው ስንል፥ ሊቋቋመው የሞከረ ኃይል ነበር ለማለት ሳይሆን፤ ጨርሶ የሚገታ አለመሆኑንና የተሞከረም አልነበረም ለማለት ነው። ይህ የዚህ ልዩ ጸጋ ባሕርይው ነው። ውጤት አስገኝ ጸጋ አይገታም። በዚህ መሠረት ኤ. ኤች. ስትሮንግ [A. H. Strong] የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ እንዲያውም ‘‘የማይገታ’’ የሚለውን ቃል ባንጠቀም ይሻላል በማለት የተሻለ አባባልን አቅርቧል፦ ‘‘ይህ ልዩ ጥሪ፥ ፍቱን እና አጥጋቢ ነው። ይኸውም ከቶ በማይሻር ሁኔታ ኃጢአተኛን ወደ ደኅንነት የመምራት ተግባሩን ይፈጽማል። ይህም ሁለት ነገሮችን ያመለክታል።

‘‘ሀ. የእግዚአብሔር ተግባር በሰው ፈቃድ ላይ የሚጫን ሳይሆን፥ ከአእምሮአችን ሕግ ጋር መስማማት ነው። ስለዚህ መግታት የሚለው ቃል ማስገደድ ወይም ግዳጅ ከሚለው፥ እግዚአብሔር በሰው ነፍስ ውስጥ ለሚሠራው ሥራ ባዕድ ከሆነ አሳብ ነጻ መሆኑ ታውቆ ይህ ስሜት ውድቅ መሆን አለበት።

‘‘ለ. በውጤት አስገኝ ጸጋ ውስጥ የእግዚአብሔር ሥራ፥ የኃጢአተኛን የጨለመ አእምሮና ፈቃድ እንዲሁም የጌታን የማዳን መንገድ እንዲመርጥ ማስቻል ነው’’ (ዮሐ. 1፡12-13)።

ውጤት አስገኝ ጸጋ በሙላት ግንዛቤ ሲያገኝ፥ በተጠቃሚዎቹ ደኅንነት ውስጥ እርግጠኛ ውጤት ይገኛል። በሁሉም ሁኔታዎች፥ ውጤት አስገኝ ጸጋን የሚቀበል በአንድ አፍታ ይድናል። በእያንዳንዱ ሰው ልምምድ ውስጥ ስናየው ደግሞ በክርስቶስ ማመን የየግለሰቡ ምርጫና

ተግባር ነው። ያም ሆኖ ክንውኑ የውጤት አሰገኝ ጸጋ ሥራም ነው። ውጤት አሰገኝ ጸጋ ዓመፀኛ በሆነ ልብ ውስጥ ሠርቶ አያውቅም። ደግሞም ማንም ከራሱ ፈቃድ ውጭ ድኖ አያውቅም። ይልቁን ‘‘ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና’’ (ፊልጵ. 2፡13) ከሚለው መመሪያ ጋር ሁልጊዜ የሚስማማ ነው።

5. የውጤት አሰገኝ ጸጋ መከላከያ

የእግዚአብሔር ሥራ የተፈለገውን ውጤት የሚያሰገኝ መሆን አለበት። ውጤት አሰገኝ ጸጋ ለሰው ልጅ እንደተሰጠና የተፈለገውን ውጤት እንደሚያስገኝ ቢያንስ አራት የተለያዩ መረጃዎችን ለማቅረብ እንችላለን። ውጤት አሰገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ሥራ እንደመሆኑ መጠን ውጤታማ ለመሆኑ እርግጠኞች ነን። ቀደም ሲል እንዳየነው ይህ ተግባር ከሰው ፈቃድ ጥገኝነት ውጭ ሁሉን ቻይ ከሆነው እግዚአብሔር የሚወጣ ስለሆነ ውጤታማ መሆኑ እርግጥ ነው። ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ አፈጻጸም ውስጥ የተገለጠው ሁኔታ የእግዚአብሔርን የማሳመን ሥራ ሊገታ ቢችልም፥ ሁሉን አድራጊነቱንና ሉዓላዊ ሥራውን ግን ጨርሶ ሊገታ አይችልም። ቻርልስ ሆጅ፡- ‘‘ውጤት አሰገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል ነው ብለን ከወሰንን፥ ይህን ርእስ በሚመለከት የሚነሡ አወዛጋቢ ጥያቄዎችን ሁሉ ይመልሳል... መላ ምቱን በመቃወም በርካታ ጽሑፎች ተጽፈዋል። ጽሑፎች ሁሉ ዳግም መፍጠር ወይም የሥርየት ጥሪ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ከተቀበሉ መላ ምታቸው ዋጋ ያጣል’’ ብሏል።

የውጤት አሰገኝ ጸጋ መሠረታዊ እምነት አስቀድሞ መወሰን ለሚለው ትምህርት በጣም አስፈላጊ ነው። ለእግዚአብሔር እቅድ የተመረጡ ሁሉ ይድኑ ዘንድ የግድ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ለተመረጡት ሁሉ ለሌሎች ከተሰጠው የበለጠ ጸጋ ይሰጣቸው ዘንድ አስፈላጊ ነው። የተመረጡትን ወደ ደኅንነት ለማምጣት ጸጋ ውጤታማ መሆን አለበት። የእግዚአብሔር አስቀድሞ መወሰንና የሥርየት ጥሪ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በግልጥ የተያያዙ ናቸው። እግዚአብሔር ሰውን የሚጠራው እንደ አሳቡ ነው (ሮሜ 8፡28)። ይህ አሳብ ሰፋ ተደርጎ በሚከተለው ሁኔታ ተገልጧል። ‘‘አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው’’ (ሮሜ 8፡30)። እዚህ ላይ ተገልጦ የምናየው ጥሪ ውጤት አሰገኝ ጥሪ እንደሆነ ግልጥ ነው። አስቀድሞ የተወሰኑ ሁሉ ተጠሩ፤ የተጠሩ ሁሉ ደግሞ ጸደቁና ከበሩ። እዚህ ላይ ለወንጌል የሚደረግ አጠቃላይ ጥሪና የተፈለገውን ውጤት የሚያመጣው ልዩ ጥሪ በግልጥ

ተለይተው ቀርበዋል። የውጤት አስገኝ ጥሪና የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ግንኙነት የቱንም ያህል ምሥጢራዊ ይሁን የውጤት አስገኝ ጥሪ ጭብጥ እርግጠኝነት አያጠራጥርም። የመዋጀት ዓላማ እንዲፈጸም የተመረጡት ሁሉ ወደ ክርስቶስ መምጣታቸው አስፈላጊ ነው (ዮሐ. 6፡37፣ 39፤ 17፡12)።

ውድቀትና መንፈሳዊ ሞት ውጤት አስገኝ ጸጋን ይሻሉ። የመንፈሳዊ ሕይወትን ከዳግም ልደት በፊት አለመኖር ስንመለከት፥ የውጤት አስገኝ ጸጋን አስፈላጊነት እንገነዘባለን። የውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የተመሠረተው በዚህ አሳብ ላይ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ምውት የሆነ ሰው መንፈሳዊ ሥራን ሊሠራ አይችልም። ከውጤቱ አንጻር ስናየው ፍጹም ውድቀት የውጤት አስገኝ ጸጋን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ይጠይቃል። ኤፌሶን 2፡8፡- ‘‘ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም’’ ይላል። ይህን ክፍል በሚመለከት የተለያየ አተረጓጎም ቢኖርም፥ ክፍሉ ጸጋ፥ ደኅንነትና እምነትም ጭምር የሚመጡት ከእግዚአብሔር መሆኑንና በርሱ ሥራ በማያምን ሰው ልብ ውስጥ ሊፈጠሩ አለመቻላቸውን ነው። ቻርልስ ሆጅ ስለዚህ ነጥብ ሲጽፍ፡- ‘‘የውርስ ኃጢአት መንፈሳዊ ሞትን አስከትሎ ማንኛውንም ዓይነት መንፈሳዊ በጎነት የማድረግ ችሎታን አጥፍቷል፤ በሚለው አቋም የሚስማሙ ሁሉ ከዚህ ሁኔታ ለመዳን የሚቻላቸው በየትኛውም ዓይነት ግብረገባዊ ወይም መለኮታዊ የማላመኛ ክርክር ሂደት ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ታላቅ ኃይልና ቅጽበታዊ ተግባር ነው’’ ብሏል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው መንፈሳዊ ሞት ደረጃና ፍጹም ውድቀት የገለጠውን ነገር ከተቀበልን፥ የችግሩ መፍትሔ የውጤት አስገኝ ጸጋ ትምህርት መሆኑንም መቀበል አለብን። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ሕይወትን ሊሰጥም ሆነ የሰውን ፈቃድ ሊያድስ አይችልም። ወንጌልንና በውስጡ ያሉ ዋና ነገሮችን የሚመለከት መረዳትን የሚሰጥ ብቻ ነው። መረዳት ብቻ ደግሞ ባገኘነው አዲስ እውቀት ላይ ተግባራዊ እርምጃ እንድንወስድ ሊያደርገን አይችልም።

ከዳግም ልደት ጋር ያለው ተመሳሳይነት። ውጤት አስገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑ ከዳግም ልደት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ጋር ባለው ተመሳሳይነት ይደገፋል። ልክ እንደ ውጤት አስገኝ ጸጋ፥ የዳግም ልደት ሂደትም የማግባባት ጉዳይ ወይም ምክንያታዊ ለውጥ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ዳግም ልደት ቅጽበታዊ የእግዚአብሔር ሥራ ከሆነ፥ ውጤት አስገኝ ጸጋም በዚሁ ውስጥ ይካተታል። ሁለቱም በቀላሉ የማንረዳቸው ቢሆኑ እንኳን ለደኅንነት አስፈላጊዎች ናቸው።

6. በውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ ትምህርት ላይ የሚቀርቡ ተቃውሞዎች

ከሰው ጥረት አንጻር። ሰፋ ባለ ሁኔታ በእምነት ላይ የተመሠረተ ትምህርት፥ በምክንያት ላይ ከተመሠረተ ትምህርት ይልቅ ተቃውሞ እንደሚገጥመው የታወቀ ነው። የተለመደው ተቃውሞ፥ ‘‘ይህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሰው ልጅ ለማመን የሚያደርገውን ጥረት ሁሉ ይፃረራል’’ የሚል ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጅ ለውጤት አስገኝ ጥሪም ሆነ በክርስቶስ ማመንን በሚመለከት ስላለበት ኃላፊነት በቂ ምስክርነት ይሰጣሉ። የሰው ልጅ የሚያደርገው ጥረት ከመለኮት ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት መገንዘብ የሚያስቸግር መሆኑ እርግጥ ነው። የዚህ ችግር መፍትሔ ግን ከእምነት ውጭ ሊገኝ አይችልም። በውጤት አስገኝ ጸጋ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥ የሰውን ልጅ ኃላፊነቱን ከመወጣት ወደ ኋላ ሊጎትተው አይገባም። ነገር ግን እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ሰው ለማድረግ መሻት የለበትም። በደኅንነት ክልል ውስጥም ሰው መፈለግ ያለበት ለመዳን ነው እንጂ ራሱን ለማዳን አይደለም። የደኅንነት ምስጢር ሊያድነን በሚችለው በእግዚአብሔር ላይ በመደገፋችን የተወሰነ ነው።

ከማመናችን በፊት የጸጋ ሥራ አስፈላጊ መሆኑን መረዳታችን፥ የሰዎችን ደካማነት ይበልጥ ያስገነዝበናል። በዚህም የተነሣ ሰዎች ሁሉን ማድረግ በሚችል እግዚአብሔር ላይ ራሳቸውን መጣል እንዳለባቸው እንረዳለን። ክርስቶስ እንዲፈውሰው የለመነው ዓይነ ስውር ራሱን ለማዳን ፈጽሞ አለመቻሉ ከልመና አላገደውም። ነገር ግን፥ መሻቱ ሊያድነው ወደሚችለው ክርስቶስ መራው። ስለዚህ ይህ ፍጹም ውድቀትን የሚመለከት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ በሚያደርገው ጥረት ተስፋ ከማስቆረጥ ይልቅ፥ የእግዚአብሔርን ኃይል ሊያንላና የደኅንነትን ፍጹም አስፈላጊነት ሊገልጥ ይገባል። ቅዱሳት መጻሕፍት ይህን ጉዳይ እንዲህ በማለት ያስታውሱናል፥ ‘‘አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፥ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም’’ (ዮሐ. 6፡37)። በአንድ በኩል የእግዚአብሔር ጥሪ እርግጠኛነት ይታየናል። የተመረጡ ሁሉ ወደ ክርስቶስ ይመጣሉ። በሌላ በኩል ወደ ክርስቶስ የሚመጣ ሁሉ ወደ ውጭ አይወጣም። ስለዚህ የሰው ልጅ ወደ ክርስቶስ የመምጣት ኃላፊነቱ እንዳልተነሣለት እናያለን።

የሰው ኃላፊነት በተቃራኒው ሲታይ። በውጤት አስገኝ ጸጋ ትምህርት ላይ የሚነሣው ሁለተኛ ተቃውሞ መሠረት ደግሞ፥ ‘‘ትምህርቱ የሰውን ልጅ ኃላፊነት ይፃረራል’’፤ ሥራውን የሚሠራው እግዚአብሔር

ራሱ ብቻ ከሆነ፥ የሰው ልጅ ባለማመን ኃላፊነት መጠየቅ የለበትም የሚል ነው። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ብቁ አለመሆን ኃላፊነትን ያስወግዳል አይልም። የሰው ልጆች የሚፈረድባቸው የተለመደውን ኃጢአታዊ ተፈጥሮ በመከተላቸው ነው። ‘‘በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል’’ (ዮሐ. 3፡18) የሚለው እውነት የማይለወጥ ነው። ያለመብቃት ጉዳይ ለሁሉ በተሰጠ ጸጋ ተቀንሷል። ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ የሰውን ፈቃድ ለማደስ ወይም ሰውን ወደ ደኅንነት ለማምጣት በቂ ባይሆንም፥ የወንጌልን ቃል፥ የደኅንነትን አስፈላጊነት፥ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የሚያመጣውን ፍርድና የሰው ልጅ ክርስቶስን የመቀበል ኃላፊነት እንዳለበት ለመግለጥ ይችላል፥ ይገልጣልም። እግዚአብሔር ለማመን የሚፈቅደውን ማንኛውንም ሰው እንደማይቃወም ግልጥ ነው። ውጤት አስገኝ ጸጋ በሌለበት በማንኛውም ሁኔታ ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱን እንመለከታለን። በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና በሰው ልጅ ኃላፊነት መካከል ያለውን ግንኙነት በሰው አእምሮ ለመፍታት ባይቻልና አለመጣጣም ያለ ቢመስል እንኳን ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል መገለጥ በእምነት ሊቀበል ይችላል።

በቂ ጸጋ ለሁሉም ተሰጥቷል? የውጤት አስገኝ ጸጋን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚቃወመው ሦስተኛ አሳብ፥ ለማመን የሚያስችል በቂ ጸጋ ለሰው ልጆች ሁሉ ተሰጥቷል በሚለው የተሳሳተ ቅድመ አሳብ ላይ ይመሠረታል። በዚህ ትምህርት መሠረት ውጤት አስገኝ ጸጋ የሚታየው አንዳንድ ጊዜ የሚፈለገውን ውጤት የሚያመጣ፥ በሌላ ጊዜ የማይሳካለት ሆኖ ነው። ይህ ከፊል-ፐሌጂያን [Semi-Pelagian] የሥነ-መለኮት ትምህርት አስተሳሰብ ሲሆን፥ በአንዳንድ አተረጓጎም ረገድ ልዩነት ቢኖራቸውም የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና፥ የአርምኒያንም አቋም ነው። የዚህ ተቃውሞ ደካማ ጎን ‘‘ሁሉም እንዲያምኑ በቂ ጸጋ ተሰጥቷቸዋል’’ የሚለው የተሳሳተ እምነት ነው። ይህን ቅዱሳት መጻሕፍት አያስተምሩም፤ ከሕይወት ልምምድ ጋርም የሚጋጭ ነው። አንዳንድ ሰዎች ወንጌልን እየሰሙ የጸጋን ሥራ የሚቃወሙት ጸጋው በባሕርዩ ውጤት አስገኝ ስላልሆነ ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ለተመረጡት የደረሰው የእግዚአብሔር የደኅንነት ጥሪ ውጤታማነቱ እርግጠኛ በመሆኑ የተጠሩት ሁሉ በዚህ ጸጋ ድነዋል። የአርምኒያን አመለካከት ለዚህ እውነታ በቂ ማብራሪያ የለውም።

የውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ ትምህርት የሰው አእምሮ የማይረዳው ነገር ነው። የውጤት አስገኝ ጸጋን ፅንሰ-አሳብ መረዳትን አስመልክቶ የሚነሡ ችግሮች ሁሉ መፍትሔ የሚገኝላቸው አይደሉም።

ይህም የሰው ልጅ መለኮታዊው ሥራ ማለትም ደኅንነት በሕይወቱ እንዴት እንደሚከናወን ለመገንዘብ ካለበት የእውቀት ውሱንነትና የራሱ ፈቃድ ከተሳሳተ ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባው ከመሆኑ የተነሣ እንጂ፥ የተገለጡት እውነቶች በራሳቸው ሥርዓት የማይሄዱ ሆነው አይደለም። ተፈላጊውን ውጤት የሚያስገኝ ጥሪ መኖሩን የሚያረጋግጡ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ይህን ትምህርት መቃወም፥ መለኮታዊን የደኅንነት ዕቅድ እርግጠኛ ተፈጻሚነትን እንደመካድ ነው።

14

ዳግም ልደት

1. የዳግም ልደት አስፈላጊነት

ከማንኛውም የሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርቶች ይልቅ የዳግም ልደት መሠረታዊ ትምህርት ለውጤታማ ስብከት እንደ መልህቅ የሚቆጠር ነው። የዚህን ትምህርት ባሕርይ ከግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት አለመቻልና አስፈላጊነቱን በግልጥ አለመረዳት፥ የወንጌል ስብከት የሚፈለገውን ውጤት እንዳያስገኝ ያደርገዋል። ወንጌላውያንም ሆኑ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን ይህን ትምህርት በሚገባ መረዳት እንዳለባቸው ሊገነዘቡ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዳግም ልደት የሚያቀርበው ፅንሰ-አሳብ ቀላል ነው። ስለሆነም ለትክክለኛነት ስብከት ሃይማኖታዊ ታሪኩን ማጥናቱ በፍጹም አስፈላጊ አይደለም። መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ታሪክ ግን ይህ ጉዳይ ለችግር የተዳረገ መሆኑን ገልጦ፥ ትምህርቱን በሚገባ አለመረዳት አደገኛ መሆኑን ያስጠነቅቃል። የዳግም ልደት መሠረታዊ ትምህርት በሚገባ ለሚመለከቱት፥ ለሚያስቡበትና ከዚህ እውነት ባገኙት ብርሃን ለሚኖሩ ሁሉ በረከትን ያስገኛል።

2. የዳግም ልደት ትርጉም

የቃሉ ፍቺ። በአጠቃላይ የዘላለምን ሕይወት ከመስጠት ጋር የተያያዘ ቢሆንም፥ ዳግም ልደት የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ስፍራ ብቻ ነው የሚገኘው (ማቴ. 19፡28፤ ቲቶ 3፡5)። ከእነዚህ ሁለት ስፍራዎች በአንዱ ብቻ በዚህ ስሜት ቀርቧል። እሱም ‘‘ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ’’ የሚለው ነው (ቲቶ 3፡5)። ‘ፐሊንጂኔስያስ’ [‘palingenesias’] የሚለው የግሪክ ቃል ‘‘አዲስ ልደት፥ እንደገና መሠራት፥ መታደስ፥ እንደገና መፈጠር’’ በሚሉ ቃሎች በሚገባ ተተርጕሟል። ይህ ቃል ለሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን፥ በሺሁ ዓመት መንግሥት የሚታደሱትን ለማይና ምድርንም በሚመለከት አገልግሎት ላይ ውሏል (ማቴ. 19፡28)። ዳግም ልደት ከሰው ተፈጥሮ ጋር ያለውን ግንኙነት ስንመለከት የዘላለምን ሕይወት የሚገልጡ የተለያዩ አገላለጾችን እንደሚያካትት መመልከት እንችላለን። እነርሱም አዲስ ሕይወት፥ አዲስ ልደት፥ መንፈሳዊ ትንሣኤ፥ አዲስ ፍጥረት፥ አዲስ አእምሮ፥ ሕያው ሆነ፥ የእግዚአብሔር ልጆችና ወደ መንግሥቱ መፍለስ የሚሉት ናቸው። በቀላል

አባባል ስንገልጠው፥ ዳግም ልደት በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ የዘላለምን ሕይወት ሊወክሉ የሚችሉ ነገሮችን በሙሉ ያካትታል።

በሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ ያለው አጠቃቀም። የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ‹‹ዳግም ልደት›› በሚለው ቃል ላይ ያላቸው መረዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር ትንሽ የተምታታ ነው። እንደ ‹‹መለወጥ››፥ ‹‹መቀደስ›› እና ‹‹መጽደቅ›› የመሳሰሉት ቃላት በዳግም ልደት አሳብ ውስጥ በመመሳሰል ወይም በመካተት ይገለጣሉ። የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት፥ ዳግም ልደት፥ በደኅንነት ውስጥ የሚካተቱትን እንደ መጽደቅና መቀደስ ብቻ ሳይሆን፥ የመክበርንም አሳብ እንደሚያጠቃልል አድርጋ ትቆጥራለች። በሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ‹‹ዳግም ልደት›› የደኅንነትን መንገድ፥ ተግባር፥ ሂደትና የመጨረሻ ግቡን ሁሉ እንደሚያካትት ተደርጎ ተወስዷል።

የፕሮቴስታንት ሥነ-መለኮት ሊቃውንት የዳግም ልደትን ትርጉም በማስፋፋት ረገድ ብዙ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ከቀድሞ ጀምሮ የነበሩ ሉተራውያን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዳግም ልደት፥ አንድ ኃጢአተኛ ጠፍቶ ከነበረበት ሁኔታ መጽደቅን ጨምሮ ወደ ደኅንነት የሚደርስበትን ጠቅላላ ሂደት እንደሚጨምር አድርገው ተጠቅመውበታል። ኋላም ሉተራውያን መጽደቅ የሕይወትን መታደስ (ለውጥ) የሚጨምር ስላልሆነ፥ የዳግም ልደት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መቀደስን አያካትትም፥ የሚለውን አቋም በመያዝ ይህን መሠረታዊ ትምህርት የሚመለከት ማብራሪያ ለመስጠት ሞክረዋል። የሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕፃናት በውኃ ጥምቀት ጊዜ ዳግም ይወለዳሉ የሚለውን አቋማቸውን አሁንም እንደያዙ ናቸው። እንዲህም ሆኖ ይህ ዳግም ልደት ወደምትታየው ቤተ ክርስቲያን የመግባታቸው ምልክት እንጂ፥ እውነተኛ ደኅንነት መቀበላቸውን የሚያመለክት አይደለም ይላሉ። ስለዚህ በዚህ አቋማቸው ዳግም ልደት ለደኅንነት የዝግጅት ሥራ ይገልጣሉ።

የሕፃናትን ዳግም ልደት በሚመለከት ቫለንታይን የተባለው የሉተራን ሥነ-መለኮት ሊቅ፥ ‹‹ሕፃናት ዳግም የሚወለዱት በጥምቀት ነው እንበልን? መልሳችን በሚገባ አዎን፥ የሚል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህን የምንለው የሕይወት መሠረቱና ፈጻሚው ጸጋው በመሆኑ፥ የመጨረሻ ቃል ኪዳናዊ የሆነ ሥራ ከእግዚአብሔር በሚሰጥ ጽድቅ፥ በመንፈስ ቅዱስ ቸርነት እና ኃይል የሚሆን ነው ለማለት ይቻላል›› ብሏል። ሆኖም ቫለንታይን ጥምቀት ለሕፃናት አዲስ ልደትን ይሰጣል የሚለውን አባባል ይቃወማል። ቫለንታይን በሌላ ስፍራ ሲጽፍ፥ ‹‹መጽደቅ ከዳግም ልደት እና ከመቀደስ የሚቀድም ነው›› ብሏል። የሉተራውያን ሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዳግም ልደት የሚለውን ቃል መጽሐፍ ቅዱስ

የዘላለም ሕይወት ስለመስጠት በሚናገር ስሜት አይጠቀሙበትም። መቀደስን ከዳግም ልደት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውጭ ማድረጋቸው ግን እርግጥ ነው።

ከተሐድሶ ሥነ-መለኮት ሊቃውንት አንዱ ካልቪንና ተከታዮቹ ይህን ጉዳይ በሚመለከት አንድ ጥርት ያለ አቋም ባለመያዝ ሌሎች የሠሩትን ስሕተት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ፈጽመዋል። በአሥራ ሰባተኛው ክፍለ-ዘመን አካባቢ መለወጥ ከዳግም ልደት ጋር ተመሳሳይ ተደርጎ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ አመለካከት መለወጥ የሰው፥ ዳግም ልደት ደግሞ የእግዚአብሔር ተግባር የመሆኑን ዋና መሠረታዊ እውነት የዘነጋ ነበር። ከዚህም ሌላ መለወጥ ብዙ ጊዜ ከዳግም ልደት ጋር የተያያዘ ቢሆንም፥ ክርስቶስ በተነበየው በጴጥሮስ መመለስና መታደስ (ሉቃስ 22፡32) እንደሚታየው ሁልጊዜ የሚሆን ግን አይደለም። ካልቪን እንኳ በመለወጥና በዳግም ልደት መካከል ግልጥ የሆነ ልዩነት ማሳየት ሳይችል ቀርቷል። ቻርልስ ሆጅ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ለመግለጥ ግሩም የሆነ አሳብ አቅርቧል። ሼድ ከሆጅ ጋር በመስማማት የሚከተለውን ተንጻጻሪ አሳብ አቅርቧል፥ ‹‹ዳግም ልደት በአንድ ወቅት የሚሆን አንድ ድርጊት ሲሆን፥ መለወጥ ግን አንድ ተግባር ወይም ሂደት ነው። ዳግም ልደት የሕይወት መነሻ ሲሆን፥ መለወጥ የሕይወት ዘገምተኛ ለውጥና መግለጫ ነው። ዳግም ልደት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ተግባር ሲሆን፥ መለወጥ ግን ሙሉ በሙሉ የሰው ልጅ ተግባር ነው። ዳግም ልደት ምክንያት፥ መለወጥ ግን ውጤት ነው። ዳግም ልደት ቅጽበታዊ፥ መለወጥ ግን ሂደታዊ ነው›› ብሏል።

ባለፈው ምዕተ ዓመት የካልቪኒዝም ሥነ-መለኮታዊ ሊቃውንት ዳግም ልደት የዘላለም ሕይወት መስጠትን በሚገባ እንደሚያመለክት ተስማምተዋል። ቻርልስ ሆጅ እንዳለው፦ ‹‹ዳግም ልደት የሚጠቅመው፥ ለጠቅላላ የመቀደስ ሥራ ወይም በመለወጥ ውስጥ ለሚኖር የመጀመሪያ ሥራ፥ ደግሞም መለስተኛ ለሆነ የማጽደቅ ሥራ ወይም በየትኛውም ደረጃ ለሚታይ ውጫዊ ለውጥ አይደለም። ነገር ግን ሰው ከመንፈሳዊ ሞት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ለሚሸጋገርበት ቅጽበታዊ ለውጥ ነው። ይህ በአሁኑ ጊዜ ስለ ዳግም ልደት የተደረሰበት ሁለንተናዊ ስምምነት ነው።›› ስለዚህ የዳግም ልደትን መሠረታዊ ትምህርት የሚያጠና ሰው ማተኮር ያለበት፥ ደኅንነት የዘላለምን ሕይወት ከመስጠት ጋር ያለውን የግንኙነት አቅጣጫ ነው። በደኅንነት ውስጥ የዘላለም ሕይወትን በመስጠት ሥራ ዙሪያ ያሉ የሚቀድሙ ወይም ከእርሱ ቀጥለው ወዲያውኑ የሚመጡ ነገሮች ተለይተው ለብቻቸው የሚታዩና የእግዚአብሔር ሥራዎች መሆን አለባቸው።

3. ዳግም ልደት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው

የእግዚአብሔር ሥራ። ዳግም ልደት በባሕርዩ ፍጹም የእግዚአብሔር ሥራ ነው ። አንዳንድ ጊዜ እንደ ውጤት የታየ ቢሆንም፥ እያንዳንዱ ሁኔታ የሚያመለክተው ዳግም ልደት የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ነው። እጅግ ጠቃሚ የሆኑ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ዳግም ልደት ይናገራሉ (ዮሐ. 1፡13፤ 3፡3-7፤ 5፡21፤ ሮሜ 6፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡17፤ ኤፌ. 2፡5፥ 10፤ 4፡24፤ ቲቶ 3፡5፤ ያዕ. 1፡18፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡9)። ዳግም የተወለደ ሰው ከእግዚአብሔር ተወለደ እንጂ ‘‘ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለደም’’ (ዮሐ. 1፡13) ተብሎ በግልጥ ተጽፏል። ዳግም ልደት ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር ከሆነው ትንሣኤ ጋር ተመሳሳይ ነው (ዮሐ. 5፡21፤ ሮሜ 6፡13፤ ኤፌ. 2፡5)። በሌሎች ክፍሎች ደግሞ ዳግም ልደት በባሕርይ ከእግዚአብሔር የሆነ የመፍጠር ሥራ ተደርጎ ቀርቧል (ኤፌ. 2፡10፤ 4፡24፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡17)። እንግዲህ ዳግም ልደት ከሌሎች አስፈጻሚ አካሎች ተለይቶ በእግዚአብሔር ተአምራዊ ኃይል የሚፈጸምና የሱ ሥራ መሆኑን በግልጥ ለመመልከት እንችላለን።

ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ሥራ ነው። ዳግም ልደት በሚገባ ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ሥራ ነው። እንደ ሥርየት አስገኝ ጸጋ ሁሉ የዳግም ልደት ሥራም ብዙ ጊዜ የተገለጠው በሥላሴ አካላት መካከል ልዩነት ሳይደረግ በእግዚአብሔር ሥራነቱ ሲሆን፥ በጥቂት ቦታዎች ተለይቶ የእግዚአብሔር አብ፥ የእግዚአብሔር ወልድ፥ በሌሎች ጥቂት ስፍራዎች ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተደርጎ ቀርቧል። ቢያንስ በአንድ ስፍራ የሥላሴ የመጀመሪያው አካል የዳግም ልደት ምንጭ እንደሆነ ተገልጧል (ያዕ. 1፡17-18)። ክርስቶስ ከዳግም ልደት ጋር የተያያዘበት ሁኔታም በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራዎች ተጠቅሷል (ዮሐ. 5፡21፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡17፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡12)። መንፈስ ቅዱስ የዳግም ልደት ፈጻሚ እንደሆነ በግልጥ ቀርቧል (ዮሐ. 3፡3-7፤ ቲቶ 3፡5)። የሥላሴ አካላት አንድነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ እያንዳንዱ አካል የራሱ የሆነ ድርሻ አለው። በሌሎቹ የእግዚአብሔር ሥራዎች እንደሆነው ሁሉ፥ የሥላሴ አካላት በክርስቶስ መፀነስ ውስጥ ስፍራ ነበራቸው። በዳግም ልደትም የመጀመሪያው የሥላሴ አካል የአማኙ አባት ይሆናል፤ ሁለተኛው የሥላሴ አካል የራሱን የዘላለም ሕይወት ይሰጠዋል (1ኛ ዮሐ. 5፡12)፥ ሦስተኛው የሥላሴ አካል፥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ዳግም ልደትን በብቃት የሚያስፈጽም ይሆናል። የደኅንነት ሥራ የክርስቶስ ነው ባልንበት መንገድ የዳግም ልደት ሥራ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ነው ለማለት እንችላለን።

4. ዳግም ልደት የዘላለምን ሕይወት የማግኘት ሂደት ነው

የዘላለም ሕይወት ለዳግም ልደት ማዕከሉ ነው። በዳግም ልደት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ ያለው ማዕከላዊው ነገር ዘላለማዊ ሕይወት ማግኘት ሲሆን፥ ያስፈለገውም በመንፈሳዊ ሞት መከሠት ምክንያት ነው። የዘላለም ሕይወት የሚገኘው እንዴት እንደሆነ ለመረዳት የሚታይ ዘዴ ወይም ሂደት ስለሌለ በእርግጥ አስቸጋሪ ይሆናል። ዳግም ልደት በባሕርዩ ተአምራዊ ስለሆነ ከሰው አእምሮ በላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዳግም ልደት ውስጥ የሚገኘውን የዘላለም ሕይወት ለመግለጥ ሦስት የተለያዩ ምሳሌዎች ያቀርባል።

ሉዲሰ ልደት። አንዳንድ ጊዜ ዳግም ልደት አዲስ ልደት በሚለው ሥዕላዊ አገላለጥ ይቀርባል። ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ እንዳለው "እንደገና መወለድ ያስፈልጋል" (ዮሐ. 3፡7)። ከሰብአዊ ወላጆች ከመወለድ ጋር ሲነጻጸር ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን "ከእግዚአብሔር" መወለድ አለበት (ዮሐ. 1፡13)። በያዕቆብ 1፡18 መሠረት፥ "ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን።" ይህ ሥዕላዊ አገላለጥ የእግዚአብሔር ልጅ ከሰማያዊ አባቱ ጋር ያለውን ጥብቅ ግንኙነትና፥ በክርስቶስ ውስጥ ያለ አማኝም ከእግዚአብሔር ከሚመጣ የዘላለም ሕይወት ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጥ እጅግ በጥሩ ሁኔታ የቀረበ ነው።

መንፈሳዊ ትንሣኤ። ቅዱሳት መጻሕፍት ዳግም ልደትን በመንፈሳዊ ትንሣኤ መስለው በተደጋጋሚ አቅርበውታል። ክርስቲያን "ከሞት ወደ ሕይወት" እንደተሻገረ ተገልጧል (ሮሜ 6፡13)። ደግሞም እግዚአብሔር፥ "ግና በበደላችን ሙታን በነበርን ጊዜ በክርስቶስ ሕያዋን እንዳደረገን" ተጽፏል (ኤፌ. 2፡5)። ኢየሱስ ራሱም እንዲህ ብሏል፦ "እውነት እውነት እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ" (ዮሐ. 5፡25)። በትንሣኤ ሕያዋን የመሆናችን እውነት ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሸጋገሩ ሰዎች እንድንኖር የሚያበረታታን ሆኗል (ሮሜ 6፡13፤ ኤፌ. 2፡5-6፤ ቈላ. 2፡12፤ 3፡1-2)።

ሉዲሰ ፍጥረት። ዳግም ልደት በፍጥረት ወይም እንደገና በመፍጠር ሥራም ተገልጧል። "መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" (ኤፌ. 2፡10)፤ ስለዚህ "ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅ እና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ ተብለን ተመክረናል (ኤፌ. 4፡24)። በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17 የተሰጠው ማብራሪያ እጅግ ግልጥ ነው። "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ

ፍጥረት ነው፥ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል።'' ዳግም ልደትን የሚገልጠው የአዲስ ፍጥረት አምሳያ፥ ይህ ሥራ በባሕርዩ በሰው ሕይወት ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት አዲስ ባሕርይንና አዲስ ችሎታን እንደሚሰጥ የሚያመለክት ነው። ይህን ያገኘ ሰው በዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ዳግም የተወለዱትን ሁሉ የሚያጠቃልለው አዲስ ፍጥረት አካል ይሆናል። የዚህ አዲስ ፍጥረት ራስም ክርስቶስ ነው። ለክርስቲያን የተሰጠው ይህ አዲስ ሕይወት፥ ዳግም በተወለዱት መካከል ብቻ በሚገኘው አዲስ ችሎታና ተግባር የሚገለጥ ይሆናል። ይህም እውነት የመነጨውና የተመሠረተው ለዳኑ ሁሉ በሚሆነው ሌላ መለኮታዊ አገልግሎት ላይም ነው።

የዘላለምን ሕይወት የተቀበልነው በእምነት ነው። በዳግም ልደት መሠረታዊ ትምህርት ሊዘነጋ የማይገባው በጣም አስፈላጊ እውነት፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ያመነ ሰው ሁሉ የዘላለም ሕይወት የተቀበለ መሆኑ ነው። ይህ እውነት፥ ዳግም ልደትን ከደኅንነት የሚቀድም ወይም አንዲት ነፍስ ወደ እምነት ትመጣ ዘንድ የሚያደርጋት ነገር አድርጎ ከማሰብ ያድናል። ዳግም ልደት የደኅንነት ማዕከል ነው። ያለ ዳግም ልደት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ዘላለማዊ ግንኙነት አይኖረውም። ዘላለማዊ ሕይወትንም ያጣል። ጽድቅ እና ቅድስና በተለይ ኃጢአትን በሚመለከት ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፥ ዳግም ልደት ደግሞ ሕይወትን የሚሰጥ ነው። ይህ ትምህርት ሰው ራሱን የማዳን ውስጣዊ ችሎታ አለው የሚለውን ፍልስፍና ውድቅ ያደርገዋል። ዳግም ልደት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ ነው፤ የትኛውም ሰብአዊ ጥረት የዘላለምን ሕይወት ሊሰጥ አይችልም። ትክክለኛው የዳግም ልደት ትምህርት፥ በኃጢአቱ ሟች ለሆነ የሰው ዘር የተትረፈረፈ ቸርነት ላሳየ እግዚአብሔር ስም ክብር ይሰጣል።

5. ዳግም ልደት የተፈጸመበት የተለየ መንገድ የለም

የካልቪን ሥነ-መለኮት ሊቃውንት ለዳግም ልደት የተለየ መንገድ አለ የሚለውን አሳብ ተቃውመዋል። ሊቃውንቱ መለኮታዊው የዳግም ልደት ሥራ ይፈጸም ዘንድ ምንም ዓይነት የተለየ መንገድ ተግባራዊ አልሆነም ይላሉ። ዳግም ልደትን ለማምጣት ልዩ መንገድ ተግባራዊ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የሚያስችለን ስለ ሥርየት አስገኝ ጸጋ ያለን አመለካከት ነው። የፐሌጂያን እና የአርምኒያን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ፥ ከሰው ልጅ ፈቃድ፥ ከሰው ከፊል ችሎታ እና ከተፈጥሮ ኃይላት ጋር በመተባበር ዳግም ልደትን የሚያመጣ ስለሆነ፥ ዳግም ልደት የሰውን ምግባር የሚጨምር መንገድ እንዳለው ያመለክታሉ።

ይህ አሳብ ችግርን የሚያስነሣ ነው። ምክንያቱም ሰው በደኅንነቱ ውስጥ ሊያደርግ የሚችለው አንዳችም ነገር እንደሌለ ከተቀበልንና የሥርየት አስገኝ ጸጋን መሠረታዊ ትምህርት ካመንን፥ ዳግም ልደት የሚከናወነው ያለ አንዳች የተለየ መንገድ መሆኑን መቀበል አያስቸግርም።

የሰው ፈቃድ ምንም ውጤት ማምጣት አይችልም። የካልቪን ሥነ-መለኮት ትምህርት የሥርየት አስገኝ ጸጋን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ከመጠበቅ አንጻር የሰው ፈቃድ የነፍስን መዳን በማስገኘት ረገድ ምንም ዓይነት ለውጦችን ለማምጣት አይችልም የሚል አቋም ያለበት ነው። ከእምነት ጋር በተገናኘ ሁኔታም ቢሆን የሰው ፈቃድ ተግባራዊ የሚሆነው በሥርየት አስገኝ ጸጋ ውስጥ ነው። ወንጌልን በመስማት ረገድ የሰው ልጅ ፈቃድ ከሥርየት አስገኝ ጸጋም ውጭ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል። በዳግም ልደት ውስጥም የሰው ፈቃድ አንዳችም ነገር ለማድረግ የሚችል አይደለም። የዳግም ልደት ሥራ ባሕርዩ ማንኛውንም ዓይነት የሰው እርዳታ አይፈልግም። ተፈጥሮአዊ በሆነው የመወለድ ሂደት ውስጥ አንድ ሕፃን ይፀነስ እና ይወለድ ዘንድ የሚያደርገው ነገር እንደሌለ ሁሉ፥ አንድ ሰውም የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ዳግም ይወለድ ዘንድ የሚያደርገው አንዳችም ነገር የለም። እርግጥ በአዲስ ልደት ውስጥ የሰው ፈቃድ የዳግም ልደትን ሥራ የሚቃወም አይደለም። በመለኮታዊ ጸጋ እንዲያምንም አይገደድም። በሥጋ ትንሣኤ ጊዜ የአካል ትንሣኤ ይፈጸም ዘንድ የሞተው አካል የሚያደርገው አንዳችም ነገር እንደሌለ ሁሉ፥ በዳግም ልደት ውስጥም የሰው ፈቃድ ምንም ማድረግ አይችልም። ይህ ነገር የሰው ፈቃድ ተጽዕኖ እንደተደረገበት ወይም ሰው ፈቃድን እንደተቀማ የሚያሳይ ወይም የማመን ኃላፊነት እንደሌለበት የሚያመለክት አይደለም። ነገር ግን ዳግም ልደት፥ በሚያምን ሰው ልብ ውስጥ የሚሠራ ፍጹም የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ሌላ መንገድ አያስፈልግም። የዳግም ልደት ሥራ በሌላ በማንኛውም መንገድ የሚፈጸም አይደለም። ብዙ ጊዜ ከዳግም ልደት በፊት የሚፈጸሙ፥ ለሁሉ እንደተሰጠ ጸጋና እሱ እንደሚያስከትለው ውጤት ያሉ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም፥ ከዳግም ልደት ሥራ በግልጥ የተለዩ መሆን አለባቸው። የሥርየት አስገኝ ጸጋ ሥራ ከዳግም ልደት ጋር አብሮ የሚሄድና ፍጹም አስፈላጊ ነገር ቢሆንም፥ በራሱ ዳግም ልደትን የሚያስገኝ አይደለም። ሥርየት አስገኝ ጸጋ ግን ዳግም ልደትን በእርግጠኝነት የሚፈጸምና የሚቻል ነገር ያደርገዋል። ዳግም ልደት ቅጽበታዊ ተግባር በመሆኑ ለአፈጻጸሙ ምንም የተለየ መንገድ አያስፈልገውም። የእግዚአብሔር ሥራ እንደሆነ በተደጋጋሚ መገለጡና ቅዱሳት መጻሕፍት

ስለ ሥርየት አስገኝ ጸጋ የሰጡት መገለጥ ዳግም ልደትን ለማምጣት ሌላ መንገድ ያስፈልጋል የሚለውን ትምህርት ውድቅ ለማድረግ በቂ መረጃዎች ናቸው።

6. ዳግም ልደት በልምምድ የምናረጋግጠው ነገር አይደለም

ልምምድ ዳግም ልደትን ተከትሎ የሚመጣ ነገር ነው። ስለ ክርስትና እምነት በሚሰጥ ምስክርነት ውስጥ ስለ ዳግም ልደት ልምምድ እጅግ ብዙ ነገር ተብሏል። ዳግም ልደት በቅጽበት የሚፈጸም የመለኮት ፈቃድና ተግባር ከሆነ፥ ልምምድ አይደለም ወደሚል ማጠቃለያ እንደርሳለን። እርግጥ አዲስ ልደትን ተከትለው የሚመጡ እጅግ በርካታ ልምምዶች በሕይወታቸን ሊፈጸሙ ይችላሉ። በተለመደው መንገድ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን ልምምድ፥ ከአዲስ ልደት በኋላ ወዲያውኑ የሚሰጥ ሊሆን ይችላል። ይህ እውነት ዳግም ልደት የልምምድ ውጤት ያለመሆኑን አሳብ የሚሽር አይደለም። ዳግም ልደት ቅጽበታዊ የእግዚአብሔር ሥራ ነው በሚለው አሳብ ከተስማማን፥ ልምምድ ጊዜ የሚጠይቅ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ አይሳነንም። ስለዚህ አዲስ ልደትን የሚመለከቱ ልምምዶች በሙሉ ከዳግም ልደት ቀጥለው የሚመጡና ከተገኘው አዲስ ሕይወት የሚመነጩ መሆናቸውን ለማሰብ እንችላለን፤ ይህን ጉዳይ በተመለከተ እውነተኛ ያልሆነን ነገር ልንለማመድ አንችልም። ልምምድ ከመገኘቱ በፊት ዳግም ልደት ሙሉ በሙሉ መፈጸም አለበት። ዳግም የተወለደች ነፍስ ቅጽበታዊ የሆነ የአዲስ ሕይወት ግንዛቤ አላት። የአዲስ ልደት ሥራ ልምምድንም ሆነ ትንተናን የሚመለከት አይደለም። አዲስ ሕይወት የበርካታ ልምምዶች መንሥኤ ሊሆን ይችላል፤ የአዲስ ልደት ሥራን ግን ሰው እንደማንኛውም ልምምድ በራሱ የሚለማመደው አይደለም።

ዳግም ልደት በልምምድ ላይ የሚመሠረት አይደለም። ዳግም ልደት በልምምድ ላይ የሚመሠረት አለመሆኑ ያልዳኑ ሰዎች ከዚያ የሚቀድሙና ልንለማመዳቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ ከሚል አሳብ እንዲገላገሉ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አለው። ነፍሳትን ለጌታ ለመማረክ የሚፈልጉትንም ዳግም ልደት ከመፈጸሙ በፊት በከፊልም ቢሆን የደኅንነትን ፍሬ ከመጠበቅ ያድናቸዋል። አንድ ሰው ከመዳኑ በፊት የተለየ ነገር ሊሰማው ይገባል የሚለው አመለካከት፥ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን እምነት ቀላልነት እና ከእግዚአብሔር ብቻ ሊመጣ የሚችለውን እውነተኛ ዳግም ልደት እንዳይረዱት አድርጓቸዋል።

የዳግም ልደት ትምህርት ልምምዳዊ አለመሆኑን የሚገልጠው አሳብ፥ የሉተራውያን ቤተ ክርስቲያን አቋም የሆነው የሕፃናት ዳግም ልደት ትምህርት እንዲጀመር በር ከፍቷል። ከዚህ በመነሣት ዳግም ልደት ልምምድ እስካልሆነ ድረስ፥ ሕፃናት ዳግም የማይወለዱበት ምንም ምክንያት የለም የሚል የመከራከሪያ አሳብ ያቀርባሉ። ሼድ የተባለው የሥነ-መለኮት ሰው ዳግም ልደት ልምምድ እስካልሆነ ድረስ፥ ሕፃናት ዳግም መወለድ ይችላሉ የሚለውን ትምህርት እንደሚከተለው ያቀርባል።

> ‘‘ዳግም ልደት ሕሊናዊ ግንዛቤን የማይጠይቅ፥ በሰው ነፍስ ውስጥ የሚሠራ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። በዳግም ልደት ምክንያት የሚፈጠር ውስጣዊ ስሜት የለም። የማንኛውም ሰው ሕሊና በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆነበትን የመንፈስ ቅዱስ ቅጽበታዊ ሥራ ሊገነዘብ አይችልም። ይህ ሥራ የእግዚአብሔር የራሱ ብቻ ስለሆነ፥ ሰው እንዲያውቀው አስፈላጊ አይደለም። ይህ እውነት ሕፃናትን እና አዋቂዎችን በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ስለሚያኖራቸው፥ የሕፃናትን ዳግም ልደት ከአዋቂዎቹ እኩል ያደርገዋል። መጽሐፍ ቅዱስ የሕፃናትን ዳግም ልደት በሚመለከት ያስተምራል። ሉቃስ 1፡15፡- ‘ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል።’ ሉቃስ 18፡15-16፡- ‘ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተውአቸው አትከልክሏቸው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና።’ የሐዋርያት ሥራ 2፡39፡- ‘የተስፋው ቃል... ለልጆቻችሁ ነው’፥ 1ኛ ቆሮ. 7፡14፡- ‘ልጆቻችሁ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው።’ የሕፃናት ዳግም ልደት በአምሳያም ተገልጧል። ሀ. በብሉይ ኪዳን በነበረ የሕፃናት ግርዘትና ለ. በአዲስ ኪዳን ባለ የሕፃናት ጥምቀት።’’

ሼድ በማስረጃነት ካቀረባቸው ጥቅሶች አንዳቸውም የሕፃናትን ዳግም ልደት አያረጋግጡም። የዳግም ልደት ተግባር የሚጠቀስበት አስቸጋሪ ልምምድ መኖሩን ብዙ ክርስቲያኖች ባያውቁትም ስለ ሕፃናት ዳግም ልደት ግልጥ ማረጋገጫ የሚያቀርቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሉም። ዳግም ልደት የሚፈጸምበት ትክክለኛው ጊዜ የሚያድን እምነት በተገለጠበት ቅጽበት ነው። ዳግም ስለተወለዳችሁ እመኑ የሚል ጥያቄ ለሰው ልጆች የቀረበበት ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። ነገር ግን አምነው የዘላለምን ሕይወት እንዲቀበሉ ነው የተጋበዙት። ክርስቲያኖች ክርስቶስን ከመቀበላቸው በፊት ‘‘በኃጢአታቸውና በበደላቸው ሙታን እንደነበሩ’’ በግልጥ ተነግሯቸዋል (ኤፌ. 2፡1)።

ውሳኔ ለማድረግ ከሚችሉበት ዕድሜያቸው በፊት የሚሞቱ ሕፃናት ሁኔታ የተለየ ችግር ነው። ትክክለኛው መሠረታዊ የእምነት

ትምህርት፥ ሕፃናት ዳግም የሚወለዱት በሚሞቱበት ጊዜ ነው እንጂ ከዚያ በፊት አይደለም፥ ውሳኔ ከሚያደርጉበት ዕድሜ ከደረሱ ደግሞ ዳግም የሚወለዱት ክርስቶስን በሚቀበሉበት ቅጽበት ነው የሚል ይመስላል። የሕፃናት ጥምቀት ዳግም ልደትን ለማምጣት የሚያስችል አለመሆኑ ግልጥ ነው። ይህን ጉዳይ የሚመለከተው የካልቪን ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት የሉተራውያንን ትምህርት ይቃረናል። የሕፃናትን ዳግም ልደት *መሠረታዊ* ትምህርት ከተቀበልን፥ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ሁሉ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ እንገባለን። ለዘላለም ድኗል ልንል የማንችለውን ሰው ዳግም የተወለደ ነው ማለቱ በጣም አሰቸጋሪ ነው።

7. የዳግም ልደት ውጤት

ከዳግም ልደት ሥራ ጋር የተያያዙ ነገሮች እጅግ ብዙ ናቸው። በአንድ ወቅት ሙት የነበረች ነፍስ የእግዚአብሔርን ሕልውና የሚያሳየውን የዘላለምን ሕይወት ትቀበላለች። የዳግም ልደት ውጤት፥ የዘላለምን ሕይወት ማግኘት ነው በሚለው እውነት ልናጠቃልለው እንችላለን። ሌሎቹ የዳግም ልደት ውጤቶች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት አስፍቶ በመመልከት የሚገኙ ናቸው። ሕይወት የሚለውን ቃል መተርጎም አስቸጋሪ ቢሆንም፥ ዘላለማዊ ሕይወት ቁሳዊ ባይሆንም፥ ዳግም በተወለደ ሰው ሕይወት ግን የሚታዩ ነገሮች ይኖሩታል።

አዲሰ ተፈጥሮ። የዘላለም ሕይወት ዳግም በተወለደ ሰው ውስጥ ከሚያከናውናቸው ሥራዎች የመጀመሪያው መለኮታዊ ተፈጥሮን ማላበስ ነው። አዲሱ ተፈጥሮ ኃጢአት የማድረግ ችሎታና ፈቃድ ያለውን አሮጌ ተፈጥሮ ሙሉ በሙሉ ሳያጠፋ እንኳን፥ ከዘላለም ሕይወት ቀጥሎ ለሚመጣው የእግዚአብሔር ፈቃድ የመገዛት ከፍተኛ ጉጉት ያለው ይሆናል። አዲሱ ተፈጥሮ ‘‘አዲስ ፍጥረት’’ (2ኛ ቆሮ. 5፡17፤ ገላ. 6፡15)፥ ወይም ‘‘አዲስ ሰው’’ (ኤፌ. 4፡24) በተባለው ሰው ውስጥ መገኘቱ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣል። አዲሱን ተፈጥሮ በተቀበለ ሰው ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የአኗኗር፥ እንዲሁም ስለ እግዚአብሔርና የእርሱም ስለሆኑ ነገሮች ያለው የአመለካከትና የልባዊ ለውጥ ይጠበቃል።

በዳግም ልደት የሚገኘው አዲስ ተፈጥሮ፥ ከውድቀት በፊት ከነበረው ከአዳም ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ጋር አንድ ተደርጎ ሊታይ አይገባም። የአዳም ተፈጥሮ ያልተፈተነና ኃጢአት የሌለበት ነበር። ዳግም ለተወለደ ሰው እንደ ምንጭና ተፈጥሮውን እንደሚወስን ተቆጥሮ የተሰጠው ዓይነት የዘላለም ሕይወት አልነበረውም። የአዳም ሰብአዊ ተፈጥሮ ለኃጢአትና ለፈተና የተጋለጠና ለመውደቅ የሚችልም ነበር። በዳግም ልደት የሚሰጠው

መለኮታዊ ተፈጥሮ ግን በቀጥታ በኃጢአት ጉዳይ የሚገባ መሆኑ አጠራጣሪ ነው። ዳግም የተወለደ ሰው ኃጢአት ሊያደርግ እንደሚችልና እንደሚያደርግም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ቢናገርም፥ ኃጢአትን የሚያደርገው ሰብእና ስሕተት በጥሞና ቢጤን፥ ኃጢአቱ የኃጢአታዊ ተፈጥሮው ውጤት እንደሆነ እናያለን። ይህ ነገር ክርስቲያን ያለ ኃጢአት መሆን ይችላል ወይም ኃጢአትን ማድረግ አይችልም ከሚለው አባባል ጋር ጨርሶ ሊምታታ አይገባም። ፍጹምነት ኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን እስካልተወገደ ድረስ የምንደርስበት ነገር አይደለም። ኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን የሚወገደው ሥጋዊ አካላችን ሲሞት ወይም በመነጠቅ ጊዜ የአሁኑ አካላችን ሲለወጥ ነው።

አዲሱ ተፈጥሮ የኃጢአት መነሻ ሊሆን ባይችልም፥ አሮጌውን ተፈጥሮ ሙሉ በሙሉ የማጥፋት ችሎታ የለውም። ድል የማድረጊያ ኃይል የምናገኘው እግዚአብሔር በውስጣችን በማደሩ ምክንያት ነው። አዲሱ ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እናደርግ ዘንድ አዲስ ፈቃድ የሚሰጠን ሲሆን፥ የኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን ዝንባሌ ባለበት ሁኔታ እንኳን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የርሱ ኃይል ያስችለናል። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆናችንን የምናውቀው በአዲሱ ተፈጥሮ ፈቃድ ውስጥ ስንገባ ነው። አዲሱ ተፈጥሮ አዲሱን ሕይወት ያመጣ ስለሆነ፥ ዘላለማዊ ሕይወትና አዲሱ ተፈጥሮ ሊለያይ በማይችል ሁኔታ አንድ ሆነዋል።

አዲሰ ልምምድ። ዳግም ልደት በራሱ ልምምድ ባይሆንም የበርካታ ልምምዶች ምንጭ ነው። ዘላለማዊ ሕይወትን የመስጠት ተግባር ቅጽበታዊ በመሆኑ ልምምድ ሊሆን ባይችልም፥ ከዳግም ልደት በኋላ የሚኖረው ዘላለማዊ ሕይወት የአዲሱ መንፈሳዊ ልምምድ ምንጭ መሆኑ የሚጠበቅ ነው። አዲስ ሕይወት አዲስ ችሎታን ይዞ ይመጣል። ከዳግም ልደት በፊት በመንፈሱ ሙት የነበረና ለመንፈሳዊ እውነት ዕውር የነበረ ሰው፥ በዳግም ልደት ለአዲስ ዓለምና እውነት ሕያው ይሆናል። አንድ ዕውር ሰው ዓይኑ በሚበራለት ጊዜ የቀለምን ውበትና እይታ ለመገመት እንደሚሞክር፥ አዲስ የተወለደ ሰው ነፍስም መንፈሳዊ እውነትን ለመረዳት ሙከራ ታደርጋለች። የመንፈስ ቅዱስን የማስተማር አገልግሎትም ለመጀመሪያ ጊዜ ለመረዳት ይችላል። ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረትን ማድረግንና በፍጹም ነጻነት የመጸለይ ደስታን ይለማመዳል። ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር በዋለ መጠን፥ ለፍጥረታዊ ሰው ፍጹም እንግዳ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ መለማመድ ይጀምራል። ሁለንተናው ደስታ፥ ኅዘን፥ ፍቅር፥ ሰላም፥ ምሕረትና በመንፈሳዊ ዓለም

ውስጥ ያሉትን እውነቶች ሁሉ ለመለማመድ አዲስ ችሎታ ያገኛል። ዳግም ልደት ልምምድ ባይሆንም፥ የክርስቲያናዊ ልምምዶች ሁሉ መሠረት ነው። ዳግም ልደት ከደኅንነት ተለይቶ የማይታይና ራሱን በሰጠ ክርስቲያን ጤናማ ልምምድ ውስጥ የሚገለጥ ነው። ሰውን ወደ ክርስቲያናዊ ልምምድ የማይመራ ዳግም ልደት አጠያያቂ ይሆናል።

የዘላለም ዎስትና። ዳግም ልደትን በሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ የሚነሣው አንዱና ዋናው ውዥንብር፥ አንዲት ነፍስ በትክክል ዳግም ከተወለደች ደኅንነትዋ ለዘላለም የተጠበቀ ነው የሚለውን ትምህርት ላለመቀበል ከሚደረግ ጥረት የተነሣ የሚፈጠረው ሁኔታ ነው። የዘላለም ሕይወት የተሰጠው ሰው ሊወሰድበት አይችልም። ይህ ዳግም የተወለደውን ሰው ወደ ክብር ለማምጣት እግዚአብሔር ያለውን የማይሻር ዓላማ ያሳያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ዳግም የተወለደ ሰው ከቶ አናይም። ክርስቲያኖች በኃጢአት ምክንያት ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ ልምምድ ሲያጡ፥ በኑዛዜና በመመለስ መታደስ ቢያስፈልጋቸውም የዳግም ልደት መሠረታዊ እውነት ግን ሊለወጥ አይችልም። በመጨረሻ ልናስበው የሚገባ ነገር፥ ይህ በምድር የምናየው መንፈሳዊ ልምምድ፥ ዳግም የተወለደ ሰው ከኃጢአትና ከፈተናው ነጻ ከሆነ በኋላ ለሚጠብቀው ከፍተኛ ልምምድ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ነው። ዳግም ልደት በሙላት የሚገለጠው ዳግም የተወለደው ሰው ሙሉ ለሙሉ በሚቀደስበትና በሚከብርበት ጊዜ ነው። በዚህ ምድር የምንለማመደው ነገር በኃጢአታዊ ተፈጥሮአችንና አካላችን ምክንያት እጅግ ውሱን ሆኖ የከበረውን የዘላለም ሕይወት በጥቂቱ ብቻ ያሳያል። በሕይወት የምንለማመደው ነገር ግን ዳግም ልደትን፥ ቋሚ ተስፋንና የውስጥ እርግጠኛነትን የሚያመለክት መሆን አለበት። ‘‘በእናንተ መልካሙን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቻለሁ’’ (ፊልጵ. 1፡6)።

15

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

1. ለረጅም ጊዜ የታወቁ የአመለካከት ልዩነቶች

ከአማኙ ደኅንነት ጋር ከተያያዙ በርካታ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መካከል በጣም የሚያስቸግረው፥ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት የሚመለከት ትምህርት ማቅረብ ነው። በባሕርዩ ከሥርየት አስገኝ ጸጋ በጣም ቀለል ያለ ቢሆንም፥ እጅግ በርካታ የሆኑ ትርጉሞች ስለተሰጡት ሰዎች ዋና ትርጉሙን በማይገባ መንገድ ተረድተውታል። በአጠቃላይ ሲታይ ይህን መሠረታዊ ትምህርት በሚመለከት የተለያዩ አመለካከቶችን ያንፀባረቁ ጸሐፊዎች ሁሉ፥ በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ላይ ይስማማሉ። ያም ሆኖ ማንኛውም ጸሐፊ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያለው የአመለካከት አዝማሚያ አጠቃላይ አቋሙን ለመገምገም እንደ መሠረት ሊቆጠር ይችላል። መሪል ኤፍ. ኧንገር [Merrill F. Unger] ‘‘የመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ሥራ’’ በሚል ርእስ በቅርቡ በጻፈው መጽሐፍ፥ ለብዙ ጊዜ የታወቀውን የተሳሳተ አመለካከት ለማስተካከል ሞክሯል።

ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በመመርመር ረገድ ውዥንብር የሚፈጠረው በብዙ ምክንያቶች ነው። ለልዩነቶች መፈጠር ዋናው ምክንያት ግን፥ የቤተ ክርስቲያንን ልዩ ባሕርይ ለይቶ ለማወቅ አለመቻል ነው። አብዛኛዎቹ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት፥ ቤተ ክርስቲያን የዘመናት ሁሉ የቅዱሳን ስብስብ ናት የሚሉ ሲሆን፥ አንዳንዶች ከዚህም ሰፋ አድርገው ደኅንነትን ሳያገኙ እንኳ በውጫዊ መልክ የቤተ ክርስቲያን አካላት የሆኑትን ይጨምራል የሚል አሳብ አላቸው። ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት ይህን አሳብ ከተቀበልን፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከዚህ አሳብ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ይሆናል። የመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ አገልግሎት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለማይገኝና፥ ስለ ሺሁ ዓመት መንግሥት በተነገረው ትንቢት ውስጥም ስለሌለ፥ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በተለይ ከጰንጠቆስጤ ዕለት ጀምሮ ጸድቃን ከሙታን ተነሥተው ሕያው የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እስከምትነጠቅበት ዕለት ድረስ ባለው የቤተ ክርስቲያን ዘመን የሚፈጸም ነው። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን ያሉ ቅዱሳንን ብቻ የምታካትት ናት ካልን፥ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ አማኞችን ሁሉ ወደ ክርስቶስ አካል የማጥመቁ ሥራ የተለየ ትርጉም ያለው ይሆናል። ይህ ምልከት በዚህ ዘመን ያሉ ቅዱሳን የሚታወቁበት ልዩ መለያና፥ ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር

የሚኖራቸውን የጠበቀ ጎብረት ምሥጢር የሚገልጥ ይሆናል። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ትምህርት መረዳት፥ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ልዩ መለያ እንደሆነ ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት።

ለውዥንብሩ መፈጠር ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች በርካታ ናቸው። ጥምቀት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ከዳግም ልደትና ከመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ማደር ጋር ተያይዟል። እነዚህ አገልግሎቶች ከማጥመቅ አገልግሎት ጋር በተመሳሳይ ቅጽበት የሚፈጸሙ ቢሆኑም፥ በተፈጥሮአቸው ግን የተለዩ ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ብዙ ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር በአንድነት ቀርቧል። በተለይ እንደ ዶልመን [Dolman] ያሉ የቀድሞ ጸሐፊዎች ጥምቀትንና ሙላትን አንድ አድርገው አቅርበዋቸዋል። የዶልመን ትምህርት በጣም ጠቃሚ ቢሆንም የቃሉ አጠቃቀም ግን በጣም ተምታቷል። የአንዳንዶቹ ጸሐፊዎች ትምህርት ደግሞ በጭራሽ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ አይደለም።

ከትክክለኛው እውነት እጅግ የራቀ ሆኖ የምናገኘው ነገር፥ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ከአንዳንድ ጊዜያዊ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና ልዩ ልምምዶች ጋር በሚያያይዙ የቅድስና እና ጰንጠቆስጣዊ* [Pentecostal] እንቅስቃሴዎች በመባል በሚታወቁ ትምህርቶች ውስጥ ነው። በጥንት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታይ የነበረ የልዩ መገለጥ ተግባር እና በልሳን የመናገር ጉዳዮች ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር መምታታት የለባቸውም። እነዚህ የተለዩ አገልግሎቶች ለዳኑ ሰዎች ብቻ የተገለጡ ቢሆኑም፥ ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተለመዱ ምልክቶች ሆነው መታየት የለባቸውም። በተለይ ልንቃወመው የሚገባ ትምህርት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ደኅንነትን ተከትሎ የሚመጣ የተለየ የመቀደስ ተግባር ነው የሚለውን አሳብ ይሆናል።

1. የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት የሚመለከቱ የአመለካከት ግጭቶች በርካታና የተምታቱም ስለሆኑ፥ ይህን ርእስ የሚያጠና ማንኛውም ሰው ለቅዱሳት መጻሕፍት እጅግ ቅርብ መሆን አለበት። በተለይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫ ሊሰጥ የማይችልባቸውን ግምታዊ አስተሳሰቦች ማራቅ ይገባዋል። ለዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ቅዱሳት መጻሕፍት በቂ መረጃዎችን የሚሰጡ ስለሆነ፥ ጠንቃቃ አጥኚ ይህን እውነት በትክክል ወደሚረዳበት ደረጃ ለመድረስ መጣር አለበት። በአጠቃላይ ስለ መንፈሳዊ ጥምቀት የሚናገሩ አሥራ አንድ ጥቅሶች አዲስ ኪዳን ውስጥ አሉ (ማቴ. 3፡11፤ ማር. 1፡8፤ ሉቃስ 3፡16፤ ዮሐ. 1፡33፤ ሐዋ. 1፡5፤ 11፡16፤ ሮሜ 6፡1-4፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡13፤ ገላ. 3፡27፤ ኤፌ. 4፡5፤ ቈላ. 2፡12)።

---

* በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የአሳታሚውን መግለጫ ይመልከቱ።

ከጳንጠቆስጤ ዕለት በፊት የተነገሩት ማመሳከሪያ ጥቅሶች በሙሉ ትንቢታዊ ናቸው። ከዚያ በኋላ የተነገሩት ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነባሪ እውነት መሆኑን ይናገራሉ። ሌሎች ምንባቦችን ለመተርጐም እንደ መሠረት ሊወሰድ የሚገባው ዓቢይ ክፍል 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 ነው።

2. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚፈጸም ነው

ደኅንነትና ጥምቀት የሚነጣጠሉ አይደሉም። ብዙ ጊዜ የሚነገር አንድ የተሳሳተ አስተሳሰብ፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለጥቂት ክርስቲያኖች ብቻ የተሰጠ ልዩ አገልግሎት ነው የሚለው ነው። በተቃራኒው ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን በዳነ ወቅት ወዲያው በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠመቅ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ስለዚህ፥ ደኅንነትና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አብረው የሚሄዱ ናቸው። እንደውም ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ መዳን የማይቻል ነው። ይህ አሳብ መሠረታዊው የእምነት ትምህርት በሚገኝበት ጥቅስ በሚገባ ተገልጧል። ‘‘አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎች ብንሆንም ባሪያዎችም ብንሆን፥ ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል’’ (1ኛ ቆሮ. 12፡13)።

ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል። ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እንደተጠመቁና ከክርስቶስ አካልም ጋር የተዋሐዱት በዚህ ምክንያት እንደሆነ ከዚህ ክፍል እናረጋግጣለን። ይህ ክፍል የሚገኘው በበርካታ ኃጢአት፥ በክፍፍልና ከእምነት ፈቀቅ በማለት ምክንያት የጥፋተኝነት ስሜት ለሚሰማት ቤተ ክርስቲያን በተጻፈ መልእክት ውስጥ መሆኑን ማስተዋል ይጠቅማል። ይሁን እንጂ በዚህ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ሰዎች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው እንደነበር ጳውሎስ ያሳስባቸው ነበር። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከሕሊና ወቀሳ ነጻ ለሆኑ ብቻ የተሰጠ ወይም ከጥረት የተነሣ የሚደረስበት ከፍተኛና ልዩ ግብ አይደለም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ሁሉ የሚሠራው ሁለንተናዊ አገልግሎት እንደሆነ ነው ቃሉ የሚያስረግጠው።

ለንዲት ጥምቀት። ይህ አሳብ በኤፌሶን 4፡5 ተደግፏል፦ ‘‘አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት።’’ ይህ ክፍል በርከት ባሉ ልዩ ልዩ መንገዶች የሚተረጎም ቢሆንም፥ ለአማኞች ሁሉ የጋራ የሆነ ነገር መሆኑ ግልጥ ነው። ሁሉም አንድ ጌታ፥ አንድ ሃይማኖት ወይም አስፈላጊ የሆነ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትና አንዲት ጥምቀት አላቸው። አሳቡ የሚናገረው ስለ ውኃ ጥምቀት እንዳልሆነ ግልጥ ነው። የውኃ ጥምቀት

በተለያዩ ክርስቲያኖች የተለያየ አተረጓጎም ተሰጥቶት የሚፈጸምና በጥቂቶች ዘንድ ደግሞ በጭራሽ የማይፈጸም ሥርዓት ነው። በዚህ ስፍራ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አምሳያ ሳይሆን እውነታ ነው የምናየው። ከፍሉ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚፈጸም እንደሆነ ለማረጋገጥ ያገለግላል። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚናገሩ ሌሎች ክፍሎች በሙሉ ከዚህ አመለካከት ጋር የሚስማሙ ናቸው።

በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅን እንሻ ዘንድ የተሰጠ ማበረታቻ አይገኝም። ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ይፈልጉ ዘንድ የተነገረ አንዳችም ነገር የለም። ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ እናዘጋጅ ዘንድ የተነገሩ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም፥ ይህ ዝግጅት ጥምቀት ተብሎ አልተጠራም። በየትኛዎቹም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከደኅንነት ቀጥሎ የተፈጸመ ነገር ተደርጎ አልቀረበም። ይልቁንም ከደኅንነት ሊነጠል የማይቻል ነገር እንደሆነ ታይቷል። በዚህም ዘመን ያለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መዳን አይቻልም። ከዚህ አንጻር ሲታይ፥ በሁሉም አቅጣጫ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚፈጸም መሆኑን በመናገር ማጠቃለል እንችላለን።

3. ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ ለመሆን መጠመቅ

የአካል አንድነት። ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ዋና ዋና ውጤቶች አንዱ የአማኞች በክርስቶስ አካል ውስጥ አንድ መሆን ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 መሠረት የአማኞች ጥምቀት፥ ‹‹አንድ አካል›› ለመሆን ነው። ቤተ ክርስቲያንን በሰው አካል ሥዕላዊ መግለጫነት በማቅረብ እያንዳንዱ ክርስቲያን ወደዚህች ሕያው ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት እንደሚቀላቀል በግልጥ ቀርቧል። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሕያው የሆነውን የቤተ ክርስቲያን አንድነት የመመሥረትና ሰዎችን ወደዚህ አንድነት ለመጨመር የሚከናወን አገልግሎት ነው።

የክርስቶስ አካል፥ እጅግ ጠቃሚ የእምነት ትምህርት። የቤተ ክርስቲያንን የክርስቶስ አካልነት የሚገልጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እጅግ ብዙ ናቸው። ከእነዚህም አብዛኛዎቹ የዚህን አካል አመሠራረት እና ዕድገት ያሳያሉ (ሐዋ. 2፡47፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡15፤ 12፡12-14፤ ኤፌ. 2፡16፤ 4፡4-5፥ 16፤ 5፡30-32፤ ቈላ. 1፡24፤ 2፡19)። ክርስቶስ የዚህ አካሉ እራስ እንደሆነ ተገልጧል (1ኛ ቆሮ. 11፡3፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 5፡23-24፤ ቈላ. 1፡18)። ክርስቶስ አካሉን እንደሚመግብ የሚናገሩም ቢያንስ ሦስት ጥቅሶች ይገኛሉ (ኤፌ. 5፡29፤ ፊልጵ. 4፡13፤ ቈላ. 2፡19)። የክርስቶስ አካል ማለት የቤተ ክርስቲያን መቀደስ ጉዳይ በኤፌሶን

5፡25-27 የተገለጠ ሲሆን፥ በሌሎች ክፍሎችም በተዘዋዋሪ ተመልክቷል። ክርስቶስ ለአካሉ ስላበረከታቸው ስጦታዎች የሚናገሩ በርካታ ጥቅሶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ (ሮሜ 12፡3-8፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡27-28፤ ኤፌ. 4፡7-16)። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል መሆኗን የሚናገረው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የአዲስ ኪዳን ዓቢይ ክፍል ነው።

በአካሉ ውስጥ ያለ ሰፍራ። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሥራ የአካሉን የተለያዩ ብልቶች አንድነት ያረጋግጣል። የዘር እና የባሕልን ልዩነት ሳይመለከት እውነተኛ አማኞች በሙሉ በክርስቶስ ሕያው አካል ውስጥ አንድ ሆነዋል። ይህ በአያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተረጋገጠ ሲሆን፥ መሠረቱም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። አንድነቱ ግለሰቦች በብዙሃን የሚዋጡበት ዓይነት ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ተግባር እያንዳንዱ አማኝ በክርስቶስ አካል ውስጥ የራሱ የሆነ ልዩ ስፍራ የሚይዝበት ነው። እያንዳንዱ አማኝ ለአጠቃላዩ አካል ሙላት እና ፍጹምነት አስፈላጊ ነው። አካሉ "እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ" በጅማት እንደተጋጠመ ነው (ኤፌ. 4፡16)። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ዋና መሠረታዊ ትምህርት በሚገባ መረዳት የቤተ ክርስቲያንን ጅማሬ ለመረዳት ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን አሠራርና ሉዓላዊ ዝግጅትም ለመገንዘብ አስፈላጊ ነው።

4. ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን መጠመቅ

ሉዲስ ሰፍራ። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማኙን ወደ ክርስቶስ አካል መጨመር ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቶስ ውስጥ የሚያኖረውም ነው። ይህን እውነት ክርስቶስ አስቀድሞ ይጠባበቅ እንደነበር ከተናገረው ቃል እንመለከታለን። "እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ" (ዮሐ. 14፡20)። "እናንተም በእኔ እንዳላችሁ" የሚለው ግንኙነት የሚፈጸመው በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። ክርስቲያኖች የሚይዙት የዚህ ስፍራ ዋናነት ብዙ መጋነንን የማይሻ፥ ራሱን በራሱ የሚገልጥና እጅግ ጠቃሚ ጉዳይ ነው። ማንኛውም ግለሰብ ከመዳኑ በፊት በአዳም ውስጥ ሆኖ የአዳምን ተፈጥሮ፥ ኃጢአት፥ እንዲሁም የመጨረሻ ዕጣ ይካፈል ነበር። በደኅንነት ደግሞ በአዳም ከነበረበት ስፍራ ተወስዶ ክርስቶስ ውስጥ እንዲሆን ተደርጓል። የደኅንነቱ ዝርዝር ሁኔታዎች ሁሉ ከዚህ አዲስ ከተሰጠ ስፍራ የሚመነጩ ናቸው። መጽደቁ፥ መቀደሱ፥ ነጻ መውጣቱ፥ ወደ እግዚአብሔር ለመግባት ያገኘው ዕድል፥ ርስቱ፥ እንዲሁም መከበሩ እውንና የሚቻል የሆነው አማኙ በክርስቶስ ባገኘው ስፍራ ምክንያት ነው። የዚህን መሠረታዊ

የእምነት ትምህርት አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በሚገባ ያለመረዳት፥ ሐሰተኛ ትምህርቶች እንዲነሡና አያሌ ክርስቲያኖችም ደኅንነታቸው ባስገኘላቸው የደስታ ልምምድ ውስጥ እንዳይኖሩ አድርጓቸዋል።

ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን (ሮሜ 6፡1-5)። "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን* ሁላችን" የሚለው አባባል በመሠረቱ የሚያሳየው ከክርስቶስ ጋር መዋሃድን ነው። አማኙ በጽድቁ፥ በሞቱ፥ በትንሣኤውና በክብሩ ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናል። እነዚህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች በአእምሮአችን ይዘን ከላይ የተጠቀሱትን የሮሜ ጥቅሶች ስናጠና፥ ከክርስቶስ የሞትና የትንሣኤ ታላቅ ተግባር ጋር አማኙ አንድ መሆኑ ግልጥ ይሆናል። "ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ፥ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን" (ሮሜ 6፡3-5)። ከክርስቶስ ጋር አንድ የመሆን የከበረ እውነት፥ ለአማኙ የውኃ ጥምቀት ከመሰጠቱ በፊት የሚያድን እምነት ባሳየበት ቅጽበት የተፈጸመ እውነትና የሚታይ ሐቅ ነው። አማኙ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት ከክርስቶስ ጋር በተገናኘ ጊዜ፥ ከክርስቶስ የመስቀል ሞትና የድል ትንሣኤ ጋር አንድ ይሆናል። የውኃ ጥምቀት አምሳያነት የደኅንነት ሳይሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። የመንፈስ ጥምቀትም ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንን ያከናውናል። የሚያሳዝነው፥ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ከቅዱሳት ምሥጢራት በአንዱ ላይ (በውኃ ጥምቀት ላይ) ስታተኩር በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ላይ የሚገባውን ትኩረት ሳትሰጥ ማለፏ ነው። የውኃ ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አምሳያ ብቻ መሆኑን ልትረዳ ይገባ ነበር። እነዚህ ቅዱሳት ምሥጢራት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስቶስን አካል አንድነትና ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንን በጥሩ ሁኔታ መግለጥ ሲገባቸው፥ ከሰው አሠራር የተነሣ ከፋፋይ ሆኑ። አንድ አማኝ በክርስቶስ ውስጥ የመሆኑ እውነት፥ ይህ ስፍራው ከሚያስገኝለት በረከት ሁሉ ጋር ሲታይ፥ ምንኛ ጠቃሚና የከበረ ነገር ነው?

ከሮሜ 6፡3-4 ጋር ተጓዳኝ አሳብ ያለው ሌላ ክፍል ቈላስይስ 2፡12 ነው፡- "... በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናቸሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ።" በቈላስይስ መልእክት የምናገኘው መገለጥ፥ በሮሜ

---

* የግሪክኛው ጥቅስ ቃል በቃል ሲተረጎም "ክርስቶስ *ውስጥ* ተጠመቅን" የሚል አሳብ እንደያዘ እንረዳለን።

ያለውን የተሟላ የሚያደርግና ከክርስቶስ ጋር የተቀበርን መሆናችንን የሚያመለክት ነው። የመቀበር ጉዳይ በመሠረታዊው ወንጌል ውስጥም የታከለ ነገር ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡4)። ፍጻሜን የሚያመለክት መሆኑ ነው ጠቃሚነቱ። የክርስቶስ መቀበር የሞቱን እርግጠኛነትና የመሥዋዕትነቱን ፍጻሜ በግልጥ ያሳያል። አማኝ ከክርስቶስ ጋር በመቀበር ለኃጢአት ሞተ፥ በትንሣኤ ደግሞ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆነ።

አዲስ የሕይወት አንድነት። ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን መጠመቅ ለሱ መለየት ብቻ ሳይሆን፥ ከርሱ ጋር አንድ መሆንም ነው። አማኝ በዳግም ልደት የዘላለም ሕይወት ተካፋይ ይሆናል። በመለኮታዊ ፈቃድ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ በዕለት ተዕለት ሕይወቱም ተባብሯል። ይህ አዲስ የሕይወት አንድነት አካሉና ራሱ (አማኙና ክርስቶስ) የሚካፈሉት ሕያው አንድነት ነው። ከዚህ መሠረተ አሳብ አስደናቂ እውነቶች ይመነጫሉ። እነርሱም፥ ኅብረት፥ ፍሬ ማፍራት፥ ለድል ብርታትን ማግኘት ሲሆኑ፥ እነዚህ ከአካሉ ራስ ጋር የአንድነት መሠረት ናቸው። በክርስቶስ መጠመቅን የሚያመለክቱ ሁለት ፅንሰ-አሳቦች (ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንና የአዲስ ሕይወት አንድነት) የማይነጣጠሉና በውህደት ወደ አንድነት የሚያመሩ ናቸው። ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር የተባለ የሥነ-መለኮት ምሁር እንደጻፈው፡-

> ‘‘ስለ ሉል ጠለቅ ያለ ትርጉም ብንሰጥ፥ የአንድን ነገር ዙሪያ በሁሉም አቅጣጫ የሚከብና እንዲያውም ያን ነገር ዘልቆ የሚገባ ነገርን ማመልከታችን ነው። በአንድ ነገር ክብ (ክልል) ውስጥ መሆን፥ በዚያ ነገርና ከእሱም የሚገኘውን ነገር ሁሉ መካፈል ማለት ነው። በዚህ መሠረት ስናየው፥ ወፍ በአየር ላይ ነች፥ አየርም በእርሷ ውስጥ አለ፤ ዓሣ በውኃ ውስጥ ይኖራል፥ ውኃም በዓሣ ውስጥ አለ፤ ብረት በእሳት ውስጥ ይደረጋል፥ እሳትም በብረት ውስጥ ይገኛል። በመንፈሳዊ ረገድም ክርስቶስ በአማኙ ዙሪያው ነው። እርሱ አማኙን ያካብበዋል፥ ይከብበዋል፥ በውስጡ ያደርገዋል፥ ያድርበታልም። አማኙ በክርስቶስ ውስጥ፥ ክርስቶስም በአማኙ ውስጥ ነው። የወይን ቅርንጫፍ፥ የወይን ግንድ፥ አንድ ብልትም የአካል ክፍል የመሆኑን ያህል፥ አማኙም በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት የክርስቶስ ሕያው አካል ይሆናል። እግዚአብሔር አብ አማኝን ከክርስቶስ ጋር ባለው አንድነት ምክንያት በርሱ ውስጥ ብቻ ያየዋል። ወይም የልጁ ሕያው ክፍል አድርጐ ይመለከተዋል። ስለዚህ ልጁን የሚወደውን ያህል ይወደዋል’’ (ኤፌ. 1፡6፤ ዮሐ. 17፡23)።

5. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በዚህ ስፍረ-ዘመን ብቻ ነው

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለሰፍረ-ዘመን ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው። አብዛኛዎቹ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት አስፈላጊነት አልተገነዘቡም። ይህ የሆነው በብዙ ምክንያት ነው። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለው ልዩ ዓላማ ተገቢው ስፍራ አልተሰጠውም። ተነጻጻሪ የሆኑት ሕግ፥ ጸጋና የእግዚአብሔር መንግሥት ብዙውን ጊዜ ይምታታሉ። መንፈስ ቅዱስ በማጥመቅ ውስጥ ያለውን ሥራ በሚገባ መረዳት እነዚህን ስሕተቶች ለማረም በጣም ይረዳል። ይህ በዚህ ስፍረ-ዘመን ብቻ የሚገኝ አንደኛው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ወይም ወደፊት የሚኖሩ ናቸው። ስለዚህ የማጥመቅ ሥራ በጣም አስፈላጊ ነው። የአሁኑ ስፍረ-ዘመን የተጀመረው የማጥመቅ ሥራ በተጀመረበት በጰንጠቆስጤ ዕለት ነበር። ወደፊትም ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የመጨረሻ ሰዎችን ትቀበላለች። ከዚያ በኋላ ክርስቶስ ወደ ራሱ ሊቀበላት ይመጣል። ይህ እውነት በሐዋርያት ሥራ ምስክርነት ግልጥ ሆኗል።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚናገሩና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ሁለት ብቻ ሲሆኑ፥ የሚደጋገፉ ናቸው (ሐዋ. 1፡5፤ 11፡16)። በሐዋርያት ሥራ 1፡5 ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በተናገረው የመሰናበቻ ቃል፥ "ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ" አለ። በዚህ ቃል ሁለት አስፈላጊ እውነቶች ተጠቅሰዋል። 1. እስከዚያ ጊዜ ድረስ መንፈስ ቅዱስ አላጠመቃቸውም ነበር። 2. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በቅርቡ ሊቀበሉ ነው። "ከጥቂት ቀናት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እስኪጠመቁ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ" ተነገራቸው (ሐዋ. 1፡4)። በዚህ ትንቢት የተመለከተው ጉዳይ በጰንጠቆስጤ ዕለት የተፈጸመ መሆኑ የሚያሳስት አይደለም። ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር ባይያያዝ እንኳ የመመስከር ኃይል የተሰጠው በጰንጠቆስጤ ዕለት ነው። ደቀ መዛሙርቱም ከእንግዲህ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለመጠበቅ በኢየሩሳሌም መቆየት እንደማያስፈልጋቸው ተረድተው በሐዋርያት ሥራ 1፡8 በተጠቀሰው እቅድ መሠረት የክርስቶስን ሥራ ወዲያውኑ ጀመሩ። በሐዋርያት ሥራ 2፡4 መሠረትም በዚሁ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። ይህ ሥራ በዘመኑ ለነበሩና ለዳኑ ሰዎች ብቻ የተሰጠ በመሆኑ የዳኑ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ (1ኛ ቆሮ. 12፡13)። አማኞች የተጠመቁት አስፈላጊ የሆኑ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በነርሱ በጀመሩበት ቅጽበት መሆኑን እንረዳለን።

በሐዋርያት ሥራ 11፡16 የሚገኘው ሁለተኛ ክፍል በሐዋርያት ሥራ 1፡5 ያለውን ምስክርነት የሚያረጋግጥ ነው። ጴጥሮስ ስለ ቆርኔሌዎስ መዳን በሚጠቅስበት ጊዜ፥ ‘‘ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ደግሞ በመጀመሪያ እንደወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው። ዮሐንስ በውኃ አጠመቀ፥ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለውም የጌታ ቃል ትዝ አለኝ’’ አለ (ሐዋ. 11፡15-17)። ጴጥሮስ በዚህ ንግግሩ በሐዋርያት ሥራ 1፡5 የተጻፈው ቃል ‘‘በመጀመሪያ’’ እንደተፈጸመና ይህም የጰንጠቆስጤ ዕለት ልምምድ እንደሆነ በማያጠራጥር አኳኋን ገልጦታል። ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቃቸው ማረጋገጫ፥ በልሳን መናገራቸው እንደነበር ተገልጧል (ሐዋ. 10፡46)። ብዙ ሰዎች ከዚህ በመነሣት በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በልሳን በመናገር መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለ አድርገው ከተሳሳተ ግንዛቤ እና ውሳኔ ደርሰዋል።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በልሳን ከመነጋገር ጋር ያለው ግንኙነት። በጰንጠቆስጤ ዕለት ብዙ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በአንድ ላይ ተጀምረዋል። በቆርኔሌዎስ ቤተሰብ ውስጥ አዲስ የተለወጡ ሰዎች፥ በጰንጠቆስጤ ዕለት የተለወጡት ሰዎች፥ ሐዋርያትን ጨምሮ ዳግም እንደተወለዱ፥ መንፈስ ቅዱስ እንዳደረባቸው፥ በመንፈስ ቅዱስ እንደታተሙና እንደተሞሉ እንረዳለን። በቆርኔሌዎስ ቤትና በጰንጠቆስጤ ዕለት እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተከናወኑት በመንፈስ ቅዱስ ከመጠመቅ ጋር በአንድ ቅፅበት ነው። ማንኛውም የደኅንነት ሥራ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ መፈጸሙ ከተገለጠ፥ በሁለንተናዊ መልኩ ሌሎችም የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በሥራ ላይ ውለዋል ማለት ነው። በዚህ መሠረት ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖረውም፥ ማንኛውም የደኅንነት ውጫዊ ምልክት፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማረጋገጫ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል። የዚህ ነገር መኖር፥ ማለትም ክርስቲያኖች ብቻ በልሳን መናገራቸው፥ በቆርኔሌዎስ ቤተሰቦች ላይ መታየቱ፥ ለቆርኔሌዎስ ቤተሰብ መዳንና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃቸው ለጴጥሮስ በቂ ማስረጃ ሆኖት ነበር። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በልሳን መናገር መኖሩ፥ ለወንጌል እውነት ጠንካራ መተማመኛ በሚያስፈልግበት ጊዜ የተከናወነ በመሆኑ እጅግ ጠቃሚ ነበር። ስለዚህ ይህ ነገር በጰንጠቆስጤ ዕለት፥ ወንጌል እንደገና ለዓለም ሁሉ በቀረበበትና ደኅንነት በታየበት የቆርኔሌዎስ ቤተሰብ ውስጥ በግልጥ ቀርቧል። በልሳን መናገር ለሐዋርያት ዘመን ከተሰጡትና ጊዜያዊ ከነበሩት መንፈሳዊ ስጦታዎች አንዱ ሆኗል። በልሳን መናገር መንፈስ ቅዱስ ለዳነ ሰው ከሚሰጠው ከማንኛውም አገልግሎት ይልቅ፥ አማኙን ከመሙላት አገልግሎት ጋር የሚገናኝ ነው። በልሳን መናገር ከዳግም ልደትና ከቅድስና

ጋር ግንኙነት እንደሌለው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ከመጠመቅ ጋርም ምንም ግንኙነት የለውም። ሁሉም ለዳነ ሰው በሚሆን አገልግሎት ክልል የሚታዩ ነበሩ።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በደኅንነት እምነት ጊዜ የሚፈጸም ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከሚናገሩና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከምናገኛቸው ሁለት ክፍሎች እንደምንረዳው፥ ይህ ነገር ከጸንጠቆስጤ ዕለት በፊት እንዳልተከናወነና አማኞች ሁሉ በክርስቶስ ባመኑበት ወቅት ከሌሎች የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ጋር የሚሰጣቸው መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን። አንዳንድ ጸሐፊዎች እንደሚያመለክቱት፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለአንዱና ለመጨረሻ በጰንጠቆስጤ ዕለት የሆነ አይደለም። ለምሳሌ ጂምስ ግሬይ [James Gray] "ስለ መንፈስ ቅዱስ የተደረገ ቀላል ንግግር" በሚል ርእስ ዶልመን በጻፈው ጽሑፍ መግቢያ ላይ፥ ሲናገር፦ "በእኔ አመለካከት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በጰንጠቆስጤ ዕለት በደቀ መዛሙርት ላይ የመጣው (ሐዋ. 2) ለአንዱና ለመጨረሻ ነው። አማኞች ወደ ክርስቶስ በእምነት በሚመጡበት ቅጽበት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን አይለማመዱም፤ ነገር ግን የጰንጠቆስጤ ዕለት ክንውን ተካፋዮች ይሆናሉ።"

የክርስቶስ ሥራ ለአንዱና ለመጨረሻ በመስቀል ላይ ተፈጽሟል። ይህ መሥዋዕትነት ለአንዱና ለመጨረሻ የተከናወነ ቢሆንም፥ በእያንዳንዱ ሰው ተግባራዊ የሚሆነው ደኅንነትን በሚቀበልበት ጊዜ ይሆናል። በጥምቀት ጊዜ የሚሆነው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ግን የተለየ ነው። ይህ የአንዲት ነፍስ በአንድ ወቅት ከክርስቶስ አካል ጋር የመገናኘቷ ክንውን ነው። ሰዎች ከመዳናቸው በፊት እንኳ ክርስቶስ ለሁሉም ሞቷል ለማለት ብንችልም፥ እያንዳንዱ ሰው የመዳን ፍላጎትና እምነት ከማሳየቱ በፊት፥ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቀ ለማለት አንችልም።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሳይደጋገምም። በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚፈጸመው ለአንዱና ለመጨረሻ ነው። ተከታታይ ሂደትም የለውም። ስለዚህ ሊደጋገምም ሆነ ሊሻሻል ጨርሶ አይችልም። በሚፈጸምበት ጊዜ ያለው ስፍራና አንድነት ጥምቀቱ ከተፈጸመበት ወቅት ጀምሮ ፍጹም ነው። በአሁኑ ዘመን ፈቱን በእምነት ወደ ክርስቶስ የመለሰ ሰው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቋል። ስለዚህ ጉዳይ የሚናገር አንድም የብሉይ ኪዳን ጥቅስ የለም። በወንጌላት ውስጥ የተጠቀሱ ነገሮችም በሙሉ ትንቢታዊ ናቸው። ደግሞም ስለ ወደፊቱ መንግሥት በተነገሩ ትንቢቶች ውስጥ ሁሉ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተነገረ አንዳችም ነገር የለም። ስለዚህ ይህ ነገር በዚህ ስፍረ-ዘመን

ብቻ የሆነ፥ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ የተለየ፥ እሷ የተመሠረተችበትና ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም የተዋሐደችበት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን እናያለን።

6. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሕዋሳዊ ልምምድ አይደለም

ከመንፈሰ ቅዱስ ሙላት ጋር የተያያዘ መንፈሳዊ ልምምድ። የመንፈስ ቅዱስን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች በሚመለከት የሚደረግ ጥንቃቄ የተሞላበት ጥናት የሚያስረዳን፥ የሚኖረው ልምምድ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት መሆኑን ብቻ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ማለት፥ ዳግም ልደት፥ በሰው ውስጥ ማደር፥ ማተም፥ እና ማጥመቅ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ተከትለውት ለሚመጡ ልምምዶች መሠረት ሲሆኑ፤ ሁሉም በራሳቸው የሚከናወኑ እንጂ የሚሰሙን ነገሮች አይደሉም። የዳግም ልደትን ሥርዓታዊ ክንውን ሰው እንደማይሰማው ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም እንዲሁ ነው። የሚከተሉት ማጠቃለያዎች በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጉዳይ ላይ በቂ ማብራሪያ ይሰጣሉ።

የመንፈሰ ቅዱሰ ጥምቀት ለአማኞች ሁሉ የሚሆን ነው። አማኞች ሁሉ ደኅንነትን በተቀበሉበት ቅፅበት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠመቁ ቀደም ብሎ ተመልክተናል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የመንፈሳዊ ብስለት፥ ራስን አሳልፎ የመስጠት ወይም በመሠረታዊ ትምህርት የመገንባት ጉዳይ አይደለም። እያንዳንዱ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቁን እስኪረዳ ድረስ የማያስተውለው ቢሆንም፥ እምነቱን በክርስቶስ ባደረገ ወቅት በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ መሆኑ ግን ሐቅ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያላቸው እውቀት ጥቂት መሆኑ ስውር አይደለም። ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነትና በእርሱ ውስጥ የሚኖረን ስፍራ በሚገባ የምንገነዘበው፥ ልባችንን ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥተን ከርሱ ስንማር ነው። ሰው ከመዳኑ የተነሣ በሕይወቱ የሚያየው ለውጥ በደኅንነቱ ላይ ዋስትና እንዲሰማው ቢያደርግም፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግን የሚሰማ ነገር አይደለም።

የመንፈሰ ቅዱሰ ጥምቀት የኅብረትን ጸውነት ያመለክታል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መንፈሳዊ ኅብረትን የሚያመለክት ስለሆነ ለአማኙ የሚሰማ አይደለም። ‘‘በክርስቶስ’’ ያለን ስፍራ ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ከመስጠታችን የተነሣ ለሚሰሙን ስሜቶች መሠረት ቢሆንም፥ ከጌታ ጋር ያለን ሕብረት በራሱ ግን ስሜትን የሚፈጥር ነገር አይደለም። አማኞች ሁሉ ተመሳሳይ የሆነ ግንኙነት ከጌታ ጋር ቢኖራቸውም፥ ብዙዎች ያላቸው መንፈሳዊ ልምምድ ውሱን ነው። በእያንዳንዱ ግለሰብ ሕይወት

ያለው እድገት ይለያይ እንጂ ሁሉም በክርስቶስ ያላቸው ሕብረት ግን አንድ ነው። በተለይ በክርስቶስ ውስጥ እንድንሆን ያደረገን የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ተግባር የስሜት ጉዳይ አይደለም። ወደ ነፍሳችን የገባው አዲሱ ሕይወት በደኅንነት የደስታ ጮርፍ ሊያጥለቀልቀን ይችላል። ይቅር መባላችንንና መጽደቃችንን ማወቃችን በውጥረት ውስጥ የነበረውን አእምሮአችንን ሊያሳርፈው ይችላል። ''በክርስቶስ ውስጥ'' እንድንሆን የሚያደርገን ሂደት (ክንውን) ግን በራሱ የሚሰማን ነገር አይደለም።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቅጽበታዊ የእግዚአብሔር ሥራ። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በባሕርይው እንደ ሂደት ተደርጎ መቆጠርን አይፈቅድም። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የእግዚአብሔር ሥራ እንደመሆኑ መጠን ቅጽበታዊ ነው። ስለዚህ በቅጽበታዊ ተግባር የልምምድ ሂደት ሊኖር አይችልም። ይህን ጥምቀት በሚመለከት ረገድ የሽግግር ወቅት የለም። አማኝ ''በአዳም'' ከነበረበት ''በክርስቶስ'' ወዳለው ስፍራ ወዲያውኑ ይመጣል። ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኋላ ምንም ዓይነት ስሜት ይሰማን፥ የጥምቀቱ ክንውን ግን በስሜታችን የሚሰማን አይደለም።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የእግዚአብሔር ቅጽበታዊ ሥራ መሆኑን መገንዘብ፥ ይህን መሠረታዊ ትምህርት ካልተለመደና ከተሳሳተ አመለካከት ነጻ በመሆን የምናቀርበው ያደርገዋል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በመሠረቱ እግዚአብሔር አንድን ነፍስ የራሱ የሚያደርግበት ሉዓላዊ ሥራ ነው።

7. ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው

መንፈስ ቅዱስ የጥምቀት ሥራ ፈጻሚ መሆኑን መሠረታዊውን የእምነት ትምህርት ያጠኑ ሰዎች ሁሉ አስቀድመው ተገንዝበውታል። ይሁን እንጂ ይህን አሳብ በሚመለከት አልፎ አልፎ የሚሰነዘር ተቃውሞ አለ። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚናገሩ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጥናት 'ኧን' ['en'] የሚለው የግሪኩ መስተዋድድ ጥቅም ላይ እንደዋለ ያሳየናል። ይህ 'ኧን' ተብሎ የሚጠራው የግሪክ መስተዋድድ በሁለት መንገድ ይተረጎማል። አንዱ መሣሪያን የሚያመለክት ሲሆን፥ በአማርኛ በ'በ' ይተረጎማል። ሁለተኛው ደግሞ ቦታን የሚያመለክት ስለሆነ በአማርኛ ''በ...ውስጥ'' በሚል ይተረጎማል። የመጀመሪያው አተረጓጎም የምንጠመቀው በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ይገልጣል። በሁለተኛው አተረጓጎም ደግሞ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ እንደሚያጠምቀን ያመለክታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ የምናገኘው የመስተዋድድ አጠቃቀም፥ በመጀመሪያ ያመለከትነው ስለሆነ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን ትርጉም ወስደናል (ማቴ. 12፡24፤ ሉቃስ 22፡49፤ ዕብ. 11፡37፤

ራእይ 2፡16፤ 6፡8፤ 13፡10ን ይመልከቱ)። ፈሪሳውያን "ይህ በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም" (ማቴ. 12፡24)፥ ሲሉ ተአምሩን የሠራው "የአጋንንት አለቃ" ነው ማለታቸው እንደሆነ ግልጥ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ደቀ መዛሙርት፥ "ጌታ ሆይ፥ በሰይፍ እንምታቸውን?" (ሉቃስ 22፡49) ብለው ሲጠይቁ፥ መሣሪያው በሰው እጅ የሚያዝ ቢሆንም የታሰበው ነገር የሚፈጸምበት መሣሪያ ሰይፍ እንደሆነ መመልከት እንችላለን። በመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ሥራ ውስጥም የመስተዋድዱ አጠቃቀም ምናልባት በተመሳሳይ መንገድ በመሣሪያነት ሳይሆን አይቀርም። የሐዋርያት ሥራ 1፡5ም ሆነ የ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 አሳብ ይህ ነው።

ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ ያለው ጠቅላላ አገልግሎት የሚፈጸመው፥ በክርስቶስ ፈቃድ መሆኑ ግልጥ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ የእርሱ ወኪልና ሥራውን የሚያከናውንለት ነውና። ስለዚህ የተጠመቅነው ክርስቶስ በላከው መንፈስ ቅዱስ ነው ለማለት ይቻላል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተፈጸመው በክርስቶስ ስለሆነ፥ የተጠመቅነው በክርስቶስ እንደሆነ የሚናገሩ ክፍሎች አሳብንም በዚህ መሠረት ለመረዳት እንችላለን። ልክ የሊቀ ካህኑ አገልጋይ ጆሮ በደቀ መዝሙሩ ወይም በደቀ መዝሙሩ ሰይፍ ተቆረጠ ማለት እንደምንችል፥ በመንፈስ ቅዱስ ወይም በክርስቶስ ተጠመቅን ማለትም እንችላለን (ሉቃስ 22፡49)።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ትክክለኛ ተግባር አማኙን ወደ ክርስቶስ አካልና ወደ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ክልል ማምጣት ነው። በዚህ መሠረት በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 እንደተመለከተው፥ "እኛ ሁላችን አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።" ይህ ቃል የሚያመለክተው፥ በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ውስጥ መሳተፍን ሳይሆን አይቀርም። ይሁን እንጂ ዳግም ልደት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደሆነ ሁሉ፥ ጥምቀትም የርሱ ሥራ ነው። በሥላሴ ሥራ ውስጥ ሊነጣጠል የማይችል የአሠራር አንድነት ቢኖርም፥ የዩኒተሪያኒዝም ተከታዮችን ስሕተቶች ለማስወገድ ከፈለግን በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ያለውን የእያንዳንዱን አካል ኃላፊነት በማሳየት ረገድ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል።

8. በእሳት መጠመቅ

አራቱም ወንጌላት መጥምቁ ዮሐንስ ሊመጣ ስላለው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሰጠውን ምስክርነት መዝግበዋል (ማቴ. 3፡11፤ ማር. 1፡8፤ ሉቃስ 3፡16፤ ዮሐ. 1፡33)። ሦስቱ ወንጌላት (የማቴዎስ፥

የማርቆስና የሉቃስ) መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ መምጣት የሰጠውን ምስክርነት የተወሰነ ክፍል ይናገራሉ። የወንጌላዊው ዮሐንስ ምስክርነት ደግሞ ክርስቶስ ተለይቶ የሚታወቀው በላዩ ወርዶ በነበረው መንፈስ መሆኑን ያመለክታል። ሁሉም ጽሑፎች ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ልዩ ባሕርይ እንዳለው የሚያሳዩ ሲሆኑ፥ ትረካዎቹ ደግሞ በባሕርያቸው ትንቢታዊ ናቸው።

በሁለት ወንጌላት ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሰጠው መገለጥ፥ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል የሚለው ነው (ማቴ. 3፡11፤ ሉቃስ 3፡16)። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች፥ ይህ ነገር በጰንጠቆስጤ ዕለት ተፈጽሟል፥ ምክንያቱም ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች እንደታዩዋቸው፥ በእያንዳንዳቸውም ላይ እንደተቀመጡባቸው ተገልጧል ይላሉ። ሌሎቹ ደግሞ ይህ ሁኔታ ዛሬም የምንለማመደው፥ ዳግም ጰንጠቆስጤ ነው ይላሉ። በወንጌላት ውስጥ የሚገኙትን ጥቅሶች በጥንቃቄ በምንመረምርበት ጊዜ ግን ሁለቱንም አተረጓጎሞች ውድቅ እናደርጋቸዋለን። የክፍሎቹ ዐውደ ንባብ የሚናገረው በክርስቶስ ዳግም ምጽዓትና መንግሥቱ በሚመሠረትበት ጊዜ ስለሚፈጸም ፍርድ ነው። የቤተ ክርስቲያን ዘመን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንደተጀመረ ሁሉ፥ የሺህ ዓመት መንግሥትም በእሳት ጥምቀት ይጀምራል። የእሳት አጠቃቀም ብዙ ጊዜ ስለ ወደፊት ፍርድ የሚናገር ሲሆን፥ በእሳት ስለ መጠመቅ በመልእክቶች ውስጥ የተጻፈ አንዳችም ነገር የለም። ይህ በእሳት የማጥመቅ ነገር በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ማብራሪያ ያልተሰጠበት ጉዳይ ነው። ስለሆነም ጥቅሱ የሚያመለክተው ለአሁኑ ጊዜ የሚጠቅም ወይም ተግባራዊ የሚሆን ነገርን ሳይሆን፥ ክርስቶስ ዳግም በሚመጣባት ጊዜ በዓለም ላይ ስለሚያመጣው ፍርድ የሚናገር ነው ማለት የተሻለ አተረጓጎምና ውሳኔ ይሆናል።

9. በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ዘላለማዊ ውጤቶች

የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት አሠራር መመርመር፥ በክርስቲያናዊ ደኅንነት ረገድ በርካታ እውነቶችና ኗሪ ውጤቶችን ይገልጥልናል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለስሜት የሚሰማ ባይሆንም፥ አስፈላጊ የሆኑና በርሱ አማካይነት እውን የሚሆኑት ክርስቲያናዊ ልምምዶች በሙሉ የሚፈልቁት ከዚህ እውነታ ነው። በዚህ የሚካተቱ እውነቶች እዚህ ላይ ተሟልተው ሊቀርቡ ባይችሉም፥ ዋና ዋና መሪ አሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው በአጭር በአጭሩ ተገልጠዋል።

ሥዲስ ሥንድነት። አዲስ ግንኙነት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቋሚ ውጤት ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ክርስቲያን ሕያው አባል ለመሆንና የጋራ ሕይወትን ለመካፈል ወደ ክርስቶስ አካል ይጨመራል። ይህ መሠረታዊ እውነት፥ ክርስቲያኖችን ለዘላለም አንድ የሚያደርጉ እውነቶች ሁሉ መሠረት ነው። ክርስቲያን ወደ ክርስቶስ አካል መጨመር ብቻ ሳይሆን፥ ከርሱ ጋር ዘላለማዊ አንድነትም ይኖረዋል። የአንድነቱ ባሕርይ ለቅዱሳን የዘላለም ዋስትና የሚሰጥ ደጋፊ አሳብ ነው። ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በምንም አካኋን የሚጠፋ አይደለም።

ሥዲስ ሰፍራ። ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት በሚገኝ አዲስ አንድነት ወደ አዲስ ስፍራ ይገባል። ይህ አዲስ ስፍራ አብዛኛዎቹን የደኅንነት አስደናቂ እውነታዎች የያዘ ነው። ክርስቲያን ለሰይጣን ዓላማ መሣሪያ በመሆን ፋንታ፥ በክርስቶስ አካል ውስጥ በመሆን የጌታን ዓላማ የሚፈጽም ይሆናል። በክርስቶስ አካል ውስጥ ባለው አዲስ ስፍራ፥ የእግዚአብሔር ዓላማ መፈጸሚያ ይሆነው ዘንድ አስፈላጊ የሆኑ ስጦታዎች ሁሉ ከርሱ ይሰጡታል። አማኝ በክርስቶስ ውስጥ አዲስ ስፍራ አለው። ክርስቲያን በአዳም ከነበረው የቀድሞ ስፍራው ወጥቶ በክርስቶስ አዲስ ስፍራ ተሰጥቶታል። ይህ አዲስ ስፍራ ቋሚ ርስት ነው። ወደ እግዚአብሔር የመቅረብና የመግባት መብት አግኝቷል፤ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ፥ ቀድሞ ሊሆን ያልቻለ፥ በዚህ ዘመን በሙላት የሚያገለግልበትን ነገር ሁሉ እንዲያገኝ ያደርገዋል። የክርስቲያን አዲስ ስፍራ እግዚአብሔርን በመፍራት ለመኖር የሚገፋፋና የሚያበረታታ፥ ኃጢአትንም ድል ለመንሳት መሠረት ነው።

1513 *ሥዲስ ኅብረት።* ክርስቲያን ባለው አዲስ አንድነትና በተሰጠው አዲስ ስፍራ ምክንያት፥ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወደ ብዙ አዲስ ኅብረቶች ይመጣል። ከሥላሴ ጋር ያለው ኅብረት በሙላት የሚገለጠው ወደፊት ቢሆንም፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱም በዚህ ዘመን ላለው ልምምዱ ወሰን የሌለውና አስደናቂ ነገር ነው። ሰው ደኅንነት ሲያገኝ ከዓለም ጋር የነበረው ኅብረት ይለወጣል። በዓለም የሚኖርና ለሰብአዊ መንግሥት የሚገዛ ቢሆንም፥ ከዚህ ዓለም አሠራር በእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ ሊወጣ ይችላል። በዚህ አዲስ ኅብረቱ ምክንያትም የሰይጣን የጥቃት ዒላማ ይሆናል። ይህ ጥቃት ሰይጣን እግዚአብሔርንና የእርሱ የሆኑትን ሁሉ የሚዋጋበት ነው። ለዚህ ነው ክርስቲያን ይህን አዲስ ጠላት መቃወሚያና ነጻ የሚያወጣው የእግዚአብሔር ኃይል ያስፈልገዋል የሚባለው። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ አማኙ ሌሎች የኅብረት ገጽታዎች ይናገራሉ። ከተደራጀች ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ኅብረትም ይገልጣሉ። በወላጆችና በልጆች፥

በባልና ሚስት፥ በባሪያና በጌታ፥ በመሳሰሉትም መካከል መኖር ስለሚገባው ግንኙነት ይጠቅሳሉ። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ኅብረትም በተደጋጋሚ ተጽፏል። ይህ ኅብረት አማኙ ከማያምነው ጋር፥ ከኃጢአተኛ ወንድሙ ጋር፥ በእምነት ወይም በተግባር ከደከሙ ጋር ሁሉ ስላለው ኅብረትና ተግሣጽ ወይም እርማት ከሚሰጡ ወንድሞች ጋር ስላለው ግንኙነት ሁሉ የሚናገር ነው። የእግዚአብሔር የተትረፈረፈ ቸርነትና ስጦታ፥ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ክርስቲያን የተጠራበት ጸጋ በሚጠይቀው አዲስ ሕይወት እንዲኖር የሚያስችለው ነው። በአጭሩ የክርስቲያን ሕይወት ከየትኛውም አንጻር የሚለወጠው፥ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት ይሆናል። የዚህ መሠረታዊ ትምህርት አስፈላጊነት ለክርስቲያንም ሆነ ለሥነ-መለኮት ሊታውንት ሁሉ ግልጥ ነው።

ከአሳታሚው መግለጫ

የታወቀ ሰባኪና የመቶዲስት ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ጆን ዌስሊ (1703-1791) ከመጀመሪያ በክርስቶስ ማመን ካለ እምነት የላቀ፥ ማለት አማኝን በክርስትና ሕይወቱ ድል እንዲቀዳጅና በክርስቶስ ከፍ ያለን ኑሮ እንዲኖር የሚያደርገው ነገር እንዳለ አስተምሯል። ቢሆንም ዌስሊም ሆነ የእርሱ ተከታዮች ይህን እምነት በደንብ አላተኮሩበትም ነበር። ነገር ግን ይህ ትምህርት ለዛሬው ‹‹የቅድስና እንቅስቃሴ›› ዕንሰ-አሳብ መነሻ ሆኗል።

‹‹የቅድስና እንቅስቃሴ፥ በ19ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ገደማ አንዳንድ ሰዎች የአማኞች የቅድስና ሕይወት ማሽቆልቆል ጉዳይ በጣም አሳስቧቸው ነበር። ከዚህ የተነሣ ሰውን በቅድስና በመኖር ወደ ፍጹምነት ሊያደርሰው የሚችል ሁለተኛ የጸጋ ሥራ ሊኖር ይገባል ወደሚል አሳብ ላይ ተደረሰ። የዚህ እንቅስቃሴ አቀንቃኞች፥ ይህን ልምምድ ለማግኘት የሰው ጥረት አስፈላጊ እንደሆነ ያምኑ ነበር። ስለዚህም ይህን ልምምድ ‹‹የዳግመኛ በረከት›› ልምምድ በማለት ይጠሩታል። ኋላም ይህ ተቀይሮ ‹‹የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት›› በመባል የሚታወቅ ሆነ። እነዚህ ሰዎች፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንድ አማኝ ብስለት የተሞላበትና ምሳሌያዊ የሆነ የክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖር የሚያስፈልገውን የመንፈስ ኃይል ሁሉ እንደሚያስገኝለት ያስተምሩ ነበር።

በዚያን ወቅት ያስተምሩት እንደነበረ ‹‹የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን›› ‹‹በመንፈስ ስጦታዎችም›› ሆነ በልሳን ከመናገር ጋር በማያያዝ አልተመለከቱትም ነበር።

"ጰንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ" [Pentecostal Movement]፥ በ1901 ቻርልስ ፓርሃም [Charles Parham] በተባለ ሰው ተጀመረ። ይህ ሰው አሜሪካን አገር በካንሳስ በተለይ ቶፒካ በተባለ ስፍራ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከፍቶ ነበር። ዳግመኛ በረከት በሚለው አሳብ ላይ በልሳን መናገር ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምልክት ነው የሚለውን አሳብ ያከለው እርሱ ነው። የዚህ ሰው ተማሪዎች ይህን ትምህርት በየአካባቢያቸው አስፋፉት።

ይህ እንቅስቃሴ በ1906 በጥቁር አሜሪካዊው ሰባኪ በዊሊየም ሲሞር [William Seymour] በካሊፎርኒያ በመቀጠል "የአዙዛ ጎዳና" [Azuza Street] መንፈሳዊ መነቃቂያ በመባል በመላው አሜሪካ የታወቀ ሆነ።

ዛሬ "ጰንጠቆስጤያዊ እንቅስቃሴ"፥ "የካሪስማዊ እንቅስቃሴ" በመባል ይታወቃል። (እነዚህ ቡድኖች ከቅድስና እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ቢሆኑም በታሪካቸው ትንሽ ለየት ያሉ ናቸው።)

የዚህ ቡድን ዋና የእምነት መለያዎች፡- 1. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከደኅንነት የተለየ ከንውን ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የእግዚአብሔር ጸጋ ሁለተኛ ሥራ ሲሆን ያም "ዳግመኛ በረከት" በመባል የታወቀ ነው። 2. በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግለሰቡ መንፈስ ቅዱስን በሙላት ይቀበላል። ይህን አሳብ "የመንፈስ ቅዱስ ሙላት" በማለት ይገልጡታል። 3. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለአማኝ ምስክር እንዲሆን እና ጌታን እንዲያገለግል የሚያስችለው ልዩ ከንውን ነው። 4. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሙላት ተሰጥተዋል። 5. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንደኛው መረጃ፥ አንድም ሆነ ከዛ በላይ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በአማኝ ውስጥ መታየታቸው ነው።

16

የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር

1. የመንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ማደር ሁለንታዊ ነው

የጸጋ ሰፍረ-ዘመን ከቀደሙት ዘመናት ሁሉ የሚለይበት አንዱ ትልቅ ነገር፥ መንፈስ ቅዱስ ዳግም በተወለዱ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የማደሩ እውነታ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር በሚሆንበት ዘመን ደግሞ፥ የዳኑ ሰዎች በሙሉ በመለኮታዊ በረከት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሚሆኑበት ሁኔታ ግልጥ ይሆናል። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የመሆን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ጠቀሜታ በዚህ ዘመን ለዳኑ ሰዎች አገልግሎቶች ሁሉ መሠረት መሆኑ ነው። መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ልብ ውስጥ ከማደሩ የተነሣ፥ የመመሥላት ሥራው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በሚሰጡ (ልባቸውን ባዘጋጁ) ሰዎች ውስጥ እውን ይሆናል። የእግዚአብሔር በአማኝ ውስጥ የማደር እውነታ መሠረታዊና ጠቀሜታ ያለው ትምህርት ነው። አንዳንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሕይወት መኖርን ራስን በተለየ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ከመስጠት ጋር አንዳንዶች ያያይዙታል።

ከዚህ በተቃራኒ ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ያደረበት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ በሰው የማደሩ ሐቅ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተጠቅሷል (ዮሐ. 7፡37-39፤ ሐዋ. 11፡17፤ ሮሜ 5፡5፤ 8፡9፥ 11፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡12፤ 6፡19-20፤ 12፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡5፤ ገላ. 3፡2፤ 4፡6፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡24፤ 4፡13)። በጳንጠቆስጤ ዕለት መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ በማደር ቤተ ክርስቲያንን መኖሪያው ለማድረግ መጣ። ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚያመለክቱ በርካታ ነጥቦች አሉ።

የመንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ውስጥ አለማደር አለመዳንን ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሁሉ ውስጥ እንደሚያድር ከሚያሳዩ ጥሩ መረጃዎች አንዱ በሮሜ 8፡9 በቀጥታ የተነገረው ቃል ነው፡- ‘‘እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም።’’ በክርስቶስ በራሱ የተላከውንና ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠውን ይህን መንፈስ ማግኘት ለመዳን እና

የክርስቶስ ለመሆን አስፈላጊ ነው። በዚህ መሠረት ያልዳኑ ሰዎች ‹‹መንፈስ የሌላቸው›› ተብለው ተገልጠዋል (ይሁዳ 19)።

በኃጢአታቸው የቀጠሉ ክርስቲያኖች እንኳ የመንፈሰ ቅዱሰ ማደሪያዎች ናቸው። በዚህ የጸጋ ስፍራ-ዘመን ክርስቲያኖች ኃጢአትን ቢያደርጉ መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ እንደሚወሰድ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ጨርሶ የለም። በተቃራኒው ሊጠቀሱ የሚገባቸው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች፥ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ስለሆኑ ኃጢአትን እንዲክዱና እግዚአብሔርን የመፍራት ሕይወት እንዲኖሩ ተመክረዋል። ‹‹ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? የራሳችሁ አይደላችሁምና›› (1ኛ ቆሮ. 6፡19)። መንፈስ ቅዱስ ራሳቸውን በሚገባ ባልሰጡና በኃጢአት በሚኖሩ ክርስቲያኖች ውስጥ እንኳ የሚያድር መሆኑን ይህ ጥቅስ ያመለክታል ለማለት ይቻላል። በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ራስን ለመንፈስ ቅዱስ መስጠት የግድ አስፈላጊ ቢሆንም፥ የእርሱ በእውነተኛ ክርስቲያኖች ውስጥ ማደር ግን ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ የማይጠይቅ ነው።

መንፈሰ ቅዱሰ ሰጦታ ነው። በብዙ ቦታ መንፈስ ቅዱስ ‹‹ስጦታ›› መሆኑ ተገልጧል (ዮሐ. 7፡37-39፤ ሐዋ. 11፡17፤ ሮሜ 5፡5፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡12፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡5)። እግዚአብሔር ስጦታን የሚሰጠን ለዚያ የምንገባ ሆነን አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለጽድቃችን እንደ ሽልማት የተሰጠ ስለመሆኑ የተነገረ አንዳችም ነገር የለም። አስፈላጊው ነገር ክርስቶስን የግል አዳኝ አድርጎ መቀበል ብቻ ነው። በዚህ መሠረት ነው ሰጦታው ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚሰጥ።

ጌታ የሚጠብቅብን የሕይወት ደረጃ መለኮታዊ አርዳታን ይጠይቃል። ለክርስቲያኖች በተጻፈ መልእክት እንደተገለጠው፥ እግዚአብሔር በአማኝ ሕይወት ከመኖሩ የተነሣ የሚታዩት ከፍተኛ የሕይወት ደረጃዎች፥ የመንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሁሉ የማደሩ ሌላ ማረጋገጫ ነው። ክርስቶስ በዮሐንስ 7፡37-39፥ ‹‹የሕይወት ውኃ ወንዝ›› ከክርስቲያኖች እንደሚፈልቅ አስቀድሞ ተናግሯል። የበረከት እና የብቃት ምንጭ ከውጭ የሚመጣ ሳይሆን፥ ከክርስቲያኑ ከራሱ የሚወጣ ነው። የሐዋርያት ትምህርት የተመሠረተው በዚህ ላይ መሆኑንና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ እንደሚከናወን ክርስቶስ በተዘዋዋሪ መንገድ ተናግሯል። እነዚህ በርካታ የቅዱሳት መጻሕፍት መረጃዎች በግልጥ የሚያሳዩት፥ የመንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ የማደር በረከት፥ ልክ እንደ ዳግም ልደትና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ለአማኝ ሁሉ የተሰጠ መሆኑን ነው።

2. አስቸጋሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

የመንፈስ ቅዱስን በሰው ውስጥ ማደር የሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በይዘቱ ቀለል ያለና ለመግለጥም የማያስቸግር ነው። ነገር ግን ትምህርቱን በአግባቡ የመረዳት ችግር የሚታይበት ስለሆነ፥ አስቸጋሪዎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥንቃቄ ማጥናት ይገባል። በአጠቃላይ ሲታይ እነዚህ ሰባት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በከፍተኛ ደረጃ በተሳሳተ መንገድ የሚተረጐሙ ሆነዋል (1ኛ ሳሙ. 16፡14፤ መዝ. 51፡11፤ ሉቃስ 11፡13፤ ሐዋ. 5፡32፤ 8፡14-20፤ 19፡1-6፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡20፥ 27)።

የስፍረ-ዘመናትን ልዩነት ባለመገንዘብ የተነሣ ለመረዳት የሚያስቸግሩ ምንባቦች። የሦስቱ ምንባቦች ችግር የመጣው፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በዘመናት ሁሉ አንድ ነው ከሚለው የተሳሳተ ግምት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ከሳኦል መለየት የሚያረጋግጠው፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳን ሁሉ ውስጥ የማይኖር መሆኑን ብቻ ነው (1ኛ ሳሙ. 16፡14)። ዳዊትም ከመዝሙር 51፡11 በሚገኘው ጸሎቱ መንፈስ ቅዱስ እንዳይወሰድበት የለመነው፥ በኃጢአት ምክንያት በሳኦል ላይ እንደሆነው ይወሰድብኛል ብሎ በማሰብ ነው። የዳዊት ጸሎት፥ መንፈስ ቅዱስ አብሮት የሚኖር ስጦታ እንደሆነ ለተረጋገጠለት ክርስቲያን የሚሠራ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ለሚለምኑ ሰዎች መሆኑን ክርስቶስ በምድር ላይ ሳለ የቅርብ ተከታዮቹ ለነበሩት ሰዎች ነግሯቸዋል (ሉቃስ 11፡13)። ነገር ግን በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት ደቀ መዛሙርቱ የወሰዱት እርምጃ ስለመኖሩ የተጻፈ አንዳችም ነገር የለም። በተቃራኒው ክርስቶስ ከተለያቸው በኋላ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣና እንደሚያድርባቸው ቃል ሲገባላቸው ወይም ተስፋ ሲሰጣቸው እንመለከታለን። ይህ ተስፋ የሚያሳየው ጌታ አብሯቸው በነበረበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ያላደረባቸው መሆኑን ነው። የእነዚህን ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አጠቃላይ አሳብ ስንመለከት *መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን በክርስቲያኖች ውስጥ ስለማደሩ የሚያመለክቱ እንዳልሆኑ በግልጥ ለመናገር እንችላለን።

የሐዋርያት ሥራ 5፡32። የሚቀጥሉት ሦስት ክፍሎች (ሐዋ. 8፡14-20፤ 19፡1-6) የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ከአዲስ ልደት ቀጥሎ የሚፈጸም ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተተርጉሟል፤ አንዳንድ ጊዜም የአማኝ ሁሉ እንዳልሆነ ሆኖ ይቀርባል። ከእነዚህ ሦስት ጥቅሶች የመጀመሪያ የሆነው የሐዋርያት ሥራ 5፡32 እንዲህ ይላል፦ "እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው።" አንዳንድ ጊዜ ይህ ቃል፥ መታዘዝ ወይም ራስን

ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ መስጠት ለመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ የሚቀርብ ይመስላል። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ‘‘ለሚታዘዙት’’ የሚለው ቃል አሳብ፥ ግብረ ገብነትን ወይም የሕይወት ጥራትን ለማመልከት ሳይሆን፥ ልንታዘዘው የሚገባን ነገር በክርስቶስ ማመን እንደሆነ መግለጥ ነው። ይህ እግዚአብሔር መንፈሱን በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያምኑ ይሰጣል፥ ወደሚል ድምደማ ያደርሳል። መታዘዝ የሚለውን ቃል ከመጀመሪያው የግሪክ ቃል አንጻር ስናየው፥ ለአንድ ባለሥልጣን ስለ መታዘዝ የሚናገር ነው። ስለዚህ ቃሉ ክርስቶስንና ሥልጣኑን መገንዘብን ይመለከታል።

የሐዋርያት ሥራ 8፡14-20። እላይ ከተጠቀሱት ሰባት ክፍሎች ሁሉ የሐዋርያት ሥራ 8፡14-20 በአማኞች ሁሉ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያድራል የሚለውን አሳብ የሚቃረን ይመስላል። በዚህ ቃል መሠረት በፊልጶስ የተጠመቁት አማኞች መንፈስ ቅዱስን አልተቀበሉም ነበር። ጴጥሮስ በመጣ ጊዜ ግን እጁን እንደጫነባቸውና መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ እናያለን። ከነዚህ ሁኔታዎች በመነሣት መንፈስ ቅዱስን መቀበል ከደኅንነት በኋላ የሚሆንና እጆችን መጫን የሚጠይቅ ነው የሚል የተሳሳተ ትርጉም እናገኛለን።

ይህ ችግር በሦስት ልዩ ልዩ መንገዶች መፍትሔ ሊገኝለት ይችላል። የመጀመሪያው፥ ምንም እንኳን የተለመደው የመንፈስ ቅዱስ መቀበል እስከ ጴጥሮስ መምጣት ድረስ መዘግየቱን ብንቀበልም፥ ይህ ድርጊት ጨርሶ እንዳልተደገመ ግልጥ ነው። የሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያ ክፍሎች ስለ ሽግግር ወቅት የሚናገሩ ናቸው። እግዚአብሔር ለዚህ ዘመን ያለው ትክክለኛ አሠራር የተገለጠው ቀስ በቀስ ነው። ለወንጌል መስፋፋት ዋና ምክንያት፥ ሐዋርያት ከጌታ የተቀበሉትን አደራ ከመፈጸማቸው ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። ያልተለመደ ከፍተኛ ኃይልና የሚያነቃቃ በረከት በፈታቸው የተገለጠበት ምክንያትም ይህ ነው። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በሙላት በአሕዛብ መካከል የተጀመረው፥ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 አሕዛብ በወንጌል አምነው መንፈስ ቅዱስ ባደረባቸው ጊዜ ነው። ከዚህ ክንውን የተነሣ፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በክርስቶስ ላይ ካለ እምነት እንጂ፥ በጴጥሮስ ማንነት ላይ እንደማይደገፍ ለጴጥሮስ በግልጥ ተነገረው። ከላይ የተነጋገርንበት መሠረታዊ አሳብ መፍትሔ፥ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሁሉ ሕይወት ውስጥ እንደሚያድር የሚናገረውን መሠረታዊ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ይደግፋል።

ሌሎች ሁለት መፍትሔዎችን በተጨማሪ ለማቅረብ ይቻላል። ሁለተኛው መፍትሔ የሚገኘው ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10

በፊት የመንፈስ ማደር ምናልባት በሐዋርያት አማካይነት አገልግሎት በተሰጣቸው አሕዛብ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን አይቀርም፤ መንፈስ ቅዱስን ወዲያው የተቀበሉት አይሁድ ብቻ ነበሩ። ቢያንስ ቢያንስ ወንጌል አዲስ በሚሰፋፋባቸው ቦታዎች ሁሉ ቅድሚያ እየሰጡ በቀጥታ ያገለግሉ የነበሩት ሐዋርያት እንደነበሩ ግልጥ ነው። ሦስተኛው መፍትሔ የሚገኘው ደግሞ፥ ‘‘መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ’’ የሚለው ቃል (ሐዋ. 8፡17) ትርጉም እንደ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ያለ ውጫዊ ሂደት እንጂ፥ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር አይደለም በሚለው አሳብ ውስጥ ነው። ‘‘ተቀበሉ’’ የሚለው ቃል በሁሉም ቦታ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገር ነው ብሎ ማመን ግን አጠራጣሪ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሁለት መፍትሔዎች ለምንባቡ በቂ መግለጫ የሚሰጡ ናቸው። በማንኛውም ጊዜ ዘግይቶ የሚፈጸም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት ጨርሶ ተደግሞ አያውቅም። ስለዚህ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ውስጥ ባለው አሳብ በመመርኮዝ ለአጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን ዘመንም የተለመደ አሠራር ነው ወደሚል አሳብ መድረሱ ልናመክረው ለምንፈልገው አሳብ በቂ ዋስትና አይሰጥም።

የሐዋርያት ሥራ 19፡1-6። የንባቡን አጠቃላይ ይዘት ማየት፥ በጥንቃቄ ማጥናት፥ እና ጥቅሱን በትክክል መተርጎም ለዚህ ክፍል ችግር መፍትሔ ያስገኙለታል። በኤፌሶን የነበሩ ደቀ መዛሙርት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እንደነበሩና ከጸጋው ወንጌል ጋር ገና እንዳልተገናኙ ከዓውደ ንባቡ እንመለከታለን። በተጠመቁና በክርስቶስ ባመኑ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ መጣ። ‘‘ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ’’ (ቁ. 6) የመንፈስ ቅዱስ ሕልውናም በመካከላቸው በልሳን በመናገራቸውና ትንቢት በመተንበያቸው ተገለጠ። ከታሪኩ የምንረዳው ነገር፥ መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እንዳደረና እንደሞላቸው ሲሆን፥ ይህ የሚያሳየው መንፈስ ቅዱስ በእነሱ ከማደሩ የተነሣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ያስከተለ መሆኑን ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ሊያድርባቸው የመጣው ከደኅንነት ቀጥሎ እንደነበር ሆኖ ሊጠቀስ አይገባም፤ ምክንያቱም ከጳውሎስ ጉብኝት በፊት እነዚህ ሰዎች ደኅንነትን አላገኙም ነበር።

በሐዋርያት ሥራ 19፡2 ያለው፡- ‘‘ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?’’ የሚለው የጳውሎስ ጥያቄ፥ ዳግም ስለመወለዳቸው ያቀረበው የማረጋገጫ ጥያቄ እንጂ፥ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሚሆኑት የተወሰኑ ክርስቲያኖች ናቸው የሚለውን ፅንሰ-አሳብ ጨርሶ የሚደግፍ አይደለም። ጥያቄው የሚያመለክተው ግን ዳግም በተወለዱ አማኞች ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚያድርባቸው መሆኑን ነው። የመንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው አለመኖር የሚያመለክተው ደኅንነት

አለማግኘታቸውን ነው። በዚህ ክፍል የተፈጸመው ነገር የሚያመለክተው፥ ክርስቲያኖች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሚሆኑት ዳግም በተወለዱ ጊዜ ነው ከሚለው ከተለመደው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የተለየ አሳብ አለመኖሩን ነው።

በመንፈስ ቅዱስ መቀባት። ሌላ ተጨማሪ ችግር የምናየው በመንፈስ ቅዱስ ስለ መቀባት በሚናገሩት ክፍሎች ነው። አንዳንዶች ከእነዚህ ክፍሎች በመነሣት በመንፈስ ቅዱስ መቀባት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከመሆን ጋር በተነጻጻሪነት የሚቀርብ የተለየ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው ይላሉ። በመንፈስ ቅዱስ ስለ መቀባት ስለሚናገሩ ሰባቱም ክፍሎች (ሉቃስ 4፡18፤ ሐዋ. 4፡27፤ 10፡38፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡21፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡20፥ 27፥ ሁለት ጊዜ) በጥንቃቄ የሚደረግ ጥናት፥ መቀባት የሚለው ቃል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተያይዞ የተገለጠባቸው ክፍሎች ሁሉ፥ ድርጊቱ የመጀመሪያው የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማደር ተግባር መሆኑን ለመተርጐም የሚያስችሉ ናቸው። መቀባት የሚለው ቃል አገባብ፥ አንድ ነገር ሰው ላይ በማፍሰስ ወይም በማኖር የመደባበስን ስሜት የሚያሳይ በመሆኑና ዘይትም በመንፈስ ቅዱስ አምሳያነት በመጠቀሱ፥ ከዚህ አመለካከት ጋር የሚስማማ ያደርገዋል። የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና የመቀባት ውጤት ሲሆን፥ ስለ መቀባት የሚናገሩ ጥቅሶች በሙሉ በዚህ ስሜት የተነገሩ ናቸው።

3. የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማደር ልዩ ባሕርያት

መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር የሚጀምረው፥ እግዚአብሔር አዲስ ለሚድነው ነፍስ ከሚያደርገው በርካታ ክንውኖች ጋር ቢሆንም፥ በተለያዩ የእግዚአብሔር ሥራዎች መካከል ያለው ልዩነት በወጉ ሊጤን ይገባል። የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር፥ ከዳግም ልደት ጋር ተመሳሳይ አይደለም። የአማኙ አዲስ ሕይወት መለኮታዊና በባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር የተመሳሰለ ቢሆንም፥ የመለኮታዊ ሕይወት ባለቤትነትና የመለኮት ሕልውና የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ሥራና በሰው ውስጥ ማደር የተለያዩ ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለአንዱና ለመጨረሻ የሚሆን ሲሆን፥ ከዓለም ከመለየትና ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆን ክንውን ጋር የተያያዘ ነው። የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር የሚጀምረው፥ ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር በተመሳሳይ ሰዓት ቢሆንም፥ የሚቀጥል ጉዳይ ነው። በውጤቱ ማረጋገጥ እንደሚቻለው፥ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ መኖር፥ በመንፈስ ቅዱስ ከመታተም ጋር ፍጹም የጠበቀ ግንኙነት ያለው መሆኑን ማጎተምን በሚያካትተው የመንፈስ ቅዱስ መገኘት እናያለን።

ለመለየት በጣም የሚያስቸግረው፥ ምናልባት የመንፈስ ቅዱስን በሰው ውስጥ ማደርና ሙላትን ነው። ሁለቱ መሠረታዊ ትምህርቶች እጅግ የተዛመዱ ቢሆኑም፥ አንድ ግን አይደሉም። ሙላት አጠቃላይ ልምምድ ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ግን በራሱ ልምምድ አይደለም። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ጥቂት ቅዱሳን በቋሚነት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሳይሆኑ ለተወሰነ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል። በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላታቸው ስንናገር በአዲስ ኪዳን እንደተገለጠው በቋሚነት ባይሆንም፥ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆነዋል። በቤተ ክርስቲያን ዘመን አንድ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አይሞላም። ማደር የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር ሲሆን፥ ሙላት የሚጠቁመው ግን መንፈስ ቅዱስ የፈቃደኛ ግለሰቦችን ሕይወት የመቆጣጠር አገልግሎቱን ነው። የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር የሰው ሥራ አይደለም። ከጎብረትና ከፍሬ ጋር የተያያዘው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትና ልምምድ የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት የተነሣ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንሆን ዘንድ ባንደፋፈርም፥ በመንፈስ ቅዱስ እንሞላ ዘንድ ግን ጠበቅ ያለ ምክር ቀርቦልናል (ኤፌ. 5፡18)።

4. መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማደሩ አስፈላጊነት

የመንፈስ ቅዱስ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የመኖሩ አስፈላጊነት ሊገመት የሚችል አይደለም ስንል ማጋነናችን አይደለም። ይህም በፍሬያማነትና በቅድስና ረገድ ያለውን መለኮታዊ ዓላማ እንዲሁም ጸጋ የሚያረጋግጥ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና ከፈታችን ያለውን በረከት የማግኘታችን "መያዣ" ነው (2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ 5፡5፤ ኤፌ. 1፡14)። መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሕይወት ላለው አገልግሎት ዋስትና ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን የማያቋርጥ እንክብካቤና የገባልንን የማይሻር ቃልና ዓላማ እንዲፈጸም የሚያደርግ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና የአማኞችን አካል የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አድርጎታል (1ኛ ቆሮ. 6፡19)። የመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ማደር፥ በዚህ ምድር ላይ ለዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ዓላማ የሚገልጥ ነው። ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ቸል ማለት፥ ወይም የነገሩን እርግጠኝነት ጥያቄ ውስጥ መጣል፥ በክርስትና አጠቃላይ የእምነት ትምህርት ላይ ከፍተኛና አወዛጋቢ ችግር ያስነሣል። እግዚአብሔር በአሁኑ ጊዜ የክርስቲያኖችን አካል ምድራዊ ቤተ መቅደስ የማድረጉ የተባረከ እውነት፥ ለሕይወትና ለአገልግሎት ኃይል እጅግ ጠቃሚ ለሆነ ክርስቲያናዊ ልምምድ ሁሉ ዋና ጉዳይ ነው።

17

የመንፈስ ቅዱስ ማተም

1. ማኅተሙ መንፈስ ቅዱስ ነው

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ‘‘በማኅተም’’ አምሳያነት እንደተገለጠ የሚናገሩ ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ (2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ ኤፌ. 1፡13፤ 4፡30)። የነዚህ ክፍሎች አጠቃላይ አሳብ፥ ማተም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን ይገልጣል። ክርስቶስ ራሱ በእግዚአብሔር አብ የታተመ ሲሆን፥ ይህ ሥራ ግን በቀጥታ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ የተገለጠ ነገር የለም (ዮሐ. 6፡27)።

ሁሉም ክፍሎች ግልጥ የሚያደርጉት፥ የማተም ተግባር ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር የሚፈጸም መሆኑን ነው። ክርስቲያንን በሚያበረታታ ሁኔታ ወይም ጥረት አድርጎበት የሚደረስበትም ግብ እንደሆነ ተደርጎ የተገለጠ ነገር አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ባዳናቸው ሰዎች ሕይወት በቸርነቱ የሚፈጽመው ተግባር ነው።

በኤፌሶን 1፡13፤ 4፡30 መሠረት አማኙ የታተመው በመንፈስ ቅዱስ ነው ወይም በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ነው። የዚህ ተግባር ተከታይ የሆነ አንዳችም ነገር የለም። ከ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡22 ልንረዳው የምንችለው፥ ማኅተሙ መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንጂ ሌላ ሊሆን እንደማይችል ነው። እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ በመንፈሱ አማካኝነት በምንም ዓይነት ነገር ውስጥ የማይገኝን እጅግ የከበረ ማኅተም ሰጥቶናል። ይህ ማኅተም የሚያመለክተው ያለቀና የተፈጸመ የውል ስምምነትን ነው። በምዕራፍ ሦስት ውስጥ እንደተመለከትነው ማኅተም ዋስትናን፥ ደኅንነትን፥ ባለቤትነትን፥ ሥልጣንንና ኃላፊነትን ያመለክታል። ማኅተም የተሰጠው በመዋጀት ቀን ከፍጻሜ ለሚደርሰው ነገር ምልክት ሆኖ ነው።

2. የመንፈስ ቅዱስ ማተም ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚሆን ድርጊት ነው

የመዋጀትን ማኅተም የሚያካትተው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት፥ በተሳሳተ መንገድ ከደኅንነት ቀጥሎ የሚመጣ የጸጋ አገልግሎት ተደርጎ በመቆጠሩ፥ ሰዎች ለማግኘት ሲመኙትና ሊያገኙትም ሲጥሩ ይታያሉ። ስለ መታተም የሚናገሩትን ሦስት ክፍሎች በጥንቃቄ

በምናጠናበት ጊዜ ግን፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የታተመው በደኅንነቱ ጊዜ እንደሆነ ያረጋግጡልናል። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በርካታ ውድቀቶች ቢኖሩባቸውም፥ በመንፈስ ቅዱስ መታተማቸው ተገልጧል (2ኛ ቆሮ. 1፡22)። በመንፈስ ቅዱስ የመታተምን በረከት ያገኙት አንዳንድ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው የሚለው አስተሳሰብ ከዚህ አሳብ ጋር ይቃረናል።

ሁለተኛው፥ በኤፌሶን 1፡13 ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የተናገረው ነው፦ ‘‘ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ፥ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ።’’ እዚህ ላይ ሁኔታዎች የተከሠቱበትን ቅደም ተከተል መገንዘብ እንደሚያስፈልግ ይገልጣል፦ ወንጌልን ሰሙ፥ በክርስቶስ አመኑ፥ በመንፈስ ቅዱስ ታተሙ። ይህ ቅደም ተከተል የሚያመለክተው፥ የጊዜን ሁኔታ ሳይሆን፥ በአንዴ አንዱን ከማድረግ የተነሣ የሚመጣ ውጤትን ነው። ጸሐፊው የሚያብራራው፥ በመንፈስ ቅዱስ መታተማቸው በክርስቶስ የማመናቸው ግልጥ ውጤት እንደነበር ነው። መታተሙ የሚፈጸመውም ልክ ሰዎች በሚያምኑበት ጊዜ ነው።

በኤፌሶን 4፡30 የሚገኘው ሦስተኛ ክፍል የመንፈስ ቅዱስ ማተም ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚፈጸም ተግባር ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ነው። በዚህ ክፍል፥ ‘‘የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ’’ የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። ምክንያቱም በእርሱ የታተምነው በተቤዥንበት ቀን ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ እንደታተሙ ስለሚታመን፥ መንፈስ ቅዱስን እንዳያሳዝኑ የምክር ቃል ተሰጥቷቸዋል። የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም መንፈሳውያን ለሆኑ ብቻ ከሆነ፥ እንደዚህ ያሉትን ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን ስለ ማሳዘን መምከር አስፈላጊ አይደለም። ስለ መታተም የሚገልጡት ጥቅሶች በሙሉ ድርጊቱ በሚያድን እምነት ላይ የተመሠረተና የተፈጸመ ተግባር መሆኑን ያሳያሉ። በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ክርስቲያን በእምነት ሊቀበለው የሚገባ እውነት፥ የእግዚአብሔር ማኅተም የሆነው መንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆኑንና ለዘላለም በመዋጀት የተለየ ሰው መሆኑን ነው።

3. በመንፈስ ቅዱስ መታተም ሕዋሳዊ ልምምድ አይደለም

ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ታተሙ ሲባል፥ ድርጊቱ በሚፈጸምበት የደኅንነት ጊዜም ሆነ በኋላ በሕዋሳቸው የሚገነዘቡት አለመሆኑን በግልጥ ለማየት ይቻላል። የታተሙ ሁሉ እስከ መቤዠት ቀን ድረስ የመታተማቸው እውነት (ኤፌ. 4፡30)፥ ለአንዴና ለመጨረሻ

የሚከናወን ነው። ስለዚህ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ይታተም ዘንድ ሊጸልይም ሆነ ልዩ ልምምድ ሊጠብቅ አይገባውም። ይህ በማይሻረው በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ ያለና በእምነት ልንቀበለው የሚገባ አስደናቂ እውነት ነው።

4. በመንፈስ ቅዱስ መታተም ቁም ነገር

በመንፈስ ቅዱስ መታተም የሚያመለክተው ታላቅ ነገር የአማኙን የዘላለም ዋስትና ነው። የአማኙ መታተም ከኃጢአት ሙሉ በሙሉ ነጻ እስከሚሆንበት እስከ መቤዠት ቀን ድረስ መጠበቁን የሚያሳይ መሆኑ ግልጥ ነው። ጉዳዩ በሰው እጅ የተተወ ሳይሆን፥ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ኃይል የተደገፈ ነው። የማኅተሙ ባሕርይ ማንኛውንም ተመሳሳይ ወይም አሳሳች ነገር ይከለክላል። የእግዚአብሔርን ባሕርያት ሁሉ የያዘው መንፈስ ቅዱስ ከሁሉ የላቀውና ማለቂያ የሌለው የእግዚአብሔር ሰፊ ጸጋ መግለጫ ነው። እግዚአብሔር በመንፈሱ በአማኙ ውስጥ ሊኖር ተስፋ እንደሰጠ ሁሉ፥ የደኅንነታችን ማኅተም የሆነው መንፈስ ቅዱስም አማኝ ሊኖሩት የሚገባውን ዋስትናዎች ሁሉ በልቡ ውስጥ ያኖራቸዋል።

— ክፍል አምስት —

መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ

18

የመንፈሳዊ ስጦታዎች ባሕርይ

1. የመንፈሳዊ ስጦታዎች ጥቅም

በክርስቶስ ኢየሱስ ባመነ ሰው መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ፥ የዚህን ርእስ ያህል ከሕይወቱ ጋር ግንኙነት ያለውና ለአሁኑ ጊዜ በጣም አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ጥቂት ነው። ትክክለኛ የቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎም እና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ግንዛቤ አስፈላጊዎች ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ሥራን በሚገባ መረዳት ግን ከእነዚህ ይበልጥ አስፈላጊነት አለው። ምክንያቱም ከአማኙ ማንኛውም ዓይነት ኑሮና ልምምድ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ስለሆነ ነው። የአማኙ መቀደስ፥ መንፈሳዊ ማስተዋል፥ ዋስትና፥ አገልግሎት፥ ጸሎት እና አምልኮ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የሚመነጩ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ ስለሚያከናውነው ሥራ የሚናገረውን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሚገባ መረዳት መንፈሳዊ በረከትና ጥቅም የሚገኝበትን መንገድ ይከፍታል። በዚሁ መሠረት ይህን የሚያስተምሩ እና የሚሰብኩ ሁሉ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በጥልቅ ጥናትና ጥንቃቄ ማወጅ ይጠበቅባቸዋል።

መንፈሳዊ ስጦታዎችን በሚመለከት ቤተ ክርስቲያን ከመነሻው ጀምሮ በሁለት ተቃራኒ አስተሳሰቦች ተቸግራለች። ከመጀመሪያው፥ የቆሮንቶስ መልእክቶች እንደሚያሳዩት፥ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ያለ አግባብ መጠቀም ታይቶ ነበር። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደምናየው ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሚመለከት እጅግ በዛ ያሉና የተለያዩ ትምህርቶች ተከሥተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ ስጦታዎች የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በመወሰን ረገድ እና ለቤተ ክርስቲያን ፍሬያማነት ያላቸው አስፈላጊነት በቂ ትኩረት አልተሰጠውም። ተገቢና ተመጣጣኝ የሆነው ትምህርት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኝ ስለሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው በቀር ሌሎች ነገሮችን መጨመር፥ አስፈላጊ ጉዳዮችን ከመተው የተሻለ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ካሉ መገለጦች ውስጥ የአንዳንዶቹ እውነት ሌሎች ከሚያስገነዝቡት ልዩ መልእክት አንጻር አስፈላጊነታቸው የላቀ ነው። ከዚህ የተነሣ በመጀመሪያ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ባሕርይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ልንመረምር ይገባል። ይህ ወዲያውኑ እውነቱን ከሐሰት ይለይልናል። በሁለተኛ ደረጃ፥ በዘመነ ክርስትና ሁሉ በአገልግሎት ላይ ያሉትን ስጦታዎች ለማወቅ መመርመርና መተንተን አለብን። እነዚህ ስጦታዎች

ለሰዎች ያልተሰጡ ቢሆን ኖሮ፥ የዳኑ ሰዎች እንኳን እግዚአብሔርን ማገልገል ይሳናቸው ነበር። በሦስተኛ ደረጃ፥ በሐዋርያት ዘመን የነበሩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ከሐዋርያት ዘመን በኋላ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ መካተት አለመካተታቸውን ለመወሰን መጠናት አለባቸው። በሌላ አባባል፥ በጊዜያዊነት ለተለየ ዓላማ ለሐዋርያት የተሰጡ፥ እነርሱ ካለፉ በኋላ ግን የሌሉ አንዳንድ ስጦታዎች ነበሩን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መቻል አለብን።

2. የመንፈሳዊ ስጦታዎች አጠቃላይ ባሕርያት

መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ የሚያከናውነውን ሥራ በግልጥና በጥንቃቄ በተብራሩ ሁለት ክፍሎች ልንከፍለው እንችላለን። በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡ ስጦታዎች፥ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በተቀዳሚነት መጠናት አለባቸው። በሁለተኛ ደረጃ መንፈስ ቅዱስ አማኙን በመሞላት ረገድ ያለውን እውነት፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ ሁኔታዎቹና ውጤቶቹ መቅረብ አለባቸው። ሁለቱ አቅጣጫዎች በአንድ ላይ የእያንዳንዱን አማኝ ስፍራና ፍሬያማነት ይወስናሉ።

ይህን አሳብ ለመግለጥ አዲስ ኪዳን የተጠቀመባቸው የተለያዩ ቃላት ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ተፈጥሮ የሚናገሩት አላቸው። ስለ ስጦታዎች የሚናገረው ዋና የአዲስ ኪዳን ጥቅስ የሚገኘው በ1ኛ ቆሮንቶስ 12-14 ነው። በዚህ ክፍል የመግቢያ ጥቅስ ላይ 'ኒዩማቲኮን' ['pneumatikon'] የሚለው ቃል የመንፈስ ቅዱስ ነገሮች ይኸውም መንፈሳዊ ስጦታዎች በማለት ዋናውን አሳብ ገልጦት እናገኛለን። ቃሉ የሰውን ትኩረት፥ ምንጩ ወደሆነው መንፈስ ቅዱስ፥ እንዲሁም ወደ እነዚህ ስጦታዎች የሚስብ ነው። ከአገባቡ እንደምንረዳው ይህ ቃል 'ከሪስማቶን' ['charismaton'] በነጠላ ቁጥር ''የጸጋ ስጦታ'' የሚል ትርጉም አለው። የብዙው ቁጥሩ ከመንፈሳዊ ስጦታዎች አንጻር ሲታይ ደግሞ፥ ''አንዳንድ ክርስቲያኖች የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ማገልገል ይችሉ ዘንድ የሚሰጣቸው በተለምዶ ከሚታወቀው በላይ የሆነ ኃይል ነው። ይህን ኃይል ሊቀበሉ የቻሉት መንፈስ ቅዱስ በነፍሳቸው በሚሠራው መለኮታዊ ጸጋ ምክንያት ነው።'' ይህ ቃል ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች መሠረትና ባሕርያቸው ያስረዳል። መንፈሳዊ ስጦታዎች ከጸጋ የተነሣ የሚሰጡ፥ ለኛ የማይገቡ፥ እና ኃይልና ሥራቸው ሙሉ ለሙሉ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ናቸው። ይህ አሳብ 'ድዶታይ' ['didotai'] በሚለው ግሥ አማካይነት ይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶታል። ትርጉሙም መስጠት ማለት ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡7ቀ.)። እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች ከማንኛውም የተፈጥሮ ችሎታ የተለዩ ናቸው። በሁሉም አማኞች ከሚገኙት መንፈሳዊ ብቃቶች ጋርም

*መ*ምታታት የለባቸውም። መንፈሳዊ ስጦታዎች በባሕርያቸው ግላዊና ከእግዚአብሔር የሚመጡ ናቸው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በመንፈሳዊ ስጦታዎችና ስጦታው ባላቸው ሰዎች መካከል ልዩነቶች ይታዩ ይሆናል። ሁለቱ አሳቦች የማይነጣጠሉ ሲሆኑ መንፈሳዊ ስጦታዎች ለግለሰቦች የተሰጠ ሰማያዊ ኃይልን ያመለክታሉ። ስጦታ ስላላቸው ሰዎች ስንናገር ደግሞ አካሉ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ያገለግሉ ዘንድ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ በቤተ ክርስቲያን ስላስቀመጣቸው ሰዎች እያመለከትን ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12-14 ያለው ዋና ትምህርት ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚናገር ሲሆን፥ ኤፌሶን 4፡11 ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ስጦታዎች ስላላቸው ሰዎች የሚናገር ክፍል ነው። ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎችና ለቤተ ክርስቲያን ስለተሰጡ ሰዎች የሚናገሩት እነዚህ ሁለት አሳቦች በዚህ ክፍል ጠበቅ ባለ ሁኔታ ተለይተው አልቀረቡም። ይሁን እንጂ ስጦታ ያላቸው ሰዎች በእግዚአብሔር ወይም በክርስቶስ የሚሰጡ ሲሆኑ፥ መንፈሳዊ ስጦታዎች ግን የሦስተኛው የሥላሴ አካል ሥራ መሆናቸው ልብ መባል አለበት። የመንፈሳዊ ስጦታዎች ክልል በተለይ የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አካል ሲሆን፥ የአሁኑ ጥናታችን ቅድሚያ ትኩረትም በዚሁ ላይ የተመሠረተ ነው።

ለመንፈሳዊ ስጦታዎች ዋና ቃል የሆነው 'ካሪስማ' አዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ስፍራ ይገኛል (ሮሜ 1፡11፤ 5፡15፥ 16፤ 6፡23፤ 11፡29፤ 12፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡7፤ 7፡7፤ 12፡4፥ 9፥ 28፥ 30፥ 31፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡11፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡14፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡6፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡10)። አብዛኛዎቹ ጥቅሶች ለዚህ ጉዳይ ማዕከላዊ በሆነው ዋና ክፍል፥ 1ኛ ቆሮንቶስ 12-14 ላይ ጥቂት ነገርን ብቻ ይጨምራሉ። በጴጥሮስ መልእክት ከሚገኘው አንድ ጥቅስ ሌላ፥ የቀሩት በሙሉ ጳውሎስ መልእክት ውስጥ የሚገኙ ናቸው። እነዚህ ክፍሎች ውስጥ ከአንዳንድ አሳቦች ጋር የተጠቀሰውና 'ካሪስማ' [ˈcharismaˈ] የሚለው ቃል፥ ያልተለመዱ ኃይሎች በመንፈሳዊ ስጦታዎች የተገለጡ መሆናቸውን የሚያመለክት አይደለም። ለምሳሌ በሮሜ 5፡15-16 ያለው ስጦታ የጽድቅ ሲሆን፥ በሮሜ 6፡23 ያለው ደግሞ የዘላለም ሕይወት ስጦታ ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ያለው ሉዓላዊ ዕቅድ አንዳንዶች እንዲያገቡ ሌሎች ደግሞ እንዳያገቡ ሲሆን፥ ይህም በ1ኛ ቆሮንቶስ 7፡7 እንደ ስጦታ ተጠቅሷል። በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ሰዎች ጸሎት ምክንያት የሚመጡ በረከቶች በ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡11 እንደ ስጦታ ቀርበዋል። በሮሜ 1፡11 ጳውሎስ ለሮሜ ቤተ ክርስቲያን ስለተሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይናገራል። ይህም በእርሱ አገልግሎት ስለተገኙ ልዩ በረከቶች ወይም የተለየ መንፈሳዊ

ስጦታ ወይም ልዩ ኃይል ስለማግኘት የሚናገር ነው። እጆችን የመጫን ተግባር ትክክለኛ ትርጉም በእግዚአብሔር የተሰጡ ስጦታዎችን የማወቅ ጉዳይና በሙሉ ኃይል ተግባራዊ እንዲሆኑ የመለየት ጉዳይ ቢሆንም፥ ምናልባት ሐዋርያት በዚህ ሁኔታ ያልተለመደ ታላቅ ሥልጣን ሊኖራቸው እንደሚችል ለጢሞቴዎስ በተሰጠው መንፈሳዊ ስጦታ መመልከት እንችላለን (1ኛ ጢሞ. 4፡14፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡6)። ከሐዋርያት በኋላ ባለው ዘመን ግን መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለመስጠት ከእግዚአብሔር በቀር የሚችል አለ ብሎ የሚያሳምን አሳብ የለም። ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚናገሩት ሌሎች ክፍሎች (ሮሜ 12፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡7፤ 12፡4፥ 9፥ 28፥ 30፥ 31፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡10) የጸጋው መግለጫዎች እንዲሆኑ በእግዚአብሔር የተሰጡ ተአምራዊ ኃይሎችንና ግለሰቡ በክርስቶስ አካል ውስጥ ባለው ቦታ የሚያበረክተው አገልግሎት እንዲሳካ የሚያደርጉ ናቸው።

3. የመንፈሳዊ ስጦታዎች ልዩ ባሕርያት

መንፈሳዊ ስጦታዎች ለግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ የሚሰጣቸው ናቸው። ከዚህ አንጻር ስናያቸው ሰው ስለፈለገ የሚያገኛቸው አይደሉም። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ምእመናን ለአንዳንድ ስጦታዎች ከፍተኛ ስፍራ ሰጥተው በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ስጦታዎች ግን ችል በማለታቸው፥ ‘‘ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ’’ በማለት ጽፎላቸዋል (1ኛ ቆሮ. 12፡31)። በሌሎች መልእክቶቹ ውስጥ ግን መንፈሳዊ ስጦታን ስለመፈለግ የሚያበረታታ ነገር ሲጽፍ አናየውም። ስጦታዎች በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ላይ እንጂ በሰው መንፈሳዊነት ላይ አይደገፉም። አንድ ክርስቲያን ብዙ መንፈሳዊ ስጦታዎች ኖረውት ራሱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አያስገዛ ይሆናል፤ በሌላ በኩል ትንሽ መንፈሳዊ ስጦታ ኖሮት ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን ያስገዛ ክርስቲያን ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ራሳችንን የመስጠት ደረጃ የግድ የሚኖሩንን የመንፈሳዊ ስጦታዎች መጠን አይወስንም ወይም በሌላ አገላለጥ፥ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ የመስጠታችንን ደረጃ የመንፈሳዊ ስጦታዎቻችን መጠን አይወስነውም። እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት አባባል፥ ‘‘ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል’’ (1ኛ ቆሮ. 12፡11)። በእርግጥ ስጦታዎች ያሉት ሰው፥ በስጦታዎቹ በሚገባ ለመጠቀም፥ መንፈሳዊ ሕይወቱ በሚገባ መስተካከል አለበት። ነገር ግን መንፈሳዊነት በራሱ መንፈሳዊ ስጦታዎችን አያመጣም።

መንፈሳዊ ስጦታዎች ሰው በደኅንነቱ ጊዜ የሚሰጠው የጸጋ ስጦታ ነው ወይስ ከዳነ በኋላ የሚመጣ? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ይህን ጉዳይ በሚመለከት ግልጥ የሆነ መልስ አይሰጡም። ነገር

ግን በዳግም ልደት ጊዜ ከሚሆነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንጻርና በዚህም ሳቢያ በክርስቶስ አካል ውስጥ በሚሰጠው አዲስ ስፍራ ምክንያት፥ መንፈሳዊ ስጦታዎች ወዲያውኑ ባይታዩና ሰውዬው ሲለማመዳቸው ባንመለከትም እንኳ፥ የሚሰጡት በዳግም ልደት ጊዜ ነው ማለት ተገቢ ነው። በዚህ መሠረት አሰጣጣቸው በጥምቀት አፈጻጸም ውስጥ ባይጨመርም እንኳ መንፈሳዊ ስጦታዎች በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሥራ ውስጥ ሳይገኙ አይቀሩም። አንድ ሕፃን ባይገነዘበውም ተፈጥሯዊ ስጦታዎች በውስጡ እንዳሉ ሁሉ፥ መንፈሳዊ ስጦታዎችም ዳግም በተወለደ ሰው ሕይወትም ውስጥ እንዲሁ ናቸው። ስለዚህ በፍጥረታዊም ሆነ በመንፈሳዊ ክልል ስጦታዎችን በሚገባ የመጠቀም እና የማነልበት እንጂ ተጨማሪ ስጦታዎችን የማግኘት ጉዳይ አይደለም።

እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታዎች አሉት። እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት አባባል፥ "መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ጥቅም ይሰጠዋል" (1ኛ ቆሮ. 12፡7)፥ ደግሞም "ይህን ሁሉ ግን ያ አንድ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል" (1ኛ ቆሮ. 12፡11)። ክርስቲያኖች ሁሉ "የክርስቶስ አካላት ናቸው" (1ኛ ቆሮ. 12፡27)፤ "ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን" (ሮሜ 12፡5)። ምንም ያህል ስጦታው ትንሽ፥ ወይም ዝቅተኛ ስፍራ ላይ ይሁን እያንዳንዱ ክርስቲያን ለክርስቶስ አካል በጣም አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፥ "ነገር ግን ደካሞች የሚመስሉ የአካል ብልቶች ይልቁን የሚያስፈልጉ ናቸው" (1ኛ ቆሮ. 12፡22)። በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር መለኮታዊ ዓላማ ያለው ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችም ይህን ዓላማ ለማከናወን የሚሰጡ ናቸው። እያንዳንዱ ክርስቲያን እግዚአብሔር ባስታጠቀው ስጦታ መሣሪያነት አገልግሎቱን ይፈጽም ዘንድ ሊወጣው የሚገባ ኃላፊነት ነው በፊቱ የቀረበለት (1ኛ ጴጥ. 4፡10)።

ሰጦታዎች በጠቀሜታ ይለያያሉ። በክርስትና እምነት የእግዚአብሔር ልጅ ከመሆን የተነሣ ሁሉም እኩል የሆነ መብት ቢኖረውም፥ እያንዳንዱ ያለው ስጦታ ግን እኩል አይደለም። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡28 በተጻፈው መሠረት፥ "እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጓል።" በተለያዩ ስጦታዎች ባሕርይ መሠረት እንዳንዶቹ ከሌሎቹ ይልቅ በጣም አስፈላጊና ውጤታማ ናቸው። ጳውሎስ የትንቢት ስጦታን፥ በልሳን ከመናገር ስጦታ ጋር እንዲህ በማለት አነጻጽሮታል፥ "ሁላችሁ

በልሳኖች ልትናገሩ እወድ ነበር፥ ትንቢት ልትናገሩ ግን ከዚህ ይልቅ እወዳለሁ'' (1ኛ ቆሮ. 14፡5)፤ እንደገናም፥ ''ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ'' (1ኛ ቆሮ. 14፡19) ብሏል።

መንፈሳዊ ስጦታዎችን መጠቀም ያለብን በፍቅር ነው። 1ኛ ቆሮንቶስ 13 በሚሰጠው ምስክርነት መሠረት መንፈሳዊ ስጦታዎች ለታቀዱበት ጥቅም ይውሉ ዘንድ በፍቅር ልንገለገልባቸው ይገባል። መንፈሳዊ ስጦታዎች በራሳቸው ሰውን ትልቅ ክርስቲያን አያደርጉትም። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሆነው መለኮታዊ ፍቅር ቀስቃሽነት በተገቢው ከተጠቀምንባቸው ግን ውጤታማና ለእግዚአብሔር ክብር ፍሬ የሚያፈሩ ይሆናሉ።

አንዳንድ ስጦታዎች ጊዜያዊ ናቸው። ሌላው የመንፈሳዊ ስጦታዎች ገጽታ አንዳንድ ስጦታዎች የሚሰጡት ለተወሰነ ጊዜና ጥቅም ብቻ መሆኑ ነው። በአሁኑ ዘመን ባለች ቤተ ክርስቲያን በጥንትዋ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታዩ የነበሩ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሙላት አይታዩባትም። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ስጦታዎች የአሁኑ ስፍረ-ዘመንን ለይተው ያሳያሉ። የእያንዳንዱን ስጦታ ክፍፍል በሚመለከት በተናጠል በምናይበት ጊዜ ይህን በትኩረት እንመለከተዋለን።

የመንፈሳዊና የተፈጥሮ ስጦታዎች ንጽጽር። በጣም አስፈላጊ የሆነውን አጠቃላይ የመንፈሳዊ ስጦታ ገጽታ ለመመልከት በመንፈሳዊና በተፈጥሮ ስጦታዎች መካከል ያለውን ሁኔታ ማነጻጸር ይጠቅማል። እግዚአብሔር የተፈጥሮ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች የሚመርጥ ቢሆንም፥ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚገኙት በዳግም ልደት እንጂ በተፈጥሮ ልደት አለመሆኑ ግልጥ ነው። የመንፈሳዊ ስጦታዎች ብቃት በግለሰቦች ውስጥ ከደኅንነት በፊት የሚረጋገጥ አይደለም። መንፈሳዊ ስጦታዎች አዲሱን እንጂ አሮጌውን ፍጥረት አይመለከቱም። መንፈሳዊ ስጦታ የፍጥረታዊ ኃይል ተቀጥላ ወይም መስፋፋት ተደርጎ የሚታይ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር በሚጣጣም አኳኋን ግለሰቡን በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚያኖር ሰማያዊ ወይም ተአምራዊ ስጦታ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል ከፍተኛ ተፈጥሯዊ ችሎታ ካላቸው ይልቅ አነስተኛ ችሎታ ባላቸው ክርስቲያኖች ሲጠቀም በተደጋጋሚ ለማየት እንችላለን። እንግዲህ መንፈሳዊ ስጦታ በምቹ ሁኔታ ውስጥ እንኳ ቢሆን ሰው ሊያደርግ የሚችለውን የሚያሳይ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በጸጋው የሚያደርገውን የሚያመለክት ነው።

19

ቋሚ መንፈሳዊ ስጦታዎች

በአዲስ ኪዳን የተገለጡትን አሥራ ስድስት መንፈሳዊ ስጦታዎች በምንመረምርበት ጊዜ በስጦታዎቹ ባሕርያት መካከል ያለው ሰፊ ልዩነት ግልጥ ይሆንልናል። ባለንበት ስፍረ-ዘመን ስጦታው ያላቸው ሰዎች በግልጥ ሲለማመዱት እንደምንመለከተው፥ አንዳንዶቹን ስጦታዎች የዛሬይቱም ቤተ ክርስቲያን የምትለማመዳቸው እንደሆኑ እናያለን። ዛሬም አንዳንድ ሰዎች የሚከተሉት ስጦታዎች እንዳሏቸው የሚያጠራጥር አይደለም። 1. የማስተማር ስጦታ፥ 2. የመርዳት ወይም የማገልገል ስጦታ፥ 3. የአስተዳደር ወይም የአገዛዝ ስጦታ፥ 4. የወንጌላዊነት ስጦታ፥ 5. የመጋቢነት ስጦታ፥ 6. የማጽናናት ወይም የመምከር ስጦታ፥ 7. የመለገስ ወይም የመስጠት ስጦታ፥ 8. ምሕረት የማድረግ ስጦታ፥ 9. የእምነት ስጦታ።

ከነዚህ በተነጻጻሪነት፥ በተናጠል በምናጠናቸው ጊዜ ከግል ሁኔታቸው እንደምንረዳው አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎች በጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ቢሆኑም ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ግን የሚታዩ አይመስሉም። አንዳንድ የእምነት ክፍሎች እነዚህ ስጦታዎች አሁንም በመሥራት ላይ እንደሆኑ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ በስጦታዎቹ በመጠቀም ረገድ የሚታየው የጥራት ጉድለት የቅዱሳት መጻሕፍት ትእዛዛት ወደ ጎን የተባሉ ለመሆኑ ምስክር ነው። ጊዜያዊ ከነበሩት ከእነዚህ ስጦታዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

1. የሐዋርያነት ስጦታ፥ 2. የነቢይነት ስጦታ፥ 3. ተአምራትን የማድረግ ስጦታ፥ 4. የመፈወስ ስጦታ፥ 5. በልሳናት የመናገር ስጦታ፥ 6. በልሳናት የተነገሩትን የመተርጎም ስጦታ፥ 7. መናፍስትን የመለየት ስጦታ።

የዚህ ክፍል ዓላማ፥ መጀመሪያ በሁሉም ዘንድ በዚህ ዘመን እንደሚሠሩ ታውቆ ተቀባይነት ያላቸውን ስጦታዎች አከራካሪ ከሆኑት ለይቶ ማቅረብ ነው።

1. የማስተማር ስጦታ

ይህ በአዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ ከተጠቀሱ ስጦታዎች አንዱ ስለሆነ ዋና ዋና ከሚባሉ ስጦታዎች መካከል መቆጠር አለበት (ሮሜ 12፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ ኤፌ. 4፡11)። የማስተማር ስጦታ መሠረታዊ

ባሕርይ በሐዋርያት አገልግሎት ተገልጧል። ዋናው ተግባራቸው ከአረማዊነት ወደ ክርስቶስ የመጣውን አዲስ ክርስቲያን ማስተማር ነበር። የማስተማር ስጦታ ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ የተቀበለችውን እውነት ለመግለጥና ለማስረዳት የሚያበቃ ተአምራዊ ችሎታ ነበር። በዚህ ዓይነት እውነትን መረዳት ከመለኮታዊ አብርሆት ጋር የተያያዘ ቢሆንም አንድ ግን አይደለም። ብዙ ክርስቲያኖች ከመንፈስ ቅዱስ የተማሩ ናቸው፥ ነገር ግን የማስተማር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ያህል የማስተማር ችሎታ እንደሌላቸው ግልጥ ነው። አንድ ሰው የማስተማር ስጦታ ያለው መሆኑ ከሰው ይበልጥ ስለ እውነቶች ሁሉ እውቀት ያለው ሰው አያደርገውም። ተናጋሪው እንደ እግዚአብሔር አፍ ከሚቆጠርበት ከነቢይነት ስጦታም ጨርሶ የተለየ ነው። አስተማሪ እውነትን መረዳትና በመንፈስ ቅዱስ መማር አለበት። የማስተማር ስጦታ የሚያመለክተው በመጀመሪያ ሰው እውነትን ከሚቀበልበት መንገድ ይልቅ ያንን እውነት የመግለጥ እና ከሕይወት ጋር የሚያዛምድበትን ችሎታ ነው። በአሁኑ ጊዜ የማስተማር ስጦታ፥ ከመለኮት በተገኘ ችሎታ የእግዚአብሔርን ቃል የማስተላለፍ አገልግሎት ብቻ ነው።

2 . የመርዳት ወይም የማገልገል ስጦታ

በደረጃ የሚለያይ ቢሆንም እንኳ ክርስቲያኖች ሁሉ አላቸው ተብሎ የሚታመነው ስጦታ የማገልገል ወይም የመርዳት ስጦታ ነው (ሮሜ 12፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡28)። ለማገልገል ወይም በመንፈሳዊ ነገር ሌሎችን ለመርዳት የተወሰነ ችሎታ የሌለው ክርስቲያን አለ ብሎ ለመገመት በጣም ያስቸግራል። ለማስተማር እና ለመምራት ስጦታ ያለው ሰው ጥቂት ቢሆንም፥ ክርስቲያኖች ሁሉ መርዳትና ማገልገል ይችላሉ። ይህ ችሎታ በሁሉም ዘንድ ያለ ቢሆንም፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን በክርስቶስ አካል ውስጥ ባለው ስፍራ መሠረት እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ የሚለግሰው ስጦታ ነው። በስጦታዎች መካከል ያለው ልዩነት በርካታ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር በስጦታው ውስጥ ባለው የተለያየ ዓላማ መሠረት የተለያዩ ሰዎች በተለያየ መንገድ ያገለግሉበታል። መሪዎችዋ የቱንም ያህል ችሎታ ያላቸው ይሁኑ ከዚህ ስጦታ ውጪ ቤተ ክርስቲያን ተግባርዋን ልታከናውን አትችልም።

3. የአስተዳደር ስጦታ

ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ በእግዚአብሔር የሚሰጥ አመራር ነው። ከዚህ አንጻር እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ የአስተዳደር እና የአመራር ስጦታን ለጥቂቶች ሰጥቷል (ሮሜ 12፡8፤ 1ኛ

ቆሮ. 12፡28)። መንፈሳዊ ነገሮችን በሚመለከት ክርስቲያኖች ሁሉ ያላቸው ደረጃ እኩል እንደሆነ ግልጥ ነው፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር በቸርነቱ ለአንዳንዶች ከፍተኛ የሥልጣን ሰፍራ ሰጥቷል። የአስተዳደርና የአመራር ስጦታ ላላቸው ወገኖች ክርስቲያኖች ተገቢውን አክብሮት ሊሰጧቸውና በመታዘዝ ሊያከብሯቸው ይገባል (ዕብ. 13፡7)።

4. የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ

ወንጌልን ለማወጅ ከሚያስፈልጉ ስጦታዎች መካከል ቀዳሚው ወንጌል ሰባኪነት ነው (ኤፌ. 4፡11)። ከዚህ ለማየት እንደሚቻለው ይህ ስጦታ የወንጌልን መልእክት ለማያምኑ ሰዎች ውጤት ባለው መንገድ ለመስበክ አስፈላጊ መሆኑንና፥ በአንጻሩም ለዳኑ ሰዎች መመሪያ የመስጠት ተግባር ካካተተው የማስተማር ስጦታ ጋር ሊወዳደር እንደሚችል በግልጥ እንመለከታለን። ከልምምድ እንደሚታወቀው ወንጌልን ማወቅ ብቻ ውጤት ባለው መንገድ ቃሉን ለመስበክ አያስችልም። ለምሳሌ ሰዎች የማስተማር ስጦታ ኖሯቸው የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ አይኖራቸው ወይም የሰባኪነት ስጦታ ኖሯቸው የማስተማር ስጦታ አይኖራቸው ይሆናል። በሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት እንደታየው፥ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የማስተማርም ሆነ የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን ሰው ሁሉ በምንም መንገድ ይሁን በምን ወንጌልን ለጠፉ ነፍሳት ለመስበክ ተጠርቷል። ስለዚህ እንደ ጢሞቴዎስ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አማኝ ሁሉ መሥራት አለበት (2ኛ ጢሞ. 4፡5)። አንዳንድ ሰዎች ለወንጌል ሰባኪነት ልዩ ስጦታ ይኖራቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዓላማ ነው።

5. የእረኝነት ወይም የመጋቢነት ስጦታ

ለክርስቲያን መንጋ አጠቃላይ እንክብካቤ የማድረግ ሥራ የእረኛው ሲሆን፥ ይህን እውን ለማድረግ አንዳንዶች የእረኝነት ስጦታን ተቀብለዋል (ኤፌ. 4፡11)። ከርእሱ እንደምንረዳው፥ ይህ ሥራ እረኛ ለበጎቹ ከሚያደርገው እንክብካቤ ጋር ይገጻጸራል። 'ፖኢሚናስ' ['poimenas'] የሚለው የግሪክ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም እረኛ ማለት ነው። ስለዚህ እረኛ (መጋቢ) መንጋውን የሚመራ፥ የሚንከባከብ፥ የሚጠብቅና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚሰጥ ነው። በተፈጥሮአዊ አፈጻጸሙ እንደምናየው ይህን የእረኝነት ሥራ በተገቢ ሁኔታ ለመወጣት በቂ ችሎታ እንደሚጠይቅ ሁሉ፥ በመንፈሳዊው ዓለምም መጋቢ (እረኛ) ሥራውን ሁሉ በሚገባ ለማከናወን ሰማያዊ ስጦታ ያስፈልገዋል።

የእውነተኛ እረኛን (መጋቢ) ሥራ ሁኔታ በጥሩ አኳኋን ማስተዋል የሚቻለው በመጋቢነትና በማስተማር ሥራ መካከል ባለው የጠበቀ ግንኙነት ነው። ኤፌሶን 4፡11 እረኛን ከአስተማሪ ጋር የሚያያይዘው የመስተጻምር 'ካይ' ['kai'] ከተለመደው መስተጻምር 'ዴይ' ['de'] ይልቅ አንድ ሰው አስተማሪ ሳይሆን ጥሩ እረኛ (መጋቢ) ሊሆን እንደሚችል ያሳያል። በዚህ ውስጥ የምናየው መመሪያ እጅግ ታላቅ ነው። የማስተማር ስጦታ ያለው ሰው የእረኝነት (የመጋቢነት) ብቃቶች በሙሉ እንዲኖሩት ባያስፈልግም እውነተኛ እረኛ ግን መንጋውን ለማስተማር መቻሉ እጅግ አስፈላጊ ነው። መንጋውን መመገብ የማይችል እረኛ ይህ መጠሪያ ሊሰጠው ወይም በዚህ ስም ሊጠራ አይገባም። በመንፈሳዊ ክልል የመጋቢ የመጀመሪያ ሥራ መንጋውን በእግዚአብሔር ቃል መመገብ ነው። እውነተኛ እረኛ ከማደራጀት፥ ከማስተባበር እና ማኅበራዊ መሪ ከመሆን ሌላ ለማስተማርና ቃሉን ለመስበክ ሥራ ራሱን መስጠት አለበት።

6. የመምከር ስጦታ

መምከር የወንጌል ስብከት ሥራ ክፍል እንደመሆኑ መጠን ትልቅ ስፍራ አለው። ከማስተማር የሚለየው፥ ለተግባር የሚያነሣሣ ወይም የሚያበረታታ መሆኑ ነው። መምከር የስብከት አገልግሎት ተግባራዊ ክፍልም ነው። አንዳንዶች በዚህ ሥራ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተግባራዊ ሊያደርጉ በሚችሉበት ሁኔታ እንዲረዱት አድርጎ ክርስቲያኖችን የመምራት ልዩ ስጦታ ተሰጥቷቸዋል። ''መምከር'' (ሮሜ 12፡8) ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል 'ፓራካሎን' ['parakalon'] (ሮሜ 12፡8) የሚለው ሲሆን ከዚህ ትርጉም ሌላ ማበረታታት፥ ማጽናናት፥ ማረጋጋት፥ የሚሉትን ትርጉሞች ያጠቃልላል።

7. የመስጠት ስጦታ

የመስጠት ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ዘንድ የሚገኝ ነው። ይህ ስጦታ በሮሜ 12፡8 ከተገለጡት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ቢሆንም ከሌሎቹ ስጦታዎች ይልቅ ያለንን ንብረት በተገቢ ሁኔታ የመጠቀም ታማኝነትን ያመለክታል። ይህ ስጦታ በክርስቲያኖች ሁሉ እንደ ግለሰቡ የመስጠት አቅም የሚከናወን ሲሆን፥ በአንዳንድ ክርስቲያኖች ሕይወት ግን እንደ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ልዩ በሆነ የለጋስነት ባሕርይ ሲገለጥ ይታያል። ከዚህ የተነሣ አንዳንድ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ሰዎችና ሥራውን ለመርዳት ንብረታቸውን በፈቃደኝነትና በደስታ የመስጠት ልዩ ችሎታ እንዳላቸው ግልጥ ነው።

8. ምሕረት የማድረግ ስጦታ

በሮሜ ምዕራፍ 12 ከተዘረዘሩት መንፈሳዊ ስጦታዎች የመጨረሻው ምሕረት የማድረግ ነው (ሮሜ 12፡8)። የመስጠት ስጦታን በአእምሮአችን የምናስበው ስለ ድሆችና ጊዜያዊ የሆነ እርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው ችግረኞች ሲሆን፥ ይህ ስጦታ የተያያዘው ግን ከበሽተኞች፥ ወይም በሥቃይ ላይ ካሉ፥ ወይም በጣም መሠረታዊ የሆነ እርዳታ ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች ጋር ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት በደስታና በልግስና ምሕረት የማድረግ ችሎታ አላቸው። በግሪኩ 'ሂላሮቴቲ' [ʿhilaroteti'] የሚለው ቃል በስም መልክ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰው በዚህ ቦታ ብቻ ሲሆን፥ በውስጡ የአእምሮ ዝግጁነትንና በፍጥነት አንድ ነገር መፈጸምን ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስ በአንዳንድ ክርስቲያኖች ሕይወት የሚያኖረው መልካም እርምጃን ለመውሰድ የተዘጋጀ ቀና አስተሳሰብን ሲሆን፥ ክርስቲያኖች ይህ ስጦታ እንዳላቸው ልንመለከት እንችላለን።

9. የእምነት ስጦታ

በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10 በተዘረዘሩት መንፈሳዊ ስጦታዎችና የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መካከል የእምነት ስጦታም ተጠቅሷል። ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይልቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች የሆኑት ''የእውቀት ቃል'' እና ''የጥበብ ቃል'' በመንፈስ ቅዱስ እንደተሰጡ በተጠቀሰበት አንቀጽ የሚገኝ ነው። ይሁን እንጂ እምነት ለየት ባለ ክፍል ያለ የሚመስል ሲሆን፥ ምናልባትም አንዳንድ ክርስቲያኖች ፍጹም የላቀ እምነት እንዳላቸው የሚያሳይ ሳይሆን አይቀርም። ክርስቲያኖች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳላቸው ግልጥ ቢሆንም፥ እምነት ልክ እንደ ስጦታ ለአንዳንዶቹ ለየት ባለ ሁኔታ የሚሰጥ በረከት ነው። በሕይወት ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በመስጠት እና በመምራት በሚሠራው የእግዚአብሔር ኃይልና ፍቅር የመተማመንን ያህል የክርስቶስን አዳኝነት በማመን የሚገለጥ አይደለም። በዚህ መልኩ በአሁኑ የጸጋ ዘመን ያለ የመንፈሳዊ ስጦታዎች ቋሚ ባሕርይ ነው።

20

ጊዜያዊ መንፈሳዊ ስጦታዎች

1. ተአምራት በአሁኑ ጊዜ ባለው የእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ ያላቸው ስፍራ

በጊዜያችን ያለውን ክርስቲያናዊ ልምምድና በሐዋርያት ዘመን የነበረውን ስንመለከት አንዳንድ ተነጻጻሪ ነገሮች መኖራቸው ግልጥ ነው።

የተአምራት እየቀነሱ መሄድ። ወንጌል የማይለወጥ መሆኑና እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን ሰዎች በሚመለከት የሚጠቀምበት አብዛኛው መንገድ ባለንበት ስፍረ-ዘመንም የቀጠለ ሲሆን፥ አንዳንድ ነገሮች ግን ከሐዋርያትና ከነርሱ ትውልድ ማለፍ በኋላ ጠፍተዋል። ይህን ለማብራራትም የተለያዩ መግለጫዎች ተሰጥተዋል። ቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ ቀድሞ ከነበረችበት ስፍራ ማፈግፈግዋና ከዚህ ቀደም የነበራትን መንፈሳዊ ኃይል ለማሳየት ብቃቱ ያነሣት እንደሆነ ጥርጥር የለውም። ይሁን እንጂ በየዘመናቱ እውነተኞች ሆነው የሚኖሩ ታማኝ ቅዱሳን ስላሉ፥ እግዚአብሔር ራሱን በሙላት ለነርሱ ያለማቋረጥ ሊገልጥላቸው ይችላል። ቢሆንም ለሐዋርያት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት እጅግ ቅርበት ያላቸው እንኳ ሐዋርያት ያደርጉት የነበረውን ሲያደርጉ አይታዩም።

የተአምራት ዓላማ። አንዳንድ ስጦታዎች የተገለጡበት ሁኔታ የታየው በሐዋርያት ዘመን ብቻ ነው ለሚለው አሳብ ጥሩ መግለጫ የምናገኘው፥ እግዚአብሔር በሐዋርያት ዘመን የነበረውን ዓላማ በምናጠናበት ጊዜ ነው። በሐዋርያት ዘመን እግዚአብሔር (አንዳንድ ጊዜ የሚሰጡት ጥቅም አስፈላጊነት በማይጠየቅበት ሁኔታ እንኳ) በርካታ ተአምራትን ማድረግ ያስደስተው ነበር። ተአምራት የተፈጸሙባቸው ዘመናት ሁሉ ለእግዚአብሔር ነቢያት እውነተኛነት ልዩ ምስክርነት የሚያስፈልግባቸው ጊዜያት ነበሩ።

የመጽሐፍ ቅዱስ የተአምራት ታሪክ። ታላላቅና የታወቁ ተአምራት የተመዘገቡባቸው ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ዘመናት አሉ፡- 1. የሙሴ ዘመን፥ 2. የኤልያስ እና የኤልሳዕ ዘመን፥ 3. የክርስቶስና የሐዋርያት ዘመን።

በነዚህ ሦስት ዘመናት ሁሉ የእግዚአብሔርን መልእክት እውነተኛነት የሚያረጋግጡ መረጃዎች አስፈላጊ ነበሩ። የሙሴን ሁኔታ ስንመለከት ያደረጋቸው ተአምራት ያስፈለጉት፥ ሕዝቡ እንደ ነቢይና እንደ መሪ እንዲቀበሉት፥ መልእክቱም ከእግዚአብሔር እንደሆነ እንዲያውቁ

ነበር። ውድቀትና ከሀደት በዝቶ በነበረበት በኤልያስና በኤልሳዕ ዘመን ደግሞ፥ ሕዝቡን ለመመለስ በተለይም ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ካህናትን አገልግሎት የሚተካና ተግባራቸውን በሚገባ ላከናወኑ ሥራ ያልተለመደ ዓይነት የእግዚአብሔር ኃይል ምስክርነት ያስፈልግ ነበር። በክርስቶስ ጊዜ ደግሞ ስለ ሰብዕናው ምስክርነት ለመስጠትና መሢሕነቱም ተአማኒ እንዲሆን ለማድረግ ተአምራት በተለየ ሁኔታ ያስፈልጉ ነበር። በሐዋርያት ዘመንም ወንጌላቸው ከእግዚአብሔር እንደሆነ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነበር። ልዩ የተአምራት መገለጥ የእያንዳንዱ ትውልድ የተለመደ ገጽታ አልነበረም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማራመድ ከርሱ ዕቅድ ጋር የተጣመረ ነበር።

ከአዲስ ኪዳን መሟላት ጋር ያለው ግንኙነት። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከተሟሉና ለእግዚአብሔር እውነተኛ የሆኑ ወገኖች ሁሉ አዲስ ኪዳንን ከተቀበሉ በኋላ፥ ያልተለመዱ ታላላቅ ተአምራት አስፈላጊነት አብቅቷል። የአሁኑ ዘመን የወንጌል ሰባኪ የሚሰብከውን ወንጌል እውነተኛነት ለማሳየት የመፈወስ ወይም በልሳን የመናገር ውጫዊ ምልክት አያስፈልገውም። የተጻፈው ቃል በራሱ ይናገራል፥ ደግሞም ሰውን በመንፈስ ቅዱስ ወቅሶ በማሳመን ኃይል ይደገፋል። ይህ የእግዚአብሔርን ተአምራት የመሥራት ኃይል የመጠየቅ ወይም የመፈታተን ጉዳይ ሳይሆን፥ ልክ በሐዋርያት ዘመን በነበረው የመለኮታዊ ኃይል መግለጫ መንገድ፥ እግዚአብሔር አሁንም የመሥራት ዓላማ ያለውና የሌለው መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ነው። አንዳንድ የእምነት ክፍሎች በየትኛውም ዘመን ያሉ ሰዎች በእምነትና በእውነት ቢፈልጉት በሐዋርያት ዘመን የተገለጠው የእግዚአብሔር ኃይል ያልተለመዱ ገጽታዎች ሊታዩ ይችላሉ የሚለውን አሳብ አጥብቀው ይዘዋል። ነገር ግን ፍጹም የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው ብለን በምንገምታቸው ባለፉት ትውልድ በነበሩ ሰዎች ሕይወት እንኳ ለጊዜው የተሰጡ ናቸው ብለን ያቀረብናቸው መንፈሳዊ ስጦታዎች የሌሏቸው እንደነበሩ ግልጥ ወይም የተረጋገጠ ነው። ደግሞም በዚህ ዘመን እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች አሉን የሚሉ አንዳንድ ሰዎች በተለያዩ አህጉራት ዜና እንደሚሰማው፥ በአጠቃላይ ለመጽሐፍ ቅዱስ፥ ለክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባርና ለከፍተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸው አመለካከት እጅግ ደካማና ለዘብተኛ መሆኑ በግልጥ ታይቷል። የእነዚህ የእምነት ክፍሎች ታሪክ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ከመጠን በላይ መፈለግ ወዳልተቀደሰና ወደ በርካታ የተበላሸ ነገር የሚመራ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው።

ቅዱሳት መጻሕፍት ከልምምዶች ሊነጻጸሩ። ከባሕርዩ የተነሣ የክርስትናን ልምምድ በጠቅላላው ለማዳረስ የሚቻለው የለም። መሠረታዊ

የእምነት ትምህርትን በተለያዩ ልምምዶች ላይ መሥርተው እውነትነታቸውን ለማሳየት የሚጥሩ ሰዎች ሲያጋጥሙ ሁልጊዜ የመጨረሻው መመዘኛ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ይላሉ? የሚል መሆን አለበት። ለማጠቃለል ልምምዶች ከፊል መመዘኛዎች ቢሆኑም፥ የመጨረሻው ሥልጣን ተደርጎ መወሰድ ያለበት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ልምምድ ሁልጊዜ ለስሕተት የሚያጋልጡ ሁለት አደገኛ መሠረቶች አሉት፡- 1. በይዘትና በመለኮታዊ ጅማሬው ልምምድን በተሳሳተ መንገድ መረዳት፥ 2. የልምምድን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ትርጉም በተሳሳተ መንገድ ማጠቃለል።

ስለዚህ በአንድ በኩል የመለኮት ጅማሬ ያለው ነው የምንለው ልምምድ፥ የሥነ-ልቦና ጉዳይ ወይም ከዚህ ከባሰ የሰይጣን የማጭበርበሪያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሥራ እንደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተደርጎ እንደተወሰደ ሁሉ፥ ትክክለኛና እውነተኛ ልምምድን በተሳሳተ መንገድ መረዳት ወይም መሰየም ይቻላል። እውነትን የሚፈልግ ክርስቲያን፥ በማናቸውም ሁኔታ እውነትን ከሚያጣምም እምነት በመራቅ ለእውነተኛ ትምህርት በመንፈስ ቅዱስ ላይ ታምኖና ተደግፎ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለበት።

2. የሐዋርያነት ስጦታ

የሐዋርያነት አገልግሎት መጠን። 'አፖስቶሎስ' ['apostolos'] ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣው ሐዋርያ የሚለው ቃል ትርጉም ''ተወካይ፥ መልእክተኛ፥ ወይም በትእዛዝ የተላከ'' ማለት ነው። ታየር የተባለ ሰው እንደተናገረው፥ ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን 78 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፥ ከእነዚህ መካከል 38ቱ የሚገኙት በሉቃስ ወንጌል፥ በሐዋርያት ሥራና በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ነው። ቃሉ በመጀመሪያ ሥራ ላይ ውሎ የምናገኘው፥ አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት የእግዚአብሔርን መንግሥት መቅረብ ይሰብኩ ዘንድ በተላኩ ጊዜ ነው (ማቴ. 10፡2፤ ማር. 3፡14፤ 6፡30፤ ሉቃስ 6፡13)። ወደ ሐዋርያነት አገልግሎት ከተጠሩት መካከል ጳውሎስ (ሮሜ 1፡1፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡1 ወዘተ.)፥ በርናባስ (ሐዋ. 14፡14፤ ገላ. 2፡9ን ይመልከቱ)፥ ማትያስ (ሐዋ. 1፡25-26) ፤ እና ምናልባት ያዕቆብ (1ኛ ቆሮ. 15፡7፤ ገላ. 1፡19)፤ አጵሎስ (1ኛ ቆሮ. 4፡6-9) ይገኙበታል። አንዳንዶች ደግሞ ከእነዚህ ሌላ ስልዋኖስና ጢሞቴዎስ (1ኛ ተሰ. 1፡1፤ 2፡6)፥ አፍሮዲጡ (ፊልጵ. 2፡25)፥ ስማቸው ያልተጠቀሰ ወንድማማቾች (2ኛ ቆሮ. 8፡23)፥ አንዲራኒቆንና ዩልያንን (ሮሜ 16፡7) ይጨምራሉ።

ይህ ቃል ለተለያዩ ጉዳዮች ጥቅም ላይ የዋለ በመሆኑ፥ አንዳንድ ሰዎች ሐዋርያ በተለይ ለሚሲዮናዊነት ሥራ በእግዚአብሔር የተጠራ

ማንኛውም ሰው ነው የሚል አቋም ይዘዋል። ጄ. ሲ. ላምበርት [J. C. Lambert] የተባለ የሥነ-መለኮት ሊቅ ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ፥ ‘‘ሐዋርያነት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለየና የተወሰነ ሥልጣንና ኃላፊነት ለያዘ ሰው የሚሰጥ ስም አይደለም። ነገር ግን አንድና ታላቅ ማለትም ውጤቱ የነቢይነት አገልግሎት የሆነ ተግባር መፈጸም ለሚችሉ በርካታ ሰዎች የተሰጠ ስም ነው’’ (1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ ኤፌ. 4፡11) ብሏል። ይበልጥ የተለመደው አቋም ግን፥ በመጀመሪያ በዚህ ስም በቀጥታ ሊጠሩ የሚገባቸው፥ የክርስቶስ ኢየሱስ ትንሣኤ ምስክሮች የሆኑና፥ በክርስቶስ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ለዚህ ዓላማ በወጉ የተጠሩት ሲሆኑ፥ ለእግዚአብሔር ምስክር ይሆኑ ዘንድ በአጠቃላይ የተጠሩትንም ሊያመለክት ይችላል። በማንኛውም ረገድ ቢሆን በሐዋርያት ዘመን የነበረ የወንጌል አገልጋይ ሁሉ ሐዋርያ ተብሎ እንዳልተጠራ ሁሉ፥ እንደ ላምበርት አስተሳሰብ ሐዋርያት ሁሉ ሚሲዮናውያን ነበሩ ብሎ ማረጋገጥም የማይቻል ነው።

ለሐዋርያነት አገልግሎት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች። ሲ. አይ. ስኮፊልድ የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ፥ ወደ አዲስ ኪዳን ሐዋርያነት ለመግባት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎችን ግሩም በሆነ መንገድ አሳጥሮ አቅርቧቸዋል።

‘‘1. ሐዋርያት የተመረጡት በቀጥታ በጌታ ወይም እንደ በርናባስ አመራረጥ በመንፈስ ቅዱስ ነበር (ማቴ. 10፡1፥ 2፤ ማር. 3፡13፥ 14፤ ሉቃስ 6፡13፤ ሐዋ. 9፡6፥ 15፤ 13፡2፤ 22፡10፥ 14፥ 15፤ ሮሜ 1፡11)፤

‘‘2. የአገልግሎታቸው መለኮታዊ የሹመት ማስረጃ ይሆኑ ዘንድ የምልክት ስጦታዎች ማለትም ተአምራትን የማድረግ ኃይል ተሰጣቸው (ማቴ. 10፡1፤ ሐዋ. 5፡15-16፤ 16፡16-18፤ 28፡8-9)፤

‘‘3. ከዳዊት መንግሥት ወራሽነት ጋር ካላቸው ግንኙነት ይህን መንግሥት ለእስራኤል ብቻ ማወጅ (ማቴ. 10፡5-6)፥ መንግሥቱ በደጅ እንደሆነ መናገር (ማቴ. 4፡17)፥ የመንግሥቱን ኃይል መግለጥ (ማቴ. 10፡7-8) ነበር፤

‘‘4. የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ፥ በማቴዎስ 13 እንደተገለጠው ክርስቲያን ለተባለ ሁሉ ጠቃሚ እንዲሆን፥ ከሐዋርያት አንዱ ለሆነው ለጴጥሮስ ተሰጥቷል (ማቴ. 16፡19)።

‘‘5. ከሚመጣው መንግሥት ጋር ያላቸው የወደፊት ግንኙነት በአሥራ ሁለቱ ነገዶች ላይ ፈራጅ መሆን ነው (ማቴ. 19፡28)፤

‘‘6. አይሁድ ክርስቶስንና ክርስቶስ ሊመሠርተው የመጣውን የዳዊት መንግሥት ባለመቀበላቸው፥ ሐዋርያት ከዚህ ቀደም ያልታወቀ

ምስጢርን ማለት ‘‘ቤተ ክርስቲያን’’ መግለጥ ጀመሩ (ማቴ. 16፡18፤ ኤፌ. 3፡1-12)። ለሐዋርያት አገልግሎት አዲስ ምልክት ተሰጠ፤ ይህም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነበር። ለእያንዳንዱ አይሁዳዊ ክርስቲያን አዲስ ኃይል ማለትም መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶታል (ሐዋ. 2፡1-4)። በመካከላቸው የተፈጠረው አዲስ ግንኙነት ለአዲሱ ቤተ መቅደስ መሠረት ነበር (ኤፌ. 2፡20-22)። የነበራቸውም አገልግሎት መልካሙን የምስራች ማለትም ስለተሰቀለውና ስለተነሣው ጌታ ለአይሁድም ሆነ ለአሕዛብ መስበክ ነበር።

‘‘7. ለሐዋርያነት በጣም አስፈላጊ ከሆኑ መመዘኛዎች አንዱ የትንሣኤው የዓይን ምስክር መሆን ነበር’’ (ሐዋ. 1፡22፤ 1ኛ ቆሮ. 9፡1)።

ሐዋርያነት ሰጦታ ነው። ከሐዋርያነት የሹመት ባሕርይ ልዩ መሆን አንጻር ሲታይ በአዲስ ኪዳን እንደ ስጦታ ቀርቧል (1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ ኤፌ. 4፡11)። እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ስጦታዎች ዋናው መሆኑን ለመግለጥ፥ ‘‘እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶችን አስቀድሞ ሐዋርያትን’’ (1ኛ ቆሮ. 12፡28) በሚለው ቃል ቀርቧል። ሐዋርያት ከነቢያት፥ ከአስተማሪዎች፥ ከተአምራት አድራጊዎች፥ ወዘተ. (1ኛ ቆሮ. 12፡28) ተለይተው ቀርበዋል። ስለዚህ ሐዋርያነት የተሰጠው ውሱን ከሆነው የቃሉ ትርጉም የተነሣ በቀጥታ ሐዋርያት ብለን ለምንጠራቸው ሰዎች ነው። ከላይ ያመለከትነውን ጥቅስ ስኮፊልድ እንዳመለከተው፥ ከጳንጠቆስጤ ዕለት በፊት የነበረው የሐዋርያነት አገልግሎት ከዚያ በኋላ ከነበረው የተለየ መሆን አለበት። ከጳንጠቆስጤ ዕለት በፊት የነበረው የሐዋርያት አገልግሎት የእግዚአብሔር መንግሥት በደጅ መሆኑን ማወጅ ነበር። ከዚያ በኋላ ወዲያውኑ የደኅንነትን ወንጌል የሚያስተዋውቁ መሪዎች፥ መለኮታዊ ሥልጣንና ኃላፊነት፥ ደግሞም ለትምህርታቸው መሠረት የሚሆን ልዩ መገለጥ የተሰጣቸው ሆኑ። የነቢይነትና ተአምራትን የማድረግ ስጦታ ያላቸው ሁሉ ሐዋርያት ባይሆኑም፥ ሐዋርያት ሁሉ ግን አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ሁለት ስጦታዎች ነበራቸው (2ኛ ቆሮ. 12፡12)። የሐዋርያነት አገልግሎት በመጀመሪያው የክርስትና ክፍለ-ዘመን ያበቃለት ጉዳይ ነው፤ ምክንያቱም ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት በኋላ እንዴት እንደሚቀጥል የተገለጠ ነገር የለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥም ከሐዋርያት ጋር ተስተካክሎ ሊቆም የሚችል አይገኝም። እነዚህ ሐዋርያት ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በዓይን ካዩት መካከል መመረጣቸው በኋለኛው ዘመን የሐዋርያነት ጥሪ ሊሰጣቸው የሚችሉ ሰዎች የመኖራቸውን ዕድል እንዲያከትም አድርጎታል። ከዚህም የተነሣ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያነትን አገልግሎት ለመቀጠል የምታደርገው ሙከራ በተደጋጋሚ ተቃውሞ ገጥሞታል።

3. የነቢይነት ስጦታ

የነቢይነት ስጦታ መጠን። በመንፈሳዊ ስጦታዎች ዝርዝር ውስጥ በሁለተኛነት ደረጃ የሚቀርበው የነቢይነት ስጦታ ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡28)። የዚህ ስጦታ አስፈላጊነትና ዋናነት በሌሎች ክፍሎች በእርግጠኝነት መጠቀሱን ያረጋግጥልናል (ሮሜ 12፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡10፤ 14፡1-40)። በሐዋርያት ዘመን ይህ ስጦታ የነበራቸው በርካታ ሰዎች ነበሩ። የነቢይነት ስጦታ በእርግጥ የነበረው አጋቦስ፥ ሊመጣ ስላለው ረሀብ አመለከተ (ሐዋ. 11፡27-28)። ደግሞም ጳውሎስን ሊደርስበት ስላለው መከራ በማመልከት አስጠነቀቀው (ሐዋ. 21፡10-11)። በርናባስ፥ ስምዖን፥ ሉክዩስ፥ ምናሔና ጳውሎስ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት "መምህራንና ነቢያት" መካከል እንደሆኑ ተጠቅሷል (ሐዋ. 13፡1)። የወንጌላዊው ፊልጶስ አራት ሴት ልጆች የነቢይነት ስጦታ ነበራቸው (ሐዋ. 21፡9)። ይህም ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን፥ በአዲስ ኪዳንም የነቢይነት ስጦታ ለወንዶች ብቻ የተሰጠ እንዳልነበረ ያመለክታል። በጳውሎስ ውስጥ የምናየው የእግዚአብሔር አመራር፥ የነቢይነት ማስተዋል እንደነበረው በግልጥ ያስረዳናል (ሐዋ. 16፡6ቀ.፤ 18፡9-10፤ 22፡17-21፤ 27፡23-24)። ይሁዳና ሲላስም ነቢያት እንደነበሩ ተነግሯል (ሐዋ. 15፡32)። ሐዋርያት ሁሉ የነቢይነት ስጦታ ነበራቸው ቢባል እውነት ይመስላል።

የአዲስ ኪዳን ነቢይ ባሕርያት። አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ነቢያት፥ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ባሕርይ ወስደዋል። ሁሉም የሚናገሩት ለእግዚአብሔር ነበር። ሁሉም በጎጢአት ላይ ስለሚመጣ ፍርድ ተናግረዋል። መልእክታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ አስተላልፈዋል። ሁሉም ስለ ጊዜያቸውም ሆነ ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች ተናግረዋል። ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ነቢያት የብሔራዊ መሪነት ወይም የጀግና ባሕርይ የነበራቸው ሲሆን፥ መልእክታቸውን ያስተላለፉት በተለይ ለእስራኤል ሕዝብ ነበር። የአዲስ ኪዳን ነቢያት ግን፥ ምንም ዓይነት የብሔርተኝነት ባሕርይ አናይባቸውም። መልእክታቸው ግላዊና ለእያንዳንዱ ሰው የሚሆን ሆኖ፥ እርሱ ካልገለጠው በቀር የማይታወቀውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይገልጡ ነበር። ይህም በጓላ በጽሑፍ በቀረልን አዲስ ኪዳን ውስጥ ያገኘነውን ነገር ያሟላል።

በነቢይነት ስጦታ ውስጥ ያሉ ነገሮች። በነቢይነት ስጦታ ውስጥ የሚያስፈልጉ ሦስት ነገሮች አሉ፡-

1. ነቢዩ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክቱን በአንድ በተለየ መገለጥ መቀበል አለበት። መልእክቱም በቀጥታ ከእግዚአብሔር የተላለፈና ከዚያ በፊት ያልታወቀ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ የተገለጠ

አይደለም። እንዲሁም መልእክቱ ለነቢዩ ሳይሆን እግዚአብሔር ላሰባቸው ሕዝቦች ጥቅም ነው፤

2. አንድ ነቢይ የተገለጠለትን መልእክት ለማስተላለፍ፥ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተሰጠው ቃል መለኮታዊ ምሪት የሚያስፈልገውን ያህል፥ ነቢይም መለኮታዊ ምሪት ያስፈልገዋል፤

3. የሚያስተላልፈው መልእክት በውስጡ የእግዚአብሔር ሥልጣን ሊኖርበት ይገባል።

የነቢዩ መልእክት የግድ ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች መሆን እንደሌለበት በተደጋጋሚ ታይቷል። አሁን ስለሚሆኑ ነገሮች ወይም ስለ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ትርጓሜ ሊሆን ይችላል። ይህ አለመሆኑ ግን መልእክቱ ከእግዚአብሔር የመጣ መሆኑን የሚሽር አይደለም። አማኝ በዘመናችን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ማስተማሩ የነቢይነት ስጦታ ማረጋገጫ አይደለም። አንድ ነቢይ እውነተኛ ከሆነ፥ የራሱን የአእምሮ ሥራ ውጤት ሳይሆን ከስሕተት ነጻ የሆነና ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነን መገለጥ ማቅረብ አለበት። ነቢያት ጴጥሮስ አመለካከቱን ከሕግ አክራሪነት ጋር ለማመሳሰል በሞከረ ጊዜ እንዳደረገው ስሕተት ቢሠሩም እንኳን፥ መልእክታቸው ግን ከስሕተት ፍጹም ነጻ መሆን አለበት። በመሆኑም በአዲስ ኪዳን ስሕተትን አስተምሮ እንደ እውነተኛ ነቢይ የተቆጠረ ማንም የለም።

በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የነቢይነት ሰጦታ አሰፈላጊነት። በሐዋርያት ዘመን የነቢይነት አገልግሎት አስፈላጊ እንደነበረ ግልጥ ነው። በተለምዶ የአይሁድ እምነት ከነበረው ወደ ክርስትና ለመምጣት ሰፊ የሆነ የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ሽግግር የሚጠይቅ ነበረ። አዲስ ኪዳን የተጻፈው ወዲያውኑ አልነበረም። ለእግዚአብሔር ፈቃድ ዳግም መገለጥ ሥልጣን ያለው ምንጭ የግድ አስፈላጊ ነበር። በተለምዶ የሚታመነውን የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሥርዓት ለማዘጋጀትም ምሪት አስፈልጓል። ይህን ለማሟላት እግዚአብሔር ሰማያዊ የሆነ የነቢይነት ስጦታ ያላቸውን ነቢያት ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ። አብዛኛዎቹ የመጀመሪያው ዘመን ክርስቲያኖች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እስኪሟሉ ድረስ በሕይወት ባይኖሩም፥ በእነርሱ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ለነቢያት አገልግሎት በቂ ትኩረትን መስጠቷ ተገቢ ሆኗል።

ነቢይነት ለማነጽ፥ ለመምከርና ለማጽናናት (1ኛ ቆሮ. 14፡3) የሚጠቅም ታላቅ ስጦታ እንደሆነ በግልጥ ቀርቧል። በልሳን ከመናገር ስጦታ ጋር ሲወዳደር፥ የማስተማርና የነቢይነት ስጦታን መጠቀም እጅግ የላቀ መሆኑ ተገልጧል። "ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር አልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ" (1ኛ ቆሮ. 14፡19)። በተለይ አማኞችን ለማስተማር

ትንቢት ልዩ ጥቅም ያለው መሆኑ ተገልጧል (1ኛ ቆሮ. 14፡22)። በቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ውስጥ ሥርዓት ለማክበር ነቢያት ተራ በተራ መናገር እንዳለባቸው ጳውሎስ ያመለክታል፥ ‘‘ሁሉም እንዲማሩ፥ ሁሉም እንዲመክሩ፥ ሁላችሁ በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ’’ (1ኛ ቆሮ. 14፡31)። ‘‘የጥበብ ቃል’’ እና ‘‘የእውቀት ቃል’’ ከነቢያት ስጦታ ጋር የተያያዙ ሳይሆኑ አይቀሩም (1ኛ ቆሮ. 12፡8)።

የነቢይነት ስጦታ ጊዜያዊ ባሕርይ። በአሁኑ ጊዜ ሰዎች የማስተማር፥ የመምከርና ወንጌልን የመስበክ ስጦታ እንዳላቸው ብንስማማም የነቢይነት ስጦታ ግን ማንም እንደሌለው መቀበል ተገቢ ውሳኔ ነው። አዲስ ኪዳን ሙሉ በሙሉ ከተጻፈ በኋላ ሌላ መገለጥ እንደማያስፈልግ ተረጋግጧል። የእግዚአብሔር ዓላማ ራሱን በቃሉ ውስጥ ብቻ መግለጥ ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤት ነው ብሎ ሌላ መጽሐፍ መጨመር እንደማይቻል ሁሉ፥ የነቢይነት ስጦታም በዚህ ዘመን አለ ብሎ መናገር አይቻልም። በ1ኛ ቆሮንቶስ 13፡8 መሠረት ፍቅር ለዘላለም የሚኖር መሆኑ ሲገለጥ፥ ትንቢት ግን የሚሻር እንደሆነ ተገልጧል። በራእይ 22፡18-19 በዚህ መጽሐፍ ላይ አንዳች ነገር የሚጨምሩ ፍርድ እንዳለባቸው በማስገንዘብ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል።

4. ተአምራት የማድረግ ስጦታ

ተአምራት ማድረግ ሉነስተኛው ስጦታ ነው። ተአምራት የማድረግ ስጦታ ከአናሳ ስጦታዎች የመጀመሪያው ሆኖ ቀርቧል (1ኛ ቆሮ. 12፡28)። ሐዋርያነት፥ ነቢይነትና አስተማሪነት በቅድሚያ የሚያስፈልጉ ስጦታዎች ሲሆኑ፥ ተአምራትን ማድረግና ሌሎች ስጦታዎች በሁለተኛነት ቀርበዋል። ጸሐፊው የተጠቀመበት ‘‘ቀጥሎም’’ የሚለው ቃል ቅደም ተከተል፥ ሆነ ተብሎ የተደረገ መሆኑን ያሳያል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እነዚህ ነገሮች ሲጽፍ፥ መጀመሪያ መሆን ያለበትን ነገር መጀመሪያ ገልጧል። ተአምራትን የሚገልጠው ‘ዱናሜስ’ የተሰኘው ቃል የተፈጥሮን ኃይል ማለት፥ አንድ ነገር በራሱ ተፈጥሮ ውስጥ የሚኖረውን ኃይል የሚያመለክት ነው። ከዚህ አኳብ ተአምራትን ለማድረግ የተለየ የኃይል አጠቃቀምን ማውጣት ይቻላል። የተአምራትን ባሕርይና ዓላማ ለመግለጥ ከሌሎች ቃላት ጋር በቅንጅት የቀረበ ቢሆንም፥ ክርስቶስ ያደረጋቸውን ተአምራት ለመግለጥ የዋለና የተለመደ ቃል ነው (ማር. 5፡30፤ ሉቃስ 5፡17፤ 6፡19 ፤ 8፡46 ወዘተ.)። በ2ኛ ቆሮንቶስ 12፡12፥ ተአምራትን ማድረግ ከምልክት፥ ከድንቅ ነገር፥ እና ከታላላቅ ሥራዎች ጋር በአንድ ላይ ተዳብሎ ‘‘የሐዋርያነት ምልክት’’ ሆኖ ቀርቧል። በዚህ መሠረት

ተአምራትን ማድረግ፥ የሐዋርያነትና የነቢይነትን አገልግሎት ሥልጣን ለማሳወቅ የሚያስችል መለኮታዊ ኃይል መግለጫ ነው።

ተአምራትን የማድረግ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን መጨረሻ ላይ ኣብቅቷል። አስቀድመን እንደተመለከትነው ይህ ያልተለመደ የመለኮታዊ ኃይል መግለጥ ተግባር፥ እግዚአብሔር ለሐዋርያት ዘመን ብቻ ያቀደው ዓላማ ነበር። ስለዚህ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተጻፈው ቃል ከተሰጠን በኋላ ተአምራትን የማድረግ ሥራ አክትሟል። ተአምራትን የማድረግ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን ብቻ የተወሰነ ነበር በሚለው አቋም ላይ ብዙ ጊዜ ተቃውሞ የሚነሣው፥ ተአምራትን ሁሉ ተአምራት ከማድረግ ስጦታ ጋር በማያያዝ ከሚሰጥ አደናጋሪ አሳብ የተነሣ ነው። የሐዋርያትን ዘመን ልዩ የሚያደርገው፥ አንዳንድ ሰዎች በፈለጉ ጊዜ በክርስቶስ ስም ተአምራት የማድረግ ኃይል ስለነበራቸው ነው። አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ ተአምራትን የማድረግ ስጦታ ነበራቸው።

ሰጦታው ያበቃ ቢሆንም ተአምራት ቀጥለዋል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አልፎ አልፎ ተአምራት መታየታቸው እግዚአብሔር ለጸሎት መልስ በመስጠት ታላላቅ ሥራዎችን የሚፈጽም መሆኑን ያመለክታል። ነገር ግን ከሐዋርያት ዘመን በኋላ የታመሙትን ሁሉ ለመፈወስ፥ ሙታንን ለማስነሣት፥ በሌላ አነጋገር ያልተለመዱ ታላላቅ ተአምራትን የማድረግ ስጦታ ለማንም አልተሰጠም። የሐዋርያነትና የነቢይነት ስጦታ እንዳበቃ ሁሉ፥ የምልክቶች ስጦታም አብቅቷል። ለስጦታዎቹ ማብቃት ምክንያት የሆነው ጌታ ቃሉን በጽሑፍ ለኛ በማስቀረቱ ነው። ክርስቲያን አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ድንቅ ሥራን እንዲሠራ ለመለመን ይችላል። እግዚአብሔር ለጸሎት መልስ ይሰጣል። እግዚአብሔር ከፈለገ አሁንም ቢሆን በሽተኞችን ሊፈውስም ሆነ ሙታንን ሊያስነሣ ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ለሰዎች ፈቃድ የማይገዙ ወይም እንደ መንፈሳዊ ስጦታ የማይሰጡ፥ ሉዓላዊና ግላዊ ስጦታዎች ናቸው። ስለዚህ ምንም እንኳ ተአምራትን የማድረግ ስጦታዎች በአሁኑ ጊዜ የእግዚአብሔር እቅድ ባይሆኑም፥ የእርሱ ተአምራትን የማድረግ ኃይል ግን ጨርሶ ያልተቋረጠና የሚሠራ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

5. የፈውስ ስጦታ

ፈውስን እንደ ስጦታ የሚያቀርብ ብቸኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚገኘው በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡9፥ 28፥ 30 ነው። በሦስቱም ቦታዎች ፈውስ የገባው ከስጦታዎች ጋር ነው። ፈውስ በተለይ የእግዚአብሔር ኃይል ከሚገለጥባቸው ተአምራት አንዱ ገጽታ ነው። ተአምራትን ማድረግ ግን ከፈውስ በተለየ መንገድ ይከናወናል። ለምሳሌ ኤልማስ በተአምራት

ማድረግ ስጦታ አማካይነት ከመፈወስ ይልቅ እንዲታወር ሆኗል (ሐዋ. 13፡11)። የፈውስ ስጦታ በተለይ አካላዊ ጤንነትን ከመመለስ ጋር የተያያዘ ነው። ተአምራትን እንደማድረግ ስጦታ ለታወጀው እውነት ምስክር ይሆን ዘንድ የቆመ ሲሆን፥ ስጦታነቱ ከሐዋርያት ማለፍ ጋር አብቅቷል። ተአምራትን ማድረግ ያለ ስጦታ ሊኖር እንደቻለ ሁሉ፥ ያለ ፈውስ ስጦታም ፈውስ ሊኖር ይችላል። የፈውስ ስጦታ የቀረ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር በእምነት የሚደረግን ጸሎት በመመለስ ረገድ ፈውስ ሊሰጥ ይችላል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ጸሎት አድርገው በሚያገኙት ፈውስ ያልተለመደ ልምምድ ሊኖራቸው ቢችልም፥ ፈውስ እንደ ስጦታ ለሰዎች የመሰጠቱና በተሰጣቸው ሰዎች ፈቃድ የመፈጸሙ ጉዳይ ግን ያከተመ ይመስላል። በሁሉም ረገድ ፈውስ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የሚሰጥ ነው። በአሁኑ ጊዜ አንድ ሰው ምንም እንኳን በጸሎት ብርቱ፥ በእምነትም የተሞላ ቢሆን የፈውስ ስጦታ ሁሌ በእርሱ ኖሮ ይፈውሳል ማለት አንችልም።

6. በልሳናት የመናገር ስጦታ

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጠቃላይ በልሳናት የመናገር ስጦታን ያህል በተከታታይ ውዝግብ ያስነሣ መንፈሳዊ ስጦታ የለም። በዚህ ስጦታ ባሕርይ ምክንያት ለተፈጠሩ ችግሮች ሁሉ በርካታ መፍትሔ የተሰጠ ቢሆንም፥ መፍትሔዎቹ የራሳቸው ድክመት ይታይባቸዋል። ይሁን እንጂ ሰፊና የተሟላ ገለጣ መስጠት የሚቻለው በዚሁ ርእስ ላይ ብቻ በተጻፈ ሥራ ቢሆንም፥ በዚህ ውስን ጥናት ችግሮቹን መግለጥ፥ በልሳናት የመናገርን ባሕርይ መመርመርና ይህ ስጦታ ጊዜያዊ የመሆኑን አሳብ አቅርቦ ለማጠቃለል ይቻላል።

ችግሩን መግለጥ። በልሳናት የመናገር ስጦታን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ለመመርመር፥ በመጀመሪያ ልንመለከተው የሚገባ ነገር የጳንጠቆስጤ ታሪክ ነው (ሐዋ. 2፡1-13)። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚገልጡት ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ያገኙት፥ በዚያ ተሰብስበው የነበሩት ሁሉ "መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር" (ሐዋ. 2፡4) በሚለው መሠረት ነው። ሁኔታው የሚሉትን እስኪያጡ ድረስ በዚያ የነበሩትንና በጌታ ያላመኑትን ሰዎች አስደንቋቸው ነበር። እያንዳንዱ በገዛ ቋንቋው ሲናገር ሰሙ። የእግዚአብሔር አስደናቂ ሥራ በልሳኖቻቸው ተገለጠ (ሐዋ. 2፡8-11)። አንዳንዶች ይህ የስካር ነገር ነው አሉ። ጴጥሮስ ግን "ደግሞ በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ" የሚለውን ከኢዩኤል 2፡29 ጠቅሶ አስቀድሞ የተተነበየ ነው ሲል አሳባቸውን

በመቃወም ያ ሁኔታ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ምልክት መሆኑን ተናገረ (ሐዋ. 2፡18)።

በሌሎች ቋንቋዎች መናገራቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል። ይህ አሳብ ግልጥ በሆነ ዓረፍተ ነገር ከመነገሩም በላይ፥ የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሰዎች እንደሰሟቸውና የሚሉትም ነገር እንደገባቸው መጠቀሱ የተረጋገጠ ነው። ተፈጥሮአዊ የሆኑ ማብራሪያዎች ሁሉ መወገድ አለባቸው። በልሳን መናገር፥ በጰንጠቆስጤ ዕለት ለተገለጠው የእግዚአብሔር ኃይል ምልክት ይሆን ዘንድ የታሰበ የእግዚአብሔር ተአምራዊ ሥራ መሆኑ ግልጥ ነው።

በሐዋርያት ሥራ 10፡46፥ የቆርኔሌዎስንና የቤተሰቡን መለወጥ በሚመለከት በተጻፈው ታሪክ ላይ በልሳናት የመናገር ነገር ለሁለተኛ ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን። ጴጥሮስ የወንጌሉን ቃል በሚናገርበት ጊዜ በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፥ "በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና" (ሐዋ. 10፡46)። የወንጌልን በአሕዛብ ዘንድ መስፋትና መድረስ ድርጊቱን ከጰንጠቆስጤ ጋር የሚያያዝ ይመስል በልሳን መናገር ተደግሞ እናገኛለን። ጴጥሮስ ያን ታሪካዊ ድርጊት በመጥቀስ ይህንኑ አመልክቷል፦ "ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ደግሞ መጀመሪያ እንደወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው" (ሐዋ. 11፡15)።

ሦስተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሐዋርያት ሥራ 19፡6 ነው። ጳውሎስ የጸጋን ወንጌል ጨርሰው ያልሰሙና በዚህም ምክንያት በእምነት ወደ ክርስቶስ ዘወር ያላሉ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት መኖራቸውን አወቀ። እነርሱ ከተጠመቁ በኋላ፥ "ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ" (ሐዋ. 19፡6)። በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ (12፡10፥ 28፥ 30፤ 14፡1-40) ከተጠቀሱት ሌላ በልሳናት ስለመናገር የሚገልጡ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ከፍ ብለን ያየናቸው ሦስቱ ናቸው። በሐዋርያት ሥራ የሚገኙት እነዚህ ጥቅሶች በልሳን ስለመናገር ስጦታ አያብራሩም። ወይም ደግሞ በእነዚህ ሦስት ክፍሎች በልሳን ስለመናገራቸው የተጠቀሰላቸው ሰዎች በሌላ ጊዜ ደግመው በልሳን ስለመናገራቸው የተጠቀሰ ነገር የለም። ከ1ኛ ቆሮንቶስ ውጭ ስለ መሠረታዊው የእምነት ትምህርት በየትኛውም መልእክት መግለጫ አልተሰጠም። በዚሁ መሠረት የስጦታውን ባሕርይ ለማጥናት የሚያስችል ፍንጭ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ የተፈጸሙ ድርጊቶችን በማጥናት ሲሆን፥ የአጠቃቀሙን ደንብና መጠን ደግሞ በ1ኛ ቆሮንቶስ መሠረት መወሰን ይቻላል።

ለችግሩ የተለያዩ መፍትሔዎች። መሠረታዊውን የእምነት ትምህርት በሚመለከት አጠቃላይ ወደሆነ ውሳኔ ከመድረሳችን በፊት፥ ችግሩን በተለያዩ ቀላል መንገዶች ለመፍታት የሚቻለው ሁሉ መደረግ አለበት። የለዘብተኛ (ሊበራል) ሥነ-መለኮት ሊቃውንት ይህን ችግር ለማቃለል የሞከሩት፥ የሐዋርያት ሥራ የተጻፈበትን ጊዜ ዘግየት በማድረግና፥ እነዚህ ክፍሎች በመጀመሪያው የሐዋርያት ሥራ ያልነበሩና በኋላ የተጨመሩ ናቸው ከሚል ፅንሰ-አሳብ በመጀመር ነው። ይህ ፅንሰ-አሳብ ምኞታዊ ለው ከማለት ውጪ አሳቡን ለመደገፍ ምንም ዓይነት የጠለቀ ማስረጃ ለማቅረብ እንደማይቻል እርግጥ ነው።

በሁሉም የሥነ-መለኮት ትምህርት ክፍሎች በሚገኙ አንዳንድ ጸሐፊዎች ዘንድ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 እና በ1ኛ ቆሮንቶስ ምንባቦች መካከል ልዩነት አለ የማለት አዝማሚያ ይታያል። አንዳንዶች በሐዋርያት ሥራ 2 ያለው በልሳን የመናገር ጉዳይ፥ ባዕድ በሆኑ በሌሎች ሰዎች ቋንቋዎች መናገርን የሚጨምርና የቋንቋዎቹ ተናጋሪዎችም የሚረዱት ዓይነት ቋንቋዎች እንደነበሩ ያምናሉ። በ1ኛ ቆሮንቶስ የተጻፈው ግን በልሳናት መናገር የሰው ቋንቋን ሳይጠቀሙ ውስጣዊ የሆነ ፍላጎት የሚገለጥበትና ከልሳናቱ የሚወጣው እንግዳ የሆነ ድምፅ፥ የመተርጎም ስጦታ ባላቸው ሰዎች የሚተረጎም መሆኑን ነው። በዚህ መሠረት በ1ኛ ቆሮንቶስ የተጠቀሰውን በልሳን የመናገር ስጦታ ታየር እንዲህ በማለት ይገልጠዋል፦ ‘‘በታላቅ ደስታ ተመስጠው የማስተዋል ኃይልና ሕሊናቸውን መቆጣጠር የማይችሉ፥ አዲስ በሆነ ቋንቋ መንፈሳዊ ስሜታቸውን የሚገልጡ፥ የሌሎችን አስተሳሰብ ለመምራትም ሆነ ለመሳብ የማይችሉ ሰዎች ልምምድ ነው’’ (ሐዋ. 10፡46፤ 19፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡30፤ 13፡1፤ 14፡2፥ 4-6፥ 13፥ 18፥ 23፥ 27፥ 39)።

አንዳንድ ጸሐፊዎች ዘመናዊውን በልሳን የመናገር እንቅስቃሴ* ለመቃወም በሚያደርጉት ሙከራ፥ በልሳን የመናገር ስጦታን የሚያሳንሱ ሲሆን፥ በተናጋሪው የማይታወቅ ቋንቋ የመኖሩን እውነታ ይክዳሉ። እንደ ታየር ያሉ አንዳንዶች ይህን አሳብ በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ያለውን አሳብ ብቻ እንደሚደግፍ ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ያለውን ክፍል በማከል፥ አንዳንድ ባዕድ ቋንቋዎችን እና ከውስጥ ስሜት የተነሣ በመፈንደቅ፥ ትርጉም የማይሰጥ ድምፅን (ቃላትን) ማስወጣትን የሚጨምር ንግግር ነው ይላሉ። በልሳን መናገርን በሰዎች እንደሚነገር እንደ ማንኛውም ቋንቋ መሆኑን የማይገልጥ ማንኛውም ዓይነት አመለካከት፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈሳዊ ስጦታ ከሚገልጡት ጋር

* በምእራፍ 15 መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የአሳታሚውን መግለጫ ይመልከቱ።

ለማስማማት የማይችል አስቸጋሪ አሳብ ነው። መንፈሳዊ ስጦታ በባሕርዩ እውን እና መለኮታዊ በመሆኑ ተፈጥሮአዊ ማብራሪያ አያስፈልገውም። በልሳን መናገርም በአማኞች ዘንድ እንደ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ሆኖ ተቀባይነት ያገኘ ነገር ነው። አንዳንዶች እንደሚያደርጉት፥ በልሳን መናገርን ከንቱ መዘላበድ ከሚታይበት ከአረማውያን አምልኮና ከጠንቋዮች አሠራር ጋር ማያያዝ፥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትክክለኛነት የሚያፋልስ ስለሆነ ልንቃወመው ይገባል።

በልሳን ስለመናገር የተጻፉ ጥቅሶች በሙሉ በመሠረቱ አንድ ናቸው የሚለውን ለዘብ ያለ የተቃውሞ አመለካከት የሚገልጠው የታየር አቋም የተመሠረተው፥ ስለ ስጦታው ባለ የግንዛቤ ጉድለት ላይ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያቶች አሉ። በሐዋርያት ሥራ 11፡15 በግልጥ እንደተጻፈው በቂሣርያ የታየው በልሳን የመናገር ክሥተት፥ በጰንጠቆስጤ ዕለት ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለት ጊዜ የተፈጸሙት እነዚህ ድርጊቶች በመሠረቱ በሐዋርያት ሥራ 19 ከተፈጸመው ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ስለዚህ በጥቅሱ የማናየውን ልዩነት ለመፍጠር መሞከር እውነትነት የሌለውና ትክክለኛ ያልሆነ አተረጓጎም ነው።

በልሳን መናገርን በሚመለከት በሐዋርያት ሥራና በ1ኛ ቆሮንቶስ ያሉት ቃላት ተመሳሳይ መሆን በመካከላቸው ልዩነት መኖሩን ለመግለጥ የሚደረገውን ሙከራ መሠረት ያሳጣዋል። በሁሉም ክፍሎች ልዩ ልዩ ሰዋሰዋዊ አገባቦች 'ላሌዮ' [ʻlaleoʼ] እና 'ግሎሳ' [ʻglossaʼ] የሚሉ ተመሳሳይ የግሪክ ቃላት ናቸው የተጠቀሱት። በግሪክኛውም ሆነ በክፍሉ በቀረበው ዓረፍተ ነገር ምንም ልዩነት አናገኝባቸውም።

አንዳንዶች ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ያለውን ችግር በመተው፥ ልሳንን በሚመለከት በ1ኛ ቆሮንቶስ የምናገኘው ችግር በቆሮንቶስ ሰዎች ዘንድ ያልታወቀውን የዕብራይስጥ ቋንቋ የሚመለከት ነው ይላሉ። ይህን አሳብ በሚመለከት በክፍሉ የምናገኘው ምንም ማስረጃ ካለመኖሩም ሌላ ለተናጋሪዎቹ በተፈጥሮአዊ መንገድ የሚታወቅ ቋንቋ መንፈሳዊ ስጦታ ተብሎ የሚሰየምበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም።

ለችግሩ መፍትሔ ለማስገኘት የሚጠቅም መመሪያ። በልሳን የመናገርን መሠረታዊ ትምህርት ለመለየት ልንጠቀምበት የሚገባ ብቸኛውና ትክክለኛው መመሪያ፥ ስለዚህ ጉዳይ የተጠቀሱት ክፍሎች በሙሉ ስለ አንድ ስጦታ የሚናገሩ መሆናቸውን አምኖ መቀበል ነው። በአጠቃቀሱ ላይ አንዳንድ ልዩነቶች ቢኖሩም፥ በልሳን የመናገር ስጦታ በግልጥ ልንረዳው የምንችለው አሳብ ብቻ ሳይሆን እውነታ መሆኑን፥ ተፈጥሮአዊ ሳይሆን መለኮታዊ መሆኑን፥ የሥነ-ልቦና ወይም የትምህርት

ጉዳይ ሳይሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑንና በተለይም ለማያምኑ ሰዎች የተሰጠ ምልክት መሆኑን በሁሉም ረገድ ልንረዳ ይገባል።

በልሳን የመናገር ስጦታ ለሐዋርያት ጊዜ ብቻ የተሰጠ ጊዜያዊ ስጦታ ወይም ቋሚና በዘመናት ሁሉ የሚሠራ መሆኑን መወሰን የሚቻለው፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ ባለው ቃል ላይ በመመሥረት ብቻ ነው። በልሳን የመናገር ስጦታ እውነተኛ ባሕርይ አስቀድሞ ከተወሰነ ችግሩን ቀላል ያደርገዋል። የተገለጡትን ማስረጃዎች ሁሉ መመርመር፥ በልሳን የመናገር ስጦታ ላለንበት ዘመን በሙሉ የተለመደ ያለመሆኑን እውነት የሚያረጋግጥ ነው።

በሐዋርያት ሥራ የተገለጠው ልሳን ጠቃሚነቱ እንደ ምልክት ማገልገሉ ነው። ቀደም ብለን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተመለከትናቸው ሦስት ጥቅሶች (2፡4፤ 10፡46፤ 19፡6)፥ ድርጊቶቹን በአንድነት የሚያጣምር የቃላት አንድነት እንዳላቸው ያሳያሉ። ቅዱሳት መጻሕፍትና የሰሙትም ሰዎች እንዳረጋገጡት፥ የተጠቀሱት ሁሉ እውነት ናቸው። ሁሉም በባሕርይ መለኮታዊ ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ናቸው። በሦስቱም ጊዜ የሆኑት ነገሮች፥ የምልክትነት ባሕርያቸው እንደተገለጠ መጠቆም መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

አማኞች አሁን የሚጠቀሙበት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሙላት የተጀመረው፥ በጰንጠቆስጤ ዕለት ነው። የዳግም መወለድ እውነታ ሙሉ በሙሉ ግልጥ ከመሆኑ ባሻገር አማኞች ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆኑ፤ እስከ መዋጀት ቀን ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ታተሙ፤ በመንፈስ ቅዱስም ተሞሉ። የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በጰንጠቆስጤ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሥራ ጀመረች። የመንፈስ ቅዱስን ሙላት የሚያሳዩ አንዳንድ ውጫዊ መግለጫዎች ያስፈልጉ ነበር። በልሳን የመናገር ችሎታ እግዚአብሔር በቸርነቱ በውስጣቸው እንደሚሠራ ለማረጋገጥና ወንጌልን ለዓለም ሁሉ የማድረስን የመጨረሻ ዓላማ ለማሳየት ሲባል ተሰጠ።

ለቆርኔሌዎስ ወንጌልን በመስበክ ሥራ ውስጥ ጠቃሚ የሆነ ሌላ እርምጃ ተወሰደ፥ ምልክትም አስፈለገ። ቀደም ሲል ወንጌል ለአሕዛብ የተሰበከ ቢሆንም፥ አሁን ግን አይሁድ በሚቀበሉበት ሁኔታ አሕዛብም ሊቀበሉ እንደሚችሉ ለማሳየት ተገለጠ። እኩል መብት እንዳላቸውም ታወቀ። ይህ እውነት ለጴጥሮስም ግልጥ ሆኗል፦ እግዚአብሔር በጰንጠቆስጤ ዕለት እንዳደረገው በልሳን መናገርን የሚያጠቃልለውን መለኮታዊ ኃይሉን አሳየ። ምልክት አስፈልጎ ነበር፥ እግዚአብሔር ሰጠ።

ግልጥ ማረጋገጫ ያስፈለገበትን ሦስተኛ ሁኔታ የምናየው ደግሞ በሐዋርያት ሥራ 19፡6 ነው። ምልክቱ ያስፈለገው የማያምኑ ሰዎችን ለማሳመን ብቻ ሳይሆን፥ አማኞችም መጥምቁ ዮሐንስ የተናገረለትን አውቀው እምነታቸው እንዲጸና ለማድረግ ነበር።

ይህ በልሳን የመናገር ልምምድ ተደግሟል ወይ የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። እስካሁን ባየናቸው ሦስት ክፍሎች በልሳን የመናገር ጉዳይ የተፈጸመው በመጀመሪያው የክርስትና ልምምድ ወቅት ብቻ መሆኑን ነው።* የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ተመሳሳይ ስለሆነ ሌላ ልምምድ የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም።

ከዚህ እውነታ እንደምንረዳው፥ በልሳን መናገር በምንም አኳኋን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊነት ወይም የደኅንነት ምልክት አልነበረም። በእውነተኛ መልኩ የመገኘቱ ጉዳይ ለደኅንነት እርግጠኝነት ምስክር ነበር፥ ቢሆንም የግድ አስፈላጊ አልነበረም። የሚታየውም አልፎ አልፎ ነበር። የአረማውያን ባዕድ አምልኮና ክፋት በበዛበት ሁኔታ ውስጥ በነበረችው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ እግዚአብሔር ይህንን ስጦታ አትረፍርፎ መሰጠቱ ግልጥ ነው። ለደኅንነት መነሻ ምልክት በሆነውና በክርስትና ልምምድ ውስጥ ቋሚ በሆነው የልሳን ስጦታ መካከል ልዩነት ሊኖር ይችላል። በሐዋርያት ሥራ 11፡17፥ የቆርኔሌዎስ ልምምድ እንደ ስጦታ ተገልጧል። በሁለቱ መካከል ልዩነት ቢኖርም በመጽሐፍ ቅዱስ ግን አልተጠቀሰም።

በልሳን መናገር በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ። በ1ኛ ቆሮንቶስ እንደተገለጠው፥ ስጦታዎችን ለመተንተን አስቸጋሪ የሆነው፥ መልእክቱ በተጻፈላት የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ በነበረው መንፈሳዊ ችግር ምክንያት ነው። በማኅኛውም ረገድ በጣም ጠቃሚ ስለሆኑ ስጦታዎች ሁሉ የተሰጠው ገለጣ የተሟላ ነው። ይህ ጉዳይ የተነሣው፥ መንፈሳዊ ስጦታዎችና አማኞችም በክርስቶስ አካል ውስጥ ስላላቸው ስፍራ በተነገረበት ክፍል ነው። በልሳን ስለ መናገር የተጠቀሰው በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡10፥ 28 ሲሆን፥ በመንፈሳዊ ስጦታዎች ዝርዝር ውስጥ የመጨረሻው ነው። የስጦታዎቹ ዝርዝር ቅደም ተከተል በአስፈላጊነታቸው መጠን የተደረገ ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ስጦታዎች ከመንፈስ ቅዱስ በተገኘ ፍቅር አገልግሎት ላይ ካልዋሉ፥ ዋጋ የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ

---

* ሀ. በጰንጠቆስጤ ዕለት በክርስቶስ ያመኑ አይሁዶች ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጨምረው ነበር። ለ. ከአሥር ጊዜ በኋላ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ወንጌል ደርሶ አሕዛብ ተቀብለውታል። ሐ. የመጥምቁ ዮሐንስ ተከታዮች ከሦስት ዓመት በፊት የመጥምቁን ትምህርት ማለት "ንስሐ ግቡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና" የሚለውን ተቀብለው የነበሩ ቢሆንም ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 19፡6 እስካስረዳቸው ድረስ ሙሉ ለሙሉ እውነቱን አልተገነዘቡም ነበር።

እጅግ አስፈላጊ መገለጥ ተሰጥቷል። በልሳን የመናገር ጉዳይ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። በመጀመሪያ በልሳን የመናገር ስጦታ በፍቅር ካልሆነ ‘‘እንደሚጮኽ ነሀስ ወይም እንደሚኼኼ ጽናጽል’’ መሆኑ የተገለጠ ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ ልሳን ከትንቢትና ከእውቀት ጋር ጊዜያዊ መሆኑ ተጠቅሷል። ‘‘ልሳኖችም ቢሆኑ ይቀራሉ’’ (ቁ. 8)። ቀጥሎ ያለው ምዕራፍ በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በልሳን ስለመናገርና በትንቢት አጠቃቀም ረገድ ስላለው ችግር የሚያወሳ ነው።

ምዕራፍ 14 ውስጥ በርካታ ጠቃሚ ነጥቦች ተጠቅሰዋል። በመጀመሪያ፥ በልሳን መናገር የማነጽ፥ የመምከርና የማጽናናት ጠቀሜታ ካለው ከትንቢት ያነሰ መሆኑ ተጠቅሷል (1ኛ ቆሮ. 14፡1-12)። ከትንቢት ያነሰበት ምክንያት ማንም ሊረዳው አለመቻሉ ነው። በዚሁ ክፍል ትንሽ ዝቅ ብሎ፥ ጳውሎስ አልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ሰው ሊገባውና ሊረዳው የሚችል አምስት ቃላት፥ መናገር እንደሚሻል ተናግሯል (1ኛ ቆሮ. 14፡19)።

ሁለተኛ፥ ተርጓሚ እስከሌለ ድረስ በልሳን የመናገርን ስጦታ በጉባዔ መጠቀም ተገቢ እንዳልሆነ ተጽፏል (1ኛ ቆሮ. 14፡13-28)። የቆሮንቶስ ሰዎች ልሳንን በግል የጸሎት ጊዜያቸው ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ የተጠቀሰ ቢሆንም፥ ጳውሎስ ሰው ሊረዳው በሚችልበት መንገድ መጸለይ እንደሚሻል ገልጧል (1ኛ ቆሮ. 14፡15)።

ሦስተኛ፥ ልሳን የተሰጠው ለማያምኑ ሰዎች ምልክት ይሆን ዘንድ እንጂ፥ በቅድሚያ አማኞችን ለማነጽ አይደለም (1ኛ ቆሮ. 14፡21-22)። በልሳን መናገር በሥርዓት እስካልተከናወነ ድረስ የማሳመኑ ተግባር ከግብ አይደርስም (ቁ. 23)። በዚህም ቢሆን ትንቢት የማያምነውን ሰው ወደ እምነትና አምልኮ ስለሚመራ የበለጠ ስፍራ አለው (ቁ. 24-25)።

አራተኛ፥ በልሳን መናገርና የትንቢት ስጦታ ቤተ ክርስቲያንን በማነጽ ረገድ ብቻ በሥርዓት ጥቅም ላይ መዋል ይገባዋል (ቁ. 26-38)። በአንድ ጉባዔ በልሳን መናገር የሚፈቀድላቸው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ብቻ ሲሆኑ ያውም ተርጓሚ ካለ ነው (ቁ. 27-28)። ሴቶች በማኅበር በልሳንም ሆነ ትንቢት መናገር አልተፈቀደላቸውም (ቁ. 34-35)። ‘‘ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን’’ (ቁ. 40) በማለት ይመክራቸዋል። እነዚህ ሕግጋት በትክክል በሥራ ላይ ቢውሉ በልሳን መናገርን አስመልክቶ በዘመናችን ያለውንና በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሠረተውን ጎጂ አሠራር ያስወግዳሉ።

አምስተኛ፥ በልሳን መናገር መከልከል የሌለበት ቢሆንም፥ የነቢይነት ስጦታ ደግሞ የተሻለና አጥብቀን ልንፈልገው የሚገባ ነው (ቁ. 39)።

በልሳን መናገር ጊዜያዊ ሰጦታ ነበር። ማንም ቢሆን በልሳን መናገር በአሁኑ ጊዜ ሊሆን የማይችል ነው ብሎ በማስረጃ ሊያረጋግጥ አይችልም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አሁን ላለው ዓላማ ስጦታው የማያስፈልግ መሆኑን ማሳየት ይቻላል። ዘመናዊውን በልሳን የመናገር ስጦታ ለማረጋገጥ የሚገለጥ ሁሉም ባይሆን አብዛኛው ክሥተት ሥነ-ልቦናዊ ወይም የአጋንንት ተግባር መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት አለ። ከሁሉ የተሻለው ማስረጃ በልሳን መናገርን አስመልክቶ ባለው ታሪክ* ውስጥ ከልክ ያለፈና አብሮት ይገለጥ የነበረ ክፉ ባሕርይ ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ እውነተኛ ክርስቲያኖችም በልሳናት እንናገራለን ከሚሉት ጋር መቀላቀላቸው የሁሉንም ልምምድ መመርመር የማይቻል አድርጎታል። በልሳን የመናገር እንቅስቃሴ ክፋት መነሻው በልሳን ከመናገር እምነት አይደለም። ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ስጦታዎች የሚያስተምሩትንና ስለአጠቃቀማቸው የተሰጠውን ትምህርት ቸል ከማለትና በዘመናዊው የእምነት ትምህርት በልሳን ስለመናገር የሚሰጠው የተሳሳተ ትምህርት ነው።

በልሳን የመናገር ስጦታ ጊዜያዊ እንደሆነ የሚያረጋግጡ አራት የተለያዩ የመከራከሪያ አሳቦች አሉ። በመጀመሪያ፥ በልሳን የመናገር ስጦታ የተጀመረው በጳንጠቆስጤ ዕለት ነው። ከዚህ ታሪካዊ ድርጊት አስቀድሞ ክርስቶስም ሆነ ደቀ መዛሙርቱ በልሳን ስለመናገራቸው የተጻፈ ነገር የለም። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በወንጌላት ጊዜ ያልተሰጠ መንፈሳዊ ስጦታ ነው። ስጦታው የተጀመረው በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ በጳንጠቆስጤ ዕለት ከሆነ፥ በሱ ፈቃድ ሊቋረጥ ይችላል።

ሁለተኛ፥ ልሳን ለእስራኤል ምልክት የመሆን ባሕርይም አለው። የጳጋ ዘመን በሚጀመርበት ጊዜ፥ የወንጌል መልእክት ከእግዚአብሔር መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲህ ያለው ምልክት አስፈላጊ ነበር። በነቢያት የተነገረ ስለሆነ፥ ትንቢቱ መፈጸም ነበረበት። ኢሳይያስ ‘‘በባዕድ አፍ በልዩም ልሳን ለዚህ ሕዝብ ይናገራል’’ ሲል ተንብዮ ነበር (ኢሳ. 28፡11)። ይህ የኢሳይያስ ቃል በ1ኛ ቆሮንቶስ 14፡21-22 ተጠቅሷል፦ ‘‘ሌሎችን ልሳኖች በሚናገሩ ሰዎችና በሌላ አንደበት ለዚህ ሕዝብ እነግራቸዋለሁ፥ እንዲህም ቢሆን አይሰሙኝም ይላል ጌታ ተብሎ በሕግ ተጽፏል። እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፥ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም።’’ ትንቢቱ ሙሉ በሙሉ የተፈጸመ በመሆኑ ምልክቱ የሚያስፈልግበት ሌላ ምክንያት የለም።

---

* ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ፥ ስለ ሞንታኑስና ትምህርቱ በገጽ 297 ላይ የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

ሦስተኛ፥ በሐዋርያነት፥ በነቢይነት፥ ተአምራትን በማድረግና በፈውስ ስጦታ እንዳየነው፥ አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎች የተሰጡት ለጊዜው ነበር። በጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን አገልግሎት ያገዙና ያልተለመዱ ምልክቶች የታለመላቸውን ተግባር ካከናወኑ በኋላ መወሰዳቸው የእግዚአብሔር ዓላማ ይመስላል።

አራተኛ፥ በልሳን የመናገር ስጦታ እንደሚያበቃ አስቀድሞ ተነግሯል (1ኛ ቆሮ. 13፡8)። በአገባቡ መሠረት ልሳን የተጠቀሰው፥ በልሳን ስለ መናገር ስጦታ ነው ለማለት ይቻላል። በተለይ ስለዚህ በሚናገሩ ጥቅሶችና በሌሎችም አመልካች ጥቅሶች ላይ በመመሥረት፥ በልሳን የመናገር ስጦታ ለሐዋርያት ዘመን በጊዜያዊነት የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ሆኖ መገለጡን ለማየት እንችላለን።

ስጦታውን ተገቢ ባልሆነ መንገድ የመጠቀም አደገኛነት። ከ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት በግልጥ እንደምንረዳው፥ በልሳን መናገር በባሕርይው ለተሳሳተ አጠቃቀም የተጋለጠ ነው። ይህን በአሳባችን ይዘን፥ በማጠቃለያ ላይ አንዳንድ እውነታዎችን እንደገና ማንሣት እንችላለን።

በመጀመሪያ፥ የምንመለከተው በልሳን መናገር፥ ከስጦታዎች ሁሉ አነስተኛው መሆኑን ነው። በመሆኑም የታላቅ መንፈሳዊ ኃይል ወይም ጠቀሜታ ማስረጃ ሆኖ ከፍተኛ ስፍራ ሊሰጠው አይገባም። በአንዳንድ የእምነት ክፍሎች የተሰጠው ስፍራ ከቅዱሳት መጻሕፍት አሳብ ጨርሶ የራቀ ነው።

ሁለተኛ፥ በልሳን መናገር በማንኛውም ረገድ የደኅንነት ማስረጃ አይደለም። በባሕርይው ስጦታ በመሆኑ በሐዋርያት ዘመን እንኳን ስጦታው የነበራቸው ክርስቲያኖች ሁሉ እንዳልነበሩ ግልጥ ነው። ከሐዋርያት ሥራና ከ1ኛ ቆሮንቶስ ውጪ፥ በሌላ ስፍራ አለመጠቀሱ እምብዛም አስፈላጊ ያለመሆኑን ያመለክታል። በልሳን መናገር እንደ ውጫዊ የደኅንነት ምልክት አስፈላጊ ሆኖ ቢቆጠር ኖሮ፥ በደኅንነት ዕቅድ ውስጥ ዋና ስፍራ ይሰጠው ነበር። የዮሐንስ ወንጌልም ሆነ ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከው መልእክት ስለ ልሳን ምንም አለመናገራቸው፥ በጉዳዩ ልንጠነቀቅ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

ሦስተኛ፥ በልሳን የመናገር ስጦታ የመንፈሳዊነት ምልክት አይደለም። ጳውሎስ ከጻፈላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሥጋዊነትና የጅምላ ኃጢአት የሚገኘው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ ሳለ፥ በልሳን የመናገር ስጦታ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይልቅ በዚያችው ቤተ ክርስቲያን ይታይ እንደነበር ግልጥ ነው። በልሳን የመናገር እንቅስቃሴ ወደ ቅድስና አለመምራቱ በታሪክ የታየ ጉዳይ ሲሆን፥ ከመጠን በላይ የመሆኑ

ነገርም ወደ ጥፋት መርቷል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እግዚአብሔርን የሚመስሉ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ከማንኛውም ዓይነት በልሳን የመናገር ልምምድ የራቁ ነበሩ።

አራተኛ፥ በልሳን መናገር ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይለያል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 መሠረት እያንዳንዱ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቋል። ክርስቲያኖች ሁሉ ግን በልሳን አይናገሩም። በልሳን መናገርን ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚያበቃ አድርጎ የማቅረብ ሙከራ የቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ከመረዳት በርካታ ስሕተቶች መካከል አንዱ ነው።

7. በልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ

በጥንት ቤተ ክርስቲያን ለአንዳንዶች በልሳን የመናገር ስጦታ ከመሰጠቱ ጋር የተነገረውን የሚተረጉሙ ሌሎች ሰዎች ያስፈልጉ ነበር። በልሳን የመናገር ስጦታ ከነቢይነት በግልጥ የተለየ ቢሆንም፥ በአንዳንድ ሁኔታ የመገለጥ መነሻ ሆኖ ነበር። ብዙውን ጊዜ ከልዩ ደስታ ጋር የተያያዘ ክብር መስጠትና አምልኮ ነው። በልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ (1ኛ ቆሮ. 12፡10፥ 14፡26-28)፥ በልሳን የተነገረውን ነገር የመተርጎም መለኮታዊ ችሎታ ነው። በልሳን የመናገር ስጦታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሌለ፥ የመተርጎም ስጦታም በተመሳሳይ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ ካለው የእግዚአብሔር ዓላማ ውጭ የሆነና ያለፈ ነገር ነው።

8. መናፍስትን የመለየት ስጦታ

በቃል የሚሰጡ ብዙ የተለያዩ መገለጦች በነበሩባት ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን፥ እውነቱን ከሐሰት ለመለየት መለኮታዊ እገዛ ያስፈልግ ነበር። ሰይጣን አሁን እንደሚያደርገው ማንኛውንም የማጭበርበሪያ መሣሪያ ይጠቀም ነበርና መናፍስትን የመለየት ስጦታ (1ኛ ቆሮ. 12፡10)፥ በቃል የተሰጠውን ሰማያዊ መገለጥ እውነትነት ከሐሰት ለመለየት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሰጥ ችሎታ ነበር። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስላልተጠናቀቁ፥ ከብሉይ ኪዳን በቀር ምንም ዓይነት የጽሑፍ ማረጋገጫ ያኔ አልነበረም። አዲስ ኪዳን በእጃችን ከገባ በኋላ ግን ይህን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የማያስፈልግ አደረገው።

በክርስቲያኖች ውስጥ ያደረው መንፈስ ቅዱስ፥ ስሕተትን ሁሉ በመግለጥ የሚረዳ መሆኑ እርግጥ ነው። በ1ኛ ዮሐንስ 2፡27 እንደተገለጠው፥ "እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል ማንም ሊያስተምራቸሁ አያስፈልጋችሁም፥ ነገር ግን የእርሱ

ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ እውነተኛም እንደሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ'' የሚለው ቃል ሁለንተናዊና የእያንዳንዱ ክርስቲያን ንብረት ነው።

አማኞች ምንጊዜም አደገኛ ወደሆነ ስሕተት እንዳያመሩ ''መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ እንዲፈትኑ'' (1ኛ ዮሐ. 4፡1) ተመክረዋል። መመርመሪያውም፦ ''ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው የሚል ነው'' (1ኛ ዮሐ. 4፡2)። እዚህ ላይ መንፈስ የሚለው ቃል የሰው ልጆችን የሚያመለክት እንደሆነ ለመገመት ይቻላል። በዚህ መሠረት ማንኛውም የሥነ-መለኮት መምህር ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መምጣቱን ማመን አለማመኑ በማንኛውም አማኝ ይፈተናል። አንዳንድ ሰባኪዎችን እንደሚገጥማቸው፥ በአጋንንት የተያዙ ሰዎችን በሚመለከት የእነዚህን ሰዎች ማንነት በዚህ መመዘኛ ዘዴ መፈተን መቻሉ አያጠራጥርም። ነገር ግን በማንኛውም ረገድ መናፍስትን የመለየት ስጦታ ያቆመ ይመስላል። በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያኖች የሚታመኑት የተጻፈውን የእግዚአብሔር ቃል መንፈስ ቅዱስ ባበራላቸው መጠን ሲሆን፥ ለክርስቲያኖች ሁሉ ከሚሆነው ውጭ መናፍስትን የመለየት ሥልጣን የመስጠቱ ነገር አብቅቷል።

የመንፈሳዊ ስጦታዎች መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር ጸጋ፥ ለሉዓላዊነቱ፥ ለጥበቡ እንዲሁም ለችሮታው ሌላ ምስክር ነው። በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ያለውን መለኮታዊ ዓላማ የማሟላት ምስጢር በአምላካዊ አሠራር መሠረት ይገለጣል። ይህም በተሻለ መንገድ ሊታይ የሚችለው፥ በእግዚአብሔር ታምኖ ለፈቃዱ ራስን በፍቅር በመስጠት ነው።

21

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ባሕርይ

1. የትምህርቱ መሠረታዊ አስፈላጊነት

ከተግባራዊ አመለካከት አንጻር ስናየው፥ ለክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን ያህል እጅግ አስፈላጊ ትምህርት የለም። በአማካይ የሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ ከተግባራዊ ተዛምዶው ጋር እጅግ የተተወና የተረሳ ትምህርት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መሠረታዊ ትምህርት ከሥነ-መለኮት እውቀት በተጨማሪ የተግባራዊ ልምምድን እውነት ይጠይቃል። ስለ ሌሎቹ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ስንነጋገር፥ ተግባራዊ ለሆነው የሕይወት ልምድ እጅግ ጠቃሚ መሠረት የሆኑ የእምነት ትምህርቶችን ከቅዱሳት መጻሕፍት እውነታ ጋር በማጣመር መሆኑን ልናስታውስ ይገባል። ብዙ ሰዎች ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ትምህርት መሠረት የሚሆኑትን፥ እንደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፥ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር፥ ዳግም ልደትና መታተም ያሉትን ሌሎች መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች በሚገባ ሳይረዱ ጉዳዩን ለመግለጥ ሙከራ አድርገዋል። ሌሎች ደግሞ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት ሙሉ በሙሉ ትተውና በልምምድ ላይ ብቻ ተመሥርተው ውሳኔ ላይ ደርሰዋል። ስለዚህ በፊታችን ያለው ተግባር፥ ይህን መሠረታዊ ትምህርት በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት፥ በተለይም በክርስቲያናዊ ልምምዶች ውስጥ አጉልቶ መግለጥ ይሆናል። ስለዚህ ይህ ርእስ በዚህ ክፍል በሦስት አቅጣጫዎች ይገመገማል። እነርሱም፦ 1. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ባሕርይ፥ 2. ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያስፈልጉ ነገሮች፥ 3. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጤት ናቸው።

2. የመንፈሳዊ ልምምድ ተቀዳሚ ምንጭ

የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ባሕርይ በጥንቃቄ በምንመረምርበት ጊዜ፥ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ የመንፈሳዊ ልምምዶች ሁሉ ምንጭ እርሱ መሆኑን እንረዳለን። በዚህ መልኩ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከደኅንነት በፊት ከሚሆኑ እንደ መውቀስ ካሉ ሥራዎችም ሆነ፥ በደኅንነት ጊዜ ከሚፈጸሙ አገልግሎቶች ሁሉ የተለየ መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ ግልጥ ይሆናል። እነዚህን መደምደሚያዎች የሚደግፉ መሠረታዊ እውነቶች የሚገኙት፥ ለሙላት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎችና ውጤቶች ጨምሮ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን በሚወክለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው።

3. የተለያዩ መንፈሳዊ ልምምዶች

እጅግ ሰፊና በርካታ የሆኑ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ልምምዶችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘውን ያህል የትም አናገኝም። ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ፡- ‘‘በዕለታዊ የክርስቲያኖች አኗኗር ውስጥ የባሕርይና የብቃት ልዩነት መኖሩ አያጠራጥርም። ይህ ልዩነት በአዲስ ኪዳን ውስጥም የታወቀና ግልጥ ነው’’ ብሏል። ቅዱሳት መጻሕፍት በዳነውና ባልዳነው ሰው መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት በርካታና ግልጥ በሆኑ ቃላት የገለጡ ሲሆን፥ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ያለው መንፈሳዊ ልዩነት ግን በዚህ የሚያበቃ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ‘‘በመንፈሳዊ’’ እና ‘‘በሥጋዊ’’ ሰው መካከል (1ኛ ቆሮ. 2፡9-3፡4) ‘‘እንደ ሰው ፈቃድ’’ በሚመላለሱና ‘‘የበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ’’ በሚያፈሩ (1ኛ ቆሮ. 3፡3፤ ቈላ. 1፡10) መካከል ያለውን ልዩነት ያቀርባል። በእነዚህ ተደጋጋሚ ንጽጽሮች የሚታየው ልዩነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው ግንኙነት መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል። በዚህ መሠረት ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንዲህ ሲል ጽፏል፡- ‘‘ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ’’ (ገላ. 5፡16)።

4. መንፈሳዊነት ከብስለት ጋር ሲነጻጸር

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ የሆነው መንፈሳዊ ልምምድና በረከት፥ አስፈላጊ ከሆነ ሌላ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ይኸውም ከክርስቲያን በጸጋ ማደግ ጋር ተነጻጽሯል። ማንኛውም ክርስቲያን፥ አዲስ የተወለደ ቢሆን፥ መንፈሳዊ ቢሆን፥ በመንፈስ ቢመላለስ፥ በክርስቶስ ውስጥ ቢኖር፥ እስኪሞት ወይም ክርስቶስ የራሱ ለሆኑት እስኪመጣ ድረስ እርሱን ወደመምሰል ቀስ በቀስ በሚከናወን መንፈሳዊ እድገት ውስጥ ይኖራል። ይህ ዝግተኛ እድገት በግለሰቡ መንፈሳዊነት ላይ በተወሰነ መጠን የተመሠረተ ቢሆንም፥ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ቁጥጥር ሥር ስለሆነ፥ በመጨረሻ ፍጹምነትን እንደሚያገኝ ለክርስቲያን ቃል ተገብቶለታል። ይህ ጉዳይ በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሱ፥ በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ ዋና ነገር መሆኑን የሚያሳይ ነው። ለአጨዳ እስኪደርስ ድረስ ስንዴውና እንክርዳዱ በአንድነት ያድጋሉ (ማቴ. 13፡30)። ስጦታው ያላቸው ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን የመሰጠታቸው ዓላማ የሚከተለው ነው፡- ‘‘ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል

ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ... ሕፃናት መሆን ወደፊት አይገባንም። ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ'' (ኤፌ. 4፡12-13፥ 15)። ክርስቲያኖች፦ ''ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃሉን ወተት ተመኙ'' ተብለው ተመክረዋል (1ኛ ጴጥ. 2፡2)። ደግሞም፥ ''ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ'' ተብለው ተመክረዋል (2ኛ ጴጥ. 3፡18)።

በክርስቲያን የጸጋ እድገትና መንፈሳዊነት መካከል እጅግ አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት አለ። ክርስቲያን በሰማይ ፍጹምነት እንደሚያገኝ የተረጋገጠ ቢሆንም፥ በምድር ላይ እያለም ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲደርስ ከፍተኛ ማበረታቻ ተሰጥቶታል። ወደ መንፈሳዊ ብስለት ለመድረስ ከዚህ የቀስ በቀስ ሂደት ውጭ የተሰጠው መንገድ ባይኖርም፥ ሁኔታዎችን አሟልቶ ከተገኘ፥ በአንድ ጊዜ ወደ መንፈስ ቅዱስ በረከት ሙላት ለመግባት ይችላል። በሥጋዊ አካል እድገት የጨንነትና የመጎልመስ ሂደት እንዳለ ሁሉ በመንፈሳዊነት ውስጥም ተመሳሳይ ሂደት አለ። አንድ ሕፃን በእድገት አንጻር ገና ያልበረታ ሆኖ ፍጹም ጨነኛ ሊሆን ይችላል። የአካል እድገት ጊዜ ይጠይቃል፤ ጨንነት ግን አካል አሁን ባለበት ሁኔታ የሚያገኘውን ደስታና እድገት የሚወስን ነው። በመንፈሳዊው ዓለምም አዲስ የተወለደ ሰው እድገቱ ከበሰለ ክርስቲያን ጋር የሚወዳደር ባይሆንም፥ የመንፈስ ሙላት ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን በመንፈሳዊነትና በብስለት መካከል በጣም አስፈላጊ ግንኙነት አለ። አንድ ቅዱስ ሰው በሥጋዊነት በመመላለስ ፋንታ ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረትና በመንፈስ ሙላት መኖር ሲጀምር፥ በእምነቱ በፍጥነት ያድጋል። ''በክርስቶስ ሕፃን ነው'' የምንለው ሰው፥ ወደ አንድ የተወሰነ የብስለት ደረጃ ለመድረስ ጊዜ የነበረው፥ ነገር ግን እድገቱ በሥጋዊነት የተገታበት ሰው ነው። የሥጋዊ አካል ጨንነት ለሥጋዊ አካል እድገት የሚያበረክተው ድርሻ እንዳለ ሁሉ፥ የመንፈስ ሙላትም ለመንፈሳዊ እድገት የሚያበረክተው ነገር አለ።

አንድ ክርስቲያን ብስለት ባይኖረው እንኳ፥ የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች ካሟላ፥ ወደ መንፈሳዊነት ወዲያውኑ ይደርሳል የሚለውን አሳብ የሚቃወሙ አመለካከቶችም አሉ። ክርስቲያኖች መንፈስ በሙላት እንዲኖርባቸው የተሰጠው የማበረታቻ ምክር ከእነዚህ አመለካከቶች የተለየና የሚቃረን ነው። ጄ. ኢስት ሄሪሰን [J. East Harrison] እንዳለው፦

> ''በዝቅተኛ መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ክርስቲያኖች በዚያው መኖራቸው ብቻ ሳይሆን የሚሻልና የሚበልጥ ነገር አለ በሚለው አሳብ ቅር ይሰኛሉ። ሌሎች ደግሞ ሁልጊዜ በማጉረምረምና

በማልቀስ፥ ምድረ በዳና አስከፊ በሆነው መንገዳቸው ይጓዛሉ። በሁለቱም ሁኔታዎች በቃል ሊገለጥ የማይችል ኪሳራ አለ። ጉድለት በሞላበት በዚህ ምስክርነታቸውና አሳዛኝ በሆነው ባሕርያቸው አማካይነት በክርስትና ላይ ሳይቀር ጉዳት አድርሰዋል።''

ስለዚህ የመንፈሳዊ ልምምድ የተለያዩ ገጽታዎች የሚፈጠሩት የመንፈስ ሙላትና መንፈሳዊ ብስለት ከምንላቸው ሁለት ነገሮች የተነሣ ነው። ከሁለቱ በመንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ የመንፈስ ሙላት እጅግ አስፈላጊ ነው። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በተገቢው ሁኔታ ተስተካክሎ በሚኖር ግን ባልበሰለ ክርስቲያን እንኳ ሊታወቁ ይችላሉ። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፥ መንፈስ በሙላት በማረከው በማንኛውም ክርስቲያን ውስጥ እንዲታይ የእግዚአብሔር እቅድ ነው። አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው የሚያከናውነውን ሙሉ አገልግሎት ያለማወቃቸው ግልጥ እውነት ሲሆን፥ ይህ የእውነትን አንድ ገጽታ የማወጅ አገልግሎት፥ ቤተ ክርስቲያን ልትወጣው የሚገባት ዋና ሥራ መሆኑን ያሳያል።

5. በውስጣችን ያደረውና ሊታገድ የማይችለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት

''የመንፈስ ቅዱስ አማኝን የመሙላት ሥራ''፥ አማኑ ራሱን ሙሉ በሙሉ በውስጡ ላደረው መንፈስ ቅዱስ በሚሰጥ ጊዜ በሕይወቱ የሚፈጸም አገልግሎት ነው ብለን በቀላሉ ልንተረጉመው እንችላለን። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገር ማንኛውም ጥቅስ፥ በተሞላው ሰው ሕይወት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ ተቆጣጣሪነት ምክንያት የመጣን መንፈሳዊ ሁኔታ ያመለክታል። በወንጌላት የተጠቀሰውን ጨምሮ በአዲስ ኪዳን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገሩ አሥራ አራት ጥቅሶች አሉ። 'ፒምፕሌሚ' [ʻpimplemi'] የሚለው የግሪክ ግሥ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስምንት ጊዜ ተጠቅሷል (ሉቃስ 1፡15፥ 41፥ 67፤ ሐዋ. 2፡4፤ 4፡8፥ 31፤ 9፡17፤ 13፡9)። የዚሁ ግሥ ሌላ ቅርፅ የሆነው 'ፕሊሩ' [ʻpleroo'] የሚለው ቃል ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል (ሐዋ. 13፡52፤ ኤፌ. 5፡18)። አሳቡን ለመግለጥ ሥራ ላይ ከዋሉት ከእነዚህ ሁለት ግሦች ሌላ 'ፕሊሬስ' [ʻpleres'] የሚለው ቅጽል አራት ጊዜ ተጠቅሷል (ሉቃስ 4፡1፤ ሐዋ. 6፡3፤ 7፡55፤ 11፡24)።

ከእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የምንገነዘበው፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ያለምንም መከልከል በነጻነት

የሚያገለግላቸው መሆኑን ነው። ይህ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚፈጸም የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን የሚያሳይ ውጫዊ ማረጋገጫም ይገኛል። አንዳንድ ሰዎች በሕይወታቸው ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥራን መሥራት የቻሉት መንፈስ ቅዱስ ላቅ ባለ ሁኔታ ስለተሰጣቸው ነው ማለት ትክክለኛ አባባል አይደለም። አማኞች ሁሉ ዳግም በተወለዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያድርባቸዋል። ስለዚህ የአማኝ መንፈሳዊ እድገት ወይም ሥራ የሚወሰነው፥ ግለሰቡ ፍላጎቱንና ዝንባሌውን ደግሞም ራሱን በፈቃደኝነትና ሙሉ በሙሉ በመስጠት የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወቱ እንዲከናወን በማድረጉ ላይ ነው። ዋናው ነገር እግዚአብሔር ይበልጥ በውስጣችን ይሁን ማለት ሳይሆን እኔነትንና የሥጋ ፍላጎትን ጥሎ፥ የእግዚአብሔር ኃይል በእኛ ውስጥ እና በእኛ እንዲሠራ ማድረግ ነው።* ምንም እንኳን አማኞች ‘‘የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ’’ (1ኛ ቆሮ. 6፡19) እንደሆኑ ቢታወቅም፥ ብዙዎች ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ በሚገባ አለመስጠታቸው የሚያሳዝን ነው። በዚህ የተነሣ በመንፈስ ቅዱስ ይሰጣቸው የነበረ ገደብ የለሽ የበረከት አገልግሎት በሕይወታቸው አይታይም።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገሩ የተለያዩ ክፍሎች ጥናት ይህን ሁኔታ ግልጥ ያደርገዋል። በሉቃስ 4፡1 መሠረት ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ። ይህም ከሥላሴ አካላት አንድነት በላይ የሚናገር ሲሆን፥ በተለይ ለክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ የተሰጠ አገልግሎት መሆኑን እናያለን። መጥምቁ ዮሐንስ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ እንደሚሆን አስቀድሞ ተተንብዮአል (ሉቃስ 1፡15)፤ እናቱ ኤልሳቤጥና አባቱ ዘካርያስም በተለያየ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር (ሉቃስ 1፡41፥ 67)። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገሩና በወንጌላት የሚገኙ እነዚህ ክፍሎች በብሉይ ከነበሩት ጋር ይመሳሰላሉ (የዚህን መጽሐፍ ምዕራፍ 8 ይመልከቱ)። ይህ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዓላማ የሚመራና ጊዜያዊ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንጂ፥ አሁን እንደሚሆነው ራሳቸውን ለሰጡ ቅዱሳን ሁሉ የሚሆን ሁለንተናዊ መብት አይደለም። በሐዋርያት ሥራና በኤፌሶን ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ የሚያመለክቱት ጥቅሶች ሁሉ በዚህ ስፍረ-ዘመን ስለተለመዱ ተግባራት የሚናገሩ ናቸው።

የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ቀስ በቀስ የተገለጠ ሲሆን፥ የአገልግሎቱ አንዳንድ ሁኔታ ግን የሐዋርያትን ውክልና

---

* ዲ. ኤል. ሙዲ [D. L. Moody] (1837-89) ‘‘ራሱን ሙሉ ለሙሉ ለጌታ ፍቃድ በማስገዛት እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን የሚሠራበትን ሰው ዓለም እስካሁን አላየችም። በእግዚአብሔር እርዳታ ያ ሰው እኔ እሆናለሁ’’ ብሎ ተናግሮ ነበር። በእርግጥ እግዚአብሔር ይህን ትሑት ሰው በሺ የሚቆጠሩ ነፍሳትን ለደኅንነት ወደሚያበቃ እምነት ለማምጫ ተጠቅሞበታል።

የሚጠይቅ ነበር። ይሁን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ ማንኛውም የአገልግሎት ሁኔታ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በሰጡ ክርስቲያኖች ውስጥ ብቻ የሚገኝ እንደሆነ እናያለን። በዚህ መሠረት በሐዋርያት ሥራ 2፡4፥ በጰንጠቆስጤ ዕለት በሰገነት ሆነው ይጠባበቁ የነበሩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን ተረድተናል። እግዚአብሔርን ለማክበር ይሻ የነበረው ጴጥሮስ በካህናት አለቆች ጉባዔ ፊት በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ (ሐዋ. 4፡8)። ጥንት ክርስቲያኖች ከጸለዩ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ እናያለን (ሐዋ. 4፡31)። የመጀመሪያዎቹን ዲያቆናት ለመምረጥ ያስፈልግ የነበረው መመዘኛ ‹‹መንፈስ ቅዱስ .... የሞላባቸው›› መሆናቸው ነበር (ሐዋ. 6፡3)። እስጢፋኖስ በገዳዮቹ ፊት ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ የእግዚአብሔርን ክብር ባየ ጊዜ ‹‹በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር›› (ሐዋ. 7፡55)። ጳውሎስ የጌታ መልእክተኛ የሆነውን ሐናንያን ከተቀበለ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ (ሐዋ. 9፡17)። በዚህ ሁኔታ የምናየው ያልተለመደ ነገር ሐናንያ እጅ እስኪጭንበት ድረስ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ አለመሞላቱ ነው። ይህም ሐናንያ የእግዚአብሔር መልእክተኛ መሆኑን ለማሳየት የተደረገ ጊዜያዊ ሁኔታ ነበር። ቆየት ብሎም ጳውሎስ እንደገና በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላቱ የምናየው ነገር አለ (ሐዋ. 13፡9)። በርናባስም ‹‹በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር›› (ሐዋ. 11፡24)። ‹‹በአንጾኪያና በጲስድያ የነበሩት ደቀ መዛሙርት ደስታና መንፈስ ቅዱስ እንደሞላባቸው›› እናያለን (ሐዋ. 13፡52)። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የተነገረው እያንዳንዱ ታሪክ፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚሞሉት ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው የሚለውን መሪ አሳብ የሚገልጥ ነው።

6. በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ትእዛዝ

አማኝን በመሙላት ረገድ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ልዩ የሚያደርገው፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን እንዲሞላ የታዘዘ መሆኑ ነው። በኤፌሶን 5፡18 መሠረት ሁሉም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ኃላፊነት አለበት፡- ‹‹መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ።›› ከዚህ አንጻር የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር በቀጥታ ይነጻጸራል። ሰዎች ለወንጌል እንዲገዙና በክርስቶስ እንዲያምኑ እንጂ፥ ዳግም መወለዳቸው፥ በመንፈስ ቅዱስ መታተማቸውና መጠመቃቸው በሥጋ ጥረት እንዲሆን አልታዘዙም። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች፥ ሰው በክርስቶስ አምኖ በሚድንበት ጊዜ ወዲያውኑ የሚገኙ ናቸው። የክርስቲያንን መንፈሳዊ ሕይወት ሳይሆን ደኅንነቱን ይመለከታሉ። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ይሞሉ

ዘንድ ታዘዋል። በእርግጥ ማንኛውም ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስን ሙላት በምኞት ወይም በመፈለግ ብቻ አያገኘውም። ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት አስፈላጊ የሆነው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጧል። እነዚህን ራስን የመስጠት መመዘኛዎች ማሟላት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነት ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በክርስቲያኑ ሕይወት ከተገለጡ ያ ሰው በመንፈስ ቅዱስ መሙላቱ አያጠራጥርም።

ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ከመታዘዛቸው እውነታ አንጻር፥ በመንፈስ ያልተሞሉ ክርስቲያኖች የመኖራቸው ነገርም ግልጥ ነው። ማንኛውም ክርስቲያን ሌሎቹን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ይፈልግ ዘንድ አልታዘዘም። ምክንያቱም አገልግሎቶቹ በባሕርያቸው በደኅንነት የሚገኙ ናቸውና። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለዳኑ ሰዎች ብቻ የተሰጠ ነገር ቢሆንም፥ የደኅንነት አካል ግን አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር በቀጥታ በተነጻጻሪነት የቀረበ መሆኑም ግልጥ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል የሚሆንበት መንገድ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ጋር መነጻጸር አለበት። ምክንያቱም ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆኑት ከደኅንነታቸው ቅጽበት ጀምሮ ሲሆን (ሮሜ 8፡9)፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚሞሉት ግን አንዳንዶች ብቻ ናቸው። ማንኛውም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ እስካልተሞላ ድረስ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ነው ሊባል አይችልም። ይህ ለክርስቲያኖች ሁሉ በእኩልነት የተሰጠ ኃላፊነትና መብትም ነው። የማያምኑትን ግን ጨርሶ አይመለከትም።

7. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በተደጋጋሚ የሚፈጸም ልምምድ ነው

ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት መሠረታዊ ትምህርት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያለው በኤፌሶን 5፡18 ይሙላባችሁ በሚለው ትእዛዝ ውስጥ ያለው ግሥ ነው። 'ፕሌሮስቴ' [ʻplerousthe'] የሚለው ግሥ የአሁን ጊዜንና ትእዛዝን ያዘለ ነው። የአሁን ጊዜን አሳብ ያዘለ መሆኑ ''ሳታቋርጡ ተሞሉ'' የሚል ትርጉም እንዲኖረው አድርጎታል። በተነጻጻሪነት የቀረበው በወይን ጠጅ የመስከር አሳብም ግልጥ ነው። በጥቅሱ እንደተገለጠው ያለማቋረጥ በወይን ጠጅ ከመስከር ፋንታ፥ በአጠቃላይ በእርሱ ኃይልና ተጽዕኖ ሥር ይሆኑ ዘንድ፥ ክርስቲያኖች ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለባቸው። የአንድ ግሥ የአሁን ጊዜ ትእዛዝ ማስተላለፊያ ይዘቱ የማያቋርጥ አሳብን

ያዘለ ነው። ይህን መሰሎቹ ግሦች አዲስ ኪዳን ውስጥ በመደበኛነት ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆኑ ቋሚ አሳብን ለመግለጥ አገልግለዋል። ይህ አሳብም እዚህ ስፍራ ላይ ትልቅ ዋጋ አለው። የሚቀጥልን አሳብ ለማመልከት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በማዘውተር ጥቅም ላይ ውሎ የሚገኘው ሰዋስዋዊ አጠቃቀም "የትእዛዝ አንቀጽ" ነው። ይህ አጠቃቀም በዚህ ነጥብ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። ይህ አገባብ በግልጥ የሚያመለክተው መሠረታዊ አሳብ፥ የማያቋርጥ የመንፈስ ቅዱስ የመሙላት አገልግሎትን ነው።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት በተሰጠው ትእዛዝ ውስጥ ዓረፍተ ነገሩ በአሁን ጊዜ መጻፉ፥ ክንውኑ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በሰጡ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የማያቋርጥ አገልግሎት መሆኑን ያሳያል። በኃጢአት ሊታገድ የሚችል ቢሆንም የዕለት ተዕለት ግንኙነት ነው። "ሁለተኛው የጸጋ ሥራ"* (ወይም "ዳግመኛ በረከት") ተብሎ የሚታወቅ ነገር ወይም የአንድ የተወሰነ ጊዜ ታሪካዊ ልምምድ አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጫዊ ማረጋገጫ የተለያየ ቢሆንም፥ መሠረታዊው ጉዳይ እግዚአብሔር የእርሱ ለሆኑት ሁሉ የደነገገው ልምምድ መሆኑ ነው። ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን እውንነት በሕይወቱ ሲለማመድ፥ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት አገልግሎት በሚገባ ይገነዘበዋል።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሰው ሕይወት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚፈጸም ተግባር ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ወሳኝ ምስክር ነው። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በጰንጠቆስጤ ቀን በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች (ሐዋ. 2፡4)። በሐዋርያት ሥራ 4፡8፥ ጴጥሮስ እንደገና በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላቱ የተጻፈ ነገር አለ። በጉባዔው መካከል እሱ ያቀረበውን የመከላከያ ገለጣ ለመስማት በኢየሩሳሌም ተሰብስበው የነበሩ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ (ሐዋ. 4፡31)። በመንፈስ ቅዱስ በመሞላቱ ምክንያት አስቀድሞ ለዲቁና ተመርጦ የነበረው እስጢፋኖስ፥ በሰማዕትነት በመሞቻው ቅጽበት "በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ" እንደነበር ተገልጿል (ሐዋ. 7፡55)። ጳውሎስና በርናባስ በተለያየ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው እንደነበር ተጽፏል (ሐዋ. 9፡17፤ 11፡24፤ 13፡9፥ 52)። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ልምምድ መሆኑ በተጠቀሱት ሁኔታዎች በማስረጃ ተጠቅሷል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ አገልግሎት በሚያመለክተው መሠረት፥ በዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጥናት የምንደርስበት ማጠቃለያ ይህ አገልግሎት በርከት ያሉና የተለያየ ደረጃ ያላቸው መንፈሳዊ ልምምዶች እንዲኖሩ የሚያስችል መሆኑን ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ራሱን ሙሉ

* በምእራፍ 15 መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የአሳታሚውን መግለጫ ይመልከቱ።

በሙሉ ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር በሰጠ ሰው ሕይወት የሚፈጸም አገልግሎት መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ይታያል። የክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ሁለንተናዊ ኃላፊነት ግልጥ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ ተደንግጓል። ክርስቲያን ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላቱ ነገር በቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ልምምድ ታይቷል። በማንኛውም ሁኔታ የሚከናወን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በደኅንነት ወቅት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሚፈጸሙት ማለት፥ ከዳግም ልደት፥ መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ከማደሩ፥ ከመታተምና ከጥምቀት ከንውን ጋር በቀጥታ በተነጻጻሪነት የሚቀርብ ነው።

22

ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያስፈልጉ ነገሮች

ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር፥ ‘‘መንፈሳዊው ሰው’’ በሚል ርእስ ስለ መንፈስ ቅዱስ በጻፈው እውቅ ሥራው፥ እንዲሁም፥ ‘‘ሥርዓታዊ የሥነ-መለኮት ትምህርት’’ በተሰኘው ባለ ስምንት ቅጾች መጽሐፉ ስድስተኛ ቅጽ ውስጥ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት አስፈላጊ የሆኑ ወይም መሟላት ያለባቸው ነገሮች በሚለው ርእስ ሥር ቀላልና ውጤታማ የሆነውንና በቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኘውን ዝርዝር ጠቁሟል። በዚያ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት መሟላት ያለባቸው ሦስት ነገሮች ተጠቅሰዋል። በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡19፥ ‘‘መንፈስን አታጥፉ’’ የሚል ትእዛዝ ይገኛል። በኤፌሶን 4፡30 ደግሞ፥ ‘‘ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ’’ የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። ሦስተኛ፥ በገላትያ 5፡16 ልንከተለው የሚገባን ትእዛዝ ተሰጥቷል፦ ‘‘ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።’’

እነዚህ ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በመለኮት የታቀዱና ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያመለክታሉ። በርካታ መንፈሳዊ ልምምዶች ቢኖሩም፥ ሁሉም ከእነዚህ ሦስት ቀላል ትእዛዛት ጋር ይያያዛሉ። እነዚህ ጥቅሶች በመንፈስ ቅዱስ የመሞላትን ሁኔታ ለመረዳት እንደ ቁልፍ ያገለግላሉ ቢባል የተጋነነ አይሆንም። ለሽንፈትና ለመንፈሳዊ ድካም ተቀዳሚ ምክንያት በሆነው ነገር ላይ ከማተኮር ይልቅ፥ ብዙው ጊዜ የሚጠፋው ‘‘ምክር’’ ተብሎ በሚነገር ውጫዊ ነገር ላይ መሆኑን ማየቱ ያሳዝናል። ወደዚህ ነገር የሚያተኩር ማንኛውም ሰው ጉዳዩ ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች አንዱ መሆኑን በአዲስ ግንዛቤ ሊያጤነው ይገባል።

1. መንፈስን አታጥፉ

ፍቺ። በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡19 ‘‘መንፈስን አታጥፉ’’ የሚለው ቃል በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በወጉ አልተገለጠም። ማጥፋት የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋለው የሚታይ አካላዊ ነገር ወይም ድርጊትን ለመግለጫነት ነው። ይህን እንደሚከተለው ለማየት እንችላለን፦ ክርስቶስ በማቴዎስ 12፡20፥ የጥዋፍ

ክር ስለማጥፋት ተናገረ። በዕብራውያን 11፡34 የእምነት አርበኞች ‹‹የእሳትን ኃይል እንዳጠፉ›› ተገልጧል። በኤፌሶን 6፡16 የእምነት ጋሻ ‹‹የክፉውን ፍላጻ ሁሉ ሊያጠፉ እንደሚችል›› ተገልጧል። በ1ኛ ተሰሎንቄ ግን ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው በምሳሌያዊ ገለጣ ነው። ታየር የተባለ ሰው እንደገለጠው፥ በዚህ ስፍራ የቃሉ ትርጉም ‹‹ማፈን፥ መጨቆን›› ነው። መንፈስ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ወይም ማግለል በአንድ መልኩ የሚቻል አይደለም። በክርስቲያኖች ሁሉ ውስጥ የማደሩ ነገር የተረጋገጠ ነው። ሕልውናው አይገሰስም። ስለዚህ ማጥፋት፥ ፈቃዱን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን ወይም መቃወም ነው። መንፈስን ማጥፋት ለእርሱ አለመገዛት ወይም ‹‹እምቢ ማለት›› ተብሎ በቀላሉ ሊተረጎም ይችላል። ስለዚህ ጉዳዩ፥ ለፈቃዱ ለመገዛት ፈቃደኛ የመሆንና ያለመሆን ጥያቄ ነው።

የሰይጣን ኃጢአት። በእግዚአብሔር ፍጥረታት መካከል ኃጢአት የገባው በሰይጣን ዓመፅ ነው። ሳጥናኤል አምስት ጊዜ ‹‹እሆናለሁ›› በማለት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደተቃወመ ልብ እንላለን። አምስተኛው በአጭሩ እንዲህ ይላል፦ ‹‹በልዑል እመሰላለሁ›› (ኢሳ. 14፡14)። የመጀመሪያው ዓመፅ በእግዚአብሔር ላይ የተካሄደው በሰይጣንና አብረውት በወደቁት መላእክት አማካይነት ነው። በአዳም በተሠራው ኃጢአት ሳቢያ የዓመፅ ሥራ ወደ ሰው ዘር በመግባት ተስፋፋ። ከመንፈሳዊ ሞትና ከኩነኔ እንደገና ነጻ የወጣው ክርስቲያን በተፈጥሮው ወደ ኃጢአት ከሚያደላው ሥጋዊ ኃይል፥ ከዓለምና ከሰይጣን ኃይል ጋር ፊት ለፊት ይፋጠጣል። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ግንዛቤ ካለ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ድርድር ሊኖር አይችልም። የአገልግሎቱን የተሟላ በረከት ለማግኘት ራስን ለእግዚአብሔር ፈቃድ መስጠት አስፈላጊ ነው። ራስን የመስጠት ሕይወት ቀጥለን እንደምንመለከተው በርካታ ገጽታዎች አሉት።

ራስን የመስጠት የመጀመሪያ ተግባር። አንድ ሰው ለሁለት ጌቶች ሊገዛ ያለመቻሉ እውነታ (ማቴ. 6፡24)፥ ማንኛውም ክርስቲያን የሚጋፈጠው ነገር ነው። አዳኙን ጌታ ሳይቀበሉ አሁን ወዳለው የደኅንነት ደስታ መግባት የማይቻል ቢሆንም፥ ይህ እውነት ግን በመሠረታዊ የእምነት ትምህርትና በልምምድ ከግንዛቤ ሊገባ የሚችል ነው። በዚህ መሠረት ክርስቲያኖች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ተመክረዋል። በሮሜ 6፡13 እንዲህ የሚል ምክር ይገኛል፦ ‹‹ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።››

በመጀመሪያ ‘‘አቅርቡ’’ የሚለው ቃል በአሁን ጊዜ ‘ፓሪስታነተ’ [‘paristanete’] ሲሆን ትርጉሙም፦ ‘‘ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ’’ የሚል ነው። ቋሚ የኃጢአተኛነት ልምምድን ማቆም እንደሚገባ ያሳያል። ከዚህ ጋር ሲነጻጸር ኃላፊነት የተሰጠው ምክር፥ ራስን ለእግዚአብሔር ስለማቅረብ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ‘ፓራስቴሳተ’ [‘parastesate’] የሚለው የግሪኩ ቃል ‘የኤሪስት’* ጊዜን ያመለክታል። ይህ ግሥ ‘‘ወዲያውኑ ራስን ለእግዚአብሔር የመስጠትን አሳብ’’፥ ማለትም የወደፊት ወቅትን መስጠት እንደማያስፈልግ ያሳያል። ክርስቲያኖች በበረከት የተሞላና ውጤታማ የሆነ ኑሮን ለመኖር ያለ ቀን ቀጠሮ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው እንዲሰጡ ተመክረዋል። (ይህ ራስን የመስጠት አሳብ መሠረታዊነት ልክ ለደኅንነት ሰዎች እምነት የሚያስፈልጋቸውን ያህል ነው።) በሮሜ 12፡1 ደግሞ ጳውሎስ ‘‘ራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን እንድንሰጥ’’ ያዛል። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ከላይ ያየነውን ቃል በመጠቀም ክርስቲያኖች በማመከር ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ያሳስባል። ሕይወትንና ፈቃድን ለእግዚአብሔር ምሪት አሳልፎ መስጠት በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ቅድመ ሁኔታ ነው። ራስን የመስጠት የመጀመሪያው ተግባር ፈቃድን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ መስጠት ሲሆን፥ በየትኛውም ሁኔታ የሚገኝ የፈቃድ ግጭት ጥያቄ አይደለም።

ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር ይህን ጉዳይ በዚህ መልኩ አጠር አድርጎ አጠቃሎታል፦ ‘‘ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራስን የመስጠት ጉዳይ በአንድ ልዩ ተግባር የሚገለጥ አይደለም፤ ይልቁንም ሕይወትን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ተገዥ ማድረግ ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆን ማለት ትእዛዛቱን ለመፈጸም ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው። እርሱ እንድናደርግ የሚፈልግብንን ነገር ከማወቃችን በፊት እንኳ ፍጹም እንደሆነ አድርገን ፈቃዱን መቀበል ማለት ነው። ስለዚህ አንድን የተለየ ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ የመሆን ጥያቄ አይደለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር የፍቅር ልብ የተሸለ በሚመስል መንገድ መቼም ይሁን የት፥ እንዴትም ይደረግ በምን፥ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የመፍቀድ ጥያቄ ነው። ተለምዶአዊና

* የግሪክኛ ግሥ ብዙ ጊዜያት አሉት። እያንዳንዱ ጊዜም ተናጋሪው ስለ ድርጊቱ ዓይነት ያለውን አመለካከት፦ ማለትም ድርጊቱ በመፈጸም ላይ ያለ፥ ወይም የተፈጸመ፥ ወይም ያልተወሰነ መሆኑን ያመለክታል። የአሁን ጊዜ ዋና አገልግሎት የማያቋርጥ ወይም በአሁኑ ጊዜ በመከናወን ላይ ያለ ድርጊትን ለመግለጥ ነው። በሌላ በኩል የኤሪስት ጊዜ አንድ የሆነ ድርጊት መፈጸሙን ብቻ የሚያመለክት ነው። ድርጊቱ ምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ወይም መቼ ተፈጽሞ እንደነበር ግን አይገልጥም። የኤሪስት ጊዜ ዋና አሳብ መላውን ድርጊት በአንድ ቅፅበት በሚያስቀምጥ ፎቶግራፍ ይመሰላል።

ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ በአባቱ ላይ እምነት ያለው ልጅ የአባቱ ፈቃድ፥ አሠራርና ምንነት ባይገለጥለት እንኳ፥ ለመታዘዝ ፈቃደኛ እንደሚሆን ማለት ነው።''

ያለማቋረጥ ራስን የመስጠት ሕይወት። ራስን የመስጠት ጉዳይ፥ በመጀመሪያው እርምጃ የሚያበቃ ሳይሆን፥ የልምምድና የመገለጥ ጉዳይ ነው። የመጀመሪያው ተግባር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመታወቁ በፊት በእምነት መቀበል ነው። የመንፈስ ቅዱስን ምሪት፥ የቃሉን ቀጥተኛ ትምህርትና የእግዚአብሔርን ሥራ በመለማመድ ረገድ ከውስጣዊው ሰው ጋር ሁልጊዜ ትግል አለ። ይህን አስመልክቶ ነው ''መንፈስን አታጥፉ'' የሚለው ቃል ተግባራዊ የሚሆነው። ማጥፋት የሚለው ቃል በአሁን ጊዜና በትእዛዝ መልክ ነው የተጻፈው። ስለዚህ ''መንፈስን አታጥፉ'' የሚለው ትእዛዝ መንፈስን ለማጥፋት አትነሣሡ፥ ወይም መንፈስን ማጥፋት ለጀመሩት መንፈስን ማጥፋታችሁን አቁሙ ማለት ሊሆን ይችላል። አማኞች እራስን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ መስጠትን በተመለከተ የመጀመሪያውን አቅጣጫ እንዲከተሉ የተሰጣቸው ምክር ነው። ጥሪው እንደገና ራስን የመስጠት ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ በላያችን የመሠልጠን መብት እንዳለው የመገንዘብ ጉዳይ ነው። አማኙ ሕይወቱንና ፈቃዱን ለርሱ አስገዝቷልና መንፈስ ቅዱስን ሊቃወመው አይገባም።

ራስን ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር መስጠት ከፈቃዱ ጋር በተለያየ አቅጣጫ የሚኖርን ግንኙነት ያካትታል። ራሱን የሰጠ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ልዩና አስደናቂ ግንኙነት አለው። አንድ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶች በሚገባ እየተረዳ ሲመጣና፥ ሕይወቱም በእነዚህ እውነቶች ሲመራ፥ ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት የመስጠቱ ጉዳይ የሚያስደስትና ቀላል እየሆነ ይመጣለታል። ለእግዚአብሔር ቃል ራስን አሳልፎ የመስጠትን ነገር መቃወም ወይም ፈቃደኛ አለመሆን፥ የመንፈስ ሙላትን የሚያግድና መንፈስን የሚያጠፋ መሆኑ ግልጥ ነው።

መንፈስን ማጥፋት እርሱ ከሚሰጠው ምሪት ጋር በጣም የተገናኘ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግልጥ መመሪያ የማይሰጥባቸው፥ ግን ውሳኔ ልናደርግባቸው የሚገቡ ብዙ መንፈሳዊ ጉዳዮች አሉ። የቅዱሳት መጻሕፍት አጠቃላይ እውነትም ከአንድ የተለየ ሕይወትና ሁኔታ ጋር ሊዛመድ ይገባል። ይህን እውነት በሚመለከት የእግዚአብሔር ቃል መመሪያን፥ መንፈሱ ደግሞ ትእዛዝን ይሰጣል። ይህ እጅግ ውድ የሆነ የአማኝ መብትና የልጅነቱ ምልክት ነው (ሮሜ 8፡14)። ይህን ማስረጃ መቃወም መንፈስን ወደ ማጥፋት ያደርሳል። ምሪት በተለያየ መልክ የሚከናወን እንጂ፥ ቋሚ የሆነ ሥርዓትን የሚከተል አይደለም። መንፈስ

ቅዱስ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለተለያዩ ሰዎች ይሰጣል። ምሪት ብዙ ጊዜ ከአገልግሎት ጋር የተያያዘና እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ሰው ራሱን ለመምራት በሚያስችለው ሁኔታ የተፈጠረ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ምሪት የሚደገፍ ነው። መንፈስ ቅዱስ በእስያና በቢታንያ ወንጌል እንዳይሰብክ ጳውሎስን እንደከለከለውና በጓላ ወደዚሁ ሥራ እንደመራው፥ በቃሉም አገልግሎቱን እንደባረከ ሁሉ፥ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ተግባራትን ይከለክላል (ሐዋ. 16፡6-7፤ 19፡10)። ለውጤታማ አገልግሎትና በማስተዋል ለሚወሰድ እርምጃ በመለኮታዊ ምሪት ላይ መደገፍ፥ እንዲሁም ሥርዓትን መከተል አስፈላጊ ነው። የበረከቱ ሙላት የሚገኘው ከመለኮት በሚሰጥ መንገድ ሲኬድ ብቻ ነው።

ራስን መስጠት ከእግዚአብሔር ቸርነት ጋር የተዛመደና የልባችንን ተፈጥሯዊ ፍላጎት የሚጻረር ነው። ስለዚህ ከሰው አመለካከት አንጻር ውጫዊ ገጽታው ከመልካም ይልቅ ክፉ ይመስላል። የ"ሥጋ መውጊያ" ባሕርይ ምንም ይሁን ምን በእምነት፥ በፍቅርና በእግዚአብሔር ጥበብ ተቀባይነት ማግኘት አለበት። መንፈስን ሳያጠፋ መኖር የሚፈልግ አማኝ፥ የራስን ፍቃድ የማስገዛትን ሕይወት ጣፋጭነት በትክክል ሊረዳ ይገባል። በሥቃይ ውስጥ ያሉ ቅዱሳን ሌሎች ሊያውቁት የማይቻላቸውን ጣፋጭ ምስክርነትና የመንፈስ ሙላት ሲገልጡ የምንሰማቸው ለዚህ ነው። ስለዚህ ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት ለቀጥተኛ ቃሉ ትምህርት መገዛትን፥ ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት መታዘዝንና ቸርነት የተሞላ ሥራውን በእምነት መቀበልን ያጠቃልላል። እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ በመኖር የሚከናወኑ ራስን የመስጠትና መንፈስን ያለማጥፋት የዕለት ከዕለት ልምምዶች ናቸው።

የክርስቶስ ታላቅ ምሳሌነት። ብዙ ጸሐፊዎች እንደሚያመለክቱት ክርስቶስ ራሱ የመንፈስ ሙላት ያለማቋረጥ የተገለጠበት ታላቅ ምሳሌያችን ብቻ ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን በአጠቃላይ ያስገዛ ነው። በፊልጵስዩስ 2፡5-11 ያለው ክፍል የጌታችንን ድልና ክብር የሚገልጥ ብቻ ሳይሆን፥ ራሱን ለመስቀል ሞት ታዛዥነት እስከ ማስገዛት ድረስ ዝቅ ማድረጉን ይጨምራል። ክርስቶስ፥ እግዚአብሔር የመረጠውን ነገር ለመሆን ፈቃደኛ ሆነ፦ "የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ።" እግዚአብሔር ወደመረጠው፥ እርሱን ወደማይቀበለውና ወደሚሰቅለው ኃጢአተኛ ዓለም ለመምጣት ፈቃደኛ ሆነ። እግዚአብሔር የመረጠውን ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ ነበር፦ "እስከ መስቀል ሞት ድረስ እንኳ የታዘዘ ሆነ።" የጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ትግል፦ "ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ" በሚልና እጅግ ሰፊ አሳብ በያዘ ቃል ቀርቧል (ሉቃስ 22፡42)። የህን መሰሉ ባሕርይ በእንጋፋ ክርስቲያኖች

ሕይወት እንኳ የተከሠተው በመጠኑ ነው። ‘‘የክርስቶስ አሳብ’’ ያለው ክርስቲያን፥ ክርስቶስ በሕይወቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደፈጸመ ሁሉ ራሱን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሰጠ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ለማግኘት ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት የግድ ይሆናል።

2. መንፈስን አታሳዝኑ

ፍቻ። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ፥ ቅዱስ እንደሆነና አካላዊ ሕልውና እንዳለው ይመሰክራል። የዚህ ቅዱስ አካል በአማኙ ሕይወት ውስጥ ማደር፥ ያን ሰው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያደርገዋል። በምንም ሁኔታ ቢሆን የኃጢአት መኖር የእግዚአብሔርን መንፈስ ያሳዝነዋል። በዚህ መሠረት ክርስቲያን ‘‘ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ’’ ተብሎ ሲመከር (ኤፌ. 4፡30)፥ የመንፈስ ቅዱስ ተጻራሪ የሆነ ነገር በሕይወቱ እንዳይኖር መጠየቁ ነው። መንፈስ ቅዱስን ከሚያሳዝኑ ነገሮች አንዱ ኃጢአት መሆኑ ይታወቃል።

መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ብዙ ነገሮችን ያካትታል። ይህም ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ያልሰጡ ክርስቲያኖች መለያ ነው። የመጀመሪያው መንፈስ ቅዱስን ማጥፋት ሲሆን፥ ይህም አመራሩን ለመከተል እምቢ ማለትና ፈቃዱን መቃወም ነው። መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን የደኅንነት ጉዳይ አይደለም፤ ደኅንነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚሆን ነገር ነውና። ሁልጊዜ የመንፈስ ቅዱስን አመራር መቃወም ከእግዚአብሔር ፈቃድ መራቅን ያመጣል። አገልግሎቱን እስከተቃወምን ድረስ በሙላት ሊባርከንና ሊመራን አይችልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ‘‘የእግዚአብሔርን መንፈስ ማሳዘን’’ ተብሎ የተጠቀሰው ይህ ነው።

የእግዚአብሔርን መንፈስ የማሳዘኑ እውነታ በክርስቲያን ልምምድ ውስጥ ይገለጣል። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ማጣትና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አለማፍራት፥ የማያምኑ ሰዎችን አእምሮ የያዘ ሲሆን፥ የዚህ አንዳንድ ሁኔታ የአማኙንም ሕሊና ሊውጠው ይችላል። በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔርን መንፈስ ያሳዘኑ ክርስቲያኖች አኗኗር ልክ የማያምን ሰው እንደሚኖረው ይሆን ይሆናል።

ይሁን እንጂ ልምምድን በሚመለከት መሳሳት ሊኖር ይችላል። የአካል ሁኔታ በመንፈሳዊ ልምምድ ላይ ብዙ ጊዜ ተጽእኖ ሊፈጥር እንደሚችል ጠንቃቃ ጸሐፊዎች ይጠቁማሉ። የራበውና የደከመ ወይም የታመመ ሰው በኃጢአት ውስጥ ሳይኖር፥ የተትረፈረፈ መንፈሳዊ ሕይወት ማሳየት ይሳነው ይሆናል። ነገሩ በክርስቲያኑ ዘንድ የተሸሸገ ኃጢአት

ሊሆንም ይችላል። መንፈስ የሚያዝነው ግልጥ በሆነ ኃጢአት እንጂ፥ በኃጢአታዊ ተፈጥሮ ላይ አይደለም። መንፈሳዊ ኅብረትና ኃይል እንደጎደለው የተሰማው አማኝ መነሾውን በጸሎትና ቃሉን በማጥናት የመፈለግ ኃላፊነት አለበት። እኛ ወደ እግዚአብሔር ከቀረብን፥ እግዚአብሔር ወደ እኛ መቅረቡ ምንጊዜም እውነት ነው።

ለመንፈስ ቅዱስ ማዘን ምክንያቱ ኃጢአት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑ ነገሮች ግልጥ እንደሆኑ ሁሉ መፍትሔውም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ ቀርቧል።

መፍትሔው ኃጢአትን መናዘዝ ነው። ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አስመልክቶ በሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዘንድ የሚያስገርም አለመረዳት አለ። ካይፐር በጻፈው ታላቅ ሥራ ውስጥ እንኳ በኤፌሶን 4፡30 ያለው አሳብም ሆነ በ1ኛ ዮሐንስ 1፡9 ያለው ኃጢአትን የመናዘዝ አሳብ በሚገባ አልተጠቀሰም። ስለ መንፈስ ቅዱስ ከተካሄዱ አብዛኛዎቹ ጥናቶች ማረጋገጥ እንደሚቻለው፥ ይህንን እውነት ቸል ማለት በጣም የተለመደ ሆኖ እናገኛለን። እጅግ የሚያሳዝነው ጉድለት የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ከአማኝ መንፈሳዊ ሕይወት ጋር አለማዛመድና መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ናቸው። እነዚህም ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኙትን ሙሉ በረከቶች ያግዳሉ። አሁንም ቢሆን ለመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ከሁሉም የተሻለ ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ይህን ቃል በጥንቃቄ የሚያነቡ ሁሉ ለችግሮቹ መፍትሔ ያገኛሉ።

መንፈስ ቅዱስን የማሳዘን መፍትሔው ተናዘዝ በሚል ቀላል ቃል ተገልጧል። በ1ኛ ዮሐንስ 1፡9 መሠረት፡- ‘‘በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፥ ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።’’ ይህ ቃል ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ኅብረትና በተሰጣቸው መገለጥ ውስጥ መካከለኛ ስፍራ ይዞ የሚገኝና (1ኛ ዮሐ. 1፡5-2፡2)፥ ለነሱ የተሰጠ መልእክት ነው። መልእክቱ ለኃጢአታቸው መሥዋዕት የሆነ ክርስቶስን ላልተቀበሉና ላልዳኑ ሰዎች አይደለም። ለነሱ የሚሰጣቸው ምክር፥ ‘‘እመኑ’’ በሚል አንድ ቃል ይጠቃለላል። በሚያድን እምነት ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለ የተባረከ ግንኙነት የገባ ክርስቲያን የሚቀረው ነገር ቢኖር፥ ይህን ኅብረት እንዲቀጥል ማድረግ ነው። 1ኛ ዮሐንስ ውስጥ የሚገለጠው ነገር ይህ ነው። ይቅር የመባል ተስፋ ከጽድቅ ወይም ከበደለኛነት ጥያቄ ጋር መምታታት የለበትም። ከፍርድ አንጻር ስናየው፥ የኃጢአት ጉዳይ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚያድን እምነት በተገለጠ ጊዜ አብቅቷል። ይሁን እንጂ የኃጢአት በክርስቲያን ሕይወት

ውስጥ መኖር ለዚህ ኅብረት እንቅፋት ከሆኑ ነገሮች አንዱ ሆኗል። የክርስቲያን የእግዚአብሔር ልጅነት በምንም ሁኔታ የማይነካ ቢሆንም፥ በኃጢአት ሳቢያ የደስተኛ ቤተሰብ ኅብረት መዛባቱ ግን አይቀርም። ከእግዚአብሔር ጋር የኅብረት ተሐድሶ ከመሆኑ በፊት ከሰው በኩል ንስሐ መኖር አለበት። መንፈስ ቅዱስ የሚያዝንበት ነገር እንደ ኃጢአት ተቆጥሮ ልንናዘዘው ይገባል። ንስሐ ክርስቲያን እንደ ዳኛ ሆኖ፥ በራሱ ኃጢአት ላይ መፍረድን፥ ኃጢአቱን መኮነንና ለሰማያዊ አባቱ መናዘዝን ያካትታል (1ኛ ቆሮ. 11፡31)።

ኃጢአትን ለሚመለከት ችግር እንዲህ ያለው አቀራረብ በእግዚአብሔር ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት እንደሚኖረው ተገቢ ዋስትና ተሰጥቷል። ይህ ለኃጢአት ዋጋ የመክፈል ወይም በራስ ላይ የሥነ-ሥርዓት ቅጣት የመፈጸም ጥያቄ አይደለም። እንዲሁም እግዚአብሔር ንስሐን በሚቀበልበት ጊዜ ቀላል አባታዊ ቅጣት መቅጣቱም አይደለም። ጠቅላላው ድርጊት ክርስቶስ በፈጸመው ሥራ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ ቅጣትን የሚመለከተው ጥያቄ በዚህ አመለካከት ውስጥ ጨርሶ የለም። ምሕረትን የሚያሰጠው ዋጋ ተከፍሎ ያለቀ ጉዳይ ነው። በዚህ መሠረት እግዚአብሔር አብ ኃጢአትን ይቅር ለማለት የታመነና ጻድቅ እንጂ፥ ቀለል ባለ ቅጣት የሚቀጣና ምሕረት የሚያደርግ ብቻ አይደለም። አንድያ ልጁ ለኃጢአት በቂ ዋጋ ባይከፍል ኖሮ፥ ይቅርታን የሚሻ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይቅርታ አያገኝም ነበር። በዚህ መሠረት ሰው የሚፈለግበት ነገር እጅግ ቀላል ነው።

ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙ ሰዎች የተሰጠው ተጨማሪ ተስፋ ብዙ ጊዜ በቂ ትኩረት ሳያገኝ ይታለፋል። ከዚህ ቀደም ለተፈጸሙ ኃጢአቶች ይቅርታ ከማግኘት ሌላ "ከዓመፃ ሁሉ የመንጻት" ተስፋም ተሰጥቷል። ይህ ተስፋ ለኃጢአት ሙሉ በሙሉ መወገድ የተሰጠ መተማመኛ ወይም ክርስቲያን ወደፊት ኃጢአት እንዳይሠራ ሊያደርገው የሚችል ነገር ባይሆንም፥ ተጨማሪ ኃጢአትን ለመከላከል እግዚአብሔር የሚሠራውን ሥራ በሚመለከት ደግሞ መገለጥን የሚያካትት መሆኑን ለማየት እንችላለን። ንስሐ የመቀደስ ኃይል ነው። ጥፋተኛነቱን በመረዳት በእግዚአብሔር ፊት በኃጢአቱ እጅግ የተጸጸተና የክርስቶስ ውድ ደም እንዲያነጻው ልመና ያቀረበ ክርስቲያን፥ በዚህ አሠራር ወደ ኃጢአት መንገድ የመመለስ አዝማሚያው በጣም ዝቅተኛ ነው። የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ከተመለሰ በኋላ፥ ከአባቱ ቤት ውጭ የነበረውን ኑሮ እንደገና ሲፈልግ አናየውም። ንስሐ ድካምን አውቆ መለኮታዊ ኃይልን በመፈለግ ለውጤቱ በእግዚአብሔር ላይ የመደገፍ ተግባር ነው። ይህ ጉዳይ በመንፈስ መመላለስ

በሚለው ርእስ ሥር በተብራራው መሠረት በኃጢአት ላይ ድል ማግኘትን በሚመለከት እጅግ አስፈላጊነት ያለው እውነት ተደርጎ ቀርቧል።

ንስሐ ሙሉ በሙሉ የሰው ኃላፊነት ነው። በ1ኛ ዮሐንስ 2፡1-2 ያለው መገለጥ የሚያመለክተው፥ በኃጢአት ምክንያት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚታየው ነገር ወዲያውኑ በመለኮት በኩል የሚስተካከል መሆኑን ነው፡- ‘‘ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህንን እጽፍላችኋለሁ፥ ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰረያ ነው፥ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለም ሁሉ ኃጢአት እንጂ።’’ ክርስቲያን ኃጢአትን በሚያደርግበት ጊዜ፥ ክርስቶስ ወዲያውኑ የጠበቃነትን ሥራ በመጀመር የራሱን ጽድቅና የተሟላ ተግባር ይዞ በኃጢአተኛው ምትክ መቅረቡ የተባረከ እውነት ነው። በመለኮት በኩል ያለው ነገር ምንጊዜም የሚለወጥ አይደለም። አማኝ ከመለኮት ጋር ያለውን ኅብረት በንስሐ ማስተካከልን እስካልተረዳ ድረስ፥ ይህ እውነት የማይገነዘበው ነገር ሆኖ ይቆያል። የኤሌትሪክ መሥመር ከተቋረጠ የኤሌትሪክ ብርሃን እንደማይተላለፍ ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረትም እንዲሁ ነው። ሁልጊዜ ግንኙነቱ የሚቋረጠው፥ ከእኛ ከሰዎች በኩል መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጥ ይናገራሉ። የተቋረጠው ግንኙነት በፍጥነት ተስተካክሎ በኅብረቱ የሚገኘው ሙሉ ኃይልና በረከት እንደገና የሚታወቀው ኃጢአትን በመናዘዝ ነው። በኃጢአት ለረጅም ጊዜ የኖረ ክርስቲያን፥ ከመታደሱ በፊት ራሱን የመመርመሪያ ጊዜ የሚያስፈልገው ቢሆንም፥ መፍትሔው በምንም አኳኋን ይሁን ያው ንስሐ ነው።

ያለማቋረጥ በኃጢአት ስለመኖር የተሰጠ ማስጠንቀቂያ። የሰው ልጅ ሥቃይ አሳሳቢ የሆነው ለሥነ-መለኮት ሊቃውንትና ለፈላስፎች ብቻ ሳይሆን፥ በመጽሐፈ ኢዮብ እንደተገለጠው ለቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችም ጭምር ነው። በመሠረቱ የሰው ዘር መከራ የሚቀበለው በአዳም ኃጢአት ምክንያት ነው። በዚህ ሳቢያ በሰው አካል ላይ ሕመም መጣ፥ ስሜቱ ተመረዘ፥ የኃጢአት ተፈጥሮ የሚተላለፍ ስለሆነ፥ ፍጥረት ሁሉ ከመርገም በታች ሆነ። የነፍስ መዳን እነዚህን የሥቃይ መሠረታዊ ምክንያቶች ሁሉ አያስወግድም። በዕብራውያን 12፡5-6 እንደተገለጠው አባት የቅጣት እጁን የሚያሳርፈው በልጆቹ ሁሉ ላይ ነው፡- ‘‘ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፤ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል።’’ የእግዚአብሔር ልጅ በቅጣት ይሠለጥናል፤ እውቀት ያገኛል፥ ኃጢአትን

ይከላከላል፥ ጠቅላላ ሕይወቱም ለበለጠ ጥቅም የተዘጋጀ ይሆናል። ታላላቅ ክርስቲያኖች በከፍተኛ መከራ ውስጥ ማለፋቸው እውነት ነው።

ይሁን እንጂ በተገቢ ሁኔታ እራስን በማስተካከልና ኃጢአትን በመናዘዝ ቅጣቶችን መከላከል እንደሚቻል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡31-32 እንዲህ ይላል፦ ‘‘ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር። ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሠጻለን።’’ በእነዚህ ቀላል ቃላት መለኮታዊ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። ክርስቲያን ራሱን ለማስተካከልና ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ እንዲናዘዝ ጊዜና ዕድል ተሰጥቶታል። ይህን ዕድል ሳይጠቀምበት ቢቀርና በኃጢአት ውስጥ ቢቆይ፥ እግዚአብሔር አብ ጣልቃ ይገባል። በመቅጣት አማካይነት ሥነ-ሥርዓት ያስይዘዋል። ከዚያ በፊት ለመናዘዝ ፈቃደኛ ያልሆነበትን ኃጢአት እንዲናዘዝ ያደርገዋል። በዚህ ምክንያት በኃጢአት መጫወት አደገኛ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት በቀጥታ ይናገራሉ። የሕይወት ልምድም ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ያረጋግጥልናል። ለዚህ ነው ክርስቲያኖች ሁሉ አለመናዘዝና በኃጢአት መቀጠል ጠቃሚ እንዳልሆነ ሊመሰክሩ የሚችሉት። ኪሳራው በማንኛውም ረገድ ቢሆን ከፍተኛ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት ካለመኖሩ የተነሣ ከጎብረቱ የሚገኘው በረከትና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን፥ የልብ ጎዘንና ፈተና ጭምር ይከተላል። ጌታውን በመካዱ ምክንያት መራራ ልቅሶ ያለቀሰው ሐዋርያ በመልእክቱ እንደጻፈው፦ ‘‘ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ። ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል’’ (1ኛ ጴጥ. 4፡14-15)።

3. በመንፈስ ተመላለሱ

የዚህ ክፍል ጉዳይ፥ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ የሚያከናውነው ሥራ ብቻ ሳይሆን፥ ለአንድ ሰፊ ጽሑፍ መሪ አሳብን የሚሰጥም ነው። በዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ በቂ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ ግንዛቤና እጅግ አደገኛ የሆኑ ኑፋቄዎች ሲነሡ ታይተዋል። ቢሆንም ትምህርቱ ሙሉ በሙሉና በጥልቀት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነው። ቀደም ሲል በመንፈስ ስለተሞላ ሕይወት የቀረቡት ሁለት ትእዛዞች በባሕርያቸው አሉታዊ ናቸው። የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ከፈለግን፥ መንፈስ ቅዱስን እንቢ ማለት፥ ማጥፋትና በመደጋገም እርሱን ማሳዘን

የለብንም። በመንፈስ ተመላለሱ የሚለው ሦስተኛ መመዘኛ ግን የእውነቱ አዎንታዊ ገጽታ ሲሆን፥ በይዘቱም ከሌላው ይልቅ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ፍቻ። ‘‘በመንፈስ ተመላለሱ’’ (ገላ. 5፡16) የሚለው ትእዛዝ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መኖር እጅግ አስፈላጊ መሆኑንና አሁኑኑ መፈጸም ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ምክር እንደሆነ እንገነዘባለን። ‘ኒዩማቲ ፔሪፓቴተ’ [‘pneumati peripateite’] የሚለው የግሪክ ቃል ቀላልና ቀጥተኛ ነው። ‘ኒዩማቲ’ በመንፈሱ ውስጥ ከማለት ይልቅ በመንፈስ ተብሎ ሊተረጎም የተገባ ነው። በገላትያ 5፡5 እንደተጻፈው ቃሉ የሚያመለክተው ሌላ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስን ራሱን ነው። ቻርልስ ጄ. ኤሊካት [Charles J. Ellicott] ስለ ገላትያ 5፡5 አሳብ ሲሰጥ፥ ጥቅሱ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገር መሆኑን በሌሎች ተመሳሳይ ሁኔታዎች እናረጋግጣለን ብሏል።

ስለዚህ አተረጓጎሙ እጅግ ግልጥ ነው። ክርስቲያኖች ከሥጋ ምኞት ለመራቅ ከፈለጉ፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መመላለስ አለባቸው። ‘ፔሪፓቴተ’ የሚለው የግሪክኛ ቃል በመንፈስ መመላለስ ያለማቋረጥ ሊደረግ የሚገባ ነገር መሆኑን ያሳያል። አሳቡ በመንፈስ ‘‘መመላለሳችሁን ቀጥሉ’’ የሚል ስሜት አለው። ያለማቋረጥ በመንፈስ መመላለሳችንን ስንተው ወዲያውኑ መንፈሳዊ ውድቀት በሕይወታችን ይከሠታል።

የክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት መለኪያ። የክርስቲያንን በከፍተኛ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ መመላለስ አስፈላጊነት ከመጽሐፍ ቅዱስ በምንመለከትበት ጊዜ የጉዳዩ ጠቃሚነት ይበልጥ ግልጥ ይሆንልናል። አስራኤላውያን እንዲኖሩበት በሕግ የተሰጣቸው የሕይወት ደረጃ ከፍተኛ ነበር። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስም ሆነ ለክርስቲያን ሁሉ የተሰጠው ችሎታ ስላልነበራቸው፥ ከክርስቲያን የሕይወት መመዘኛ አንጻር ሲታይ፥ የኖሩት ሕይወት ክርስቲያን ከሚጠበቅበት ለየት ያለ መለኪያ ነበረው። ወደፊት የሚመጣው የክርስቶስ መንግሥት መለኪያም እጅግ ከፍተኛ ቢሆንም፥ መመዘኛዎቹ የወጡት ግን የተለዩ ሁኔታዎች እጅግ ከተመቻቹላቸው በኋላ ነው። በዚያን ጊዜ ሰይጣን ይታሰራል፥ ክርስቶስ በዙፋኑ ላይ ይሆናል፥ በአጠቃላይ በዓለም ሁሉ ሰላምና ጽድቅ ይሰፍናል፤ ያም ቢሆን የአኗኗሩ ሁኔታ በባሕርዩ ሕጋዊ ይሆናል። ለዚህ ስፍረ-ዘመን የሚሆኑ የአኗኗር መለኪያዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሐዋርያት ሥራ፥ በመልእክቶችና በአንዳንድ የወንጌል ክፍሎች ይገኛሉ። እነዚህን የአኗኗር መለኪያዎች ስንመረምር፥ በመንፈስ የሚራመዱ ሰዎች ብቻ ሊደርሱበት የሚቻላቸው መሆኑን እንመለከታለን። በሙሴ ሕግ የሚገኙት አንዳንድ ትእዛዛት ከእነዚህ እኩል የማይታዩ የሕይወት መመዘኛዎች ቢሆኑም፥ በመካከላቸው ልዩነት መኖሩ ግን ግልጥ ነው። የሙሴ ሕግ በሰዎች ላይ ፍርድን

ለማምጣት ወይም ሰዎችን ለመኮነን የታቀደ ነበር። በዚህ ዘመን ያሉ የጸጋ የሕይወት መለኪያዎች ግን ሰዎችን ለመቀደስ ታቅደዋል። ሰው በሕግ ሊፈጽመው ያልቻለውን ነገር በጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይፈጽመዋል። በዚህ እውነት ውስጥ ክርስቲያን፥ ቀደም ባሉት ስፍረ-ዘመናት ቅዱሳን ባልነበራቸውና ከእግዚአብሔር በነጻ በተገኘው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመኖር ኃላፊነት እንዳለበት ይታያል።

እነዚህን የሕይወት መለኪያዎች በአጭሩ ማጥናት ጉዳዩን በበቂ ሁኔታ ግልጥ ያደርገዋል። ክርስቶስ እንደወደደን እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ ታዘናል (ዮሐ. 13፡34፤ 15፡12)። "አእምሮን ሁሉ" እንኳ ለክርስቶስ መማረክ አለብን (2ኛ ቆሮ. 10፡5)። "ሰውን ሁሉ ልንታገሥና መልካም የሆነውን ለማድረግ ልንተጋ" ያስፈልጋል (1ኛ ተሰ. 5፡14-15)። "ሁልጊዜ ደስ ሊለን ሳናቋርጥ ልንጸልይና በሁሉ ልናመሰግን ይገባል" (1ኛ ተሰ. 5፡16-18)። ለሥጋ ጨርሶ የማይቻሉትን ተመሳሳይ የሕይወት መለኪያዎች መዘርዘር ይቻላል። ሰው ሊያደርገው የማይቻለው ነገር በመንፈስ ለሚመላለስ ሁሉ ይቻለዋል። በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ፍጹም አስፈላጊነት ከልምምድም ሆነ ከመገለጥ ታላላቅ እውነታዎች አንዱ ነው።

የዓለም አሠራር ኃይል። የክርስትና ሕይወት የዚህ ዓለም የተበላሸ አኗኗር ከሚያስከትለው የአመለካከት ተጽዕኖ አንጻር ሲታይ፥ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል። ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ የጸለየው ከዓለም እንዲወጡ ሳይሆን፥ በዓለም ከክፋት እንዲጠበቁ ነበር (ዮሐ. 17፡15)። በሥጋ በምድር ቢሆኑም አሳባቸው ሁሉ ሰማያዊ እንዲሆን ጸለየላቸው። ቅዱሳት መጻሕፍት የዓለምን አስጸያፊነት በግልጥ ይናገራሉ። ከዓለም ጋር ወዳጅነትን መፍጠር፥ መንፈሳዊ ምንዝርና ተብሎ የተጠራ ሲሆን፥ የዓለም ወዳጅ መሆን ደግሞ የእግዚአብሔር ጠላት መሆን ነው ተብሏል (ያዕ. 4፡4)። ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ይሽራል (1ኛ ዮሐ. 2፡15)። ከዓለም ጋር መመላለስና ዓለምን መምሰል ተከልክሏል (ሮሜ 12፡2፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14)። ከሰው ልጅ ነፍስ ጋር ሲወዳደር የዓለም ሁሉ ዋጋ ኢምንት እንደሆነ ተጽፏል (ማቴ. 16፡26)። ዓለማዊነት ክርስቲያን እንዳያፈራ እንደሚያደርገውና ውስጡ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያንቀም ተጽፏል (ማቴ. 13፡22)። ዓለም በክርስቶስ መስቀል እንደተሰቀለ ተገልጧል (ገላ. 6፡14)። ክርስቲያን ለዓለም ይመሰከር ዘንድ በዓለም ቢኖርም ዓለም እንድትበርዘው ስለማይፈቅድ ከዓለም አይደለም። ከዚህ ሁሉ አንጻር ሲታይ በእግዚአብሔር መንፈስ ካልሆነ በቀር ብርቱውን የዓለም ኃይል ለማሸነፍ አይቻልም።

የሰይጣን ኃይል። ሰይጣንን ስለሚያስተምረው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በብዙ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች ውስጥ ቸል መባሉ የክርስትናን ሕይወት ደረጃና ኃላፊነት ይበልጥ አስቸጋሪ አድርጎታል። ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ከሁሉ የሚልቅ ኃይል ያለው ሰይጣን ሲሆን፥ የክርስቲያን ውጊያም ከርሱ ጋር ነው። ጳውሎስ ከልምምድም ሆነ ከመገለጥ እንደተረዳው፥ ''መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ'' (ኤፌ. 6፡12)። ሰይጣን፥ የማያምኑ ሰዎች የወንጌልን ብርሃን እንዳያዩ አሳባቸውን ያሳውራል (2ኛ ቆሮ. 4፡4)። ለዚህ ነው የማያምኑ ሰዎች ወደ እምነት ይመጡ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊ የሚሆነው። ክርስቲያኖች ቀጥሎ ያለው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። ''በመጠን ኑሩ ንቁም፤ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና'' (1ኛ ጴጥ. 5፡8)። በሌላ በኩል ደግሞ ሰይጣን ራሱን የብርሃን መልአክ እንደሚያስመስል መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (2ኛ ቆሮ. 11፡14)። ክርስቶስ ራሱ እንደመሰከረው ሰይጣን ሐሰተኛና ነፍሰ ገዳይ ነው (ዮሐ. 8፡44)። የሰይጣን ኃይል ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ፥ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ስለ ሙሴ ሥጋ ከእርሱ ጋር በተነጋገረ ጊዜ፥ ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ቃል ሊናገረው አልደፈረም (ይሁዳ 9)። የእግዚአብሔር ጠላት የሆነ ሁሉ የቅዱሳንም ጠላት መሆኑንና ከመለኮታዊ ኃይልና ጥበቃ ውጪ በእርሱ ላይ ድል ማግኘት እንደማይቻል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ክርስቲያን በመንፈስ እስካልተመላለሰ ድረስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመኖር የማይችለው በዚህ ጠላት ምክንያት ነው። የሐሰት አባት የሆነው ሰይጣን ራሱ የሌለ አስመስሎ ብዙዎችን እስከማሳመን የሚደርስ ጠላታችን ነው። የዘመኑ ሰው ሰይጣን ነክ ስለሆነ ትምህርት ፍላጎት ከማጣቱ አንጻር ሲታይ፥ በመንፈስ ስለመመላለስ ያለው ግንዛቤ ጥቂት መሆኑ የሚገርም ነውን?

ኃጢአታዊ ተፈጥሮ። እያንዳንዱ ነፍስ በድል ለመኖር በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ ያለበት፥ ከውጭ ባለ ጠላት ብቻ ሳይሆን ከውስጥም ባለ ድካም ምክንያት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት የአዳም ልጆች ሁሉ ከአዳማዊ ተፈጥሯቸው የተነሣ ኃጢአትን የማድረግ ዝንባሌ እንዳላቸው ይናገራሉ። ኃጢአታዊ ተፈጥሮ (ሮሜ 5፡21፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡8)፥ አዳማዊ ተፈጥሮ፥ ሥጋ (ሮሜ 13፡14፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡5፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡1፤ 10፡2-3፤ ገላ. 5፡16-24፤ 6፡8፤ ኤፌ. 2፡3)፥ አሮጌው ሰው (ሮሜ 6፡6፤ ኤፌ. 4፡22፤ ቈላ. 3፡9-10) ወይም ሌሎች አገላለጦችን ስንጠቀም ያላቸው አሳብ የሚያመለክተው ሰብአዊ ተፈጥሮን ነው። ሰብአዊ ተፈጥሮ ነፍስን፥

መንፈስንና ሥጋዊ አካልን የሚጨምረው ነው። ለምሳሌ ኃጢአት የሚለው ቃል በሮሜ 6 እና 7 እንደምናገኘው በነጠላ ቁጥር ሲጠራ ከተግባር ይልቅ የኃጢአት ተፈጥሮን የሚያመለክት ነው። ይህ ነገር ኃጢአት ለማድረግ ለሚፈልግና የሰይጣንን ድምፅ ለሚሰማ፥ በውስጣችን ላለ ክፋት ሁሉ ምንጭ ነው። በመንፈስ የመመላለስን አስፈላጊነት በግልጥ ለመገንዘብ ይህን መሠረታዊ ትምህርት አጥርቶ መረዳት ይገባል።

ከተግባር አንጻር ስናየው ሐሰተኛ የቅድስና ትምህርት ወይም ፍጹምነትን የሚመለከት የተሳሳተ የእምነት ትምህርት መለያዎች ወይም የኑፋቄዎች ሁሉ መነሻቸው፥ ስለ ኃጢአት ተፈጥሮ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሰጡትን ትምሕርት ለመገንዘብ አለመቻል ነው። በአሁኑ የውይይት ክልል የተካተቱትን እውነቶች ሁሉ በጥልቀት ለመመርመር ባይቻልም፥ ዋና ዋናዎቹን መገንዘቡ ግን አያዳግትም።

የፍጹምነት ፅንሰ-ሓሳብ። የፍጹምነት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ በሚያምኑ ሰዎች ዘንድ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ትርጉም የሚሰጠው አይደለም። የዌብስተር [Webster] እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ፍጹምነትን ለሚያመለክተው የእንግሊዝኛው ቃል የሚሰጠው ትርጉም፥ ለሁሉም ክፍሎች የሚስማማ ሳይሆን አይቀርም፡- ‘‘በመሠረታዊ የእምነት ትምህርት አመለካከት ፍጹምነት ሲባል በምድራዊ ሕይወት፥ ያለ ኃጢአት ወደ መሆን ደረጃ መድረስ ይቻላል’’ የሚል ነው። አንዳንድ የፍጹምነት ትምህርት መምህራን፥ ይህን ፅንሰ-አሳብ በፈቃድ በሚሠራ ኃጢአት ብቻ ይወስኑታል። ሌሎቹ ደግሞ ለሚታወቁ ኃጢአቶች ብቻ ያደርጉታል። በዚህ አመለካከታቸው በቸልተኝነት የሚደረግን ኃጢአት ወይም በምንም መንገድ ይሁን በፍጹምነት ውስጥ ጣልቃ ሊገቡ አይችሉም የሚሏቸውን ኃጢአቶች አያካትቱም። የቀሩት የኃጢአት ባሕርይ ራሱ ይወገዳል ይላሉ። የኃጢአትን ባሕርይ በጥንቃቄ መመርመር ግን ትምህርቱ የኃጢአትን መሠረታዊ ነገሮች ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የፍጹምነት ትምህርት አራማጆቹ በያዙት መልክ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጨርሶ የሌለ መሆኑን እንረዳለን።

ብሉይ ኪዳን ውስጥ በርካታ የዕብራይስጥ ቃሎች ‘‘ፍጹም’’ ተብለው ቢተረጎሙም፥ ከአገባቡ እንደምንረዳው ቃሉ የሚያመለክተው በጉዳዩ የተጠቀሱትን ሰዎች ኃጢአት የለሽነት አይደለም (ዘፍጥ. 6:9፤ 1ኛ ነገሥት 15:14፤ 2ኛ ነገሥት 20:3፤ 1ኛ ዜና 12:38፤ ኢዮብ 1:1፥ 8፤ መዝ. 37:37፤ 101:2፥ 6 ወዘተ.)።

በአዲስ ኪዳን ሦስት የግሪክኛ ቃላት ‘‘ፍጹም’’ በሚል የአማርኛ ቃላት የተተረጎሙ ሲሆን፥ ከእነዚህ ሁለቱ ብቻ የፍጹምነትን ትምህርት ከኃጢአት ከመንጻት አሳብ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚያሳዩ ናቸው።

'ካታርቲዞ' ['katartizo'] የሚለው ቃል አንደኛው ሲሆን (ይህ ቃል እንደ ግሥ፥ ስምና ቅጽል ''ፍጹም''፥ ''ፍጹማን''፥ ''መቃናት''፥ ''መሞላት''፥ ''መዘጋጀት'' እና ''መተባበር'' የሚሉ ትርጉሞች ተሰጥቶታል)። ቃሉ ''በነገር ሁሉ የተሞላ መሆን''፥ ''ተገቢ''፥ ''የተስተካከለ'' የሚል አሳብንም አዝሏል። ሌላው የግሪክ ቃል 'ቴሌዮ' ['teleioo'] (''ፍጹም''፥ ''ፍጹማን''፥ ''ፍጹምነት''፥ ''ሙሉ''፥ ''መብሰል''፥ ''መሞላት'' እና ''መሻል'' ተብሎ ተተርጉሟል) ''ወደ ፍጻሜ ማምጣት'' ወይም ''ወደ ግብ ማድረስ'' ማለት ነው። ስለዚህ የቃሉ ትርጉም ''አንድን ነገር የመጨበጥን'' አሳብ የያዘ ነው።

ፍጹምነት ከኃጢአት ጋር በተያያዘ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሦስት መልክ ይገኛል። አንደኛው፥ ስፍራዊ (የመብት ስፍራን የሚመለከት) ፍጹምነት ሲሆን፥ ያም የሁሉም ክርስቲያን መብት መሆኑ ተገልጧል። ዕብራውያን 10፡14 እንዲህ ይላል፦ ''አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን ['ቴቴሌዮኬን'/'tetelioken'] አድርጓቸዋልና።'' ቃሉ የቅርብ ጊዜ ኃላፊ ግሥ ስለሆነ ፍጹምነት ለአንዴና ለመጨረሻ በመፈጸሙ የማይደጋገም መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራው የተሟላ ፍጹምነት ነው። በመሆኑም ስለ ክርስቲያናዊ ሕይወት ጥራት በዚህ ስፍራ የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም። ያለ ኃጢአት የመሆን ነገርም አልተጠቀሰም። ቅዱሳን ሁሉ (አንድ ጊዜ የተቀደሱት) በክርስቶስ የተከናወነው ፍጹምነት ተካፋዮች ናቸው።

ሁለተኛው፥ አንጻራዊ ፍጹምነት፥ በጽሑፉ አገባብ እንደተመለከተው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል። አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ ብስለት እንደ ፍጹምነት ይታያል። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ሲጽፍ፦ ''እንግዲህ ፍጹማን ['ቴሌዮ'] የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ'' (ፊልጵ. 3፡15) ብሏል። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የሚናገረው ያለ ኃጢአት ከሆነ ፍጹምነት ይልቅ፥ ስለ መንፈሳዊ ብስለት መሆኑን ሌላ ስፍራ ከገለጠው ቃል እንገነዘባለን፦ ''አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ'' (ፊልጵ. 3፡12)። ይህ ቁጥር የሚናገረው የመጨረሻውን ፍጹምነት ሲሆን፥ ጳውሎስም አሁን ፍጹም መሆን የሚለውን አይቀበልም። መንፈሳዊ ብስለት ከሥጋዊ እድገት ጋር ሊወዳደር ይችላል። ዳሩ ግን ይህ አሳብ ሙሉ እድገትን የሚያሳይ ቢሆንም ፍጹምነትን ግን አያመለክትም። ፊልጵስዩስ 3፡15 ውስጥ ግን ፍጹምነት እንደተደረሰበት ሆኖ ቀርቧል። በሌሎች ክፍሎች የመንፈሳዊ

ብስለት የተለየ ገጽታ ይታይ ይሆናል። ከታወቀው የእግዚአብሔር ፈቃድ አንጻር በመንፈሳዊ ሕይወታችን የበሰልን እንሆን ይሆናል (ቈላ. 4፡12) [ʻቴሌዮ']፥ ወይ በፍቅር (1ኛ ዮሐ. 4፡17-18) [ʻቴሌዮ']፥ በቅድስና (2ኛ ቆሮ. 7፡1) [ʻቴሌዮ']፥ በትዕግሥት (ያዕ. 1፡4) [ʻቴሌዮ']፥ ‘‘በመልካም ተግባራት ሁሉ’’ (ዕብ. 13፡21) [ʻካታርቲዞ'] የበሰልን ልንሆን እንችላለን። በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ለእንዴና ለመጨረሻ ወደዚህ ስኬታማነት (ፍጹምነት) የመድረስን ነገር ጨርሶ አናይም። ፍጹምነት በተሻለ ሁኔታ ላይ ከመድረስ አንጻር በየወቅቱ የሚታይ ነው።

በ2ኛ ቆሮንቶስ 7፡1፥ ‘‘እንግዲህ ወዳጆች ሆይ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን *ሥጋንና መንፈስን* ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ።’’ እንዲሁም በገላትያ 3፡3፦ ‘‘እንዲህ የማታስተውሉ ናችሁን? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በ*ሥጋ* ትፈጽማላችሁን?’’ በሚሉት ዓረፍተ ነገሮች በሰዋሰው ሥርዓት የአሁን ጊዜን የሚያሳይ አሳብ ስላላቸው፥ መንፈሳዊ ብስለት ከማያቋርጥ እድገት ጋር ተገልጦ እናያለን። በክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ስጦታ ዓላማ፥ ‘‘...ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን [ʻካታርቲስሞን'/ʻkatartis-mon'] እንሆን ዘንድ ነው’’ (ኤፌ. 4፡12)። ይህ በሁሉም ነገር ቅዱሳንን ፍጹም የማድረግ አሳብ ነው። ስጦታዎቹን በመለማመድ በአንጻራዊነት ወደሚገኝ ፍጹምነት ሊደርስ የሚችል የመንፈሳዊ ብስለት ሂደትም ነው። ይህንና ሌሎችንም ክፍሎች አሁኑ ከሚኖረው ያለ ኃጢአት ከመሆን ጋር ለማያያዝ መሞከር፥ አሳቡን ወደ ራስ አሳብ የመጠምዘዝ ተግባር ነው። ይህን የመጠምዘዝ አሳብ፥ ግሪክኛው ቃልና በአጠቃላይም የተገለጡት እውነቶችና የሕይወት ልምምዶች ውድቅ ያደርጉታል።

የዚህ እውነት ሦስተኛ ገጽታ ስለ መጨረሻው ፍጹምነት በሚናገሩ ክፍሎች የተገለጠው አሳብ ነው። ለዚህ ጉዳይ ግልጥ የሆነውን አሳብ የምናገኘው፥ ከላይ በጠቀስነው በፊልጵስዩስ 3፡12፥ ‘‘አሁን ፍጹም እንደሆንኩ አይደለም’’ ሲል ጳውሎስ በተናገረው ቃል ነው። በክርስቶስ ያለው ስፍራ ፍጹም ቢሆንም እንኳ፥ ጳውሎስ የተጠቀመው ግሥ (ʻቴቴሌዮማይ') [ʻteteleiomai'] የቅርብ ኃላፊ ጊዜን የሚያመለክት ስለሆነ (ዕብ. 10፡14)፥ የመጨረሻ ሙሉ ፍጹምነት ለሙታን ትንሣኤ ቀን እንደተጠበቀ መገንዘቡን ያሳያል (ፊልጵ. 3፡11)። ያን ዕለት በነፍስ፥ በመንፈስና በ*ሥጋ* ፍጹም ይሆናል። ስለዚህ በዚህ ምድር ወደ ሙሉ ፍጹምነት መድረስ እንደሚቻል መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም።

የቅድሰና ፅንሰ-አሳብ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቅድስና የተሟላ ትምህርት ያስተምራል። ይህን ትምህርት በትክክል ስንገነዘብ፥

መጠራታችን የተቀደሰ መሆኑ ብሩህ ሆኖ ይታየናል። የቅድስና ትምህርት በተሳሳተ መልክ ከመታየቱ የተነሣ፥ በዚህ ምድር ሙሉ ለሙሉ ፍጹም መሆን እንችላለን የሚል ትምህርት ወደማቅረብ ተደርሷል። በዚሁ መሠረት ክርስቲያኖች ለጠቅላላ ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲለምኑ ተነግሯቸዋል። በአንዳንዶች አመለካከት ይህ ጉዳይ ‘‘ሁለተኛው የጸጋ’’ ሥራ ተብሏል። ከዚህ የተነሣ ፍጹምነትን ያልጨበጡ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ፈቃድ ለመከተል ያልፈቀዱ በደለኞች ሆነው ተቆጥረዋል።

መቀደስ፥ ቅድስና፥ ቅዱስ፥ መለየት የተሰኙትና ሌሎችም ቃሎች ‘ሃጊያዞ’ [‘hagiazo’] ከሚለው የግሪክ ቃል የመጡ ናቸው። እነዚህ ቃሎች በሙሉ አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን፥ ታየር እንደተባለው ሰው አተረጓጎም፥ ‘‘የተለየ ወይም የተቀደሰ’’ ማለት ነው። ሁለተኛ ትርጉም አድርገን የምንወስደው ‘‘ከንቱ ከሆነ ነገር ተለይቶ ለእግዚአብሔር መሰጠት’’ እና ‘‘መንጻት’’ የሚለውን ነው። ሦስቱ ዋና ዋና አሳቦች (ማቅረብ፥ መለየትና መንጻት) በማዕከላዊው የመቀደስ አሳብ ውስጥ ያሉ ናቸው። ይህ መሠረታዊ ትምህርት በብሉይ ኪዳን መሥዋዕትና ቁርባን ውስጥ ጥሩ መሠረት ያለው ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን በተጨማሪ በተገለጠ እውነት ይበልጥ ተብራርቷል። በአዲስ ኪዳን በአጭሩ እንደቀረበው፥ ቅድስና ፍጹምነትን ከሚመለከተው የእምነት ትምህርት አከፋፈል ጋር በመጠኑ በሚያያዝ መልኩ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተመድቧል። እነርሱም፦ ‘‘ስፍራዊ (የመብት ስፍራን የሚመለከት) ቅድስና’’፥ ‘‘ልምምዳዊ (ተግባራዊ) ቅድስና’’ እና ‘‘የመጨረሻ (የወደፊት) ቅድስና’’ ናቸው። በሰፊው ያየነው እንደሆነ በቅድስና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ የሚገኘው አሳብ በተለይ የሚያተኩረው ከፍጹምነት ይልቅ ለቅድስና ወይም ለተቀደሰ አገልግሎት መለየት በሚለው ላይ ነው። ቅድስና ሕይወት ለሌላቸው ነገሮችም ያገለግላል። ለምሳሌ ወርቅ በቤተ መቅደስ ተቀድሷል (ማቴ. 23፡17)፥ ያላመነ ባል ባመነች ሚስቱ፥ ያላመነች ሚስት ባመነ ባልዋ ተቀድሰዋል (1ኛ ቆሮ. 7፡14)፥ ምግብ በጸሎት ይቀደሳል (1ኛ ጢሞ. 4፡5)። ቅድስና ክርስቶስን ለተቀደሰ ሥራ ከመለየቱ አንጻርም አገልግሏል (ዮሐ. 10፡36፤ 17፡19፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡ 15)። ቅድስና፥ በዚህ ስሜት፥ ማንጻት ሳይሆን ካልተቀደሰ ነገር ለይቶ ለተቀደሰ አገልግሎት ለእግዚአብሔር ማቅረብ ማለት ነው።

አዲስ ኪዳን ብዙ ጊዜ የሚናገረው፥ ክርስቶስ ለአማኙ ስለሠራውና እርሱም ከዳነበት ጊዜ ጀምሮ ስላገኘው ቅዱስ ስፍራ ነው። በአዲስ ኪዳን በግምት ወደ ስድሳ አምስት ጊዜ ቅዱሳን ተብሎ የተጠቀሰው

ቃል በዚህ ክፍል ይመደባል። በጣም አስፈላጊ የሆኑና ልናነሣቸው የሚገቡ ክፍሎችም አሉ (ሐዋ. 20፡32፤ 26፡18፤ ሮሜ 15፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡2፥ 30 ፤ 6፡11፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13፤ ዕብ. 2፡11፤ 10፡10፥ 14፤ 13፡12፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2፤ ይሁዳ 1)። እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነው አንድ ክፍል በተለይ አስቸጋሪና ብልሹ ዓለማዊ ሕይወት የነበራቸው የቆሮንቶስ ሰዎች ‘‘ቅዱሳን’’ ተብለው የተጠሩበት ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡2)። ቅድስና ማለት ያለ ኃጢአት መሆን ማለት እንዳልሆነ ይህ ክፍል ብቻውን ያረጋግጥልናል።

ልምምዳዊ ቅድስና ስፍራዊ ቅድስናን ያህል ባይጠቀስም፥ እጅግ አስፈላጊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው። በዮሐንስ 17፡17፥ ‘‘በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው’’ ሲል ጌታ በጸለየው ጸሎት የምናገኘው ቅድስና ይህን የመሰለ ቅድስና ነው። ይህ ቅድስና የተጠቀሰበት ሌላ ሁኔታ ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ የሰጠበት ጉዳይ እንደሆነ በኤፌሶን 5፡26 ላይ ይናገራል፡- ‘‘በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ።’’ ብዙዎች ይህን ጥቅስ ስለ ውኃ ጥምቀት የሚናገር ነው ቢሉም፥ ጥቅሱ ራሱ የሚደግፋቸው አይደለም። ይልቁን ስለ እግዚአብሔር ቃል የመቀደስ ኃይል የሚናገር ይመስላል። በዕብራውያን 9፡13-14 ደግሞ የክርስቶስ ደም እንደ ማንጺያ መሣሪያ ሆኖ ተገልጧል። በምድራዊ ሕይወታችን ከኃጢአት ሊያነጻን እግዚአብሔር የሚሠራው ሥራ ሁሉ ቅድስና በሚለው ቃል ተጠቀሰም አልተጠቀሰ ይህን እውነታ የሚያሳይ ነው። ቅዱሳን የልምምድ ቅድስናን አስፈገላጊነት እንዲገነዘቡ ተነግሯቸዋል (1ኛ ተሰ. 4፡3-4፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡18)። የዚህ ቅድስና ገጽታ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ዋና ግብ ሲሆን፥ ተግባራዊ የሚሆነው በመንፈስ በመመላለስ ነው።

ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር በመንፈስ መመላለስ በሚለው ጽሑፉ በሚገባ እንደገለጠው፥ ልምምዳዊ ቅድስና ሦስት ግንኙነቶች አሉት። እነርሱም፡- 1. የአማኙ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር መስጠት፥ 2. የአማኙ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከኃጢአት ኃይል ነጻ መሆን፥ 3. የአማኙ ያለማቋረጥ በጸጋ ማደግ ናቸው። ይህ የመንፈሳዊ ሕይወት መሠረታዊ ትምህርት እምብርት ስለሆነ፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን ከልቡ ሊያጠናውና ሊጸልይበትም ይገባል።

‘‘የመጨረሻው ቅድስና’’ እግዚአብሔር በአማኝ የሚያከናውነው ሥራ ውጤት ነው። ስፍራን የሚመለከተው ቅድስና፥ የቅዱሳን የዘላለም ዕድል ፋንታ የሆነው ‘‘የመጨረሻ ቅድስና’’ ነው። ልምምዳዊ ቅድስና በመጪው ሕይወት እንደ መጨረሻ ግብ የሚፈጸም መሆኑ ይታወቃል። የመጨረሻ ቅድስናን የሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የተገኘው፥ በዚህ የሕይወት ዘመናችን ልንደርስበት የምንፈልገውን ግብ

ከሚያሳዩት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ነው። ለምሳሌ በ1ኛ ዮሐንስ 3፡2፥ ‘‘ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን’’ የሚል ቃል እናነባለን። ይህ ጥቅስ የመጨረሻ ቅድስና የሚሆንበትን ጊዜ በመጠቆም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በኤፌሶን 5፡27፥ አሁን ያለንበት ቅድስና ወደፊት ፍጹም በሚሆንበት መልኩ ቀርቧል፡- ‘‘እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።’’ በሮሜ 8፡29 ደግሞ፥ ‘‘የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗል’’ ተብሏል። ይህ ወደፊት የሚፈጸም ነው። በዕብራውያን 12፡14፥ እያንዳንዱ አማኝ ጌታን በሚያይበት ጊዜ ፍጹም እንደሚቀደስ ተገልጧል። እነዚህና ሌሎችም ብዙ ተመሳሳይ ጥቅሶች በአንድ ላይ ሆነው የወደፊቱ ዘላለማዊ ሁኔታ በሁሉም አቅጣጫ የመጨረሻ ፍጹምነት የሚገኝበት መሆኑን ያሳያሉ። እነዚህ ጥቅሶች በግልጥ የሚያሳዩት የመጨረሻ ቅድስና በወደፊት ሕይወት ዘመን የሚደረስበት መሆኑን ነው።

ፍጹም ቅድስና በምድር ላይ ሊገኝ ይችላል የሚለውን አሳብ ለመደገፍ የሚጠቀሱ ጥቅሶችን በጥንቃቄ ስንመረምር፥ ቀደም ሲል ካየናቸው እውነታዎች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን እናያለን። የተሳሳተ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚመነጨው ከሦስት ነገሮች ነው። የመጀመሪያው ስሕተት ስፍራዊ ቅድስና ማለት በዚህ ሕይወት ፍጹም ያለ ኃጢአት መሆን ነው ብሎ መረዳት ነው። ስለ ትምህርቱ የሚናገሩ ክፍሎችን በማጥናት ይህን አሳብ በቀላሉ ውድቅ ለማድረግ ይቻላል። ቅዱሳን በክርስቶስ ያላቸው ስፍራ ፍጹም ቢሆንም፥ ኃጢአት እንደሚያደርጉ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይናገራል። ሁለተኛው የተሳሳተ ግንዛቤ ምክንያት ደግሞ ቅድስና የሚለው ቃል ራሱ ለተለያየ ጥቅም መዋሉን ያለመረዳት ነው። ቅድስና የሚለው ቃል ያለ ኃጢአት የመሆንን ስሜት በሚያመለክት መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አገልግሎት ላይ አልዋለም። መለየትን ወይም መንጻትን በሚያመለክት ሁኔታ ቢጠቀስ እንኳ እንደ ፍጹምነት ሊቆጠር አይገባም። ሦስተኛው የተሳሳተ አሳብ ለደኅንነት ያለ ኃጢአት መሆን ያስፈልጋል የሚል ሲሆን፥ ይህ ነጥብ በአንዳንድ ይህን አሳብ የሚደግፉ በሚመስሉ ምንባቦች ላይ የተመሠረተ ነው። በእነዚህ ምንባቦች ላይ የሚደረግ ጠንቃቃ ጥናት ችግሮቹን ያቃልላቸዋል።

ያለ ኃጢአት መሆን ለደኅንነት አስፈላጊ ነው የሚለው የተሳሳተ አሳብ የተመሠረተው በ1ኛ ዮሐንስ 3፡6-9 ነው፡-

“በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም፥ አላወቀውምምና። ልጆች ሆይ፥ ማንም አያስታችሁ። እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአት ያደርጋልና። ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና። ከእግዚአብሔርም ተወልዷልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።”

በአማርኛም ሆነ በእንግሊዝኛው ንባብ የዚህን ክፍል ፅንሰ-አሳብ በተሳሳተ መንገድ የመረዳት ሁኔታ አለ። በግሪኩ ግን ችግሩ እምብዛም ነው። ክፍሉ በሙሉ የቀረበው በአሁን ጊዜ ሰዋሰዋዊ አገባብ ነው። በዚህ ስፍራ የተሰጠው መገለጥ የሚያስረዳው፥ ያለማቋረጥ ኃጢአት የሚያደርግ ወይም ባሕርዩ በኃጢአት መኖር የሆነ ሰው ያልዳነ መሆኑ ነው። ዳግም የተወለዱና በክርስቶስ የሆኑ ሰዎች፥ አዲስ ፍጥረት ስለሆኑ ያለማቋረጥ በኃጢአት ውስጥ ሊኖሩ አይችሉም። በሁለት መንገድ ሊታዩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ፍርድ መስጠት አስቸጋሪ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ኃጢአት የሚሠሩ ክርስቲያኖችን እንደሚቀጣ፥ በተለያዩ መንገዶች እየተገናኘም ወደራሱ እንደሚመልሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ራሳቸውን ሳይቆጣጠሩ ያለማቋረጥ በኃጢአት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ደኅንነት፥ በሰብአዊ አእምሮአችን በጥያቄ የመመልከት መብት አለን።

ከ1ኛ ዮሐንስ 3፡6-9 መልእክት ለሚወጣ የተሳሳተ አተረጓጎም ሌላ መፍትሔ ለመስጠት “አዲስ ፍጥረት” የሚለው ቃል ፅንሰ-አሳብ ጠቃሚ ነው። በዚህ አቀራረብ መሠረት፥ ትምህርቱ አዲስ ፍጥረት፥ ማለት ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን አያደርግም የሚል ይሆናል። በእግዚአብሔር የተሰጠው አዲስ ፍጥረት በአማኙ ሕይወት ውስጥ ኃጢአት የማያመነጭ መሆኑ እውነት ነው። ትርጉሙን እስከዚህ ድረስ ለመቀበል ይቻላል። ነገር ግን ምንባቡ ክፍሉ የሚጠቀምበት ግሥ የአሁን ጊዜ መሆኑ፥ ኃጢአት የሚቀጥል ባይሆንም እንኳ አልፎ አልፎ የመከሠቱን ሁኔታ የሚያሳይ ነው። አሳቡ አዲሱ ፍጥረት ኃጢአትን ጨርሶ አያደርግም የሚል ቢሆን ኖሮ በሰዋሰው አጠቃቀሙ ከአሁን ጊዜ ይልቅ ያልተወሰነ ጊዜን ይጠቀም ነበር። ምንባቡ በአሁን ጊዜ የመሆኑ ጉዳይ የመጀመሪያውን መፍትሔ የተሻለ ያደርገዋል።

በማንኛውም ረገድ ያለ ኃጢአት መሆን ለደኅንነት አስፈላጊ ነው የሚለው ትምህርት፥ የጸጋንና የዋስትናን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ከመሻሩም ሌላ ደኅንነትን በሰው ሥራ ደረጃ ዝቅ ያደርገዋል። በዚህ

ምክንያት ታሪካዊት በሆነችው ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የእምነት ትምህርቶችን የመገንዘብ ጉድለት ቢኖርም፥ ያለ ኃጢአት መሆን ብቻውን ለደኅንነት መሠረታዊ ነገር አለመሆኑን አበክራ አስገንዝባለች። መሠረታዊው የቅድስና ትምህርት ለእግዚአብሔር ክብር መስጠትን ብቻ ሳይሆን፥ በመንፈስ መመላለስም አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ መገለጥ ለአማኙ ይሰጠዋል። ደኅንነት ከእግዚአብሔር ኃይል ውጭ በምንም አኳኋን የማይሆን ጉዳይ ነው።

የኃጢአትን ባሕርይ የመደምሰስ (ከሥሩ ነቅሎ የመጣል) ፅንሰ-አሳብ [Eradication/ኢራዲኬሽን]። በምድራዊ ሕይወት የኃጢአት ባሕርይን ነቅሎ በመጣል እንዳይሠራ ከሚደረግበት ወይም ከሚደመሰስበት መንፈሳዊ የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ይቻላል የሚል ትምህርት በመስፋፋት ላይ ነው። ይህ አሳብ በዚህ ሕይወት ፍጹምነትና ያለ ኃጢአት የመሆን አሳቦችን በአንድነት አቀናብሮ ለማቅረብ የሚሞክርና በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ ለማድረግ የሚጥር ነው። ፅንሰ-አሳቡ ከበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር የሚጋጭና ለአምንታዊ ልምዶች እንግዳ በመሆኑ በአስተዋይ ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም። ከሥጋ ጋር ስለሚካሄድ ትግልና ለመዋጀት በእግዚአብሔር ላይ ስለመደገፍ አጠቃላይ አስፈላጊነት የሚናገሩ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሊታለፉ የማይችሉ የዚህ ትምህርት እንቅፋቶች ናቸው።

የኃጢአትን ባሕርይ ማሸነፍ ስለሚቻልበት መለኮታዊ መንገድ ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር እንደጻፈው፡-

> ‘‘በአማኙ ሕይወት ውስጥ የኃጢአትን ባሕርይ ማሸነፍን የሚመለከቱ ሁለት የተለያዩ አጠቃላይ መለኮታዊ መንገዶች መኖራቸውን የሚቀበሉ ንድፈ አሳቦች አሉ። የመጀመሪያው ንድፈ አሳብ አሮጌው ተፈጥሮ አንድ ሰው በሚድንበት ጊዜ ወይም ከደኅንነት በኋላ ባሉ መንፈሳዊ በረከቶችና ልምምዶች ይወገዳል የሚል ነው። የአንድ አማኝ ሕይወት ብቃት የሚለካውም የኃጢአት ተፈጥሮው ዝንባሌ ከመወገዱ አንጻር ነው። ሌላው ንድፈ አሳብ ግን አሮጌው ተፈጥሮ ክርስቲያን በአካለ ሥጋ እስካለ ድረስ የሚኖር ሲሆን፥ የሕይወቱ ጥራትና ብቃት የሚለካው የእግዚአብሔር መንፈስ በሥጋ ላይ በሚያደርገው ቅጽበታዊና የማያቋርጥ ቁጥጥር ነው። ይህ ሊሆን የቻለው በክርስቶስ ሞት አማካይነት ነው ይላል። እነዚህ ሁለት ንድፈ አሳቦች አማኝ በእግዚአብሔር የተሰጠውን የድል ተስፋ እንዴት በዕለታዊ ኑሮው በልባዊ ጥረት ሊለማመደው እንደሚችል ያሳያሉ።

የሁለቱም ንድፈ አሳቦች ግብ ከኃጢአት ባርነት ነጻ የወጣ ሕይወት ነው። ስለዚህ በግንዛቤው ውስጥ ያለው ጥያቄ የእግዚአብሔር እቅድና መንገድ የትኛው ነው? የሚል ይሆናል። ሁለቱ ንድፈ አሳቦች እርስ በርሳቸው ስለሚጋጩ እውነት ሊሆኑ አይችሉም።''

ቼፈር የኃጢአት ባሕርይን ስለመደምሰስ የሚያወሳው ንድፈ አሳብ እግዚአብሔር ከአማኙ ጋር ያለውን ጉዳይ የሚያካሂድበት መለኮታዊ መንገድ እንዳልሆነና፥ ንድፈ አሳቡ በልምምድ የሚታየው ነገር ተቃራኒ መሆኑን ከተመለከተ በኋላ ይህ ንድፈ አሳብ ከመለኮታዊ መገለጥ ጋር እንደማይስማማ ለማረጋገጥ ሰባት አሳቦችን አቅርቧል፦

''በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ 'ትምህርት'፥ 'ተግሣጽ' እና 'ምክር' ይገኛል። ስለዚህ ማጠቃለያችን በየትኛውም የአእምሮ አስተሳሰብ ወይም በማንኛውም ግላዊ ልምድ መሆን የለበትም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን፦

''1. አማኞች በሙሉ የኃጢአትን ባሕርይ ከመደምሰስ ንድፈ አሳብ እንዲጠነቀቁ መመከራቸውን ነው፤ '[የ]ኃጢአት [ባሕርይ] የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም' (1ኛ ዮሐ. 1፡8)።

''2. መንፈስ ቅዱስ የመጣው ነጻ ሊያወጣን ነው፤ ስለዚህ ድላችን የተመሠረተው በሌላ ነገር ከሆነ ስለርሱ ሕልውና፥ ዓላማና ኃይል ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ነገር ትርጉም የለሽ ይሆናል። ለዚህ ነው ስለ ኃጢአት ባሕርይ መደምሰስ የሚያወሳው ንድፈ አሳብ ለመንፈስ ቅዱስ ሕልውናና ሥራ አነስተኛ ስፍራ የሚሰጠው።

''3. መንፈስ ቅዱስ ነጻ የሚያወጣን በማያቋርጥ ትግል ነው። 'ሥጋ [አሮጌውን ተፈጥሮ የሚጨምረው] በመንፈስ ላይ፥ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፤ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ። ስለዚህ [በመንፈስ ስትመላለሱ] የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም' (ገላ. 5፡17ን ከያዕቆብ 4፡5 ጋር ያነጻጽሩ)። ደግሞም በሮሜ 7፡15-24 እንዲሁም 8፡2 በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚታየው የኃጢአት ምንጭ በሥጋ የሚሠራ የኃጢአት ባሕርይ ነው። ድል የሚገኘውም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት ነው። አከራሪነት የሚታይበትና የኃጢአት ባሕርይን መደምሰስ ንድፈ አሳብ የሚያቀነቅነው ትምህርት፥ ክርስቲያን ነገ ኃጢአት የመሥራት ዝንባሌ አያሳይም ስለሚል፥ ሰው በእውነተኛ ጥንቃቄ ነቅቶና በእግዚአብሔር ላይ ተደግፎ እንዳይኖር ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአት ድብቅ ኃይል ነዋሪ ስለሆነ

'በመንፈስ መመላለስ' ስናቋርጥ የሥጋ 'አምሮትና' 'ምኞት' ወዲያውኑ ይመለሳል ብሎ ያስተምራል። ስለዚህ 'በመንፈስ የምትመላለሱ እንደመሆናችሁ የሥጋን ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።'በልማድ የምንጓዝ ፍጥረታት ስለሆን በመንፈስ የመመላለስን እድገት ልንለማመድ እንችላለን። እውቀትን በልምድ ጭምር እናካብታለን። ስለዚህ 'በሥጋ' መመላለስ በተወሰነ ጊዜ ሊቆም ሲችል፥ 'በሥጋ' የመኖር ችሎታ ግን ሁልጊዜ ይኖራል። በዚህ ረገድ እውነተኛ መንፈሳዊነት ማለት፥ ለጊዜው ኃጢአትን ለማድረግ አለመፈለግ ማለት ነው (ፊልጵ. 2፡13)። ይህ ድርጊት ግን ኃጢአት የማድረግ ችሎታን የሚያስወግድ ወይም የኃጢአት ባሕርይን የሚደመስስ አይደለም። ቢሆንም ብርታትን በሚሰጠው የእግዚአብሔር ኃይል ለአሁን የሚሆን ፍጹም ድል ለማግኘት ይቻላል። ሁልጊዜ በሙላት እርሱን መፈለጋችን እውነት ነው። ጌታ 'ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም' (ዮሐ. 15፡5) ብሏል። የኃጢአት 'መርዝ' ሁልጊዜ በውስጣችን ስላለ፥ በማንኛውም ጊዜ 'አሸናፊ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ የማጥቃት ሥራ' ያስፈልገናል። ማንኛውም መንፈሳዊ እርምጃችን በመለኮታዊ ኃይል እርዳታ የምንራመደው ነው።

"4. አምላክ በቸርነቱ 'የሥጋንና የአሮጌውን ሰው' ጉዳይ ማየቱ የኃጢአት ባሕርይን መጥፋት አያመለክትም። እኛ 'በአዲስ ሕይወት መመላለስ' እንችል ዘንድ፥ እግዚአብሔር በልጁ ሞት በኩል መንገድ አዘጋጅቶልናል። የመመላለሱ ሁኔታ 'ቁጠሩ'፥ 'ስጡ'፥ 'አውልቁ'፥ 'ግደሉ'፥ 'ኑሩ' የሚሉትን በመሳሰሉ ትእዛዛት የተገለጠ ሲሆን፥ የትኞቹም ትእዛዛት በኃጢአት ባሕርይ መደምሰስ ንድፈ አሳብ ውስጥ ካሉ አዛማጅ ትርጉሞች ጋር የሚሄዱ አይደሉም። ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያስተምሩን፥ ኃጢአታዊ ተፈጥሮ እንደሞተ እንድንቆጥር ሳይሆን፥ እኛ ለኃጢአት የሞትን መሆናችንን ነው።

"5. የኃጢአት ባሕርይን መደምሰስ ንድፈ አሳብ የሚከተሉ ሰዎች የያዙት ትምህርት፥ መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ከክርስቶስ ጋር ስላለው ኅብረት የሚናገረውን በተሳሳተ መንገድ ከመተርጎም የተነሣ የሚፈጠር ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኝ ስፍራን ይመለከታል ተብሎ የሚታመነው ቅድስና (በእግዚአብሔር አሳብ እንዲሁም እይታ ውስጥ ብቻ ያለው)፥ ለእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ለአንዴና ለመጨረሻ የሚከናወን ነው። ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ አሳብ፥ ራሳቸውን ከኃጢአት ዝንባሌ ነጻ አድርገው በሚመድቡ

በጥቂቶች ዕለታዊ ኑሮ ውስጥ የሚታይ ልምምድ ነው ተብሎ በተሳሳተ መንገድ ተወስዷል።

“6. የዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ማጠቃለያ የተመሠረተው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ‘ሥጋ’ ስለሚለው ቃል ለሚያስተላልፈው ትምህርት የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ላይ ነው። የዚህ ትምህርት አራማጆች ‘ሥጋ’ የሚለው ቃል ሁሉንም ማለት የፍጥረታዊውን ሰው መንፈስ፥ ነፍስና አካል የሚያመለክት መሆኑን አይረዱም። የኃጢአት መወገድ፥ በአካል ውሱንነት የተፈጠሩትን ችግሮች ሁሉ የማስወገድ ዝንባሌ የለውም። ‘በእኔ [በአካሌ] ምንም መልካም ነገር የለም’። ስለዚህ ‘ሥጋ’ በ‘ሽክላ ዕቃ’ የተመሰለውና ያልከበረው (የተዋረደው) አካላችን እስካለ ድረስ ይኖራል። በእርግጥ አካላችን አይደመሰስም።

“7. የኃጢአት ባሕርይ መደምሰስን የሚመለከተው ትምህርት ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ በልምድ ላይ ያተኩራል። ልምምድን ማሰላሰል፥ ማጠቃለያውንም በዚህ አጠናን ላይ መመሥረትና ማረጋገጥ ሁልጊዜ የተለመደ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነጻ የመውጣት ተገቢ ልምምድ ‘ኃጢአት የሌለበት ፍጹምነት’፥ ‘አጠቃላይ የሆነ ቅድስና’ እና ‘የኃጢአት ባሕርይን የመደምሰስ’ ማረጋገጫ አድርጎ ማቅረብም እንዲሁ ተለምዷል። ነገር ግን የሰው ግምት መለኮታዊ መገለጥን ሊተካ ጨርሶ አይችልም።

“ሁለቱ ንድፈ አሳቦች የማይታረቁ ናቸው። ነጻ የወጣነው አንድም የእግዚአብሔር እርዳታ ወይም ኃይል ሳያስፈልገን የኃጢአት ባሕርይ ዝንባሌያችን በቅፅበት ተወግዶ ነው፤ አለዚያም በመንፈስ ቅዱስ ቅጽበታዊና ቋሚ ኃይል ነው የሚለውን መቀበል ይኖርብናል። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ የሚያስተምረው ሁለተኛውን ነው።”

ለራስ የመሞት ንድፈ አሳብ። የኃጢአት ባሕርይ መደምሰስን ከሚመለከተው ንድፈ አሳብ ጋር የሚቀራረበው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ክርስቲያን ፈቅዶ በሚያከናውነው ተግባር ሙሉ በሙሉ ለራሱ ሊሞት ይችላል የሚለው ነው። ፍጹምነትንም ሆነ የኃጢአት ባሕርይ የመደምሰስን ጽንሰ አሳብ የማይቀበሉ ሰዎች እንኳ ይህን ለራስ የመሞት አቋም ይዘው እናገኛቸዋለን። ችግሩ ያለው ራስን ስለ መስቀል ወይም ለራስ ስለ መሞት የሚናገሩ የመጽሐፍ ክፍሎች የሚገኙበትን የግሪክኛ ጥቅሶች ለመመርመር ካለመቻል ላይ ነው። እነዚህ ግሪክኛ ጥቅሶች የሚያመለክቱት ስላለፈ ጊዜ መሆኑን ያረጋግጣሉ። በክርስቶስ ውስጥ ያለ ክርስቲያን

ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ ሞቷል። ይህ የአሁን ጊዜ ልምምድ ሳይሆን የምትክነት እውነታ ነው። ‘‘አሮጌው ሥጋችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ’’ (ሮሜ 6፡6) የሚለው ግሥ በኤሪስት ጊዜ መሆኑ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ለዘላለም የፈጸመውን ሥራ ያመለክታል። ይበልጥ ወሳኝነት ያለው በገላትያ 2፡20 የሚገኘው ጥቅስ ነው፡- ‘‘ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፥ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።’’ ‘‘ተሰቅዬአለሁና’’ የሚለው ግሥ የቅርብ ኃላፊ ጊዜ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ውጤቱ ግን በመቀጠል እስከአሁን ደርሷል። ‘‘ተሰቅዬአለሁና’’ ከሚለው የቅርብ ኃላፊ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር ‘‘አሁን የምኖረው እኔ አይደለሁም’’ በማለት ጳውሎስ ግሡን በአሁኑ ጊዜ ገልጦታል። የጳውሎስ ሕይወት አሁን ድል ሊያገኝ የቻለው፥ ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ በመሞቱ ነው። ምክሩ በራሳችን ድርጊት ለራሳችን እንድንሞት ሳይሆን፥ ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ መሞታችንን እንድንገነዘብና በዚህ የመገለጥ ብርሃን መኖር እንድንችል ነው። አስፈላጊ የሆነው እውነት ለራሳችን እንደሞትን እንድንቆጥርና ይህም ያለማቋረጥ ልናደርገው የሚገባ መሆኑን መረዳት ይሆናል።

ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ መሞቱ የኃጢአት ባሕርይውን አያስወግድም ወይም ኃጢአት የማይሠራ አያደርገውም። ስለ አማኞች ከክርስቶስ ጋር መሞት የሚናገረውና ሮሜ 6 ላይ ያለው ጠቃሚ ክፍል እንደዚህ በማለት ይመሰክራል፡- ‘‘እንግዲህ ለምኞቱ እንዳትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ’’ (ሮሜ 6፡12)። ክርስቲያን ራሱን ለኃጢአት [ባሕርይ] እንደሞተ መቁጠር አለበት፤ ምክንያቱም በክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔር ኃይል በእርሱ ላይ ሊሆን ይችላል። የክርስቶስ ሞት ለኃጢአት ቤዛ መሆን ብቻ ሳይሆን፥ አማኝ ከኃጢአት እሥራትና ብልሹነት ነጻ የሚወጣበትን ኃይል ይሰጠዋል።

የሥጋ ፍጹም ደካማነት። የፍጹምነት፥ የመቀደስ፥ የኃጢአት ባሕርይ መደምሰስና ለራስ የመሞት መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች በእግዚአብሔር ቃል መገለጥ መሠረትነት ብንረዳቸው፥ ስለ ሥጋ ደካማነትና እያንዳንዱ አማኝ ድል ለማድረግ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ የሚገባው ስለመሆኑ ጠንካራ ምስክርነት ይሰጣሉ። ኃጢአታዊ ተፈጥሮን የሚመለከተው መሠረታዊ ትምህርት፥ አማኝ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠውን ክርስቲያናዊ ሕይወት ለመኖር የሰይጣን ኃይል፥ የጨለማ ሠራዊትና ሰዎችን የሚያበላሸው የዓለም ባሕርይ ስለሚገጥመው፥ ኃይል ሰጭ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ማግኘቱ እጅግ የሚያስፈልገው

መሆኑን ያመለክተናል። ክርስቲያን የሚቀናቀኑትን ኃይላት ድል ለማድረግ፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከመኖርና በመንፈስ ከመመላለስ በስተቀር ሌላ አማራጭ የለውም።

የመንፈሰ ቅዱስ ማደሪያ መሆን። መካከለኛ ወይም ያልጸና ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ተገቢ የሆነ የክርስትና ድል እንዳያገኝ የሚያግደውን ችግር የሚረዳው በድንግዝግዝ መሆኑ አያጠራጥርም። የክፋት ኃይላትን ማሳወቅና ያለ እግዚአብሔር እርዳታ እነርሱን መጋፈጥ የማይቻል መሆኑን ግልጥ የማድረግ ትእዛዝ የግድ አስፈላጊ ነበር። ጦርነትን ለማካሄድ መወሰድ ያለበት የመጀመሪያ እርምጃ ጠላትንና የራስን መሣሪያ ማወቅ ነው። በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ የተካተቱት በርካታ ነገሮች ‘‘መንፈስ አታጥፉ’’፥ ‘‘መንፈስን አትሳዝኑ’’፥ ‘‘በመንፈስ ተመላለሱ’’ በሚሉ ቀላል ዓረፍተ ነገሮች ተጠቃለዋል። ይህ የትምህርት ጉዳይ ብቻ አይደለም። እውነቱን መረዳትና ሙሉውን የእግዚአብሔር ፈቃድ መፈለግ ተገቢ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የሚፈልግ አማኝ ራሱን የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚገለጥበት ቃል ጥናት ሊሰጥ ይገባል። ፈቃዱን ለማድረግ ፈቃደኞች ሆነን እንገኝ ዘንድም በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መቆየት ያስፈልጋል። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ባለን ኅብረት መነቃቃትና የርሱን በረከት ከሕዝቡ ጋር መካፈል በጣም አስፈላጊ የሆነ የእርዳታ ምንጭ ነው። በመንፈስ መመላለስና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የተያያዙ ናቸው። ይህ ጠላትን የመከላከል አቋም ሳይሆን፥ ለመንፈሳዊ ሕይወት ችግር መፍትሄ መሻትና በእግዚአብሔር ፈቃድና በእርሱ ብቃት ላይ የማረፍ ጉዳይ ነው። ዋናው ነገር ልናደርገው ያልቻልነውን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንዲያደርግልን ያለማቋረጥ በእርሱ ላይ መደገፍና ለምሪቱ ራስን የመስጠት እንዲሁም የታወቁ ኃጢአቶችን ሁሉ የመናዘዝና የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት በእምነት የመፈለግ ጉዳይ ነው፤ ‘‘ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና’’ (ፊልጵ. 2፡13)። በመንፈስ መመላለስ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የማድረግ ጥልቅ ደስታ የሚታወቅበት፥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በአማኙ ልብና ሕይወት ውስጥ የሚታይበትና ከፍተኛ ደስታ የሚያገኝበት ነው። በመጨረሻም እርሱ ድል ባደረገበት በዚህ ዓለም ላይ ድል ይኖረን ዘንድ የተሠቃየውን ከሞት በድል አድራጊነት የተነሣውን ጌታ የከበረ ፊት ስናይ የሚኖረንን ወሰን የሌለው በረከት አሻግረን የምናይበት ይሆናል።

23

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጤቶች

በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ውጤት በሁሉም የክርስትና ሕይወት ልምምድ ውስጥ ይገለጣሉ። የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን የታጠቀና በርሱ የተመራ ሕይወት የተለያዩ መንፈሳዊ ብቃቶች እንደሚታዩበት ግልጥ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን መመርመር እግዚአብሔር በቅድስና፥ በመንፈሳዊነትና በአገልግሎት ውስጥ ያለው የአሁን እቅድ በመንፈስ በመሞላት የሚረጋገጥ መሆኑን ለመረዳት ይረዳል። ቢያንስ ቢያንስ ሰባት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጤቶች አሉ።

1. ልምምዳዊ ቅድስና

ቀደም ሲል እንደተነጋገርነው ቅድስና በሦስት ዓይነት ሁኔታዎች ይታያል። እነርሱም ስፍራዊ ፥ ልምምዳዊ እና የመጨረሻ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ በተለይ የተያያዘው በአሁኑ ጊዜ ከሚሆነው ከምንለማመደው ቅድስና ጋር ነው። በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር የሆነና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈጽም ኃይል የተሰጠው ክርስቲያን መሠረታዊ የባሕርይ ለውጥ ያሳያል። የቀድሞው የኃጢአት ባሕርይ አሁንም ያለ ቢሆንም፥ እንደሞተ ስለሚቆጠር አዲሱ ባሕርይ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመንፈስን ፍሬ ያፈራል። በገላትያ 5፡22-23 በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት ፍሬ እንደሚያፈራ ተጽፏል፦ ‘‘የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።’’ ይህን ክፍል በቅርበት ልናጠናው ይገባል። ስኮፊልድ የተባለው ጸሐፊ እንደጠቆመው፥ በአንዳንዶች ዘንድ ይህ በሦስትዮሽ ሊቀርብ የሚችል ነው ተብሏል።

> ‘‘ክርስቲያናዊ ባሕርይ የሥነ-ምግባር ወይም የሕግ ትክክለኛነት ብቻ አይደለም። ነገር ግን የዘጠኝ ጸጋዎች ባለቤትነትና መግለጫ ነው፡- ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም- የውስጣዊ ክፍል ባሕርያት መግለጫ፤ ትዕግሥት፥ በጎነት፥ ቸርነት- ለሰዎች የሚገለጥ ባሕርይ መግለጫ፤ እምነት፥ የዋህነት፥ ራስን መግዛት- ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያ ባሕርያት መግለጫ ናቸው። በአንድነት ያየናቸው እንደሆነ እነዚህ የክርስቶስን ግብረ ገባዊ ሥዕል ያቀርባሉ። በመሆኑም ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ 2፡20፥ ‘እኔ አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል’ ሲል የተናገረውን ቃል የሚገልጡ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ደግሞም በዮሐንስ 15፡1-8 የተጻፈው ‘ፍሬ’

የሚለው ቃል መግለጫ ሆነው እንደቀረቡ አድርገን ለማሰብ እንችላለን። አማኝ ይህ ባሕርይ ሊኖረው የቻለው፥ ከክርስቶስ ጋር ባለው ግንኙነት ምክንያት ነው (ዮሐ. 15፡5፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)። ራሳቸውን በሰጡ ክርስቲያኖች ሕይወትም የሚታይ የመንፈስ ፍሬ ነው›› (ገላ. 5፡22-23)።

በዚህ ክፍል የምናገኘው ሌላ አመለካከት፥ የመንፈስ ፍሬ ፍቅር ሲሆን፥ ቀጥሎ ከርሱ የፍቅር ማስረጃዎች የሆኑት ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ በጎነት፥ ቸርነት፥ እምነት፥ የዋሃት፥ ራስን መግዛት ይፈልቃሉ። በአንጻራዊነት ሲታይ የአቀራረቡ ዘዴ ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም። ማዕከላዊው እውነት፥ ልምምዳዊ ቅድስና የሚመነጨው፥ ከግል ጥረት ወይም ከፍጥረታዊ ሰው ፍላጎትና ፈቃድ ወይም ከአዲሱ ባሕርይ አይደለም። ለእግዚአብሔር በተሰጠ ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውነው ሥራ ነው። አጠቃላዩ እውነት የሚያሳየው እውነተኛ ክርስቲያናዊ ባሕርይ ከመንፈስ ቅዱስ ተነጥሎ ሊኖር እንደማይችል ነው። ስለዚህ በመሠረቱ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚጠይቁት በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት ትክክለኛ ጎብረት እንዲኖር ሲሆን፥ በዚሁ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አዲሱ ፍጥረት በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር ያለው ምኞት ይረካል።

2. ማስተማር

የመንፈስ ቅዱስ የማስተማር አገልግሎት ለሐዋርያት አገልግሎት አስፈላጊ የሆነ መገለጥን እንደሚሰጥ ክርስቶስ አስቀድሞ የተናገረ ሲሆን (ዮሐ. 16፡12-15)፥ በመጀመሪያ የተፈጸመውም በእነርሱ ነው። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ረገድ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለሁሉም ተሰጥቷል። የእግዚአብሔር ቃል በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተጻፈ ሲሆን፥ መለኮታዊ ደራሲው መንፈስ ቅዱስ፥ ከሁሉም የተሻለ አስተማሪ ነው። ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን ያለማወቅ ችግር አይቶ እንዲህ አለ፦ ‹‹የምነግራቸሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም፥ ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፥ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል›› (ዮሐ. 16፡12-13)። ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ሞቱና ትንሣኤው፥ እንዲሁም ለአሁኑ ዘመን ያለውን ዓላማ ስለሚመለከት ታላቅ እውነት አልነገራቸውም። ምክንያቱም ይህን ትምህርት ለመረዳት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም። ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በሰጠው አገልግሎት እነዚህ ነገሮች ቢኖሩም፥ ከዚያ በኋላ ግን ዋናው መምህር መንፈስ ቅዱስ ነበር።

መንፈሳዊ ለሆኑ፥ ማለት በመንፈስ ለተሞሉ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች ሊገልጥላቸው ይችላል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 2፡9-3፡2 ያለው አሳብ የሚያስተምረን፥ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች ሊረዱ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ ለመማር መመዘኛዎችን ያለፉ ብቻ እንደሆኑ ነው። ፍጥረታዊው ሰው መንፈስ ለሚያስተምራቸው ሰዎች ቀላል የሆነውን እውነት እንኳ ለመረዳት አይችልም። ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ያለማወቃቸው ምክንያት፥ ሥጋዊ መሆ ናቸውና በመንፈስ የተሞላ ሕይወት የሚያገኘውን በረከት ከመሻት መቆጠባቸው ነው። የመንፈስ ቅዱስ የማስተማር ሥራ ከስሕተት በማስጠንቀቅ ይመክራል። በ1ኛ ዮሐንስ 2፡27 የእርሱ ቅባት (የእርሱ በሰው ማደር) እውነትን ያለ አስተማሪ እንኳ ለመማር ያስችለናል። ይህን በጣም አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ እዚህ በሰፊው መመልከት ባይቻልም፥ በክርስቲያን እውቀትና ልምምድ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። የመንፈሳዊ እውቀትንና ያለማወቅን ምክንያቶችም ይገልጣል።

3. ምሪት (አመራር)

ከመንፈስ ቅዱስ የማስተማር ሥራ ጋር በቅርብ የተዛመደው ሌላ ጉዳይ ክርስቲያንን መምራቱ ነው። ምሪት በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለሚኖር ሕይወት ጠቃሚና በክርስቲያናዊ ልምምድ ውስጥም ዋና ነገር ነው። ምሪት ከመንፈስ ቅዱስ የማስተማር ሥራ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም፥ ልዩነትም አለው። የመንፈስ ቅዱስ የማስተማር ሥራ በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል ግልጥ ማድረግ ሲሆን፥ ምሪት ግን በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ችግር በሚከሠትበት ጊዜ ያ ሰው የተማረውን እውነት በተግባር የሚገልጥበት መንገድ ነው። ምሪት ሁልጊዜ አጠቃላይ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎችን አሁን ላለ ልዩ ችግር ተግባራዊ ያደርጋል። ወንጌል በዓለም ሁሉ እንዲሰበክ የእግዚአብሔር ዓላማ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ የገለጠው ቢሆንም፥ ማንኛውንም ክርስቲያን ወደ አንድ አገልግሎት የሚጠራና የሚሾም መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ለሚከሠት ዝርዝር ጉዳይ አስፈላጊውን ምሪትም ይሰጣል።

በዚህ አንጻር መጠቀስ ያለበት አስፈላጊ ነጥብ፥ ምሪት የሚሰጠው በእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ለጀመሩና ለሚመላለሱ ሰዎች ብቻ መሆኑን ነው። በሮሜ 12፡1-2 መሠረት ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት ያስፈልጋል፦ ‘‘ይህን ብታደርጉ እግዚአብሔር የሚደሰትበትን ፍጹምና በጎ ፈቃዱ ምን እንደሆነ ማወቅ ትችላላችሁ።’’ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንኳ የአብርሃም ሎሌ ለዚህ ነገር ምስክርነት ሲሰጥ እንዲህ ብሏል፦ ‘‘...እኔ በመንገድ ሳለሁ እግዚአብሔር ወደ ጌታዬ ወንድሞች ቤት መራኝ’’

(ዘፍጥ. 24፡27)። ምሪት በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላ ሰው የሕይወት አቅጣጫው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆን የማድረግ ተግባር ነው። ምሪት እግዚአብሔር ለክርስቲያን ከሰጣቸው የቸርነት ስጦታዎች ውስጥ አንዱና አስፈላጊ ነገር መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ቀርቧል። በሮሜ 8፡14 መሠረት፥ ምሪት የእውነተኛ ደኅንነት ምልክት ነው፡- "በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።" በገላትያ 5፡18፡- "በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም" ተብሎ እንደተጻፈ ምሪት ግላዊ ካልሆነውና በዘፈቀደ ይታይ ከነበረው የእስራኤላውያን ሕግ መመዘኛ ይልቅ፥ ነጻነትን የሚሰጥ የአሁኑ ዘመን ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው።

4. ዋስትና

ለእውነተኛ መዳን የደኅንነት ዋስትና የግድ አስፈላጊ ባይሆንም፥ የእያንዳንዱ ክርስቲያን መብት ነው። ይሁን እንጂ ዋስትናን ማግኘት የእግዚአብሔርን ቃልና የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት በተገቢው በመረዳት ላይ ይመሠረታል። አንዳንድ ክርስቲያኖች የደኅንነት ዋስትና ያለማግኘታቸው ዋና ምክንያት ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ቅድመ ሁኔታዎችን ስላላሟሉና፥ ልባቸው ይህን ተከትሎ ለሚመጣው ሌላ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ዝግጁ አለመሆኑ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት አንዱ አስደናቂ ነገር፥ እኛ የእርሱ እርሱም የእኛ መሆኑ ነው። ስለዚህ እውነት መንፈስ ቅዱስ የሚመሰክረው ነገር አለ። በተለይ ሮሜ 8፡16 እንዲህ ይላል፡- "የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።" ሌሎች ክፍሎችም ተመሳሳይ ምስክርነት ይሰጣሉ (ገላ. 4፡6፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡24፤ 4፡13)። የሰው አእምሮ ያለመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ወደተለያዩ ማጠቃለያዎች ሊደርስ ይችላል። ሆኖም የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ በኩል በተገኘው ደኅንነት ውስጥ ከአባቱ ጋር ያለውን ዘላለማዊ ግንኙነት ያረጋግጣል። የዚህ ደኅንነት ማኅተምም ነው። ብዙዎች የዋስትናን በረከት ማጣታቸውና ለጊዜውም ቢሆን ይህን በረከት መገፈፋቸው፥ በክርስቲያኑ ሕይወት ከሚታየው ሥጋዊነትና የኃጢአት ቅጣት አንዱ ነው።

5. አምልኮ

በአንዳንድ ክርስቲያኖች አመለካከት፥ አምልኮ ከምድራዊ አምልኮ ቤቶች፥ ከሥርዓቶች እንዲሁም ከተለመዱ ሌሎች የሕዝብ አምልኮ ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል ግን፥

አምልኮ የእግዚአብሔር በሚያውቁት ሰዎች መወደስ፥ በሙሉ ልብ መከበርና መመስገን ነው። ይህ የሚሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢ የሆነ መንፈሳዊ ግንኙነት ባለው ሰው ነው። በኤፌሶን 5፡18-20 በመንፈስ ተሞሉ ከሚለው ትእዛዝ ቀጥሎ፥ ከእግዚአብሔር ጋር በጎብረት የምትኖር ነፍስ ፍሬ የሆነውና መንፈስ ራሱ ምንጭ እንደመሆኑ መጠን ደስታን፥ ሰላምንና ዋስትናን በማምጣቱ የሚገኙት ምስጋናና አክብሮት ተጠቅሰው እናያለን። ከእግዚአብሔር ጋር በማያቋርጥ ጎብረት የምትኖር ነፍስ፥ እጅግ ክቡር በሆነው የእግዚአብሔር በረከት ውስጥ የሚገኘውን ነገር ማስተዋል ብቻ ሳይሆን፥ በሁሉም ረገድ እርሱን ማመስገንና ማክበር ሥራዋ ነው። "እግዚአብሔርን ለሚወዱ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ" ለሚያውቅ ሰው ይህ የተባረከ እውነት ነው (ሮሜ 8፡28)። ምንም ዓይነት ሁኔታ በሕይወት ዘመናችን ይግጠመን፥ የምንገነዘበው ነገር የእግዚአብሔር ፍቅር ኃይልና ጥበብ ድል ነሺ መሆኑን ነው። እውነተኛ አምልኮን ለማካሄድ የሚችሉት በመንፈስ የተሞሉ ሰዎች ብቻ ናቸው።

6. ጸሎት

የአማኝ የጸሎት ሕይወት ከመንፈሳዊ ሕይወቱ ጋር ሊነጣጠል በማይችል አኳኋን የተዋሐደ ነው። የመንፈስ ቅዱስ የማስተማር አገልግሎት በርካታ የእግዚአብሔር ቃል ተስፋዎችን ያስታውሰናል። የመንፈስ ቅዱስ ምሪት የእግዚአብሔርን የተገለጠ ፈቃድ በመለመን ረገድ በማስተዋል ለሚደረግ ጸሎት አስፈላጊ ነው። ጸሎት ለመንፈሳዊ ሕይወትም ሆነ እድገት እስትንፋስ በመሆኑ፥ ከልምምዳዊ ቅድስና ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው። የጸሎት አስፈላጊ ክፍል በሆኑት ምስጋናና ውዳሴ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት መኖሩ ግልጥ ነው። የመንፈሳዊ ሕይወት ገጽታ ሆኖ፥ ከጸሎትና ከመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ጋር ያልተያያዘ ነገር ጨርሶ የለም። የጸሎት ሕይወት የሚበለጽገው አማኙ በክርስቶስ ባለው መንፈሳዊ ሕይወት መጠን ነው።

በጸሎት ውስጥ ካሉት ከእነዚህ ግልጥ ጉዳዮች ሌላ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የምልጃ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ይነግረናል። በሮሜ 8፡26 እንዲህ ይላል፦ "እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል።" የዚህ አገልግሎት ባሕርይ ምን እንደሆነ የሚናገር መግለጫ የለም። ከክርስቶስ ምልጃ ጋርም የተያያዘ አይደለም። ነገር ግን የዚህ ክፍል ይዘት እንደሚያመለክተው፥ የሚገባንን ያህል መጸለይ ሲያቅተን፥ መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛ አካል እንደመሆኑ፥

በእኛ ውስጥ ባለው ስፍራ ሆኖ ስለ እኛ ይማልዳል። አገልግሎቱ የሚያስፈልገንን ነገር በመግለጥ፥ ጸሎታችንን በመምራት ከሰው ጥበብ በላይ የሆነውን ነገር እንድንለምን እንደሚያግዘን ጥርጥር የለውም። የመንፈስ ቅዱስ አግልግሎት በሁሉም ገጽታው ሲታይ፥ አስፈላጊ ከሆነ የጸሎት ሕይወት ፈጽሞ አይለይም።

7. አገልግሎት

ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሰፊው በተነጋገርንበት ክፍል፥ ፍጥረታዊው ሰው እግዚአብሔርን ማገልገል እንደማይችል ሁሉ፥ መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሉት አማኝም በስጦታዎቹ በሙላት ሊሠራባቸው የሚችለው፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲኖረው ብቻ መሆኑን ተመልክተናል። በዚህ መሠረት ለእግዚአብሔር የሚሰጥ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ፍሬያማ ይሆን ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መደገፍ አለበት። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚገኝ ገደብ የሌለው በረከት፥ በክርስቶስ ተገልጦ ነበር። "በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፥ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና" (ዮሐ. 7፡38-39)። በጥሩ ሁኔታ የተገለጠው ምሳሌ ስለ ፍጥረታዊው ሰው ብቁ አለመሆን፥ ስለ አገልግሎት፥ ስለ በረከት ምንጭ፥ ስለ "ሕይወት ውኃ ወንዝ" ይናገራል። ያ የበረከት ሁሉ ምንጭ የሚፈልቀው አማኝ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ጊዜ ሲሆን፥ ሊታገድ የማይገባው ነው። አማኝ በክርስቶስ የተፈጠረበትን መልካም ሥራ ሊያከናውን የሚችለው ይህ ሲሆን ብቻ ነው (ኤፌ. 2፡10)።

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት የሚሰጠው አገልግሎት፥ እንደ ሌሎቹ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ውጤቶች እርስ በርሱ የተዛመደ ነው። አገልግሎትና ልምምዳዊ ቅድስናችን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለን እውቀት፥ ምሪት፥ ዋስትና፥ አምልኮና የጸሎት ሕይወት የተለያዩ አይደሉም። ይልቁንም በአንድ ላይ ሲሆኑ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የሚሆን የተቀደሰ ሕይወት ይፈጥራሉ። ሰብአዊ ፍልስፍና ከሆነው ግላዊ እድገት ወይም ድርጊት ባሻገር፥ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን ለማንኛውም ክርስቲያን የልምምድና የፍሬያማነት ምንጭ ሆኖ እንዲገኝ የሚያደርግ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል። ይህ ብቻ አይደለም፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈስን ሳያጠፋና ሳያሳዝን በተጣመረ ጎብረት በመንፈስ እንዲመላለስም ይማጸናል።

— ክፍል ሰድሰት —

የመንፈስ ቅዱስ ትንቢቶች

24

መንፈስ ቅዱስ በታላቁ መከራ ዘመን

1. የዚህ የእምነት ትምህርት ቸል መባል

የወደፊቱን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በአሁኑ ጊዜ በሚገኙ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ በተጻፉ መጻሕፍቶችም ሆነ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች ትኩረት ያልተሰጠውና ጨርሶ የሌለ ጉዳይ ነው። እነ ሆጅ፥ ስትሮንግ፥ ሼድ፥ አሌክሳንደር [Alexander] ፥ ዋትሰን [Watson]፥ ዋርድሎው [Wardlaw]፥ ዶርነር [Dorner]፥ ዲክ [Dick]፥ ማይሊ [Miley]፥ ጌርሃርት [Gerhart]፥ ቢዩወል [Buell] ፥ ቫለንታይንን [Valentine] በመሳሰሉት በርካታ የሥነ-መለኮት ጠበብትና የበርክሃፍ [Berkhof] የቅርብ ጊዜ ሥራዎች ይህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አልተነካም። በተለይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰፊ ሥራ የሠሩና የጻፉ ካይፐር፥ ስሚተን፥ ሙል፥ ከሚንግስና ሲምፕሰንን የመሰሉ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን ስለሚያከናውነው ሥራ አንዳችም አልተናገሩም።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ በመጨረሻው ዘመን በሚገባ አለመገለጥ መነሻ የሆነ ዋና ምክንያት የሥነ-መለኮት አስተማሪዎች ወደፊት ሊሆኑ ባሉ ነገሮች ላይ ካላቸው ሦስት የተለያዩ አመለካከቶች የተነሣ ነው። የድህረ ሺህ ዓመት አገዛዝ አመለካከት [Postmillenialism/ፖስትሚሌኒያሊዝም] በትንቢት የተነገረው ሺህ ዓመት የሚፈጸመው፥ ባለንበት ዘመን በሚከናወን የወንጌል ስብከት፥ ወይም ‘‘መንፈሳዊ’’ በሆነውና በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ነው ይላሉ። ይህን ንድፈ አሳብ ከተቀበልን የአሁኑ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በዘመናት ሁሉ ውስጥ ይቀጥልና በመጨረሻው ፍርድ የሁሉ ነገር ፍጻሜ ሲሆን ይጠቃለላል። በዚህ ንድፈ አሳብ መሠረት የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት በመጨረሻው ዘመን በማለት ለይቶ ማመልከት አያስፈልግም። የአልቦ ሺህ ዓመት አገዛዝ አመለካከትም [Amillenialism/አሚሌኒያሊዝም] ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። ምክንያቱም አሁን ያለንበት ዘመን አንድ ሺህ ዓመት የሚባል መካከለኛ ነገር ሳይፈጥር ወደ ዘላለም ይገባል የሚል ስለሆነ ነው። ስለዚህ ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት ወደዚች ምድር ከተመለሰ በኋላ የአንድ ሺህ ዓመት ይኖራል ብለው የሚያምኑት ማለት ቅድመ ሺህ ዓመት አገዛዝ አመለካከት

[Premillenialism/ፕሪሚሌኒያሊዝም] ያላቸው ሰዎች ብቻ ይህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ሊኖራቸውና ስለ ጉዳዩ ገለጣ ሊሰጡ ይገባል።

በቅድመ ሺህ ዓመት አገዛዝ መምህራንና የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ጽሑፍ ይህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ቸል መባሉ ግን የሚያስገርም ነው። እንደ ቫን ኡስተርዚ [Van Oosterzee] ያሉ የቅድመ ሺህ ዓመት አገዛዝ አመለካከት ተከታዮች፥ ይህን አቋማቸውን ለመደገፍ አነስተኛ ማብራሪያና መከላከያ ያቀረቡ ሲሆን፥ በሺህ ዓመቱ አገዛዝ ወቅት መንፈስ ቅዱስ ስለሚኖረው አገልግሎት ለተነገረው ትንቢት አንዳችም ትኩረት አልሰጡትም። ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ለሌሎች ዋና ዋና ትንቢቶች ነው። በዚህ ምክንያት፥ በታላቁ መከራና በሺህ ዓመቱ መንግሥት አገዛዝ ወቅት መንፈስ ቅዱስ ስለሚኖረው አገልግሎት ለተነገረው ትንቢት ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ ሆኗል።

የተለመደው የቅድመ ሺህ ዓመት አገዛዝ አቋም ለዚህ ውይይት እንደ መሠረት ተወስዷል። ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ ሊል ከተመለሰ በኋላ ለግምት የሚያስቸግር ታላቅ መከራ በዓለም ላይ እንደሚኖር ቅዱሳት መጻሕፍት ይተነብያሉ። በዳንኤል 9፡27 የተገለጠው ለሰባት ዓመታት ያህል የሚካሄደው የመከራ ዘመን በመጠኑ እንዲያጥር የተደረገ ሲሆን (ማቴ. 24፡22)፥ ይህ የመከራ ዘመን እያንዳንዳቸው ሦስት ዓመት ተኩል በሚፈጁ ሁለት ጊዜያት ተከፍሏል። ሁለተኛው ሦስት ዓመት ተኩል በበርካታ ኃጢአት መገለጥና በኃጢአት ላይ በሚመጣ መለኮታዊ ፍርድ ምክንያት "ታላቁ የመከራ ዘመን" በመባል ይታወቃል። ይህ የመከራ ጊዜ በድንገት የሚፈጸመው ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት በሚመለስበት ጊዜ ሲሆን፥ ከዚህ በኋላ ሁለንተናዊ ጽድቅና ሰላም የሚሰፍንበት የአንድ ሺህ ዓመት መንግሥት ይመሠረታል። ይህ አንድ ሺህ ዓመት የሚያበቃው ለመጨረሻ ጊዜ በሚስፋፋ ኃጢአት ነው። ያኔ ክፉዎች የመጨረሻ ፍርድ ይፈረድባቸውና አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ተመሥርቶ ጽድቅ የሰፈነበት ዘመን ይጀመራል። በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ ለትንቢቶች ፍጻሜ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎቱን ይሰጣል። ያኔ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ካለው ሥራ የተለየ መሆኑ ግልጥ ነው። ስለዚህ ጉዳይ የሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሰፊ ባይሆንም፥ አንዳንድ ጠቃሚ ነጥቦችን ማመልከቱ ግን እርግጥ ነው።

2. በደኅንነት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

በታላቁ መከራ ዘመን ብዙዎች ይድናሉ። ስለ መከራው ዘመን ከቀረቡ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች አንዱ ወደዚህ ዘመን የሚገቡ ሰዎች ሁሉ በማይለወጥ ውሳኔ ይጠፋሉ የሚል ነው። ባለንበት የጸጋ ስፍረ-ዘመን

የወንጌል ቃል ለመስማትና ክርስቶስን ለመቀበል ዕድል ያገኙት ሰዎች በታላቁ የመከራ ዘመን ቢኖሩ ኖሮ ወንጌልን ለመቀበል የሚኖራቸው ዕድል እጅግ ጠባብ ይሆን ነበር። በመከራው ዘመን የሚድኑ አንዳንድ ነፍሳት የዘመኑን ታላቅ ሥቃይ በማለፍ ወደ ሺህ ዓመቱ አገዛዝ ሲገቡ፥ ሌሎቹ ሰማዕታት ሆነው ያልፋሉ። የቤተ ክርስቲያን ከሰባቱ ዓመት መከራ በፊት መነጠቅ፥ ክርስቲያኖች ሁሉ ከዓለም እንዲወሰዱ ያደርጋል። ይሁን እንጂ ወዲያውኑ የእስራኤል መንፈሳዊ ዕውርነት በከፊልም ቢሆን ስለሚበራ (ሮሜ 11፡25)፤ ከመካከላቸው በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ለረጅም ጊዜ ከደውት ወደነበረው መሢሕ ይመለሳሉ። ከአሕዛብ መካከልም ከሁሉም ሕዝብና ቋንቋ የሚድኑ ይኖራሉ (ራእይ 7፡9-17)። የክህደቱ ዘመን በክፋት የተሞላ ቢሆንም፥ ከፍተኛ የመከር መሰብሰቢያ ጊዜ ይሆናል። በዚህ እውነታ መሠረት ያየነው እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን ማገልገሉ የግድ አስፈላጊ ነው።

የኢዩኤል ትንቢት። ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ ዕለት ስብከቱ መግቢያ ላይ በብሉይ ኪዳን የታወቀውን ትንቢት ጠቅሷል፦

> "እግዚአብሔር ይላል፦ በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፥ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዞቻቸውም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤ ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፥ ትንቢትም ይናገራሉ። ድንቆችን በላይ በሰማይ፥ ምልክቶችንም በታች በምድር እሰጣለሁ፤ ደምም እሳትም የጢስ ጭጋግም ይሆናል፤ ታላቅ የሆነ የተሰማም የጌታ ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ፥ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ። የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል" (የሐዋርያት ሥራ 2፡16-21ን ከኢዩኤል 2፡28-32 *ጋር ያነጻጽሩት*)።

ትንቢቱ በተለይ ከአሁኑ ዘመንና በጰንጠቆስጤ ዕለት ከተከናወኑት ነገሮች ጋር የተያያዘ ነው። ይህን ክፍል በጥንቃቄ ማጥናት ትንቢቱ በከፊል ብቻ የተፈጸመ መሆኑን ለመረዳት ያስችላል። የኢዩኤል ትንቢት ሙሉ በሙሉ የሚፈጸመው፥ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ዓላማ በሚሞላ ጊዜ ነው። በሰማይና በምድር የሆኑት ድንቆችና ምልክቶች (ሐዋ. 2፡19-20) በጰንጠቆስጤ ዕለትም ሆነ ከዚያ ቀጥሎ ባለው የክርስትና ዘመን የተፈጸሙ አይደሉም። በዮሐንስ ራእይ እንደተገለጠው ይህን ዝርዝር ለማሟላት የቀረው ነገር የሚፈጸመው በታላቁ መከራ ጊዜ ነው።

በሐዋርያት ሥራ 2፡21 የሚገኘው አንድ ዋና እውነት፦ "የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል" የሚለው ነው። ይህ በጸጋ ስፍረ-ዘመን

የሚሠራበት ሥርዓት ሲሆን፥ በመከራው ዘመንም ይቀጥላል። ከሰው ልብ የተፈጥሮ ዕውርነትና ከመንፈስ ቅዱስ የማሳመን ሥራ ውጭ ፍጥረታዊው ሰው ወንጌልን ለመረዳት ካለመቻሉ አንጻር (ዮሐ. 16፡7-11) ስንመለከተው፥ የመንፈስ ቅዱስ ለጠፋው ሰው ደኅንነትን የመግለጥ ሥራ በመከራው ዘመንም የሚቀጥል መሆን አለበት ለማለት ያስችለናል። የታላቁ መከራ ጊዜ ዋና መገለጫ የሆነው መንፈሳዊ ጨለማ፥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የግድ አስፈላጊ ያደርገዋል። በዚህ ዘመን ክርስቶስ በተለይ የእስራኤል አዳኝና መሢሕ መሆኑን የሚያመለክቱ አገልግሎቶች እንደሚኖሩ ለመገመት እንችላለን።

የእስራኤል ተስፋ። ክርስቶስ ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ንግግር (ዮሐ. 3፡1-21)፥ በታላቁ መከራ ጊዜ ደኅንነት እንደሚኖር የሚያረጋግጥና ይህም ሥራ የመንፈስ ቅዱስ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ለአንድ እስራኤላዊ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት መንፈሳዊ የሆነው የእግዚአብሔር መንግሥት አካል ከመሆን የላቀ ነገር ነበር። የክርስቶስን በምድር መንገሥ የሚመለከተው አሳብ ለእስራኤል ፖለቲካዊ፥ የሚታይ፥ ግብረ ገባዊ መንግሥትና መንፈሳዊ ነገርንም የያዘ ነበር። የእስራኤል ተስፋ ያለው በመንግሥት ሰማያት አልነበረም። እንደዚህ ያለውን አሳብ በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ብንፈልግ አናገኘውም። ተስፋ የሚያደርጉት መንፈሳዊ የሆነ፥ ፖለቲካዊና የሚታይ አዲስ የክርስቶስ መንግሥት በምድር ላይ ይኖራል ብለው ነበር። ተስፋቸው በሰማይ አልነበረም። በአሳባቸው የደኅንነትና የመንፈሳዊ ዳግም ልደት ጉዳይ ያለ ቢሆንም፥ ያ ሁኔታ የወደፊቱ ምድራዊ መንግሥት መግቢያ መንገድ ተደርጎ ነበር የሚታየው።

የድህረ ሺህ ዓመት አገዛዝ አስተሳሰብና የአልቦ ሺህ ዓመት አገዛዝ አስተሳሰብ አራማጆች በአሁኑ የጸጋ ዘመን ምስጢራዊ በሆነ መንገድ አለ በሚሉት መንፈሳዊ መንግሥት በመተካት የፖለቲካዊ መንግሥት አስተሳሰብን ያስወግዳሉ። ነገር ግን የእነዚህ ሁለት አስተሳሰብ አራማጆች ስለ ምድራዊ መንግሥት በግልጥ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ማብራራቱ ያስቸግራቸዋል (ኢሳ. 11)። ለዚህ ነው ለኒቆዲሞስ ወደ መንግሥቱ ለመግባት ዳግም መወለድ እንደሚያስፈልግ ክርስቶስ በነገረው ጊዜ ይህን እውነት አስቀድሞ ባለመረዳቱ የተገረመው። ክርስቶስ ወደ መንፈሳዊ መንግሥት ለመግባት አዲስ ልደት እንደሚያስፈልግ መናገሩ ብቻ ሳይሆን ወደ አንድ ሺህ ዓመት መንግሥት ለመግባትም ዳግም ልደት እንደሚያስፈልግ መግለጡ ነበር። በዚህ መሠረት የእግዚአብሔር መንፈስ፥ ሰዎች ክርስቶስ እንደሚያስፈልጋቸውና የደኅንነት መንገድ ምን እንደሆነ መግለጥ ብቻ ሳይሆን፥ የሚያምኑ ዳግም እንዲወለዱ ያደርጋል። በዚህ

ሁኔታ ወዲያውኑ የዘላለምን ሕይወት ይቀበላሉ፥ የመከራውን ዘመን ካለፉ በኋላም ወደ አንድ ሺህ ዓመት መንግሥት ይገባሉ።

በተለይ እስራኤል በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ በምትመለስበት ጊዜ ዳግም ልደት የምታገኝ መሆኑ በተሰጣት ቃል ኪዳን ተገልጧል። በረከቱን የሚቀበሉት የሚያምኑት እስራኤላውያን ብቻ መሆናቸውን የምናረጋግጠው፥ በታላቁ መከራ ዘመን በሚመጣባቸው መከራ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ተገድለው አንድ ሦስተኛ ብቻ የሚቀሩበት ሁኔታ በመኖሩ ነው (ዘካ. 13፡8-9)።

3. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በታላቁ መከራ ጊዜ በሚኖሩት አማኞች ሕይወት

መንፈስ ቅዱስ በታላቁ መከራ ጊዜ ለሚድኑ ሰዎች ስለሚያከናውነው አገልግሎት የተሰጠው አሳብ አብዛኛው ይህን ይመስላል ከሚል የራስ መረዳት የመጣ ነው። በዚህ ዘመን ግን መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ማገልገሉ የታገደ ቢመስልም፥ ያለማቋረጥ መቀጠሉ ግልጥ ነው። በታላቁ መከራ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች እንደሚያድር በማስገንዘብ የሚቀርበው ማስረጃ በጣም አነስተኛ ነው። ያኔ አማኞች በሙሉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ይሆናሉ የሚለው ንድፈ አሳብ ተቃውሞ የገጠመው በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡7 ያለውና ዓለምን ከኃጢአት የሚከለክል፥ ማለት መንፈስ ቅዱስ፥ በታላቁ መከራ ጊዜ ‘‘ከመንገድ ይወገዳል’’ በሚለው አሳብ ነው። የሚከለክለው ነገር አጠቃላይ ባይሆንም (ራእይ 7፡3፤ 12፡6፥ 14-16) የታላቁ መከራ ዘመን ዋና ባሕርይ የክፋት መንፈስ ነው። የመንፈስ ቅዱስ በቅዱሳን ውስጥ ማደር ኃጢአትን ለመከልከል የሚረዳ ሲሆን፥ እርሱም በዚያ ዘመን ይወሰዳል። የታላቁ መከራ ዘመን በብዙ መልኩ ወደ ብሉይ ኪዳን የሚመለስ ይመስላል። በብሉይ ኪዳን ዘመን በርካታ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና በርሱም ለአገልግሎት መታጠቅ የነበረ ቢሆንም፥ በቋሚነት የርሱ ማደሪያ መሆን ግን አልፎ አልፎ ካልሆነ በተቀር የሚገኝ አልነበረም። ሁኔታዎችን ሁሉ ከግምት ውስጥ ካስገባን በታላቁ የመከራ ዘመን መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የሚያድር መሆኑን የሚያስረዳ ምንም መረጃ የለም። በታላቁ የመከራ ዘመን መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ያድራል ካልን፥ በመንፈስ ቅዱስ መታተማቸው የተረጋገጠ ይሆናል። ይህ መታተም ደግሞ የእርሱ በአማኞች ውስጥ መገኘት ነው።

በመከራው ዘመን መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሁሉ ውስጥ ባያድርም፥ አንዳንዶች በመንፈስ እንደሚሞሉና ለምስክርነት በርሱ ኃይል

እንደሚታጠቁ ግልጥ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ የመከራ ዘመን በዓለም ሁሉ ወንጌል እንደሚሰበክ በማስረጃ ተረጋግጧል (ማቴ. 24፡14)። የመመስከር ኃይል ምንጊዜም የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ቢሆንም፥ ይህ ጊዜያዊ ከሆነው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር እንጂ ቋሚ ከሆነው የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ጋር የግድ የሚያያዝ አይደለም። በታላቁ መከራ ጊዜ ለእምነታቸው ሲሉ የሚሞቱ ሰማዕታት የሚያገኙት መንፈሳዊ ድል፥ ከመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ኃይል ውጭ ይቻላል ብሎ መገመት ፈጽሞ አስቸጋሪ ነው። በታላቁ መከራ ጊዜ የሚፈጸመው ማንኛውም ዓይነት መንፈሳዊ ስኬት ከእግዚአብሔር ኃይል ውጭ የሚቻል አይደለም።

4. በታላቁ መከራ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውሱን ነው

በታላቁ የመከራ ዘመን፥ ለመንፈስ ቅዱስ በሙላት ማገልገል አመቺ ሁኔታዎች አይኖሩም። ቀዳሚነት ካለው የጸጋ ዘመንና ቀጥሎ ከሚመጣው የአንድ ሺህ ዓመት መንግሥት ጋር ሲነጻጸር፥ ታላቁ የመከራ ዘመን ወደር በሌለው አኳኋን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትና ዓመፅ የሚሠራበት ነው። ለሚያምኑ ሁሉ ደኅንነት የሚቻል ቢሆንም፥ የዳኑ ሰዎች ቁጥር ከአሁኑ የጸጋ ዘመን ጋር ሲነጻጸር በጣም አነስተኛ ይሆናል። የሐሰት ትምህርቶች፥ ማታለልና ክህደት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ይወገዳል (2ኛ ተሰ. 2፡7)።

በዚህ ዘመን የሚጎድለው የመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ትልቅ አገልግሎት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከጰንጠቆስጤ ዕለት በፊት ሁልጊዜ የወደፊት ጉዳይ ተደርጎ ይታይ ነበር። ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በኋላ፥ በታላቁ መከራ ጊዜም ሆነ በሺሁ ዓመት መንግሥት ጨርሶ አይገኝም። የክርስቶስ አካል ከሆነች ቤተ ክርስቲያን ውጭ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚናገር ትንቢት አናገኝም (1ኛ ቆሮ. 12፡13)። መንፈስ ቅዱስ በታላቁ መከራ ጊዜ አገልግሎቱን ቢቀጥልም በምንም አኳኋን ወደ አንድ ሕያው አካል የሚደርስ የአማኞች የአካል አንድነት የለም። ከዚህ ይልቅ ወደ ብሔራዊ መለያና፥ ለአንድ ሺህ ዓመት መንግሥት በሚደረገው ዝግጅት ለሕዝቡ የተገባው ቃል ወይም የተሰጠው ተስፋ ወደሚፈጸምበት ሁኔታ መመለስን ያመለክታል።

25

መንፈስ ቅዱስ በሺሁ ዓመት መንግሥት

1. መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን በመከላከል ተግባር

ከስፍረ-ዘመናት ሁሉ እጅግ የከበረው ይህ የሺህ ዓመት መንግሥት መሆኑ እርግጥ ነው። በዚህ ዘመን ጽድቅ በሙላት ይገለጣል፥ ዓለም አቀፋዊ ሰላምና ብልጽግና ይሰፍናል። ክርስቶስ በምድር ሁሉ ይገዛል፥ አሕዛብም ሁሉ ኢየሱስን ያውቃሉ። ስለዚህ ምድር ሁሉ ከአጽናፍ አጽናፍ እርሱን በማወቅ ትሞላለች። በዚያ መንግሥት ዘመን ሰይጣን ስለሚታሰር፥ ምንም ዓይነት የአጋንንት ሥራ አይኖርም። የኃጢአት ባሕርይ ከድካሙ ጋር ቢኖርም ሰውን ለኃጢአት የሚያነሣሣ ውጫዊ ፈተና ግን አይኖርም። ከሞት የሚነሡት ቅዱሳን በምድር የሚሰጡት አገልግሎት ልዩ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። የሺህ ዓመቱ መንግሥት ከሌሎቹ ስፍረ-ዘመናት በላቀ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ በሙላትና በኃይል አገልግሎቱን የሚገልጥበት ዘመን ነው። ይህ የሺህ ዓመቱ ዘመን በአሁኑ ስፍረ-ዘመን እንደሚሆነው በጸጋ የምንመላለስበት ሳይሆን፥ ሰው ሁሉ በንጉሡ በኢየሱስ ሕግ ሙሉ ለሙሉ የሚመራበት ወቅት ነው።

ከወቅቱ አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ከጨለማ ኃይላት ጋር የሚደረግ መንፈሳዊ ጦርነት እንደማይኖር ለመረዳት ይቻላል። መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ሥራ የሚያከናውነው በሰው ልብ ውስጥ ያለውን የኃጢአት መገለጥ በሚመለከት ብቻ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያመለክቱት ወደ ሺህ ዓመት መንግሥት በሥጋ የሚገቡት ሁሉ የሚድኑ ከሆነ፥ መንፈስ ቅዱስ ከውስጥ ኃይልን ይሰጣቸዋል። በዚህም መሠረት ዛሬ በዚህ ክፉ ዓለም እንደሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከላከሉ ተግባር የሚያስፈልገው አይሆንም። በፍጥረት ላይ ያለው እርግማን በሺሁ ዓመት መጀመሪያ ላይ ስለሚነሣ የሰው ልጅ፥ በተለይም ያኔ የሚወለዱ ሰዎች ዕድሜ ረጅም ይሆናል። በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ በምድር የሚኖረው አብዛኛው ሰው ሺሁ ዓመት ከተጀመረ በኋላ የተወለደ እንደሚሆን ለመገመት እንችላለን። በዚያ ዘመን የሚወለዱ ሰዎች ወላጆቻቸው እንዳደረጉት ሁሉ በክርስቶስ በማመን መዳን ይገባቸዋል። በክርስቶስ ላይ የሚነሣ ማንኛውም ዓመጽ ወዲያውኑ የሚቀጭ ሲሆን፥ ዓመጸኞች ሁሉ ቢያንስ በእርሱ የማመን ውጫዊ ምልክት ወዲያው

ያሳያሉ። ከዚህ ማረጋገጫ በመነሣት ነው የዓመፀኞች የመጨረሻ ኃጢአት በአንድ ሺሁ ዓመት ማጠቃለያ አካባቢ የሚፈጸመው። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከክርስቶስ ሉዓላዊ አገዛዝ ጋር የሚሄድ መሆኑ ምንም አያጠራጥርም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በሺሁ ዓመት ኃጢአትን ለመከልከል የሚያከናውነውን ሥራ በሚመለከት ቅዱሳት መጻሕፍት ያለው መረጃ በጣም አነስተኛ ነው። ስለዚህ ቀደም ባሉት ዘመናት መንፈስ ቅዱስ ያከናውነው ከነበረ ሥራ በመነሣት ጉዳዩን ማጤን ያስፈልጋል።

2. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በደኅንነት ውስጥ

አስቀድመን እንደገለጥነው በሺሁ ዓመት ውስጥ የሚወለዱ ልጆች የኃጢአት ደኅንነት ያስፈልጋቸዋል። በዚህ ዘመን በእምነት ወደ ክርስቶስ የሚመጡት ሰዎች መጠን በመቶ እጅ ስናነጻጽረው ከማንኛውም ዘመን የሚበልጥ መሆኑ ጥርጥር የለውም። በርካታ ጥቅሶች የዚህን ደኅንነት ፍጻሜ ይጠቁማሉ። ሕዝቅኤል 36፡25-31 ስለ እስራኤል ደኅንነት መፈጸም ይናገራል። ከኃጢአት ይነጻሉ፥ አዲስ ልብ ይሰጣቸዋል፥ ከኃጢአት ኃይል ይድናሉ። በተለይ በሺሁ ዓመት መንግሥት ዘመን መጀመሪያ ላይ ደኅንነት ሁለንተናዊ እንደሚሆን ኤርምያስ 31፡31-34 ላይ በሥዕላዊ አኳኋን ቀርቧል። በርካታ ጥቅሶች ይህንኑ አሳብ ይደግፋሉ (ኢሳ. 44፡2-4፤ 60፡21፤ ኤር. 24፡7)። ይህ በረከት አሕዛብንም ይጨምራል (ዘካ. 14፡16)።

ሕዝቅኤል 36፡25-31 እና ዮሐንስ 3፡1-21 ውስጥ የደኅንነቱ ሁኔታ ዳግም ልደትን እንደሚጨምር በግልጥ ተጽፏል። መዳን የሚገኘው በክርስቶስ በማመን ሲሆን፥ የርሱ በአካል መገኘትና ኃይሉ የማዳን ችሎታውን በቀላሉ ያስረዳል። ለሚያድን እምነት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊነት የማይቀር ነው፤ ይህም ሊሆን የቻለው ሰው በዚህ ዘመን ለደኅንነት ያለው ውሱንነት ያኔም ስለሚኖር ነው። በሺህ ዓመቱ ዘመን ሰይጣን ቢታገድም ሰው የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ያስፈልገዋል። የሺህ ዓመቱ መንግሥት ዘመን ነፍሳትን በማዳን ረገድ የእግዚአብሔር ኃይል የመጨረሻው መግለጫ ነው።

3. በሺህ ዓመቱ መንግሥት መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ

ቀደም ሲል የጠቀስናቸውና ስለ ሺሁ ዓመት የተነገሩት ትንቢቶች፥ ከየትኛውም ስፍረ-ዘመን ይልቅ በሺህ ዓመቱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በአማኙ ሕይወት ውስጥ የተትረፈረፈ እንደሚሆንና በሰፊው እንደሚገለጥ ይመሰክሩልናል። ልክ እንደ አሁኑ ዘመን አማኞች በሙሉ

የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደሚሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ የተረጋገጠ ነው (ሕዝ. 36፡27፤ 37፡14ን ከኤርምያስ 31፡33 ጋር ያነጻጽሩት)።

መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ የሚያሩ እውነት በሕዝቅኤል 36፡24 እና በተከታዮቹም ቁጥሮች የተገለጠው፥ የከበረው የእስራኤል ተሐድሶ አንድ ክፍል ሆኖ ነው። ከዚህ ጋር በማያያዝ ሕዝቅኤል እንዲህ በማለት ተንብይዋል፦

> ‹‹ከአሕዛብ መካከል አወጣችኋለሁ፥ ከየአገሩም ሁሉ እሰበስባችኋለሁ፥ ወደ ገዛ ምድራችሁም አመጣችኋለሁ። ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ፥ እናንተም ትጠራላችሁ፥ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖታችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ። አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፥ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፥ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፥ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ፥ በትእዛዜም አስሄዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ፥ ታደርጉትማላችሁ›› (ሕዝ. 36፡24-27)።

በሕዝቅኤል 37፡14ም፦ ‹‹መንፈሴን በውስጣችሁ አሳድራለሁ፥ እናንተም በሕይወት ትኖራላችሁ›› ተብሎ ተጽፏል። ይህም እግዚአብሔር ሕጉን በልባቸው እንደሚያኖር በኤርምያስ 31፡33 ከተነገረው ጋር የሚገናኝ መሆኑ ግልጥ ነው። በሺህ ዓመት መንግሥት የክርስቶስ በክብር መገኘት፥ የመንፈስ ቅዱስን በቅዱሳን ውስጥ በይበልጥ መታየት ተገቢ ያደርገዋል።

በሌሎች ዘመናት አዘውትሮ ካለመኖሩ ጋር ሲነጻጸር የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሺህ ዓመቱ መንግሥት ዘመን የተለመደ ይሆናል። የሚገለጠውም በአምልኮና ጌታን በማመስገን፥ እንዲሁም በፈቃደኝነት በመታዘዝ፥ በመንፈሳዊ ኃይልና በውስጣዊ የሰው ለውጥ ነው (ኢሳ. 32፡15፤ 44፡3፤ ሕዝ. 39፡29፤ ኢዩ. 2፡28-29)። ባለንበት ዘመን ካለው መንፈሳዊ ግድየለሽነት፥ መቀዝቀዝና ዓለማዊነት አንጻር ሲታይ መንፈሳዊ ጥማት፥ የእግዚአብሔር ፍቅር፥ ቅዱስ ደስታ፥ ሁለንተናዊ መንፈሳዊ ግንዛቤ፥ እንዲሁም ከቅዱሳን ጋር አስደናቂ የሆነ ኅብረት ይኖራል። በጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን ይታይ የነበረው መንፈሳዊ አንድነትና በረከት በሺሁ ዓመት መንግሥት ዘመንም በዓለም ሁሉ የሚኖሩ ቅዱሳንን ኅብረት የሚያሳይ ይሆናል። ትኩረቱ በጽድቅ፥ በሕይወትና በመንፈስ ደስታ ላይ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በክርስቶስ ላይም ይሆናል (ኢሳ. 11፡2)፥ በርሱነቱና ምድርን በጽድቅ በመግዛቱ አማካይነትም ይገለጣል። የሺሁ

ዓመት መንግሥት ዘመን ዘላለማዊው መንግሥት ከመምጣቱ በፊት የእግዚአብሔር ልብ የሚገለጥበት የመጨረሻ ዘመን ነው። በእርሱም እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ጻድቅ፥ የደስታና የሰላም ሁሉ ምንጭ ሆኖ ይገለጣል። በዚያ ዘመን መጨረሻ ገደማ ሰዎች የኃይሉን የከበረ ማረጋገጫ ካዩ በኋላ እንኳ ለመታዘዝ ፈቃደኞች ባለመሆን በልባቸው በእግዚአብሔር ላይ እንደሚያምፁ እናያለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱትና በአሁኑ ጊዜ ሲሠሩ ከምናያቸው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ሁሉ፥ በጸጋ ስፍረ-ዘመን ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሳይጨምር ሁሉም አገልግሎቶች በሺሁ ዓመት ዘመን ይገኛሉ። በዓለም ላይ ክህደት እየጨመረ በሚሄድበትና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆኑ ሰዎች እንኳ ለመንፈስ ቅዱስ ግድየለሽነትን በሚያሳዩበት ወቅት ብንኖርም፥ ሊመጣ ስላለው ዘመን ሁኔታ አርቀን ለመመልከት እንችላለን። የመግዛት መብት ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ስንጠብቅ በውስጣችን ላደረው መንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ብንሰጥና በእርሱ ብንደገፍ፥ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ሊያፈራና የዚህ ፍሬ ጣፋጭ ሽታም በሕይወታችን ሊገኝ ይችላል።

— ክፍል ሰባት —

ታሪክ

26

የመንፈስ ቅዱስ ትምህርተ-ሃይማኖት አጭር ታሪክ

የመንፈስ ቅዱስ ትምህርተ-ሃይማኖት በአብዛኛው በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የሚደረግ ጥናት ነው። ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የመረዳት ችግር በተማሩ ሰዎች ዘንድ እንኳን ይታያል። ይህ የሚሆነው ከእውቀት ማነስ ሳይሆን፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጡትን ቀጥተኛ ትምህርት ካለመረዳት ነው። የመሠረታዊው ትምህርት ታሪክ ይበልጥ ግልጥ የሚሆነው በቅድሚያ ቅዱሳት መጻሕፍትን፥ ቀጥለን ደግሞ ታሪኩን በጥንቃቄ ስናጠና ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ታሪክ በርካታ ሥነ-ጽሑፎች አሉ።$

በዚህ ክፍል አጠር ብሎ የቀረበው አሳብ፥ ሌሎች የደከሙበት ሲሆን፥ በጣም አስፈላጊ የሆነ ማጠቃለያ ተሰጥቶታል። በመሆኑም ዋና ዋና የሆኑ ሰፊ ሥራዎችን ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች የሚረዱ ጎላ ጎላ ያሉ ነጥቦችና ማረጋገጫዎች ቀርበዋል።

የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ታሪክ ያየን እንደሆነ በቀላሉ በታሪክ ወቅቶች ሊከፋፈል የሚችል አይደለም።

ከመጀመሪያው አንሥቶ ዋና ዋናዎቹ ገጽታዎች በቀድሞ አባቶች አእምሮ ውስጥ የነበሩ ሲሆን፥ በተለያዩ መንገዶች ተገልጠዋል። ቴክኒካዊ የሆኑት ቃላት ግን ቀስ በቀስ የተቀመሩ ናቸው። የአብዛኛዎቹ ክፍፍል የተመሠረተው የቀድሞ አባቶች በሚያምኑበት ነገር ሲሆን፥ ያ ወደ ሥነ-መለኮት ትምህርት መግለጫነት አልተለወጠም። ቢሆንም የዚህን ትምህርተ-ሃይማኖት ታሪክ የራሳቸው ባሕርይ ባላቸው ስምንት ክፍሎች መከፈል ይቻላል፦

1. ቅድመ ኒቅያ ዘመን (100-300)፥ 2. የኒቅያ ዘመን (300-325)፥ 3. ድህረ ኒቅያ ዘመን (325-451)፥ 4. መካከለኛው ዘመን (451-1100)፥ 5. ቅድመ ተሐድሶ ዘመን (1100-1517)፥ 6. የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ዘመን (1517-1600)፥ 7. ድህረ ተሐድሶ ዘመን (1600-1800)፥ 8. የአሁኑ ዘመን (1800-)።

1. ቅድመ ኒቅያ ዘመን

በ325 ዓ.ም. ከተካሄደው ከኒቅያ ጉባዔ በፊት የነበሩት ዘመናት በአጠቃላይ ሲታዩ፥ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች የተቀነባበሩባቸውና ዝግጅት የተደረገባቸው ቢሆኑም፥ በተለይ የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት በሚመለከት በርካታ ምስክርነት የተሰጠባቸው ናቸው። የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች በሚመለከት ልዩነት የነበረ ቢሆንም፥ ከሥነ-መለኮት ትምህርት ይልቅ ለተግባራዊና ለመንፈሳዊ ገጽታው ትኩረት የተሰጠበት ዘመንም ነው። የመንፈስ ቅዱስ ትክክለኛ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ባጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘው፥ በሚከተሉት ነገሮች አማካይነት በተገኘው ምስክርነት ነው፦ (1) የጥምቀት ሥርዓተ ደንብ፥ (2) የሐዋርያት የእምነት መግለጫ፥ (3) ቀደም ሲል የነበሩ መዝሙሮችና ቅዳሴዎች፥ (4) ቀደም ሲል በተከሠቱ ስሕተቶች ላይ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበችው ጽኑ ተቃውሞ። በሁለተኛውና በሦስተኛው ምዕተ ዓመት የነበሩ ቀደምት ጸሐፊዎች የተጠቀሙበት የቋንቋ ዘዴ ሁልጊዜ ትክክል ባይሆንም፥ ዓላማቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት አሳብ ላለመራቅ እንደነበር ግልጥ ነው። ምስጋናንና ክብርንም ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስ፥ ለአብና ለወልድ ይሰጡ ነበር። የኑፋቄ አመለካከት የነበራቸው እንደ ግኖስቲኮች [Gnostics/ ናስቲክስ]፥ ኢቦናይቶች [Ebionites] እና የስምዖን ማግነስ [Simon Magnus] ተከታዮች የሆኑ ክፍሎች፥ ሁልጊዜ የነበሩ ቢሆንም፥ በአጠቃላይ ከክርስቲያናዊው ጎብረት የተወገዱ ስለነበሩ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ እንደሆኑ መቁጠር ይቻላል።

ስለ መንፈስ ቅዱስ መለኮትነት የተሰጡ ቀደምት ምስክርነቶች በርካታ ናቸው። ፊሸር [Fisher] እንደተባለው ሰው አመለካከት፥ ‘‘የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውናና የተለየ ሥራውን አግናጢዮስ [Ignatius] መንፈሳዊ መምህር በግልጥ አቅርቦታል።’’ የሮማው ቀሌምንጦስ [Clement] (100 ዓ.ም.) ሲጽፍ፥ ‘‘አንድ አምላክ፥ አንድ ክርስቶስና ለእኛ የፈሰሰ አንድ የጸጋ መንፈስ የለንምን?’’ ብሏል። እንደ ስሚተን አመለካከት፥ ጀስቲን ማርቲር [Justin Martyr] የተባለው ሰው፥ ‘‘መንፈስ ቅዱስ የራሱ የተለየ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ጽኑ ምስክርነት የሰጠ ነው።’’ ኤሬኔዎስ [Irenaeus]፥ መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ ጥንኛ፥ ወልድም የአብ ጥንኛ እንደሆነ አድርጎ ቢናገርም፥ የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነትና ዘላለማዊነት አረጋግጧል። የእስክንድርያው ቀሌምንጦስ (150-215) የአብን፥ የወልድን፥ የመንፈስ ቅዱስን ‘‘ሥሉስነት’’ በሚመለከት የተናገረ ሲሆን፥ መንፈስ ቅዱስ ግን በራሱ አካል መሆኑን

አረጋግጧል። ስሚተንም፥ ‘‘በ175 ዓ.ም. የነበረው የአንጾኪያው ቴዎፍሎስ [Theophilus of Antioch] በእግዚአብሔር ውስጥ ሦስትነት እንዳለ ይናገራል’’ ብሏል። ተርቱሊያን [Tertulian] መለኮታዊ ባሕርይን ለመግለጥ (160-220 ዓ.ም.) ሥላሴ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በመጠቀሙ ባለውለታችን ነው።

ከቀደሙት ምሁራን በቀጥታ ከሚጠቀሱት ቁምነገሮች ሌላ፥ በጸሎት መጻሕፍት ውስጥም በጣም ጠቃሚ ነገሮች ተገኝተዋል። ስለዚህ ጉዳይ ግሪፊስ ታመስ [Griffith Thomas] የሚከተለውን ተናግሯል፦ ‘‘ብዙ አሳብ ባልነበረበት በዚህ ዘመን እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሚመለከት ጥንካሬ ያለው መረጃ የሚገኘው፥ በቤተ ክርስቲያን የጸሎት ሕይወት ውስጥ ነው። በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ዘንድ ያለውን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት እውነታ በሚመለከት የሕይወት ልምምድ ከሁሉም የተሻለ ምስክር መሆኑ ተረጋግጧል። በዘመናችን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሚመለከቱት ማስረጃዎች ሁሉ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ እውነተኛነት አጠያያቂ ያልሆነ ምስክርነት ይሰጣሉ።’’ ስዊትም [Swete] ወደዚሁ ተመሳሳይ መደምደሚያ የሚያደርስ ምስክርነት ሰጥቷል፦ ‘‘የጥንት ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቋንቋ፥ መሪ የሆነ የመሠረታዊ የእምነት ትምህርቷ መግለጫ እንደነበረ እርግጥ ነው፥ በክርስቲያን ሃይማኖታዊ ሕይወት ውስጥ ለሥላሴ የሚሰጥ አምልኮ የቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊ ትምህርት ከመሆኑ በፊት እንኳ ነበር።’’

በሁለተኛውና በሦስተኛው ምዕተ ዓመት የተከሠተው የኑፋቄ ማዕበል፥ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ቸል በመባል ፋንታ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው አድርጓል። ግኖስቲኮችና ሌሎች መናፍቃን ከመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ይልቅ ለክርስቶስ አካላዊ ሕልውና የበለጠ ትኩረት እንዲሰጠው አድርገዋል። ይህ እንቅስቃሴ መደበኛ የሆነው የኒቅያ የሃይማኖት መግለጫ አጀማመር ከከፍተኛ ነጥብ ላይ እንዲደርስ አድርጓል። በ151-171 ዓ.ም. ገደማ የተነሣው የሞንታነስ ትምህርት [Montanism/ሞንታኒዝም] የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ለያዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ወሳኝ የሆነ የመጀመሪያ ድል አስገኝቷል። ሞንታነስ [Montanus] ራሱን ከሐዋርያት ጋር በማመሳሰል ልክ እንደነሱ መንፈስ ቅዱስን፥ መንፈሳዊ ስጦታዎችን፥ የሐዋርያነትን ሥልጣን፥ እና የተለየ መገለጥን የሚቀበል እንደሆነ አድርጎ ይቆጥር ነበር። ይህ እንቅስቃሴ አስቀድሞ የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ድርጅት በመቃወም የተከሠተ ሲሆን፥ ተርቱሊያን ጭምር የሚገኝባቸው በርካታ ተከታዮችን አፍርቷል። የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሚመለከት እውነትን ለማጽናት ሲባል ነበር የቅዱሳት መጻሕፍት መዘጋት ወይም

ፍጻሜ የሆነው። የመንፈስ ቅዱስ ሥራም አዲስ መገለጥን ከመስጠት ይልቅ ስለተሰጡት መገለጦች አብርሆት መስጠት እንደሆነ የታመነበት ጊዜም ነበር። ይህም እውነተኛ መንፈሳዊ ምሥጢራትን ከሐሰተኞቹ ለመለየት መሠረት ጣለ። ስሚተን ስለዚህ ጉዳይ ዐቢይ የሆነ ጥያቄ በማንሣት እንዲህ ሲል መልሱን ሰጥቷል፦ ‹‹የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ካበቃ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ቅጽበታዊ የሆነ ሌላ ተጨማሪ መገለጥ ወይም የነቢያት ራእይ መጠበቅ አለባትን? የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሞንታኑሳውያንን [Montanists] በመቃወም አሉታዊ መልስ ሰጥታለች። ይህም እግዚአብሔር ምን ለመሥራት ይችላል? የሚል ጥያቄ ሳይሆን፥ ቃሉ በጽሑፍ ከሚነግረን ሌላ መንፈስ ቅዱስ መገለጥን ከፈቃዱ ምክር ይሰጣል ወይ›› የሚል ነው። ይህ ዘመን ስለ መንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚያበረክተው ጠቃሚ አስተዋጽኦ፥ ስለ መንፈሳዊ ስጦታና ስለ ተአምራዊ መገለጥ የተሰጠው የተሟላ ማጠቃለያ ነው። የጥንት ቤተ ክርስቲያን አቋሟን እንዲህ በማለት ገልጣለች፦ ‹‹ያልተለመዱ ታላላቅ ስጦታዎች የቤተ ክርስቲያን ቋሚ ሀብት ይሆኑ ዘንድ የተሰጠ ተስፋ የለም።››

በዚህ ዘመን ለመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት እጅግ አስፈላጊ የሆኑት የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና የሚመለከቱት ውዝግቦች ነበሩ። አብዛኛውን ጊዜ የተካሄደው ክርክርና ውይይት ያተኮረው፥ በወልድ ግለትም በሁለተኛው የሥላሴ አካል ላይ ቢሆንም፥ እርሱን በሚመለከት የሚሠራው ስሕተት በሦስተኛው የሥላሴ አካል ላይም እኩል እንዲሠራ አድርጓል። በዚህ ዓይነት የተነሡት ሁለት ዋና ዋና ስሕተቶች በሰባሊያኒዝም [Sabellianism] እና ከእርሱ በቀደሙት ተመሳሳይ ክፍሎች ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ አርያኒዝም [Arianism] ነው።

ሰባሊያኒዝም እግዚአብሔር ሦስት አካላዊ ሕልውና እንዳለው የሚክድ ሲሆን፥ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸው የተለያዩ ስልቶች ናቸው ይላል። በሌላ በኩልም አርያኒዝም የግኖስቲሲዝምን [Gnosticism/ናስቲሲዝም] ስሕተት በመደገፍ፥ ወልድ የራሱ የሆነ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ቢቀበልም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጡሮች ናቸው ብሏል። ሰባሊያኒዝም የተስፋፋው በሦስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በሕዝብ ዘንድ መታወቅ በጀመረው ሰባሊዩስ [Sabellius] በተባለው ሰው ነው። ይህ ሰው ቀደም ሲል ተርቱሊያን የተባለው ሰው ሥላሴን በሚመለከት ሞናርኪያኒዝም [Monarchianism] ብሎ የሰየመውን አሳብ ወስዷል። እነዚህ ክፍሎች ‹‹አሎጊ›› [Alogi] በሚል ስም በመጀመሪያ በ170 ዓ.ም. በትንሿ እስያ የተነሡት፥ ክርስቶስ

በእግዚአብሔር ተመርጦ በማደጎ መልክ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሰው ነው በሚል አሳብ መሠረትነት ነበር። ነገር ግን ይህ ‘‘የሰብዓዊ መልክ’’ ያለው የሞዳሊዝም ትምህርት [Modalism] በሁለተኛው ምዕተ ዓመት ገደማ አከተመ። ሦስቱ አካላት የመግለጫ ሞዴሎች (ዓይነቶች) ናቸው። የሚል አቋም ይዞ በ200 ዓ.ም. ገደማ ሌላው ዓይነት ሞዳሊዝም ከፕራክሲዩስ [Praxeus] ብቅ አለ። የዚህ ክፍል ተከታዮች አመለካከት የተወለደው መከራ የተቀበለውና የተሰቀለው አብ ራሱ ነው ወደሚል አሳብ ስለሚያመራ ‘‘ፓትሪፓሺያኒስቶች’’ [Patripassionists] በመባል ይታወቃሉ።

የሰባሊሳውያንን ኑፋቄ ማወቅ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ተከታዮቹ ዘመናዊውን የዩኒተሪያኒዝም አስተሳሰብ ጀማሪ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ በርካታ ተከታዮችን በቤተ ክርስቲያን ያገኘ፥ በሥላሴ ትምህርት ላይ ትልቅ ስሕተት ያስከተለ የመጀመሪያ ትምህርት በመሆኑም ነው። ስሚተን እንዳለው፦ ‘‘በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመግባት ዕድል ያገኘ፥ የመጀመሪያው፥ ወይም ከመጀመሪያዎቹ ስሕተቶች አንዱ ሥላሴን የሚመለከተው ነው። ዘመናዊ አስተሳሰብ ወደዚያ ለመመለስ ዝንባሌ ያሳየበት ስሕተትም ነው።’’

በዚህ የሞዳሊዝም አመለካከት ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ተሰንዝሯል። ተርቱሊያንም በኃይል የተቃወመው ሞንታኒዝምን በከፊል ያወግዝ ስለነበር ነው። የእስክንድርያ ጳጳስ የነበረው ዲዮናስዮስ [Dionysius] መሪዎችን በማስጠንቀቅና በመጨረሻም በጽሑፍ ይህን ትምህርት መቃወሙን አሳይቷል። የመቃወሚያ ጽሑፉ ግን ለዘብ ባለ ቃል የተጻፈ በመሆኑ እርሱ ራሱ አርያኒዝምን ይከተላል ተብሎ እንዲከሰስ አድርጎታል። ይህ እንቅስቃሴ ከተመረመረ በኋላ በ261 ዓ.ም. ሰባሊዩስ በውግዘት ተወግዷል። ቤተ ክርስቲያንም አርዮሳውያን ስለ ሥላሴ ባላቸው አመለካከትና በኋላ ደግሞ መቅዶናውያን [Macedonians] የሚባሉ የመንፈስ ቅዱስን መለኮታዊነት የሚክዱ፥ በከፊል የአርዮሳውያን [Semi-Arians] አስተሳሰብ ያላቸውን ሰዎች ትምህርት ማስተካከል ነበረባት።

2. የኒቅያ ዘመን

‘‘የአርዮስ ክርክር’’ የሚለውን ስያሜ ያስገኘው አርዮስ የተባለው ሰው፥ በእስክንድርያ የሚያስተምር የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር (በ336 ዓ.ም. ገደማ)። ሰባሊሳውያን ስለ ሥላሴ የሰጡትን መግለጫ የተቃወመ ቢሆንም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጡሮች ናቸው ብሎ ስለ ወልድና

መንፈስ ቅዱስ ጥገኝነት በመግለጥ፥ ከአብ ጋር ያላቸውን እኩልነት ከዷል። ስሚተን የአርዮስን አመለካከት እንደሚከተለው አጠቃሎታል፦ ‘‘መለኮትና ከአንድ አካል የመውጣት አሳብ የሚጋጩ ናቸው በማለት አጥብቆ ተቃውሟል። በአርዮስና ስለ እርሱ ጥልቅ እውቀት ያለው ዩኖሚየስ [Eunomius] የሚሰነዝሩትን በርከት ያሉ መከራከሪያ ነጥቦች አትናቴዎስ፥ ባስልዮስ [Basil]፥ የእንዚናዙ ጎርጎርዮስ [Gregory of Nazianus] በሁለት ነጥቦች የተመረኮዘ ነው ለማለት ይቻላል በማለት እንደሚከተለው አስቀምጠውታል። ዘላለማዊነት ያለው እና ጥገኛ ካልሆነ አንድ ነገር አንድ አካል ሲወጣ፥ ያ አካል የጥገኛ ስለሆነ፥ ይህን ባሕርይውን ትቶ ዘላለማዊ ሊሆን አይችልም ለማለት እንደሞከሩ ገልጠዋል። አንድ የሆነው መለኮታዊ ባሕርይ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ የጋራ ነገሮች ሁሉ ውስጥ መኖሩን ለማስረዳት መጽሐፍ ቅዱስ በማስረጃነት የሚያንፀባርቃቸውን ነገሮች ቁርጥ ባለ መንገድ ሽሯል።’’ የመንፈስ ቅዱስንም መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሚመለከት የአርዮስ አቋም መንፈስ ቅዱስ በልጁ (በወልድ) የተፈጠረ ነው የሚል ይመስላል። ይህም ማለት እርሱ በፍጡር የተፈጠረ ነው ማለቱ ነው። ስሚተን እንዳለው፦ ‘‘በኢፒፋኒዩስም [Epiphanius] ሆነ በአውግስጢኖስ እንደተገለጠው፥ አርዮስ መንፈስ ቅዱስን ወልድ ፈጠረው በማለት በፍጡር የተፈጠረ እንደሚያደርገው በማያጠራጥር መልኩ ገልጦታል። እንደ አርዮስ እምነት የእግዚአብሔር ልጅ ከፍጡር የተሻለ ስፍራ የለውም። መንፈስ ቅዱስ በወልድ ከተፈጠረ ወልድ ራሱ ፍጡር በመሆኑ መንፈስ ቅዱስም በፍጡር የተፈጠረ ይሆናል ማለት ነው።’’

በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ጉባዔ በተካሄደው ሰፊ ውይይት ‘‘ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋል’’ በሚለው ቃል መሠረት፥ መንፈስ ቅዱስ በወልድ ተፈጠረ የሚለው የአርዮስ አቋም ይፋ ወጣ። የኒቅያ ጉባዔ የእምነት መግለጫ ከአብ ጋር እኩልነትን ስለሚካፈለው ስለ ወልድ መለኮትነትና ዘላለማዊነት ግልጥ የሆነ የእምነት መመሪያ ቢያወጣም፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የገለጠው ግን፥ ‘‘በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ’’ የሚል ቃል ብቻ ነው። ጉዳዩ እንዲህ በቀላሉ ስለመቅረቡ ብዙ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች መስጠት ቢቻልም፥ ጉባዔው ወልድን የሚመለከቱ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶችን ለማቀነባበር ብዙ ውይይቶችን እንዳካሄደ ይጠቁማል። ደግሞም በቀጠሉት ‘ነምሳ ዓመታት እንደታየው የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ለመረዳት ቤተ ክርስቲያን ገና አለመብሰሏን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። በዚህ ምክንያት ነው የመጨረሻውን ግልጥ የእምነት መግለጫ ለማውጣት ሌላ ተጨማሪ ክርክርና ኑፋቄ እንዲነሣ ያስፈለገው።

3. የድህረ ኒቅያ ዘመን

የድህረ ኒቅያ ዘመን በሁለት የተከፈለ ነው። እነርሱም የመጀመሪያው በ325 ዓ.ም. ከተደረገው የኒቅያ ጉባዔ ጀምሮ በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ እስከተካሄደው ጠቅላላ ስብሰባ የሚሄድ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ከ381 ዓ.ም. ጀምሮ በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን [Chalcedon] እስከተካሄደው ጉባዔ የሚዘልቅ ነው። ከኒቅያ ጀምሮ እስከ ቁስጥንጥንያው ጉባዔ ድረስ የነበረው ጎምላ ዓመት በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ላይ አለመረጋጋትና ጥርጥር የበዛበት ነበር። የሽግግር ወቅት ከመሆኑም ሌላ በመቅዶንዮስ [Macedonius] የተጀመረው የመቅዶናውያን የእምነት ክፍል ውዥንብሩን አባባሰው። መቅዶንዮስ የተባለው ሰው አቋሙን ወይም አመለካከቱን በሚገባ ሳይገልጥ መንፈስ ቅዱስ ፍጡር ብቻ ነው በሚለው ትምህርቱ ገፋበት። በመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊነት ላይ የተነሣው ተቃውሞ ሽንጣቸውን ገትረው ለእምነቱ የሚከላከሉ እንደ አትናቴዎስ፥ ባስልዮስ፥ የእንዚናዙ ጎርጎርዮስ፥ እንዲሁም የኑሲሱ ጎርጎርዮስ [Gregory of Nyssa] ያሉትን ሰዎች አስነሣ። እነዚህ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ሁሉን አዋቂ፥ ሁሉን ቻይና፥ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ መሆኑንና ግርማውም በመንፈስ ቅዱስ ላይ መኖሩን በማስረዳት መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ያለውን እኩልነት ያለ ምንም ስሕተት ለሚያሳየው ለጥምቀት መመሪያ ልዩ ትኩረት በመስጠት አሳይተዋል ሲል ስሚተን ይገልጣል። ለአንዳንዶች ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚህ ርእስ የሚሰጡት ምስክርነት ግልጥ ስላልሆነ ችግሩን ለመፍታት የበለጠ ውይይት ያስፈልጋቸው ነበር።

ከዚህ የሚቀጥለው ዓረፍተ ነገር በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ የተደረገው ጉባዔ በኒቅያ የእምነት መግለጫ ስለ መንፈስ ቅዱስ በተጻፈው ላይ የታከለ ነው፦ ‹‹ሕይወት ሰጪና ጌታ ከአብ በመውጣት ከአብና ከወልድ ጋር ሊመለክና ክብር ሊሰጠው የሚገባ በነቢያት የተናገረ።›› ይህ ዓረፍተ ነገር መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፥ ወይም ከአብና ከወልድ ጋር የጋራ ሕልውና አለው ባይልም የመቅዶናውያንን ኑፋቄ የተቃወመችውን ቤተ ክርስቲያን በሚመለከት በመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ላይ የተፈጠረውን ችግር ያስወገደ መሆኑ ግልጥ ነው።

ከ381-451 ዓ.ም. የነበረው ሁለተኛ ዘመን የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ትምህርት ያስፋፋ ነበር። በ451 ዓ.ም. የተካሄደው የሮም፥ የኢየሩሳሌም፥ የቁስጥንጥንያ፥ የአንጾኪያ አብያተ ክርስቲያናት ኃላፊዎች የተካፈሉበት ጉባዔ ከዚያ ቀደም የነበሩት ጉባዔዎች የደረሱበትን

አረጋግጧል። በዚህ ዘመን በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ላይ ይደረግ የነበረው ውይይት መለኮትነቱ ከአብና ከወልድ የመሥረፁ ጉዳይ ተላልፎ ነበር።

4. መካከለኛው ዘመን

በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ የተካሄደው ጉባዔ መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው (የወጣው)፥ ማለትም አካላዊ ሕልውናውን ያገኘው ከአብ ነው የሚል ግልጥ ዓረፍተ ነገር አስፍሯል። መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ስለ መሥረፁ ግን የተናገረው አንዳችም ነገር የለም። በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን ከተካሄደው ጉባዔ በፊት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሙሉ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ስለመስረፁ ያላቸው አቋም አንድ ይመስል ነበር። ስሚተን ከጽሑፎቻቸው በመጥቀስ እንዳረጋገጠው አትናቴዎስ፥ ዲዲመስ [Didymus]፥ ኢጲፋኒዩስ፥ የኒሱሱ ጎርጎርዮስ፥ ባስልዮስ፥ አውግስጢኖስና ሌሎችም ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ለማስተማር በአንድ ድምፅ ተስማምተው ነበር። ስሚተን ሲያጠቃልል፦ ‘‘የግሪክ ቤተ ክርስቲያን በደኅናው ጊዜም ቢሆን ምንም ጥርጣሬ አልነበራትም። በ4ኛው ምዕተ ዓመት ታላቅ መሠረቷን ያስፋፋችበትና መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ከአብና ከወልድ ነው ያለችበት ጊዜ ነበር።’’

የዚህ ትምህርት ተቃራኒ የሆነውና ወደ እኛ የደረሰው ነገር የተነሣው ከ431 ዓ.ም. ጀምሮ በቴዎዶሪጦስ [Theodoret] አማካይነት ሲሆን፥ አሳቡም መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ከወልድ ነው የሚል ነበር። ይህ ውዝግብ በተለይ በ589 ዓ.ም. በቶሌዶ ጉባዔ በኃይል እስከተጧጧፈ ድረስ ቀጠለ። ጉባዔው ምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናትን ብቻ ያቀፈ ሲሆን፥ በኒቅያና በቁስጥንጥንያ በነበረው ጉባዔ የእምነት መግለጫ ላይ ‘‘ከልጁም’’ [‘ፊሊዮክዌ’] የሚል ቃል በመጨመር መሥረፅን የሚመለከተው ዓረፍተ ነገር ‘‘የሠረፀው ከአብና ከወልድ ነው’’ የሚል እንዲሆን አድርጓል።

መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ‘‘ከልጁም’’ ነው በሚለው አሳብ ላይ የተነሣው ይህ ውዝግብ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ስምምነት መለወጥ የነበረበትን የእምነት መግለጫ ምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት ብቻቸውን ለመለወጥ ታግለዋል በሚል በቂ መነሻ በምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ወዲያውኑ ተቃውሞና ጥላቻን አስነሣ። ይህም ሆኖ የሮም ጳጳሳት ለውጡን ለመቀበል በጣም ቢዘገዩም፥ ምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት ወዲያውኑ በቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ ሥርዓታቸው ላይ ጨመሩት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የግሪክ አብያተ ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ

ከአብ እንጂ፥ ከወልድ መሥረፁን የማይቀበሉ ሆኑ። በ867 ዓ.ም. ፎቲየስ [Photius] የተባለው ሰው የግሪክ ቤተ ክርስቲያንን አቋም በመደገፍ ምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናትን ቅር ያሰኘ ሲሆን፥ በዚህም ምክንያት በ1054 ዓ.ም. በዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ረገድ የተፈጠረው ችግር በምዕራብና በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ላለው ልዩነት ዋና መሠረት ሆነ።

በ1439 ዓ.ም. በሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት ያለው የእምነት መግለጫ ለማውጣት ሙከራ ቢደረግም፥ ፍጻሜው እንደተጠበቀው ሳይሆን ቀረና በ1453 ዓ.ም. የምሥራቁ ንጉሣዊ አገዛዝ ሲፈራርስ ፍሬ አልባ ሆነ። የግሪክ ቤተ ክርስቲያን እስካሁንም ድረስ የምዕራብ ቤተ ክርስቲያንን አቋም እንደ ኑፋቄ ትቆጥረዋለች። የምዕራብና ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት፥ እንዲሁም ከአብና ከወልድ ጋር እኩል ኃይልና ክብር ያለው መሆኑን ተቀብለው ስለነበር፥ የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ስለ መንፈስ ቅዱስ ስርፀት ያካሄዱት ክርክር የማያስፈልግና ፍሬ አልባ ነበር። ይህ ክርክር እየቀነሰ በመጣ ቁጥር፥ የዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ታሪክ ትኩረት በመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ላይ ከመሆን ይልቅ ወደ ሥራው እየሆነ ሄደ። የቤተ ክርስቲያን ትኩረት በተለይ የመንፈስ ቅዱስ ዋና ሥራ ሥርየት ያስገኘ ጸጋ ነው በሚለው የአውግስጢኖስ አስተሳሰብ ላይ ሆነ (354-430 ዓ.ም.)። ምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት ስለ ሰውና ስለ ኃጢአት ለነበራቸው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ ለየት ባለ ሁኔታ ቅርፅ የሰጠው አውግስጢኖስ ነው። የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን በሚመለከት ያላት አስተሳሰብ ደካማ በመሆኑ፥ በጽድቅ ለመኖር ሰው ተፈጥሯዊ የሆነ ፈቃድ አለው ብላ ታምናለች። የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን የሰውን ጠቅላላ የውድቀት አሳብ ሰፋ በማድረግ ለማጤንና፥ ሰው ለመዳን እና ለማመን የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገዋል የሚለውን አሳብ አስፋፍታለች። ስሚተን እንደጠቆመው፥ የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን አቋም በታሪክዋ ሁሉ ከሚገባ በላይ የግሪክ ፍልስፍና ተጽዕኖ የተደረገበት ሲሆን፥ ሰውን ከፍ አድርጎ ኃጢአትን የሚያሳንስ ነው። ታላቁ ክሪሶስቶም [Chrysostom] ለምሥራቅ የሥነ-መለኮት ዋና ምሳሌ ሲሆን፥ ከእርሱም ጋር የኢየሩሳሌሙ ቄርሎስ [Cyril]፥ የእንዚናዙ ጎርጎርዮስ፥ ባስልዮስና ሌሎችም ይገኛሉ። በምዕራብ ግን ስለ ጸጋ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አውግስጢኖስ ጽኑ አቋም የወሰደ ሲሆን፥ አቋሙም በፕሮቴስታንት ተሐድሶ ውስጥ እንደገና በእጅጉ ታይቷል።

የፐሌጂያን ውዝግብ ነው ችግሩን ይፋ እንዲወጣ ያደረገው። ፐሌጂየስ [Pelagius] የተባለው የእንግሊዝ መነኩሴ በ400 ዓ.ም. ወደ ሮም ሄዶ የውርስን ኃጢአት የሚቃወም ንድፈ አሳብ በማንፀባረቅ "ሰው ከመለኮታዊ ጸጋ ውጪ እንኳ፥ በጎ ለማድረግ ይችላል" በማለት የአዳም ኃጢአት ራሱን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ ነው ብሏል። አውግስጢኖስ ከኃጢአት ጋር የነበረው ልምምድና ያደረገው የሥነ-መለኮት ጥናት ይህን ኑፋቄ ለመቃወም አስችሎታል። ስለዚህ ጉዳይ የነበረው ክርክር ከ411 ዓ.ም. ጀምሮ በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን ጉባኤ መፍትሔ እስካገኘ ድረስ እየተባባሰ ሄዶ ነበር። በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን በተደረገው ጉባዔ ግን ፐሌጂየስን፥ ኮለስትዮስን [Coelestius] እና ሌሎች የፐሌጂያኒዝም [Pelagianism] ተባባሪዎችን በማውገዝ ጉዳዩ ረገበ። ነገር ግን የውዝግቡ ታሪክ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን፥ በተለይም የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን የፐሌጂየስን አመለካከት ብትቃወምም፥ ወደ አውግስጢኖስ አስተሳሰብ ለመድረስ ፈቃደኛ ባለመሆኗ፥ ለከፊል ፐሌጂያኒዝም አሳብ መንገድ ከፈተች። ይህ አሳብ በመጨረሻ የሮም ቤተ ክርስቲያን አቋም በመሆን በኋላም ለፕሮቴስታንት ተሐድሶ መውጣት ምክንያት ሆኗል። የፐሌጂየስ መወገዝ ግን መንፈስ ቅዱስ በደኅንነት ውስጥ ያለው ሥራ እንደገና እንዲታወቅ ምክንያት ሆኗል።

በኦሬንጅ በተደረገው ጉባዔ [Synod of Orange] (529 ዓ.ም.) በተከናወነው ሥራ ደግሞ የከፊል ፐሌጂያኒዝምን አሳብ ለመቃወም ተጨማሪ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን፥ የሥነ-መለኮቱ ትምህርት አቋም ነጥብ በነጥብ በጥቂት በጥቂቱ ተወግዟል። የዚህ ጉባዔ የመጀመሪያ ሰባት ደንቦች በግለት ስሚተን የጠቀሳቸው ነገሮች የጉባዔው የሥነ-መለኮት ትምህርት ፀረ-ከፊል ፐሌጂያኒዝም እንደሆነ ግልጥ አድርገውታል። ቤተ ክርስቲያን እምነትን በማነቃቃትና ያልዳኑ ነፍሳት ፈታቸውን ወደ ክርስቶስ እንዲመልሱ በማድረግ መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውነውን ሥራ በማረጋገጥ የአውግስጢኖስን አቋም በይፋ ደግፋለች።

5. የቅድመ ተሐድሶ ዘመን

ቤተ ክርስቲያን የፐሌጂያኒዝምን፥ በኋላም የ'ከፊል ፐሌጂያኒዝም'ን አቋም ካወገዘች በኋላ፥ እስከ ተሐድሶ ዘመን የወሰደችው እርምጃ ቢኖር መጠነኛ ነበር። የአውግስጢኖስ አመለካከት አንዳንዶች በከፍተኛ ተአቅቦ የሚመለከቱት ቢሆንም፥ በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን አቋም እንደሆነ ተቆጥሮ ነበር። የሚያሳዝነው ግን የሮማን ቤተ ክርስቲያን ዓላማ ለማስፋፋት ይረዳ ዘንድ እንዲጣመም መደረጉ ነው። አውግስጢኖስ

አስቀድሞ የመወሰንን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት [Predestination/ ፕሪዴስቲኔሽን] በሚመለከት የታወቀ ነው። ይህም ውጤት አስገኝ ጸጋን በጋጢአት ከመውደቅ ትምህርቱ ጋር ሙሉ በሙሉ ያያይዘዋል። እነዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ቀጥሎ ካሉት ትምህርቶች ጋር እንዲስማሙ ተደርገው ነበር። አንደኛ ቤተ ክርስቲያን ለማንኛውም መሠረታዊ ትምህርት ሙሉ ሥልጣን አላት የሚል ሲሆን፥ ሁለተኛው የቅዱሳን ምሥጢራት ሥርዓት ማለትም ጸጋ የሚያስገኘውን ለማስፈጸም ሙሉ ኃላፊነት አለባት የሚሉ ነበሩ። ቤተ ክርስቲያን ያላትን ሥልጣንና የቅዱሳን ምሥጢራት ሥርዓትን አስፈላጊነት አበክራ ብትገልጥም፥ አስቀድሞ ስለመመረጥና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊነት የሚያስገነዝቡ ትምህርቶችን ግን ቸል ብላቸው ነበር። እግዚአብሔር ጸጋውን እንዲሰጥ በመንፈሱ በኩል ከመሻት ይልቅ፥ ሰዎች ቅዱሳት ሥርዓትን በመፈጸምና በመጠኑም ቢሆን የእግዚአብሔርን ቃል በማዳመጥ በኩል የእግዚአብሔርን ጸጋ እንዲሹ ትገፋፋ ነበር። ይህ ትምህርት በመጨረሻ ሥርዓታዊ ብቻ ወደሆነ ልምምድና አልፎም በምዕመናን ላይ መገፋትን ስላስከተለ፥ ሉተር ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን አንድነት እንዲያቋርጥ አድርጎታል።

ከተሐድሶ ዘመን በፊት በነበሩት የጨለማ ዘመናት ጥቂት የብርሃን ብልጭታ ብቻ ታይቶባቸዋል። የክሌርቮው በርናርድ [Bernard of Clairvoux] (1091-1153) ‘‘ጸጋና ነጻ ፈቃድ’’ በሚለው ሥራው ይህን ጉዳይ በአዲስ ትኩረት ተመልክቶታል። ደግሞም የቤተ ክርስቲያን ብልሹነት መንፈሳዊ ዕረፍት የሚፈልጉ ነፍሳትን ወደ ሥርዓተ ምንኩስናና መንፈሳዊ ምሥጢራትን ወደ መፈለግ መራቸው። አንዳንዶች በአንድ ወይም በሌላ አቅጣጫ የቤተ ክርስቲያንን የቀዘቀዘ ወገኛነትና ግብረ ገባዊ ልቅነት ሞቅ ባለና በጣም ጠቃሚ በሆነ መንፈሳዊ ልምምድ ለመተካት ሞክሩ። በእነዚያ የጨለማ ዘመናት በርካታ መሰናክሎች ቢከሠቱም፥ ታላላቅ መንፈሳዊ ጀግኖችም እንደነበሩ አያጠራጥርም። እነዚህን መንፈሳዊ ምሥጢራት የሚቃረኑት የሰብዓዊነት [Humanism/ሂዩማኒዝም] እና የስኮላስቲሲዝም [Scholasticism] ተጽዕኖዎች ነበሩ። ‘‘የመስቀል ጦርነት’’ አለመሳካት የመንፈሳዊ ፍላጎቶችን አዳፍኗል። በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን ሰንደቅ ዓላማ ሥር ያሉ የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ፍልስፍናዎች በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ረገድ ምንም ዓይነት እድገት እንዳይኖር እንቅፋት ሆኑ።

በአጠቃላይ ሲታይ መካከለኛው ዘመን በመንፈሳዊም ሆነ በአእምሮ እውቀት ጨለማ የነበረ ሲሆን፥ በዘመናችን ባሉ አውነተኛ

የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ሚዛናዊ የሆነ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አልነበራቸውም። መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት በአጠቃላይ ምንም ግንዛቤ አልነበራቸውም። ጥቂቶች ብቻ ነበሩ የግል ለውጥን አስፈላጊነትና መንፈስ ቅዱስ በዳግም ልደት ውስጥ ስላለው ሥራ የሚናገሩ አሳቦችን አጥብቀው የጨበጡ። እንደ እውነቱ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር፥ ጥምቀትና ሙላት ምንም ዓይነት ትኩረት አልተሰጠውም። መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ክርስቲያኖችን ለማስተማር ያለው ችሎታ በግልጥ ተክዷል። በመንፈስ ቅዱስ ቦታ ምድራውያን ቀሳውስት ተተኩ። ‘‘የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር’’ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፥ ቃሉን ቸል በማለትና በመተው፥ በአጉል እምነት፥ በሰብዓዊነትና በፍልስፍና ሥርዓት ምድረ በዳዎች ተዋጠ።

6. የፕሮቴስታንት ተሐድሶ

የፕሮቴስታንት ተሐድሶ፥ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሥልጣንን ያለ አግባብ መጠቀምዋን በመቃወም የተነሣ ዓመፅ ነው። ለዚህ ዓመፅ መንገድ የተከፈተው በአስተሳሰብ ነጻ የመሆን ሁኔታ እያደገ በመምጣቱ ቢሆንም፥ እውነተኛው የዓመፅ ምክንያት ግን፥ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን እየተበላሸች መሄዷ ነበር። የደቡብ አውሮፓ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ እንዳይከሠት ቢያደርግም፥ የሰሜን አውሮፓ አገሮች አዝማሚያና በአካባቢው የነበሩ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ለሉተርና ሌሎች አዳሮች ምቹ ነበሩ።

ከመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አንጻር የፕሮቴስታንት ተሐድሶ፥ መለኮታዊውን ጥንተ ውሳኔ፥ ፍጹም ውድቀትንና ሥርየት አስገኝ ጸጋን አስመልክቶ አውግስጢኖስ ያቀረበውን ትምህርት አድሶታል። አዳሮች በሙሉ በዚህ ነጥብ ላይ የተስማሙ ወይም አንድ የሆኑ ሲሆን፥ በ1600 ዓ.ም. ብቻ አነስተኛ ልዩነት ታይቷል። በአንድ አሳብ ተስማምተው የሰጡት ይህ ምስክርነት የሚያድን እምነት በሰው ሕይወት ውስጥ ይገለጥ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊ መሆኑ እንደገና እንዲነሣሣ አድርጓል። ሥርየት አስገኝ ጸጋ እና ዳግም በመንፈስ መወለድ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ስለ ግለሰብ ሕይወት መለወጥ ከነበራት ግዴለሽነት ጋር ሲነጻጸር፥ ትምህርቱ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ሆኖ ነበር። ሉተር የሮማን ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ማለትም ሰው የጌታ እራትን በመካፈል የእግዚአብሔርን ጸጋ ይቀበላል የሚለውን ለመጣል ፈጽሞ አልቻለም ነበር። ሉተር የነበረው ሌላ ለየት ያለ አሳብ፥ ጸጋ

ከእግዚአብሔር ቃል እንጂ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ አይደለም የሚል ነበር። እርሱ እንደዚህ ቢያስብም፥ የሉተራውያን የእምነት ትምህርት የመንፈስ ቅዱስን አስፈላጊነት አበክሮ ያሰማል።

የተሐድሶው ዘመን ያበረከተው ሌላ አስተዋጽኦ፥ የአብርሆት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ነው፤ ማለትም የመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል የመግለጥ አገልግሎት "የእግዚአብሔርን ቃል መተርጎም የሚችሉ ቀሳውስት ብቻ ናቸው" ከሚለው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ፅንሰ-አሳብ በተቃራኒ፥ እያንዳንዱን ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ በቃሉ በኩል በቀጥታ ሊያስተምረው ይችላል በማለት የቤተ ክርስቲያን አዳኞች መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን በግልጥ አስተዋወቁ። ይህ ነገር በአንዳንድ ረገድ ሥልጣን በነበራት የመንግሥት ቤተ ክርስቲያን ፅንሰ-አሳብ የታገደ ቢሆንም አሳቡ ግን ነበረ።

በእርግጥ የተሐድሶ ዋና አሳብ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ባይሆንም፥ በአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች በሁሉ ተጠቃሚ የሆኑበት የተሐድሶ ትኩረት ተካፋይ ሆኗል። የተሐድሶ ዋና ዋና መሪዎች ሁሉ የሰውን ሙሉ ለሙሉ በኃጢአት መውደቅ፥ የጸጋንና የግል ለውጥን አስፈላጊነት የሚናገሩ ማዕከላዊ ፅንሰ-አሳቦችን ተቀብለዋል። እነ ሉተር፥ ዝዊንግሊ [Zwingli]፥ ካልቪን፥ ኖክስ [Knox] እና ሌሎችም በጽሑፋቸው የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ዓላማ ለመፈጸም ሰው የሚያስፈልገውንና የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አስፈላጊነት ጠቁመዋል።

የተሐድሶ እንቅስቃሴ የተለያዩ ክፍሎችን ስለሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ስሚትን ያደረገው ጥናት የተሐድሶን አስተዋጽኦ ያረጋግጣል። በሉተራን ቤተ ክርስቲያን የአውግስበርግ የእምነት መግለጫና የካንኮርድ መጽሐፍ [Book of Concord] ይህን ነጥብ በሚመለከት ይስማማሉ። ስሚተን የካንኮርድን መጽሐፍ በሚከተለው ሁኔታ ጠቅሶታል፦ "ነገር ግን በተቃራኒው እንዲህ ተብሏል፥ የሰውን ሕይወት በመለወጥ ጊዜ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ፈቃደኛ ያልነበሩና ራሳቸውን ያልሰጡ ጠንካራ ሰዎችን ወደ ራሱ በመሳብ ያዘጋጃቸዋል። ይህን ከመሰለው ለውጥ በኋላም ዳግም የተወለደው ሰው ፈቃድ በዕለታዊ የንስሐ ልምምድ ውስጥ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ ውስጡ በሚሠራቸው ሥራዎች ሁሉም ተባባሪ ይሆናል።"

ስሚተን የሄልቬቲክ የእምነት መግለጫንም [Helvetic Confession] በተመሳሳይ ሁኔታ ጠቅሶታል፦ "በዳግም ልደት ውስጥ ማስተዋል የእግዚአብሔርን ምሥጢርና ፈቃድ ለመረዳት እንዲችል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ብሩህ ይሆናል። እንዲሁም ፈቃድ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ

መለወጥ ብቻ ሳይሆን፥ በነውን ለመምረጥና ለማድረግ ይችል ዘንድ በኃይል ይሞላል›› (ሮሜ 8፡5-6)።

የዌስትሚንስተር የእምነት መግለጫ በሌሎቹ የእምነት መግለጫዎች እንደምናገኘው፥ የመንፈስ ቅዱስ ሠራዒነት ከአብና ከወልድ መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን፥ ሰዎች ለማመን ይችሉ ዘንድ ቅዱሳት መጻሕፍትን የመግለጥ (የአብርሆት)፥ መዋጀት የሚያስገኘውን ጥቅም በሕይወት ማለማመድ፥ ዳግም ልደትን ተፈጻሚ ማድረግ፥ መቀደስ፥ ዋስትናን የመስጠትና መጽናትን ማረጋገጥ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መሆናቸውን አረጋግጧል።

ተቀዳሚ የሆኑ የፕሮቴስታንት የእምነት መግለጫዎች ማለትም እንደ ስኮትሽ የእምነት መግለጫ፥ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሠላሳ ዘጠኝ የእምነት አናቅጽ፥ የፈረንሳይ የእምነት መግለጫ፥ የባዘል የእምነት መግለጫ [Confession of Basel] እና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የክርስትና ትምህርቶች ያሉት በሰው ልጅ ውድቀትና አምኖ ለመዳን ሥርየት አስገኝ ጸጋ አስፈላጊ በመሆኑ ላይ ያተኩራሉ። የጥንት ቤተ ክርስቲያን በዘመናት ሁሉ የምዕራቡ ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ሆኖ ለቆየው የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መልክ በመስጠት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጋለች። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በሥርዓት አስገኝ ጸጋ፥ በዳግም ልደት፥ በቅዱሳት መጻሕፍት አብርሆት (መገለጥ) እና በመንፈሳዊ ብቃት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ዘርዝሮ አቅርቦታል። በአጠቃላይ የተሐድሶ እንቅስቃሴ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ለማሻሻል ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ጉልህ አስተዋጽኦ የለም።

7. ድህረ ተሐድሶ ወቅት

ከተሐድሶ ድል በኋላ በ17ኛውና በ18ኛው ምዕተ ዓመት በተሐድሶ መሪዎች ታላላቅ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ላይ የሚያሳዝን ማሽቆልቆል ሆነ። ይሁን እንጂ እውነትን በተመለከተ የድል ምልክቶች ታይተዋል። በሜላንክቶን [Melancthon] የተሳሳተ አመራር፥ በ‹‹ሲነርጂዝም›› [Synergism] ላይ የነበረው ውዝግብ በሉተራን ቤተ ክርስቲያን ተጀመረ። ሜላንክቶን፥ ፈቃዳችን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይተባበራል የሚል እምነት ነበረው፤ አመለካከቱም ‹‹ሲነርጂዝም›› በመባል ይታወቃል። የጀናው ስትሬገል [Strigel of Jena] የተባለው ሰው ከሜላንክቶን ጎን በቆመበትና በ1555 ዓ.ም. በተጀመረው ውዝግብ ሳቢያ በቅንዓት በመነሣሣት የሉተርን አመለካከት የደገፈው ፍላሲየስ [Flacius]

ተቃራኒ አቋም ያዘ። የሉተር ደጋፊዎች ‘‘ኃጢአት የሰው ተፈጥሮ ክፍል ሆኗል’’ የሚል ጽኑ አቋም ነበራቸው። የዚህ ውጤት፥ እንደታሰበው የካንኮርድ መጽሐፍ ወደተባለው ወደ ሉተር መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መመለስ ሆነ። የውዝግቡ መንፈስ ግን የሉተራንን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አጥብቆ መከላከሉን ስለቀጠለ፥ ትምህርቱ መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ምንም ተጨማሪ እና ጠንካራ እድገት ሳይገኝ ቀረ።

በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ላይ ከበድ ያለ ፈተና የመጣው ከ1560-1609 በኖረውና አርምኒየስ በተባለ ሰው በተመራው በአርምኒያን የሥነ-መለኮት ትምህርት ነበር። ይህ ትምህርት ‘‘የደኅንነትን ጉዳይ የሚወስነው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሳይሆን ሰው በፈቃዱ ነው’’ የሚል ነው። የዶርት ሲኖዶስ [Synod of Dort] (1618-1619) የአዳሾችን አመለካከት እንደገና አረጋገጠ። አርምኒያኒዝም ከባድ ቀውስ የገጠመው ቢሆንም፥ በሆላንድና በፈረንሳይ በፕሮቴስታንቲዝም ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን ግን ገፋበት።

በመካከሉ በ16ኛው ምዕተ ዓመት እንግሊዝ ውስጥ የተጀመረው የፒዩሪታን [Puritan] እንቅስቃሴ፥ በ17ኛው ምዕተ ዓመትም ቀጠለ። የተቀደሰ ሕይወትንና የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናትን አጥብቆ ይፈልግ የነበረው ይህ እንቅስቃሴ፥ በዳግም ልደት ትምህርት ረገድ ተጨማሪ እድገት እንዲኖርና የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ በማስተማር ሥራ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት ባለውለታችን ነው። ዘመኑ ምሥጢራዊ የሆኑ መንፈሳዊ ልምምዶች የበዙበት እንዳንድ ሁኔታዎች ይታዩበት ነበር። እነዚህም የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መሪ ሳይጠቀሙ፥ መገለጥን በቀጥታ ከመንፈስ ቅዱስ ለመቀበል ጥረት ማድረግ የሚታይባቸው ነበሩ። ይህ ሐሰተኛ ወደሆነ መንፈሳዊ ምሥጢራት ልምምድ ይመራል።

ቤተ ክርስቲያንን ከሮም የባርነት ሥርዓት ነጻ ያወጣት ተሐድሶ፥ ፍልስፍናንም ከዚህ ሥርዓት ውጪ በራሱ አቅጣጫ እንዲሄድ ረድቶታል። ከተሐድሶ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ላይ ተጨማሪ እድገት እንዳይታይ እንቅፋት የመሆን አዝማሚያ የነበራቸው በርካታ ነገሮች ተከሥተዋል። አንዳንዶችን ይዞ የነጎደው የተሳሳቱ መንፈሳዊ ምሥጢራት ጉዳይ [Mysticism/ሚስቲሲዝም] በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተመሩና ያልተጤኑ በርካታ መንፈሳዊና ስሜታዊ ልምምዶች እንዲታዩ አደረገ። በሌላ በኩል ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በኢጣሊያ መሠረቱን በመጣል የተጀመረው ሂዩማኒዝም ወደ ራሽነሊዝም የማደግ ዝንባሌ በማሳየቱ መጽሐፍ ቅዱስንና የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በሙሉ የካደ

ትምህርት ተከሠተ። የእንግሊዝ ራሽነሊዝም የዲይዝምን [Deism] አሳብ በመያዝ የእግዚአብሔርን አብሮን መሆን፥ በጎ ስጦታና የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ሁሉ የመካድ አቅጣጫን ተከተለ። የእንግሊዝ አብያተ ክርስቲያናት በንድፈ አሳብ ደረጃ አሁንም በዚያው በቀድሞው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ደንብ ቢመሩም፥ የሕጋዊነት፥ የመቀዝቀዝና ለትምህርቱ ግድየለሽ የመሆን ዝንባሌ ይታይባቸው ነበር። ይህ ዓይነቱ ማሽቆልቆል በሌሎች አገሮችም ታይቷል። የሉተራን አብያተ ክርስቲያናት በመሠረታዊ የእምነት ትምህርት ረገድ ሊታዩ የሚገቡ እድገቶችን በሙሉ በመግታት ሕጋዊና ሥርዓት ፈጻሚ ብቻ ወደ መሆን አድልተዋል። በፈረንሳይም ፕሮቴስታንትነት በካቶሊክነት [Catholicism] ተዋጠ። በአእምሮአዊ እውቀት የማደግ ባሕርይ ያለው ራሽነሊዝም ወደ እግዚአብሔር የለሽነት [Atheism/ኤቲይዝም] እና ወደ ተጠራጣሪነት የሚመራ ሆነ። ራሽነሊዝም ከፈረንሳይ ወደ ጀርመን ተስፋፋና በጀርመን እጅግ አድጎ ዛሬ ከለዘብተኛ (ሊበራል) የሥነ-መለኮት ትምህርት ጋር የሚመደቡ በርካታ ፍልስፍናዎችን ወለደ። በዚህ ሳቢያ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በተገቢው አኳኋን ሳይከናወን ቀረ። ይሁን እንጂ 17ኛውና 18ኛው ምዕተ ዓመት አንዳንድ መልካም ነጥቦችን አስመዝግበዋል። ፒዩሪታኖች ካበረከቱአቸው ጠቃሚ አስተዋጽኦዎች አንዱ፥ ከ1616-1691 በኖረው በጆን ኦዌን የተጻፈው ‘‘ስለ መንፈስ ቅዱስ የተደረጉ ንግግሮች’’ የሚለው ጽሑፍ ነው። ካይፐር ስለዚህ የጆን ኦዌን ሥራ ሲናገር፦ ‘‘በዚህ ርእስ ጆን ኦዌን የሠራው ሥራ ከሁሉም በላይ የታወቀና አሁንም ሊታለፍ የማይችል ነው። በመሠረቱ ጆን ኦዌን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሦስት ሥራዎችን ጽፏል። እነርሱም በ1674፥ በ1682 እና በ1693 የታተሙት ናቸው’’ ብሏል። ከ1635-1708 የኖረው ፊሊፕ ስፔነር [Philip Spener] በጀርመን ባካሄደውና በኋላ የሞራቪያንን [Moravian] (ወይም ፓየቲስት [Pietist]) እንቅስቃሴ ባስከተለው መንፈሳዊ መነቃቃት ውስጥ ስሕተት ቢኖርበት እንኳ፥ በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትና በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ እንደገና ትኩረት እንዲደረግ ጥናት ያካሄደ ነበር። የዚህ እንቅስቃሴ ፍሬ ወደ ስካንዲኔቪያን አገሮችና ወደ አሜሪካ ተስፋፋ።

ከ1703-1791 የኖረው ጆን ዌስሊን ታላቅ የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ መሪና በእንግሊዝ የመቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ጀማሪ የሆነው፥ የእንግሊዝ ሞራቪያንስ እና በተለይ በአሜሪካ የነበረው የሞራቪያን እንቅስቃሴ መሪ ስፓንገንበርግ [Spangenburg] ባሳደሩበት አዎንታዊ ተጽዕኖ ነው። በዌስሊና በህዊትፊልድ [Whitefield] የተመራው፥ አብዛኛውን እንግሊዝና ስኮትላንድ ያጥለቀለቀውና ወደ አሜሪካ የተስፋፋው መንፈሳዊ

እንቅስቃሴ፥ በመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ውስጥ በግልጥ የሚታወስ ታላቅ ታሪክ ነው። በተለይ ዌስሊ በዳግም ልደት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ያለውን አስፈላጊነትና በአማኙ ውስጥ የሚኖረውን ምስክርነት በሚመለከት አስተምሯል። የሚያሳዝነው ግን የዮሐንስ አፈወርቅን (የክሪሶስትም) የቀድሞ ግሪኮችን የእምነት ድክመት የሚያሳየውን አመለካከት መከተሉ ነበር። አሳቡም ስለ ሰው ልጅ ብቁነት የሚናገረውን የእምነት ትምህርት እንደገና እንዲያንሰራራ አደረገ። ይሁን እንጂ እርሱ ይከተለው የነበረው አርምኒያኒዝም በዚያን ጊዜ በአውሮፓ ወቅታዊ ከነበረውና ወደ ሱስንያኒዝም [Socinianism] ካደላው አርምኒያኒዝም ፈጽሞ የተለየ ነበር። በዳግም ልደትና በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊ እንደሆነ አጥብቆ ይናገር ነበር።

ዌስሊ መንፈሳዊ ብስለትንና "በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን" በማምታታት ቅጽበታዊና መንፈሳዊ ፍጹምነት በዚህ ሕይወት ሊገኝ ይችላል የሚለውን አሳብ ተቀብሏል። ይህም አሳብ በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ላይ እስከዚህ ዘመን ድረስ ለቀጠለው አደናጋሪ ሁኔታ አስተዋጽኦ ያደረገ ነው። ዌስሊ ያበረከተው አስተዋጽዖ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሕጋዊነት፥ በውጭ ደግሞ ራሽነሊዝም በተስፋፋበት ዘመን መካከል የመጣ በመሆኑ የ18ኛው ምዕተ ዓመት ከፍተኛ ነጥብ ነው። ውጥረቱን ለማርገብ ያበረከተው አስተዋጽኦ ግን ዝቅተኛ ነበር። አብዛኛው የፐሮቴስታንት አመለካከት ሳይነካ ቀጠለ። የመቶዲስቶች የመጀመሪያ ቅንዓት፥ የፓየቲስት እንቅስቃሴ በአውሮፓ በያንክሃይም [Junkheim] ሲናቅ ለመከላከል እንኳ እንዳልቻለ፥ የእነሱም ቅንዓት እንዲሁ ተዳፍኖ ነበር። በአውሮፓ፥ በተለይም በጀርመን ቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው ጉዳት እንግሊዝን ስላልነካት እንደገና ለመነሣት ችላለች።

8. መንፈስ ቅዱስ በአሁኑ ዘመን

እዚህ ላይ ልንመለከታቸው የምንችለው ጥቂቶቹን ነገሮች ብቻ ቢሆንም፥ የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትን በተመለከተ በ19ኛው ምዕተ ዓመት ከፍተኛ ግኝቶች ተከናውነዋል። በ1888 በሆላንድ ቋንቋ የታተመው የአብርሃም ካይፐር ሥራ በሥነ-መለኮት ትምህርት መግለጫነት እጅግ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ቢያበረክትም በመንፈስ ቅዱስ የእምነት ትምህርት ረገድ ግን በአውሮፓ የታየው እድገት በጣም አነስተኛ ነው። በአብዛኛው ራሽነሊዝም ምንም ዓይነት እድገት እንዳይኖር አደረገ። ከ1768-1834 የኖረውና የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና የካደው ሽለይርማከር [Schleiermacher]፥ ጤናማው የሥነ-መለኮት ትምህርት

እንዲናቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ከ1822-1889 የኖረውና ሪችል [Ritschl] የተባለው ሰው ሥራ የሰውን ትኩረት ተግባራዊ ወደሆነ የክርስትና ኑሮ የሳበ ቢሆንም፥ የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ጉድለት ታይቶበታል። ስለ መንፈስ ቅዱስ ትምህርት ብቸኛ አስተዋጽኦ ያደረገው በጀርመናዊው ካንስ [Kahnis] የተከናወነው ሥራ ነበር። ሥራው በዘመኑ በነበሩ የጀርመን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዘንድ ንቀትና ፈተና ስለገጠመው ከፍጻሜ አልደረሰም።

እንግሊዝ ውስጥ የትራክቴሪያን [Tractarian] እንቅስቃሴ የሊበራሊዝምን (የለዘብተኝነትን) ትምህርት ለመቃወም ሙከራ ያደረገ ቢሆንም፥ በመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ረገድ ግን አንዳችም አስተዋጽኦ አላደረገም። በኤድወርድ ኧርቪንግ [Edward Irving] በስኮትላንድ የተጀመረው "የኧርቪንግ ቡድን" ቅጽበታዊ መገለጥ የተባለውን የጥንት ኑፋቄ እንደገና በማነሣሣት የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ዝቅተኛ ግምት እንዲሰጠው አድርጓል። የፕሊመስ ወንድማማቾች [Plymouth Brethren] መሠረታዊ የእምነት ትምህርትን የሚመለከቱ አንዳንድ ጠቃሚ አስተዋጽኦዎችን ቢያበረክቱም፥ ግሪፊስ ታመስ የተባለ ሰው እንዳለው መልካም ሥራቸው "በመከፋፈል አዝማሚያቸው" ተበላሽ። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ትርጉም፥ ስለ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ልዩ ባሕርይ፥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ስለ ገላጭ ስብከት አስፈላጊነት እንዲሁም የክርስቶስ መምጫ ቅርብ መሆኑን በትንቢታዊ ቃላት ሁሉ በሚገባ መግለጥን በሚመለከት አስተዋጽኦ ያበረከተው ይህ እንቅስቃሴ ነበር። የዚህ እንቅስቃሴ እውቅ መሪዎች የሆኑት የዳርቢ [Darby] እና ኬሊ [Kelly] ሥራዎች የቅድመ ሺሁ ዘመን መንግሥትን አስመልክቶ በሚቀርበው ትምህርት ስለሚኖሩ አመለካከቶችና ስለ ቤተ ክርስቲያን አዎንታዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ የመጨረሻ ክፍል ስለ መንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ሊኖር የሚችለውን ከፍተኛ ነጥብ ያሳያል። ይህ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ከ1856-1859 ባሉትና በተከታዮቹም ዓመታት በእንግሊዝ፥ በአየርላንድና በአሜሪካ ከተደረገው ወንጌልን የማስፋፋት ጥረት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ጊዜው ለመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ሙሉ ትኩረት የሰጡ የተለያዩ የቅድስና እንቅስቃሴዎች ከበጎና መጥፎ ገጽታዎቻቸው ጋር የመነጩበት ነበር። ዘላቂ ጠቀሜታ ከነበራቸው እንቅስቃሴዎች መካከል የኬዚክ [Keswich] እንቅስቃሴና፥ በአሜሪካ የዚሁ እንቅስቃሴ አካል የሆነው የዲ. ኤል. ሙዲ [D. L. Moody] ሥራ በቤተ ክርስቲያን ላይ ባሳደረው

አዎንታዊ ተጽዕኖና ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሰጠው ትኩረት ምክንያት በሚገባ የታወቀ ሊሆን ችሏል።

19ኛው ምዕተ ዓመት በተለይም ሁለተኛው አጋማሽ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ብዙ ጽሑፎች በተከታታዩ የተጻፉበት ዘመን ነው። ከእነዚህም መካከል በስሚተን የተጻፈውና በዚህ አጭር የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ታሪክ በተደጋጋሚ የተጠቀሰው፥ ‹‹የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት››፤ በጂ. ኢ. ከሚንግስ የተጻፈው፥ ‹‹በዘላለማዊ መንፈስ››፤ በኤች. ሲ. ጂ. ሙል የተጻፈው ‹ቬኒ ክሪኤተር›፤ በኤ. ቢ. ሲምፕሰን የተጻፈው፥ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ወይም ከላይ የሚመጣ ኃይል››፤ በቫውን [Vaughn] የተጻፈው ‹‹የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች›› የሚሉት ይገኙባቸዋል። ከእነዚህ መጻሕፍት መካከል የትኛውም ትምህርቱን በሚመለከት በቂና የተሟላ ገለጣ ለመስጠት ባይችል፥ ሁሉም የየራሳቸው ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

20ኛው ምዕተ ዓመት ለመንፈስ ቅዱስ ለመሠረታዊ የእምነት ትምህርት ትኩረት በመስጠት ረገድ ማሽቆልቆል የታየበት ዘመን ነው። አሳቡ በቸልታ አልታለፈም፥ የተከናወኑት ሥራዎች ግን ጥቂት ናቸው። ከጀርመን ዩኒቨርስቲዎች የሰረገው ለዘብተኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ዝቅ ተደርጎ እንዲታይ አድርጓል። ምንም እንኳን እምነትን አጽንቶ የመያዝ መልካም ጥረት ቢደረግ፥ እና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ገላጭ ትምህርት ቢሰጥ የአብርሆት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አጠያያቂ የሆነ ሁኔታ ላይ ወድቆ ነበር፤ እንደውም በአንዳንዶች ዘንድ ሙሉ ለሙሉ መሠረት የሌለው ነገር በመባል ተጥሏል።

ባለፉት ዓመታት የታየውን ማሽቆልቆል ተቋቁመው የዘለቁት ጥቂት ሥራዎች ብቻ ናቸው። ግሪፈስ ታመስ የጻፈውና ‹‹የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ›› የሚለው ጽሑፍ አጭርና ብስለትን የተሞላ የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት የቀረበበት ነው። በማብራሪያነቱ፥ በግልጥነቱና ሠርዖ በመግባት ባሕርይው ሲታይ ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር ‹‹መንፈሳዊው ሰው››* በሚል ርእስ የደረሰው መጽሐፍ የሚጠቀስ ነው። መጽሐፉ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት የተለየ መሆኑን፥ የቅድስና ባሕርይና ስፋት፥ በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና በመንፈሳዊ ብስለት መካከል ያለውን ልዩነት በግልጥ በማቅረብ ረገድ እጅግ ጠቃሚ ነው። ቼፈር በስምንት ተከታታይ መጻሕፍት ባቀረበው ታላቅና ክቡር የሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ ስድስተኛውን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ ለዚህ ዓላማ አውሎ በሚገባ በማብራራቱ ባለውለታ ነው። የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ለመንፈስ ቅዱስ

* ይህ መጽሐፍ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ገበያ ላይ ውሏል።

መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች መግቢያነት ይህንና ሌሎቹን የቼፈር ጽሑፎች በአያሌው ተጠቅሞባቸዋል።

የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ታሪክ፥ የሥነ-መለኮትን ትምህርት አስፈላጊ ገጽታዎች በመገንዘብ ረገድ የሚገጥሙ ችግሮችን ያመለክታል። ስሚተን የዚህ ምዕተ ዓመት ታሪክ ከመፈጸሙ በፊት በጻፈውና በሚከተለው ከበድ ያለ ቃል ከልብ ለመስማማት ይቻላል፦ ‘‘የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ በክርስቶስ ምሕረት ከሚሆነው በእምነት የመጽደቅ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚያንስ አይደለም። ይህ የአንዲትን ቤተ ክርስቲያን መቆም ወይም መውደቅ የሚመለከት የእምነት መግለጫ ነው። ከዚህ ግንዛቤ ውጭ መንፈሳዊ ብልጽግና አይኖርም ወይም ሊኖር አይችልም።’’

27

መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን ባሉ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች ውስጥ

ቀደም ሲል ስለ መንፈስ ቅዱስ የተመለከትናቸው ነገሮች ትኩረት የተሰጣቸው፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ፍጹምነት ከተቀበሉ ሰዎች አመለካከት አንጻር ብቻ ነው። በዚህ ርእስ ሥር የምንመለከታቸው አብዛኛዎቹ ነገሮች ግን ‘‘የመጽሐፍ ቅዱስን ፍጹምነት ማሳመን፥ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም ነው ብሎ መከላከል ስለማይቻል፥ ቅዱሳት መጻሕፍት በሰው አመለካከት ወይም በሰብዓዊ ፍርድ መመዘን አለባቸው’’ የሚሉ ሰዎችን አቋም ነው። የእነዚህን ሰዎች አመለካከት በዚህ ክፍል ‘‘ይህ አመለካከት’’ እያልን እንጠራዋለን። የመንፈስ ቅዱስን የሥነ-መለኮት ትምህርት በዚህ አቀራረብ የሚያሳዩትን ለዘብተኛ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት፥ ማለት እንደ ካርል ባርት ያሉ የክራይስስ ትምህርተ-መለኮት [Crisis Theology/ክራይስስ ቲያሎጂ]* ሊቃውንትን፥ እና በአሜሪካ ያለው የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት አስተሳሰብን (ኒዮ-ኦርቶዶክስ) ያሉትን በአጭሩ መመልከት አስፈላጊ ነው። የለዘብተኞች አስተዋጽኦ በሌሎች የሥነ-መለኮት ትምህርቶች ከሚገባ በላይ ስፍራ የተሰጠው ሲሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ላይ የጨመረው ነገር መኖሩ ግን አጠራጣሪ ነው። በአሁኑ ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚጻፉ ጽሑፎችን ለመገንዘብ የእነዚህን ሁኔታዎች እድገት መረዳቱ አስፈላጊ ነው።

1. መንፈስ ቅዱስ በለዘብተኝነት የሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ

የመንፈስ ቅዱስ ሉካላዊ ሕልውና። በጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች ለተገለጠና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለተመሠረተው የሥላሴ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ከለዘብተኝነት የመከሰቻ ነጥቦች አንዱ ሲሆን፥ ይህም በሀያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በነበሩ 30 ያህል

* ‘‘የክራይስስ ትምህርተ-መለኮት [Crisis Theology] በመባል የታወቀው የሥነ-መለኮት ትምህርት ሁኔታ የተፈጠረው በአንደኛ የዓለም ጦርነት ወቅትና በኋላ ከተከሠቱ ግራ አጋቢ ሁኔታዎች የተነሣ ነበር። ዛሬ ይህ አሳብ ‘‘ኒዮ-ኦርቶዶክሲ’’ (‘‘አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት’’) ወይም ‘‘ባርቲያኒዝም’’ በመባል ይታወቃል።

ዓመታት ውስጥ የታየ ነገር ነው። ለዚህ ዘመን ለዘብተኛ የሥነ-መለኮት መምህራን፥ በአንድ አምላክ ውስጥ ሦስት አካላዊ ሕልውና መኖሩ በመሠረቱ እርስ በርስ የሚጋጭና በምክንያታዊ የሥነ-መለኮት ትምህርት ረገድ ተቀባይነት የለውም። ዝንባሌው የዩኒተሪያንን አቋም የሚመለከት ሆኖ፥ እግዚአብሔር ራሱን በተለያየ መንገድ ቢገልጥም አንድ ነው የሚል ነው። ለዘብተኝነት በመሠረቱ የክርስቶስን መለኮታዊነት ስለማይቀበለው የሦስትዮሽ ባሕርይ ማለት የክርስቶስ ሥጋ መልበስና አካላዊ ሕልውና ጉዳይ ችግር አይፈጥርበትም።

ለዘብተኛ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት እንደሚሉት ‘‘በሥላሴ ትምህርት ላይ ያለ ችግር’’ የተፈጠረው የቀጥተኛ ሃይማኖት ተከታዮች ነን የሚሉ የሥነ-መለኮት አዋቂዎች መጽሐፍ ቅዱስን በጥሬ ቃሉ ከመረዳትና ከመተርጎማቸው የተነሣ ነው። ሁለተኛውን የሥላሴ አካል ጉዳይ በዚህ መልኩ ካቃለሉ በኋላ፥ የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በተመሳሳይ ሁኔታ ለማጥፋት ይጥራሉ። መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ያለው መሆኑን ከደው የመለኮት ሥራ መግለጫ በማድረግ ያቀርቡታል። በቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኙትንና የሥላሴን ትምህርት የሚደግፉ ክፍሎች አይመለከቷቸውም።

እግዚአብሔር አብሮን ስለመሆኑ የተሰጠ ትኩረት። አያሌ ለዘብተኞች መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና እንዳለው የሚናገሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከመካድ ጋር፥ አብረው የእግዚአብሔርን ከምንም የላቀ መሆን ከነአካላዊ ሕልውናው ይክዱና፥ በሁሉም ስፍራ በመገኘቱ ላይ ትኩረት ይሰጣሉ። ብዙ ለዘብተኞች ፍልስፍናዊ ምክንያት በማቅረብ፥ እግዚአብሔር በዚህ ክፉ ዓለም ሁሉን አድራጊ ወይም ከሁሉ በላይ አይደለም፤ ቢሆን ኖሮ ኃጢአትን፥ ሥቃይን፥ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የምናየውን የፍርድ መዛባት አይፈቅድም ነበር በማለት ይደመድማሉ። በእነርሱ ዘንድ እግዚአብሔር የተወሰነ፥ እጅግ በጣም ጥሩ፥ ነገር ግን ክፉን ለማጥፋት የሚታገልና ያልተሳካለት ነው።

የ18ኛው ምዕተ ዓመት ዲይስቶች መልካም በሆነው እግዚአብሔርና በክፉው ዓለም መካከል ያለውን ግንኙነት ሲገልጡ፥ እግዚአብሔር ከምንም የላቀ ቢሆንም፥ በየትኛውም ስፍራና በሁሉም ነገር ውስጥ የሚገኝ ግን አይደለም። ስለዚህ ዓለም የምትንቀሳቀሰው በእግዚአብሔር ቢሆንም በቀጥታ በቁጥጥሩ ሥር ግን አይደለችም ይላሉ። ዘመናዊው ለዘብተኛ ግን ተቃራኒውን፥ ማለትም እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይገኛል፥ ነገር ግን ከሁሉ በላይ አይደለም የሚል ማብራሪያ መርጧል። ሁሉን ስለማይችል ያለምንም ውጤት ከፍርድ መዛባትና

ከኃጢአት ጋር በመታገል ላይ ነው ይላሉ። ለእነርሱ እግዚአብሔር መልካምም ሁሉን አድራጊም መሆን እንደማይችል ግልጥ ነው፥ ምክንያቱም በእነርሱ አስተሳሰብ መልካምና ሁሉን አድራጊ የሆነ አምላክ፥ ዓለም ክፉ እንድትሆን አይፈቅድም።

ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይልን ወይም ልዕልናን መካድ። በዚህ የለዘብተኝነት አቀራረብ መሠረት መንፈስ ቅዱስ በዓለም ላይ የመለኮታዊ በጎ ጫና መግለጫ ነው። ለዘብተኞች አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርን ከተፈጥሮ ጋር የሚደምሩት የተፈጥሮ ኃይሎች፥ ሕጐችና መግለጫዎች ሁሉ አምላክ ናቸው ከሚለው የፓንቲይስት እምነት የሚለዩት በመጠኑ ነው። በዚህ መሠረት የእግዚአብሔርን አሠራር ተፈጥሮአዊ ወደሆነ፥ ተአምራትን ወደማይጨምር ነገር ዝቅ፥ መንፈሳዊ ልምምድን ደግሞ ተለምዶአዊ ማብራሪያ መስጠት የሚችል ሥነ-ልቦናዊ ጉዳይ ያደርጉታል። የክርስትና ሃይማኖት ተግባር በሰው ሕይወት ውስጥ ያለውን ሃይማኖታዊ ዝንባሌ ሥርዓታዊ፥ ማራኪና ግብረ ገባዊ የሆኑ መንገዶችን በመጠቆም ኮትኩቶ ማሳደግና ፍጥረታዊ ከሆነ ሰብዓዊነት በላይ እንዳይሄዱ ማድረግ ነው። ምንም እንኳን ለዘብተኞች በሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሥነ-መለኮት ትምህርት ራሳቸውን ባያርቁ፥ ሁሉም መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ መለኮታዊ አካል ስለመሆኑ ዋጋ አይሰጡትም። የእምነት ትምሕርታቸውም የመንፈስ ቅዱስን ከፍጥረታት እጅግ የላቀ መሆንና በፍጥረታቱ መካከል የመሆኑን እውነት የማስወገድ ዝንባሌ አለው።

የተአምራዊ መገለጥ ወደ ሰብአዊ ግኝት ዝቅ ማለት። በዚህ አቀራረብ ተአምራዊ መገለጥ ተወግዶ፥ በእርሱ ፋንታ ሰው እግዚአብሔርን ፈልጎ ማግኘት ወደሚል አስተሳሰብ ዝቅ ብሏል። የቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት፥ ተአምራዊው አዲስ ልደትና ሌሎቹ የክርስትና እምነት ተአምራዊ ገጽታዎች እንዲቀሩ ተደርጓል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያቀርባቸው የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውናና ሥራዎች በሙሉ ተጋርደዋል።

2. የካርል ባርት ሥነ-መለኮት

በሀያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ዓመታት የተፈጸሙ ሁኔታዎች፥ ሁለት የዓለም ጦርነቶችን ጨምሮ፥ በሥነ-መለኮትና በፍልስፍናዊ አስተሳሰቦች ላይ ሊቀሩ የማይችሉ ውጤቶችን አስከትሏል። ለዘብተኛ አስተሳሰብ ባላቸው ምሁራን የሚጸፉ ነገሮች በሥቃይና በሞት ዓለም ያለውን ሕዝብ ሊረዱ አልቻሉም። ስለዚህ ይህን አሳባዊ ብቻ የሆነና ተግባር ላይ የማይውል የለዘብተኞች አዋጅ የሚቃወም ሁኔታ መፈጠሩ

የማይቀር ሆነ። ከፍልስፍና በላይ የሆነው ሰብአዊ ፍጡር ራሱን ችሎ የሚቆምበት ነገር ያስፈልገው ነበር። የጦርነት አስፈሪነትና የኃጢአት ዋጋ እውንነት፥ ሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ጋር ይበልጥ ሊስማማ በሚችልበት መንገድ የራሱን ችግር ለማቃለል ያለመቻሉን ከግንዛቤ በማስገባት ፍላጐቱን የሚያቃልልለት መለኮታዊ መልስ መኖር አለመኖሩን ለመመልከት የመጽሐፍ ቅዱስን ሥነ-መለኮት ትምህርት እንደገና መመርመሩ የግድ ሆነበት።

የሥነ-መለኮትን ትምህርት የመመርመሩ እንቅስቃሴ እጅግ ሰፊ ቢሆንም፥ በዚህ ረገድ ከታወቁት አፈቀላጤዎች አንዱ የሆነው የስዊስ የሥነ-መለኮት ሊቅ ካርል ባርት ነው። ይህ ሰው አውሮፓን ጨለማና ተስፋ መቁረጥ ውጪት በነበረበት በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ከመጠን ያለፈ ለዘብተኝነት በሚታይበት የሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ ስለነበረ፥ እምነቱና መልእክቱ በራሱ ማኅበረ ምእመናን (ጉባኤ) ውስጥ ለነበሩና ተስፋ ለቆረጡ ምእመናን ፍላጐት ጨርሶ በቂ እንዳልሆነ ተመለከተ። በሰብዓዊ ሁኔታዎች ውስጥ መለኮት ጣልቃ እንዲገባ ለማድረግ ምእመናኑ ያሳዩት ለነበረው ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት ባደረገው ጥረት ይህ ስሕተት የመጣው የእግዚአብሔርን ሁሉን አድራጊነትና ከሁሉ በላይ መሆን በመካድ መሆኑን ቀስ በቀስ ደረሰበት። ባርት ‘‘ለሮማውያን የጻፈው መልእክት’’ በ1918 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ እንደወጣ፥ የሥነ-መለኮት ድርቅ መብረቅ የወደቀበት ያህል ሆኖ ነበር። ሥራው በብዙ ውስብስብ ሁኔታዎችና በክርክር መልክ የተጻፈ የሥነ-መለኮት ትምህርት በመሆኑና የቅዱሳት መጻሕፍትን እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት ከመካድ ያልተለየ በመሆኑ በመሠረተ አሳቡ ከለዘብተኞች ጋር አንድነት ያለው መሆኑን አሳይቷል። ሰው ደስተኛ በማይሆንበት ሁኔታ እንኳ ቅጽበታዊና መለኮታዊ የችግር መፍቻ መገለጥን የሚሰጠው፥ እንዲሁም ተአምራዊ በሆነ መንገድ ችግሩ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት የሚችለው እግዚአብሔር ነው በማለት መፍትሔ አግኝቶለታል። ከቀድሞው ቀጥተኛ ሃይማኖት የራቀ ቢሆንም፥ ጠፍቶ የነበረ አንዳንድ የከበረ እውነት እንዲታወቅና እንደገና ሥራ ላይ እንዲውል ከማድረጉ ጋር በአሁኑ ጊዜ ያሉ ሌሎች የሥነ-መለኮት ትምህርቶች በአጠቃላይ እንደገና የሚጠኑበትን መንገድ ጠቁሟል። ከጥቆማዎቹም መካከል ቅዱሳት መጻሕፍት አንዳችም ስሕተት የሌለባቸው መሆኑን እስከአሁን የማይቀበሉትን የሚመለከቱ አሉበት።

ባርት ሰለ መንፈሰ ቅዱስ ሉካሳዊ ሕልውና ያለው ሉመለካከት። የቀድሞ የእምነት አባቶች የሥላሴን ትምህርት ችግር እንዴት ይመለከቱት እንደነበር እንደገና እንዲመረምር ያደረገው ጥናት ባርትን ረድቶታል።

ላበረከተው አስተዋጽኦ ቁልፍ የሆነው ነገር የተመሠረተው፥ መንፈስ ቅዱስ አዲስ የእምነት ትምህርት በመጀመሩ ላይ ነው። ይህም ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ጥናት እንዲያካሄድና ግልጥ የሆነ ትርጉም እንዲፈልግ አድርጎታል። ባርት መንፈስ ቅዱስ ከሥላሴ አንዱ ወይም እግዚአብሔር ራሱን ከገለጠባቸው መንገዶች አንዱ መሆኑን በመምረጥ ፍጥጫ ውስጥ በገባ ጊዜ ሁለቱንም ሳይቀበል ቀርቷል። በአንድ በኩል ‘‘አካላዊ ሕልውና’’ የሚለውን ቃል ወደ ሥሉስ አምላክነት አሳብ ይመራል በማለት ውድቅ ሲያደርገው፥ በሌላ በኩል ደግሞ ‘‘ሞዳሊዝም’’ ወይም የመለኮት በሦስት መንገዶች የመገለጥን አሳብ በቂ መግለጫ አይደለም በማለት አልተቀበለውም።

ስለ መንፈስ ቅዱስ የሰጠው ትርጉም በግልጥ የተብራራ ሳይሆን ግምታዊ አሳብ ሆኖ ሥላሴ፦ ሦስት መለኮታዊ ሕልውናዎችን ወይም ማንነታቸውን መግለጫ ሳይሆን፥ የተነጣጠሉ አካላት ናቸው ከሚለው መረዳት ያነሰ፥ አንዱ ራሱን የገለጠባቸው ሦስት መንገዶች ናቸው ከሚለውም የበለጠ ፅንሰ-አሳብን የያዘ ነው ይላል። ወበር [Weber] እንዳለው፦ ‘‘ባርት በሥላሴ ታሪካዊ ትምህርት ውስጥ አካል በሚለው አሳብ ቅሬታ ስላለው በዚያ ምትክ የሕልውና መግለጫ ‘ሦስት መንገዶች’ ማለትን መርጧል።

ባርት ስለ ሥላሴ የሰጠው መግለጫ፥ የቀጥተኛ ሃይማኖት ተከታዮች የእምነት መግለጫ፥ ‘‘አካል’’ በማለት የሰየመው ቃል ሥላሴን ለመግለጥ ጥቅም ላይ መዋሉ የሚያስነሣውን ግልጥ ችግር በዘዴ ለማቃለል ያደረገው ሙከራ ነበር። በዚህም ምክንያት የእርሱ አመለካከት በአንዳንድ የቀጥተኛ ሃይማኖት ይዘት ባላቸው ዘንድ እንኳን ተቀባይነት አግኝቷል። ባርት መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ መሆኑን ይቀበላል። ስለዚህም እንዲህ ብሏል፥ ‘‘መንፈስ ቅዱስ በፍጹም መለኮትነቱ በፍጹም ሉዓላዊነቱና በጸጋ ተግባሩ፥ በመሰወሩና በመገለጡ ጌታ አምላክ ነው።’’

ባርት ስለ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነት ያለው አመለካከት። መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የሚሠራውን ተአምራዊ ተግባር ባርት እንደሚከተለው በጽሑፉ ግልጥ አድርጐታል፦

> ‘‘1. ሰው የእግዚአብሔር አምሳል የመሆኑ ጉዳይ እውነት የሚሆነው መንፈስ ቅዱስ በሰው ፋንታ በስፍራው በሚገኝበት ቅጽበት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን መምሰል የተፈጠረው የሰው መንፈስ የግል ባሕርይ አይደለም፥ አይሆንምም፤ ነገር ግን ፈጣሪ በፍጥረቱ ላይ ያደረገው ነጻ የመፍጠር ሥራ ነበር፥ ነውም። ጸጋነቱን ብቻ እንጂ ከዚያ ባሻገር ሰው ሊረዳው የሚቻለው ነገር አይደለም፤

2. የክርስቲያን ሕይወት፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ቃሉን እንዲቀበል የተደረገ ሕይወት ነው። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ልብ መኖሩና የሚያከናውነው ሥራ በግልጥ የሚታየው፥ በሰው ሕይወት ውስጥ መገለጥ ሲኖር ነው። ሰው ፈጣሪው ከእርሱ የሚፈልግበትን ነገር፥ ተፈጥሮን በሚመለከት፥ ያለው እውቀት በራሱ ጥረት ያገኘው ሳይሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጠው ነው።''

ከሁሉ በላይና ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ፥ እውነተኛ መገለጥን ለሰው ለመስጠት ግርማዊና ሉዓላዊ በሆነ መንገድ ወደ ሰብዓዊ ሁኔታ መግባቱን ባርት እንደሚገምት ከዚህ ማጠቃለያ በግልጥ እንረዳለን። ለባርት አመለካከት ቁልፉ ነገር መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ተግባር ባለው ተሳትፎ መሠረት ሰው ''ከእግዚአብሔር ቃልና ከልምምድ...'' ለሚያገኘው እውቀት እውነትን መግለጥ ነው። ባርት የቀጥተኛ ሃይማኖት ፅንሰ-አሳብ የሆነውንና መጽሐፍ ቅዱስ ስሕተት የሌለውና የማይሻር ነው የሚለውን ትንታኔ አይቀበልም። በተቃራኒው ''ጥልቅ የትንተና ጥናት''* [Higher Criticism/ሀየር ክሪቲሲዝም] የተባለውን አመለካከት ተቀብሏል። ለእርሱ ቅዱሳት መጻሕፍት ከስሕተት ያልራቁ ቢሆኑም እንኳ፥ ከሃይማኖታዊ ልምምድ ጋር በመንፈስ ቅዱስ በኩል ለሆነው መለኮታዊ መገለጥ መሣሪያ ሆነዋል። ሥልጣኑ ለመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ለልምምድ ሳይሆን፥ በነርሱ በኩል በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ቅጽበታዊና መለኮታዊ መገለጥ ነው።

---

* ይህ ጥናት የተመሠረተው የጥንት ጸሐፊዎችንና መጻሕፍቱ የተጻፉበትን ወቅት በማጥናት ላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ይህ ሥርዓታዊ ጥናት የተጀመረው ከተጠራጣሪነትና በጥያቄ ከመሞላት የተነሣ ነው። በዚህ ጥናት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ከማንኛውም መጽሐፍ የማይለይ፥ የተለያዩ የሃይማኖት ሰዎች የጽሑፍ ስብስብና ጽሑፋቸውም በጥንት ታሪክተና ባህሎች የተመረኮዘ መጽሐፍ ነው ብለው ይወስዱታል። ይህን አሳባቸውን ለመደገፍ ሲሉ የሚታረኑ ነገሮችን በመፈለግ መጽሐፍ ቅዱስን ባጠያያቂ መልክ ያቀርቡታል። በዚህ ሥራ የተሰማሩ ቡድኖች፥ ዓላማቸው የትክክለኛውን ጸሐፊ ማንነትና የጽሑፎችንም ምንጭ ለመለየት እንደሆነ ይናገራሉ።

በዚህ ጥናት ውጤት ልክ የቤተ ክርስቲያን የመገለጥና የእስትንፋሱ-እግዚአብሔር አሳብ ሰዎች ተቃውሞና ትችት እንዳስነሡበት፥ ያስከተለው ነገር ቢኖር የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊነትና አስፈላጊነትን መቃወም ነው። ወንጌላትን በተመለከተ ስለ ኢየሱስ የሚናገሩ የታሪክ ጥርቅሞች እንደሆኑና ጓላም በተነሡ ጸሐፊዎች ተጣሞ የቀረበ በማለት ይወስዱታል። የአራት መጻሕፍትን በተመለከተ አንድ ሰው (ሙሴ) እንዳልጻፈውና ከጸሐፊዎቹ ሌላ በአንድነት እንደተጠናከሩ ይናገራሉ። የሐዋርያው ጳውሎስን የመልእክት ጽሑፎችንም እርሱ እንዳልጻፋቸው በማድረግ ያቀርበዋል። የተጻፉበትን ጊዜያት በተመለከተ ወቅቶችን በማሸጋሸግ የትንቢቶችን አፈጻጸም ለማፋለስ ይጥራል። የዚህ ጥናት አቀንቃኞች የደረሱበት ማጠቃለያ ''መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም'' የሚል ሲሆን ይህም የሚያስደንቅ አይደለም ከተነሡበት የጥናት አኳያ ስናየው።

ይህ የመገለጥ ማብራሪያ፥ ባርት ለዘመኑ የሥነ-መለኮት ትምህርት ያበረከተው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነው። የሥልጣንን ጥያቄ በሚመለከት የሚሰጠው አሳብ ቀኖናዊና በምክንያት ላይ ያልተመሠረተ ነው። መለኮት መገለጥ የሚሰጥበትን ተአምራዊ ልምምድ መረዳቱ የሚያስቸግርና በተለመደ መመዘኛ የማይፈተን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ፈቃድ የመጨረሻና ፍጹም መገለጥ ሆነው ከመጻፋቸው በፊት፥ ነቢያት የተለማመዱት ይህን ዘመናዊ የመለኮታዊ መገለጥ ዘዴ ነበር።

ሰለ መንፈስ ቅዱስ አሰታራቂነት የባርት አመለካከት። ባርት ስለ መገለጥ ካለው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ጋር መንፈስ ቅዱስ ዓመፀኛውን የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ የጸጋ መንፈስ እንደሆነ ያምናል። አመለካከቱን በሚከተለው ሁኔታ አስፍሮታል፦

> "1. መንፈስ ቅዱስ የጸጋ መንፈስ ስለሆነ ሰው በጸጋ ላይ እንዳያምፅ ይተጋል። በሌላ አባባል ሰው ራሱን በሥራ ሊያጸድቅ ይፈልጋል። ይህ ሰው ሊያስወግደው ወይም ማሰቡን ሊያቆም የማይቻለው ኃጢአት ነው። መንፈስ ቅዱስ የዚህ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ይተጋል፤ 2. ክርስትና ሰው በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ የሚኖረው እውነተኛ ሕይወት ነው። ሰው በእግዚአብሔር ቃል ወይም በክርስቶስ የተነሣ ጻድቅ ሆኖ ይቆጠራል። በበኩሉ ማድረግ ያለበት እምነቱን በንስሐና በመታመን መግለጥ ነው። ምክንያቱም ይህ እንደ ጻድቅ መቆጠር ከሰው ጋር መያያዙ ከቅድስናው ጋር ይዛመዳል። ሰው የተቀደሰ እንደመሆኑ መጠን፥ ለእውነተኛ እርሱነቱ የሚያሳየው ታዛዥነት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው። ይህ እውን የሚሆነው ለመንፈስ ቅዱስ ምላሽ ሲሰጥ ነው።"

ባርት ክርስቶስ በመስቀል የፈጸመውን ሥራ ሳይከድ፥ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅን ሥራ፥ በአንድ ቃል የቅድስናን አገልግሎት የፈጸመው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ተናግሯል። ይህን አቋም በመከተልም ለዘብተኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት ተከታዮች የመንፈስ ቅዱስን ወሰን የለሽና ተአምራዊ ተግባር መካዳቸውን ተቃውሟል። አመለካከቱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ከሚባለው አመለካከት ጋር ሙሉ ለሙሉ አንድ ባይሆንም፥ የሚቀራረብና መንፈስ ቅዱስን የሚያከብር ነው።

የባርት አመለካከት ሰለ መንፈሰ ቅዱስ የመቤዠት ሥራ። ባርት መንፈስ ቅዱስ የመቤዠት ሥራ ይሠራል ሲል፥ የክርስቶስን የመቤዠት ሥራ ማለዋወጡ ሳይሆን፥ ሰውን በሚመለከት ካለው ተግባራዊነት አንጻር መናገሩ ነው። አመለካከቱን እንደሚከተለው ይገልጣል፦

"1. በእግዚአብሔር መገለጥ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ለሰው የተሰጠ ተስፋ መሆኑ ተነግሯል። በመሠረቱ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ በመጨረሻ ከሰው ምድራዊ ሕልውና በላይ የሆነው ነገር፥ ሰው አዲስ ፍጡርና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ነው፤ 2. ክርስትና ከመንፈስ ቅዱስ የተገኘ አዲስ የተስፋ ሕይወት ነው። ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ውስጥ የተሰወረ ሰው መሆኑ፥ ሁልጊዜ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራ ሕሊና አለው። ከእግዚአብሔር ጋር በምስጋና ለመራመድ ዘወትር ዝግጁ ነው። ስለዚህ በነጻነት ውስጥ ነው ያለው። ይጸልያል፤ ሁልጊዜ በመጸለዩም ጸሎቱ ይሰማል።"

ባርት ስለ መንፈስ ቅዱስ ባለው አመለካከት፥ አማኝ በክርስቶስ ያለው አዲስ ሕይወት መለኮታዊ አስፈጻሚ አካል፥ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ያምናል። ሰው በክርስቶስ በሚለወጥበት ጊዜ፥ ሕይወቱ መሠረታዊ የሆነ ለውጥን እንዲያገኝ የሚያደርግና ለተስፋ የአዲስ ሕይወት ምንጭ የሚሆንለት መንፈስ ቅዱስ ነው። ባርት በሌሎች የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርቶች አካባቢ እንዳለው አመለካከት የቀጥተኛ ሃይማኖት ተከታዮች ሊቀበሉት በሚችሉት መንገድ በማያሻማ አኳኋን ባይገልጠውም፥ በይዘቱ እኩል ወይም ተመሳሳይ ነው። በዚህ ድርጊቱ የለዘብተኞችን አለማመን ይፃረራል።

የባርቲያኒዝም ጉድለቶች። ከክርስትና እምነት ብዙ ገጽታዎች አንጻር ያየነው እንደሆነ፥ የባርት አመለካከት ለቀጥተኛ ሃይማኖት እጅግ የቀረበ ነው። ይህንንም በተለይ በሐዋርያት የእምነት መግለጫ ላይ ያሉ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶችን አንድ በአንድ ባቀረበበትና ባረጋገጠበት፥ "የክርስትና እምነት በዝርዝር" በሚለው ጽሑፉ ገልጦታል። ነገር ግን በቀጥተኛ መመዘኛ ሲታይ እንደ እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ደጋፊ ለመታየት የማይችልባቸው በርካታ ነጥቦች አሉ። ባርት ቀደምት የሆኑት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ሊሻሩ የማይችሉ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሆናቸውን አይቀበልም። እንዲሁም ሁሉንም ባይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚሰነዘሩ አንዳንድ ጥልሀ ትችቶችን ይደግፋል። የአዳምና ሔዋንን ታሪክ እውነተኛነት በግልጥ ይቃወማል። ከዘመናዊ ለዘብተኞች ይልቅ ለቅዱሳት መጻሕፍት ስፍራ የሚሰጥ ቢሆንም፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚመለከታቸው ከመለኮታዊ መገለጦች እንደ አንድ ክፍል አድርገው ነው። መለኮታዊ እውነት እንደመሆኑ መጠን፥ ሥልጣን እንዳለው የሚቆጠረው በመንፈስ ቅዱስ ሕያውና ሰው የሚረዳው ሲሆን ብቻ ነው ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ከመሆን ይልቅ፥ ቃሉ ወዲያውኑ ወደ ሰው የሚሸጋገርበት መተላለፊያ ነው ብሎ ያምናል።

ባርት ዘመናዊ ለዘብተኛ እንደመሆኑ ሃይማኖታዊ ሥልጣንን ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ይልቅ በመገለጥ ልምምድ ውስጥ አግኝቻለሁ ይላል። አክራሪ ከሆኑ ለዘብተኞች በተቃራኒ ይህ ልምምድ ለባርት ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ተአምራዊ ነው። መገለጥን የሚመለከተው የባርት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ድክመት የሚታየው በተለይ ከሰው ልምምድ ውጭ በሆኑ እንደ ፍጥረት ታሪክና ትንቢት በመሳሰሉ መለኮታዊ መገለጦች አካባቢ ነው። ባርት ስለ መለኮታዊ ፍርድ፥ ስለ ዘላለማዊ ቅጣትና ስላልተፈጸሙ ትንቢቶች ያለው አመለካከት በጣም ደካማ ነው። ባርቲያኒዝም ከመጀመሪያው ለዘለብተኝነት ወደ ቀጥተኛ ሃይማኖት የተደረገ ሽግግር ቢሆንም፥ በብዙ አቅጣጫ ለመረዳት የሚያስቸግር፥ የሚያደነጋግርና ከቀጥተኛ ሃይማኖት ጋር የማይጣጣም ነው።

3. መንፈሰ ቅዱስ በአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት የሥነ-መለኮት ትምህርት

አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት (Neo-Orthodoxy/ኒዮ-ኦርቶዶክሲ) የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ የባርትን አመለካከት ለማመልከት የሚያገለግል ቢሆንም፥ ብዙ ጊዜ የተያያዘው ግን ከአሜሪካና ከእንግሊዝ የባርቲያኒዝም አመለካከት ጋር ነው። ይህ ቃል በብዙ ረገድ ትክክለኛ አገላለጥ አይደለም። በትምህርትነቱም ከቀጥተኛ ሃይማኖት የራቀ ነው። የመሠረተ አሳቡ አብዛኛው ክፍል አዲስ የሆነው በይዘት ሳይሆን ከስፍራ ጋር በተገናዘበ መልኩ ሆኖ፥ በለዘብተኛና ቀጥተኛ ሃይማኖት ትምህርት መካከል ያለ አመለካከት ነው።

የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት እንቅስቃሴ። የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት እንቅስቃሴ፥ እንደ ባርቲያኒዝም ሁሉ ቀጥተኛ ሃይማኖተኛነትም በ1ኛውና በ2ኛው የዓለም ጦርነት መካከል በነበረው ዘመን ለዘለብተኝነትን ለመቃወም የተጀመረ የሥነ-መለኮት ትምህርት ነው። ከለዘለብተኝነት የመሸሽ አዝማሚያ የተጀመረው በ1ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት [1914-1918] ቢሆንም፥ በሥነ-መለኮት ትምህርት በእንቅስቃሴ ላይ የነበረው የለዘለብተኝነት አዝማሚያ እስከ 2ኛው የዓለም ጦርነት [1939-1945] ድረስ ሽንፈት አልገጠመውም፥ አልተቀለበሰም። ፍልስፍናም ሆነ የሥነ-መለኮት ትምህርት በ1940 ዓ.ም. ወደ እውነተኛነት በማዘንበሉ የለዘለብተኝነትን እድገት ገታው። ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ለሥነ-መለኮት ትምህርት ውይይት የሚታመን አቀራረብ ያለው አዲስ ቀን መምጣቱ፥ ተስፋ የሚያስቆርጠው የሰው ሁኔታ የመለኮትን ድምፅ የሚገነዘብበት አዲስ መንገድ መገኘቱን ጠቆመ። በአሜሪካ የለዘለብተኝነት ተቃውሞ የቀረበው

በመጠኑ ነበር። ለዚህም ምክንያቱ፥ በቅድሚያ ለዘብተኝነት እራሱ እንደ አውሮፓ በአሜሪካ አለመስፋፋቱና በአንጻራዊነት የጦርነቱ ችግር የአውሮፓን ያህል ያልጎዳት መሆኑ ነበር።

ከአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት መምህራን መካከል ኤሚል ብሩነር [Emil Brunner]፥ ራይንሆልድ ኒቡር [Reinhold Neibuhr] እና ፓውል ቲሊክ [Paul Tillich] ከበርካታ ሰዎች ጋር በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ብሩነር እንደ ባርት ሁሉ የስዊዘርላንድ ተወላጅ ቢሆንም፥ በጽሑፍም ሆነ በአገሪቱ በሰጠው ትምህርት ለአሜሪካ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ በባርትና በአሜሪካ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዘንድ መጠነኛ ግንኙነት ፈጥሯል። ራይንሆልድ ኒቡር አዲሱን የቀጥተኛ ሃይማኖት ትምህርት በአጠቃላይ ያቀረበ ሲሆን፥ በጣም የታወቀና ይህንን ትምህርት በሥልጣን ያስፋፋ ነው። ቲሊክ ደግሞ በአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖትና በቀድሞው ለዘብተኝነት መካከል ግንኙነት የፈጠረ ሲሆን፥ በዚህ ድርጊቱ አዲሱን የቀጥተኛ ሃይማኖት ግራ ክንፍ ይወክላል።

አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት የሥነ-መለኮት ትምህርት በአጠቃላይ ሲታይ። አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ከማንኛውም ዓይነት የእምነት መግለጫ ጋር ያልተያያዘና በርካታ ነገሮችን ያካተተ ስለሆነ ለትምህርቱ ደንብ ማብጀት አስቸጋሪ ነው። በአጠቃላይ ሲታይ ግን እንደ ባርቲያኒዝም የተአምራዊ እንቅስቃሴ አንዱ ገጽታ ነው። ሃይማኖትን ወደ ተፈጥሮአዊ ነገር እንዲያዘነብል የሚያደርገውና ተአምራዊነትን የሚቃወመው የቀድሞው ለዘብተኝነት፥ በእግዚአብሔር ከሁሉ በላይ መሆንና በተአምራዊነት ተተካ። አዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት የቅዱሳት መጻሕፍት ተአምራት ተአማኒ አይደሉም የሚል ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ጸጋውን ለሰው ልጆች መስጠቱንና ራሱን መግለጡን እንድ ተአምር ይቆጥረዋል።

ሌላው የባርቲያኒዝምና የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት (ኒዮ-ኦርቶዶክሲ) ተመሳሳይነት እግዚአብሔርንና ሰውን በተነጻጻሪነት ማቅረቡ ነው። ሰው ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔር የሚያስፈልገው ኃጢአተኛ ነው። የእግዚአብሔር ልዑልነት እንደገና ግንዛቤ ሲያገኝ የሰው ፍላጐት የሚሚላው በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ መሆኑ ታወቀ። ይሁን እንጂ የቀጥተኛ ሃይማኖት የምትክ መሥዋዕትነት አሳብ በአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ውስጥ ስፍራ የለውም። የክርስቶስ ሞት የደኅንነት ዋጋ የሆነበት እውነተኛ የመዋጀት ድርጊት ፅንሰ-አሳብም ተቀባይነት አላገኘም። የክርስቶስን ትንሣኤ በመተርጎም ረገድ የቀድሞ ለዘብተኞችን አዝማሚያ ይከተላሉ። ባርት የክርስቶስን ትንሣኤ ታሪክ በሚመለከት ጨርሶ ጥያቄ የሚያነሣ አይመስልም። የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ትምህርት ግን

ክርስቶስም ሆነ፥ ሰዎች ሁሉ ትንሣኤ የማግኘታቸውን ጉዳይ አጠያያቂ ያደርገዋል። ባርቲያውያንም ሆኑ የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ተከታዮች፥ ዘላለማዊ ፍርድን በሚመለከት ጥርጥርን የሚያስነሡ ሲሆን፥ ቢያንስ ለተወሰነ የሰው ዘር የሚሆን ሕያውነት አለ ብለው ያምናሉ። የክርስቶስን አምላክነት በሚመለከት ግልጥ ያልሆነ ወይም ከቀጥተኛ የእምነት መግለጫ ጋር የሚጋጭ ትምህርት ማቅረባቸው እርግጥ ነው። እንደ ባርት ያሉ የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ሥነ-መለኮት ትምህርት አዋቂዎች ከቃል በቃል የመጻፍ ዘዴ ጋር እኩል የሚያደርጓቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ፍጹም እስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሆናቸውን ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም።

በአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ክልል በርካታ የተለያዩ ትኩረቶችን ማድረግ ይቻላል። ቻርልስ ራይሪ [Charles Ryrie] ስለ አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ባደረገው ጥናት እንደጠቆመው፥ ባርትን በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ላይ አጥብቀው ከሚያተኩሩት ወገን ደምሮታል። ብሩነር ደግሞ ከሰው ተፈጥሮ በመጀመር ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ መሆኑን ተናግሯል። የኒቡር አቀራረብ ደግሞ ሰው የጎበረተሰቡ አካል ከመሆኑ ይጀምርና የሃይማኖት ግቡ ጎብረተሰቡን መለወጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ቲሊክ ከኒቡር ጋር የሚቀራረብ አመለካከት አለው። ባርትን ሳይጨምር፥ አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት በጣም አስፈላጊ በሆኑ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች ላይ ያለው አመለካከት፥ በተወሰነ መጠን ተአምራዊነትን ተፈጥሮአዊ በሆነ የለዘብተኝነት ትኩረት ከመተካቱ በቀር፥ ከቀድሞ ለዘብተኝነት ፈቀቅ ያለው በጥቂቱ ነው።

አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ሰለ መንፈሰ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ያለው አመለካከት። የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ሥነ-መለኮት ሊቃውንት በአጠቃላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ያላቸውን ግንዛቤ የሚገልጡት በጥቂቱ ነው። አብዛኛዎቹ የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ምሁራን፥ ባርት የተቀበለውን የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት አይቀበሉም። መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ካለመቀበላቸውም በላይ አምላክነቱንም የሚቀበሉት እንደ ዩኒተሪያኖች ‘‘መንፈስ ቅዱስ የመለኮት መግለጫ ነው’’ በማለት ነው። አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ስለ ጉዳዩ ያለው እውነተኛ መግለጫ በጣም ውሱን ነው። የዚሁ ሃይማኖት ቀኝ ክንፍ የሆነው ጆርጅ ሄንድሪ [George Hendry] ብቻ ከሌሎቹ ይለያል። ሄንድሪ የሥላሴ ትምህርት የአዲስ ኪዳን ትምህርት መሆኑን ተቃውሟል። ነገር ግን የትምህርቱ አንዳንድ ክፍሎች በአዲስ ኪዳን እንደሚገኙ ይቀበላል። በመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ላይ ያቀረበው አሳብ፥ ስለ ሥላሴ ትምህርትና ከእርሱም ጋር ስለተያያዙ ሁኔታዎች ግልጥ የሆነ

ማብራሪያ መስጠት ያልተቻለባቸው ችግሮች እንደገና እንዲነሡ አድርጓል። የሄንድሪ ትምህርት ዋና ነጥብ፥ በሥላሴ አካላት መካከል ያለው የቅድሚያ ግንኙነት የተግባር ጉዳይ ነው የሚል ነው፡- ‘‘በመካከላቸው ያለው ልዩነት የተግባራቸውን ክልል የሚያሳይ ነው . . . የአንዳቸው ስም ለሌላው ይሆናል’’ ብሏል። ይሁን እንጂ፥ በኋላ የሚከተለውን በማረጋገጥ እራሱን ከሞዳሊዝም ለመለየት ሙከራ አድርጓል፡- ‘‘የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ለእምነት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ የሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ግንኙነት የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና የሚያረጋግጠው እምነት ነው ማለት ሳይሆን፥ ከእኛ ጋር ባለው ግንኙነት መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና እንዳለው የሚያረጋግጠው እምነት ነው ማለታችን ነው። መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ተጽዕኖ ወይም ኃይል ብቻ አይደለም።’’

ብሩነር ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ያለው አመለካከት የባርትን አቋም ያህል እጅግ ግልጥ የሆነና የአሜሪካን የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት የሚጻረር ነው። በቀድሞ አባቶች ስሜት እግዚአብሔር በትክክል አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አረጋግጧል። ሰው ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለው ልምምድ ግላዊ ነው። ብሩነር ተጨማሪ ማብራሪያ ሲሰጥ፡- ‘‘ስለዚህ መንፈስ ቅዱስም አካላዊ ሕልውና ያለው መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፥ በአዲስ ኪዳን እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ሊነሣ አይችልም። እግዚአብሔር ራሱ አካላዊ ሕልውና አለው ወይ? ብሎ የመጠየቅ ያህል ነውና’’ ብሏል። በአንዳንድ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች፥ አንዳንድ የመንፈስ ቅዱስ መገለጦች ግላዊ እንዳልሆኑ ተደርገው ሊተረጎሙ የሚችሉ መሆናቸውን ከጠቆመ በኋላ፡- ‘‘ነገር ግን በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ታላላቅ መምህራን፥ በጳውሎስና በዮሐንስ ጽሑፎች ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ባሕርይ አንዳችም ጥርጥር የለም። በመጨረሻም ዮሐንስ ይህ አካላዊ ሕልውና ከጌታ የሥነ-ልቡናና አካላዊ ሕልውና፥ እንዲሁም ከአጽናኙ ጋር የሚመሳሰል መሆኑን ከመግለጥ ወደ ኋላ አላለም። መንፈስ ቅዱስ ራሱ እግዚአብሔር ነው፥ . . . እርሱ ስጦታ ብቻ ሳይሆን ሰጪ ነው። እርሱ የሚናገር፥ የሚፈጥር፥ የሚፈርድ፥ የሚመራና የሚያቅድ አካላዊ ሕልውና ነው። መንፈስ ቅዱስ ይመሰክራል፥ ያስተምራል፥ ይቀጣል፥ ይሠራል፥ ይሰጣል፥ ይፈቅዳል፥ ይጸልያል። ሰውም ሊያሳዝነውና ስሙን በከንቱ ሊያንድፈው ይችላል’’ በማለት ያረጋግጣል። ከዚህ ግልጥ ዓረፍተ ነገር የምንረዳው፥ ብሩነር ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ያለው አቋም ከባርትም ጠንካራ መሆኑን ነው።

በተቃራኒው ቲሊክ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና አይቀበልም። ስለ ሥላሴ በሚሰጠው ትንተና ስለ ክርስቶስ በማስተማሩ ላይ ያደላል። እንደ ቀጥተኛ ሃይማኖተኞች ሁሉ የክርስቶስን መለኮታዊነት የማይቀበል መሆኑ እርግጥ ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ያለው አስተሳሰብ በግልጥ ያልቀረበ ቢሆንም፥ የዩኒተሪያኒዝምና የሞዳሊዝም አመለካከት ያለው መሆኑ እርግጥ ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ማገናዘቢያ መንፈስ ቅዱስ እውነትን የሚገልጥና የእግዚአብሔርን ተግባር የያዘ ነው ይላል።

ኒቡር፥ ከቲሊክ በምንም የተሻለ የቀጥተኛ ሃይማኖት ተከታይ አይደለም። በክርስትናና በማኅበራዊ ጉዳይ ላይ ይበልጥ ትኩረት ስለሚያደርግ፥ እራሱን እንደ ሥርዓታዊ የሥነ-መለኮት ሊቅ አይቆጥርም። ‘‘የሰው ተፈጥሮና የመጨረሻ ዕጣው’’ የሚለውና እንደ ታላቅ አስተዋጽኦ የሚቆጠረው ሥራው፥ ሰው ከክርስቶስና ከሥራው ጋር ያለውን ግንኙነት በሰፊው የሚገልጥ ሲሆን፥ በሰው ልጅ አኗኗር ጥናት [Anthropology/ አንትሮፖሎጂ] ውስጥ ቀጥተኛ ለውጥ ያደርጋል። ይህ ሰው በክርስቶስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ላይ ያደረገው ትኩረት፥ የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሚጻረር መልክ በመሆኑ፥ ‘‘ባይኒታሪያን’’ [Binitarian] (ሁለትዮሽ አማኝ) እንደሆነ ፓውል ሌማን [Paul Lehman] ጠቁሟል። ሌማን እንዳመለከተው ኒቡር፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርት ያለው አመለካከት በመረጃዎች ላይ የተደገፈ ሳይሆን የራሱን ስሜት ያካተተ (ሚስቲሲዝም) ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስን መለኮታዊ ትምህርት በሥሉሥነት (ሥላሴን በሚያሳይ ስሜት) የሚገነባ አይደለም።

እነዚህ የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት አፈ ቀላጤዎች ወይም አራማጆች፥ ይህ እምነት፥ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና በሚመለከት ታሪካዊ በሆኑት የቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች ውስጥ የተገነዘብነውን ነገር በግልጥ የማሳየት አቀራረብ እንደሌለው ያሳያሉ። መንፈስ ቅዱስም ተአምራዊና ጸጋን የተሞላ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን እንጂ ከሥላሴ አካላት አንዱ መሆኑን አይቀበሉም። ከባርትና ከብሩነር በስተቀር የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና ለሚመለከተው ትምህርት ግዴለሾች መሆናቸውን ጽሑፋቸው ያመለክታል። ትኩረታቸው መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰው በሚደርስበት ሁኔታ ላይ ነው።

አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ስለ መገለጥ ያለው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት። የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት እንቅስቃሴ ቁልፍ የሚገኘው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በአጠቃላይ በሰጠው መገለጥ ላይ ባለው

መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ነው። ኃያሉ እግዚአብሔር ኢምንት ከሆነ ሰው ጋር እንዴት ይገናኛል? የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ችግር በአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ጽሑፍ ውስጥ ዋናው ነገር ነው። መልሱም የሚወሰነው መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ መገለጥን በመስጠት ረገድ ባለው ሚና ነው። የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት የሥነ-መለኮት ምሁራን "የእግዚአብሔር መንፈስ በቤተ ክርስቲያን በኩል በሥልጣን ይናገራል" የሚለውን የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንም ሆነ "የእግዚአብሔር መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል በሥልጣን ይናገራል" የሚለውን የቤተ ክርስቲያን አዳሾችን አቋም አይቀበልም። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በመሥራትና ሰብአዊ ልምምድን በመፍጠር ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ቅዱሳት መጻሕፍት ለብቻቸው ከሚያስገኙት የበለጠ ውጤት ያመጣል። የእግዚአብሔር መንፈስ በሥነ-መለኮት መለያዎችም ሆነ በቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች ውስጥ የመሥራት ሥልጣን ያለውን መለኮታዊ የመገለጥ ልምምድን ለሰዎች ይሰጣል።

አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለውን አመለካከት ሄንድሪ እንዲህ በማለት ገልጦታል፦ "ለማጠቃለል ያህል፥ መንፈስ ቅዱስ በቃሉ ውስጥ ያለው ምስክርነት የተመዘገበው የመጽሐፍ ቅዱስን የአመዘጋገብ ባሕርይ በሚገልጥ መንገድ ሳይሆን፥ ቤተ ክርስቲያን በተቀበለችውና የራሷን እምነት በሚመለከት በምስክርነት ባቀረበችው ቃል ላይ ብቻ ነው። ስለዚህ ነገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነትና የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት በሚገኙበት ነጥብ፥ እንዲሁም ሕያው የሆነው ጌታ በፈጸመው ሥራ ኃይል ላይ መገኘቱ ነው።"

ወበር የባርትን "የቤተ ክርስቲያን ዶግማቲክስ" የሚለውን ትምህርት ሲያጠቃልል፥ የባርቲያንን የመገለጥ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ዋና ጉዳይ "እግዚአብሔር እራሱን በጌትነት ይገልጣል" በሚለው አሳብ ገልጦታል። ይህን ጉዳይ ይበልጥ ሲያብራራ "የእርሱ መገለጥ እውነታ፥ እራሱን ከእራሱ መለየቱ እንግዳ ነገር ነው" ብሏል። ወበር ባርትን ጠቅሶ ይህንኑ እንዲህ አጠቃሎታል፦ "የእግዚአብሔር ቃል በመገለጡ ውስጥ ያለው እግዚአብሔር ራሱ ነው። እግዚአብሔር ራሱን ጌታ አድርጎ ገልጧልና። ይኸውም በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት የመገለጥ ፅንሰ-አሳብ እግዚአብሔር ራሱ መገለጥን ሰጪ ነው። መገለጡና የሚገለጠው የማይነጣጠል አንድነት ያላቸውና እንዲሁም የማይካድ ልዩነት እንዳላቸው ያሳያሉ።" ባርት የመገለጥ ተግባር ዋና ክፍል የክርስቶስ ሥጋ መልበስ ነው ብሏል። ወበር እንዳቀረበው፥ "ለእኛ የእግዚአብሔር መገለጥ

የሚታይ እውነታ፥ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። እርሱ ሥጋ የለበሰ ቃል ነው።'' ደግሞም፥ ''መገለጥ ሆኗል። ቃልም ሥጋ ሆነ ...። መገለጥ የሚታይ እውነታ ነው፥ ስለዚህ ይሆናል ...። መንፈስ ቅዱስ መገለጥን የሚሰጥ እውነታ ነው፥ ስለዚህ የሚቻል ነው።'' ይህን ሲል እግዚአብሔር የተገለጠው በመንፈስ ቅዱስ ነው የሚል ይመስላል። የባርቲያንን ልዩነትና የረቀቀ አገላለጥ ሁሉ ብናስወግድ፥ አሳቡ እግዚአብሔር እራሱን ለሰው የገለጠው በተአምራዊ መንገድ መሆኑን ያስረዳል። እግዚአብሔር ይህን መገለጥ እስካሁን ድረስ በቃሉ ውስጥ በምስጢር የጠበቀው ቢሆንም፥ መገለጡ የሚከናወነው በቃሉ ነው። የመገለጥ መንገድ በቤተ ክርስቲያን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ይሁን ውጤቱ ለሰው ይሆናል። ይህ መገለጥ፥ የመጨረሻ ሥልጣን ያለው፥ የማይሻርና የተጻፈ ቃል ነው ከማለት ይበልጥ በባሕርይው ሥልጣን የተሞላ ነው።

ብሩነር ስለ መገለጥ ያለው ፅንሰ-አሳብ፥ ከባርት አሳብ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፥ አቀራረቡ ግን አነስ ባለ ክርክር እውነትን የማግኛ መንገድ ነው። እንደ ብሩነር አባባል፥ ''ምንጊዜም፥ መገለጥ ማለት አንድ የተደበቀ ነገር ታወቀ፥ ምስጢር የሆነው ነገር ተገለጠ ማለት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ግን ሙሉ ለሙሉ ተሸፍኖ የነበረው ነገር ሙሉ ለሙሉ ተገለጠ ማለት ነው። ይህ እውቀትን የማግኛ መንገድ ፍጹምና አስፈላጊ እንጂ ከተለመደው የሰው እውቀት ማግኛ መንገዶች ማለት ከማስተዋል፥ ከምርምር፥ ከአስተሳሰብ ውጪ በመሆኑ ተቃራኒ ነው። መገለጥ ማለት ሰው በራሱ ጥረት ሊያውቀው የማይችለው ሆኖ በአስደናቂ መንገድ የሚሰጥ ተአምራዊ እውቀት ነው።'' በዚህ አተረጓጎሙ ብሩነር ከቀጥተኛ ሃይማኖት ትምህርት ጋር እጅግ ተቀራራቢነት አለው። እንደ ባርት ሁሉ ከእውነት ፈቀቅ የሚልበት ስፍራ፥ መገለጥ በመሠረቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠ ታሪካዊ መመሪያ ከመሆን ይልቅ እግዚአብሔር እራሱን የሚገልጥበት መንገድ ነው የሚለው ነው። ብሩነር ራሱ እንዳለው፥ ''የተባሉት ነገሮች ሁሉ በመጨረሻ እስከዚህ ነጥብ ያደርሳሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የመገለጥ እውነታ እግዚአብሔር እራሱ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። መገለጥ እግዚአብሔር እራሱን የሚያሳውቅበት መንገድ ነው።''

ብሩነር በመቀጠል እንደሚያመለክተው፥ መገለጥ መለኮታዊ ተግባር ሲሆን፥ የመገለጥ እውነት እንዲከናወን ሰው መገለጥን መቀበል አለበት። ሰው መገለጥን በእምነትና ራስን በመስጠት መቀበል አለበት። ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ ቤተ ክርስቲያን የመገለጥ ምንጭነት ምንም ይባል ምን፥ ከእውቅ መጻሕፍቱ በአንዱ እንደምንመለከተው የመለኮታዊ መገለጥ

አሳብ ለብሩነር "የመለኮታዊና ሰብአዊ ግንኙነት" የሚል አሳብን ያዘለ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ይሰማል። ነገር ግን የሚገለጠው በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ሆኖ፥ ለእውነት የሚመሰክረውም መንፈስ ቅዱስ ነው። ብሩነር ሲጽፍ፥ "ቃል (ክርስቶስ) እውነት መሆኑን (ዮሐ. 1፡1) መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ሲመሰክር፥ እኔም እውነት መሆኑን አውቃለሁ፤ ሌላ ሰብአዊ ዋስትና አልፈልግም" ብሏል። ሰው በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ይህን መለኮታዊ መገለጥ በእምነት ይቀበላል። በሌላ በኩል፥ "እውነተኛ እምነት በሰው ትእዛዝ የተመሠረተ የሥራ ግብ አይደለም። በሥልጣን የማመንም ጉዳይ አይደለም። ራስን ያዋረደ ለሕግ መታዘዝም አይደለም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ አብርሆት የእግዚአብሔርን እውነት በክርስቶስ የሚያዩበት በመለኮት የሚፈጸም ተአምር ነው።" ስለዚህ ሰውን በሚመለከት እውነትን መግለጥ እግዚአብሔር የሚፈጽመው ቀጥተኛ ተግባር ነው። የምስክርነቱና የሥልጣኑ ዋስትና በምንም ዓይነት በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በቤተ ክርስቲያን የተመሠረተ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ የሚገኝ ነው።

ለቲሊክ መለኮታዊ መገለጥ የመለኮትና የሰው ግንኙነት ነው። ነገር ግን ከተአምራዊ ነገር ጋር ሲነጻጸር አነስ ያለ ድምፅ ነው ያለው። የመለኮት እውነት መመዘኛ የእግዚአብሔር መንፈስ ምስክርነት ሳይሆን "አዲስ ፍጥረት" የሚኖረው ምስክርነት ነው። ይኸውም እኛ በክርስቲያንነታችን እንደምንሆነው ማለት ነው። ቲሊክ እንደሚገልጠው፥ "የክርስትናን መልእክት ለዚህ ዘመን እንደሚገባ አጠቃለህ በሁለት ቃል አቅርብ ቢባል እንደ ጳውሎስ ይህ 'የአዲስ ፍጥረት' መልእክት ነው እል ነበር። ስለ አዲስ ፍጥረት ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ሁለተኛ መልእክቱ ያለው ነገር አለ። ትክክለኛ ከሆነ ትርጉም አንዱን ዓረፍተ ነገር በድጋሚ ልጥቀስ፦ 'ማንም ከክርስቶስ ጋር አንድ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው። የአሮጌው ሁኔታ አልፏል፥ የአዲሱ ሁኔታ አሁን ይሠራል" አለ። ይህ አዲስ ነገር አስተሳሰብን ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርስ ስለሆነ፥ በመደነቅና ሐሴትን በማድረግ ይሞላናል። "የጊዜያት ምልክት" ይኸውም የሚታይ መለኮታዊ መገለጥ ይህን የሐሴት ምክንያት ወይም የሰው ልምምድ ተግባራዊነት የሚያመጣው ውጤት መገለጥ ነው። ለቲሊክ፥ መገለጥ ምንም እንኳን ተአምራዊና በቀላሉ የማይረዱትን ነገር የያዘ ቢሆንም፥ ከሰው የዕለት ከዕለት አስተሳሰብ በጥቂት ነው የሚለየው። እንደ ሌሎቹ የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ሁሉ የዚህም ውጤት ሥልጣናትን ሁሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት መለየትና ወደ ሰብዓዊ ፍርድ ማስተላለፍ ነው።

